፩ ፤ ቀዳሜ ፡ ጸሐፍኩ ፡ ለከ ፡ መጽሐፈ ፡ አ ፡ ታዎፊላ ።

ፊላታዎ ፡ ቢል ፡ ይቀናል ፡ የተዘዋወረ ፡ ቀለም ፡ ነው ፡ ፊላ ፡ መፍቀሪ ፡ ታዎ ፡ ስመ ፡ አምላክ ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ወንጌልን ፡ ጻፍሁልህ ፡ በወግ ፡ በታሪክ ፡ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ካህን ። ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ወፅአ ፡ ትእዛዝ ። ወአመ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወኀምስቱ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ እያልሁ ፡ ይህንማ ፡ ምን ፡ ስቶት ፡ ወንጌልን ፡ አክብረህ ፡ እንደተቀበልህ ፡ ይህንም ፡ አክብረህ ፡ ተቀበል ፡ ሲለው ፡ ነው ።

በኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘአኀዘ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይግበር ፡ ወይምሀር ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ፡ የሠራውን ፡ ትሩፋት ፡ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፡ በወንጌል ፡ ጻፍሁልህ ። አንድም ፡ ከፅንስ ፡ ዠምሮ ፡ ያደረገውን ፡ ፍጹም ፡ ትሕትናውን ፡ በወንጌል ፡ ጻፍሁልህ ፡ (ጥቅ) ፡ ነጽርኬ ፡ ኀበ ፡ ሠዓሌ ፡ ሕፃናት ፡ ዘበጥንተ ፡ ሙላዱ ፡ ወጠነ ፡ ፍኖተ ፡ ነኪረ ፡ እንዲል ፡ በዠመረበት ፡ ስዠምር ፡ በጨረሰበት ፡ ስጨርስ ። አንድም ፡ ያስቀደመውን ፡ ሳስቀድም ፡ ያስከተለውን ፡ ሳስከትል ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ሉቃስ ፡ ተራ ፡ ያቀናል ፡ ይባላልና ፡ ኀበሂ ፡ ዓርገ ፡ ደብረ ፡ ወኀበሂ ፡ ነበረ ፡ ወኀበሂ ፡ መሐረ ፡ ኀበሂ ፡ ዓርገ ፡ ሐመረ ፡ ወኀበሂ ፡ ገሠጸ ፡ ባሕረ ፡ እንዲል ። ይግበር ፡ አሪትን ፡ ይምሐር ፡ ወንጌልን ። አንድም ፡ ይግበር ፡ ተአምራቱን ፡ ይምሐር ፡ ትሩፋቱን ። አንድም ፡ ይግበር ፡ የርድእናውን ፡ ይምሐር ፡ የተባሕትዎውን ፡ ጻፍሁልህ ። አንድም ፡ ይግበር ፡ ለራሱ ፡ ይምሐር ፡ ለሌላው ፡ ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፫ ፡

፪ ፤ እስከ ፡ ዕለት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ዓርገ ፡ አዚዞ ፡ ለሐዋርያቲሁ ፡ ለእለ ፡ ኀረዮሙ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የመረጣቸው ፡ ሐዋርያትን ፡ አዞ ፡ እስካረገባት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ጸሐፍኩ ፡ ለከ ፡ ከቀደመው ፡ ሲለይ ፡ የቀደመው ፡ የሚመረጡት ፡ እስራኤል ፡ ዘሥጋ ፡ የሚመረጡበት ፡ መንፈስ ፡ ረድኤት ፡ የሚመረጡላት ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ ነበረች ፡ የሚመርጣቸው ፡ ሙሴ ፡ ነበር ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ የሚመረጡት ፡ እስራኤል ፡ ዘነፍስ ፡ የሚመረጡበት ፡ መንፈስ ፡ ልደት ፡ የሚመረጡላት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ የሚመርጣቸው ፡ ቃል ፡ ሥግው ፡ ነውና ። አንድም ፡ አጥመቆሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያጠመቃቸው ፡ ሐዋርያትን ፡ አዞ ፡ እስካረገባት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ (ጥቅ) ፡ እምቅድመ ፡ ይባኡ ፡ ውስተ ፡ ኀሬት ፡ ይደሉ ፡ ይምሐርዎሙ ፡ ቃሉ ፡ ሃይማኖትናሁ ፡ አስተዳለወ ፡ መሥዋዕቶ ፡ ወቀደሶሙ ፡ ለኀሩያኒሁ ፡ እንዲል ። ወለኵሎሙ ፡ አጥመቆሙ ፡ ሙሴ ፡ በደመና ፡ ወተጠምቃ ፡ እገሪሆሙ ፡ ለካህናት ። አጥመቃ ፡ ለምድር ፡ በማየ ፡ አይኅ ፡ ቢል ፡ ያ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ግን ፡ አማናዊ ፡ ነውና ።

፫ ፤ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ አርአዮሙ ፡ ወከሠተ ፡ ሎሙ ፡ ርእሶ ፡ ሕያወ ፡ እምድኅረ ፡ ሞተ ፡ በተአምር ፡ ብዙኅ ።

በመስቀል ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ አድርጎ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ራሱን ፡ የገለጠላቸው ፡ እሊህ ፡ ናቸው ። ሞተ ፡ በተአምር ፡ ብዙኅ ፡ ሕያው ፡ በተ

www.ethiopianorthodox.org

አምር ፡ ብዙኀ ፡ ከሠተ ፡ በተአምር ፡ ብዙ
ኀ ፡ ሞተ ፡ በተአምር ፡ ብዙኀ ፡ በመስ
ቀል ፡ ሰባት ፡ ተአምራት ፡ አድርጎ ፡ ከሞ
ተ ፡ በኋላ ፡ ሕያው ፡ በተአምር ፡ ብዙኀ ፡
በመለኮታዊ ፡ ሕይወት ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ከጎኑ ፡ ትኩስ ፡ ደም ፡ ጥሩ ፡ ውኃ ፡
አፍሶ ፡ ከሠተ ፡ በተአምር ፡ ብዙኀ ፡ በዝ
ግ ፡ ደጅ ፡ ገብቶ ፡ ሰላም ፡ ለክሙ ፡ ብሎ ፡
ራሱን ፡ የገለጠላቸው ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡
አርብዓ ፡ ዕለተ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ አርባ ፡
ቀን ፡ ሲታያቸው ፡ ኑሮ ፡ እስካረገባት ፡
ቀን ፡ ድረስ ፡ ምነው ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ አይ
ደለም ፡ የታየቸው ፡ ቢሉ ፡ ከዚያው ፡
ገብቶ ፡ ከተቈጠረ ፡ ብሎ ። አንድም ፡ የጉ
ባኤውን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ላን
ዱም ፡ ለሁለቱም ፡ ባለሟሎቹ ፡ ሳይታያ
ቸው ፡ አይውልም ፡ አያድርም ፡ ነበር ፡

ወይዜንዎሙ ፡ ወይነግሮሙ ፡ በእንተ ፡ መንግሥተ ፡
እግዚአብሔር ።

ይዜንዎሙ ፡ አሪትን ፡ ይነግሮሙ ፡ ወን
ጌልን ። አንድም ፡ ይዜንዎሙ ፡ ወንጌ
ልን ፡ ይነግሮሙ ፡ ከዚያው ፡ ከውስጡ ፡
እምቅድመ ፡ ይትወለድ ፡ አብርሃም ፡
ሀሎኩ ፡ አነ ፡ ትላለችና ። አንድም ፡ ይነ
ግሮሙ ፡ ወንጌልን ፡ ይዜንዎሙ ፡ መጽ
ሐፈ ፡ ኪዳንን ፡ ሲያስተምራቸው ፡ ሉቃ፡
፲፯ ፡ ፳ ፡ ፳፩፡ ሮሜ ፡ ፲፬ ፡ ፲፯ ።

፬ ፤ ክፍል ፡ ፩ ፤ ወእንዘ ፡ ይመስሕ ፡ ምስሌሆሙ ፡

አብሯቸው ፡ ሲመገብ ፡ ኑሮ ፡ እስካረገ
ባት ፡ ቀን ፡ ድረስ ። አዘዞሙ ፡ ማንሻ ፡
አብሯቸው ፡ ሲመገብ ፡ ኑሮ ፡

አዘዞሙ ፡ ኢይፃኡ ፡ እምኢየሩሳሌም ።

በአርብዓ ፡ ዕለት ፡ አዘዞሙ ፡ በአርባኛ
ደቱ ፡ ቀን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ እንዳይወጡ፡
አንትሙሰ ፡ ንበሩ ፡ ሀገረ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
እስከ ፡ ትለብሱ ፡ ኃይለ ፡ እምዓርያም ፡
ብሎ ፡ አዘዛቸው ፡

አላ ፡ ይጽንሑ ፡ ተስፋሁ ፡ ለአብ ።

እሠውጥ ፡ እምነ ፡ መንፈስየ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ፡
ዘሥጋ ፡ ብሎ ፡ ያናገረው ፡ ተስፋ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ደጅ ፡ ይጠኑ ፡ ዘንድ ፡
እንጅ ፡ በሰቂለ ፡ ሕሊና ፡ ለማኖር ፡ ለማ
ለበም ። አንድም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
የሚወርድ ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ነው ፡ ካንዱ ፡
ወደ ፡ አንዱ ፡ ሲሉ ፡ ከነግ ፡ ከሠልስት ፡
እንመለሳለን ፡ ሲሉ ፡ እንዳይቀርባቸው ።
አንድም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባልታደሰ ፡
ሰውነታቸው ፡ አሕዛብ ፡ መከራ ፡ አጽን
ተውባቸው ፡ እንዳይክዱ ፡ ዮሐ፡ ፲፫፡ ፳፮።
ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፵፱ ።

፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ዮሐንስ ፡ አጥመቀ ፡ በማይ ፡

ዮሐንስ ፡ በውኃ ፡ ብቻ ፡ አጠመቀ ፡

ወአንትሙሰ ፡ ታጠምቁ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡

እናንተ ፡ ግን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ታ
ጠምቃላችሁ ፡

እስከ ፡ ኀዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ዘኢኮነ ፡ ርሑቀ ።

ሩቅ ፡ ያይደለ ፡ እስከ ፡ ቅርብ ፡ ቀን ፡ ብዙ፡
ያይደለ ፡ እስከ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡
ታጠምቃላችሁ ፡ አላቸው ፡ ም፡ ፲፩ ፡ ፲፮ ፡
፲፫ ፡ ፳፬። ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

፮ ፤ ክፍል ፡ ፫ ፤ ወእንዘ ፡ ጉቡአን ፡ እሙንቱ ፡ ተስ
እልዎ ፡ ወይቤልዎ ፡ እግዚእ ፡ በዝኑ ፡ መዋዕል ፡ ታግ
ብእ ፡ መንግሥተ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ።

መንፈሳዊ ፡ ነገር ፡ ቢነግራቸው ፡ ሥጋዊ ፡
ነገር ፡ ይጠይቁታል ፡ ብሎ ፡ ባንድነት ፡
ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፡ አቤቱ ፡ በዘሩባቤል ፡
የሄደችውን ፡ መንግሥት ፡ ለእስራኤል ፡
ልጆች ፡ የምትመልሰው ፡ መቸ ፡ ነው ፡
በዚህ ፡ ወራት ፡ ነውን ፡ ብለው፡ ጠየቁት።



አንድም ፡ መንፈሳዊ ፡ ነገር ፡ ቢነግራ
ቸው ፡ መንፈሳዊ ፡ ነገር ፡ ይጠይቁታል ፡
ብሎ ፡ በአዳም ፡ የሄደችውን ፡ ልጅነት ፡
መቸ ፡ ትመልሳለህ ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡
ነውን ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ፡ በዚህ፡ ወራት ፡
ትመልሳለህን ፡ ቢል ፡ ይሆናል ፡ ሉቃ ፡
፳፬፡ ፳፩ ።

፯ ፤ ወአውሥአሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ኢኮነ ፡ ለክሙ ፡
ታእምሩ ፡ መዋዕለ ፡ ወአዝማነ ፡ ዘሠርዐ ፡ አብ ፡ በም
ኵናኑ ፡ ባሕቲቱ ።

አብ ፡ ብቻውን ፡ በሥልጣኑ ፡ ባራቱ ፡ ክ
ፍለ ፡ ዘመን ፡ በሰባቱ ፡ ዕለታት ፡ የወሰነ
ውን ፡ የጊዜውን ፡ የዘመኑን ፡ ነገር ፡ ልታ
ውቁ ፡ አይቻላችሁም ፡ አላቸው ፡ አብ ፡
ባሕቲቱ፡ አለ፡ አብን፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ፡
ሲለየው፡አይደለም፡ ከፍጡራን፡ ሲለየው ፡
ነው፡ እንጅ ፡ ራሱን፡ መተው ፡ ግን ፡ አላዋ
ቂ ፡ የነበረ ፡ ሥጋን ፡ እንደተዋሐደ ፡ ለማ
ጠየቅ ፡ (ጥቅ)፡ አኮ፡ ኢያእሚሮ፡ ኅቡዓተ፡
አላ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ መካነ ፡ ለጥንተ ፡ ትስ
ብእቱ ፡ ዘኢየአምር ፡ ኅቡዓተ ፡ እንዲል ፡
ፍጡር ፡ የፈጣሪውን ፡ ዕለተ ፡ ኃይል ፡
ማወቅ ፡ አይቻለውምና ። አንድም ፡ ነገር ፡
በሳቡበት ፡ ነበርና ፡ ነገር ፡ ለማስቆም ፡
ለማለበም ።

፰ ፤ አላ ፡ ሶበ ፡ ይወርድ ፡ ላዕሌክሙ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ትነሥኡ ፡ ኃይለ ፡

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በወረደላችሁ ፡ ጊዜ ፡
አለ ፡ ባደረባችሁ ፡ ጊዜ ፡ ሰማያዊ ፡ ሀብ
ትን ፡ ሰማያዊ ፡ ዕውቀትን ፡ ገንዘብ ፡ ታደ
ርጋላችሁ ፡ እንጅ ፡

ወትከውኑኒ ፡ ሰማዕትየ ፡ በኢየሩሳሌም ፡

በኢየሩሳሌምም ፡ ትመሰክሩልኛላችሁ ፡
እንጅ ። አንድም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባደ
ረባችሁ ፡ ጊዜ ፡

ወትነሥኡ ፡ ኃይለ ፡

ሰማያዊ ፡ ሀብትን ፡ ሰማያዊ ፡ ዕውቀትን ፡
ገንዘብ ፡ ባደረጋችሁ ፡ ጊዜ ፡

ወትከውኑኒ ፡ ሰማዕትየ ፡ በኢየሩሳሌም ፡

በኢየሩሳሌም ፡ ትመሰክሩልኛላችሁ ፡
እንጅ ፡

ወበኵሉ ፡ ይሁዳ ፡

በይሁዳ ፡ ሁሉ ፡

ወሰማርያ ።

በሰማርያም ፡ ሁሉ ፡

ወእስከ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ፡

ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ ትመሰክሩልኛላችሁ ፡
እንጅ ፡

፱ ፤ ወዘንተ ፡ እንዘ ፡ ይብሎሙ ፡ ተለዓለ ፡

ይህን ፡ ሲነግራቸው ፡ አፍ ፡ አለ ፡ በድ
ረግ ፡ አለ ፡ ምድር ፡ ለቀቀ ፡ (ጥቅ) ፡ ወተ
ለዓለ ፡ መርፈቀ ፡ ኖኅት ፡ እምቃል ፡ ዘይ
ኬልሑ ፡ እንዲል ።

ወነሥአቶ ፡ ደመና ፡

ደመና ፡ አፍ ፡ አደረገችው ፡ በድረግ ፡ አደ
ረገችው ፡ ምድር ፡ አስለቀቀችው ፡

ወዓርገ ፡ ሰማየ ፡ እንዘ ፡ እሙንቱ ፡ ይኔጽሩ ፡ ኀቤሁ ፡

እያዩት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዓረገ ፡

ወተሠወረ ፡ እምአዕይንቲሆሙ ።

ካይናቸው ፡ ተሠወረ ፡ የርቀት ፡ ያይደለ ፡
የርኅቀት፡ ማር፡ ፲፮ ፡ ፲፱። ሉቃ ፡ ፳፬፡ ፶፩ ፡

፲ ፤ ወእስተርአይዎሙ ፡ ክልኤቱ፡ ዕደው ፡ ወቆሙ ፡
ኀቤሆሙ ፡

ሁለት ፡ መላእክት፡ ባጠገባቸው፡ ቁመው ፡
ታይዋቸው ፡ በአምሳለ ፡ ብእሲ ፡ ነውና ፡
ዕደው ፡ አላቸው ፡

ወይለብሱ ፡ ጸዓዳ ።

ብሩህ ፡ ብሩህ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ አለ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወርኅ ፡ ትፍሥሕት ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፬ ።

፲፩ ፤ ወይቤልዎሙ ፡ አንትሙ ፡ ሰብአ ፡ ገሊላ ፡ ምንትኑ ፡ ቆምክሙ ፡ ትርአዩ ፡ ሰማየ ፡

ለምንት ፡ ቆምክሙ ፡ ትርአዩ ፡ ሰማየ ፡ ምንተ ፡ ትርአዩ ፡ ይላል ፡ እናንተ ፡ የገሊላ ፡ ሰዎች ፡ ሰማይ ፡ ሰማይ ፡ እያያችሁ ፡ ለምን ፡ ቆማችኋል ፡ በሰማይ ፡ ምን ፡ ልታዩ ፡ ቁማችኋል ፡ አሏቸው ፡

ዝውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘዓርገ ፡ እምኀቤክሙ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ።

ከናንተ ፡ ተለይቶ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲያርግ ፡ ያያችሁት ፡ ይህ ፡ ኢየሱስ ፡ ነው ፡

ወከማሁ ፡ ካዕበ ፡ ይመጽእ ፡ በከመ ፡ ርኢክምዎ ፡ የዓርግ ፡ ሰማየ ።

በብርሃን ፡ በሥልጣን ፡ በቅዳሴ ፡ ሲዓርግ፡ እንዳያችሁት ፡ ዳግመኛ ፡ በብርሃን ፡ በሥልጣን ፡ በቅዳሴ ፡ ይመጣል ፡ ሲመጣ ፡ ታዩታላችሁ ። አንድም ፡ በክበበ ፡ ትስብእት ፡ ሲዓርግ ፡ እንዳያችሁት ፡ ዳግመኛ ፡ በክበበ ፡ ትስብእት ፡ ይመጣል ፡ ሲመጣ ፡ ታዩታላችሁ ፡ አሏቸው ፡ መላእክት ፡ ሐፀ፡ እሳት ፡ ኩናተ ፡ እሳት ፡ ይዘው ፡ አይተው፡ ነበርና ፡ ያ ፡ ያየነው ፡ እሳት ፡ አቃጥሎት ፡ ይሆን ፡ እንዳይሉ ፡ በክበበ ፡ ትስብእት ፡ ሲያርግ ፡ እንዳያችሁት ፡ ዳግመኛ ፡ በክበበ ፡ ትስብእት ፡ ሲመጣ ፡ ታዩታላችሁ ፡ አላቸው ፡ ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፳፯ ።

፲፪ ፤ ወእምዝ ፡ ተሠውጡ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እምደብረ ፡ ዘይት ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከደብረ ፡ ዘይት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ፡ እንዲያው ፡ አይደለም ፡ መላእክት ፡ አ ፡ ውሉደ ፡ ሰላም ፡ እትዉ ፡ በሰላም ፡ ብለዋቸዋል ፡ ሰግደው ፡ ተመልሰዋል ፡

ዘእቱት ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ መጠነ ፡ ምርዋጸ ፡ ብእሲ፡

ጉልማሳ ፡ አፍታ ፡ ሩጦ ፡ ክቡድ ፡ ሸክም ፡ ተሸክሞ ፡ የሚያርፍባትን ፡ ያህል ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የምትርቅ ፡ ብሎ ፡ ለደብረ ፡ ዘይት ፡ ይቀጥላል ፡

እንተ ፡ ይእቲ ፡ መንገደ ፡ ቀዳም ።

ይችውም ፡ የቅዳሜ ፡ መንገድ ፡ ያህል ፡ የምትርቅ፡ ናት ፡ ቅዳሜ፡ እስከ ፡ ሠለስት ፡ ድውይ ፡ ለመጠየቅ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ለመንሣት ፡ ምውት ፡ ለመቅበር ፡ መንገድ ፡ ታዝዟልና ፡ አንድም ፡ መንገለ ፡ ቀዳም ፡ ይላል ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ያለች ፡ ሰብአ ፡ ቄዴም ፡ እንዲል ፡ ሰብአ ፡ ምሥራቅ ፡ ሲል ፡ ጽባሒሃ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ይላታልና ፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፶ ።

፲፫ ፤ ወበጺሖሙ ፡ ማኅደሮሙ ፡ ኀበ ፡ ይነብሩ ፡ ጽርሐ ፡

ማኅደርና ፡ ጽርሕ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ወደሚአድሩበት ፡ አዳራሽ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡

ወዓርጉ ፡

ገቡ ። አንድም ፡ ማኅደርና ፡ ጽርሕ ፡ በየራሱ ፡ ወደሚያድሩበት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ዓርጉ፡ ጽርሐ፡ ከአዳራሽ፡ ገቡ፡ (ጥቅ)፡ ወዓርጉ፡ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ እርከን ፡ እርከን ፡ ያለው ፡ ነውና ፡ ዓርጉ ፡ አለ ፡

ጴጥሮስ ፡ ወዮሐንስ ፡ ወያዕቆብ ፡ ወእንድርያስ ፡ ወፊልጶስ ፡ ወቶማስ ፡ ወማቴዎስ ፡ ወበርተሎሜዎስ ፡ ወያዕቆብ ፡ ወልደ ፡ እልፍዮስ ፡ ወስምዖን ፡ ቀናዒ ፡ ወይሁዳ ፡ ወልደ ፡ ዮሴፍ ።

ዮሐንስ ፡ ያዕቆብ ፡ እንድርያስ ፡ ቶማስ ፡ ማቴዎስ ፡ በርተሎሜዎስ ፡ ያዕቆብ ፡ ስምዖን ፡ ቀናኢ ፡ ይሁዳ ፡ ወልደ ፡ ዮሴፍ ፡ ገቡ ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፪ ። ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፲፫ ።



፲፬ ፤ እሉ ፡ ኵሎሙ ፡ ይፀመዱ ፡ ጸሎተ ፡ ኅቡረ ፡ ምስለ ፡ አንስት ፡

እሊህ ፡ ሁሉ ፡ ከሠላሳ ፡ ስድስቱ ፡ ቅዱሳት ፡ አንስት ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ይጸልዩ ፡ ነበር ፡ ምነው ፡ ምቅዋሞን ፡ ለአንስት ፡ ለባሕቲቶን ፡ ምጽላዮን ፡ ለአንስት ፡ ለባሕቲቶን ፡ ይል ፡ የለም ፡ ቢሉ ፡ ለሌላው ፡ አዎን፡እሊህ፡ ግን፡ ጦር፡ ጠፍቶላቸዋልና ፡

ወማርያም ፡ እሙ ፡ ለኢየሱስ ፡

የጌታ ፡ እናቱ ፡ እመቤታችንም ፡ ከዚያ ፡ ነበረች ።

ወአኃዊሁኒ ።

ወንድሞቹም ፡ ከዚያ ፡ ነበሩ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፩ ። ዮሐ ፡ ፯ ፡ ፫ ።

፲፭ ፤ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ ተንሥአ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወቆመ ፡ ማእከለ ፡ አኃዊሁ ፡

ምስለኔ ፡ ሁን ፡ እንደኔ ፡ ነውና ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጴጥሮስ ፡ ተነሥቶ ፡ በወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ ቆመ ፡

ወይቤሎሙ ፡ እንዘ ፡ ሀለዉ ፡ ህየ ፡ ሰብእ ፡ ወየአክሉ ፡ ምእተ ፡ ወዕሥራ ።

መቶ፡ ኻያው፡ ቤተ፡ ሰብ፡ባንድነት፡ሳሉ ።

፲፮ ፤ ስምዑ ፡ ኦ፡አኅዊነ ፡ አማን ፡ ሀለዎ ፡ ይብጻሕ፡ ቃለ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘይቤ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአፈ ፡ ዳዊት ፡ በእንተ ፡ ይሁዳ ፡

መጽሐፍ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በዳዊት ፡ አድሮ ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ ወይጥፋዕ ፡ እምድር ፡ ዝክሩ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ይደርስ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ዛሬ ፡ ደርሶ ፡ ተፈጽሞ ፡ እንዳለ ፡ ዕወቁ ፡ አላቸው ፡

ዘውእቱ ፡ ኮኖሙ ፡ መርሐ ፡ ለእለ ፡አኃዝዎ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ።

ይኸውም ፡ ፈታውራሪ ፡ ሁኖ ፡ ጌታን ፡ ያስያዘው ፡ ነው ፡ [illegible] ፡ ፲ ።

፲፯ ፤ እንዘ ፡ ኍልቈ ፡ ውእቱ ፡ ምስሌነ ።

ቊጥሩ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ሲሆን ፡ ኍሉቅ፡ ይላል ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ የተቈጠረ ፡ ሲሆን ፡

ወከፈሎ ፡ ዘንተ ፡ መልእክተ ።

ይኸን ፡ ክታብ ፡ የሰጠው ፡ ሲሆን ፡ አለ ፡ ይኸን ፡ ሐዋርያነት ፡ ያደለው ፡ ሲሆን ፡ ከዚህ ፡ መዓርግ ፡ ቢያደርሰው ፡ በሞቱ ፡ ገባ ፡ ለማለት ።

፲፰ ፤ ወእምዝ፡ ተሣየጠ፡ ዓጸደ፡ በአስበ፡ ዓመፃሁ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዓመፁ ፡ ዋጋ ፡ ቦታ ፡ ገዛ ፡ እሱስ ፡ አልገዛውም ፡ የነሱን ፡ ለሱ ፡ ሰጥቶ ፡ ተሣየጠ ፡ አለ ፡ እንጅ ፡

ወተነጽሐ ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ በገጹ ፡

በግምባሩ፡ ተደፍቶ፡ ወደ፡ ምድር፡ ወደቀ ፡

ወተሠጥቀ ፡ ገቦሁ ።

ጎኑ ፡ ተቀደደ ።

፲፱ ፤ ወተክዕወ ፡ ኵሉ ፡ አማዑቲሁ ።

ንዋየ ፡ ውስጡ ፡ ፈሰሰ ፡ ከዚህ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ወንጌል ፡ ተሐንቀ ፡ ወሞተ ፡ ይላል ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ሁሉም ፡ ተደርጓል ፡ ለልማዱ ፡ ጌታ፡ አይሁድ ፡ እንይዘዋለን፡ ብለው ፡ ሲሄዱ፡ በተአምራት፡ ሲያመልጥ፡ ያየው፡ ነበር፡ እሱም፡ እንደ፡ ልማዱ፡ በተአምራቱ፡ ያመልጣል፡ እኔም፡ወርቄን ፡ እንደያዝሁ ፡ እቀራለሁ ፡ ብሎ ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ ተቀብሎ፡ አሲዝዋቸዋል ፡ ይሞት ፡ በቃ ፡ እንደ ፡ ተፈረደበት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ያስገደልሁ ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ ያፈሰስሁ ፡ አላበጀሁም ፡ በደልሁ ፡ ብሎ ፡ ሠላሳውን ፡ ብር ፡ ይዞ ፡ ሂዶ ፡ ተቀበሉኝ ፡ አላቸው ፡ ሚ ፡ ላዕሌነ ፡ ለሊከ ፡ አእምር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የወደድኸውን ፡ ሰጥተንሃል ፡ የወደድነውን ፡ ሰጥተኸናል ፡ ለኛ ፡ ካንተ ፡ ላንተ ፡ ከኛ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ምን ፡ አለህ ፡ አንት ፡ ለራስህ ፡ ዕወቅ ፡ አሉት ፡ ወገደፈ ፡ ውእተ ፡ ብሩረ ፡ ውስተ፡ ምኵራብ ፡ ወሐረ ፡ ወተሐንቀ ፡ ወሞተ ፡ ይላል ፡ ሠላሳውን ፡ ብር ፡ ከዕቃ ፡ ቤቱ ፡ አፍሶ ፡ ገመድ ፡ ይዞ ፡ ሂዶ ፡ ሊታነቅ ፡ ከዛፍ ፡ አሠረ ፡ ነስሐ ፡ ከመ ፡ እኁከ ፡ ጴጥ ሮስ ፡ አለችው ፡ ያልኋትን ፡ ትታ ፡ ያላል ኋትን ፡ ብሎ ፡ ሂዶ ፡ ካንዲት ፡ ዕፅ ፡ አሠረ፡ ነሥሕ ፡ ከመ ፡ እኁከ ፡ ጴጥሮስ ፡ አለችው ቀባጣሪት፡ ዕፅ፡ ብሎ፡ ሂዶ፡ በቀትር ፡ ጊዜ፡ ዕፀዋት ፡ ሁሉ ፡ አድንኖ፡ አድርገዋል፡ አን ሥታ፡ ከምድር፡ ፈጨችው፡ ደም፡ ከልቡ ፡ ላይ፡ወድቆ፡ሲፈራገጥ፡ነጋድያን፡አልፈው፡ ሲሄዱ ፡ አይተው ፡ ሂደው ፡ ለዘመዶቹ ፡ ለምሽቱም ፡ ይላሉ ፡ ያ ፡ ክፉ ፡ ዘመዳችሁ፡ ከዚያ ፡ ወድቆ ፡ ይፈራገጥላችኋል ፡ ብለ ው ፡ ነገሯቸው ፡ አፋፍሰው ፡ ወስደው ታል ፡ ወቀቢዖ ፡ ነቅዓ ፡ እማዕከሉ ፡ቀበ ወ ፡ ወነቅዓ ፡ እማዕከሉ ፡ ይላል ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ አብጦ ፡ ተነፋፍቶ ፡ ኑሯል ፡ ባርባ ፡ ቀኑ ፡ ጌታ ፡ ባረገ ፡ ጊዜ፡ ያ፡ ያሰቀልኸው፡ ዓረገልህ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፡ አያለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲወጣ ፡ መድረኩ ፡ ቢአነቅፈው ፡ ሲወድቅ ፡ የሣንቃው ፡ ወንዳወንዶ ፡ መ ወርወርያውም ፡ ይላል ፡ ጎኑን ፡ ቀደደው ፡ ንዋየ ፡ ውስጡ ፡ ፈሶ፡ ሙቷል ። አንድም ፡ አያለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲወጣ ፡ መላእክት ፡ ነፀ ፡ እሳት ፡ ኩናተ ፡ እሳት ፡ ይዘው ፡ ታዩት ፡ ወደ ፡ አልጋ ፡ ኋሮ ፡ እሸሻለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲገባ ፡ ያገራቸው ፡ አልጋ ፡ ጠገጉ ፡ ብረ ት ፡ ነው ፡ ጎኑን ፡ ቀደደው ፡ ንዋየ ፡ ውስ ጡ ፡ ፈሶ ፡ ሙቷል ፡ ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፫ ።

ወተሰምዐ ፡ ነገሩ ፡ በኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ በኢየሩሳሌም ፡

የሞቱ ፡ ዜና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ከሁሉ ፡ ደርሶ ፡ ተሰማ ፡

ወተሰምየ ፡ ዓጸዱ ፡ ዘተሣየጠ ፡ በዓስቡ ፡ ሰመይዎ ፡ በነገሮሙ ፡ ሐቅለ ፡ ድማኅ ።

ሰመይዎና ፡ ተሰምየ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ በዓ መፁ ፡ ዋጋ ፡ የገዛውንም ፡ ቦታ ፡ በቋንቋ ቸው ፡ ሐቅለ ፡ ድማኅ ፡ አሉት ፡

ገራኅተ ፡ ደም ፡ ብሂል ።

ሐቅለ ፡ ድማኅም ፡ ማለት ፡ ገራኅተ ፡ ደ ም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አኮልዳማኅ ፡ አሴል ዳማኅ ፡ አኮልዳማግ ፡ አሴልዳማግ ፡ የሚ ል ፡ ጥሬ ፡ ይገኛል ፡ ትርጓሜው ፡ አንድ ፡ ነው ።

፳ ፤ በከመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፈ ፡ መዝሙር ፡ ለትኩን ፡ ሀገሩ ፡ በድወ ፡

የይሁዳ ፡ ሀገሩ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ትሁን ፡

ወአልቦ ፡ ዘይነብር ፡ ውስቴታ ፡

የሚኖርባት ፡ ሰው ፡ አይኑር ፡ ብሎ ፡ መጽ ሐፍ፡ እንደ፡ ተናገረ፡ ሰመይዎ። አንድም ፡ የይሁዳ፡ ሀገረ፡ ስብከቱ፡ ምድረ፡ በዳ፡ ትሁ ን ፡ የሚኖርባት ፡ ሰው ፡ አይኑር ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ተነጽሐ ፡ ወሞተ ፡ ይህስ ፡ ወሢመቶሂ ፡ ይንሣእ ፡ ባዕድ ፡ ብሎ ፡ አሁን ፡ እንዲያመጣው ፡ ባዕድ ፡ ማትያስ ፡ ገብቶባታል ፡ ብሎ ፡ የይሁዳ ፡ ሀገረ ፡ ስብከቱ ፡ ከሱ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ትሁን ፡ እሱ ፡ የሚኖርባት ፡ መኖር ፡ አይኑር ፡

ወሲመቶሂ ፡ ይንሣእ ፡ ባዕድ ።

በሹመቱም ፡ ባዕድ ፡ ይግባበት ፡ ብሎ ፡ መ ጽሐፍ፡ እንደ ፡ ተናገረ፡ ተነጽሐ ፡ ወሞተ ፡ ወይደሉ ፡ ማንሻ ። አንድም ፡ ለትኩን ፡ ሀገሩ፡በድወ፡ወአልቦ፡ዘይነብር፡ውስቴታ ፡ እንዳለ ፡ ተነጽሐ ፡ ወሞተ ፡ ወሢመቶሂ ፡ ይንሣእ ፡ ባዕድ ፡ እንዳለ ፡ ይደሉ ፡ ለአሐ ዱ ። አንድም ፡ ለትኩን፡ ሀገሩ ፡ በድወ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይ [illegible]

www.ethiopianorthodox.org



ቶሂ ፡ ይንሣእ ፡ ባዕድ ፡ እንዳለ ፡ ይደሉ ፡ ለአሐዱ፡ ላለው፡ ዳዊት ፡ ለትኩን ፡ ሀገሩ ፡ በድወ፡ ወአልቦ፡ ዘይነብር፡ ውስቴታ፡ ያለ፡ በስሳ፡ ስምንተኛው ፡ አንቀጽ፡ ነው ፡ ወሢ መቶሂ ፡ ይንሣእ ፡ ባዕድ ፡ ያለ ፡ በመቶ ፡ ስምንተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ነው ፡ ስለምን ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ ፡ ቢሉ ፡ የተነገ ረበት ፡ አንድ ፡ ይሁዳ ፡ ተናጋሪው ፡ አንድ ዳዊት ፡ አናጋሪው ፡ አንድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መዝ ፡ ፷፱ ፡ ፳፭ ፡ ፻፱ ፡ ፰ ።

፳፩ ፤ ወይደሉ ፡ ለአሐዱ ፡ እምእሉ ፡ እደው ፡ እለ ፡ ነበሩ ፡ ምስሌነ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ መዋዕለ ፡ ዘቦአ ፡ ወወፅአ ፡ በኀቤነ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ከኛ፡ ዘንድ፡ እየወጣ፡ እየገባ ፡ በኖረበት፡ ዘመን፡ ሁሉ ፡ ከነበሩት ፡ ላንዱ ፡ ይገባል ፡ አለ ፡ ቦአ ፡ ምድረ ፡ እስራኤል ፡ ወፅአ ፡ ምድረ ፡ አሕ ዛብ ። አንድም ፡ ቦአ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወፅአ ፡ ገዳም ። አንድም ፡ ቦአ ፡ ምኵራ ብ ፡ ወፅአ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ዮሐ ፡ ፲፰ ፡ ፳፯ ።

፳፪ ፤ እኂዞ፡ እምጥምቀተ ፡ ዮሐንስ፡ እስከ፡ አመ ፡ ዓርገ ፡ እምኀቤነ ።

በዮሐንስ ፡ እጅ ፡ ከተጠመቀ ፡ ዠምሮ ፡ ከኛ ፡ ተለይቶ ፡ እስካረገበት፡ ቀን፡ ድረስ ፡ እየወጣ ፡ እየገባ፡ በኖረበት፡ ዘመን፡ ሁሉ ፡

ከመ ፡ ይኩን ፡ ውእቱ ፡ ምስሌነ ፡ ስምዓ ፡ ተንሥኦቱ።

ከኛ ፡ ጋራ ፡ እንደኛ ፡ የትንሣኤው ፡ ምስ ክር ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይደሉ ፡ ለአሐዱ ፡ ላለው ።

፳፫ ፤ ወአቀሙ ፡ ክልኤተ ፡ ዮሴፍሃ ፡ ዘተሰምየ ፡ በርናባስ ፡ ዘይብልዎ ፡ ኢዮስጦስ ፡ ወማትያስሃ ።

ባንድ ፡ ልሳን ፡ ኢዮስጦስ ፡ የሚሉት ፡ በርናባስ ፡ የተባለ ፡ ዮሴፍንና ፡ ማትያ ስን ፡ ሁለቱን ፡ መርጠው ፡ በፊታቸው ፡ አቆሟቸው ።

፳፬ ፤ ወጸለዩ ፡ ወይቤሉ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ማእ ምረ ፡ ኵሉ ፡ ልብ ፡ አርኢ ፡ አሐደ ፡ እምእሉ ፡ ክል ኤቱ ፡ ዘኀረይከ ።

ልቡና ፡ ያሰበውን ፡ ኵላሊት ፡ ያመላለሰ ውን ፡ የምታውቅ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ የምታ ውቅ ፡ አቤቱ ፡ ከሊህ ፡ ከሁለቱ ፡ የመረጥ ኸውን ፡ አንዱን ፡ ግለጥ ፡ መዝ ፡ ፯ ፡ ፲ ።

፳፭ ፤ ዘይነሥእ ፡ ለመልእክተ ፡ ዛቲ ፡ ሢመተ ፡ ሐዋርያት ።

ይችን፡ የሐዋርያትን፡ ሹመት ፡ ተልእኮ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያደርጋትን ፡ ከሊህ ፡ ከሁ ለቱ ፡ የመረጥኸውን ፡ ግለጥ ። አንድም ፡ ሢመት ፡ ሐዋርያዊት ፡ ይላል ፡ የሐዋ ርያነት ፡ ምልክት ፡ የምትሆን ፡ የዚችን ፡ ሹመት ፡ ተልእኮ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያደርጋ ትን ፡ ከሊህ ፡ ከሁለቱ ፡ የመረጥኸውን ፡ ግለጥ ፡ ብለው ፡ ጸለዩ ፡

ዘኀደጋ ፡ ይሁዳ ፡ ይሑር ፡ ብሔሮ ።

ወደ ፡ ሀገረ ፡ ስብከቱ ፡ ሌላው ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ ይሁዳ ፡ የተዋት ። አንድም ፡ ሀገ ሩ ፡ ወደ፡ ገሃነም ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ ይሁዳ ፡ የተዋት ። አንድም ፡ ለይሁዳሰ ፡ ኅድጎ ፡ ይሑር ፡ ብሔሮ ፡ ይሁዳንስ ፡ ተወው ፡ አገ ሩን ፡ ገሃነምን ፡ ሂድና ፡ አርኢ ፡ አሐደ ፡ ላለው ።

፳፮ ፤ ወአስተዓፀውዎሙ ።

ዕፃ ፡ አጣጣሉዋቸው ፡ አሁን ፡ ሐዋርያት ፡ የበቃውንና ፡ ያልበቃውን ፡ የማያውቁ ፡ ሁኖ ፡ አይደለም ፡ ተዘምዶተ ፡ ሥጋ ፡ እንጅ ፡ ኑሯቸው ፡ አድልተው ፡ ማማለጃ ፡ በልተው ፡ እንዳይሏቸው ። አንድም ፡ ሁለት ፡ የበቁ ፡ ሰዎች ፡ ቢገኙ ፡ በዕፃ ፡ ይሁን ፡ ለማለት ፡ ላብነት ።

ወበጽሐ ፡ ዕፃ ፡ ዲበ ፡ ማትያስ ፡

ለማትያስ ፡ ዕፃ ፡ ወጣለት ፡ ዋጋ ፡ የሚያገኝበት ፡ ነውና ፡ በማትያስ ፡ ዕፃ ፡ ወጣበት ፡ መከራ ፡ የሚቀበልበት ፡ ነውና ፡

ወተኈለቈ ፡ ምስለ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአሐዱ ፡ ሐዋርያት ፡

ከአሥራ ፡ አንዱ ፡ ጋራ ፡ አሥራ ፡ ሁለተኛ ፡ ሁኖ ፡ ተቈጠረ ፡ ምሳ ፡ ፲፮ ፡ ፴፫ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ክፍል ፡ ፬ ።

፩ ፤ ወአመ ፡ ተፈጸመ ፡ መዋዕለ ፡ ጰንጠቈስቴ ።

ጰንጠቆስጤ ፡ ጰንጠቆስቴ ፡ ይላል ፡ መዋዕል ፡ አርባ ፡ ዘጠኙ ፡ ቀን ፡ ጰንጠቆስጤ ፡ አምሳኛይቱ ፡ ቀን ፡ ከአምሳኛይቱ ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ የሚሆን ፡ አርባ ፡ ዘጠኙ ፡ ቀን ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ። አንድም ፡ መዋዕል ፡ ሰሙነ ፡ ጳራቅሊጦስ ፡ ጰንጠቆስጤ ፡ አምሳኛይቱ ፡ ቀን ፡ ከአምሳኛይቱ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ የሚሆን ፡ ሰሙነ ፡ ጳራቅሊጦስ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ዘሌዋ ፡ ፳፫ ፡ ፲፭ ። ም ፡ ፩ ፡ ፲፬ ።

እንዘ ፡ ሀለዉ ፡ ኵሎሙ ፡ ኅቡረ ፡ አሐተኔ ።

ሁሉም ፡ ባንድነት ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ።

፪ ፤ መጽአ ፡ ግብተ ፡ እምሰማይ ፡ ድምፅ ፡ ከመ ፡ ድምፀ ፡ ነፋስ ፡ ዓውሎ ።

ከወደ ፡ ሰማይ ፡ እንደ ፡ ዓውሎ ፡ ነፋስ ፡ ድምፅ ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ ነጐዶ ፡ ተሰማ ፡ አለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ ነፋስ ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ረቂቅ ፡ ነውና ፡ ነፋስ ፡ ኃያል ፡ ነው ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ኃያል ፡ ነውና ፡ ነፋስ ፡ ፍሬውን ፡ ከገለባው ፡ ይለያል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጻድቃንን ፡ ከኃጥአን ፡ ይለያልና ፡ ነፋስ ፡ በምላት ፡ ሳለ ፡ አይታወቅም ፡ ባሕር ፡ ሲገሥፅ ፡ ዛፍ ፡ ሲያናውጥ ፡ ነው ፡ እንጅ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም፡ በምላት ፡ ሳለ ፡ አይታወቅም፡ ቋንቋ፡ ሲያናግር፡ ምስጢር፡ ሲያስተረጉም ፡ ነውና ፡ ነፋስ ፡ መንቅሂ ፡ ነው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ መንቅሒ ፡ ነውና ፡ ነፋስ ፡ መዓዛ ፡ ያመጣል ፡ መንፈስ፡ ቅዱስም፡ መዓዛ፡ ጸጋን ፡ ያመጣልና። አንድም ፡ በነፋስ ፡ ጥቅመ ፡ ራግውን ፡ ባፈረሰ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ፈጅቶበታል፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ለመዓት ፡ እንጅ ፡ ለምሕረት ፡ አልተፈጠረም ፡ ባሉ ፡ ነበርና ፡ ለምሕረትም ፡ እንደ ፡ ተፈጠረ ፡ ለማጠየቅ ፡

ወመልአ ፡ ኵሎ ፡ ቤተ ፡ ኀበ ፡ ሀለዉ ፡ ይነብሩ ።

ያሉበተን ፡ ቤት ፡ መላው ።

፫ ፤ ወአስተርአይዎሙ ፡ ልሳናተ ፡ እሳት ፡ ክፉላት ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ ዘይትከፈል ፡

ላንቃ ፡ ላንቃ ፡ ያለው ፡ እሳት ፡ ሁኖ ፡ ታያቸው ፡ በአምሳለ ፡ እሳት ፡ ዘይትከፈል ፡ ይላል ፡ ላንቃ ፡ ላንቃ ፡ ባለው ፡ እሳት ፡ አምሳል ፡ ታያቸው ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ ዘይትከፈል ፡ ይላል ፡ ላንቃ ፡ ላንቃ ፡ እንዳለው ፡ እሳት ፡ ሁኖ ፡ ታያቸው ፡ ሐተታ ፡ እንደ ፡ ወንጌለ ፡ ማቴዎስ ፡ ምዕ ፡ ፫ ፡ ቍጥር ፡ ፲፪ ።

ወነበረ ፡ ዲበ ፡ ኵሎሙ ፡

በሁሉም ፡ አደረባቸው ፡ ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ፡

ወተመልኡ ፡ ኵሎሙ ፡ መንፈስ ፡ ኃይል ።

ኃይል ፡ የሚሆናቸው ፡ ሀብትን ፡ ሀብት ፡ የሚሆናቸው ፡ ዕውቀትን ፡ ገንዘብ ፡ አደረጉ ።

www.ethiopianorthodox.org



፬ ፤ ወአኀዙ ፡ ይንብቡ ፡ ዘዘዚአሆሙ ፡ በነገረ ፡ ዙሉ ፡ በሐውርት ።

ሁሉም ፡ በየራስ ፡ በየራሳቸው ፡ በሰብዓ ፡ ሁለት ፡ ቋንቋ ፡ መናገር ፡ ዠመሩ ፡

ብከመ ፡ ወሀቦሙ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይንብቡ ።

ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሀብቱን ፡ እንዳደላቸው ፡ መጠን ፡ በሐዋርያት ፡ ሰብዓ ፡ ሁለት ፡ ቋንቋ ፡ አልተከፈለባቸውም ፡ የቀሩት ፡ ግን ፡ ካሥራ ፡ አምስት ፡ በታች ፡ የወረደ ፡ የለም ፡ እን፳ ፡ እንደ ፡ መጠኑ ፡ ኻያም ፡ ኻያ ፡ አምስትም ፡ ሠላሳም ፡ አርባም ፡ አምሳም ፡



[illegible] ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በሐዋርያት ፡ እንዳደረባቸው ።

ስሳም ፡ ተገልጦላቸዋል ፡ ም ፡ ፲ ፡ ፴፬ ።

፭ ፤ ወሀለዉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሰብእ ፡ ኄራን ፡ አይሁድ ፡ ይነብሩ ፡ እምኵሉ ፡ አሕዛብ ፡ ዘመትሕተ ፡ ሰማይ ።

ከሰማይ ፡ በታች ፡ ባለ ፡ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ካሉ ፡ አሕዛብ ፡ ተለይተው ፡ መጥተው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ ደጋግ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡ ከሚጠት ፡ በኋላ ፡ እስራኤል ፡ በወደዱት ፡ አገር ፡ በሕጋቸው ፡ ይኖራሉ ፡ ለበዓል ፡ ይወጣሉ ፡ በዓለ ፡ ፋሲካን ፡ አክብረው ፡ ከዚያ ፡ አያይዘው ፡ ሰባት ፡ ሱባኤ ፡ ቈጥረው ፡ በአምሳኛይቱ ፡ ቀን ፡ በዓለ ፡ ሰዊትን ፡ ለማክበር ፡ አገር ፡ የቀረበው ፡ በየሀገሩ ፡ እየሄደ ፡ አገር ፡ የራቀበት ፡ ሥንቁን ፡ ይዞ ፡ ከዚያው ፡ ይሰነብታል ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የሄዱትም ፡ ተመልሰው ፡ ያሉትም ፡ ተሰብስበው ፡ ባንድነት ፡ ሳሉ ፡ ም፡፲፫ ፡ ፳፮ ።

፮ ፤ ወሰሚያሙ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ፡ ተጋብአ ፡ ኵሎሙ ፡ ድንጉፃኒሆሙ ፡

በሰባ ፡ ሁለት ፡ ቋንቋ ፡ ሲናገሩ ፡ ሰምተዋቸው ፡ የአንክሮ ፡ ድንጋጤ ፡ እየደነገጡ፡ ተሰበሰቡ ፡

እስመ ፡ ሰምዕዎሙ ፡ ይነብቡ ፡ ኵሎሙ ፡ በነገረ ፡ በሐውርቲሆሙ ።

በየሀገራቸው ፡ ቋንቋ ፡ ሲናገሩ ፡ ሰምተዋቸዋልና ።

፯ ፤ ወደንገፁ ፡ ወአንከሩ ፡ ወይቤሉ ፡ አኮኑ ፡ ሰብአ ፡ ገሊላ ፡ እሉ ፡ ኵሎሙ ።

እሊህ፡ ሁሉ፡ የገሊላ፡ሰዎች፡ አይደሉምን ።

፰ ፤ እፎኑ ፡ እንከ ፡ ንሰምዖሙ ፡ ይነብቡ ፡ በነገረ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርቲነ ።

በየሀገራችን ፡ ቋንቋ ፡ ሲናገሩ ፡ እንደምን ፡ እንሰማቸዋለን ፡ ብለው ፡ የአንክሮ ፡ ድንጋጤ ፡ ደነገጡ ፡ ሐተታ ፡ እሊህ ፡ የጥሊላ ፡ ሰዎች ፡ ስንኳን ፡ የሌላ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ያገራቸውን ፡ ቋንቋ ፡ ስንኳ ፡ ያላ ከናወኑ ፡ ናቸውና ፡

እንዘ ፡ ፍጥረትነ ፡ ጸርቱ ፡

ትውልዳችን ፡ ፋርስ ፡

ወሜድ ፡

ሜዶን ፡

ወኢላሜጤ ፡

ኤላም ፡ ሲሆን ፡ በየሀገራችን ፡ ቋንቋ ፡ ሲናገሩ ፡ እንደምን ፡ እንሰማቸዋለን ።

፱ ፤ ወእለሂ ፡ ይነብሩ ፡ ማዕከለ ፡ አፍላግ ፡ አይሁድ ፡

በደሴት ፡ መካከል ፡ የሚኖሩ ፡ አይሁድም ፡ ነበሩ ፡

ወቀጰዶቅያ ፡

በቀጰዶቅያ ፡

ወእስያ ፡

በእስያ ፡

ወፍርግያ ፡

በፍርግያ ፡

ወጵንፍልያ ፡

በጵንፍልያ ፡ የሚኖሩ ፡ አይሁድ ፡ ነበሩ ፡ የምንኖር ፡ አይሁድ ፡ ስንሆን ።

፲ ፤ ወግብፅ ፡

በግብፅ ፡ የሚኖሩ ፡ አይሁድ ፡ ነበሩ ፡ የምንኖር ፡ ስንሆን ፡

ወደወለ ፡ ልብያ ፡

ፋስቆሎ ፡

ወእለሂ ፡ እምቀርኔን ፡

ከቀርኔን ፡

www.ethiopianorthodox.org



ወእለሂ ፡ መጽኡ ፡ እምሮሜ ፡ አይሁድ ፡ ፈላስያን ፡

ከሮም ፡ ተሰደው ፡ የመጡ ፡ አይሁድ ፡ ነበሩ ፡ የመጣን ፡ አይሁድ ፡ ስንሆን ፡

ወእለሂ ፡ እምቀርጤስ ፡

ከቀርጤስ ፡

ወዓረብ ።

ሥናር ፡ ነው ፡ ከሥናር ፡ የመጡ ፡ አይሁድም ፡ ነበሩ ፡ የመጣን ፡ አይሁድ ፡ ስንሆን ።

፲፩ ፤ ወናሁ ፡ ንሰምዖሙ ፡ ይነብቡ ፡ በነገረ ፡ በሐውርቲነ ፡ ዕበያቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

ንሰምዖሙና ፡ ንሰምዖሙ ፡ አንድ ፡ ወገን፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጌትነቱን ፡ በየሀገራችን ፡ ቋንቋ ፡ ሲናገሩ ፡ እንደምን ፡ እንሰማቸዋለን። አንድም ፡ በየሀገራችን፡ ቋንቋ፡ ሲናገሩ ፡ እንሰማቸዋለን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነቱ ፡ ብለው ፡ አደነቁ ።

፲፪ ፤ ወደንገፁ ፡ ኵሎሙ ፡

ሁሉም ፡ የአንክሮ ፡ ድንጋጤ ፡ ደነገጡ ፡

ወኃጥኡ ፡ ዘይብሉ ፡ ወዘይነብቡ ።

ዘይብሉ ፡ ለራሳቸው ፡ ወዘይነብቡ ፡ ለሌላው ፡ የሚመልሱት ፡ ምላሽ ፡ ቸገራቸው።

ወተበሀሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ምንትኑ ፡ እንጋ ፡ ዝ ።

እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይህ፡ ምንድንነው ፡ ተባባሉ ።

፲፫ ፤ ወመንፈቆሙሰ ፡ ሰሐቅዎሙ ፡

እኵሌቶቹ ፡ ግን ፡ ሣቁ ፡ ያደነቁ ፡ ከብሔረ ፡ አሕዛብ ፡ የመጡ ፡ ምዕመናን ፡ አይሁድ ፡ ናቸው ፡ የዋሀን ፡ ይላቸዋልና ፡ የሣቁ ፡ በከተማ ፡ የሚኖሩ ፡ እኩያን ፡ ሰቃልያን ፡ አምላክ ፡ አይሁድ ፡ ናቸው ፡ [illegible]ልና ፡

ወይብሉ ፡ እሉሰ ፡ ፃዕፈ ፡ ጸግቡ ፡ ወሰከሩ ።

እሊህስ ፡ ያልፈላ፡ ጉሽ ፡ ጠጅ ፡ ጠጥተው፡ የሆነ ፡ ያልሆነውን፡ ይቀባጥራሉ፡ ብለው፡ መጥላት ፡ ምቀኝነት ፡ ፈራሽ ፡ ነገር ፡ አናገራቸው ፡ ለልማዱ ፡ ጉሽ ፡ ጠጅ ፡ ቢጠጡት ፡ ከናላ ፡ ይወጣል ፡ አእምሮ ፡ ያለ ፡ በናላ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ስንኳን ፡ የማያውቁትን ፡ ቋንቋ ፡ ሊያናግር ፡ የሚያውቁትን ፡ ስንኳ ፡ ቋንቋ ፡ ያስጠፋል ፡ እንዲህም ፡ ብለው ፡ በተናገሩ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ፍጡራንን ፡ ሰድበው ፡ የቀሩ ፡ አይደለም ፡ ፈጣሪንም ፡ ሰድበዋል ፡ እንጅ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ነገር ፡ ለወይን ፡ ሰጥተው ፡ ከተናገሩ ።

፲፬ ፤ ወቆመ ፡ ጴጥሮስ ፡ ምስለ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአሐዱ ፡

ጴጥሮስ ፡ ካሥራ ፡ አንዱ ፡ ጋራ ፡ ቁሞ ።

ወከልሐ ፡ በቃሉ ፡

በዕብራይስጥ፡ ቋንቋ። አንድም፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ ፡ በታደሰለት ፡ ቃሉ ፡ ተናገረ ፡

ወይቤ ፡ አንትሙ ፡ ሰብአ ፡ ይሁዳ ፡

እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡

ወእለሂ ፡ ትነብሩ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኵልክሙ ፡ አእምሩ ፡ ዘንተ ።

በኢየሩሳሌም ፡ የምትኖሩ ፡ ሁላችሁም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ዕወቁ ፡

ወስምዑኒ ፡ ቃልየ ።

የምነግራችሁን ፡ ነገር ፡ ስሙ ።

፲፭ ፤ አኮ ፡ ከመ ፡ ትትሐዘብዎሙ ፡ አንትሙ ፡ ስኩራን ፡ እሙንቱ ፡ ዘትብሉ ፡

እንዘ ፡ ትብሉ ፡ እናንተ ፡ ጠጥታችሁ ፡ ሰክራችኋል ፡ እያላችሁ ፡ እንደምትጠረጥሯቸው ፡ አይደለም ፡ ጠጥታችሁ ፡ ሰክራችኋል ፡ የምትሉ ፡ እናንተ ፡ እንደምትጠረጥሯቸው ፡ አይደለም ፡

እስመ ፡ ነግህ ፡ ብሔሩ ።

ጊዜው ፡ ነግህ ፡ ነውና ፡ (ጥቅ) ፡ ወትእ
ምርት ፡ ለብሔር ፡ እንዲል ፡

ወሶቤሁ ፡ ሠለስቱ ፡ ሰዓት ።

እልፍም ፡ ቢል ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ነውና ፡
ይላል ፡ ጴጥሮስ። አንድም ፡ ጊዜው፡ ነግህ፡
ነውና ፡ ይላል ፡ ጴጥሮስ ፡ እልፍም ፡ ቢል፤
ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ነበርና ፡ ይላል ፡ ሉቃስ።
አንድም፡ ጊዜው፡ ነግህ፡ ነበርና፡ እልፍም፡
ቢል ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ነበርና ፡ ይላል ፡
ሉቃስ ፡ ባገራቸው ፡ ልማድ ፡ ረታቸው ፡
ባገራቸው ፡ የሚጽፍ ፡ ሲጽፍ ፡ የሚደ
ጉስ ፡ ሲደጉስ ፡ አርፍዶ ፡ ቀትር ፡ ሲሆን ፡
እህል ፡ ቀምሶ ፡ አርፎ ፡ ይነሣልና ።

፲፮ ፤ አላ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ዘይቤ ፡ ኢዩኤል ፡ ነቢይ ፡

ነቢዩ ፡ ኢዩኤል ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡
ቢደርስ ፡ ቢፈጸም ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ይደ
ርስ፡ይፈጸም፡ዘንድ፡ነው፡እንጅ፤ኢዩ፡፫፡፩ ።

፲፯ ፤ ወይከውን ፡ እምድኅረ ፡ ዝ ፡ መዋዕል፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ እሰውጥ ፡ እምነ ፡ መንፈስየ ፡ ዲበ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ።

አምስት ፡ ሺሕ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡
ሲፈጸም ፡ በሥጋዊ ፡ በደማዊ ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ የባሕርይ ፡ ሕይወቴ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስን ፡ አሳድርበታለሁ ፡

ወይትኔበዩ ፡ ደቂቅክሙ ፡

ደቂቅክሙ ፡ ሐዋርያት ፡

ወአዋልዲክሙ ፡

ሠላሳ ፡ ስድስቱ ፡ ቅዱሳት ፡ አንስት ፡

ወወራዙቲክሙ ፡

ሰብዓ ፡ አርድእት ፡ ራእይ ፡ ያያሉ ፡

ወሊቃውንቲክሙ ፡ ሕልመ ፡ የሐልሙ ፡

ጴጥሮስ ፡ በናሕሰ ፡ ኢዮጴ ፡ ዮሐንስ ፡
በደሴተ ፡ ፍጥሞ ፡ ራእይ ፡ ያያሉ ፡

፲፰ ፤ ወላዕለ ፡ አግብርትየ ፡ ወአዕማትየ ፡ እክዑ ፡ እምነ ፡ መንፈስየ ፡

በሰብአ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ የባሕርይ ፡ ሕይ
ወቴ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አሳድርባቸዋ
ለሁ ፡ ይትኔበዩና ፡ ይትኔበዩ ፡ አንድ ፡
ወገን ፤

ወይእተ ፡ አሚረ ፡ ይትኔበዩ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ በሰባ ፡ ሁለት ፡ ቋ
ንቋ ፡ ይናገራሉ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡
ብሎ ፡ ነቢዩ ፡ ኢዩኤል ፡ የተናገረው ፡
ቢደርስ ፡ ቢፈጸም ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ይደ
ርስ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጅ ።
አንድም ፡ (ወይትኔበዩ ፡ ደቂቅክሙ) ፡ ሰብ
ዓ ፡ አርድዕት፡ (ወአዋልዲክሙ)፡ አርባዕ ፡
አዋልደ ፡ ፊልጶስ ፡ (ወወራዙቲክሙ) ፡
እለ ፡ እስጢፋኖስ ፡ እለ ፡ አጋቦስ ፡ (ወሊ
ቃውንቲክሙ)፡ ሐዋርያት ፡ ራእይ፡ ያያሉ፡
አንድም፡ ሊቃውንቲክሙሰ፡ የናንት፡ ሊቃ
ውንት ፡ ሐና ፡ ቀያፋስ ፡ የሐሰት ፡ ትም
ህርት ፡ ያስተምራሉ ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፱ ። (ወላ
ዕለ ፡ አግብርትየ ፡ ወአእማትየ ፡ እክዑ ፡
እምነ ፡ መንፈስየ) ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡
ድረስ ፡ በሚነሱ ፡ በምእመናን ፡ የባሕርይ፡
ሕይወቴ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አሳድርባ
ቸዋለሁ ፡ (ወይእተ ፡ አሚረ ፡ ይትኔበዩ) ፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ በቋንቋ ፡ ይናገራሉ ።

፲፱ ፤ ወእሁብ ፡ ትእምርተ ፡ በሰማይ ፡ በላዕሉ ፡

ከምድር ፡ በላይ ፡ ባለ ፡ በሰማይ ፡ ምል
ክት ፡ አሳያለሁ ፡ ሰማይ ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡
ጠል ፡ ለመከር ፡ እንዳይሰጥ ፡ አደርጋለሁ ፡

ወመንክረ ፡ በምድር ፡ በታሕቱ ፡

ከሰማይ ፡ በታች ፡ ባለ ፡ ምድርም ፡ ምል
ክት ፡ አሳያለሁ ፡ አለ ፡ ምድር ፡ የዘሩባትን፡
እንዳታበቅል ፡ [illegible]
ጸድቅ ፡ አደርጋለሁ ፡



ደመ ፡

ደመ ፡ በጼዋዌ ፡ የእስራኤል ፡ ደማቸው ፡
ይፈሳል ፡

ወእሳተ ፡

ቤታቸው ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላል ፡

ወጢሰ ፡

ጢስ ፡ ይታያል ።

፳ ፤ ፀሓይኒ ፡ ይጸልም ፡

ፀሓይ ፡ ጨለማ ፡ ይሆናል ፡ አለ ፡ ፀሓይ ፡
ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ይጠፋል ፡

ወወርኅኒ ፡ ደመ ፡ ይከውን ፡

ጨረቃም ፡ ደም ፡ ይሆናል ፡ አለ ፡ ወርኅ ፡
ንጉሡ ፡ ይጠፋል ።

፳፩ ፤ ዘእንበለ ፡ ትብጻሕ ፡ ዕለተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐባይ ፡ ወግርምት ፡ ወኵሉ ፡ ዘጸውዐ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይድኅን ።

ዐባይ ፡ ግርምት ፡ የምትሆን ፡ ዕለተ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ዕለተ ፡ ጼዋዌ ፡ ሳትደስር ፡ ስመ ፡
እግዚአብሔርን ፡ የጠራ ፡ ሁሉ ፡ ይድናል ፡
እንባቆም ፡ ለጼዋዌ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡
ሲቀር ፡ ፍልስጥኤም ፡ ሂዶ ፡ ድኗል ።
አንድም ፡ በሚጠት ፡ ቢሉ ፡ ደመ ፡ የአ
ሕዛብ ፡ ደማቸው ፡ ይፈሳል ፡ ወእሳተ ፡
ቤታቸው ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላል ፡ ወጢሰ ፡
ጢስ ፡ ይታያል ። ፀሓይኒ ፡ ይጸልም ፡ ፀሓ
ይ ፡ የአሕዛብ ፡ ንጉሡ ፡ ይጠፋል ፡ ወወ
ርኅኒ ፡ ደመ ፡ ይከውን ፡ ወርኅ ፡ ቢትወ
ደዱ ፡ ይጠፋል ፡ ዘእንበለ ፡ ትብጻሕ ፡
ዕለተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓባይ ፡ ወግር
ምት ፡ ዕለተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕለተ ፡
ሚጠት ፡ ሳትደርስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ስም ፡ የጠራ ፡ ሁሉ ፡ ይድናል ። አንድም ፡
በሰማይ ፡ ምልክት ፡ አሳያለሁ ፡ በምድር
ም ፡ ምልክት ፡ አሳያለሁ ፡ ሁለት ፡ አር
እስት ፡ ተናግሯል ፡ ለሁለቱም ፡ ያመጣ
ል ፡ (ደመ) ፡ ምድር ፡ ላለው ፡ አመጣ ፡
ደመ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈሳል ፡
(ወእሳተ) ፡ ሰማይ ፡ ላለው ፡ አመጣ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአምሳለ ፡ እሳት ፡ ይሰ
ጣል ፡ ወጢሰ ፡ ስለ ፡ ሀብቱ ፡ ብዛት ። አን
ድም ፡ አንድ፡ ወገን፡ ምድር፡ ላለው፡ ደመ፡
ደመ፡ ወልደ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈሳል ፡ ወ
እሳተ ፡ሙቀት ፡ ያለው ፡ ነውና ፡ ወጢሰ ፡
ተንታ ፡ ያለው ፡ ነውና ፡ ፀሓይኒ ፡ ይጸ
ልም ፡ ፀሓይ ፡ ሰማይ ፡ ላለው ፡ አመጣ ፡
ፀሓይ ፡ ጨለማ ፡ ይሆናል ፡ ወወርኅኒ ፡
ደመ ፡ ይከውን ፡ ጨረቃም ፡ ደም ፡ ይሆ
ናል ፡ ዘእንበለ ፡ ትብጻሕ ፡ ዕለተ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ዐባይ ፡ ወግርምት ፡ ወኵሉ ፡
ዘጸውዐ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይድኅን ፡
ዕለተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕለተ ፡ ትንሣኤ ፡
ሳትደርስ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የጠ
ራ ፡ ሁሉ ፡ ይድናል ፡ ፈያታዊ ፡ ዘየማን ፡
ተዘከረኒ ፡ እግዚኦ ፡ በውስተ ፡ መንግሥ
ትከ ፡ ብሎ ፡ ድኗል ። አንድም ፡ በሰማይ ፡
ምልክት ፡ አሳያለሁ ፡ አለ ፡ በሮም ፡ አን
ጻርና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አንጻር ፡ ያሉ ፡
ከዋክብት ፡ ሰልፍ ፡ ሠርተው ፡ ሲዋጉ ፡
በሮም ፡ አንጻር ፡ ያሉት ፡ በኢየሩሳሌም ፡
አንጻር ፡ ያሉትን ፡ ድል ፡ ሲያደርጓቸው ፡
ታይቷል ፡ ይህን ፡ ምልክት ፡ አድርገው ፡
መጥተው ፡ ወግተዋቸዋል ፡ በምድርም ፡
ምልክትን፡ አሳያለሁ፡ አለ ፡ ይቤ ፡ ቃል ፡
ለለፍኖቱ ፡ እንዲል ፡ ዕንጨት ፡ ሰባሪው ፡
ውኃ ፡ ቀጂው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትጠፋለች ፡
ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ትፈርሳለች ፡ የሚል ፡ ሁኗ
ል። አንድም ፡ መልአክ፡ በአምሳለ፡ ወሬዛ፡
ሠናየ ፡ ላህይ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ አን
ጻር ፡ ዘልቆ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትጠፋለች ፡
ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ትፈርሳለች ፡ ሲል ፡ ተሰ

www.ethiopianorthodox.org

ምቷል።አንድም፡ የቤተ፡ መቅደስ፡ ቅጽሩ፡ ሦስት ፡ ነው ፡ ሦስተኛው ፡ ገና ፡ አልተፈ ጸመም ፡ ነበር ፡ ይህ ፡ ሲጨረስ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ትፈርሳለች ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትጠፋለች ፡ የሚል ፡ ንግር ፡ ነበርና ፡ ጥጦስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በሩን ፡ ይዘን ፡ መ ዋጊያ ፡ ይሆነናል ፡ ብለው ፡ እጅ ፡ በጅ ፡ ብለው፡ ጨርሰውታል፡ መጥቶ፡ አጥፍቷቸ ዋል። አንድም፡ ለመሥዋዕት፡ ያቀረቧት ፡ ላም ፡ በግ ፡ ወልዳለች ፡ መሥዋዕታች ሁን ፡ እለውጠዋለሁ ፡ ሲል ። አንድም ፡ ተለውጣ ፡ አህያ፡ ሁናለች ፡ መሥዋዕታች ሁን፡እጸየፈዋለሁ፡ሲል።አንድም፡ላምሳ፡ ለስሳ ፡ ካልሆነ ፡ የማይከፈት ፡ የብረት ፡ ሣንቃ ፡ ከመዝ ፡ ሀለወነ ፡ ንትረኀው ፡ በበይናቲነ ፡ እያለ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ እየተ ከፈተ ፡ የሚገኝ ፡ ሆኗል ፡ ደመ ፡ በጥጦስ፡ የአይሁድ ፡ ደማቸው ፡ ይፈሳል ፡ ቤታ ቸው ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላል ፡ ጢስ ፡ ይታ ያል ፡ ፀሐይ ፡ ጨለማ ፡ ይሆናል ፡ ጨረ ቃም ፡ ደም ፡ ይሆናል ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ እንደተፈረደባቸው ፡ ለማጠየቅ ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ የተደረገው፡ ሁሉ ፡ ተአምራት ፡ ተደርጎባቸዋል ፡ ዕለተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕለተ ፡ ጥጦስ ፡ ሳትደርስ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የጠ ራ ፡ ሁሉ ፡ ይድናል ፡ ስምዖን ፡ የሚባል ፡ ኤጲስ፡ ቆጶስ ፡ ፸ ፡ ረበዋትን ፡ ይዞ ፡ ወጥ ቷል ፤ ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፲፫ ።

፳፪ ፤ ስምዑ ፡ ሰብአ ፡ እስራኤል ፡ ዘንተ ፡ ነገረ፡ ኢየሱስሃ ፡ ናዝራዌ ፡ ብእሴ ፡ ዘአርአየክሙ ፡ እግዚ አብሔር ።

እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እግዚአ ብሔር ፡ የገለጸላችሁ ፡ የናዝሬት ፡ ሰው ፡ የኢየሱስን፡ ነገር፡ ስሙ። አንድም ፡ ኢየሱ ስና ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ የገለጸላችሁን ፡ ነገር ፡ ስሙ ፡

በኃይል ፡

ዘአርአየክሙ ፡ በኃይል ፡ ምውት ፡ በማ ስነሣት ፡

ወበተአምር ፡

ድውይ ፡ በመፈወስ ።

ወበመንክር ።

ጋኔን ፡ በማውጣት ፡ የገለጸላችሁን ፡ ነገር ፡ ስሙ ።

ዘገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእደዊሁ ፡ በማዕከሌክሙ ።

እግዚአብሔር ፡ በሥልጣኑ ፡ በናንት ፡ መካከል ፡ ባደረገው ፡ ጋኔን ፡ በማውጣት ፡ ድውይ ፡ በመፈወስ ፡ ምውት ፡ በማስ ነሣት ፤ ም ፡ ፲ ፡ ፴፰ ።

፳፫ ፤ ዘከመ ፡ ርኢክምዎ ፡ በሥርዐተ ፡ ምክሩ ፡ ወበአእምሮቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔር ፡ ወዶ ፡ መክሮ ፡ ባደረ ገው ፡ ሥጋዌ ፡ እንዳያችሁት ፡ መጠን ፡ ወበአእምሮ ፡ ቅድምናሁ ፡ ወበቅድምና ፡ አእምሮቱ ፡ ይላል ፡ ቅድምናውን ፡ ሥጋ ዌውን ፡ እንዳያችሁት ፡ መጠን ፡

ወመጠውክምዎ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ኃጥአን ፡

ለኃጥአን ፡ አሳልፋችሁ ፡ ሰጣችሁት ፡

ወሰቀልክምዎ ፡ ወቀተልክምዎ ።

ሰቅላችሁ ፡ ገደላችሁት ፤ ም ፡ ፬ ፡ ፳፰ ።

፳፬ ፤ ወእግዚአብሔር ፡ አንሥአ ፡ እምውታን ፡ ፈቲሖ ፡ ማዕሠሪሁ ፡ ለሞት ፡

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ የሞት ፡ ቍራኘ ነትን፡አጥፍቶ፡ከሙታን፡ለይቶ፡አስነሣው፡

እስመ ፡ ኢይክል ፡ እኂዞቶ ፡ ሞት ።

ሞት ፡ ሊይዘው ፡ ሊገታው ፡ አይቻለውም ና ፤ ም ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።



፳፭ ፤ ወዳዊትኒ ፡ ይቤ ፡ በእንቲአሁ ።

የሞት ፡ ቍራኝነትን ፡ አጥፍቶ ፡ እንዳ ስነሣው ፡ ሞት ፡ ሊገታው፡ እንዳይቻለው፡ ሲያስረዳ ፡ ዳዊት ፡ የሱን ፡ ተናገረ ፡

ዘልፈ ፡ እሬእዮ ፡ ለእግዚአብሔር፡ ቅድሜየ፡ ውእቱ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ።

እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድን ፡ ሁልጊዜ ፡ በፊቴ ፡ አየዋለሁ ፡ አለ ፡ በህልውናየ ፡ ነው ።

፳፮ ፤ እስመ፡ በየማንየ፡ ውእቱ፡ ከመ፡ ኢይትሀወክ ፡

እንዳይለይ ፡ በቀኜ፡ ነውና ፤ መዝ፡ ፲፮፡፰ ።

ወበእንተዝ ፡ ተፈሥሐ ፡ ልብየ ፡

ስለዚህ ፡ እኔን ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡

ወተሐሥየ ፡ ልሳንየ ፡

ቃሌን ፡ ወልድንም ፡ ደስ ፡ አለው ። አንድ ም ፡ (ዘልፈ፡ እሬእዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅ ድሜየ ፡ ውእቱ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ)፡ እግዚአ ብሔር ፡ ወልድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብን ፡ ሁልጊዜ ፡ በፊቴ ፡ በህልውናዬ ፡ አየ ዋለሁ ፡ አለ ። (እስመ ፡ በየማንየ) ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ኢይትሀወክ ፤ እንዳይ ለይ ፡ በቀኝ ፡ ነውና ፡ ምነው ፡ ወልድ ፡ ይነብር ፡ በየማነ ፡ አብ ፡ ይላል ፡ እንጅ ፡ አብ ፡ ይነብር ፡ በየማነ ፡ ወልድ ፡ ይላ ልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ መቸስ ፡ ለሥ ላሴ ፡ ቀኝ ፡ ግራ ፡ አላቸውን ፡ በክብር፡ ሲል፡(ጥቅ)፡እስመ፡ነቢር፡በዕሪና፡ያኤምር፡ ኀበ ፡ ተዋሕዶቶሙ ፡ በክብር ፡ እንዲል ፡ (ወበእንተዝ ፡ ተፈሥሐ፡ ልብየ)፤ ስለዚህ፡ ልቤን ፡ አብን ፡ ደስ ፡ አለው ፤ ወተሐ ሥየ ፡ ልሳንየ ፤ እኔንም ፡ ደስ ፡ አለኝ ።

፳፯ ፤ ወዓዲ ፡ በተስፋሁ ፡ ኀደረ ፡ ሥጋየ ፡

ዳግመኛም፡ ያስነሣኛል፡ በማለት፡ ተስፋ፡ ሰውነቴ ፡ ጸና ፡(ጥቅ)፡ መኑ ፡ ዘአስተኀደረ፡ ማዕዘኒሃ፡ ለምድር፡ እንዲል።አንድም፡ ያስ ነሣኛል ፡ በማለት ፡ ተስፋ ፡ ሥጋዬ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከ ርሠ ፡ መቃብር ፡ አደረ ፡

እስመ ፡ ኢተኀድጋ ፡ ውስተ ፡ሲኦል ፡ ለነፍስየ ፡

ነፍሴን ፡ በሲኦል ፡ አትተዋትምና ፡

ወኢትሁቦ ፡ ለጻድቅከ ፡ ይርአይ ፡ሙስና ፡

ኢትሁቦ ፡ ጻድቅከ ፡ ይርአይ ፡ ጻድቅ ፡ ልጅህ ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ ያይ ፡ ዘንድ፡ ኢትሁቦ ፡ ለጻድቅከ ፡ ጻድቅ ፡ ልጅህን ፡ ለሙስና ፡ መቃብር ፡ አሳልፈህ ፡ አትሰ ጠውም ።

፳፰ ፤ ወመራኀከኒ ፡ ፍኖተ ፡ ሕይወት ፡

አይሁድ ፡ ፍኖተ ፡ ሞትን ፡ ቢመሩኝ ፡ አንተ ፡ ፍኖተ ፡ ትንሣኤን ፡ መራኸኝ ፡

ወአጽገብከኒ ፡ ሐሤተ ፡ ምስለ ፡ ገጽከ ፡

ከነቢር ፡ በየማን ፡ ጋራ ፡ ትንሣኤን ፡ ዕር ገትን ፡ ሰጥተኸኝ ። አንድም ፡ ከባለሟ ልነት ፡ ጋራ ፡ በፍጹም ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ አሰኘኸኝ ፡ (ጥቅ) ፡ እስመ ፡ አልበስከኒ ፡ ልብሰ ፡ ትፍሥሕት ፡ ወልብሰ ፡ መድኃ ኒት ፡ እንዲል ፡

ወትፍሥሕት ፡ ውስተ ፡ የማንከ ፡ ለዝሉፉ ።

በኔ ፡ በልጅህ ፡ ድኅነተ ፡ ምእመናን ፡ ተደ ረገ ፡ ልጅነት ፡ ተሰጠ ።

፳፱ ፤ ታብውሁኒሁ ፡ እንከ ፡ አሰብእ ፡ እንግርክሙ ፡ ክሡተ ፡ በእንተ ፡ ዳዊት ፡ ርእሰ ፡ አበው ፡

እስመ ፡ ኢተኀድጋ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ለነፍስየ ፡ እያለ ፡ መጥቶ ፡ ነበርና ፡ ይህ ንማ ፡ ዳዊት ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ተናግሮት ፡ የለም ፡ እንዲሉት ፡ አውቆ ፡ አመጣ ፡ እንዲሉትም ፡ አውቆ ፡ ማምጣት ፡ ልማ ድ ፡ ነው ፡ ዮሐንስ ፡ ትውልደ ፡ አራዊት፡ ምድር ፡ ቢላቸው ፡ አብርሃምን ፡ ያህል ፡

www.ethiopianorthodox.org

አባት ፡ ሳለን ፡ ትውልደ ፡ አራዊተ ፡ ምድር ፡ ይለናል ፡ እንዲሉት ፡ አውቆ ፡ ኢይምሰልክሙ ፡ በብሂል ፡ ዘትብሉ ፡ አብ ፡ ብነ ፡ አብርሃም ፡ ዘታመሥጡ ፡ እንዳለ ፡ ጌታም ፡ ብፁዓን ፡ ብፁዓን ፡ እያለ ፡ ሲያስተምር ፡ ሰምተው ፡ አሪትን ፡ ነቢያትንማ ፡ እንጅ ፡ ሊያሳልፋቸው ፡ መጥቷል ፡ እንዲሉት ፡ አውቆ ፡ ኢይምሰልክሙ ፡ ዘመጻእኩ ፡ እስዓሮሙ ፡ ለኦሪት ፡ ወለነቢያት ፡ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ እፈጽሞሙ ፡ እንዳለ ፡ ከዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ወንድሞቻችን ፡ የአበው ፡ ጥንታቸው ፡ የሚሆን ፡ የዳዊትን ፡ ነገር ፡ ገልጬ ፡ እነግራችሁ ፡ ዘንድ ፡ ታሰናብቱኛላችሁን ፡

ከመሂ ፡ ሞተ ፡

እንደ ፡ ሞተ ፡

ወተቀብረ ፡

እንደ ፡ ተቀበረ ፡

ወኀቤነ ፡ ሀሎ ፡ መቃብሪሁ ፡ እስከ ፡ ዮም ።

እስከ ፡ ዛሬ ፡ መቃብሩ ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለ ፡ መቃብሩማ ፡ ወዴት ፡ ይሄድ ፡ ኑሯል ፡ ፈርሶ ፡ በስብሶ ፡ እንዳለ ፡ እነግራችሁ ፡ ዘንድ ፡ ታሰናብቱኛላችሁን ፤ ም ፡ ፲፫ ፡ ፴፯ ። ፩ ፡ ነገሥ ፡ ፪ ፡ ፲ ።

፴ ፤ እስመ ፡ ነቢይ ፡ ውእቱ ።

ነቢይ ፡ ነውና ።

ወአእመረ ፡ ከመ ፡ በመሐላ ፡ መሐለ ፡ ሎቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ እምፍሬ ፡ ከርሡ ፡ ያነብር ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ።

ከባሕርዩ ፡ የተከፈለ ፡ ልጁን ፡ እንዲያነግሥለት ፡ እንደማለለት ።

፴፩ ፤ አቅዲሙ ፡ አእሚሮ ፡ ነገረ ፡ ከመ ፡ ይትነሣእ ፡ ክርስቶስ ፡ እምዉታን ።

አእመረና ፡ አእሚሮ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ከሙታንም ፡ ለይቶ ፡ እንዲያስነሣለት ፡ አውቆ ፡ አስቀድሞ ፡ ተናገረ ፡ እንጅ ። አንድም ፡ ነቢይ ፡ እሱ ፡ ከባሕርዩ ፡ የተከፈለ ፡ ልጁን ፡ በዙፋኑ ፡ እንዲያነግሥለት ፡ እንደማለለት ፡ ከሙታንም ፡ ለይቶ ፡ እንዲያስነሣለት ፡ አውቋልና ፡ አስቀድሞ ፡ ተናገረ ፡ እንጅ ። አንድም ፡ አእመረንና ፡ አእሚሮን ፡ በየራሱ ፡ ለማውጣት ፡ ነቢይ ፡ እሱ ፡ ከባሕርዩ ፡ የተከፈለ ፡ ልጁን ፡ እንዲያነግሥለት ፡ እንደማለለት ፡ እንዳወቀ ፤ መዝ ፡ ፹፱ ፡ ፬ ፡ ፰ ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ። ከሙታንም ፡ ለይቶ ፡ እንዲያስነሣለት ፡ አውቆ ፡ ተናገረ ፡ እንጅ ።

ወከመ ፡ ኢትትኀደግ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ነፍስቱ ፡

ሥጋው ፡ በመቃብር ፡ ፈርሳ ፡ በስብሳ ፡ እንዳትቀር ፡

ወከመሂ ፡ ኢይሬኢያ ፡ ለሙስና ።

ሙስና ፡ መቃብርም ፡ እንዳያገኛት ፡ አስቀድሞ ፡ ተናገረ ፡ እንጅ ፡ ሎቱ ፡ ለኢየሱስ ፡ አንሥአ ፡ ማንሻ ። አንድም ፡ ሙስና ፡ መቃብር ፡ እንዳያገኘው ።

፴፪ ፤ ሎቱ ፡ ለኢየሱስ ፡ አንሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወንሕነ ፡ ኵልነ ፡ ሰማዕቱ ።

ኢየሱስን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ አስነሣው ፡ እንዳስነሣውም ፡ ምስክሮቹ ፡ ነን ።

፴፫ ፤ ከመ ፡ በየማነ ፡ እግዚአወሔር ፡ ተለዓለ ፡

ተነሥቶም ፡ በአብ ፡ ቀኝ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ እኛ ፡ ምስክሮቹ ፡ ነን ።

ወነሢኦ፡እምኀበ፡አቡሁ፡ዘአሰፈዎ፡መንፈሰ፡ቅዱሰ ።

እሰውጥ ፡ እምነ ፡ መንፈስየ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ብሎ ፡ ያናገረው ።

ሦጠ ፡ ላዕሌነ ፡ ለዝ ፡ ዘትሬእዩ ፡ ወዘትሰምዑ ።

ይህን ፡ በአምሳለ ፡ እሳት ፡ የምታዩትን ፡ በአምሳለ ፡ ነፋስ ፡ የምትሰሙትን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ከአባቱ ፡ ነሥቶ ፡ በኛ ፡ አሳድሮታል ፡ እንዳሳደረው ፡ እኛ ፡ ምስክሮቹ ፡ ነን ፡ ነሢእ ፡ ሳይኖር ፡ ነሢአ አለ ፡ (ጥቅ) ፡ ወነሥአ ፡ እመንፈስ ፡ ዘላዕለ ፡ ሙሴ ፡ ወሦጠ ፡ ላዕለ ፡ ካልአን ፡ እንዲል ።

፴፬ ፤ ቦኑ ፡ ዳዊት ፡ ዐርገ ፡ ሰማየ ፡

ስለ ፡ ራሱማ ፡ ተናግሮታል ፡ ትሉት ፡ ዘንድ ፡ በውኑ ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዓረገን ፡

ኢይቤኑ ፡ ለሊሁ ፡ ዳዊት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ለእግዚእየ ፡ ንበር ፡ በየማንየ ።

ስለ ፡ ራሱ ፡ እንዳይደለ ፡ ስለ ፡ ጌታ ፡ እንደሆነ ፡ ሲያስረዳ ፡ እርሱ ፡ ቅሉ ፡ ዳዊት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገልጦለት ፡ እግዚእ ፡ አብ ፡ እግዚእየ ፡ ወልድን ፡ በዕሪናዬ ፡ ኑር ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ የለምን ፡ መዝ ፡ ፻፲ ፡ ፩ ።

፴፭ ፤ እስከ ፡ አገብኦሙ ፡ ለጸላእትከ ፡ ታሕተ ፡ መከየደ ፡ እገሪከ ፡

ጠላቶችህን ፡ በእግርህ ፡ እርግጥ ፡ በጅህ ፡ ጭብጥ ፡ አድርጌ ፡ እስካስገዛልህ ፡ ድረስ ፡ በዕሪናዬ ፡ ኑር ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ የለምን ፡ የማን ፡ የባለቤትነት ፡ ነቢር ፡ የእንግድነት ። አንድም ፡ ነቢር ፡ ቅሉ ፡ የእንግድነት ፡ የባለቤትነት ፡ ይሆናል ።

፴፮ ፤ ጥዩቀ ፡ እንከ ፡ ያእምሩ ፡ ኵሉ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡ ከመ ፡ እግዚእኒ ፡ ወመሢሐኒ ፡ ረሰዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘአንትሙ ፡ ሰቀልክምዎ ።

እናንት ፡ ሰቅላችሁ ፡ የገደላችሁትን ፡ ኢየሱስን ፡ እግዚአብሔር ፡ እግዚእ ፡ መሢሕ ፡ እንዳደረገው ፡ በጉላ ፡ በተረዳ ፡ ነገር ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፡ ይወቁ ፡ እግዚእ ፡ የማንን ፡ መሢሕ ፡ ነቢርን ፡ ያያል ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፴፩ ።

፴፯ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ ተከሥተ ፡ ልቦሙ ፡

ይህንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ልቡናቸውን ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ አመኑ ፡

ወይቤልዎሙ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ወለቢጹ ፡ ሐዋርያት ፡ ምንተ ፡ ንግበር ፡ አኃዊነ ።

ጴጥሮስን ፡ ወንድሞቹን ፡ ሐዋርያትንም ፡ ጠርተው ፡ ወንድሞቻችን ፡ ምን ፡ እናድርግ ፡ አሏቸው ፡ ግብር ፡ ገብተው ፡ በአእምሮ ፡ ፍጹማን ፡ ያልሆኑ ፡ ናቸውና ፡ አኀዊን ፡ አሉ ፡ እንጅ ፡ እንደነገሩስ ፡ አጋእዝቲነ ፡ መምህራኒነ ፡ አበዊነ ፡ ሊቃውንቲነ ፡ ባሉ ፡ ባማረ ፡ በተገባ ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ፴ ።

፴፰ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ጴጥሮስ ፡ ነስሑ ፡ ወተጠመቁ ፡ ኵልክሙ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

ድኀነትስ ፡ ከሻችሁ ፡ ሁላችሁም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አምናችሁ ፡ ተጠመቁ ፡

ወይትኀደግ ፡ ለከሙ ፡ ኃጢአትከሙ ፡

ኃጢአታችሁ ፡ ይሠረይላችኋል ፡

ወትነሥኡ ፡ ጸጋሁ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ጸጋውን ፡ ታገኛላችሁ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ፲፬ ።

፴፱ ፤ እስመ ፡ ለከሙ ፡ ውእቱ ፡ ተስፋሁ ፡

ተስፋነቱ ፡ ለናንት ፡ ነውና ፡

ወለውሉድክሙ ፡

ለልጆቻችሁም ፡ ነውና ።

ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ርሑቃን ፡ እለ ፡ ጸውዖሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ከተስፋው ፡ ርቀው ፡ ለነበሩ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ወደተስፋው ፡ ለጠራቸው ፡ ለአሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ ነውና ፡ ኢዩ ፡ ፫ ፡ ፳ ።

፵ ፤ ወባዕደኒ ፡ ብዙኀ ፡ ነገረ ፡ ነገሮሙ ።

ከዚህ ፡ አያይዞ ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ነገራቸው ፡ አለ ፡ ምስጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ ነገራቸው ፡



www.ethiopianorthodox.org

ወገሠጾሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ አድኅኑ ፡ ነፍሰክሙ ፡ እምዝ ፡ ዓለም ፡ እኩይ ።

ከፈ.ቃደ ፡ ሰይጣን ፡ ከፈ.ቃደ ፡ ሥጋ ፡ ሰው ነታችሁን ፡ አድኑ ፡ ብሎ ፡ መከራቸው ።

፵፩ ፤ ወተወክፉ ፡ ቃሎ ፡

ትምህርቱን ፡ ተቀበሉ ፡

ወተጠምቁ ፡

አምነው ፡ ተጠመቁ ፡

ወተወሰኩ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ መጠነ ፡ ሠላሳ ፡ ምእት ፡ ነፍስ ።

ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ያህል ፡ ሰዎች ፡ ተጨመሩ ፡ ተወሰኩ ፡ በሙቶ ፡ ኻያ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ላይ ፡ ነው ።

፵፪ ፤ ወነበሩ ፡ ይፀመዱ ፡ ትምህርተ ፡ ሐዋርያት ፡

ከሐዋርያት ፡ በመማር ፡ የሐዋርያትን ፡ ትምህርት ፡ በመማር ፡ ፅሙዳን ፡ ሁነው ፡ ኖሩ ። አንድም ፡ ሐዋርያት ፡ በማስተማር ፡ ፅሙዳን ፡ ሁነው ፡ ኖሩ ፡

ወኅቡረ ፡ ይባርኩ ፡ ማዕደ ፡ በውስተ ፡ ጸሎት ።

በጸሎተ ፡ ቅዳሴም ፡ ጊዜ ፡ ባንድነት ፡ ሥጋ ውን ፡ ደሙን ፡ ያከብሩ ፡ ይለውጡ ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፺ ።

፵፫ ፤ ወፈርሀሙ ፡ ኵሉ ፡ ዘነፍስ ፡

ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ፈራቸው ፡ እስ ፡ አከበራቸው ፡

ወብዙኅ ፡ ተአምር ፡ ወመንክር ፡ ይከውን ፡ በእደዊሆሙ ፡ ለሐዋርያት ፡

በሐዋርያት ፡ ቃል ፡ በሐዋርያት ፡ ሥል ጣን ፡ ብዙ ፡ ደጋግ ፡ ተአምራት ፡ ይደ ረግ ፡ ነበር ።

፵፬ ፤ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ ኅቡረ ፡ ይነብሩ ፡

ያመኑትም ፡ ሁሉ ፡ ባንድነት ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፴፪ ፡

ወድሙር ፡ ኵሉ ፡ ንዋዮሙ ።

ገንዘባቸውም ፡ ሁሉ ፡ ባንድነት ፡ ነበር ።

፵፭ ፤ ወጥሪቶሙ ፡ ይሠይጡ ፡ ወይሁቡ ፡ ለነዳያን ።

ገንዘባቸውንም ፡ ሁሉ ፡ እየሸጡ ፡ ለነዳ ያን ፡ ይመጸውቱ ፡ ነበር ።

፵፮ ፤ ወኵሎ ፡ አሚረ ፡ ይፀመዱ ፡ በአሐዱ ፡ ነፍስ ፡ ወበአሐዱ ፡ ሕሊና ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡

በቤተ ፡ መቅደስም ፡ ሁልጊዜ ፡ አንዳንድ ፡ ልብ ፡ መካሪ ፡ እንዳንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ሁነው ፡ ሲያገለግሉ ፡ ኖሩ ፡

ወይባርኩ ፡ ማዕደ ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡

በቤትም ፡ ጸሎተ ፡ ማዕድ ፡ እየጸለዩ ።

ወይሴሰዩ ፡ ሲሳዮሙ ፡ በትፍሥሕት ፡ ወበየውሀተ ፡ ልብ ።

ምግባቸውን ፡ ባንድነት ፡ ይመገቡ ፡ ነበ ር ፡ በትፍሥሕት ፡ የሌለው ፡ ሳይሰቀቅ ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ በየውሃት ፡ ያለው ፡ ሳይ መካ ፡ በቅንነት ፡ ቍ ፡ ፵፪ ።

፵፯ ፤ ወያአኵቱ ፡ እግዚአብሔርሃ ።

እግዚአብሔርንም ፡ ያመሰግኑ ፡ ነበር ፡

ወቦሙ ፡ ሞገስ ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡

በሕዝቡም ፡ ዘንድ ፡ መወደድ ፡ ባለሟ ልነት ፡ ነበራቸው ፡

ወእንተ ፡ ጸብሐት ፡ ይዌስክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዲቤሆሙ ፡ ለእለ ፡ ሐይዉ ።

የሚያምኑትንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ያበዛቸው ፡ ነበር ፡ እንተ ፡ ጸብ ሐት ፡ ይዌስክ ፡ ይዌስክ ፡ ዲቤሆሙ ፡ ዲቤሆሙ ፡ እለ ፡ ሐይዉ ፡ እንተ ፡ ጸብ ሐት ፡ እለ ፡ ሐይዉ ።



## ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ክፍል ፡ ፳ ።

፩ ፤ ወዐርጉ ፡ ምኵራበ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወዮሐንስ ፡ ጊዜ ፡ ተሱዓት ፡ ለጸሎት ።

ዕለቱን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ በነጋውም ፡ ቢሉ ፡ በሳምንቱም ፡ ቢሉ ፡ ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ሊጸልዩ ፡ ወደ ፡ ምኵራቡ ፡ ገቡ ፡ (ጥቅ) ፡ ወዓርጉ ፡ ቤተ ፡ አዎን ፡ ክል ኤቱ ፡ ዕደው ፡ ዓርጉ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንዲል ። አንድም ፡ እርከን ፡ እርከን ፡ ያለው ፡ ነውና ፡ ወደ ፡ ምኵራቡ ፡ ወጡ ፡ ጌታ ፡ በተሰቀለ ፡ ጊዜ ፡ አድሮባት ፡ የነ በረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በነጭ ፡ ርግብ ፡ አምሳል ፡ ተለይቶ ፡ ወጥቶ ፡ ሲሄድ ፡ ታይ ቷል ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገበያ ፡ እንደ ፡ በረት ፡ ሆነች ፡ ይላል ፡ ምን ፡ ብለው ፡ ይጸልዩባታል ፡ ቢሉ ፡ ጴጥሮስና ፡ ዮሐ ንስ ፡ ምኵራበ ፡ ወንጌል ፡ ብለው ፡ ይጸ ልዩባታል ፡ እንጅ ፡ ምኵራበ ፡ አሪት ፡ ብለው ፡ ይጸልዩባታልን ፡ ያውስ ፡ ቢሆን ፡ ጸሊ ፡ በኀቡዕ ፡ ይል ፡ የለም ፡ ቢሉ ፡ ለሰ ው ፡ አብነት ፡ የማይሆኑበትን ፡ ተሠው ረው ፡ ይሠሩታል ፡ ለሰው ፡ አብነት ፡ የሚ ሆኑበትን ፡ ገልጠው ፡ ይሠሩታልና ፡ ይህ ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ አብነት ፡ የሚሆኑበት ፡ ነውና ።

፪ ፤ ወሀሎ ፡ ብእሲ ፡ ዘዕዉስ ፡ እገሪሁ ፡ ተወልደ ፡ ከማሁ ፡ እምከርሠ ፡ እሙ ፡

ከናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ጀምሮ ፡ ልምሾ ፡ ሁኖ ፡ የተወለደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡

ወይጸውርዎ ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ፡ ወያነብርዎ ፡ በኆኅተ ፡ ምኵራብ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ኦርያ ፡

ዕለት ፡ ዕለት ፡ እየተሸከሙ ፡ እየወሰዱ ፡ ኦርያ ፡ በምትባል ፡ በምኵራብ ፡ ደጅ ፡ ይጥሉት ፡ ነበር ፡ ኦርያን ፡ ለምኵራብ ፡ ቢቀጥሉ ፡ እድምተ ፡ ስን ፡ ሠናይተ ፡ ሱራሬ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ለኆኅት ፡ ቢቀጥሉ ፡ የብርሃን ፡ ፀሓይ ፡ መግቢያ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከመ ፡ ይስአል ፡ ምጽዋተ ፡ እምኀበ ፡ እለ ፡ ይበውኡ ፡ ምኵራበ ፡

ወደ ፡ ምኵራቡ ፡ ከሚገቡት ፡ ሰዎች ፡ ምጽዋት ፡ ይለምን ፡ ዘንድ ፡ ያስቀምጡት ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ፰ ።

፫ ፤ ወርእዮሙ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ወለዮሐንስ ፡ ይበውኡ ፡ ምኵራበ ፡ ወሰአሎሙ ፡ የሀብዎ ፡ ምጽዋተ ፡

ጴጥሮስንና ፡ ዮሐንስን ፡ ወደ ፡ ምኵራብ ፡ ሲገቡ ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ ምጽዋት ፡ ምጽ ዋት ፡ ብሎ ፡ ለመናቸው ፡

ወተመይጥዎ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወዮሐንስ ፡ ኀቤሁ ፡

የምጽዋት ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ይሰጣል ፡ የሌ ለው ፡ ተበድሬ ፡ ተቀድሜ ፡ ልስጥ ፡ አይ ልምና ፡ አልፈው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ተመ ልሰው ። አንድም ፡ ምጽዋት ፡ ምጽዋት ፡ ብሎ ፡ ሲለምን ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መሄድ ፡ አይ ገባምና ፡ ከዚያ ፡ ተመልሰው ። አንድም ፡ ለተግባረ ፡ ነፍስ ፡ ይፋጠኑ ፡ ነበርና ፡ ከዚያ ፡ ደርሰው ፡ ተመልሰው ፡

ወይቤልዎ ፡ ተመየጥ ፡ መንገሌነ ።

ተመየጥ ፡ መንገሌነ ፡ አሉት ፡ እሱም ፡ የከተማ ፡ ለማኝ ፡ ፈሊጠኛ ፡ ነው ፡ የሚ መጣውን ፡ ይመለከታል ፡ እንጅ ፡ ያለፈ ውን ፡ አይዘበዝብምና ፡ የሚመጣውን ፡ ለመመልከት ፡ ፊቱን ፡ መልሶ ፡ ሳለ ። አንድም ፡ የምስጢር ፡ ነው ፡ ወደኛ ፡ ሃይ ማኖት ፡ ተመለስ ፡ ሲሉት ፡ ነው ።

፬ ፤ ወነጸረ ፡ ኀቤሆሙ ፡

፭ ፤ ወተሰፈወ ፡ የሀብዎ ፡ ምጽዋተ ፡

ወርቅ ፡ ብር ፡ የያዙልኝ ፡ መስሎት ፡ ዙሮ ፡ አየ ።

፮ ፤ ወይቤሎ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወርቅሰ ፡ ወብሩር ፡ አል ብየ ፡

ጴጥሮስም ፡ አውቆበት ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ አልያዝሁም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወእምዘብየሰ ፡ እሁበከ ፡

እንኪ.ያ ፡ ምን ፡ ይዘህልኛል ፡ ትለኝ ፡ እን
ደ ፡ ሆነ ፡ ከያዝሁትስ ፡ እሰጥሃለሁ ፡

ናሁ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ናዝራዊ ፡ ተን
ሥእ ፡ ወሑር ።

እነሆ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ስም ፡ አምነህ ፡ ተነሣ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡

ወአኀዞ ፡ በእዴሁ ፡ ዘየማን ፡ ወአንሥኦ ።

እዴሁ ፡ ለጴጥሮስ ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ይዞ ፡
አንድም ፡ እዴሁ ፡ ለድውይ ፡ ቀኝ፡ እጁን፡
ይዞ ፡ አስነሣው ።

፯ ፤ ወተንሥአ ፡ ሶቤሃ ፡ ወጸንዐ ፡ እገሪሁ ፡ ወሐ
ቌሁ ፡

እግሩ ፡ ጸንቶለት ፡ ወገቡ ፡ ቀንቶለት ፡
ጥግ ፡ መቋሚያ ፡ ሳይሻ፡ ተነሥቶ ፡ ማቴ ፡
፳ ፡ ፲፰ ።

ወሖረ ፡ ምስሌሆሙ ፡ እንዘ ፡ ይሠግር ።

ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስ ፡ የተራመዱትን ፡
እየተራመደ ፡ ሄደ ።

፰ ፤ ወቦአ ፡ ምኵራበ ፡ ወአእኰተ ፡ እግዚአብሔ
ርሃ ።

ከምኵራቡ ፡ ገብቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡
አመሰገነ ፡ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ያደረስኸኝ ፡
ከደዌዬ፡የፈወስኸኝ፡ ብሎ፡ ኢሳ፡ ፴፭፡ ፮ ።

፱ ፤ ወርእይዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ እንዘ ፡ የሐውር ፡
ወያአኵት ፡ እግዚአብሔርሃ ።

ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያ
መሰገነ ፡ ሲሄድ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ።

፲ ፤ ወአእመርዎ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ዘይነብር፡ ኆኅተ፡
ምኵራብ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ኦርያ ፡ ወይስእል ።

ኦርያ ፡ በምትባል ፡ ምኵራብ ፡ ደጅ ፡
ተቀምጦ ፡ ምጽዋት ፡ ሲለምን ፡ የነበረው፡
ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቀው ፡

ወደንገፁ ፡ ወአንከሩ ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ተአምር ፡
ላዕሌሁ ።

ለርሱ ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ ነገር። አንድም ፡
በርሱ ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ ነገር ፡ የአንክሮ ፡
ድንጋጤ ፡ ደነገጡ ።

፲፩ ፤ ወእንዘ ፡ ይእኅዝዎ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወዮሐንስ ፡
ይበውኡ ፡ ምኵራበ ፡ ሮጹ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ኀቤሆሙ ፡
ኀበ ፡ ሕዋረ ፡ ሰሎሞን ፡ ድንጉጻኒሆሙ ።

ጴጥሮስ ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ዮሐንስ ፡ ግራ ፡
እጁን ፡ ይዘውት ፡ ወደ ፡ ምኵራቡ ፡ ሲ
ገቡ ፡ በሕዋረ ፡ ሰሎሞን ፡ የነበሩ ፡ ወደሕ
ዋረ ፡ ሰሎሞን ፡ ሲገቡ ፡ በምኵራቡ ፡ የነ
በሩ ፡ ሕዝቡ ፡ የአንክሮ ፡ ድንጋጤ ፡
እየደነገጡ ፡ ወደነሱ ፡ ቀረቡ ፡ ም፡ ፳፡ ፲፪ ፡

፲፪ ፤ ክፍል ፡ ፯ ፤ ወሶበ ፡ ርእዮሙ ፡ ጴጥሮስ ፡ ለሕ
ዝብ ፡

ጴጥሮስም ፡ ሕዝቡን ፡ እያደነቁ ፡ ሲመ
ጡ ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡

ይቤሎሙ ፡ አንትሙ ፡ ሰብአ ፡ እስራኤል ፡ ምንተኑ ፡
ታነክሩነ ፡

እናንት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለምን ፡
ታደንቁናላችሁ ፡

ወምንተኑ ፡ ትኔጽሩነ ፡

አክብራችሁስ ፡ ለምን ፡ ታዩናላችሁ ፡

ከመ ፡ ዘበኃይልነ ፡ ገበርናሁ ፡ ወከመ ፡ ዘበሥልጣ
ንነ ፡ ረሰይናሁ ፡

በኛ ፡ ኃይል ፡ በኛ፡ ሥልጣን፡ እንዳዳነው ፡
አድርጋችሁ ፡

አው ፡ እምኀበ ፡ ነፍሳቲነኑ ፡ አሕየውናሁ ፡ ለዝንቱ ፡
ከመ ፡ ይሑር ፡ በእገሪሁ ።

በእግሩ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ ከራሳችን ፡ አን
ቅተን ፡ እንዳዳነው ፡ አድርጋችሁ ፡ ለምን፡
ታደንቁናላችሁ ፡ አክብራችሁስ ፡ ለምን ፡
ታዩናላችሁ ።



፲፫ ፤ አልቦኬ ።

በኛ ፡ ኃይል ፡ በኛ ፡ ሥልጣን ፡ ያዳነው ፡
አይደለም ፡

አላ ፡ አምላከ ፡ አብርሃም ፡ ወአምላከ ፡ ይስሐቅ ፡
ወአምላከ ፡ ያዕቆብ ፡ አምላከ ፡ አበዊነ ፡ ሰብሐ ፡
ለወልዱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ አም
ላክ ፡ ያባቶቻችን ፡ ፈጣሪ ፡ የባሕርይ ፡
ልጁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በተአም
ራት ፡ ቢገልጠው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡

፲፬ ፤ ዘአንትሙ፡ ዓለውክምዎ፡ ወክሕድክምዎ፡ በቅድ
መ፡ገጸ ፡ ጲላጦስ፡ ፈቂዶ፡ ውእቱ፡ ያሕይዎ፡ ለክሙ ።

እሱ ፡ ሊያድነው ፡ ወዶ ፡ ሳለ ፡ በጲላጦስ፡
ፊት ፡ አምፃችሁ ፡ የካዳችሁት ፡ አለ ፡
ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ብላችሁ ፡ ሰቅላችሁ፡ የገ
ደላችሁት ፡ ም፡ ፳ ፡ ፴። ዘፀአ ፡ ፫ ፡ ፯ ፡ ፲፳፡
፲፮ ። የሐዋ፡ ፪ ፡ ፳፫ ።

ወአንትሙሰ፡ክሕድክምዎ፡ለቅዱስ፡ወለጻድቅ፡

እናንተ ፡ ግን ፡ ጽኑ ፡ ከሃሊ ፡ ጻድቀ ፡ ባሕ
ርይ፡የሚሆን፡እሱን፡ሩቅ፡ብእሲ፡ ብላችሁ ፡

ወሰአልክሙ ፡ ብእሴ ፡ ቀታሌ ፡ ነፍስ ፡ ያሕዩ ፡ ለክሙ

ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ በርባንን ፡ ያድንላችሁ ፡ ዘን
ድ ፡ አሕዩ ፡ ለነ ፡ በርባንሃ ፡ ብላችሁ ፡
ተካሰሳችሁ ፡ ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ።

፲፭ ፤ ወለመልአከ ፡ ሕይወትሰ ፡ ቀተልክምዎ ፡

የድኅነት ፡ ባለቤት ፡ የድኅነት ፡ ምክን
ያት፡ እሱን፡ ግን፡ ሰቅላችሁ ፡ ገደላችሁት ፡

ወእግዚአብሔር ፡ አንሥኦ ፡ እሙታን ።

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡
አስነሣው ።

፲፮ ፤ ወንሕነ ፡ ኵልነ ፡ ሰማዕቱ ፡ ከመ ፡ በሃይማ
ኖተ ፡ ስሙ ፡ ለዝ ፡ ዘትሬእዩ ፡ ወተአምሩ ፡ አጽንዖ ፡
ወበሃይማኖት ፡ ዚአሁ ፡ ወሀቦ ፡ ዘንተ ፡ ሕይወተ ፡
በቅድሜክሙ ።

በሃይማኖቱ ፡ ስሙ ፡ ያለውና ፡ በሃይማ
ኖተ ፡ ዚአሁ ፡ ያለው ፡ በየራሱ ፡ ይህን ፡
የምታዩትን ፡ የምትሰሙትን ፡ ስሙ ፡
ሕይወት ፡ መድኃኒት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እሱ
ም ፡ ቢያምን ፡ እኛም ፡ ብናምን ፡ በፊታ
ችሁ ፡ ድኅነት ፡ ሰጥቶ ፡ እንዳስነሣው ፡
እኛ ፡ ምስክሮቹ ፡ ነን ። አንድም ፡ አንድ ፡
ወገን፡ ስሙ፡ ሕይወት፡ መድኃኒት፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ቢያምን፡ ይህን፡ የምታዩትን ፡ የምት
ሰሙትን ፡ ሰው ፡ ድኅነት ፡ ሰጥቶ ፡ እንዳስ
ነሣው ፡ ምስክሮቹ ፡ ነን ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፳፬ ፡
፴፪ ፡ ፬ ፡ ፲ ። ሮሜ ፡ ፬ ፡ ፳፬ ፡ ፳ ፡ ፲፩ ። ፩ ፡
ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፬ ፡ ፲፭ ።

፲፯ ፤ ወይእዜኒ ፡ አኀውየ ፡ አእምሩ ፡ ከመ ፡ በኢ
ያእምሮ ፡ ገበርክምዎ ፡ ለዝ ፡ ከመ ፡ ገብሩ ፡ መላእክ
ቲክሙ ፡

አሁንም ፡ ወንድሞቼ ፡ አለቆቻችሁ ፡ ባለ
ማወቅ ፡ እንዳደረጉት ፡ እናንተም ፡ ባለ
ማወቅ ፡ እንዳደረጋችሁት ፡ ወከመ ፡ ገብ
ሩ ፡ አለቆቻችሁም፡ ባለማወቅ ፡ እንዳደረ
ጉት ፡ ዕወቁ።አንድም፡ እናንተማ ፡ ምን ፡
ባይ ፡ አለቆቻችሁ፡ ባለማወቅ ፡ እንዳደረ
ጉት ፡ ዕወቁ ፤ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፴፬ ።

፲፰ ፤ ወእግዚአብሔርሰ ፡ በከመ ፡ አቅደመ ፡ ነጊረ ፡
በአፈ ፡ ኵሎሙ ፡ ነቢያት ፡ ከመ ፡ ይትቀተል ፡ ክር
ስቶስ ፡ አብጽሐ ፡ ከማሁ ፡

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲ
ሞት ፡ በነቢያት ፡ አድሮ ፡ አስቀድሞ ፡
እንዳናገረ ፡ ፈጸመ ፤ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፳፯ ።

፲፱ ፤ ወይእዜኒ ፡ ነሥሑ ፡ ወተጠመቁ ፡

ከዚህ ፡ አያይዞ ፡ ምስጢረ ፡ ትንሣኤ ፡
ሙታንን ፡ ቢነግራቸው፡ ምንተ፡ ንግበር ፡
አኃዊነ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ምን ፡ እናድርግ፡
አሉ ፡ ግብር ፡ ገብተው ፡ በአእምሮ ፡ ፍጹ
ማን ፡ ያልሆኑ ፡ ናቸውና ፡ አኀዊነ ፡ አሉ ፡
እንጅ ፡ እንደ ፡ ነገሩስ ፡ አበዊነ ፡ መምህ
ራኒነ ፡ አጋእዝቲነ ፡ ሊቃውንቲነ ፡ ባሉ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ባማረ ፡ በተገባ ፡ ነበር ፡ ድኅነትስ ፡ ከሻ
ችሁ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ስም ፡ እምናችሁ ፡ ተጠመቁ ፡

ወይደመሰስ ፡ ለክሙ ፡ ኃጢአትክሙ ፡

ኃጢአታችሁ ፡ ይሠረይላችኋል ፡ አላ
ቸው ፡

ወይመጽእ ፡ ለክሙ ፡ መዋዕለ ፡ ሣህል ፡ እምቅድመ ፡
ገጹ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የይቅርታ ፡ ዘ
መን ፡ ይመጣላችኋል ፡ አለ ፡ በይቅርታ ፡
የሚገኝ ፡ ክብር ፡ ይሰጣችኋል ፤ ም ፡ ፪ ፡
፴፰ ፡ ኢሳ ፡ ፴፫ ፡ ፰ ።

፳ ፤ ወይፌንዎ ፡ ለክሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ዘአቅደመ ፡ ቀቢአ ፡

አስቀድሞ ፡ ያነገሠው ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ
ቶስን ፡ ይሰድላችኋል ፤ ዳን ፡ ፺ ፡ ፳፪ ፡ ፳፯ ።
ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፩ ። ራእ ፡ ፳ ፡ ፮ ።

፳፩ ፤ ዘኪያሁ ፡ ይሴፈዉ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡
እስከ ፡ አመ ፡ ያስተራትዕ ፡ ኵሎ ፡

ሁሉን ፡ እስቲያከናውን ፡ ድረስ ፡ ሰማይ ፡
ምድር ፡ ያሳልፈናል ፡ ብለው ፡ ደጅ ፡ የሚ
ጠኑት ። አንድም ፡ መላእክት ፡ ደቂቀ ፡ አዳም ።
አንድም ፡ በአጸደ ሥጋ ፡ በአጸደ ፡ ነፍስ ፡ ያሉ
ት ፡ ልዑላኑ ፡ ትሁታኑ ፡ ዋጋችንን ፡ ይሰ
ጠናል ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ የሚያደርጉት ።
አንድም ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡ ከአምስት ፡ መቶ ፡
ዘመን ፡ የነበሩ ፡ ነፍሳት ፡ ዋጋችንን ፡
ይሰጠናል ፡ ብለው ፡ ደጅ ፡ ይጠኑት ፡ የነ
በሩ ፡

በከመ ፡ ነበበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢያቲሁ ፡ ቅዱሳን ፡
እለ ፡ እምዓለም ፡

ከደጋጉ ፡ ወገን ፡ በሚሆኑ ። አንድም ፡ አስቀ
ድመው ፡ በነበሩ ፡ በነቢያት ፡ አድሮ ፡
እንደ ፡ ተናገረ ፡ ሁሉን ፡ እስቲያከናውን ፡
ድረስ ።

፳፪ ፤ ሙሴሂ ፡ ይቤሎሙ ፡ ለአበዊነ ፡ ነቢየ ፡ ያነ
ሥእ ፡ ለክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ እምአኃ
ዊክሙ ፡ ዘከማየ ፡

ሙሴም ፡ ለአባቶቻችን ፡ ከወገኖቻችሁ ፡
እንደኔ ፡ ያለ ፡ ነቢይ ፡ ያስነሣላችኋል ፡

ወሎቱ ፡ ስምዕዎ ፡ ኵሎ ፡ ዘይቤለክሙ ፡

ያስተማራችሁን ፡ ትምህርት ፡ ተቀበሉት ፤
ዘዳግ ፡ ፲፰ ፡ ፲፩ ።

፳፫ ፤ ወኵላ ፡ ነፍስ ፡ እንተ ፡ ኢትሰምዖ ፡ ለውእቱ ፡
ነቢይ ፡ ለትሠረው ፡ እምሕዝባ ፡

እሱ ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ፡ የማት
ቀበል ፡ ሰውነት ፡ ሁሉ ፡ ከወገኗ ፡ ተለ
ይታ ፡ በደንጊያ ፡ ተወግራ ፡ በእሳት ፡
ተቃጥላ ፡ ትሙት ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ።

፳፬ ፤ ወኵሎሙ ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ እምአመ ፡ ሳሙ
ኤል ፡ ነቢይ ፡

ከሳሙኤል ፡ አስቀድሞ ፡ በሳሙኤል ፡ ጊዜ ፡

ወእለሂ ፡ እምድኅሬሁ ፡ ነገሩ ፡ ወአይድዑ ፡ በእንተ ፡
እላንቱ ፡ መዋዕል ፡

ከሳሙኤል ፡ በኋላ ፡ የተነሡ ፡ ነቢያትም ፡
የዘመኑን ፡ የጊዜውን ፡ ነገር ፡ ተናግረዋል ፡ ዘ
መን ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ትውልድ ፡ ሐዋርያት ፡ እንደ ፡ ሆኑ ።

፳፭ ፤ ወአንትሙ ፡ ውሉዶሙ ፡ ለነቢያት ፡

እናንተም ፡ የነቢያት ፡ ልጆች ፡ ናችሁ ፡

ወውሉደ ፡ ሥርዐት ፡ ዘሠርዖ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአበዊነ ፡

እግዚአብሔር ፡ ለአባቶቻችን ፡ ያናገረ
ውን ፡ ተስፋ ፡ መውረስ ፡ የሚገባቸው ፡
ልጆች ፡ ናችሁ ፡

እስመ ፡ ይቤሎ ፡ ለአብርሃም ፡ በዘርዕከ ፡ ይትባረኩ ፡
ኵሎሙ ፡ አሕዛበ ፡ ምድር ፡

እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ በዘርዕከ ፡
ይትባረኩ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛበ ፡ ምድር ፡
ብሎ ፡ ተስፋውን ፡ ነግሮት ፡ ነበርና ፤ ዘፍ
ጥ ፡ ፲፪ ፡ ፫ ።



፳፮ ፤ ወለክሙ ፡ ቀደመ ፡ አንሥኦቶ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ለወልዱ ፡

ለናንተስ ፡ አስቀድሞ ፡ እግዚአብሔር ፡
ልጁን ፡ በመምህርነት ፡ አስነሥቶታል ፡
ቀደመ ፡ ከአሕዛብ ፡ ነው ፡

ወፈነዎ ፡ ይባርከሙ ፡

ያስተምራችሁ ፡ ዘንድ ፡ ሰዶታል ፡

ከመ ፡ ትነሥሑ ፡ ኵልክሙ ፡ እምእከይክሙ ፡

ከኃጢአታችሁ ፡ ትመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ሰዶ
ታል ፤ ም ፡ ፲፫ ፡ ፵፯ ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ፡ ክፍል ፡ ፺ ፡

፩ ፤ ወእንዘ ፡ ይነግሮሙ ፡ ለሕዝብ ፡ መጽኡ ፡ ሊ
ቃነ ፡ ካህናት ፡ ወመገብተ ፡ ምኵራብ ፡ ወሰዱቃው
ያን ፡

ጴጥሮስም ፡ ይህን ፡ ሲነግራቸው ፡ የካህ
ናቱ ፡ አለቆች ፡ የምኵራብ ፡ ሹማምት ፡
ሰዱቃውያን ፡ መጡ ፡ መገብት ፡ እንደ ፡
ገበዝ ፡ እንደ ፡ ሊቀ ፡ዲያቆን ፡ ያሉ ፡
ናቸው ፤ ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፬ ፡ ፶፪ ።

፪ ፤ ወቀንኡ ፡ ላዕሌሆሙ ፡

በሐዋርያት ፡ ቀኑባቸው ፡

እስመ ፡ ይሜህርዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ወይነግርዎሙ ፡
በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ከመ ፡ ሐይወ ፡ እምውታን ፡

ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ የጌ
ታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡
ለሕዝቡ ፡ አስተምረዋቸዋልና ፡ ሲያስተ
ምሯቸው ፡ ሰምተዋቸዋልና ፡ ወሕይወተ ፡
ሙታን ፡ ይላል ፡ የትንሣኤ ፡ ሙታንን ፡
ነገር ፡ ሲያስተምሯቸው ፡ ሰምተዋቸዋልና ።

፫ ፤ ወአኀዝዎሙ ፡ ወአውዐልዎሙ ፡ ሙዓለ ፡ እስ
ከ ፡ ጌሠም ።

እስኪነጋ ፡ ይዘው ፡ አስረው ፡ አሣደሯቸው ፡

እስመ ፡ ወድአ ፡ መስየ ፡

ፈጽሞ ፡ መሽቶ ፡ ነበርና ፡ አውዐልዎሙ ፡
ማለቱ ፡ መዓልቱ ፡ አልተፈጸመም ፡ ነበ
ርና ። አንድም ፡ ሌሊት ፡ መብራት ፡ እያበሩ ፡
ዘበኛው ፡ ተሰብስቦ ፡ እየዘፈነ ፡ በተድላ ፡
[illegible] ፡ ዘግተ

ውባቸው ፡ በጨለማ ፡ ይውላሉና ፡ ጽኑ ፡
ግዞት አጋዟቸው ፡ ሲል ፡ አውዐልዎሙ ፡ አለ ።

፬ ፤ ወብዙኃን ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ሰምዕዎ ፡ ለዝ ፡ ነገር ፡
ወአምኑ ፡

ይህንንም ፡ ነገር ፡ ሰምተው ፡ ያመኑ ፡ ብዙ ፡
ናቸው ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡

ወኮነ ፡ ኍልቆሙ ፡ ለዕደው ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ ሃምሳ ፡
ምእተ ፡

ያመኑትም ፡ ሰዎች ፡ ቍጥራቸው ፡ አም
ስት ፡ ሺሕ ፡ ያህል ፡ ነበር ፡ የቀደሙት ፡
ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ያሁኑ ፡ አምስት ፡ ሺሕ ፡
ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ማኅበረ ፡ እስጢፋኖስ ፡
የሚያሰኙ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡ በቀረው ፡
ግን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሁለትም ፡ መቶ ፡
ሳያምን ፡ አይውልም ፡ አያድርም ፡ ነበር ፡
ሺሕ ፡ ካልመላ ፡ ብሎ ፡ መተዉ ፡ ነው ፡
እንጅ ፤ ም ፡ ፪ ፡ ፵፺ ።

፭ ፤ ወእምዝ ፡ በሳኒታ ፡ ተጋብኡ ፡ መላእክት ፡ ወረ
በናት ፡ ወጸሐፍት ፡ በኢየሩሳሌም ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በነጋው ፡ መላእክት ፡ አለ
ቆቹ ፡ ረበናት ፡ እንደ ፡ እስላም ፡ ፉቂራ ፡
ያሉ ፡ ናቸው ፡ ጸሐፍት ፡ በኢየሩሳሌም ፡
ተሰበሰቡ ።

፮ ፤ ወሐና ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ወቀያፋ ፡ ወዮሐንስ ፡
ወእለ ፡ እስክንድሮስ ፡

የካህናቱ ፡ አለቃ ፡ ሐና ፡ ቀያፋ ፡ ዮሐንስ ፡
እለ ፡ እስክንድሮስ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኵሎሙ ፡ ዘመደ ፡ ካህናት ፡

የካህናት ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ካህናት ፡ ደቂቀ ፡ አሮን ፡ ዘመድ ፡ ደቂቀ ፡ ቀዓት ፡ ካህናት ፡ ደቂቀ ፡ ቀዓት ፡ ዘመድ ፡ ደቂቀ ፡ ሚራሪ ፡ ካህናት ፡ ደቂቀ ፡ ሚራሪ፡ ዘመድ ፡ ደቂቀ ፡ ጌድሶር ፤ ዘኁ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፪ ።

፯ ፤ ወአቀምዎሙ ፡ ማዕከለ ፡ አውድ ፡ ወሐተትዎሙ ፡

ባደባባይ ፡ መካከል ፡ አቁመው ፡ መረመሯቸው ፡

ወይቤልዎሙ ፡ በኀይለ ፡ መኑ ፡ ወበስመ ፡ መኑ ፡ ገበርክሙ ፡ ዘንተ ፡ አንትሙ ፡

ይህን ፡ ተአምራቱን ፡ በማን ፡ ስም ፡ በማን ፡ ኃይል፡ አደረጋችሁት፡ ብለው፤ ማቴ ፡ ፳፩ ፡ ፳፫ ።

፰ ፤ ወመልአ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሶቤሃ ፡ ላዕለ ፡ ጴጥሮስ ፡

ያን፡ጊዜ፡ በጴጥሮስ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ አደረበት፡ተለይቶትን ፡ ያውቃል፡ ምላሽ፡ ገለጠለት ፡ ለማለት፡ ነው ፤ ሉቃ፡ ፲፪ ፡ ፲፩ ።

፱ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ስምዑ ፡ መላእክተ ፡ ሕዝብ ፡ ወረበናት ፡ ለእመሁ ፡ ንሕነ ፡ ንትኴነን ፡ ኀቤክሙ ፡ በእንተ ፡ ረድኤተ ፡ ሕሙም ፡ ዘኮነ ፡ ዮም ፡

የሕዝቡ ፡ አለቆች ፡ ረበናት ፡ ስሙ ፡ ዛሬ ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ ስለ ፡ ሕሙሙ፡ ድኅነት፡ ከናንት ፡ ዘንድ ፡ ይሞት ፡ በቃ ፡ የሚፈረድብን ፡ ከሆነ ፤ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፴፪ ።

በምንትኑ ፡ እንከ ፡ ሐይወ ፡ ዝንቱ ፡

ይህ ፡ ሰው ፡ በማን ፡ ስም ፡ በማን ፡ ኃይል፡ ዳነ ፡ ትላላችሁ ።

፲ ፤ አእምሩ ፡ እንከ ፡ ጥዩቀ ፡ ኵልክሙ ፡

በጉላ ፡ በተረዳ ፡ ነገር ፡ ሁላችሁም ፡ ዕወቁ ፡

ወኵሉ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡

እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ይወቁ ፡

ከመ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘአንትሙ ፡ ቀተልክምዎ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ አንሥኦ ፡ እሙታን ፡

እናንት ፡ ሰቅላችሁ ፡ በገደላችሁት ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ ባስነሣው ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አእምሩ ፤ ዕወቁ ፡

ወቦቱ ፡ ሐይወ ፡ ዝንቱ ፡

ቦቱ ፡ ሐይወና ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ በሱ ፡ ስም ፡ እንደ ፡ ዳነ ፡ ዕወቁ ፡ እስራኤልም ፡ ሁሉ ፡ ይወቁ ፡

ወቆመ ፡ ቅድሜክሙ ፡

በፊታችሁ ፡ ቁሞ ፡ ታዩታላችሁ ፤ ምሳ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ።

፲፩ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ዕብን ፡ ዘመነንክምዎ ፡ አንትሙ ፡ ነደቅት ፡

የሰውን ፡ ልቡና ፡ በትምህርት ፡ ምክንያት ፡ እናንጻለን ፡ የምትሉ ፡ እናንት ፡ የናቃችሁት ፡ ወልድ ፡

ወውእቱ ፡ ኮነ ፡ ውስተ ፡ ርእሰ ፡ ማዕዘንት ፡

ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በኵረ ፡ ምእመናን ፡ ሁኗልና ፤ ማቴ ፡ ፳፩ ፡ ፵፪ ። መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፳፪ ።

፲፪ ፤ ወአልቦ ፡ ካልእ ፡ ሕይወት ፡ በዘየሐይዉ ፡

በሚያምኑ ፡ በሚድኑ ፡ ገንዘብ ፡ ሌላ ፡ ሕይወት ፡ የለም ፡

ወአልቦ ፡ ካልእ ፡ ስም ፡ በታሕተ ፡ ሰማይ ፡ ዘይትወሀብ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ፡

ከሰማይ ፡ በታች ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ድኅነት፡ ሁኖ ፡ የሚሰጥ ፡ ሌላ፡ ስም፡ የለምና፤ ማቴ፡ ፩ ፡ ፳፩ ።

፲፫ ፤ ወሶበ ፡ ርእይዎሙ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ወለዮሐንስ ፡ ከመ ፡ ገሃደ ፡ ይነግርዎሙ ፡

ጴጥሮስንና ፡ ዮሐንስንም ፡ ገልጠው ፡ ሲያስተምሯቸው ፡ ባዩዋቸው ፡ ጊዜ ፡

ወአእመርዎሙ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ የዋሃን ፡ እሙንቱ ፡

ያልተማሩ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አውቀው ፡

ወኢየአምሩ ፡ መጽሐፈ ፡

መጽሐፍ ፡ ያልተማሩ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አውቀው ፡

ወአንከርዎሙ ፡

አደነቁባቸው ፡

እስመ ፡ የአምርዎሙ ፡ ዘልፈ ፡ ከመ ፡ ምስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ሀለዉ ፡

ከጌታ ፡ ጋራ ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ያውቋቸዋልና፡ ምነው ፡ ከጌታ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ ሁሉ ፡ አላዋቂ ፡ ደንቆሮ ፡ ማለት ፡ ነውን ፡ ቢሉ ፡ እየተከራከሩ ፡ ምላሽ ፡ ያሳጧቸው ፡ ነበርና ።

፲፬ ፤ ወይሬእይዎ ፡ ለዝኩሂ ፡ ብእሲ ፡ ዘሐይወ ፡ ይቀውም ፡ ምስሌሆሙ ፡

የዳነውንም ፡ ያንን ፡ ሰው ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ አይተውት ፡ ነበርና ፡

ወኃጥኡ ፡ ዘይብሉ ፡ ወዘይነብቡ ፡

ዘይብሉ ፡ ለራሳቸው ፡ ወዘይነብቡ ፡ ለሌላው ፡ የሚመልሱት ፡ ምላሽ ፡ ቸገራቸው ፤ ምሳ ፡ ፫ ፡ ፳ ፡ ፱ ፡

፲፭ ፤ ወአዘዙ ፡ ያእትትዎሙ ፡ ሕቀ ፡ እምዓውድ ፡

ሊመክሩለትም ፡ ሊመክሩበትም ፡ ቢሆን ፡ ቆይ ፡ ማለት ፡ ልማድ ፡ ነውና፡ ቆዩ ፡ በሏቸው ፡ አሉ ፡

ወተናገሩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡

በጸሎት ፡ አርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተነጋገሩ ።



፲፮ ፤ ወይቤሉ ፡ ምንተ ፡ ንሬስዮሙ ፡ ለእሉ ፡ ሰብእ፡

እሊህን ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ እናደርጋቸዋለን ፡ ንረስዮሙ ፡ ምን ፡ እናድርጋቸው ፡

ናሁ ፡ ተዐውቀ ፡ ትምህርቶሙ ፡ በኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ኢየሩሳሌም ፡

ትምህርታቸው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ከሁሉ ፡ ደርሶ ፡ ተረዳ ፡

ወገሃደ ፡ ኮነ ፡

የተገለጠ ፡ ሆነ ፡

ወኢንክል ፡ ከቢቶቶ ፡

ሰውረን፡ ልናስቀረው፡ አይቻለንም ፤ ዮሐ፡ ፲፩ ፡ ፵፯ ።

፲፯ ፤ ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ ፈድፋደ ፡ ኢይብዛኅ ፡ በላዕለ ፡ ሕዝብ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ ለሕዝቡ ፡ ፈጽሞ ፡ እንዳይረዳ ፡

ንገሥጾሙ ፡ ከመ ፡ ዳግመ ፡ ኢይንግሩ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ለሰብእ ፡

ስሙ ፡ ሕይወት፡ መድኃኒት፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዳያስተምሩ ፡ ሸመጣጠን ፡ እንተዋቸው ፡ ብለው ፤ ምሳ ፡ ፭ ፡ ፳፰ ።

፲፰ ፤ ወጸውዕዎሙ ፡ ወይቤልዎሙ ፡ ግሙራ ፡ ኢትንግሩ ፡ ወኢትምሀሩ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡

ጠርተው ፡ ስሙ ፡ ሕይወት ፡ መድኃኒት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በስሙ ፡ አታስተምሩ ፡ አሏቸው ።

፲፱ ፤ ክፍል ፡ ፰ ። ወተሠጥውዎሙ፡ ጴጥሮስ፡ ወዮሐንስ ፡ ወይቤልዎሙ ፡ ይረትዕኑ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኪያክሙ ፡ ንስማዕ ፡ ወአኮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስም ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚያውቀው ፡ ነገር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ያይደለ ፡ የናንተን ፡ ትእዛዝ ፡ ልንሰማ ፡ ይገባልን ።

www.ethiopianorthodox.org

ፍትሐ ፡ እስኩ ፡ ለሊክሙ ፡

ይህንን ፡ ነገር ፡ እስኪ ፡ እናንተ ፡ ፍረዱት፡ ም ፡ ፫ ፡ ፳፱ ።

፳ ፤ ንሕነሰኬ ፡ ኢንክል ፡ ከቢቶቶ ፡ ለዝንቱ፡ ነገር ፡

እኛስ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሠውረን ፡ ልናስቀረው፡ አይቻለንም፡ ብለው፡ መለሱላቸው ፡

ወእምዝ ፡ገሠጽዎሙ ፡ ወኀደግዎሙ ፡ ሶበ ፡ ኃጥኡ ፡ በዘይኴንንዎሙ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይሞት ፡ በቃ ፡ በሚፈርዱባቸው ፡ ገንዘብ ፡ የሚፈርዱበት ፡ ምክንያት ፡ ባያገኙ ፡ ሸመጣጠው ፡ ተዋቸው ።

፳፩ ፤ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ የአኵቱ ፡ እግዚአብሔርሃ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ተአምር ፡ ዘኮነ ፡

ስለ ፡ ተደረገው ፡ ነገር ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፡ ነበርና ።

፳፪ ፤ እስመ ፡ ፈድፋዶ ፡ እምአርብዓ ፡ ዓመት ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘበላዕሌሁ ፡ ኮነ ፡ ዝ ፡ ተአምረ ፡ ሕይወት ፡

ይህ ፡ የድኅነት ፡ ምልክት ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ከታመመ ፡ ካርባ ፡ ዘመን ፡ በልጦት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡

ወተፈቲሖሙ ፡ ሖሩ ፡ ኀበ ፡ ሰብኦሙ ፡

ከሥራታቸው ፡ ተፈተው ፡ ተፋቲሆሙ ፡ ይላል ፡ ከነሱ ፡ ተሰናብተው ፡ ወደ ፡ ወገኖቻቸው ፡ ሄዱ ።

፳፫ ፤ ወነገርዎሙ ፡ ኵሎ ፡ ዘይቤልዎሙ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወረበናት ፡

ተመልሰው ፡ የካህናቱ ፡ አለቆች ፡ ረበናት ፡ ያሏቸውን ፡ ሁሉ ፡ ነገሯቸው ።

፳፬ ፤ ወሰሚያሙ ፡ አንሥኡ ፡ ቃሎሙ ፡ ኅቡረ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡

ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ጸሎት ፡ ጸለዩ ፡

ወይቤሉ ፡ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ዘገበርከ ፡ሰማየ ፡ ወምድረ ፡

ሰማይ ፡ ምድሩን ፡ የፈጠርህ ፡ አምላክ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ የፈጠርህ ፡ አቤቱ ፡

ወባሕረ ፡

ባሕሩን ፡ የፈጠርህ ፡

ወኵሎ ፡ ዘውስቴቶሙ ፡

በውስጣቸው ፡ ያሉትንም ፡ የፈጠርህ ፡ አለ ፡ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃን ፡ ከዋክብትን ፡ መላእክትን ፡ በምድር ፡ ያሉ ፡ ደቂቀ ፡ አዳምን ፡ እንስሳትን ፡ አራዊትን ፡ አእዋፍን ፡ ዕፀው ፡ አዕባንን ፡ በባሕር ፡ ያሉ ፡ ዓሣ ፡ አንበሪ ፡ አዞ ፡ ጉማሬን ፡ የፈጠርህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ የፈጠርህ ፡ አቤቱ ።

፳፭ ፤ ዘለሊከ ፡ ነበብከ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በአፈ፡ ዳዊት ፡ ገብርከ ፡ አቡነ ፡

በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሕልው ፡ ሁነህ ፡ በባለሟልህ ፡ በዳዊት ፡ አድረህ ፡ የተናገርህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ የተናገርህ ፡ አቤቱ ፡

ወትቤ ፡ ለምንት ፡ አንገለጉ ፡ አሕዛብ ፡

አራቱ ፡ ቤት ፡ ጭፍራ ፡ ሮማውያን ፡ ለምን ፡ ተሰበሰቡ ፡ ለምን ፡ ዶለቱ ፡

ወሕዝብኒ ፡ ነበቡ ፡ ከንቶ ፡

ኢሊያስ ፡ የተነገረውን ፡ ትንቢት ፡ የተቈጠረውን ፡ ሱባኤ ፡ ባያውቁ ፡ ነው ፡ የተነገረውን ፡ ትንቢት ፡ የተቈጠረውን ፡ ሱባኤ ፡ የሚያውቁት ፡ ከንቱ፡ ነገርን ፡ ለምን፡ ተናገሩ ፡ ከንቱ ፡ አለው ፡ ሞቱን ፡ ከንቱነቱ ፡ በነሱ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ ሰቅለን ፡ ገለን፡ ሙቶ ፡ ፈርሶ ፡ በስብሶ ፡ ይቀራል ፡ ብለው፡ ነበረ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ተነሥቶባቸው ፡ ነገራቸው ፡ ከንቱ ፡ ሆኖባቸዋልና ፡ መዝ ፡ ፪ ፡ ፩

፳፮ ፤ ወተንሥኡ ፡ ነገሥተ ፡ ምድር ፡

ሕዝቡ ፡ ቢያጠፉ ፡ ነገሥታቱ ፡ ሊሠሩ፡ ሊቀጡ ፡ ነበር ፡ ነገሥታቱ ፡ እለ ፡ ሄሮድስ ፡ እለ ፡ ጲላጦስ ፡ ለምን ፡ ተነሡ ፡ ምነው ፡ ነገሥት ፡ ብሎ ፡ አበዛ ፡ አንድ ፡ ሄሮድስ ፡ አይደለም ፡ ቢሉ ፡ መጽሐፍ ፡ ስም ፡ ካልጠራ ፡ ማብዛት ፡ ልማዱ ፡ ነውና ። አንድም ፡ በሄሮድስ ፡ አጸግቶ ፡ ጲላጦስን ፡ ንጉሥ ፡ አለው ፡ ባንዱ ፡ አጸግቶ፡ አንዱን ፡ መጥራት ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ ካህናት ፡ ኅሉፋነ ፡ ፍና ፡ ከበቱ ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአሙ ፡ አመ ፡ ቀተልዋ ፡ ለሰቂማ ፡ እንዳለ ፡ በሌዊ ፡ አጸግቶ ፡ ስምዖንን ። አንድም ፡ ንጉሥ ፡ ዘሢሜሞ ፡ ንጉሥ ፡ ውእቱ ፡ ይላልና ፡

ወመላእክትኒ ፡ ተጋብኡ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ኅቡረ ፡ ላዕለ እግዚአብሔር ፡ ወላዕለ ፡ መሢሑ ፡

ነገሥታቱ ፡ ቢያጠፉ ፡ አለቆቹ ፡ ሊመክሩ ፡ ሊያስተምሩ ፡ ነበረ ፡ ባነገሠው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ ተሰበሰቡ ፡ ለምን ፡ ዶለቱ ፡ ምነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ላይ ፡ ተነሥተዋል ፡ እንጅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ላይ ፡ ተነሥተዋልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ በወልድ ፡ መነሣት ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ መነሣት ፡ ነው ፡ ወልድን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ማለት ፡ አብን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ፡ ማለት ፡ ነው ፡ የዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አባት ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ነውና ።

፳፯ ፤ አማን ፡ አንገለጉ ፡ በዛቲ ፡ ሀገር ፡ ላዕለ ፡ ቅዱስ ፡ ወልድከ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘቀባእካሁ ፡

በዚች ፡ አገር ፡ ወልድየ ፡ ፍቁርየ ፡ ዘኃረይኩ፡ባልኸው ፡ በልጅህ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ ተሰበሰቡ ፡ ለምን ፡ ዶለቱ ።

ሄሮድስ ፡ ወጲላጦስ ፡ ጰንጤናዊ ፡

ነገሥት ፡ ያለውን ፡ ሄሮድስ ፡ ወጴላጦስ ፡ አለ ፡ ሄሮድስና ፡ ጲላጦስ ፡

ምስለ ፡ ሕዘቢሆሙ ፡

አሕዛብ ፡ ያለውን ፡ ምስለ ፡ ሕዘቢሆሙ ፡

ወሕዝበ ፡ እስራኤል ፡

ሕዝብ ፡ ያለውን ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ከሕዝብና ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ለምን ፡ ተሰበሰቡ፡ ለምን፡ ዶለቱ፡ ሉቃ፡ ፳፫፡ ፲፪ ።

፳፰ ፤ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ በከመ ፡ ሥርዐተ ፡ እዴከ ፡

እንደ ፡ ሥልጣንህ ፡ ትእዛዝ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ በከመ ፡ ሠርዐት ፡ እዴከ ፡ ሥልጣንህ ፡ እንዳዘዘች ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡

ወምክርከ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡

ምክርህ ፡ ሥጋዌ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ።

፳፱ ፤ ወይእዜኒ ፡ እግዚኦ ፡ ርኢ ፡ ትምክህቶሙ ፡ ወሀቦሙ ፡ ለአግብርቲከ ፡ ገሃደ ፡ ይንግሩ ፡ ቃለከ ፡

አሁንም ፡ አቤቱ ፡ ትምክህታቸውን ፡ አይተህ ፡ ወንጌልን ፡ ገልጠው ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ ማስተማሩን ፡ ሰጣቸው ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፳፫ ።

፴ ፤ ወትስፋሕ ፡ እዴከ ፡

ሥልጣንህ ፡ ትገለጥ ፡ ዘንድ ፡

ወትግበር ፡ ትእምርተ ፡ ወመንክረ ፡ በስመ ፡ ወልድከ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጹሕ ፡

ንጹሕ ፡ ከተፈልጠ ፡ ከተድኅሮ ። አንድም ፡ ካለ ፡ መመለክ ፡ ንጹሕ ፡ በሚሆን ፡ በልጅህ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ተአምራት፡ ታደርግ፡ ዘንድ፡ማስተማሩን ፡ ስጣቸው ፡ ብለው ፡ ጸለዩ ።

፴፩ ፤ ወእንዘ ፡ ይጼልዩ ፡ አድለቅለቀ ፡ ውእቱ ፡ መካን ፡ ኀበ ፡ ሀለዉ ፡ ይነብሩ ፡ ኅቡረ ፡ ጉቡአን ፡

እንዲህ ፡ ብለው ፡ ሲጸልዩ ፡ ተሰብስበው ፡ ያሉበት ፡ ቤት ፡ ተነዋወጠ ፡ ትእምርተ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኅልፈተ ፡ ምኵራብ ፡ ትእምርተ ፡ ምዝ
ባሬ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ትእምርተ ፡ ኅል
ፈተ ፡ ዓለም ፡ ትእምርተ፡ ዕርገተ፡ ጸሎት ፡
አንድም ፡ የሰውን ፡ ሁሉ ፡ ልቡና ፡ እን
ዲህ ፡ አንብርላችኋለሁ ፡ ሲል ፡

ወመልአ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዲበ ፡ ኵሎሙ ፡

በሁሉም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አደረባቸው፡
ተለይቷቸው ፡ ያውቃልን ፡ ሥራ ፡ አሠራ
ቸው ፡ ሲል ፡ ነው ፡

ወነገሩ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገሃደ ፡

ወንጌልን ፡ ገልጠው ፡ አስተማሩ ፡ ኤፌ ፡
፬ ፡ ፲፱ ።

፴፪ ፣ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ በአሐዱ ፡ ልብ ፡
ወበአሐቲ ፡ ነፍስ ፡

ያመኑትም ፡ ሁሉ ፡ እንዳንድ ፡ ልብ ፡ መ
ካሪ፡ እንዳንድ፡ ቃል፡ተናጋሪ፡ሆነው፡ኖሩ፡

ወአልቦ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ዘይብል ፡ ዝስ ፡ ዚአየ ፡
ንዋይ ፡

ከነሱም ፡ ወገን ፡ ይህ ፡ የኔ ፡ ገንዘብ ፡ ነው፡
ይህ ፡ የኔ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ አልነ
በረም ፡

አላ ፡ ዘኵሎሙ ፡ ኅቡረ ፡

የሁሉም ፡ ገንዘብ ፡ ባንድነት ፡ ነበረ ፡
እንጅ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፵፬ ።

፴፫ ፣ ወዐቢየ ፡ ኃይለ ፡ ይገብሩ ፡ ሐዋርያት ፡ ስምዐ፡
ተንሥአቱ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡

ሐዋርያትም ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክር
ስቶስ ፡ የትንሣኤው ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡
ደጋግ ፡ ተአምራት ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።

ወዐቢይ ፡ ሞገስ ፡ ቦሙ ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡

በሰው ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ መወደድ ፡ መታ
ፈር ፡ ነበራቸው ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፵፯ ።

፴፬ ፣ ወአልቦ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ጽኑስ ፡

ከነሱም ፡ ወገን ፡ ችግረኛ ፡ አልነበረም ።

ወኵሉ ፡ ዘቦ ፡ ቤት ፡ ወዐጸድ ፡

ቤት ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡

ይሠይጡ ፡ ወያመጽኡ ፡ ሤጦ ፡

እየሸጡ ፡ ዋጋውን፡ እያመጡ፡ ፪፡ ፵፭ ።

፴፭ ፣ ወያነብሩ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሆሙ ፡ ለሐዋርያት፡

ከሐዋርያት ፡ ከእግራቸው ፡ በታች ፡ ያፈ
ሱት ፡ ነበር ፡

ወእሙንቱ ፡ ይከፍሉ ፡ ለጽኑሳን ፡ ለለ፩ ፡ በከመ ፡
መፍቅዱ ፡

እነሱም ፡ ለተቸገረው ፡ ላንዱም ፡ ላን
ዱም ፡ እንደ ፡ ችግሩ ፡ ልብስ ፡ ለሌለው ፡
ልብስ ፡ ምግብ ፡ ለሌለው ፡ ምግብ ፡ ያድ
ሉት፡ ነበር፡ዘዳግ፡ ፲፭፡ ፲፩። ኢሳ፡ ፶፰፡ ፯ ።

፴፮ ፣ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ ዮሴፍ ፡

ዮሴፍ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡

ዘይብልዎ ፡ በርናባስ ፡

ባንድ ፡ ልሳን ፡ በርናባስ ፡ የሚባል ፡

እምውስተ ፡ ሐዋርያት ፡

ከሰብዓ ፡ አርድእት ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡

ወበትርጓሜሁ ፡ ይብልዎ ፡ ወልደ ፡ ፍሥሓ ፡

በርናባስ ፡ ማለት ፡ ትርጓሜው ፡ ወልደ ፡
ፍሥሓ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ከነገሩ ፡ የለውም ፡
ስብ ፡ ሊያርዱ፡ ጉፋያን ፡ ይነዱ፡ እንዲሉ ፡
ከሐናንያ ፡ ለማያያዝ ፡ ያመጣዋል ።

ሌዋዊ ፡ ዘምድረ ፡ ቆጵሮስ ፡

በቆጵሮስ ፡ የተሠራ ፡ ካህን ፡ ነበር ።

፴፯ ፣ ወቦ ፡ ገራህት ፡ ወሤጠ ፡

እርሻ ፡ ነበረው ፡ ሸጠ ፡

ወአምጽአ ፡ ሤጦ ፡ ወአንበረ ፡ ታሕተ ፡ እግረ ፡ ሐዋ
ርያት ፡

ዋጋውን ፡ አምጥቶ ፡ ከሐዋርያት ፡ ከእግ
ራቸው ፡ በታች ፡ አኖረ ።



## ምዕራፍ ፡ ፭ ፡

፩ ፣ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ ሐናንያ ፡

ሐናንያ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡
ሐናንያ ፡ ማለት ፡ በግዕ ፡ ደመና ፡ ማለ
ት ፡ ነው ፡

ወስመ ፡ ብእሲቱ ፡ ሰጲራ ፡

ምሽቱም ፡ ሰጲራ ፡ ትባላለች ፡ ሽቱ ፡
ማለት ፡ ነው ፡

ወሤጡ ፡ ዐጸዶሙ ፡

ቦታቸውን ፡ ሸጠው ።

፪ ፣ ወቀሠጠ ፡ መንፈቀ ፡ ሤጡ ፡ ተማኪሮሙ ፡
ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡

ተማኪሮሙ ፡ ካለ ፡ ሐናንያ ፡ ወብእሲቱ ፡
ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ካለ ፡ ተማኪሮ ፡ ባለ ፡
በቀና ፡ ነበር ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ መዓልት ፡
ምስለ ፡ ሌሊት ፡ ይትካፈልዎ ፡ ለዘመን ፡
በዕሩይ ፡ ከንቶ ፡ ይትናገሩ ፡ አሐዱ ፡
ምስለ ፡ ካልኡ ፡ እንዲል ፡ ይህ ፡ ማኅበር ፡
እፈታ ፡ እፈታ ፡ ብሏል ፡ ኋላ ፡ እኛ ፡ እን
ደምን ፡ እንሆናለን ፡ ብለው ፡ መክረው ፡
እኩሌታ፡ዋጋውን፡ከፍለው፡ አስቀርተው ፡

ወአምጽኡ ፡ መንፈቀ ፡ ሤጡ ፡

እኩሌታ ፡ ዋጋውን ፡ አምጥተው ፡

ወአንበሩ ፡ ታሕተ ፡ እግረ ፡ ሐዋርያት ፡

ከሐዋርያት ፡ ከእግራቸው ፡ በታች ፡ አፈ
ሰሱ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፴፯ ።

፫ ፣ ወይቤሎ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኦ ፡ ሐናንያ ፡ እፎ ፡ መል
አ ፡ ሰይጣን ፡ ውስተ ፡ ልብከ ፡

ኦ ፡ ቃለ ፡ አኅሥሮ ፡ ነው ፡ ኦ ፡ አብዳን ፡
ሰብአ ፡ ገላትያ ፡ እንዲል ፡ ሐናንያ ፡ ሰይ
ጣን ፡ በልቡናህ ፡ እንዴት ፡ ሰፈረ ፡

ከመ ፡ ተሐስዎ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡

ቦሁ ፡ ዘይሴወር ፡ እምኔየ ፡ እምኔየሁ ፡
ይሴወር ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ዘእፈትን ፡ ልበ ፡
ወኵልያተ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ብርሃኑ ፡ ለዓ
ለም ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አላዋቂ ፡
ታደርገው ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ስንኳን ፡
ከብትህን ፡ ሰውነትህን ፡ አስገዛለታለሁ ፡
ያልኸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ትከዳው ፡
ዘንድ ። አንድም ፡ ወአናቅጸ ፡ ሲኦልኒ ፡
ኢይኄይልዋ ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡
ታሳብለው ፡ ዘንድ ፡ ሰይጣን ፡ በልቡ
ናህ ፡ እንዴት ፡ ሰፈረ ፡

ወትቅስጥ ፡ እምሤጠ ፡ ዐጸድከ ፡

ከቦታህ ፡ ዋጋ ፡ ከፍለህ ፡ ታስቀር ፡ ዘ
ንድ ፡ የሐ ፡ ፲፫ ፡ ፪ ።

፬ ፣ አኮኑ ፡ ለከ ፡ ነበረ ፡ እምቅድመ ፡ ትሢጦ ፡

ሳትሸጠው ፡ ያንተ ፡ አልነበረምን ፡

ወሶበሂ ፡ ሤጥከ ፡ በፈቃድከ ፡

ብትሸጠውም ፡ ወደህ ፡ ሸጠኸዋል ፡

ለምንትኬ ፡ ሐለይከ ፡ በልብከ ፡ ትግበር ፡ ከመ ፡ ዝ ፡

እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡
በልቡናህ ፡ ለምን ፡ አሰብህ ፡

ለእግዚአብሔርኬ ፡ ሐሰውኮ ፡ ወአኮ ፡ ለሰብእ ፡

ሰውን ፡ ያይደለ ፡ ቦሁ ፡ ዘይሴወር ፡ እም
ኔየ ፡ እምኔየሁ ፡ ይሴወር ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡
ዘእፈትን ፡ ልበ ፡ ወኵልያተ ፡ አነ ፡ ውእ
ቱ ፡ ብርሃኑ ፡ ለዓለም ፡ ያለ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ አላዋቂ ፡ አደረግኸው ። አንድም፡
ሰውን ፡ ያይደለ ፡ ስንኳን ፡ ከብትህን ፡ ሰ
ውነትህን ፡ አስገዛለታለሁ ፡ ያልከው ፡
እግዚአብሔርን ፡ ከዳኸው ። አንድም ፡
ሰውን ፡ ያይደለ ፡ ወአናቅጸ ፡ ሲኦልኒ ፡
ኢይኄይልዋ ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡
አሳበልኸው ።

www.ethiopianorthodox.org

፭ ፤ ወሰሚዖ፡ዘንተ፡ነገረ፡ሐናንያ፡ተነጽሐ፡ ወሞተ ፡

ሐናንያም፡ይህን፡በሰማ፡ጊዜ፡ወድቆ፡ሞተ።

፮ ፤ ወኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ግርማ ፡

ጽኑ ፡ ፍርሃት ፡ ሆነ ፡

ወፈርሁ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሰምዑ ፡

በሰሙትም ፡ ሁሉ፡ ፍርሃት፡አደረባቸው ፡

ወተንሥኡ ፡ መሐዛት ፡ እምኔሆሙ ፡

ከነሱም ፡ ወገን ፡ ደጎቦች ፡ ተነሥተው ፡

ወጾርዎ ፡ ወገነዝዎ ፡ ወአውፅእዎ ፡ ወቀበርዎ ፡

አውፅእዎ ፡ ከሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ፊት ፡ መገ ነዝ ፡ አይገባም ፡ ብለው ፡ ከቤት ፡ አው ጥተው ፡ ገነዝዎ ፡ ከደጅ ፡ አውጥተው ፡ ገንዘው ፡ ጾርዎ ፡ ተሸክመው ፡ ወስደው ፡ ቀበርዎ ፡ ቀበሩት ። አንድም ፡ ገነዝዎ ፡ ከሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ፊት ፡ ገንዘው ፡ አው ፅእዎ ፡ ከቤት ፡ አውጥተው ፡ ጾርዎ ፡ ተሸ ክመው ፡ ወስደው ፡ ቀበርዎ ፡ ቀበሩት ። አንድም ፡ አውፅእዎ ፡ ከቤት ፡ አው ጥተው ፡ጾርዎ ፡ ተሸክመው ፡ ወስደው ፡ ገነዝዎ ፡ ከዚያው ፡ ከመቃብሩ ፡ ገንዘው ፡ ቀበርዎ ፡ ቀበሩት ፡ ዘሌዋ ፡ ፲ ፡ ፬ ፡ ፭ ።

፯ ፤ ወእምዝ ፡ እምድኅረ ፡ ሠለስቱ ፡ ሰዓት ፡ መጽ አት ፡ ብእሲቱ ፡

ከተቀበረ ፡ በኋላ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ምሽቱ ፡ ስትከናወት ፡ መጣች ፡

ወኢያእመረት ፡ ዘኮነ ፡ ምታ ፡

ባሏ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ አላወቀችም ፡

ወቦአት ፡

ከቤት ፡ በገባች ፡ ጊዜ ።

፰ ፤ ወይቤላ ፡ ጴጥሮስ ፡ ንግርኒ ፡ እስኩ ፡ በመጠ ነዝኑ ፡ ሤጥክሙ ፡ ዐጸደክሙ ፡

ጴጥሮስም ፡ ቦታችሁን ፡ በምን ፡ ያህል ፡ ሸጣችሁት ፡ እስኪ ፡ ንገሪኝ ፡ አላት ፡

ወትቤ ፡ እወ ፡ ከማሁ ፡

እሷም ፡ እንደ ፡ ባሏ ፡ በዚህን ፡ ያህል ፡ ነው ፡ አለችው ። አንድም ፡ ቦታችሁን ፡ በምን ፡ ያህል ፡ ሸጣችሁት ፡ በዚህን ፡ ያህል ፡ ነውን ፡ ቢላት ፡ እሷም ፡ እንደ ፡ ጴጥሮስ ፡ አዎን ፡ በዚህን ፡ ያህል ፡ ነው ፡ አለች ።

፱ ፤ ወይቤላ ፡ ጴጥሮስ ፡ በእፎ ፡ እንከ ፡ ኅበርክሙ ፡ ታመክርዎ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡

ጴጥሮስም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ትፈታ ተኑት ፡ ዘንድ ፡ እንደምን ፡ ተባበራችሁ ፡

ናሁኬ ፡ እገሪሆሙ ፡ ለእለ ፡ ቀበርዎ ፡ ለምትኪ ፡ ኅበ፡ ኆኅት ፡

ባልሽን ፡ የቀበሩት ፡ ሰዎች ፡ ተመልሰው ፡ ከበር ፡ ደርሰዋል ፡

ወእሙንቱ ፡ ይወስዱኪ ፡ ኪያኪኒ ፡

አንቺንም ፡ ወስደው ፡ ይደርቡሻል ፡ ይደ ርቡሽ ፡ አላት ።

፲ ፤ ወተነጽሐት ፡ ሶቤሃ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ወሞ ተት ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ወድቃ ፡ ሞተች ፡

ወቦኡ ፡ ወራዙት ፡ ወረከብዋ ፡ በድና ፡

ደጎቦች ፡ ቢገቡ ፡ ሙታ ፡ አገኟት ፡

ወወሰድዋ ፡ ወቀበርዋ ፡ ኅበ ፡ ምታ ፡

እሷንም ፡ ወስደው ፡ ከባሏ ፡ ደረብዋት ።

፲፩ ፤ ወኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ግርማ ፡

ጽኑ ፡ ፍርሃት ፡ ሆነ ፡

ወፈርሁ ፡ ኵሎሙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡

በምእመናን፡ ሁሉ፡ ፍርሃት፡ አደረባቸው ፡

ወእለ ፡ ሰምዕዎ ፡ ለዝ ፡ ነገር ፡

ይህንን ፡ ነገር ፡ በሰሙም ፡ ሁሉ ፡ ፍር ሃት ፡ አደረባቸው፡ ቀሌምንጦስ ፡ ቅዱስ ፡



ጴጥሮስን ፡ እንደምነው ፡ ብሎ ፡ ጠይቆ ታል ፡ ተናግሬ ፡ እስክጨርስ ፡ መላክ ፡ ሰይፉን ፡ መዞ ፡ ይጠብቀኛል ፡ ስጨርስ ፡ ይቀጣቸዋል ፡ እሊህስ ፡ በነፍስ ፡ ተጎድ ተዋል ፡ ቢሉ ፡ አዎን ፡ ተጎድተዋል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ከድተዋልና ፡ ይህስ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ የደከሙበት ፡ ገንዘባ ቸው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለሌላው ፡ አብነት ፡ እንዳይሆኑ ፡ በሥጋ ፡ አጥፍቷቸዋል ፡ እንጅ ፡ አልተጎዱም ።

፲፪ ፤ ወበእደዊሆሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ ይትገበር ፡ ተአምር ፡ ወመንክር ፡ ብዙኅ ፡ በውስተ ፡ ሕዝብ ፡

በሐዋርያት ፡ ቃል ፡ በሐዋርያት ፡ ሥል ጣን ፡ ደጋግ ፡ ተአምራት ፡ ይደረግ ፡ ነበር ፡

ወሀለዉ ፡ ኅቡረ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስተ ፡ ሕዋረ ፡ ሰሎሞን ፡

በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሰሎሞን ፡ ባሠራው ፡ ባንድነት፡ እያስተማሩ ፡ ኖሩ፡ ም፡ ፫፡ ፲፩ ።

፲፫ ፤ ወእምዝ፡ እንከ፡አልቦ፡ ዘተኀበለ፡ይስሐጦሙ ፡

ከዚህ፡ በኋላ፡ ሊጣላቸው፡ የደፈረ፡ የለም፡

ዳዕሙ ፡ አክበርዎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ወአዕበይዎሙ ፡

ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመው ፡ አከበሯ ቸው ፡ እንጅ ።

፲፬ ፤ ወብዙኃን ፡ ይትዌሰኩ ፡ እለ ፡ የአምኑ ፡ በእ ግዚእነ ፡

በጌታችን ፡ የሚያምኑትም ፡ ዕለት ፡ ዕለ ት ፡ እየተጨመሩ ፡ ይበዙ ፡ ነበር ።

ወብዙኃን ፡ ዕደው ፡ ወአንስት ፡

ሴቶችም ፡ ወንዶችም፡ ም፡ ፪ ፡፵፯ ፡ ፬፡ ፬ ፡ ፯ ፡ ፯ ።

፲፭ ፤ ወያመጽኡ ፡ ድውያነ ፡ በአራታት ፡

ድውያንን ፡ በአልጋ ፡ እየተሸከሙ ፡ እያ መጡ ፡

ወያነብርዎሙ ፡ ከመ ፡ ይብጽሖሙ ፡ ጽላሎቱ ፡ ለጴ ጥሮስ ፡ ሶበ ፡ የኀልፍ ፡

ጴጥሮስ ፡ አልፎ ፡ ሲሄድ ፡ ጥላውን ፡ ይጥ ልባቸው ፡ ዘንድ ፡ አልፎ ፡ በሚሄድበት ፡ በኩል ፡ ያስተኟቸው ፡ ነበር ፡

ወይትፌወሱ ፡ እምደዌሆሙ ፡

ከደዌያቸውም ፡ ይድኑ ፡ ነበር ፡ የጥዋት ፡ የማታ፡ጥላ፡ሰባ፡ ሰማንያ፡ጫማ፡ ይሆናል ፡ በዚያ ፡ ልክ ፡ ድውያንን ፡ ወስደው ፡ ደር ድረው፡ ያስተኟቸዋል፡ አልፈው ፡ ሲሄዱ፡ ጥላቸው ፡ ሲወድቅባቸው ፡ እየዳኑ ፡ ይኼ ሡ ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።

፲፮ ፤ ወይመጽኡ ፡ ብዙኃን ፡ እምአህጉረ ፡ አድ ያም ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡ ወያመጽኡ ፡ ድውያነ ፡

በኢየሩሳሌም ፡ አውራጃ ፡ ካሉ ፡ አገሮች፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ድውያንን ፡ እየያዙ ፡ ይመ ጡ ፡ ነበር ፡

ወእለ ፡ አጋንንት ፡ እኩያን ፡

አጋንንት ፡ ያደሩባቸውን ፡ እየያዙ ፡ ይመ ጡ ፡ ነበር ፡

ወየሐይዉ ፡ ኵሎሙ ፡

ሁሉም ፡ ይድኑ ፡ ነበር ።

፲፯ ፤ ክፍል ፡ ፱ ፡ ወተንሥኡ ፡ ሊቀ፡ ካህናት ፡

የካህናት ፡ አለቆች ፡ ተነሡ ፡ ተንሥእ ፡ በነገር ፡ ነው ፡

ወእለ ፡ ምስሌሁ ፡

ከሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡

ወሕዝበ ፡ ሰዱቃውያን ፡

የሰዱቃውያንም ፡ ወገኖች ፡ ተነሡ ፡

ወቀንኡ ፡ ዲቤሆሙ ፡

በሐዋርያት ፡ ቀኑባቸው ፡ ም፡ ፬ ፡ ፭ ፡ ፯ ።

፲፰ ፤ ወአኀዝዎሙ ፡ ለሐዋርያት፡ ወአውዐልዎሙ፡ ሙዓለ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡

ይዘው ፡ አስረው ፡ አሳደሯቸው ፡ አውዓል

www.ethiopianorthodox.org

ዎሙ፡ ማለቱ ፡ መዓልቱ ፡ አልተፈጸመም፡ ነበርና ። አንድም ፡ ሌሊት ፡ መብራት ፡ እያበሩ ፡ ዘበኛው ፡ ተሰብስቦ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ እየዘፈነ ፡ ያድራሉ ፡ ቀን ፡ የኋ ሊት ፡ ዘግተውባቸው ፡ ይሄዳሉ ፡ በጨለ ማ ፡ ይውላሉና ፡ ጽኑ ፡ ግዞት ፡ አጋዟቸው፡ ሲል ፡ አውዓልዎሙ ፡ አለ ።

፲፱ ፤ ወመልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አርኀወ ፡ አና ቅጸ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ በሌሊት ፡ ወአውጽኦሙ ፡

ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ በሌሊት ፡ የሥሩን ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ ከፍቶ ፡ አወጣቸው ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ፯ ።

፳ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ሑሩ ፡ ባኡ ፡ ምኵራብ ፡ ወመ ሀርዎሙ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ሕይወት ፡

ሂዳችሁ ፡ ከምኵራብ ፡ ገብታችሁ ፡ ይህን፡ የድኅነት ፡ ነገር ፡ ለሕዝቡ ፡ አስተምሩ ፡ አላቸው ፡ ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፶ ።

፳፩ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ ዘንተ ፡ ጌሠ ፡ ነግሀ ፡ በጽባሕ ።

ይህን፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ማልደው፡ገስግሰው ፡

ወቦኡ ፡ ምኵራበ ፡ ወመሀሩ ፡

ከምኵራቡ ፡ ገብተው ፡ ጉባኤ ፡ ሠርተው ፡ አስተማሩ ፡

ወሊቃነ ፡ ካህናትሰ ፡

የካህናቱ ፡ አለቆች ፡

ወእለ ፡ ምስሌሆሙ ፡

ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ግን ፡

አስተጋብኡ ፡ ዓውዶሙ ፡

ሕዝቡን ፡

ወኵሎ ፡ ሊቃነ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡

የእስራኤልን፡የቤት፡ አለቆች፡ ሰብስበው ፡

ወለአኩ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ያምጽእዎሙ ፡ ለሐዋርያት፡

ሐዋርያትን ፡ ይዛችሁ ፡ አምጡ ፡ ብለው ፡ ከእስሩ ፡ ቤት ፡ ላኩ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፭ ።

፳፪ ፤ ወበጽሑ ፡ ወዓልያኒሆሙ ፡ ወኃጥእዎሙ ፡

ብላቴኖቻቸውም ፡ ደርሰው፡ ባያገኟቸው፡

ወተሠውጡ ፡ ወነገርዎሙ ፡

ተመልሰው፡ ነገሯቸው ፡

፳፫ ፤ ወይቤልዎሙ ፡ ረከብነ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ንሡገ ፡ ወቅቱረ ፡ ወዘጉሐ ፡ እንተ ፡ ኵለሄ ፡

የዕሥር፡ ቤቱን ፡ ዝጉሐ፡ ተመልሶ፡ቅቱረ፡ ተወርውሮ ፡ ንሡገ ፡ በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ተቈልፎ፡ አገኘው ፡

ወሠገራተ ፡ የዐቅቡ ፡ አናቅጺሁኒ ፡

ጭፍሮችም ፡ በሩን ፡ ይዘው ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ፡

ወአርኀወነ ፡ አልቦ ፡ ዘረከብነ ፡ በውስጥ ፡

ከፍተን ፡ በገባን ፡ ጊዜ ፡ በውስጥ ፡ ያገኘ ነው ፡ የለም ፡ ብለው ፡ ነገሯቸው ።

፳፬ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት፡ ወመገብተ ፡ ምኵራብ ፡ ኃጥኡ ፡ ዘይገብሩ ፡

የካህናቱ ፡ አለቆች ፡ የምኵራቡ ፡ ሹማም ት ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የሚያ ደርጉት ፡ ቸገራቸው ፡

ወይቤሉ ፡ ምንትኑ ፡ እንጋዝ ፡

ይህ ፡ ነገር ፡ እስኪ ፡ ምንድነው ፡ አሉ ።

፳፭ ፤ ወመጽአ ፡ አሐዱ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ነዮሙ ፡ እሙንቱ ፡ ዕደው ፡ እለ ፡ ሞቃሕክምዎሙ ፡ ውስተ ፡ ምኵራብ ፡ ይቀውሙ ፡ ወይሜህሩ ፡ ለሕዝብ ፡

ከሐናንያ ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ሰው፡ መጥቶ ፡ በቀል ፡ ደገል ፡ የመለስሁ ፡ መስ ሎት ፡ አስራችኋቸው ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ከምኵራቡ ፡ ገብተው ፡ ለሕዝቡ ፡ ያስተም ራሉ ፡ ብሎ ፡ ነገር ፡ ሠራ ።

፳፮ ፤ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ መጋቤ ፡ ምኵራብ ፡ ምስለ ፡ ወዓሊሁ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የምኵራቡ ፡ ሹም ፡ ብላ ቴናውን ፡ አስከትሎ ፡ ሄደ ፡

ያምጽእሙ ፡ እንዘ ፡ ይዬውሆሙ ፡

እያባበለ ፡ ያመጣቸው ፡ ዘንድ ፡

እስመ ፡ ይፈርህዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ኢይውግርዎሙ ፡

ሐዋርያት ፡ እንዳይጣሏቸው ፡ ሕዝቡን ፡ ይፈሯቸው፡ ነበርና ፡ እያባበለ። አንድም ፡ እንዳይጣሏቸው ፡ ሕዝቡ ፡ ሐዋርያትን ፡ ይፈሯቸው ፡ ነበርና ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ማኀበር፡ ናቸው፡ አግባ ፡ መልስ ፡ ብለው ፡ ቢጣሉንሳ ፡ ብለው ፡ ይፈሯቸው፡ ነበርና።

፳፯ ፤ ወአምጽእዎሙ ፡ ወአቀምዎሙ ፡ ማዕከለ ፡ ዓውድ ፡

አስመጥተው ፡ በአደባባይ ፡ መካከል ፡ አቁመው ፡

ወሐተትዎሙ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡

የካህናት ፡ አለቆች ፡ መረመሯቸው ።

፳፰ ፤ ወይቤልዎሙ ፡ አኮኑ ፡ ከላእናክሙ ፡ ከመ ፡ ኢትምሀሩ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ወኢለመኑሂ ፡

ስሙ ፡ ሕይወት ፡ መድኃኒት ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ለማንም ፡ ለማን ፡ አታስተምሩ ፡ ብለና ችሁ ፡ አልነበረምን ፡ ብለው ፡

ወናሁ ፡ መላእክምዋ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ትምህርተ ክሙ ፡

እነሆ ፡ ትምህርታችሁን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከሁሉ ፡ አደረሳችኋት ፡

ወትፈቅዱኑ ፡ ታግብኡ ፡ ላዕሌነ ፡ ደሞ ፡ ለዝ ፡ ብእሲ፡

የዚያን ፡ ሰው ፡ ደም ፡ በኛ ፡ ልትመልሱት ትወዳላችሁን ፡ አንድም ። እኛን ፡ ገፋ ዕያን ፡ ልታሰኙ ፡ ትወዳላችሁን ፡ አሏ ቸው ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፲፰ ። ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፳፭ ።

፳፱ ፤ ወተሰጥዎሙ ፡ ጴጥሮስ ፡ ምስለ ፡ ሐዋርያት ፡ ወይቤሎሙ ፡ ይኄይስነ ፡ ናድሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምነ ፡ አድልዎ ፡ ለሰብእ ፡

ጴጥሮስም ፡ ከሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ ሰውን ፡ ደስ ፡ ከማሰኘት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ማሰኘት ፡ ይሻለናል ፡ ብሎ ፡ መለሰላ ቸው ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፲፱ ። ዳን ፡ ፮ ፲ ።

፴ ፤ አምላከ ፡ አበዊነ ፡ አንሥአ ፡ ለኢየሱስ ፡ ዘአ ንትሙ ፡ ዓለውክምዎ ፡ ወሰቀልክምዎ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ፡ ወቀተልክምዎ ፡

ያባቶቻችን ፡ ፈጣሪ ፡ እናንት ፡ አምፃችሁ፡ ዕሩቅ፡ ብእሲ፡ ብላችሁ፡ በዕፅ፡ ሰቅላችሁ ፡ የገደላችሁት ፡ ኢየሱስን ፡ አስነሣው ።

፴፩ ፤ ኪያሁ ፡ ረሰዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልአከ፡ ሕይወት ፡

እሱን ፡ የድኅነት ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ አስነሣው ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።

ወአልዐሎ ፡ በየማኑ ፡

አስነሥቶም ፡ በዕሪናው ፡ አኖረው ፡

ወወሀቦሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ንስሓ ፡ ከመ ፡ ይትኅደግ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ ፡

ኃጢአታቸው ፡ ይሠረይላቸው ፡ ዘንድ ፡ ነስሑ ፡ ብሎ ፡ ለእስራኤል ፡ አስተማራ ቸው። አንድም ፡ አርባ ፡ ዘመን፡ መዋዕለ ፡ ንስሓን ፡ ሰጣቸው ፡ ኃጢአታቸው ፡ ይሠ ረይላቸው ፡ ዘንድ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፴፫ ፡

፴፪ ፤ ወንሕነሰ ፡ ሰማዕቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ነገር ፡

ለዚህም ፡ ነገር ፡ ምስክሮቹ ፡ እኛ ፡ ነን ፡

ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘወሀቦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእለ ፡ የአምኑ ፡ ቦቱ ፡

እግዚአብሔር ፡ ለሚያምኑበት ፡ ለምእመ ናን ፡ የሰጣቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ምስክር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፵፰ ። ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮ ፡

፴፫ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ ዘንተ ፡ ተምዕዑ ፡

ይህንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ተበሳጩ ፡

ወሐቀዩ ፡ ስነኒሆሙ ፡

ጥርሳቸውን ፡ አፋጩ ፡ አለ ፡ አጽንተው ፡ ተጣሏቸው ፡ ትእምርተ ፡ ጸብዕ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ወፈቀዱ ፡ ይቅትልዎሙ ፡

ሊገሏቸው ፡ ወደዱ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ፶፬ ፡

፴፬ ፤ ወተንሥአ ፡ አሐዱ ፡ እምውስተ ፡ ዓውድ ፡ እምሕዝበ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ዘስሙ ፡ ገማልያል ፡

ሽማግሌ ፡ ባለበት ፡ ነገር ፡ አይሰረቅ፡ ጉል ማሳ ፡ ባለበት ፡ ከብት ፡ አይነጠቅ ፡ እን ዲሉ ፡ ከፈሪሳውያን ፡ ወገን ፡ ገማሊያል ፡ የሚባል፡አንድ፡ሰው፡ ካደባባይ፡ ተነሥቶ ፡

መምህረ ፡ ኦሪት ፡

ኦሪትን ፡ የተማረ ፡ ነበር ፡

ወክቡር ፡ ውእቱ ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ፡

ሕዝቡም፡ሁሉ፡ያከብሩት፡ነበር፡ ተነሥቶ ፡

ወአዘዘ ፡ ያእትትዎሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ ሕቀ ፡ እምውስተ ፡ ዓውድ ፡

ሊመክሩለትም ፡ ሊመክሩበትም ፡ ቢሆን ፡ ቆዩ ፡ ማለት ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡ ከአደባ ባይ ፡ ጥቂት ፡ ቆዩ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ፫ ።

፴፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አንትሙ ፡ ሰብአ ፡ እስራኤል ፡ አድኀኑ ፡ ርእሰክሙ ፡

እናንት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ራሳች ሁን ፡ አድኑ ፡

ወዑቁ ፡ በእንተ ፡ እሉ ፡ ሰብእ ፡ ዘከመ ፡ ትገብሩ ፡

ስለ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የምታደርጉትን ፡ ዕወቁ ።

፴፮ ፤ ቀዲሙኒ ፡ እምቅድመ ፡ ዝ ፡ መዋዕል ፡ ተንሥአ ፡ ቴዎዳስ ፡ ዘግብፅ ፡

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ የግብፅ ፡ ሰው ፡ የሚ ሆን ፡ ቴዎዳስ ፡ ተነሣ ፡

ወአዕበየ ፡ ርእሶ ፡

አምላክ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡

ወተለውዎ ፡ አርባእቱ ፡ ምእት ፡ ሰብእ ፡

አራት፡መቶ፡ሰዎችም፡አምነው፡ተከተሉት

ወጠፍአ ፡ ውእቱኒ ፡

እሱም ፡ ጠፋ ፡

ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ ቦቱ ፡ ተዘርዉ ፡

አምነውበት፡ የተከተሉትም፡ ሁሉ፡ ጠፉ ፡

ወኮኑ ፡ ከመ ፡ ዘኢተፈጥሩ ፡

እንዳልነበሩ ፡ ሆኑ ።

፴፯ ፤ ወእምድኅሬሁ ፡ ተንሥአ ፡ ይሁዳ ፡ ዘገሊላ ፡

ከዚህ፡በኋላ፡የገሊላው፡ሰው፡ይሁዳ፡ተነሣ ፡

በመዋዕል ፡ ዘትጽሕፉ ፡ ሰብእ ፡ በእንተ ፡ ጸባሕት ፡

ሰዎች ፡ ከግብር ፡ በተቈጠሩበት፡ ወራት ፡

ወተለውዎ ፡ ብዙኃን ፡ ሕዝብ ፡

ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አምነው ፡ ተከተሉት ፡

ወሞተ ፡ ውእቱሂ ፡

እሱም ፡ ሞተ ፡

ወእለ ፡ ተለውዎሂ ፡ ተዘርዉ ፡ ኵሎሙ ፡

አምነው ፡ የተከተሉትም ፡ ሁሉ ፡ ጠፉ ።

፴፰ ፤ ወይእዜኒ ፡ እብለክሙ ፡ ኅድግዎሙ ፡ ለእሉ፡ ሰብእ ፡ ወኢትስሐጥዎሙ ፡

አሁንም ፡ እሊህን ፡ ሰዎች ፡ ተዉዋቸው ፡ አትጣሏቸው ፡ እላችኋለሁ ፡

ለእመሁ ፡ ዘእምኀበ ፡ ሰብእ ፡ ዝ ፡ ምክሮሙ ፡ ወዝ ፡ ግብሮሙ ፡ የኀልፍ ፡ ወይሰዐር ።

ይህ፡ የሚያስተምሩት ፡ ትምህርት ፡ የሚያ ደርጉት ፡ ተአምራት ፡ በሰው ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያልፋል ፡ ይጠፋል ፡ ማቴ ፡ ፲፭ ፡ ፲፫ ።

፴፱ ፤ ወለእመ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኮነ ፡ ኢትክሉ ፡ አኅድኖቶሙ ፡

በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ማስተው ፡ አይቻላችሁም ፡

ወከመ፡ ዘምስለ፡ እግዚአብሔር፡ ይትበአስ፡ኢትኩኑ፡

ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ እንደሚጣላ ፡ እን ደ፡ ማናቸውም፡ ሰው። አንድም፡እንደ፡ናም ሩድ ፡ እንደ ፡ ፈርዖን ፡ እንደ ፡ ብልጣሶር፡ እንደ ፡ ሄሮድስ ፡ አትሁኑ ። አንድም ፡ ከእ ግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ እንደምትጣሉ ፡ አት ሁኑ ፡ ብሎ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፭ ።

፵ ፤ ወአሆ ፡ አበሎሙ ፡

እሺ ፡ አሰኛቸው ፡

ወጸውዕዎሙ፡ ለሐዋርያት፡ ወቀሠፍዎሙ፡ ወገሠጽዎሙ፡ኢይንግሩ፡እንከ፡በስሙ፡ለኢየሱስ፡ወኀደግዎሙ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሐዋርያትን ፡ ጠርተው ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ስሙ ፡ ሕይወት ፡ መድ ኃኒት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዳያስተምሩ ፡ አታስተምሩ ፡ ብለው ፡ ሽመጣጠው ፡ ተውዋቸው ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ፲፱ ።

፵፩ ፤ ወወጽኡ ፡ እምዓውድ ፡ እንዘ ፡ ይትፌሥሑ ፡

ሐዋርያትም ፡ ገፈው ፡ ገርፈው ፡ ከአደባ ባይ ፡ ሲያስወጧቸው ፡ እንደ ፡ ተሾመ ፡ እንደ ፡ ተሸለመ ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ሄዱ ።

እስመ ፡ ከፈሎሙ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ያኅሥርዎሙ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡

በስሙ ፡ ስላመኑ ፡ በስሙ ፡ ስለ ፡ ተጠሩ ፡ ስሙን፡ስላስተማሩ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ለመ ከራው፡ አብቅቷቸዋልና ማቴ ፡ ፭፡ ፲፡ ፲፪ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፲፫ ።

፵፪ ፤ ወኢያርመሙ ፡ ዘኢይመሀሩ ፡ ትምህርተ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡

ሁል ፡ ጊዜ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ። በማስተ ማር ፡ ጽሙዳን ፡ ሁነው ፡ ኖሩ ፡

ወውስተ ፡ ቤትኒ ፡ ኢኀደጉ ፡ ነጊረ ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

በቤትም ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስ ቶስን ፡ ነገር ፡ ማስተማር ፡ አልተዉም ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ፡ ክፍል ፡ ፲ ፡

፩ ፤ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ በዝኀ ፡ ሕዝብ ፡

ወኵሎ ፡ አሚረ ፡ ይፀመዱ ፡ በቤተ ፡ መቅ፡ ደስ ፡ ወውስተ ፡ ቤትኒ ፡ ኢኀደጉ ፡ ነጊረ ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ በዙ ፡

ወግዕዝዎሙ፡ለእለ፡እምአረሚ፡አርድእት፡ለአይሁድ ፡

ሰው ፡ ከበዛ ፡ መነቃቀፍ ፡ አይቀርምና ፡ የአይሁድ ፡ ሴቶች ፡ የአረሚን ፡ ሴቶች ፡ ነቀፉዋቸው ፡

እስመ ፡ ይሬእይዎን ፡ ለመበለታቲሆን ፡ እንዘ ፡ ኢይፀመዳ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡

ለተግባረ ፡ ሥጋው ፡ እንጅ ፡ ለተግባረ ፡ ነፍሱ ፡ ጽሙዳን ፡ ሳይሆኑ ፡

ወያሰትታ ፡ ተልእኮቶን ፡

ተግባረ ፡ ሥጋውን ፡ እንጅ ፡ ተግባረ ፡ ነፍሱን ፡ ቸል ፡ ሲሉት ፡ ያይዋቸዋልና ፡ አሁን ፡ እኒህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ተውንለት ፡ ይላሉ ፡ መሽ ፡ ለሆዴ ፡ ጠባ ፡ ለሆዴ፡ ቀድሞም፡ ይኸው፡ ዛሬም፡ይኸው፡ ብለው ። አንድም፡ የሴት ፡ ነቀፋ ፡ ለዚህ ፡ ወጧ ፡ ለዚህ ፡ እንጀራዋ ፡ ሥራ ፡ ፈታ ፡ ትውልን ፡ ብለው። አንድም ፡ መነቃቀፍ ፡ የጋራ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወግዕዝዎሙ ፡ እለ ፡ እምአረሚ ፡ አርድእት ፡ ለአይሁድ ፡ የአ ረሚ ፡ ሴቶች ፡ የአይሁድን ፡ ሴቶች ፡ ነቀ ፋዋቸው ፡ ለተግባረ ፡ ነፍሱ፡ እንጅ ፡ ለተ ግባረ ፡ ሥጋው ፡ ጽሙዳን ፡ ሳይሆኑ ፡ ተግባረ ፡ ነፍሱን ፡ እንጅ ፡ ተግባረ ፡ ሥጋ ውን ፡ ቸል ፡ ሲሉት ፡ ያይዋቸዋልና ፡ ሐዋ ርያት ፡ ሥራት ፡ ሠርተዋል ፡ በለመዱ ፡ በለመዱት ፡ ይዋሉ ፡ ብለው ፡ የአይሁድ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ሴቶች ፡ ጊዜያት ፡ በማድረስ ፡ ድውይ ፡
በመጠየቅ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅ ፡
በመንሣት ፡ መጽሐፍ ፡ በመመልከት ፡
የአረሚ ፡ ሴቶች ፡ በመቁላት ፡ በመፍጨ
ት ፡ እንጀራ ፡ በመጋገር ፡ ወጥ ፡ በመሥ
ራት ፡ ይዋሉ ፡ ብለው ፡ የአረሚ ፡ ሴቶች ፡
አንዳች ፡ ሁላችንስ ፡ በየሀገራችን ፡ ሳለን ፡
አንዳንድ ፡ ሎሌ ፡ አንዳንድ ፡ ገረድ ፡ የሌ
ለውን ፡ አለ ፡ እንጸድቅ ፡ ብለን ፡ ነው ፡
እንጅ ፡ ተግባረ ፡ ሥጋውንስ ፡ ተግባረ ፡
ነፍሱንስ ፡ አንድ ፡ አድርገን ፡ ብንይዝ ፡
ይሆን ፡ የለም ፡ ብለዋል ፡ ይህ ፡ ሲሳሳብ ፡
ከወንዶች፡ ደረሰ፡ ወንዶችም፡ ይህ፡ ሁሉ ፡
ሐዋርያት፡ ሥርዐት ፡ ባይሠሩላቸው ፡ አይ
ደለም ፡ ብለዋል ፡ ም፡ ፩ ፡ ፴፭ ።

፪ ፤ ወጸውዕዎሙ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ለኵሉ ፡
ሕዝብ ፡

ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሐዋርያትም ፡ ይህን ፡
ሰምተው ፡ ሕዝቡን ፡ ጠርተው ፡

ወይቤልዎሙ ፡ ኢይደልወነ ፡ ከመ ፡ ንኅድግ ፡ ቃለ ፡
እግዚአብሔር ፡ ወንፀመድ ፡ ማዕዳተ ፡

እኛስ ፡ ወንጌልን ፡ ማስተማር ፡ ትተን ፡
ራቅ ፡ ማሰርነት ፡ ልንሾም ፡ አይገባንም ።

፫ ፤ ኅረዩ ፡ እምውስቴትክሙ ፡ ሰብዐተ ፡ ዕደወ ፡
እለ ፡ ምሉአን ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ ወጥበበ ፡ እለ ፡
ንሠይም ፡ ዲበ ፡ ዝ ፡ ግብር ፡

አላ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ራቅማሰርነት ፡ የም
ንሾማቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያደረባ
ቸው ፡ ዕውቀት ፡ የተመላባቸው ፡ ከናንት፡
ወገን ፡ ሰባት ፡ ሰዎች ፡ ምረጡ ፡ እንጅ ።
፩፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፯ ፡ ፰ ።

፬ ፤ ወንሕነሰ፡ንፀመድ፡ጸሎተ፡ ወመልእክተ፡ ቃሉ ፡

እኛስ ፡ ሑሩ ፡ ወመሀሩ፡ ያላት፡ ወንጌልን፡
በማስተማር ፡ በጸሎት ፡ ጽሙዳን ፡ ሁነን ፡
እንኖራለን ፡ አሏቸው ፡

ወኅብሩ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡

ሁሉም ፡ አንድ ፡ ሁነው ።

፭ ፤ ወሠናየ ፡ ኮነ ፡ ዝ ፡ ነገር ፡ በኀቤሆሙ ፡

ይህ ፡ ነገር ፡ በነሱ ፡ ዘንድ ፡ ያማረ ፡ የተ
ወደደ ፡ ሆነ ፡ አለ ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ሰው ፡
ለልማዱ ፡ ልሹምብህ ፡ ከሚሉት ፡ የወደ
ድኸውን ፡ መርጠህ ፡ ሹም ፡ ቢሉት፡ ይወ
ዳልና ። አንድም ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡
ሥራ፡ ፈት፡ ሁኖ፡ የሚውል፡ የለም ፡ ሲሉ ፡

ወኀረዩ ፡ እስጢፋኖስሃ ፡ ብእሴ ፡ ዘምሉእ ፡ ሃይማኖተ
ወመንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡

ሃይማኖቱ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ያደረበት ፡ እስጢፋኖስን ፡ መር
ጠው ፡ መደበኛ ፡ አድርገው ፡

ወፊልጶስ ፡

ፊልጶስን ፡

ወጰርኮሮን ፡

ጰርኮሮንን ፡

ወኒቃሮና ፡

ኒቃሮናን ፡

ወጢሞና ፡

ጢሞናን ፡

ወጰርሜና ፡

ጰርሜናን ፡

ወኒቃላዎስ ፡ ፈላሴ ፡ ዘሀገረ ፡ አንጾኪያ ፡

ከአንጾኪያ ፡ ተሰዶ ፡ የመጣ ፡ ኒቃላዎስን ፡
እሊህን ፡ ስድስቱን ፡ መርጠው ።

፮ ፤ ወአቀምዎሙ ፡ ቅድመ ፡ ሐዋርያት ፡

በሐዋርያት ፡ ፊት ፡ ወስደው፡ አቆሟቸው፡

ወጸለዩ ፡ ወወደዩ ፡ እደዊሆሙ ፡ ላዕሌሆሙ ፡

ሐዋርያትም ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ጸለዩ
ላቸው ። ሀብተ ፡ እርድናን ፡ አሳደሩባቸ



ው ፡ ሢመተ ፡ ዲቁና ፡ ሾሟቸው ፡ ሢመተ
ዲቁናስ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሀብ
ተ ፡ እርድና ፡ አሳደሩባቸው ፡ ሢመተ ፡
እርድና ፡ ሾሟቸው ።

፯ ፤ ወዐብየ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡

እለ ፡ እስጢፋኖስ ፡ በአፍአ ፡ ቢያስተ
ምሩ ፡ እሊህ ፡ በውስጥ ፡ ቢያስተነትኑ ፡
ኦሪት ፡ እጠፋ ፡ እጠፋ ፡ ወንጌል ፡ እሰፋ ፡
እሰፋ ፡ አለች ፡

ወበዝኁ ፡ ሕዝብ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ፈድፋደ ፡

ሕዝቡም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እጅግ ፡ በዙ ፡

ወብዙኃን ፡ እምውስተ ፡ ካህናት ፡ እለ ፡ አምኑ ፡

ከካህናት ፡ ወገንም ፡ ወንጌልን ፡ ያመኑ ፡
ብዙ ፡ ናቸው ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።

፰ ፤ ወእስጢፋኖስሰ፡ ምሉእ ፡ ጸጋ፡ እግዚአብሔር ፡

እስጢፋኖስ ፡ ግን ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡

ወኃይል ፡

ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረበት ፡ ነበር ።

ወይገብር ፡ ዐቢየ ፡ ተአምረ ፡ ወመንክረ ፡ በውስተ ፡
ሕዝብ ፡

በሕዝቡም፡ ዘንድ፡ ደጋግ፡ ተአምራት፡ ያደ
ርግ ፡ ነበር ፡ (ታሪክ) ፡ ናዖስ ፡ የሚባል ፡ አ
ንድ ፡ መሠርይ ፡ ነበር፡ እስጢፋኖስ፡ ዲዳ ፡
ደንቆሮ ፡ አግኝቶ፡ እፍ፡ ቢለው፡ ዲዳ፡ የነ
በረው ፡ ተናገረ ፡ ደንቆሮ ፡ የነበረው ፡ ሰ
ማ ፡ ሕዝቡ፡ ተአምራትስ፡ ይህታ፡ ብለው፡
ወደ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ተመልሰዋል ፡ ናዖስ
ም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ በሬ ፡ ሂዶ ፡ በጆሮው ፡
ሹክ፡ቢለው፡ ከሁለት፡ ተከፈለ፡ ሚዛን፡ ቢ
ያገቡት፡ ተካከለ፡ ሕዝቡም፡ ተአምራትስ፡
ይህታ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ናዖስ ፡ ተመልሰ
ዋል ፡ እስጢፋኖስ ፡ በሬውን ፡ አስነሥቶ፡
ናዖስን ፡ ጠርተህ ፡ አምጣው ፡ አለው ፡
[illegible] ፡ አመጣው ፡

ተአምራትስ ፡ ይህታ ፡ ብለው ፡ ሕዝቡ ፡
ወደ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ተመልሰዋል ፡ ይህ ፡
ናዖስ ፡ ሕዝቡን ፡ ሰብስቦ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡
ስሕተቴን ፡ ሳይገልጥብኝ ፡ አልቀረም ፡
ብሎ ፡ የዕገሌ ፡ ሀብቱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የዕ
ገሌ ፡ ሀብቱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ማዕርግ፡
የሰጠ ፡ መስሎ ፡ አጋንንትን ፡ በምስሐብ ፡
ጠርቶ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ይዛችሁኝ ፡ ውጡ ፡
አላቸው ፡ ይዘውት ፡ ሲወጡ ፡ በምር ፡
ከፍ ፡ ሲል ፡ አይቶ ፡ ቢያማትብባቸው ፡
አጋንንት ፡ ጥለውት ፡ ሸሹ ፡ ወርዶ ፡ ተን
ቈጫቍጮ ፡ ሙቷል ።

፱ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ ተንሥኡ ፡ እምኵራብ ፡ እንተ ፡
ስማ ፡ ሊብርጢኖን ፡ ወቀሬኔዎን ፡ ወእለስክንድሬዎ
ን ፡ ወእለሂ ፡ እምቂልቅያ ፡ ወእስያ ።

አይሁድ ፡ ለምቀኝነት ፡ አያርፉምና ፡
ሊብርጢኖን ፡ ቀሬኔዎን ፡ እስክንድሬዎን፡
ቂልቅያ ፡ እስያ ፡ ከሚባሉ ፡ ምኵራብ ፡
ተወጣጥተው ።

፲ ፤ ወተኃሠሥዎ ፡ ለእስጢፋኖስ ፡

ተስፋ ፡ ያልደረሰውን ፡ ተስፋ ፡ ደረሰ ፡
ሥጋ ፡ ያለበሰውን ፡ ሥጋ ፡ ለበሰ ፡ እያለ፡
ያስተምራል ፡ ብለው ፡ እስጢፋኖስን ፡
ተከራከሩት ።

ወስእኑ ፡ ተቃውሞቶ ፡

መርታት ፡ ተሳናቸው ፡

እስመ ፡ በጥበብ ፡ ወበመንፈስ ፡ ይትናገሮሙ ፡

አእምሮ ፡ ጠባይ ፡ ቀንቶለት ፡ ጥበብ ፡
መንፈሳዊ ፡ ተሰጥቶት ፡ ይከራከራቸው ፡
ነበርና ፡ ዛሬም ፡ ሰው ፡ አእምሮ ፡ ጠባይ ፡
ካልቀናለት ፡ ጥበብ ፡ መንፈሳዊ ፡ ካልተሰ
ጠው ፡ ተከራክሮ ፡ መርታት ፡ አይቻለ
ውም ፡ እሱ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጸንቶ ፡
ሱባኤ ፡ ትውልድ ፡ የሄኖክን ፡ ሱባኤ ፡
ሰንበት ፡ የዳንኤልን ፡ ሱባኤ ፡ ዕለት ፡

www.ethiopianorthodox.org

የኤርምያስን ፡ ቆጥሮ ፡ አስማምቶ ፡ ቢነ
ግራቸው ፡ ይህንስ ፡ ባፍና፡ በመጣፍ፡ የሚ
ችል ፡ የለም ፡ ብለው ፡ ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፲፫ ፡

፲፩ ፤ ወእምዝ፡አቅፀሩ፡ሎቱ፡ዕደወ፡ሰማዕተ፡ ሐሰት ፣

የሐሰት ፡ መሳክርት ፡ ዋጁበት ፡

ወመሀርዎሙ ፣ ከመ ፣ ይበሉ ፣ ሰማዕናሁ ፡ ለዝ ፡ ብ
እሲ ፣ እንዘ ፣ ይነብብ ፣ ነገረ ፣ ፅርፈት ፣ ላዕለ ፡ ሙሴ ፣
ወላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ ሲሰድብ ፡ ሙሴን ፡
ሲያዋርድ ፡ ሰማነው ፡ ብላችሁ ፡ መስ
ክሩ ፡ ብለው ፡ መከሯቸው፡ማቴ ፡ ፳፮፡ ፷ ።

፲፪ ፤ ወሆክዎሙ ፣ ለሕዝብ ፣ ረበናት ፣ ወጸሐፍት ፣

ሕዝቡንም ፡ ረበናት ፡ ጸሐፍት ፡ አነሳሷ
ቸው ።

ወሮድዎ ፣ ወሰሐብዎ ፡

ከበው ፡ እየጐተቱ ፡

ወተባጽሕዎ ፣ ኀበ ፣ ዐውድ ፣

ወደ ፡ አደባባይ ፡ አደሱረት ፡

፲፫ ፤ ወዓቀሙ ፣ ሎቱ ፣ ሰማዕተ ፣ ሐሰት ፣

እሊያን ፡ የሐሰት ፡ መሳክርት ፡ አስነሡ
በት ፡ እሊያም ፡ ውጆች ፡ ናቸውና ፡ ሳይ
ጠሯቸው ። አንድም ፡ ጠርተዋቸው ፡

ወይቤሉ ፣ ዝ ፡ ብእሲ ፣ አበየ ፣ ያርምም ፣

ይህ ፡ ሰው ፡ ዝም ፡ አልልም ፡ አለን ፡

እንዘ ፣ ይነብብ ፣ ጽርፈተ ፣ ዲበ ፣ ቤተ ፡ መቅደስ ፣
ወዲበ ፡ኦሪት ፣

ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ትፈርሳለች ፡ ኦሪት ፡
ትጠፋለች ፡ እያለ ፡ ያስተምራል ፡ ዝም፡
አልልም ፡ አለን ፡ ኤር ፡ ፳፮ ፡ ፲፩ ።

፲፬ ፤ ወሰማዕናሁ ፣ እንዘ ፣ ይብል ፡ ኢየሱስ ፣ ናዝ
ራዊ ፣ ይነሥቶ ፣ ለቤተ ፣ መቅደስ ፣ ወይሠዐር ፣
ኦሪተከሙ ፣ ዘወሀበከሙ ፣ ሙሴ ፣

የናዝሬቱ ፡ ሰው ፡ ኢየሱስ ፡ ቤተ ፡ መቅ
ደስን ፡ ያፈርሳል ፡ ሙሴ ፡ የሠራላችሁን ፡
ኦሪትን ፡ ያሳልፋል ፡ እያለ ፡ ሲያስተምር ፡
እንሰማዋለን ፡ ዝም ፡ አልልም ፡ አለን ፡
ብለው ፡ መሰከሩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይሰ
ድባል ፡ ማለታቸው ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ ባዮች፡
ነበሩና ፡ በአካል ፡ ሦስት ፡ በባሕርይ ፡
በሕልውና ፡ አንድ ፡ ቢልባቸው ፡ ነው ፡
ሙሴን ፡ ያዋርዳል ፡ ማለታቸው ፡ እስካ
ሁን ፡ ምግበ ፡ ሙሴ ፡ ነበር ፡ አለፈ ፡ እን
ግዲህ ፡ ግን ፡ ምግበ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡
ቢላቸው ፡ ነው ፡ ኦሪት ፡ ትጠፋለች ፡ ይ
ላል ፡ ማለታቸው ፡ እስካሁን ፡ ምግበ ፡
ኦሪት ፡ ነበረ ፡ አለፈ ፡ እንግዲህ ፡ ግን ፡
ምግበ ፡ ወንጌል ፡ ነው ፡ ቢላቸው ፡ ነው ፡
ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ትፈርሳለች ፡ ይላል ፡
ማለታቸው ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ይሏች
ኋል ፡ ይህ ፡ ዕንጨት ፡ ደንጊያው ፡ ይመ
ስላችኋል ፡ አርአያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው
ነታችሁ ፡ እንጅ ፡ ነው ፡ ቢላቸው ፡ ነው ።

፲፭ ፤ ወነጸርዎ ፣ ኵሎሙ ፡ እለ ፣ ይነብሩ ፡ ዐውደ ፣

የተመሰከረበትን ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይመልስ፡
ይሆን ፡ ብሎ ፡ አቅንቶ ፡ ማየት ፡ ልማድ ፡
ነውና፡ ባደባባይ፡ የተቀመጡት፡ሁሉ፡ዐይ
ናቸውን፡አቅንተው፡ በተመለከቱት፡ጊዜ ።

ወርእዩ ፡ ገጾ ፣ ከመ ፡ ገጸ፡ መልአከ ፣ እግዚአብሔር ፣

ፊቱ ፡ ብሩህ ፡ ሁኖ ፡ አዩት ፡ እንደ ፡ መል
አክ ፡ ገጹ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡
እንደ ፡ ሙሴ ፡ ይኸውም ፡ ዕሤተ ፡ ገድሉ፡
ነው ፡ ከዚህ ፡ አያይዘው ፡ ሐዋርያት ፡ ሥ
ርዐት ፡ ሠርተዋል ፡ ሃይማኖቱን ፡ በዐላ
ውያን ፡ መኳንንት ፡ በዐላውያን ፡ ነገሥ
ታት ፡ ፊት ፡ ሳያፍር ፡ ደፍሮ ፡ የመሰከረ ፡
ሕዝባዊ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ እንበለ ፡ አንብ
ሮተ ፡ እድ ፡ በዲቁና ፡ ዲያቆን ፡ ነው ፡
ቢሉ ፡ በቅስና ፡ ገብቶ ፡ ያገልግል ፡ ከዚያ፡
በላይ ፡ ግን ፡ ለሌላ ፡ የሚተርፍ ፡ ነውና ፡
አይሆንም ፡ ብለዋል ።



ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩ ፤ ወይቤሎ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡አማንኑ፡ከመ፡ዝ፡ትቤ ፡

አለቃውም ፡ አለቃ ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡
ጠበቃ ፡ ያለ ፡ ነውና ፡ እውነት ፡ እንዲህ ፡
ትላለህን ፡ አለው ፡

፪ ፤ ወይቤ ፡ ስምዑ ፡ አኀዊነ ፣ ወአበዊነ ፣

ወይቤሎ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አማንኑ ፡ ከመ
ዝ ፡ ትቤ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ወይቤ ፡ ስምዑ፡
አበዊነ ፡ ወአኀዊነ ፡ አለ ፡ አባቶቻችን ፡
ወንድሞቻችን ፡ ስሙ ።

አምላከ ፣ ስብሐት ፣ አስተርአዮ ፣ ለአቡነ ፣ አብር
ሃም ፡

የክብር ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ ላባ
ታችን ፡ ለአብርሃም ፡ ታየው ፡ ተነጋገ
ረው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይሰድባል ፡ ብለ
ውታልና ፡ የክብር፡ ባለቤት ፡ ብለው ፡
እንጅ ፡ እንደምን ፡ እሰድበዋለሁ ፡
ለማለት ፡ አብርሃምንም ፡ አነሣ ፡ በዚያ
ውስ ፡ ላይ ፡ የማን ፡ ልጅ ፡ ሁኜ ፡ የጥንተ ፡
ተገዢ ፡ የመምለኬ ፡ እግዚአብሔር ፡
የአብርሃም፡ልጅ፡አይደለሁምን፡ ለማለት ፡

እንዘ ፣ ሀሎ ፣ በማዕከለ ፣ አፍላግ ፣ ዘሶርያ ፣ ዘእንበለ ፣
ይፍልስ ፣ ካራን ፣

በሶርያ ፡ ወንዞች ፡ በኤፍራጥስና ፡ በጤ
ግሮስ ፡ መካከል ፡ በከላውዴዎን ፡ ሳለ ፡
ወደ፡ ካራን፡ ሳይወጣ፡ ታየው፡ ተነጋገረው፡
ኤፍራጥስና ፡ ጤግሮስ ፡ የባቢሎን ፡ አይ
ደሉም ፡ ስለምን ፡ አፍላግ ፡ ዘሶርያ ፡ አለ፡
ቢሉ ፡ ተያይዘው ፡ ሶርያ ፡ የሚደርሱ ፡
ስለ፡ ሆነ ፡ በሽሎ፡ ባማራ፡ በኩል፡ ወርዶ
ካባይ፡ ተገናኝቶ፡ ዐባይ፡ እንዲባል። አንድ
ም፡በባቢሎንና፡በፋርስ፡መካከል፡ በካራን፡
ሳለ ፡ ወዘእንበለ ፡ ይፍልስ ፡ ካራን ፡ ወደ ፡
[illegible] ፡ በከላውዴዎን ፡ ሳለ ፡
ታየው ፡ ተነጋገረው ፡ እንዲህ ፡ ግን ፡ ስለ ፡
ሆነ ፡ ካራን ፡ የተባለች ፡ ሶርያ ፡ ከላውዴ
ዎን ፡ የተባለች ፡ ባቢሎን ፡ ናት ፡ በመስ
ጴጦምያ ፡ ዘሶርያ ፡ ይላል ፡ አብነት ፡ ማዕ
ከለ ፡ ክልኤቱ ፡ አፍላግ ፡ ማለት ፡ ነው ።
ሙሴ ፡ ከኮሬብ ፡ እስከ ፡ ቃዴስ ፡ በርኔ ፡
ለአበው ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡ ያስተማራቸ
ውን ፡ ለውሉድ ፡ ዐሥር ፡ ጉባኤ ፡ አድ
ርጎ ፡ አስተምሯቸዋል ፡ ለውሉድ ፡ ዐሥ
ር ፡ ጉባኤ ፡ አድርጎ ፡ ያስተማራቸውንም ፡
እስጢፋኖስ ፡ ለአይሁድ ፡ ሦስት ፡ ጉባኤ ፡
አድርጎ ፡ አስተምሯቸዋል ፤ ዘፍጥ ፡ ፲፩ ፡
፴፩ ። ፲፭ ፡ ፯ ።

፫ ፤ ወይቤሎ ፡ ፃእ ፣ እምብሔርከ ፣

ከሀገርህ ፡ ውጣ ፡

ወተፈለጥ ፡ እምአዝማዲከ ፣

ከዘመዶችህ ፡ ተለይ ፡

ወነዓ ፡ ውስተ ፡ ብሔር ፡ ዘአነ ፣ አርእየከ ፣

እኔ ፡ ወደማወርስህ ፡ ሀገር ፡ ና ፡ ብሎ ፡
ለአባታችን ፡ ለአብርሃም ፡ ታየው ፡ ተነ
ጋገረው ፡ ዘፍ ፡ ፲፪ ፡ ፩ ፡

፬ ፤ ወእምዝ ፣ ወፂአ ፣ እምከላውዴዎን ፣ ነበረ ፣
ውስተ ፣ ካራን ፣

ከከላውዴዎን ፡ ወጥቶ ፡ በካራን ፡ ሁለት ፡
ሱባኤ ፡ ዘመን ፡ ኖረ ፡

ወእምዝ ፣ መዊቶ ፣ አቡሁ ፣ አፍለሶ ፣ ውስተ ፣ ዛ ፡ ም
ድር፣ ኀበ ፣ ሀለውከሙ ፣ አንትሙ፣ ይእዜ ፣ ትነብሩ፣

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባቱ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ዛሬ፡
እናንት ፡ ወርሳችኋት ፡ ወዳላችሁባት ፡
አገር ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ አወጣው ፤

፭ ፤ ወኢወሀቦ ፣ በውስቴታ ፣ ርስቶ ፣

ርስቱን ፡ አልሰጠውም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኢመጠነ ፡ ምክያደ ፡ እግር ፡
ጫማ ፡ ሙሉ ፡ ስንኳ ፡
ወኢምሥጋረ ፡ እግር ፡
አንድ ፡ እርምጃም ፡ አልሰጠውም ፡

ወባሕቱ ፡ አሰፈዎ ፡ ይኲንና ፡ ውእቱ ፡ ወዘርዑ ፡ እም
ድኅሬሁ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ውሉድ ፡ ይእተ ፡ አሚረ ፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ ልጅ ፡ ሳይኖረው ፡ እሱ ፡ ከሱም ፡
በኋላ ፡ ልጆቹ ፡ ይወርሷት ፡ ዘንድ ፡ ተስ
ፋውን ፡ ነገረው ፡ እንጅ ፡ ለከ ፡ ወለዘር
ዕከ ፡ እሁበከሃ ፡ ለዛቲ ፡ ሀገር ፡ እስከ ፡
ዕፅ ፡ ነዋህ ፡ ብሎ ፡ ዘፍጥ ፡ ፲፪ ፡ ፯ ።

፮ ፤ ወከመ ፡ ዝ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሀለዉ ፡
ደቂቅከ ፡ ይነብሩ ፡ ፈላስያነ ፡ ብሔረ ፡ ነኪር ፡
ልጆችህ ፡ በባዕድ ፡ ሀገር ፡ በግብፅ ፡ መጻ
ተኞች ፡ ስደተኞች ፡ ሁነው ፡ ይኖራሉ ፡

ወይቀንይዎሙ ፡ ግብፅ ፡ ወያሐምምዎሙ ፡ አርባዕተ ፡
ምእተ ፡ ዓመተ ፡
አራት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ መከራ ፡ እያጸኑባ
ቸው ፡ ግብጻውያን ፡ ይገዟቸዋል ፤ ዘፍጥ ፡
፲፭ ፡ ፲፫ ። ዘፀ ፡ ፲፪ ፡ ፵ ።

፯ ፤ ወለሕዝብሰ ፡ እለ ፡ ይቀንይዎሙ ፡ አነ ፡ እኴን
ኖሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡
አገዛዝ ፡ የሚያጸኑባቸው ፡ አሕዛብንም ፡
እኔ ፡ ፈርጄ ፡ አጠፋቸዋለሁ ፡ አለ ፡ እግ
ዚአብሔር ።

ወእምዝ ፡ ይወፅኡ ፡ ዝየ ፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከግብፅ ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡
ይወጣሉ ፡

ወያመልኩኒ ፡ በዝ ፡ ብሔር ፡
በከነዓን ፡ ያመልኩኛል ፡ ብሎ ፡ ተስፋ
ውን ፡ ነገረው ፡ እንጅ ። ታራ ፡ አብርሃ
ምን ፡ በመቶ ፡ ዘመን ፡ ወልዶታል ፡ ስሳ ፡
አንድ ፡ ዓመት ፡ አብረው ፡ ይኖራሉ ፡ ከዚህ ፡ በ
ኋላ ፡ ፃእ ፡ እምብሔርከ ፡ ወተፈለጥ ፡ እም
አዝማዲከ ፡ ብሎ ፡ ከከላውዴዎን ፡ ወደ ፡
ካራን ፡ ያወጣዋል ፡ በካራን ፡ ሁለት ፡
ሱባኤ ፡ ዘመን ፡ ይኖራል ፡ ፃእ ፡ እምብሔ
ርከ ፡ ወተፈለጥ ፡ እምአዝማዲከ ፡ ወነዓ ፡
ውስተ ፡ ብሔር ፡ ዘአነ ፡ አርእየከ ፡ ብሎ ፡
ከካራን ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ ያወጣዋል ፡ የከነ
ዓንን ፡ ምሥራቋን ፡ ምዕራቧን ፡ ሰሜኗን ፡
ደቡቧን ፡ በዓይነ ፡ ሥጋ ፡ አሳይቶ ፡ በእ
ግረ ፡ ሥጋ ፡ አስረገጠው ፡ ይህስ ፡ ለሁሉ ፡
አይቻልም ፡ ብሎ ፡ በዓይነ ፡ ሕሊና ፡ አሳ
ይቶ ፡ በእግረ ፡ ሕሊና ፡ አስረግጦ ፡ ለከ ፡
ወለዘርዕከ ፡ እሁበከሃ ፡ ለዛቲ ፡ ሀገር ፡
እስከ ፡ ዕፅ ፡ ነዋኅ ፡ ብሎ ፡ ተስፋውን ፡
ነግሮታል ፡ በከነዓን ፡ ሠላሳ ፡ ዘመን ፡
ይኖራል ፡ አባትህ ፡ ሞተ ፡ ይሉታል ፡
ተመልሶ ፡ አባቱን ፡ ቀብሮ ፡ ይወጣል ፡
አብርሃምስ ፡ የመናንያን ፡ አምሳል ፡ ነው ፡
ከወጣ ፡ በኋላ ፡ አይመለስም ፡ ብሎ ፡ ታራ ፡
አብርሃምን ፡ በመቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዘመን ፡
ወልዶታል ፡ ስሳ ፡ አንድ ፡ ዘመን ፡ አብ
ረው ፡ ይኖራሉ ፡ ፃእ ፡ እምብሔርከ ፡ ወተ
ፈለጥ ፡ እምአዝማዲከ ፡ ብሎ ፡ ከከላው
ዴዎን ፡ ወደ ፡ ካራን ፡ ያወጣዋል ፡ በካ
ራን ፡ ሁለት ፡ ሱባኤ ፡ ዘመን ፡ ይኖራል ፡
አባቱ ፡ ይሞታል ፡ አባቱን ፡ ቀብሮ ፡ ፃእ ፡
እምብሔርከ ፡ ወተፈለጥ ፡ እምአዝማ
ዲከ ፡ ብሎ ፡ ከካራን ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡
ያወጣዋል ፡ የከነዓንን ፡ ምሥራቋን ፡ ምዕ
ራቧን ፡ ሰሜኗን ፡ ደቡቧን ፡ በዓይነ ፡
ሥጋ ፡ አሳይቶ ፡ በእግረ ፡ ሥጋ ፡ አስረ
ገጠው ፡ ይህስ ፡ ለሁሉም ፡ አይቻልም ፡
ብሎ ፡ በዓይነ ፡ ሕሊና ፡ አሳይቶ ፡ በእ
ግረ ፡ ሕሊና ፡ አስረግጦ ፡ ለከ ፡ ወለዘር
ዕከ ፡ እሁበከሃ ፡ ለዛቲ ፡ ሀገር ፡ እስከ ፡
ዕፅ ፡ ነዋኅ ፡ ብሎ ፡ ተስፋውን ፡ ነግሮታል ፡
አብርሃምም ፡



አምስት ፡ ይስሐቅን ፡ ወልዷል ፡ ይስ
ሐቅ ፡ በተወለደ ፡ በስሳ ፡ ያዕቆብን ፡ ወል
ዷል ፡ ያዕቆብ ፡ በተወለደ ፡ በመቶ ፡
ሠላሳ ፡ ርደተ ፡ ግብፅ ፡ ሆኗል ፡ ይኸውም ፡
በፈርያን ፡ አጠያየቅ ፡ ታውቋል ፡ እስፍ
ንቱ ፡ መዋዕሊከ ፡ አ ፡ አረጋዊ ፡ ዘሐዮከ ፡
በዲበ ፡ ምድር ፡ ቢለው ፡ መዋዕልየሰ ፡
ምእት ፡ ወሠላሳ ፡ ወኅዳጣን ፡ እማ
ንቱ ፡ በኀበ ፡ መዋዕለ ፡ አበውየ ፡ ወባ
ሕቱ ፡ እኩያተ ፡ ኮናኒ ፡ ወኀልቃ ፡ በእን
ባዜ ፡ ብሎታል ፡ ይህንም ፡ ገብተው ፡
ይቆጥሩታል ፡ ያዕቆብ ፡ በተወለደ ፡ በሰ
ማንያ ፡ ሦስት ፡ ሌዊን ፡ ይወልዳል ፡ ሌዊ ፡
በተወለደ ፡ ባርባ ፡ አራት ፡ ቀዓትን ፡ ይወ
ልዳል ፡ ቀዓት ፡ በተወለደ ፡ በሦስት ፡
ርደተ ፡ ግብፅ ፡ ሆኗል ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡
አስራ ፡ አምስት ፡ ይሆናል ፡ ርደተ ፡
ግብፅ ፡ በሆነ ፡ በስድሳ ፡ አምስት ፡ ቀዓት ፡
እንበረምን ፡ ይወልዳል ፡ እንበረም ፡ በተወለ
ደ ፡ በሰባ ፡ ሙሴን ፡ ይወልዳል ፡ ሙሴ ፡ በተ
ወለደ ፡ በሰማንያ ፡ እስራኤል ፡ ከግብፅ ፡
ወጥተዋል ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ አምስ
ት ፡ ይሆናል ፡ ሁለተኛም ፡ ከወንድሙ ፡
ከሎጥ ፡ በተለየ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ከናት ፡
ካባት ፡ መለየት ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ካንድ ፡
ወንድም ፡ መለየት ፡ ብሎ ፡ አዝኗል ፡ አይ
ዞህ ፡ አትዘን ፡ ደቂቅከ ፡ ይነብሩ ፡ ፈላስ
ያነ ፡ ብሔረ ፡ ነኪር ፡ ወይቀንይዎሙ ፡
ግብፅ ፡ ወየሐምምዎሙ ፡ አርባዕተ ፡ ምዕ
ተ ፡ ዓመተ ፡ ወለሕዝብሰ ፡ እለ ፡ ይቀንይ
ዎሙ ፡ አነ ፡ እኴንኖሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ወእምዝ ፡ ይወጽኡ ፡ ዝየ ፡ ወያ
መልኩኒ ፡ በዝ ፡ ብሔር ፡ ብሎታል ፡
ይህስ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከለያ
ልይ ፡ ባንድ ፡ ሌሊት ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡
አውጥቶ ፡ ኖልቍ ፡ ከዋክብተ ፡ ሰማይ ፡
ጐልቆቶሙ ፡ ቢለው ፡
ከማሁ ፡ ይከውኑ ፡ ዘርዕከ ፡ ብሎታል ፡ ከዕ
ለታት ፡ ባንድ ፡ ዕለት ፡ ከከንፈረ ፡ ባሕር ፡
አውርዶ ፡ ኈልቍ ፡ ኖፃ ፡ ባሕር ፡ ብሎ
ታል ፡ ኢይክል ፡ ኈልቆቶሙ ፡ ቢለው ፡
ከማሁ ፡ ይከውኑ ፡ ዘርዕከ ፡ ብሎታል ፡
ኃጥአን ፡ ልጆቹን ፡ በኖፃ ፡ መስሎ ፡ ተና
ገረ ፡ ኖፃ ፡ ቈሪር ፡ ነው ፡ ቈሪራን ፡ አእ
ምሮ ፡ ናቸውና ፡ ኖፃ ፡ ይቡስ ፡ ነው ፡ ይቡ
ሳን ፡ አእምሮ ፡ ናቸውና ፡ ኖፃ ፡ ክቡድ ፡
ነው ፡ ክቡዳነ ፡ አእምሮ ፡ ናቸውና ።
ኖፃ ፡ ምድራዊ ፡ ነው ፡ ምድራዊ ፡ ሥራ ፡
ይሠራሉና ፡ ጻድቃን ፡ ልጆቹን ፡ በኮከብ ፡
መስሎ ፡ ተናገረ ፡ ኮከብ ፡ ብሩህ ፡ ነው ፡
ብሩሃን ፡ አእምሮ ፡ ናቸውና ፡ ኮከብ ፡ ሰማ
ያዊ ፡ ነው ፡ ሰማያዊ ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉና ፡
ኮከብ ፡ በብርሃን ፡ ይበላለጣል ፡ (ጥቅ) ፡ ኮከብ ፡
እምኮከብ ፡ ይኄይስ ፡ ክብሩ ፡ እንዲል ።
ጻድቃንም ፡ በክብር ፡ ይበላለጣሉና ። በባ
ሕርይ ፡ ብቻ ፡ የሚወልዳቸው ፡ ልጆቹን ፡
በኖፃ ፡ መስሎ ፡ በባሕርይም ፡ በግብርም ፡
የሚወልዳቸውን ፡ በኮከብ ፡ መስሎ ፡ ተና
ገረ ። ሦስተኛም ፡ አብርሃም ፡ ላምስቱ ፡
ነገሥተ ፡ ሰዶም ፡ ረድቶ ፡ አራቱን ፡ ነገ
ሥተ ፡ ኮሎዶጎሞር ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ በተ
መለሰ ፡ ጊዜ ፡ ብዙኅ ፡ ዓስብከ ፡ ብሎታል ፡
ምንት ፡ ይከውነኒ ፡ ወናሁ ፡ ዘቀደመ ፡
ንዋይየ ፡ ይወርሰኒ ፡ ኢያቡር ፡ ወልደ ፡
ዘመድየ ፡ አለው ፡ አኮ ፡ ዘይወርሰከ ፡ ኢያ
ቡር ፡ ወልደ ፡ ዘመድከ ፡ አላ ፡ ወልድከ ፡
ዘይወፅእ ፡ እምሐቌከ ፡ ውእቱ ፡ ይወር
ሰከ ፡ ብሎታል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለከ ፡ ወለ
ዘርዕከ ፡ እሁበከሃ ፡ ለዛቲ ፡ ሀገር ፡ እስከ ፡
ዕፅ ፡ ነዋህ ፡ ቢለው ፡ በምንት ፡ አእምር ፡
ከመ ፡ አነ ፡ እትዋረሳ ፡ ብሎት ፡ ነበርና ፡
ንሣእ ፡ ላሕመ ፡ ዘሠለስቱ ፡ ዓመቱ ፡ ሦስ
ት ፡ ዓመት ፡ የሆነው ፡ ላም ፡ ሦስት ፡ ዓመ

www.ethiopianorthodox.org

ት ፡ የሆነው ፡ ፍየል ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ የሆነው ፡ በግ ፡ ይዘህ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ውጣ ፡ ዋኖስ ፡ ርግብንም ፡ አትተዋቸው ፡ አንብር ፡ ዘተመትረ ፡ በአንጻረ ፡ ቢጹ ፡ እየለየህ ፡ በየወገን ፡ በየወገኑ ፡ አኑር ፡ ዋኖስ ፡ ርግብን ፡ ግን ፡ አትለያቸው ፡ ከርክረህ ፡ ተዋቸው ፡ ብሎታል ፡ ወለአእዋፍሰ፡ ኢነተፎን ፡ እንዲል ። ይህን ፡ ሲያዘጋጅ ፡ ወኮነ ፡ ምሴተ ፡ ወመጽአ ፡ ግሩም ፡ ጽልመት ፡ ይላል ። በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ጨለማ ፡ ሆነ ፡ ወመጽአ ፡ ለአብራም ፡ ድንጋጼ ፡ ይላል ፡ ተደሞ ፡ መጣበት ፡ እሳት ፡ በምድጃ ፡ ሁኖ ፡ በመካከል ፡ ሲመላለስ ፡ ሥጋው ፡ እሳቱን ፡ ሳያጠፋው ፡ እሳቱ ፡ ሥጋውን ፡ ሳያቃጥለው ፡ አእዋፍ ፡ ሥጋውን ፡ እንበላለን ፡ ብለው ፡ ሲመጡ ፡ በዘንግ ፡ ሲከለክላቸው ፡ አይቷል ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡ ሦስቱ ፡ ላም ፡ ፍየል ፡ በግ ፡ የሦስቱ ፡ ትውልድ ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ። አንድም ፡ የሦስቱ ፡ ፈርያኖች ፡ እየለየህ ፡ አለ ፡ ክፍለ ፡ ዘመንን ፡ ሲነግረው ፡ ነው ፡ ሁለት ፡ መቶ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዘመን ፡ በከነዓን ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ዘመን ፡ በግብፅ ፡ የሚኖሩትን ፡ ሲነግረው ፡ ነው ፡ በየወገን ፡ በየወገኑ ፡ አለ ፡ መከራውን ፡ እንደ ፡ ኋላው ፡ በፋርስ ፡ በባቢሎን ፡ በጽርዕ ፡ በሜዶን ፡ ተለያይተው ፡ እንደ ፡ ተቀበሉት ፡ ተለያይተው ፡ አይቀበሉትምና ፡ ምሴት ፡ የፍጻሜ ፡ ዘመን፡ ጨለማ፡ እሳት፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የመከራ ፡ እንቅልፍ ፡ የሞተ ፡ አብርሃም ፡ ሥጋው ፡ የእስራኤል ፡ ሥጋው ፡ እሳቱን ፡ አለማጥፋት ፡ እስራኤል ፡ መከራውን ፡ ግብር ፡ ገብተን ፡ ቀኖና ፡ ይዘን ፡ እናርቀው ፡ አላሉምና ፡ እሳቱ ፡ ሥጋውን ፡ አለማቃጠሉ ፡ መከራው ፡ እስራኤልን ፡ ፈጽሞ ፡ አያጠፋቸውምና ፡ አእዋፍ ፡ ሥጋውን ፡ እንበላለን ፡ ብለው ፡ ሲመጡ ፡ በዘንግ ፡ ሲከለክላቸው ፡ ማየቱ፡ አሕዛብ ፡ እናጠፋቸዋለን ፡ ሲሉ ፡ እስራኤል ፡ በኪዳነ ፡ አብርሃም ፡ በኪዳነ ፡ ይስሐቅ ፡ በኪዳነ ፡ ያዕቆብ ፡ ተጠብቀው ፡ ለመኖራቸው ፡ ምሳሌ ፡ ላም ፡ ከሁሉ ፡ ይበረታል ፡ በመገርመሪያው ፡ ፈርያን ፡ በርትተው ፡ ተገዝተዋል ፡ ፍየል ፡ ከላም ፡ ይደክማል ፡ ከበግ ፡ ይበረታል ፡ በሁለተኛው ፡ ፈርያን ፡ ከጉልበት ፡ ተገዝተዋል ፡ በግ ፡ ከሁሉም ፡ ይደክማል ፡ በሦስተኛው ፈርያን ፡ ደክመው ፡ ተገዝተዋል ። አንድም ፡ በግ ፡ ከሁሉ ፡ ይደክማል ፡ በመገርመሪያው ፡ ፈርያን ፡ ደክመው ፡ ተገዝተዋል ፡ ፍየል ፡ ከላም ፡ ይደክማል ፡ ከበግ ፡ ይበረታል ፡ በሁለተኛው ፡ ፈርያን ፡ ከጉልበት ፡ ተገዝተዋል ፡ ላም ፡ ከሁሉ ፡ ይበረታል ፡ በሦስተኛው ፡ ፈርያን ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ ወጥተዋል ፡ ዋኖስ ፡ ርግብ ፡ የሙሴ ፡ የአሮን ፡ ዋኖስ ፡ በበረሃ ፡ መኖርን ፡ እንድትወድ ፡ ሙሴ ፡ ከዘመዶቹ ፡ ተለይቶ ፡ በምድያም ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡ ኑሯል ፡ ርግብ ፡ በግምብ ፡ መኖርን ፡ እንድትወድ ፡ አሮን ፡ ከዘመዶቹ ፡ ሳይለይ ፡ ኑሯል ፡ ከርክረህ ፡ ተዋቸው ፡ አትለያቸው ፡ ማለቱ ፡ መከራውን ፡ ይቀበላሉ ፡ ከቀቢጸ፡ ተስፋ ፡ አይደርሱምና ። አንድም ፡ ዋኖስ፡ ርግብ ፡ የእስራኤል ፡ ዋኖስ ፡ በበረሃ ፡ መኖርን ፡ እንድትወድ ፡ እስራኤል ፡ ዓርባ ፡ ዘመን ፡ በበረሃ ፡ ኑረዋል ፡ ርግብ ፡ በግምብ ፡ መኖርን ፡ እንድትወድ ፡ ምድረ ፡ ርስት ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ሠርተዋል ። አንድም ፡ ሦስት ፡ ላም ፡ ሦስት ፡ ፍየል ፡ ሦስት ፡ በግ ፡ ይዘህ ፡ ወደ ፡ [illegible]

ብንም ፡ አትተዋቸው ፡ አንብር ፡ ዘተመትረ ፡ በአንጻረ ፡ ቢጹ ፡ በየወገን ፡ በየወገኑ ፡ አድርገው ፡ ዋኖስ ፡ ርግብንም ፡ አትለያቸው ፡ ከርክረህ ፡ ተዋቸው፡ ብሎታል፤ ምሳሌ ፡ ነው ፡ አልሕምት ፡ የሐዋርያት ፡ አጣሊ ፡ የሰማዕታት ፡ አባግዕ ፡ የምእመናን ። አንድም ፡ አልሕምት ፡ አይለወጥም ፡ አባግዕ ፡ የሰማዕታት ፡ አጣሊ ፡ የምእመናን ፡ ዋኖስ ፡ ርግብ ፡ የዮሐንስ ፡ መጥምቅና ፡ የመቤታችን ፡ ዋኖስ ፡ በበረሃ ፡ መኖርን ፡ እንድትወድ ፡ ዮሐንስ ፡ በገዳም ፡ ኑሯል ፡ ርግብ ፡ በግምብ ፡ መኖርን ፡ እንድትወድ ፡ እመቤታችን ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ኑራለች ፡ ከርክረህ ፡ ተዋቸው ፡ አትለያቸው ፡ ማለቱ ፡ መከራውን ፡ ይቀበላሉ ፡ ከቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ አይደርሱምና ። አንድም ፡ ዋኖስ ፡ ርግብ ፡ የመቤታችንና ፡ የዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ምሳሌ ፡ ከርክረህ ፡ ተዋቸው ፡ አትለያቸው ፡ ማለት ፡ ከእግረ ፡ መስቀል ፡ አልተለዩምና ፡ ሁለት ፡ ሁለቱ ፡ አስራ ፡ ስምንት፡ ይሆናል፡ ዋኖስ፡ ርግብን ፡ ቢጨምሩ ፡ ኻያ ፡ ይሆናል ፡ አብርሃም ፡ ተስፋውን ፡ በሰማ ፡ በሁለት ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ጌታ ፡ ከቤተ ፡ አብርሃም ፡ መወለዱን ፡ ያጠይቃል ፡ ከነዓን ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ አብርሃም ፡ በአንቀጸ ፡ ከነዓን ፡ በካራን ፡ ሁለት ፡ ሱባኤ ፡ ዘመን ፡ ኑሮ ፡ ከነዓን ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ አዳም ፡ በአንቀጸ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ በገነት ፡ ሁለት ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ኑሮ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ እንዲገባ ፡ ያጠይቃል ።

፰፤ ወወሀቦ ፡ ሥርዐተ ፡ ግዝረት ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግዝረትን ፡ ሰጠው ፡ አለ ፡ ተገዝር ፡ አለው ፡ በነፍስ ፡ እንዳከበረው ፡ ለማጠየቅ ። አንድም ፡ ከአሕዛብ ፡ መለያ፡ [illegible] ፡ በመገዘር ፡ የፈቲው ፡ ጸር ፡ ይቀላልና ፡ (ጥቅ) ፡ እስመ ፡ በተገዝሮ ፡ ይደክም ፡ ዋዕየ ፡ ፍትወት ፡ እንዲል ።

ወእምዝ ፡ ወለዶ ፡ ለይስሐቅ ፡ ወገዘሮ ፡ አመ ፡ ሳምንት ፡ ዕለት ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይስሐቅን ፡ ወለደው ፡ በስምንተኛው ፡ ቀን ፡ ገዘረው ። አማሐይ ፡ ቀን ፡ ሽቶ ፡ ወደ ፡ ሰባት ፡ ወደ ፡ ስድስት ፡ ዝቅ ፡ ቢል ፡ በላላ ፡ ነበር ፡ ወደ ፡ ዘጠኝ ፡ ወደ ፡ ዐሥር ፡ ከፍ ፡ ቢል ፡ በጠነከረ ፡ ነበርና ፡ አማሐይ ፡ ቀን ፡ ሽቶ ፡ ምስጢሩ ፡ ግን ፡ የስምንቱ ፡ ብሔረ ፡ አሪት ፡ ምግብና ፡ ሲፈጸም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ግዝረተ ፡ ነፍስ ፡ የስምንቱ ፡ ሽሕ ፡ ዘመን ፡ ምግብና ፡ ሲፈጸም ፡ ግዝረተ ፡ ሥጋ ፡ እንዲገዘር ፡ ያጠይቃል ።

ወከማሁ ፡ ይስሐቅኒ ፡ ለያዕቆብ ፡

ይስሐቅም ፡ ያዕቆብን ፡ ወለደው ፡ ገዘረው ።

ወያዕቆብኒ ፡ ለዐሥርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ አበው ፡ ቀደምት ፡

ያዕቆብም ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱን ፡ አለቆች ፡ ወለደ ፡ ገዘረ ፤ ዘፍጥ ፡ ፲፯ ፡ ፲ ። ዘፍጥ ፡ ፳፩ ፡ ፪ ። ዘፍጥ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮ ። ዘፍጥ ፡ ፳፱ ፡ ፴፩ ፡ ፴ ፡ ፳ ።

፱፤ ወአበዊነሂ ፡ ቀደምት ፡ ቀኒአሙ ፡ (ቀንኡ) ፡ ላዕለ ፡ ዮሴፍ ፡ ወሤጥዎ ፡ ለብሔረ ፡ ግብፅ ፡

አባቶቻችን ፡ በዮሴፍ ፡ ቀንተው ፡ ወንድማቸው ፡ ዮሴፍን፡ ለግብጻውያን፡ ሸጡት ፡ የሸጡትማ ፡ ምነው ፡ ለእስማኤላውያን ፡ ነጋድያን ፡ አይደለምን ፡ ቢሉ ፡ ወንድሞቹ ፡ ለእስማኤላውያን ፡ ነጋድያን ፡ ሸጠውታል ፡ የእስማኤላውያን ፡ ነጋድያንም ፡ ግብፅ ፡ አውርደው ፡ ሸጠውታልና ፡ መዱረሻውን ፡ ሲያይ ፡ በምን ፡ ይቀኑበት ፡



www.ethiopianorthodox.org

ነበር ፡ ቢሉ ፡ ያዕቆብ ፡ ራሔልን ፡ ይወ
ዳት ፡ ነበር ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ እሱን ፡
ይወደው ፡ ነበርና ፡ ሲያረጁ ፡ የወለዱ
ትም ፡ ልጅ ፡ ይወደዳልና ፡ ከመወደዱም ፡
የተነሣ ፡ አራት ፡ ኅብር ፡ አምስተኛ ፡ ወ
ርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ አልብሶት ፡ ነበር ፡
በዚህ ፡ ይቀኑበት ፡ ነበር ፡ ከዕለታት ፡ በአ
ንድ ፡ ዕለት ፡ ሕልም ፡ አይቶ ፡ ላባቱ ፡
ነገረው ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ነዶ ፡ በኔና ፡
በወንድሞቼ ፡ ፊት ፡ ተከምሮ ፡ በወንድ
ሞቼ ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡
ነዶ ፡ ተነሥቶ ፡ በኔ ፡ ፊት ፡ ላለው ፡ ነዶ ፡
ሲሰግድ ፡ አየሁ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፡ ዐሥራ ፡
አንድ ፡ ነዶ ፡ ወንድሞችህ ፡ ናቸው ፡ በረ
ኃብ ፡ ምክንያት ፡ ይገዙልህ ፡ ይሆናላ ፡
ብሎ ፡ ተርጕሞለታል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አት
ንገራቸው ፡ ይጣሉሃል ፡ አለው ፡ ሂዶ ፡
ይህን ፡ ነግሯቸዋል ፡ ሁለተኛ ፡ ፀሐይ ፡
ጨረቃ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ከዋክብት ፡
ሲሰግዱልኝ ፡ አየሁ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፡
አንተ ፡ ልጅ ፡ ተው ፡ አላልሁህም ፡ አለ
ምሁ ፡ አለምሁ ፡ እያልህ ፡ ይጣሉሃል ፡
አለው ፡ ነገሩም ፡ አልቀረ ፡ ይተረጕምለ
ታል ፡ ፀሐይ ፡ የተባልሁ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ጨ
ረቃ ፡ የተባለች ፡ እናትህ ፡ ናት ፡ ምነው ፡
እናቱማ ፡ ሙታ ፡ የለም ፡ ቢሉ ፡ መቾስ ፡
የወለደ ፡ ብቻ ፡ እናት ፡ ይባላልን ፡ ሞግ
ዚቱ ፡ ነበረችና ፡ እሷን ፡ እናት ፡ ብሎ ፡
ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ከዋክብት ፡ ወንድሞችህ፡
ናቸው ፡ እንገዛልህ ፡ ይሆናላ ፡ ብሎ ፡ ተር
ጕሞለታል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አትንገራቸው ፡
ይጣሉሃል ፡ አለው ፡ ሂዶ ፡ ይህን ፡ ነግሯ
ቸዋል ፡ በዚህም ፡ ሁሉ ፡ ይቀኑበት ፡ ነበ
ር ፡ ለልማዱ ፡ ዐሥሩ ፡ ሁሉ ፡ በግ ፡ ይጠ
ብቃሉ ፡ አምስቱ ፡ ሲጠብቁ ፡ አምስቱ ፡
ሥንቃቸውን ፡ ያቀብላሉ ፡ በዚያ ፡ ወራ

ት ፡ ሁሉም ፡ ተያይዘው ፡ ጠፉ ፡ ልጄ ፡
ወንድሞችህ ፡ እንዲያውን ፡ በረኃብ ፡ ይ
ሞታሉን ፡ ሥንቃቸውን ፡ ይዘህ ፡ ሂደህ ፡
ጠይቀሃቸው ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ሰደደው ፡ ሲሄ
ድ ፡ በመንገድ ፡ ወንድሞቹ ፡ ጠፍተውት ፡
ሲባክን ፡ መንፈስ ፡ ረኃብ ፡ ተነሥቶበት ፡
አዝኖ ፡ ሳለ ፡ መልአክ ፡ ተገለጠለት ፡
አዝኖ ፡ ቢያየው ፡ ምን ፡ ሁነህ ፡ አዝነ
ሃል ፡ አለው ፡ ቢርበኝ ፡ አለው ፡ ምነው ፡
የያዝኸውን ፡ አትበላም ፡ አለው ፡ ይህንማ ፡
አባቴ ፡ ለወንድሞችህ ፡ ስጥ ፡ አለኝ ፡ እን
ጅ ፡ መች ፡ ለኔ ፡ አዘዘልኝ ፡ ብሎታል ፡
ያባትህን ፡ ፈጣሪ ፡ ደንጊያውን ፡ ዳቦ ፡
አድርግልኝ ፡ ብለህ ፡ አትለምነውም ፡
ብሎታል ፡ ወንድሞቼን ፡ አላየሃቸውም ፡
አለው ፡ ትናንት ፡ ተምናታ ፡ ውለው ፡
ነበር ፡ ወደ ፡ ዶታዮን ፡ እንሄዳለን ፡ ሲሉ ፡
ሰምቻቸዋለሁና ፡ የዶታዮንን ፡ መንገድ ፡
ይዘህ ፡ ሂድ ፡ አለው ፡ ሲሄድ ፡ ከሩቅ ፡
ባዩት ፡ ጊዜ ፡ መጽአ ፡ ዝኩ ፡ ሐላሜ ፡ ሕ
ልም ፡ ንዑ ፡ ንቅትሎ ፡ ወንርአይ ፡ ጽድቀ፡
ሕለሚሁ ፡ ይላል ፡ አለምሁ ፡ አለምሁ ፡
የሚል፡ ያ፡ መጣ፡ ኑ ፡ እንግደለው ፡ እስቲ ፡
ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ተነሥቶ ፡ ይገዛን ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ እናያለን ፡ ብለው ፡ እየተቀዳደሙ ፡
ሄዱ ፡ እሱም ፡ የፍቅር ፡ መስሎት ፡ እየ
ሮጠ ፡ ሂዶ ፡ ተቀበላቸው ፡ የያዘላቸውን ፡
ተቀብለው ፡ ይመቱት ፡ ጀመረ ፡ ሂዶ ፡
ከስምዖን ፡ ተጠጋ ፡ በሰይፍ ፡ ጥፊ ፡ መታ
ው ፡ ከሮቤል ፡ ተጠጋ ፡ ታላቅ ፡ ወንድም ፡
እንዳባት ፡ ያለ ፡ ነውና ፡ አፍረው ፡ ትተ
ውታል ፡ ተዉ ፡ እናንተ ፡ ወንድማችነን ፡
ገለን ፡ ምን ፡ እንጠቀማለን ፡ ቀበሮ ፡ ትብ
ላው ፡ ብሎ ፡ ወዐዘቅታ ፡ ሐዳስ ፡ ይላል ፡
ውኃዋ ፡ ካልወጣላት ፡ ጉድጓድ ፡ አስጥሎ
ታል ፡ ካባ[illegible]



ሠውሬ ፡ ወስጄ ፡ መታረቂያ ፡ ይሆነኛል ፡
ብሎ ፡ ነው ፡ በግ ፡ የሚመልሱት ፡ በተራ፡
ነው ፡ ሲበሉ ፡ በግ ፡ የመመለሱ ፡ ተራ ፡
የሮቤል ፡ ደረሰ ፡ በግ ፡ ሊመልስ ፡ ሂዶ ፡
ሳለ ፡ የእስማኤላውያን፡ ነጋድያን፡ መጡ ፡
የይሁዳ ፡ ፊታውራሪ ፡ ይሁዳ ፡ እናንት ፡
ወንድማችነን ፡ ገለን ፡ ደሙን ፡ ብንሰው
ር ፡ ምን ፡ እንጠቀማለን ፡ እንሽጠው ፡
አለ ፡ እንሽጠው ፡ እንሽጠው ፡ ብለው ፡
ለእስማኤላውያን ፡ ነጋድያን ፡ ለሠላሳ ፡
ብር ፡ ሽጠውታል ፡ እስማኤላውያን ፡
ግብፅ ፡ አውርደው ፡ ለጲጥፋራ ፡ ለኻያ ፡
ብር ፡ ሽጠውታል ፡ ምነው ፡ በሠላሳ ፡
ብር ፡ ገዝተውት ፡ አልነበረም ፡ ቢሉ ፡
የሚዛኑ ፡ ደግነት ፡ ነው ፡ በከነዓን ፡ ሠላ
ሳው ፡ በግብፅ ፡ ኻያ ፡ ይሆናልና ። አን
ድም ፡ በቀረጥ ፡ ምክንያት ፡ ተቈጣጠሩ ፡
ብለው ፡ አስቀርተውባቸዋል ፡ የበግ ፡
ጠቦት ፡ አርደው ፡ ወጸንቀቅዋ ፡ ይላል ፡
ልብሱን ፡ ደም ፡ ቀብተው ፡ ለያዕቆብ ፡
ልከውለታል ፡ ይህ ፡ የልጅህን ፡ ልብስ ፡
ይመስላል ፡ ወደኛ ፡ ልከሽው ፡ ኑሯልን ፡
ቀበሮ ፡ በልታውም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እና
ውቅ ፡ ብለው ፡ አይቶ ፡ አዎን ፡ የልጄ ፡
ልብስ ፡ ነው ፡ እኩይ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ በ
ልዖ ፡ ልጄን ፡ ቀበሮ ፡ በልታዋለች ፡ እያ
ለ ፡ ሲያለቅስ ፡ ዓይኑ ፡ ጠፍቷል ፡ ምሳሌ ፡
ነው ፡ ዮሴፍ ፡ የጌታ ፡ ወንድሞቹ ፡ የአይ
ሁድ ፡ የያዘላቸውን ፡ ተቀብለው ፡ እሱን ፡
ጠልተው ፡ እንደ ፡ ደበደቡት ፡ ጌታም ፡
ምግበ ፡ ነፍስ ፡ ወንጌልን ፡ ቢያስተምራ
ቸው ፡ ተአምራቱን፡ ወደው፡ ትምህርቱን፡
ጠልተው ፡ ሰቅለው ፡ ገድለውታልና ፡ በእ
ንተ ፡ ሠናይሰ ፡ ግብርከ ፡ ኢንዌግረከ ፡
ባሕቱ ፡ በበይነ ፡ ፅርፈትከ ፡ እንዲል ።
ስምዖን ፡ የጸሐፍት ፡ በሰይፍ ፡ ጥፊ ፡ እን

ደመታው ፡ ተነበይ ፡ ለነ ፡ ክርስቶስ ፡
መኑ ፡ ጸፍዓከ ፡ እያሉ ፡ ፊቱን ፡ በሻሽ ፡
ሸፍነው ፡ ጸፍተውታል ፡ ሮቤል ፡ የጲ
ላጦስ ፡ ወንድማችነን ፡ ብንገል ፡ ምን ፡
እንጠቀማለን፡ ብሎ፡ እንዳዳነው፡ ንጹሕ ፡
አነ ፡ እምደሙ ፡ ለዝ ፡ ብሎ ፡ እጁን ፡ ታጥ
ቧል ፡ ይሁዳ ፡ የይሁዳ ፡ እንሽጠው ፡ ባለ ፡
ጊዜ ፡ እንሽጠው ፡ እንሽጠው ፡ ማለታ
ቸው ፡ ስቅሎ ፡ ስቅሎ ፡ ማለታቸውን ፡
መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ ዮሴፍ ፡ የመ
ለኮት ፡ ልብስ ፡ የትስብእት ፡ ደም ፡ ከል
ብስ ፡ እንጅ ፡ ከዮሴፍ ፡ እንዳልተገኘ ፡
ሕማም ፡ ሞትም ፡ በሰውነቱ ፡ ነው ፡ እን
ጅ ፡ በመለኮቱ ፡ የለበትምና ፡ እንዲህ ፡
ግን ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ምሳሌው ፡ የተካከለ ፡
አይደለም፣ ምሳሌ፡ ዘየሐጽጽ ፡ ነው ፡ (ጥቅ)
ወሶበ ፡ ንሜስል ፡ ለክሙ ፡ ዘንተ ፡ ምሳሌ ፡
ኢይምሰልክሙ ፡ ዘንፈልጦ ፡ ለመለኮቱ ፡
እምትስብእቱ ፡ በከመ ፡ ተፈልጠ ፡ ዮሴፍ፡
እምልብሱ ፡ ብሎ ፡ ሊቁ ፡ ወስዶታል ፡
ዘፍጥ ፡ ፴፯ ፡ ፳፰ ።

፲ ፤ ወሀሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌሁ ፡

እግዚአብሔርም ፡ አልተለየውም ፡

ወአድኅኖ ፡ እምኵሉ ፡ ምንዳቤሁ ፡

ከመከራው ፡ ሁሉ ፡ አዳነው፡ ወንድሞቹ ፡
ካመጡበት ፡ መከራ ። አንድም ፡ ከብእ
ሲተ ፡ ጲጥፋራ ፡ አዳነው ፡ ጲጥፋራም ፡
ገዝቶ ፡ ባለሟል ፡ አድርጎታል ፡ እሱ ፡
ከገባለት ፡ በኋላ ፡ ገንዘቡ ፡ እየበዛለት ፡
ሂዷል ፡ በታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ምክንያት ፡
የአቢዳራ ፡ ከብት ፡ እንደ ፡ በዛለት ፡ የው
ስጥ ፡ ጉስጉሱ ፡ የሜዳ ፡ ንስንሱ ፡ ባንተ ፡
ፈቃድ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ አሠልጥኖታል ፡
መልከ ፡ መልካም ፡ ነበርና ፡ ምሽቱ ፡
ሲወጣ ፡ ባቱን ፡ ሲገባ ፡ ፊቱን ፡ ደረቱን ፡

www.ethiopianorthodox.org

እያየች ፡ ወወደየት ፡ አዕይንቲሃ ፡ ይላል ፡
ዐይኗን ፡ ጣለችበት ፡ ነዓ ፡ ስክብ ፡ ምስ
ሌየ ፡ ትለዋለች ፡ እሱም ፡ ጌታዬ ፡ በሁሉ፡
ሲያሰለጥነኝ ፡ ባንች ፡ አላሠለጠነኝም ፡
በዚያውም ፡ ላይ ፡ ለሔዋን ፡ አንድ ፡ አዳ
ምን ፡ ፈጠረላት ፡ እንጅ ፡ ሁለተኛ ፡ አል
ፈጠረላትም ፡ እያላት ፡ ይሄዳል ፡ አንድ ፡
ቀንም ፡ ጫ ፡ ብሎ፡ ሳለ ፡ ሰው ፡ በሌለበት፡
ወርቅ ፡ ብር፡ ለመቍጠር ፡ ግምጃ ፡ ለማ
ናፈስ ፡ ቢሉ ፡ ከዕቃ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ሳለ ፡
አንት ፡ ባሪያ ፡ ዛሬ ፡ አለቀቅሁህም ፡ ብላ ፡
ልብሱን ፡ ያዘችው ፡ ጥሎላት ፡ ነጥቆ ፡
ወጣ ፡ ስትስብ ፡ ወሠበረ ፡ ማዕጾሃ ፡ ሐይ
ከላ ፡ ይላል ፡ የሣንቃው ፡ ወንዳ ፡ ወንዴ ፡
ጨለንቃዋን ፡ ሰበረባት ፡ ብታፍር ፡ ልብ
ሱን ፡ እንደያዘች ፡ ጮኸች ፡ ተሰብስበው፡
መጥተው ፡ ምን ፡ ሆነሻል ፡ አሏት ፡ ባሪያ፡
የሚገዛ ፡ ሰው ፡ መልከ ፡ ክፉ ፡ ጥቁር፡
ጠጕረ ፡ ከርዳዳውን ፡ አይቶ ፡ ይገዛል ፡
እንጅ ፡ ከሱ ፡ የበለጠ ፡ መልከ ፡ መልካ
ም ፡ ገዝቶ ፡ እመቤቴን ፡ እንዲህ ፡ አደረ
ግኋት፡ ለማለት፡ አይሆንም፡ ብዬ፡ ብለው፡
ልብሱን ፡ ጥሎልኝ ፡ ሄደ ፡ አለቻቸው ፡
ነገሩ ፡ አይመስልም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እን
ዲህ ፡ ስትይ ፡ ምን ፡ እናደርጋለን ፡ ብለው፡
ይዘው ፡ አቆይተውታል ፡ ሲመጣ ፡ ነገ
ሩት ፡ የቅናት ፡ የለው ፡ ጽናት ፡ እን
ዲሉ ፡ አያደርግም ፡ አላለም ፡ በሁሉ ፡
አሠልጥኘዋለሁና ፡ ያደርጋል ፡ ወስዳች
ሁ ፡ ከፈርዖን ፡ ግዞት ፡ ቤት ፡ እሠሩት ፡
አለ ፡ ወስደው ፡ ከፈርዖን ፡ ግዞት ፡ ቤት ፡
አሠሩት ፡ ብእሲ-ተ፡ ጲጥፋራ፡ የኃጢአት፡
ዮሴፍ ፡ የጌታ ፡ ምሳሌ ፡ ከዚያም ፡ እስሮ
ች ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ እየተመ
ገቡ ፡ ሳይጠቀሙ ፡ አይቶ ፡ እንዲህ ፡ አይ
ደለም ፡ ቆዩ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሰብ
ስቦ ፡ ማታ ፡ ግብር ፡ አግብቶላቸዋል ፡
ለራት ፡ አይበቃቸው ፡ የነበረ ፡ ለምሳ ፡
የሚተርፋቸው ፡ ሆኗል ፡ ይኸን ፡ አይቶ ፡
የሥር ፡ ቤት ፡ ጠባቂው ፡ ባንተ፡ ፈቃድ ፡
ይደሩ ፡ ብሎ ፡ ሹሞታል ፡ ኢኀደረ ፡ ዮሴ
ፍ ፡ እንበለ ፡ ሢመት ፡ ያሰኘው ፡ ይህ ፡
ነው ፡ የፈርዖን ፡ ጠጅ ፡ አሳላፊው ፡ የእን
ጀራ ፡ አሳላፊው ፡ በድለው ፡ ከዚያ ፡ ታስ
ረው ፡ ነበር ፡ ሕልም ፡ አይተው ፡ የሚተ
ረጕምላቸው ፡ አጥተው ፡ አዝነው ፡ ሳለ ፡
ወጥቶ ፡ ሲገባ ፡ አይቷቸው ፡ ምነው ፡
አዝናችኋል ፡ አላቸው ፡ ሕልም ፡ አይተን፡
የሚተረጕምልን ፡ አጥተን ፡ አሉት ፡ ሕል
ምንማ ፡ እንጅ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጠ
ለት ፡ ይተረጕማል ፡ ንገሩኝ ፡ አላቸው ፡
ጠጅ ፡ አሳላፊው ፡ ሦስት ፡ የወይን ፡ ዘለላ፡
በጌታዬ ፡ ጽዋ ፡ ጠምቄ ፡ ለጌታዬ ፡ ሳሳል
ፍለት ፡ አየሁ ፡ አለው ፡ ሠላስ ፡ አውያን ፡
ሠላስ ፡ ዕለታት ፡ ናቸው ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡
ቀን ፡ ጌታህ ፡ ከቀደመ ፡ ሹመትህ ፡ ይመል
ስሃል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በግፍ ፡ ታስሬያለሁና፡
አዘክረኒ ፡ በቅድመ ፡ ፈርዖን ፡ እግዚእከ ፡
አለው ፡ ሊፈታ ፡ ቀርቦ ፡ የነበረው ፡ ይህ ፡
ዕዳ ፡ ሆኖበት ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ኑሯል ፡
የእንጀራ ፡ ቤቱም ፡ ይኸን ፡ አይቶ ፡ ለኔ
ም ፡ የሚተረጕምልኝ ፡ መስሎት ፡ እኔም ፡
እንጅ ፡ አዝማደ ፡ መባልዕትን ፡ በሦስት ፡
እንቅብ፡ ደራርቤ፡ ተሸክሜ ፡ ስሄድ ፡ አዕ
ዋፍ ፡ ከላዬ ፡ ላይ ፡ እየተነጣጠቁ ፡ ሲመ
ገቡት ፡ አየሁ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፡ ሠላስ ፡
አክፋር ፡ ሠላስ ፡ ዕለታት ፡ ናቸው ፡ እስከ፡
ሦስት ፡ ቀን፡ ጌታህ፡ ያሰቅልሃል ፡ ንጉሥ ፡
የገደለው ፡ አንበሳ ፡ የሰበረው ፡ ይታፈራ
ልና ፡ የሚቀብርህ ፡ የለም ፡ ሥጋህን ፡ አዕ
ዋፍ ፡ እየተነጣጠቁ ፡ ይመገቡታል ፡አለ
ው ፡ ይህ ፡ በሆነ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡



ፈርዖን ፡ የተወለደበትን ፡ ቀን ፡ ለማክ
በር ፡ በአዳራሽ ፡ ተገኝቶ ፡ ሳለ ፡ አሕዛብ ፡
የተወለዱበትን ፡ ቀን ፡ ያከብራሉ ፡ ከጨ
ለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ከጠባብ ፡ ወደ ፡
ሰፊ ፡ የወጣንበት ፡ ነው ፡ ሲሉ ። አንድም
በዚህ ፡ ቀን ፡ ተወልደን ፡ ለዚህ ፡ መዓርግ፡
ደረስን፡ ሲሉ፡ ጠጅ፡ አሳላፊው፡ ሲያጠፋ ፡
እንጀራ ፡ ቤቱ ፡ ሲያከናውን ፡ አይቶ ፡
ታሰበው ፡ ያነን ፡ ጠጅ ፡ አሳላፊውን ፡
ከቀደመ ፡ ሹመቱ ፡ መልሱት ፡ ብሏቸው ፡
መልሰውታል ፡ እንጀራ ፡ አሳላፊውን ፡
ስቀሉት ፡ ብሏቸው ፡ ሰቅለውታል ፡ ለዚ
ያም ፡ ተረጐመለት ፡ ተደረገለት ፡ በዚ
ያም ፡ ተረጐመበት ፡ ተደረገበት ፡

ወወሀቦ ፡ ሞገሰ ፡ ወጥበበ ፡ በቅድመ ፡ ፈርዖን፡ ንጉሠ
ግብፅ ፡

ባለሟልነትን ፡ ሰጠው ፡ ሕልም ፡ መተ
ርጐምንም ፡ ገለጠለት ፡ ይህ ፡ በሆነ ፡
በሁለት ፡ ዓመቱ ፡ ወቆመ ፡ ፈርዖን ፡ ው
ስተ ፡ ገበዘ ፡ ተከዚ ፡ ይላል ፡ ራእይ ፡ ያያ
ል ፡ ከወንዝ ፡ ዳር ፡ የቆምሁ ፡ መስሎት ፡
ሰባት ፡ የወፈሩ ፡ የሰቡ ፡ ላሞች ፡ ከባሕር፡
ሲወጡ ፡ ሰባት ፡ የከሱ ፡ የጐፈዩ ፡ ላሞች፡
ተከታትለው ፡ ወጥተው ፡ ውጠዋቸው ፡
ከቀደመ፡ ክሳታቸው ፡ ሳይለወጡ ፡ ሰባት፡
የለመለሙ ፡ ያፈሩ ፡ ገብሶች ፡ ከዛፍ ፡
ሥር ፡ ሲወጡ ፡ ሰባት ፡ የደረቁ ፡ የሰለቱ ፡
ገብሶች ፡ ተከታትለው ፡ ወጥተው ፡ ውጠ
ዋቸው ፡ ከቀደመ ፡ ክሳታቸው ፡ ሳይለ
ወጡ ፡ አይቶ ፡ አዘነ ፡ ጠጅ ፡ አሳላፊው ፡
ቢገባ ፡ አዝኖ ፡ አገኘው ፡ ምነው ፡ አዝነ
ሃል ፡ አለው ፡ ሕልም ፡ አይቼ ፡ የሚተረ
ጕምልኝ ፡ አጥቼ ፡ አለው ፡ እዜከራ ፡ ለኃ
ጢአትየ ፡ ይላል ፡ ዝንጋዔየ ፡ ሲል ፡ ነው።
አንድም ፡ አንተን ፡ በድዬ ፡ ታስሬ ፡ ሳለ ፡
የተደረገልኝን ፡ ነገር ፡ አስብሁ ፡ ሲል ፡
ነው፡ ጲጥፋራ፡ በግፍ ፡ ያሠረው ፡ አንድ ፡
ዕብራዊ ፡ ነበረ ፡ ሕልም ፡ አይቼ ፡ ተረጐ
መልኝ ፡ ተደረገልኝ ፡ ወንድሜም ፡ ሕል
ም ፡ አይቶ ፡ ተረጐመበት ፡ ተደረገበት ፡
እሱ ፡ ይተረጕምልሃል፡ አለው ፡ ልብሱን፡
ለውጣችሁ ፡ ገላውን ፡ አጥባችሁ ፡ ጠጕ
ሩን ፡ ላጭታችሁ ፡ አምጡት ፡ አላቸው ፤
ኀሠር ፡ ከንጉሥ ፡ ፊት ፡ አይቀርብምና ፡
ምንም ፡ ቢሆን ፡ የእሥር ፡ ልማድ፡ አልቀ
ረለትምና ፡ ጠጕሩን ፡ ላጭተው ፡ ልብ
ሱን ፡ ለውጠው ፡ ገላውን ፡ አጥበው ፡
አመጡለት ፡ ሕልም ፡ አይቼ ፡ የሚተረጕ
ምልኝ ፡ አጥቼ ፡ አለው ፡ ሕልምንማ ፡
እንጅ ፡ እግዚአብሔር ፡ የገለጠለት ፡ ይተ
ረጕማል ፡ በል፡ ንገረኝ፡ አለው ፡ ነገረው ፡
አሐዱ ፡ ሕልሙ ፡ ለንጉሥ ፡ የንጉሥ ፡
ሕልሙ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሰባት ፡ የወፈሩ ፡
የሰቡ ፡ ላሞች ፡ ሰባት ፡ የለመለሙ ፡ ያፈ
ሩ ፡ እሸቶች ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሰባት ፡ የከ
ሱ ፡ የጐፈዩ ፡ ላሞች ፡ ሰባት ፡ የደረቁ ፡
የሰለቱ ፡ እሸቶች ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሰባት ፡
ዓመት ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ጽጋብ ይሆናል ፡
ከሰባት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የሰባቱን ፡ ዓ
መት ፡ ጽጋብ ፡ የሚያዘነጋ ፡ ሰባት ፡ ዓመ
ት ፡ ጽኑ ፡ ረኃብ ፡ ይሆናል ፡ አለው ፡ ከባ
ሕር ፡ ዳር ፡ መሆኑ ፡ ኑሯችሁ ፡ በመስኖ ፡
ነውና ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ መሆኑ ፡ ይህ ፡ ሁሉ፡
የሚደረግ ፡ ባንድ ፡ ባንት ፡ ዘመን ፡ ነውና፡
አለው ፡ ለዚህ ፡ ምን ፡ ይሻላል ፡ አለው ፤
ብልህ፡ሹም፡ መሾም፡ነዋ፡ አለው፡ ሹመት፡
ተካሰሰ፡ ይሏል፡ በዘመነ፡ ጽጋብ፡ ሰውን ፡
ወርቅ ፡ ብር ፡ አምጣ ፡ ከሚሉት ፡ እህል ፡
አምጣ ፡ ቢሉት ፡ ይወዳል ፡ የወርቁን ፡
የብሩን፡ በሺሬታው ፡ እህሉን ፡ እየተቀበ
ልህ ፡ የሚነቅዘውን ፡ እንደ ፡ ኖራ ፡ እያስ
ወገጥህ ፡ እያስረገጥህ ፡ እንደ ፡ጡብ ፡ እያ

www.ethiopianorthodox.org

ስጣልህ ፡ የማይነቅዘውን፡ ከነነዶው ፡ እያ
ስከመርህ ፡ አኑር ፡ ብሎታል ፡ አልቦ ፡ ዘይ
ጠበብ ፡ እምኔከ ፡ ካንተ ፡ በቀር ፡ የሚያው
ቅበት ፡ የለም ፡ ብሎ ፡

ወሤሞ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ግብፅ ፡

በግብፅ ፡ ሁሉ ፡ ሾመው ፡

ወአመገቦ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ቤቱ ፡

በገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ አሠለጠነው ፡ ወአልቦ ፡
ዘይፈደፍደከ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ መን
በረ ፡ መንግሥትየ ፡ እኔ ፡ ከዚህ ፡ ከዙፋኔ፡
በቀር ፡ የምበልጥህ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ሐቲ
ም ፡ ቀለበቱን ፡ በጣቱ ፡ አግብቶ ፡ ልብሰ ፡
መንግሥቱን ፡ አልብሶ ፡ የወርቅ ፡ ዘንግ ፡
አሲዞ ፡ እሱ ፡ በተቀመጠበት ፡ መደብ ፡
አስቀምጦ ፡ ሹሞታል ፡ ኢል ፡ አብሬል ፡
ብሎ ፡ አብሬል ፡ አዋጅ ፡ አዋጅ ፡ ኢል ፡
ገብር ፡ ኮነ ፡ እግዚአ ፡ ማለት ፡ ነው ፡
ስሙን ፡ ለውጦ ፡ እስቶፎኔሳ ፡ ብሎታል ፡
ሊቀ ፡ ጠቢባን ፡ ሊቀ ፡ ማእምራን ፡ ማለ
ት ፡ ነው ፡ አስኒት ፡ ወለተ ፡ ጲጥፋራ ፡
ማሪ ፡ ካህን ፡ ዘሀገረ ፡ ሔልዮቱ ፡ ይላል ፡
የቢትወደዱን ፡ የጲጥፋራን ፡ ልጅ ፡ አጋ
ብቶታል ፡ ግብፅን ፡ ዞሮ ፡ ተመርቷታል ፡
ዘፍ ፡ ፵፩ ፡ ፵—፵፭ ፡

፲፩ ፤ ወመጽአ ፡ ረኃብ ፡ ለብሔረ ፡ ግብፅ ፡

በግብፅ ፡ ሀገር ፡ ረኃብ ፡ ሆነ ፡

ወበከነዓን ፡ ዐቢይ ፡ ሕማም ፡

ይልቁንም ፡ በከነዓን ፡ ጽኑ ፡ ረኃብ ፡ ሆነ ፡
በግብፅ ፡ ውለው ፡ ይመገቡ ፡ ነበር ፡ በከነ
ዓን ፡ ግን ፡ ውሎ ፡ ማደር ፡ ሁኗል ፡

ወኃጥኡ ፡ ዘይሴሰዩ ፡ አበዊነ ፡

አባቶቻችን ፡ የሚመገቡት ፡ አጥተው ፡
ተቸገሩ ።

፲፪ ፤ ወሰምዐ፡ ያዕቆብ ፡ ከመ፡ ቦ፡ እክል፡ በብሔረ ፡
ግብፅ ፡ ወፈነዎሙ ፡ ለአበዊነ ፡ ቅድመ ፡

ያዕቆብም ፡ በግብፅ ፡ አገር ፡ እህል ፡ እን
ዳለ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ አባቶቻ
ችነን ፡ ላከ ፡ ወገብኡ ፡ ዳግመ ፡ ለግብፅ ፡
የሚል ፡ ነውና ፡ ፈነዎሙ ፡ ቅድመ ፡ አለ፡
ከማን ፡ ሰምቷል ፡ ቢሉ ፡ ሰፈሩ ፡ ከመን
ገድ ፡ ዳር ፡ ነበር ፡ የእስማኤላውያን ፡ ነጋ
ድያን ፡ አልፈው ፡ ሲሄዱ ፡ ሲነጋገሩ ፡
ሰምቷል ። አንድም ፡ አዝኖ ፡ ሳለ ፡ አል
ፈው ፡ ሲሄዱ ፡ አይተው ፡ ምን ፡ ያሳዝን
ሃል ፡ በግብፅ ፡ እህል ፡ ተርፏል ፡ ወርቅ ፡
ሰደህ ፡ አታሸምትምን ፡ ብለውታል ።
አንድም ፡ መልአክ ፡ ነግሮታል ፡ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ልጆቹ ፡ በግብፅ ፡ እህል ፡ ተርፏል፡
አሉ ፡ እንዲያውን ፡ በረኃብ ፡ እንሞታለን፡
ወርቅ ፡ ይዛችሁ ፡ ሸምታችሁ ፡ ኑ ፡ እንጅ፡
አላቸው ፡ በሥሩ ፡ ሁሉ ፡ ወርቅ ፡ ይዘው ፡
እህል ፡ ሊሸምቱ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ሄዱ ፡
ዮሴፍ ፡ ነገር ፡ ሲሰማም ፡ ቢሉ ፡ ኩዳድ ፡
ሲያስኮድድም ፡ ቢሉ ፡ ደረሱ ፡ ከሩቅ ፡
ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ አወቃቸው ፡ እሊያ ፡
ሰዎች ፡ ሰላዮች ፡ ናቸው ፡ ያዟቸው ፡ አለ ፡
እኛስ ፡ ሰላዮችም ፡ አይደለነ ፡ ወርቅ ፡
ይዘን ፡ ከከነዓን ፡ እህል ፡ ልንሸምት ፡
መጥተናል ፡ እንጅ ፡ በዚያውስ ፡ ላይ ፡
ሰላይ ፡ ካንድ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡
ካንድ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተወጣጥቶ ፡
ይመጣል ፡ እንጅ ፡ ያንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ል
ጆች ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንለቅ ፡ ብለን ፡
ባንድ ፡ ላይ ፡ እንመጣለን ፡ አሉ ፡ ደግሞ ፡
ሐሰታቸው ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ እንዲህ ፡
አስተካክሎ ፡ ዐሥር ፡ ልጆች ፡ አንድ ፡
ጊዜ ፡ አስገኘን ፡ አላቸው ፡ እረ ፡ ዐሥራ ፡
ሁለት ፡ ነበርነ ፡ አንዱን ፡ ቀበሮ ፡ በላ
ችው ፡ አንዱ ፡ የማይችል ፡ ሁኖ ፡ ከቤት ፡
ቀርቷል ፡ አሉት ፡ ሞተ ፡ ዮሴፍ ፡ አኀዊሁ፡
ነገርዎ ፡ ለዮሴፍ ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ነው ፡
ወስዳችሁ ፡ እሰሯቸው ፡ አለ ፡ እስከ ፡
ሦስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ አስረው ፡ አሰንብተ
ዋቸዋል ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ሹሙን ፡
ጠርቶ፡ እህሉን፡ ባቆማዳቸው ፡ እየመላህ ፡
ወርቃቸውን ፡ እየመለስህ ፡ እያሰርህ ፡
ስጣቸው ፡ አለው ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፡
እናንት ፡ እንግዲህ ፡ እውነተኛነታችሁ ፡
የሚታወቅ ፡ ከቤት ፡ ቀረ ፡ ያላችሁትን ፡
ወንድማችሁን ፡ ያመጣችሁት ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ነው ፡ ያለዚያ ፡ ግን ፡ ፊቴን ፡ አታዩ
ትም ፡ ይህ ፡ ዘመነ ፡ ረኃብ ፡ ሰባት ፡ ዓመ
ት ፡ ነው ፡ ገና ፡ መጀመሩ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡
ስምዖንን ፡ በመያዣ ፡ አስቀርቶ ፡ ሰደ
ቸዋል ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡
ጸንዐ ፡ በቀዳማይ ፡ ተሠይጦቱ ፡ እንዲል ፡
ይሸጥ ፡ በማለት ፡ ጸንቶ ፡ ነበርና ፡ መለ
የትን ፡ ይቅመሰው ፡ ብሎ ። አንድም ፡ ሰ
ውነቱ ፡ ተጐድቶ ፡ አይቶ ፡ አዝኖለት ፡
አፍቅሮ ፡ ጸላእት ፡ ሲሄዱ ፡ በመንገድ ፡
ከሰፈር ፡ ሲደርሱ ፡ አንዱ ፡ የከብት ፡ ገፈ
ራ ፡ ለመስጠት ፡ አቆማዳውን ፡ ፈቶ ፡
ቢያይ ፡ ወርቁን ፡ አገኘ ፡ ገብአተኒ ፡ ወር
ቅየ ፡ ብሏል ፡ ከቤት ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡
ሁሉም ፡ አቆማዳቸውን ፡ እየፈቱ ፡ ቢያዩ፡
ወርቃቸውን ፡ አገኙ ፡ ገብአተኒ ፡ ወርቅየ፡
ተባብለዋል ፡ ልጆቼ ፡ ደህና ፡ መጣችሁ ፡
አላቸው ፡ ደህና ፡ መጣን ፡ ነገር ፡ ግን ፡
አገረ ፡ ገዢው ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ከሩቅ፡
ሲያየን፡ ያልሆነ ፡ ነገር ፡ ተናገረን ፡ እሊህ፡
ሰዎች ፡ ሰላዮች ፡ ናቸው ፡ ያዟቸው ፡ አለ
ን ፡ እኛስ ፡ ሰላዮችም ፡ አይደለነ ፡ ወርቅ ፡
ይዘን ፡ ከከነዓን ፡ እህል፡ ልንሸምት ፡ መጥ
ተናል ፡ በዚያውስ፡ ላይ ፡ ሰላይ፡ ለልማዱ ፡
ካንድ ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ካንድ ፡ አገ
ር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተወጣጥቶ ፡ ይመጣል፡
እንጅ ፡ ያንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ልጆች ፡ አንድ፡
ጊዜ ፡ እንለቅ ፡ ብለን ፡ እንመጣለን ፡ አል
ነው ፡ ደግሞ ፡ ሐሰታቸው ፡ አንድ ፡ ሽማ
ግሌ ፡ እንዲህ ፡ አስተካክሎ ፡ ዐሥር ፡
ልጆች ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አስገኘን ፡ አለን ፡
እረ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ነበርን ፡ አንዱን ፡
ቀበሮ ፡ በላችው ፡ አንዱ ፡ የማይችል ፡
ሆኖ ፡ ከቤት ፡ ቀርቷል ፡ አልነው ፡ እንግ
ዲህ ፡ እውነተኛነታችሁ ፡ የሚታወቅ ፡
ከቤት ፡ ቀረ ፡ ያላችሁትን ፡ ወንድማች
ሁን ፡ ያመጣችሁት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡
ያለዚያ ፡ ግን ፡ ፊቴን ፡ አታዩትም ፡ ብሎ ፡
ስምዖንን ፡ በመያዣ ፡ አስቀረው ፡ አሉት፡
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ምን ፡ ያስቀባጥር ፡ ነበር ፡
ብሎ ፡ አዝኖ ፡ ዝም ፡ ብሏል ፡ ባቆማዳ ፡
ጆሮ ፡ የመጣ ፡ እህል ፡ ያን ፡ ያህል፡ ነውና፡
አለቀ ፡ ሁለተኛ ፡ ልጆቼ ፡ እንዲያውን ፡
በረኃብ ፡ እንሞታለን ፡ ሂዳችሁ ፡ ሸምታ
ችሁ ፡ ኑ ፡ አላቸው ፡ ነግረንሃል ፡ ብንያ
ምን ፡ ስጠን ፡ እንሂድ ፡ ያለዚያ ፡ ፊቴን ፡
አታዩትም ፡ ብሎናል ፡ አሉት ፡ እናንተ ፡
ሰዎች ፡ በኔ ፡ በጠላትነት ፡ ተነሥታች
ኋልን ፡ ዮሴፍን ፡ ቀበሮ ፡ በላችው ፡ ስም
ዖንን ፡ በመያዣ ፡ አስቀረው ፡ አላችሁኝ ፡
ደግሞ ፡ ይህነን ፡ ወስዳችሁ ፡ ይህን ፡ ያረ
ጀውን ፡ ሰውነቴን ፡ በኀዘን ፡ ወደ ፡ መቃ
ብር ፡ ልታወርዱት ፡ ትወዳላችሁን ፡ አላ
ቸው ፡ ሮቤል ፡ አባቴ ፡ መልሼ ፡ ያላመጣ
ሁት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኔን ፡ ልጆች ፡ እያነ
ቅህ ፡ ፍጃቸው ፡ አለው ፡ ያላዋቂ ፡ አነጋ
ገር ፡ የሱ ፡ ልጆች ፡ ያልሆኑ ፡ መስሎት ፡
ይሁዳ ፡ ያዋቂ ፡ አነጋገር ፡ አባቴ ፡ መልሼ፡
ያላመጣሁት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርገምህ ፡
ይመራመረኝ ፡ አለው ፡ ጌታችን ፡ እመቤ
ታችን ፡ በባሕርዩ ፡ ያሉ ፡ ናቸውና ፡ ነገ



www.ethiopianorthodox.org

ሩን ፡ ይቀበለዋል ፡ እንዲያውስ ፡ ረኃቡ ፡
ይገለው ፡ የለምን ፡ ይዛችሁት ፡ ሂዱ ፡
የመጣውንም ፡ ወርቅ ፡ ተሳስቶ ፡ ይሆ
ናል ፡ መልሳችሁ ፡ ውሰዱት ፡ ላገረ ፡
ገገሮም ፡ በግብፅ ፡ የሌለውን ፡ በዚህ ፡ ያለ
ውን ፡ ማሩን ፡ ሽቱውን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡
ይዛችሁለት ፡ ሂዱ ፡ አላቸው ፡ ዘፍጥ ፡
፵፪ ፡ ፩ ።

፲፫ ፤ ወሶበ ፡ ገብኡ ፡ ዳግመ ፡ ለግብፅ ፡ አፍለጠሙ ፡
በነፍስቱ ፡ ዮሴፍ ፡ ለአኀዊሁ ፡

ሁለተኛ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ፡
ዮሴፍ ፡ ለወንድሞቹ ፡ በግዝራቱ ፡ አስረዳ
ቸው ። እንድም ፡ እንደ ፡ ማርያም ፡ ሳመ
ችኝ ፡ ያለ ፡ ነበረበት ፡ እንደ ፡ ቀደመው ፡
ነገር ፡ ሲሰማም ፡ ቢሉ ፡ ኩዳድ ፡ ሲያስኮ
ድድም ፡ ቢሉ ፡ ደረሱ ፡ ዳኅንኑ ፡ ዝስኩ ፡
አረጋዊ ፡ አቡክሙ ፡ አላቸው ፡ እወ ፡ ዳኅ
ን ፡ አሉት ፡ ቡሩክ ፡ ብእሲሁ ፡ እንዲየ
ውም ፡ ቡሩክ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢመርቅላ
ቸው ፡ ሰገዱ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ስግደት ፡
ተፈጸመ ፡ ከቤት ፡ ቀረ ፡ ያላችሁት ፡ ወን
ድማችሁ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አላቸው ፡ አዎን ፡
አሉት ፡ ወልድየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሣ
ሃልከ ፡ አለው ፡ ከእሊህ ፡ ምቀኝነት ፡
ያድንኅ ፡ ሲለው ፡ ነው ፡ ሹሙን ፡ ወስ
ደህ ፡ ከወንድማቸው ፡ አገናኛቸው ፡ አለ
ው ፡ ይዟቸው ፡ ሲሄድ ፡ የሚያስረን ፡ መስ
ኋቸው ፡ ከነዓን ፡ የወጣውን ፡ ወርቅ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ካቆማዳችን ፡ ያገባውን ፡
ሳናውቀው ፡ አግኝተን ፡ መልሰን ፡ አምጥ
ተነዋል፡አሉት፡ ወርቀክሙሰ፡ ፈቲንየ፡ ሠ
መርክዎ፡ወርቃችሁንስ፡ፈትኜ፡ ለግብር፡አ
ሳልፌዋለሁ፡ወባሕቱ፡እግዚአብሔር፡ ወሀ
በክሙ ፡ መድፍነ ፡ ኅቡዓ ፡ ያባታችሁ ፡
ፈጣሪ ፡ ኅቡዕ ፡ መድፍን ፡ ሰጥቷችሁ ፡
ይሆናል ፡ እንጅ ፡ እኔስ ፡ ከወንድማችሁ ፡

ሳገናኛችሁ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወስዶ ፡ ከወን
ድማቸው ፡ አገናኝቷቸዋል ፡ ማዕድ ፡ ሠር
ታችሁ፡ ቆዩ፡ ብሎ ፡ አዘዘ፡ አንዱን ፡ ለግብ
ፃውያን፡ አንዱን፡ ለቤተ ፡ ሰቦቹ፡ አንዱን፡
ለሱና፡ ለወንድሞቹ ፡ ምንም ፡ ላም ፡ ቢያመ
ልኩ፡ግብፃውያን፡እስራኤልን፡ ላም፡ ጠባ
ቆች ፡ እያሉ ፡ ይጸየፏቸው ፡ ነበርና ፡ በሉ፡
እንደትውልዳችሁ ፡ ተቀመጡ ፡ አላቸው ፡
ተቀመጡ ፡ ብንያም ፡ መጥቶ ፡ በሱ ፡ አጠ
ገብ ፡ ተቀመጠ፡ ለማጉረስ ፡ እንዲመቸው፡
ነው ፡ ወአልዐለ ፡ ክፍሎ ፡ ለብንያም ፡
ይላል ፡ ደራርቦ ፡ አስጥሎለታል ፡ ስለምን፡
ቢሉ ፡ ይቀኑበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ።
አንድም ፡ በእንግዳ ፡ ልማድ ፡ እነሱ ፡
ሁለተኛቸው ፡ ነው ፡ እሱ ፡ ግን ፡ መጀ
መሪያው ፡ ነውና ፡ ደራርቦ ፡ አስጥሎለ
ታል ፡ በልተው ፡ ጠጥተው ፡ ሁለት ፡
ሁለት ፡ እየሆኑ ፡ ሲጫወቱ ፡ እሱን ፡ ዝም፡
ብሎ ፡ አይቶታል ፡ እነዚያ ፡ ሁለት ፡ ሁለ
ት ፡ እየሆኑ ፡ ይጫወታሉ ፡ አንተ ፡ አት
ጫወትምን ፡ አለው ፡ እነዚያ ፡ ሁሉም ፡
ያንዳንድ ፡ እናት ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡ እኔ ፡
የናት ፡ ልጅ ፡ የለኝ ፡ ከማን ፡ ጋራ ፡ ልጫ
ወት ፡ አንድ ፡ ነበረ ፡ ቀበሮ ፡ በላችው ፡
ይሉኛል ፡ አለው ፡ ወስዕነ ፡ ተዓግሦ ፡
ይላል ፡ አልቻለው ፡ ብሎ ፡ መጋረጃውን ፡
ገልጦ ፡ አልቅሶ ፡ ተመልሶ ፡ የሚጠጣ
በትን ፡ ጽዋ ፡ በሐቲም ፡ ቀለበቱ ፡ ሲመ
ታት ፡ ትጮኻለች ፡ በዚያ ፡ ኳ ፡ እያደረገ፡
ይህች ፡ ጽዋ ፡ ሮቤል ፡ ትላለች ፡ ከናንተ ፡
ሮቤል ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ አለ ፡ ይላቸዋል፡
አዎን ፡ ስምዖን ፡ ትላለች ፡ ስምዖን ፡ የሚ
ባል ፡ ሰው ፡ አለ ፡ ይላቸዋል ፡ አዎን ፡ እኔ፡
ነኝ ፡ እያሉ ፡ ይነሣሉ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡
ሁሉንም ፡ አድርሷቸዋል ፡ በነጋው ፡ ሹ
ሙን ፡ ጠርቶ ፡ እህሉን፡ ባቆማዳቸው፡ እየ



መላህ ፡ ወርቃቸውን ፡ መልሰህ ፡ አግብ
ተህ ፡ እያሰርህ ፡ ስጣቸው ፡ ይህችን ፡ ጽዋ፡
ከብንያም ፡ አቆማዳ ፡ አግብተህ ፡ አስ
ረህ ፡ ስጠው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ተከትለህ ፡
የጌታዬን ፡ ጽዋ ፡ ለምን ፡ ሠርቃችሁ ፡
ትሄዳላችሁ ፡ በላቸው ፤ አልሰረቅንም ፡ ይ
ሉሃል ፡ የተገኘበት ፡ ተገገር ፡ ሁኖ ፡ ይኑ
ር ፡ ብለህ ፡ መልሰው ፡ አለው ፡ እንዲህ ፡
ማለቱ ፡ የቀደመ ፡ ክፋታቸውን ፡ አል
ተዉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ትተውት ፡ ይሄዳሉ ፡
ትተዉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይመለሳሉ ፡ ጥለ
ውት ፡ አይሄዱም ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እህሉን ፡
ባቆማዳቸው ፡ እየመላ ፡ ወርቃቸውን ፡
እያገባ ፡ እያሠረ ፡ ሰጣቸው ፡ ጽዋውን ፡
ከብንያም ፡ አቆማዳ፡ አግብቶ፡ አስሮ፡ ሰጠ
ው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ፡ ተከትሎ፡ ምነው፡ እን
ዲህ ፡ አደረጋችሁ ፡ ወርቅ ፡ ላበደረ ፡ ጠ
ጠር ፡ የበኅ ፡ ወረታ ፡ ክፋት ፡ አላቸው ፡
ምነው ፡ ምን ፡ አደረግን ፡ አሉት ፡ ለም
ንት ፡ ሰረቅሙ ፡ ገይበ ፡ እግዚእየ ፡ ዘባቲ ፡
ያቃሪ ፡ የጌታዬን ፡ ጽዋ ፡ ለምን ፡ ሠርቃ
ችሁ፡ትሄዳላችሁ፡ አላቸው፡ ያቃሪ፡ማለቱ፡
በሐቲም ፡ ቀለበቱ ፡ ሲነካት ፡ ትጮህ ፡
ነበርና ፡ የማሚረት ፡ መስሎት ፡ ነው ፡
እኛስ ፡ አልወሰድንም ፡ የተገኘበት ፡ ይ
ሙት ፡ አሉ ፡ ለምን ፡ ይሞታላ ፡ ተገገር ፡
ሁኖ ፡ ይኖራል ፡ እንጅ ፡ አላቸው፡ ተገገር፡
ሁኖ ፡ ይኑር ፡ አሉ ፡ ጠላቱን ፡ ሲያው
ቀው ፡ በወዳጁ ፡ እንዲሉ ፡ ከሮቤል ፡ ጀም
ሮ ፡ እየፈታ ፡ ያይ ፡ ጀመረ ፡ ከብንያም ፡
ሲደርስ ፡ አገኛትና፡ በል ፡ ተመለስ ፡ ብሎ፡
መልሶታል ፡ እነሱም ፡ ተመለሱ ፡ ይህ ፡
ክፉ ፡ የክፉ ፡ ልጅ ፡ እናታቸው ፡ በክፋታ
ቸው ፡ ከፈረስ ፡ መፈተኛ ፡ ወድቃ ፡ ቀረ
ች ፡ ወንድሙን ፡ ቀበሮ ፡ በላችው ፡ እሱ ፡
ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ ያደርገናል ፡ እያሉ ፡

ያዝኑ ፡ ጀመረ ፡ ይሁዳ ፡ እሱን ፡ ተውልኝ፡
እኔን ፡ አስቀር ፡ ከሱ ፡ እኔ ፡ እሻላለሁ ፡
የቆመውን ፡ እቆርጣለሁ ፡ የወደቀውን ፡
እፈልጣለሁ ፡ በዚያውም ፡ ላይ ፡ አባቴ ፡
ዮሴፍን ፡ ቀበሮ ፡ በላችው ፡ ስምዖንን ፡
በመያዣ ፡ አስቀረው ፡ አላችሁኝ፡ ደግሞ፡
ይኽን ፡ ወስዳችሁ ፡ ይህን ፡ ያረጀ ፡ ሰው
ነቴን ፡ በኀዘን ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ልታወ
ርዱት ፡ ትወዳላችሁን ፡ ቢለን ፡ አባቴ ፡
መልሼ ፡ ያላመጣሁት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መር
ገምህ ፡ ይመራመረኝ ፡ ብያለሁና ፡ እሱን፡
ተውልኝ ፡ አለው ፡ ለምኔ ፡ የተገኘበትን ፡
ትቼ ፡ ብሎ ፡ እሱን ፡ ይዞ ፡ ተመለሰ ፡ እነ
ሱም ፡ አብረው ፡ ተመለሱ ፡ ወእንዘ ፡ መ
ተርጉም ፡ ምስሌሆሙ ፡ ይላል ፡ በአስተር
ጓሚ ፡ ሲነጋገሩ ። አንድም ፡ መተርጉም፡
ዮሴፍ ፡ ሳለ ፡ የማይሰማን ፡ መስሏቸው ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ የዚያ ፡ የወንድማችን ፡ ደም ፡
አይደለምን ፡ እየተመራመረ ፡ ሊያጠፋን ፡
ሳይበድለን ፡ በግፍ ፡ ሽጠነው ፡ ሲሉ ፡
ሰምቶ ፡ አልቻለው ፡ ብሎ ፡ ከቤት ፡ ገብቶ
አልቅሶ ፡ ፊቱን ፡ በውኃ ፡ አጥቦ ። አን
ድም ፡ ፊቱን ፡ በእንቡ ፡ አጥቦ ፡ ወንድሞ
ቹን ፡ በቆይታ ፡ አስጠርቶ ፡ እኔ ፡ ወንድ
ማችሁ ፡ ዮሴፍ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ግዝራቱን ፡
አሳይቷቸዋል ። አንድም ፡ እንደ ፡ ማር
ያም ፡ ሳመችኝ ፡ ያለ ፡ ነበረበት ፡ በዚያ ፡
አስረድቷቸዋል ፡ አዘኑ ፡ ደነገጡ ፡ አይዟ
ችሁ ፡ እናንተ ፡ ለክፋት ፡ ብታደርጉት ፡
ውስጡ ፡ ጥበበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡
በዚህ ፡ በዘመነ ፡ ረኃብ ፡ በኔ ፡ ምክንያት ፡
ሊያድናችሁ ፡ ይሆናል ፡ አላቸው ፡

ወአእመሮሙ ፡ ፈርዖንሂ ፡ ለአዝማደ ፡ ዮሴፍ ፡

ፈርዖንም ፡ አዝማደ ፡ ዮሴፍ ፡ እንደ ፡
ተገኙ ፡ አውቆ ፡ ደስ ፡ አለው ፡ በምን ፡
አውቆ ፡ ቢሉ ፡ በቤተ ፡ ዮሴፍ ፡ የደስታ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ጩኸት ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ የኀዘን ፡ ጩኸት ፡ ሁኗል ፡ ይህ ፡ ምንድነው፡ ብሎ፡ ቢጠይቅ ፡ አዝማደ ፡ ዮሴፍ ፡ ተገኝተው ፡ ነው ፡ አሉት ፡ በዚህ ፡ ደስ ፡ አለው ፡ የግ ብፅ ፡ ሰዎች ፡ ያልታወቀ ፡ ኮብላይ ፡ ባሪያ፡ አሠልጥኖብን ፡ ሲሉት ፡ ነበርና ፡ የደግ ፡ ሰው ፡ የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ ቢያገ ኘው ። አንድም ፡ ካንድ ፡ ከዮሴፍ ፡ ይህን፡ ያህል ፡ ጥበብ ፡ ያገኘሁ ፡ ከመላውማ ፡ ምን፡ ያህል ፡ አገኝ፡ ብሎ፡ ዘፍጥ፡ ፵፭፡ ፲፰።

፲፬ ፤ ወለአከ ፡ ዮሴፍ ፡ ወጸውዖሙ ፡ ለአቡሁ ፡ ወለኵሎሙ ፡ አዝማዲሁ ፡

ዮሴፍም ፡ አባቱን ፡ ዘመዶቹን ፡ ልኮ ፡ አስመጥቷቸዋል ፡ ይህ ፡ ዘመነ ፡ ረኃብ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነበረ ፡ ሁለቱ ፡ ዓመት ፡ አልፏል ፡ አምስቱ ፡ ቀርቷል ፡ ባቆማዳ ፡ ጆሮ ፡ እህል ፡ ተመላልሶ ፡ አይሆንምና ፡ አባቴንም ፡ ጓዛችሁንም ፡ ይዛችሁ ፡ ኑ ፡ ብሎ ፡ ከመ ፡ ኢይንሐኩ ፡ ቈሳቍሳቲ ሆሙ ፡ ይላል ፡ ይህ ፡ ቀረን ፡ እንዳይሉ ፡ ለጓዝ ፡ ማንሻ ፡ ዐሥር ፡ ሠረገላ ፡ ለነሱ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ልብስ ፡ ለብንያም ፡ ሦስ ት ፡ መቶ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ አምስት ፡ ልብስ ፡ ላባቱ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ አምስት ፡ ልብስ ፡ ሰጥቶ ፡ እንግ ዲህ ፡ አሁን ፡ በመንገድ ፡ አንተነህ ፡ እንጅ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እንጅ ፡ እያላችሁ ፡ ትጣላላችሁ ፡ አትጣሉ ፡ ብሎ ፡ ሰደዳ ቸው ፡ ሂደው ፡ ዮሴፍ ፡ ወልድከ ፡ ሕያው ፡ በግብፅ ፡ አሉት ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ይነሣልን ፡ ብሎ ፡ አላመነም ። አንድም ፡ ልጄ ፡ ቢሆን ፡ ይሆናል ፡ እንጅ፡ እንዲህ ፡ ያደርግልኝ ፡ ኑሯል ፡ ብሎ ፡ ተጠራጠረ ፡ መሥዋዕት ፡ ልሠዋ ፡ ብሎ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋ፡ መልአክ፡ መጥቶ፡ ኢት ፍራህ ፡ ወሪደ ፡ ግብፅ ፡ እስመ ፡ ዮሴፍ ፡ ወልድከ ፡ ሕያው ፡ በግብፅ ፡ ወይከድነከ፡ አዕይንቲከ ፡ አማውቶ ፡ የሚቀብርህ ፡ ልጅህ ፡ ዮሴፍ ፡ ነውና ፡ አትፍራ ፡ ሂድ ፡ አለው ፡ ሄደ ል ።

ወኮነ ፡ ፍቅዶሙ ፡ ሰብዓ ፡ ወኃምስቱ ፡ ነፍስ ፡

ቍጥራቸውም፡ ሰባ፡ አምስት፡ ነበር ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ ቢል፡ ዮሴፍ፡ ሁለቱን፡ ልጆቹን፡ ይዞ ፡ እስከ ፡ ቋቴሮአስ ፡ ድረስ ፡ ወጥቶ ፡ ተቀብሎታልና ፡ ዮሴፍን ፡ ከነልጆቹ ፡ ቆጥሮ ፡ የኤርና ፡ የአውናን ፡ አፅማቸው ፡ ወርዶ ፡ ነበርና ፡ ኤርን ፡ አውናንን ፡ ቈጥ ሮ ፡ ሰባ ፡ ሦስት ፡ ቢል ፡ ኤርን ፡ አውና ንን ፡ ትቶ ፡ ዮሴፍን ፡ ከነልጆቹ ፡ ቈጥሮ ፡ ሰባ ፡ ሁለት ፡ ቢል ፡ ኤርን ፡ አውናንን ፡ ብቻ ፡ ቈጥሮ ፡ ዮሴፍን ፡ ከነልጆቹ ፡ ትቶ ፡ ሰባ፡ቢል፡ሁሉንም፡ትቶ፤ዘፍጥ፡፵፮፡ ፱፡ ፲ ።

፲፭ ፤ ወወረደ ፡ ያዕቆብ ፡ ብሔረ ፡ ግብፅ ፡

ያዕቆብም ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ሄደ ፡ ዮሴፍም ፡ ተቀበለው ፡ ወዲያው ፡ ወንድሞቹን ፡ ይ መክራቸዋል ፡ እንግዲህ ፡ የኔ ፡ ዘመዶች፡ አውቅባችኋለሁ ፡ ምን ፡ ታውቃላችሁ ፡ ሲሏችሁ ፡ ወንዶቹ ፡ ሰንጠረዥ ፡ በገና ፡ ውኃ ፡ ዋና ፡ ፈረስ ፡ ግልቢያ ፡ ሴቶቹም ፡ ምን ፡ ታውቃላችሁ ፡ ሲሏችሁ ፡ ፈትል ፡ ስፌት ፡ እናውቃለን ፡ ትላላችሁ ፡ ይህ ፡ በዘመነ ፡ ረኃብ ፡ አይጠቅምም ፡ በዘመነ ፡ ረኃብ ፡ ከእህል ፡ የተጠጋ ፡ ነው ፡ የሚድ ነው ፡ ምን ፡ ታውቃላችሁ ፡ ሲሏችሁ ፡ ወንዶቹ ፡ ማረስ ፡ መቆፈር ፡ ከብት ፡ መጠ በቅ ፤ ሴቶቹም ፡ እንጀራ ፡ መጋገር ፡ ወጥ ፡ መሥራት ፡ መፍጨት ፡ መቁላት ፡ እናው ቃለን ፡ በሉ ፡ ብሎ ፡ አምስቱን ፡ ከጓዝ ፡ ትቶ ፡ አምስቱን ፡ አስከትሎ ፡ አባቱን ፡ ይዞ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ቤት፡ ገብቷል፡ ከጓዝ፡ የቀሩት ፡ አምስቱ ፡ የኀምስ ፡ አብዳት ፡

www.ethiopianorthodox.org



አብረው ፡ የሄዱት ፡ አምስቱ ፡ የኀምስ ፡ ጠባባት ፡ ቤተ ፡ ፈርዖን ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ዮሴፍ ፡ የጌታ ፡ ምሳሌ ፡ ወባረኮ ፡ ይላል ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ያንግሥህ ፡ አለው፡ እስፍንቱ ፡ መዋዕሊከ ፡ አረጋዊ ፡ ዘሐዮከ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ ቢለው ፡ መዋዕልየሰ ፡ ምእት ፡ ወሠላሳ ፡ ወኀዳጣን ፡ እማንቱ ፡ በኀበ ፡ መዋዕለ ፡ አበውየ ፡ ወባሕቱ ፡ እኩያተ ፡ ኮናኒ ፡ ወኀልቃ፡ በእንባዜ፡ ብሎ ታል ፡ ከብታችን ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ ለከብት፡ የሚበቃ ፡ ቦታ ፡ ስጠን ፡ አለው ፡ ልጅህ ፡ ዮሴፍ ፡ ባወቀ ፡ ይስጥህ ፡ አለው ፡ ራምሴ፡ ጋምሴ ፡ የምትባል ፡ ለምለም ፡ ቦታ ፡ ሰጥቷቸው ፡ ከዚያ ፡ ኑረዋል ፡

ወሞተ ፡ ውእቱ ፡

ያዕቆብም ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ዘመን ፡ በግ ብፅ ፡ ኑሮ ፡ ሞተ ፡ ወደክመ ፡ ያዕቆብ ፡ አቡከ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፡ ሳይሞት ፡ ልጆ ቹን ፡ ላስባርክ ፡ ብሎ ፡ ሄደ ፡ ልጅህ ፡ ዮሴፍ ፡ መጣ ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡ ተቀመጠ ፡ ከዚህ ፡ እንዳትቀብረኝ ፡ ከነ ዓን ፡ አውጥተህ ፡ እንድትቀብረኝ ፡ ማል ልኝ ፡ ብሎ ፡ አምሎታል ፡ አሁን ፡ ያዕ ቆብን ፡ ያህል ፡ ሰው ፡ በግብፅ ፡ ቢቀበር ፡ የሚረክስ ፡ በከነዓን ፡ ቢቀበር ፡ የሚቀ ደስ ፡ ሁኖ ፡ አይደለም ፡ ለጊዜው ፡ ፀአት ፡ እንዳላቸው ፡ ለማጠየቅ ፡ ነው ፡ ፍጻሜው፡ ግን ፡ ግብፅ ፡ የመቃብር ፡ ከነዓን ፡ የትን ሣኤ ፡ ግብፅ ፡ የሲኦል ፡ ከነዓን ፡ የመን ግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ምሳሌ ፡ ናትና ፡ ዘፍጥ ፡ ፵፯ ፡ ፩ ። ፵፱ ፡ ፴፫ ።

፲፮ ፤ ወአበዊነሂ ፡ አፍለስዎ ፡ ኀበ ፡ ሴኬም ፡ ወተቀ ብረ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ ዘተሣየጦ ፡ አብርሃም ፡ በወ ርቁ ፡ እምኀበ ፡ ደቂቀ ፡ ኤሞር ፡ በሴኬም ፡

ከኤሞር ፡ ልጅ ፡ ከሴኬም ፡ አብርሃም ፡ [illegible] ፡ ቀበሩት ።

አንድም ፡ ሴኬምና ፡ ሴኬም ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ አብርሃም ፡ ከኤሞር ፡ ልጅ ፡ በወ ርቁ ፡ በገዛው ፡ በሴኪም ፡ ቀበሩት ፡ ምን ፡ ባለሟል ፡ ቢሆን ፡ የራሱን ፡ ነገር ፡ መና ገር ፡ የሚቻለው ፡ የለምና ፡ አባቴ ፡ ከግ ብፅ ፡ አውጥተህ ፡ በከነዓን ፡ እንድትቀብ ረኝ ፡ ከዚህ ፡ እንዳትቀብረኝ ፡ ማልልኝ ፡ ብሎ ፡ አምሎኛልና ፡ አውጥቼ ፡ ልቅበር ፡ ንገሩልኝ ፡ አለ ፡ ነገሩለት ፡ አውጥተህ ፡ ቅበር ፡ አለው ፡ ባለሟል ፡ ነውና ፡ ወይዛ ዝሩ ፡ መኳንንቱ ፡ ተከትለውት ፡ ሂደዋ ል ፡ ሰባ ፡ ቀን ፡ አልቅሰው ፡ ቀብረውት ፡ ተመልሰዋል ፡ ከመዝኑ ፡ ላሐ ፡ ግብፅ ፡ እስኪሉ ፡ ድረስ ፡ የከነዓን ፡ ሰዎች ፤ ዘፍ ጥ ፡ ፳፫ ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ። ኢያ ፡ ፳፬ ፡ ፴፪ ።

፲፯ ፤ ወአመ ፡ በጽሐ ፡ ዕድሜሁ ፡ ዘአሰፈዎ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ በመሐላ ፡ በዝኀ ፡ ሕዝብ ፡

እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ ባርኮ ፡ እባ ርከከ ፡ አስተባዝኖ ፡ አስተባዝኃከ ፡ ብሎ፡ ምሎ ፡ የነገረው ፡ ተስፋ ፡ የሚፈጸምበት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ በዙ ፡

ወመልኡ ፡ ብሔረ ፡ ግብፅ ፡

ግብፅን ፡ መሉ ፡ በግብፅ ፡ መሉ ፡ እምእን ሞሙ ፡ እምአንሞሙ ፡ ይላል ፡ ከሠፈራ ቸው ፡ ከድንኳናቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ዘፀአ ፡ ፩ ፡ ፯ ።

፲፰ ፤ እስከ ፡ አመ ፡ ነግሠ ፡ ካልእ ፡ ንጉሥ ፡ ለብ ሔረ ፡ ግብጽ ፡ ዘኢየአምሮ ፡ ለዮሴፍ ፡

ዮሴፍን ፡ የማያውቀው ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ በግብጽ ፡ እስቲነግሥ ፡ ድረስ ፡ ሐተታ ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ በእልፍኝ ፡ ተወልዶ ፡ በእልፍኝ ፡ ያድጋልና ፡ ይህስ ፡ ዮሴፍ ፡ ባለሟል ፡ ነው ፡ ከዚያው ፡ ይወጣል ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ ዮሴፍ ፡ ለቤተ ፡ መንግ ሥቱ ፡ ያደረገውን ፡ ወረታ ፡ የማያውቅ ።

አንድም ፡ ዮሴፍን ፡ የማይወድ ፡ (ጥቅ) ፡ አእመርኩከ ፡ ሙሴ ፡ ወልደ ፡ እንበረም ፡ ወኪያከሙ ፡ አእመርኩ ፡ እምኵሉ ፡ አሕዛበ ፡ ምድር ፡ እንዲል ።

፲፱ ፤ ወውእቱ ፡ ተጠቢቦ ፡ አሕመሞሙ ፡ ለአበዊነ ፡

እሱም ፡ ተተንኩሎ ፡ ባባቶቻችን ፡ መከራ ፡ አጸናባቸው ፡ ላዕላይ ፡ ግብፅና ፡ ታሕታይ ፡ ግብጽ ፡ ይዋጋሉ ፡ ላዕላይ ፡ ግብጽ ፡ ድል ፡ ያደርጓቸዋል ፡ አንድ ፡ ቀንም ፡ ባሮቻችን ፡ እስራኤልንም ፡ እለፉ ፡ በኋቸው ፡ ይገዙን ፡ አሉ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ተሰልፈው ፡ ያሉበትን ፡ ፈጅተው ፡ የአሕዛብ ፡ ድምበር ፡ የለውም ፡ ደርበህ ፡ በለው ፡ ብለው ፡ ከነሱ ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ፈጅተውባቸዋል ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ እየጨፈሩ ፡ ሲመለሱ ፡ አይተው ፡ አማቾችን ፡ አፈኛ ፡ ቢመለስ ፡ ወደኛ ፡ ወይኛ ፡ ወይኛ ፡ እንግዲህማ ፡ እኛንስ ፡ ተመልሰው ፡ ሊያጠፉን ፡ አይደለምን ፡ ብለው ፡ መክረውባቸዋል ። አንድም ፡ ያዕቆብን ፡ ቀብረው ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ባመት ፡ ባመት ፡ ከነዓን ፡ ይወጡ ፡ ነበርና ፡ እነዚያ ፡ ከላይ ፡ እሊህ ፡ ከታች ፡ ሁነው ፡ ይወጉናል ፡ ብለው ። አንድም ፡ ከንጉሥ ፡ መምክሮን ፡ ተላልከው ፡ ይወጉናል ፡ ብለው ፡ መክረውባቸዋል ፡ ሴት ፡ ሴቱ ፡ ኖራ ፡ ይውገጥ ፡ ወንድ ፡ ወንዱ ፡ ጡብ ፡ ይርገጥ ፡ ብለው ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይደክማሉ ፡ ዘር ፡ አይዘሩም ፡ አይበዙም ፡ ብለው ፡ ነው ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ የእስራኤል ፡ ብዛት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ነውና ፡ እየበዙ ፡ ሄዱ ፡

ወአዘዘ ፡ ይቅትሉ ፡ ኵሎ ፡ እጓለ ፡ ተባዕተ ፡

ወንድ ፡ እየተወለደ ፡ ለሞት ፡ ሴት ፡ እየተወለደ ፡ ለትሎት ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ አዋጅ ፡ ነግሯል ። ዘፀአ ፡ ፩ ፡ ፳፪ ፡

፳ ፤ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ ተወልደ ፡ ሙሴ ፡

ወንድ ፡ እየተወለደ ፡ ለሞት ፡ ሴት ፡ እየተወለደ ፡ ለትሎት ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ አዋጅ ፡ በነገረበት ፡ ወራት ፡ ሙሴ ፡ ተወለደ ፡

ወኮነ ፡ ሠናየ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡

በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የተወደደ ፡ ብላቴና ፡ ሆነ ፡ ለዝንቱ ፡ ሕፃን ፡ ይከድኖ ፡ ሞገስ ፡ እምንእሱ ፡ ወተሰብሐ ፡ ገጹ ፡ ለሙሴ ፡ እንዲል ፡ በፊቱ ፡ ብርሃን ፡ ተስሎበት ፡ ተወልዷል ፡

ወሐፀንዎ ፡ ሠለስተ ፡ አውራኀ ፡ በቤተ ፡ አቡሁ ፡

በናት ፡ ባባቱ ፡ ቤት ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሠውረው ፡ አኖሩት ፡ ፋሃ ፡ ሲፖራ ፡ የሚባሉ ፡ ሁለት ፡ ዓቀብተ ፡ መወልዳቶች ፡ ሹሟል ፡ መልኩን ፡ አይተው ፡ ወሰሐቦን ፡ አርአያሁ ፡ መንገለ ፡ አሚን ፡ ይላል ፡ ለዝሰ ፡ ዘፈጠሮ ፡ ይቅትሎ ፡ ብለው ፡ ትተውታል ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ የሴትና ፡ የወንድ ፡ ድምፅ ፡ ተለይቶ ፡ ይታወቃልና ፡ ለናንተም ፡ ለኛም ፡ መልካም ፡ አይደለም ፡ ለዚህ ፡ ብላቴና ፡ እወቁለት ፡ ብለዋቸዋል ፡ ወነፈቀት ፡ ይላል ፡ ሣጥን ፡ ጠርበው ፡ በውስጥ ፡ ባዘቶውን ፡ ጐዝጉዘው ፡ ብላቴናውን ፡ አድርገው ፡ ወቀብዓቶ ፡ አስፈሊጡ ፡ ይላል ፡ ሙጫ ፡ አደሮማር ፡ ሰም ፡ ቀብተው ፡ ዘፀአ ፡ ፪ ፡ ፪ ። ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫ ።

፳፩ ፤ ወእምዝ ፡ ገደፍዎ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ።

ከባሕር ፡ ወስደው ፡ ከጀጀባና ፡ ከጀጀባ ፡ መካከል ፡ ጣሉት ፡ ሌሊት ፡ ሌሊት ፡ እናቱ ፡ እየሄደች ፡ ታጠባዋለች ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ እኅቱ ፡ ማርያም ፡ ስትጠብቀው ፡ ትውላለች ፡ አገ



አለ ፡ ሣጥኑን ፡ አንሥቶ ፡ ሲጥለው ፡ ይሰበራል ፡ ብላቴናው ፡ ይወድቃል ፡ አንሥቶ ፡ ይበላዋልና ፡ እንዳይበላው ።

ወአንሥአቶ ፡ ወለተ ፡ ፈርዖን ፡ ወሐፀነቶ ፡ ወረሰየቶ ፡ ወልደ ፡

ተርሙት ፡ ወለተ ፡ ፈርዖን ፡ ልጅ ፡ ይሆነኛል ፡ ብላ ፡ አንሥታ ፡ አሳደገችው ፡ ከባሕር ፡ ለምን ፡ ሂዳ ፡ አገኘታዋለች ፡ ቢሉ ፡ ኮብሽ ፡ የሚባል ፡ ደዌ ፡ ነበረባትና ፡ ለመታጠብ ። አንድም ፡ ዓሣ ፡ አንበሪ ፡ አዞ ፡ ጉማሬ ፡ ታመልክ ፡ ነበርና ፡ ለማማረት ፡ ሂዳ ። አንድም ፡ ነጋዴ ፡ ወዳጅ ፡ ነበራት ፡ ለመገናኘት ። አንድም ፡ ለመዋኘት ፡ ሂዳ ፡ በኀርኀሪ ፡ መንግሥት ፡ የነገሥታት ፡ ልጆች ፡ ከባሕር ፡ እየሄዱ ፡ ይዋኙ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ወአንሶሰዋ ፡ አዋልዲሃ ፡ ውስተ ፡ ገበዘ ፡ ተከዚ ፡ ይላል ፡ ደንገጥሮችዋ ፡ እየተመላለሱ ፡ ሲጨዋወቱ ፡ አይታ ፡ የነጋድያን ፡ ዕቃ ፡ ይሆናል ፡ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ አስቀርቶባቸዋል ፡ እስቲ ፡ ወዲህ ፡ አምጡት ፡ አለች ፡ አመጡላት ፡ ከፍታ ፡ ብታይ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ብላቴና ፡ አገኘች ፡ ይህስ ፡ ልጅ ፡ ይሆነኛል ፡ አሳድገዋለሁ ፡ አለች ፡ እኅቱ ፡ ማርያም ፡ ከደንገጥሮችዋ ፡ ድፋት ፡ ያላት ፡ ነበረችና ፡ ቀርባ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ልጅ ፡ ይሆንሻል ፡ አሳድጊው ፡ ሞግዚትም ፡ ትናንት ፡ ልጅዋ ፡ የሞተባት ፡ አንዲት ፡ ዕብራዊት ፡ አለች ፡ እሷን ፡ አመጣልሻለሁ ፡ ብላ ፡ ሂዳ ፡ እናቱን ፡ ጠርታ ፡ ይዛ ፡ መጣች ፡ ሕፅኒዮ ፡ በሠናይ ፡ ደህና ፡ አድርገሽ ፡ አሳድጊልኝ ፡ ልብስሽን ፡ ቀለብሽን ፡ እሰጥሻለሁ ፡ ብላ ፡ ሰጠቻት ፡ እናቱ ፡ ሞግዚት ፡ አባቱ ፡ የሞግዚት ፡ ባል ፡ እኅቱ ፡ የሞግዚት ፡ ደንገጥር ፡ ሁነው ፡ አሳድገውታል ፡ ሲያሳድጉትም ፡ ተስፋ ፡ ያልተነገረላቸው ፡ የነዚህ ፡ የአሕዛብ ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ እንዳይመስልህ ፡ ተስፋ ፡ የተነገረላቸው ፡ የእስራኤል ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡ እያሉ ፡ እየመከሩ ፡ አሳድገውታል ፡ ዘፀአ ፡ ፪ ፡ ፲ ።

፳፪ ፤ ወተምህረ ፡ ሙሴ ፡ ተግሣጸ ፡

ሙሴም ፡ መታጠቅ ፡ መፍታትን ፡

ወኵሎ ፡ ጥበበ ፡ ግብጽ ፡

ያጠ ፡ ሥርን ። አንድም ፡ ነፍጥ ፡ መጠረቅ ፡ ጋሻ ፡ መሰኀድን ፡ ፋል ፡ የሚባል ፡ ጥንቆላን ፡ ተማረ ፡

ወኮነ ፡ ጽኑዐ ፡ በቃሉ ፡ ወበምግባሩ ፡

በሚናገረው ፡ ነገር ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አዋቂ ፡ ሆነ ።

፳፫ ፤ ክፍል ፡ ፲፩ ። ወአመ ፡ ተፈጸመ ፡ አርብዓ ፡ ዓመት ፡ ሀለየ ፡ በልቡ ፡ የሐውጾሙ ፡ ለአኃዊሁ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ።

በናት ፡ ባባቱ ፡ ቤት ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ በቤተ ፡ ፈርዖን ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ አርባ ፡ ይሆናል ፡ አርባው ፡ ዓመት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ወንድሞቹ ፡ እስራኤልን ፡ ሊጐበኛቸው ፡ ወደደ ፡ ጌታ ፡ አርባ ፡ ጹሞ ፡ ምእመናንን ፡ በትምህርት ፡ መጐብኘቱን ፡ ያጠይቃል ፡ ዘፀአ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።

፳፬ ፤ ወረከበ ፡ አሐደ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ እንዘ ፡ ይገፍዖ ፡ ለካልኡ ፡

ሲሄድ ፡ ዕብራዊና ፡ ግብፃዊ ፡ ተጣልተው ፡ አገኘ ፡

ወተበቀለ ፡ ሎቱ ፡ ለውእቱ ፡ ዘተገፍዐ ፡ ወቀተሎ ፡ ለግብፃዊ ።

ለዕብራዊ ፡ ረድቶ ፡ ግብፃዊን ፡ ገሎ ።

ወደፈኖ ፡ ውስተ ፡ ኆፃ ።

ከአሸዋ ፡ ቀላቀለው ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ተጣልተዋል ፡ ቢሉ ፡ በዓሣ ፡ ቀረጥ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ምክንያት ። አንድም ፡ ዕብራዊ ፡ በበጠበጠው ፡ እንዶድ ፡ ግብፃዊ ፡ ልጠብበት ፡ ብሷል ፡ እሱ ፡ በበጠበጠው ፡ እንዶድ ፡ ተው ፡ እንጅ ፡ ይጠብበት ፡ ብሎታል ፡ አሁን ፡ ገላውን ፡ እንደ ፡ ቈርበት ፡ ሥጋውን ፡ እንደ ፡ እንዶድ ፡ ደሙን ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ አድርጌ ፡ ባጥብበት ፡ ታድነዋለህ ፡ ብሎታል ፡ ወነጸረ ፡ ሙሴ ፡ ለፌ ፡ ወለፌ ፡ ይላል ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አይቶ ፡ ክቡደ ፡ መዝራዕት፡ ነውና፡ በጥፌ፡ ቢለው፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ካሸዋ ፡ ቀላቅሎታል ፡ ምሳሌ ፡ ነው፡ ሙሴ ፡ የጌታ ፡ ዕብራዊ ፡ የአዳም ፡ ግብፃዊ ፡ የዲያብሎስ ፡ ጥፃ ፡ የሦስቱ ፡ አርእስተ ፡ ኃጣውእ ። አንድም ፡ የመስቀል።

፳፭ ፤ ወመሰሎ ፡ ዘየአምሩ ፡ አኃዊሁ ፡ ከመ ፡ በእዴሁ ፡ ይሁቦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኀኒተ ፡

ወንድሞቹ ፡ እስራኤል ፡ በሱ ፡ እጅ ፡ እንዲያድናቸው ፡ የሚያውቁ ፡ መስሎት ፡ ነበር ፡

ወእሙንቱሰ ፡ ኢለበዉ ፡

እነሱ ፡ ግን ፡ አላወቁም ። አንድም ፡ አኃዊሁ ፡ አይሁድ ፡ ናቸው ፡ በጌታ ፡ እጅ ፡ እንዲያድናቸው ፡ አለማወቃቸውን ፡ ማወቁን ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እነሱም ፡ አላወቁም ።

፳፮ ፤ ወበሳኒታ ፡ ረከበ ፡ ክልኤተ፡እምውስቴቶሙ፡ እንዘ ፡ ይትበአሱ ፡

በነጋው ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ተጣልተው ፡ አገኘ ፡ ዕብራዊና ፡ ዕብራዊ ፡ ናቸው ።

ወፈቀደ ፡ ይዕርቆሙ ፡

ሊያስታርቃቸው ፡ ወዶ ፡

ወይቤሎሙ ፡ ናሁ ፡ አንትሙሰ ፡ አኃው ፡ አንትሙ ፡

እናንተማ ፡ ወንድማማቾች ፡ አይደላችሁምን ፡

ለምንት ፡ ትትዔመፁ ፡ በበይናቲክሙ ፡

እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ለምን ፡ ትጣላላችሁ ፡ አላቸው ።

፳፯ ፤ ወይቤሎ ፡ ዝኩ ፡ ዘይዔምፆ ፡ ለካልኡ ፡ መኑ ፡ ሤመከ ፡ መልአከ ፡ ወመኰንነ ፡ ላዕሌነ ።

ጠብ ፡ አንሽው ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ ፈራጅ፡ አድርጎ ፡ ማን ፡ ሹሞሃል ፡ አለው ፡ ጌታን፡ በመቤቱ ፡ ጣ ፡ ትንብር ፡ ዘንተ ፡ ማስ ታቸውን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፳፰ ፤ ወሚመ ፡ ትቅትለኒኑ ፡ ትፈቅድ ፡ ኪያየኒ ፡ በከመ ፡ ቀተልኮ ፡ ትማልም ፡ ለግብፃዊ ።

ወይስ ፡ ትናንት ፡ ያን ፡ ግብፃዊ ፡ እንደ ገደልኸው ፡ እኔንም ፡ ልትገለኝ ፡ ትወዳለህን ፡ አለው ፡ ምነው ፡ ወነጸረ ፡ ሙሴ ፡ ለፌ ፡ ወለፌ ፡ ብሎ ፡ የለም ፡ ቢሉ ፡ እሱ ፡ አላየም ፡ አለ ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አላየውም ፡ አለ፡ በቅጠል፡ ቀዳዳ፡ ሁኖ፡ ሲመለከተው፡ የነበረ ፡ ነው ። አንድም ፡ ያዳነው ፡ ሰው ፡ የነገረው ፡ ነው ፡ ዛሬ ፡ ወንድሜ ፡ ሙሴ ፡ ባይኖር ፡ ያ ፡ ግብጻዊ ፡ ሊገለኝ ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ አመስጋኝ ፡ አማሳኝ ፡ እንዲሉ ። አንድም ፡ ያዳነው ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ድኃን ፡ ካሳደገ ፡ ያነቀ ፡ ጸደቀ ፡ እንዲሉ ።

፳፱ ፤ ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ነገር ፡ ተኀጥአ ፡ ሙሴ ።

ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ሙሴ ፡ ኮበለለ ፡ ወከመ፡ዝ፡ ኮነ፡ዝ፡ነገር ፡ ክሡተ ፡ ወዝርዙረ ፡ ይላል ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ከሁሉ ፡ ደርሷልን ፡ ፈርዖን ፡ የሰማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይጣላኝ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡

ወነበረ ፡ ፈላሴ ፡ ብሔረ ፡ ምድያም ፡

በምድያም ፡ አገር ፡ ስደተኛ ፡ ሁኖ ፡ ኖረ ፡ ሲሄድ ፡ ውሎ ፡ ከውኃ ፡ ዳር ፡ አረፈ ፡ ወሀለዋ ፡ ሰብዑ ፡ አዋልዲሁ ፡ ለማርያ ፡ ምድያም ፡ ይላል ፡ ዮቶር ፡ ካህነ ፡ ምድያም ፡ ሰባት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፡ ወንድ ፡

www.ethiopianorthodox.org



ልጅ ፡ ግን ፡ አልነበረውም ፡ ሰባቱ ፡ ሁሉ ፡ በግ ፡ ይጠብቃሉ፡ ውኃ፡ ሊያጠጡ፡ መጥተው ፡ የሚከፍትላቸው ፡ አጥተው ፡ ቆሙ ፡ ምነው ፡ አታጠጡም ፡ አላቸው ፡ መላው ፡ ኖሎት ፡ እንጅ ፡ ካልተሰበሰቡ ፡ አይሆንልንም ፡ አሉት ፡ ይኸን ፡ ሲነጋገሩ ፡ ኖሎት ፡ ደረሱ ፡ ከፍተው ፡ እናጠጣለን ፡ ሲሉ ፡ ምነው ፡ እኛ ፡ እያለን ፡ አሉ ፡ ከመቼ ፡ ወዲህ ፡ ነው ፡ እኛ ፡ ከፍተን ፡ እናንት ፡ የምታጠጡ ፡ አሏቸው ፡ ዛሬስ ፡ ለኛም ፡ ለናንተም ፡ የማይል ፡ ሰው ፡ አለ ፡ ይፍረደን ፡ አሉ ፡ ምነው ፡ ግዳይ ፡ ለፈለመ ፡ ውኃ ፡ ለቀደመ ፡ አይደለም ፡ ተዋቸው ፡ እንጅ ፡ እነሱ፡ ያጠጡ፡ አላቸው ፡ ምነው ፡ እኛ ፡ ከፍተን ፡ አሉት፡ መልሳችሁ ፡ ግጠሙት ፡ አላቸው ፡ ገጠሙት ፡ ብቻውን ፡ ከፍቶ ፡ አጠጥቶላቸው፡ ሂደዋል ፡ መልካም ፡ ልጆቼ ፡ ዛሬስ ፡ በጎ ፡ እናንተም ፡ በጊዜ ፡ መጣችሁ ፡ በጎቼም ፡ ጠግበዋል ፡ አላቸው ፡ ዛሬማ ፡ እንጅ ፡ አነጋገሩ ፡ ዕብራዊ ፡ አጠማጠሙ ፡ ግብጻዊ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ አግኝተን ፡ እሱ ፡ አጠጣልን ፡ አሉት ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሰው፡ ይዞ፡ ይመጧል፡ እንጅ፡ ትቶ፡ ይመጧልን፡ አላቸው ፡ ሲፖራ ፡ ባሏ ፡ የሚሆን ፡ ነውና፡ አሁንም ፡ አላጣውም ፡ ብላ ፡ ሂዳ ፡ ይዛው፡ መጣች ፡ ከዚያው ፡ አደረ ፡ ሌሊት ፡ ሲተሳሰቡ ፡ አድረዋል ፡ ሙሴ ፡ አሁን ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ከልጆቼ ፡ አንዲቱን ፡ ሰጥቶኝ ፡ በግ ፡ እየጠበቅሁ ፡ ብኖር ፡ እያለ ፡ ሲያስብ ፡ አድሯል ፡ እሱም ፡ አሁን ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ከልጆቼ ፡ አንዲቱን ፡ ሰጥቸው ፡ በግ ፡ እየጠበቀልኝ ፡ ቢኖር ፡ እያለ ፡ ሲያስብ ፡ አድሯል ፡ በነጋው ፡ አሰናብተኝ ፡ ልሂድ ፡ አለው ፡ ወዴት ፡ ትሄዳለህ ፡ አለው ፡ የምሄድበትን ፡ አላውቀውም ፡ ከፈርዖን ፡ ተጣልቼ ፡ እግሬ ፡ እንዳወጣኝ ፡ እሄዳለሁ ፡ አለው ፡ መንገድ ፡ ቢሄዱት ፡ ቢሄዱት ፡ ውኃ ፡ ቢቀዱት ፡ ቢቀዱት ፡ አያልቅም ፡ ከልጆቼ ፡ አንዲቱን ፡ ሰጥቼህ ፡ ከዚህ ፡ በግ ፡ እየጠበቅህ ፡ አትኖርም ፡ አለው ፡ ምን ፡ ይከፋል ፡ አለው ፡ ሲፖራን፡ሰጥቶት፡በግ፡ እየጠበቀ፡ ኑሯል ፡

ወወለደ ፡ በህየ ፡ ክልኤተ ፡ ደቂቀ ።

በምድያም ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ወለደ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ጌርሣም ፡ አለው ፡ በስደት፡ ማለት ፡ ነው ፡ ፈላሲ ፡ አነ ፡ ብሔረ ፡ ነኪር ፡ ሲል ፡ ይህ ፡ የሱ ፡ ፈንታ ፡ ነው ፡ ገዝሮታል ፡ ሁለተኛ ፡ ወለደ ፡ ስሙን ፡ ኤልዛር ፡ ብሎታል ፡ በረድኤት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ፈጣሪ ፡ ዘአቡየ ፡ ረድአኒ ፡ ሲል ፡ ይህ ፡ የሷ ፡ ፈንታ ፡ ነው ፡ አልተገዘረም ፡ ዘፀአ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ።

፴ ፤ ወተፈጺሞ ፡ አርብዓ ፡ ዓመት ፡

አርባው ፡ ዓመት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በቤተ ፡ ፈርዖን ፡ ኻያ ፡ በእናት ፡ ባባቱ ፡ ቤት ፡ ኻያ ፡ ሰማንያ ፡ ይሆናል ፡ በምድያም ፡ የኖረውን ፡ ብቻ ፡ ቈጥሮ ፡ ወተፈጺሞ ፡ አርብዓ ፡ ዓመት ፡ አለ ፡

አስተርአዮ ፡ በገዳም ፡ በደብረ ፡ሲና ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነደ ፡ እሳት ።

ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ ነደ ፡ እሳትን ፡ መስሎ ፡ በነደ ፡ እሳት ፡ አጠገብ ፡ በነደ ፡ እሳት ፡ አምሳል ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ታየው ፡ ተነጋገረው፡ ዘፀአ፡ ፫፡ ፪። ዘዳግ፡ ፴፫፡ ፲፮ ።

፴፩ ፤ ወርእዮ ፡ ሙሴ ፡ አንከረ ፡ ግርማሁ ፡

ሙሴም ፡ መልኩን ፡ አይቶ ፡ አደነቀ ፡

ወቀርበ ፡ ይጠይቆ ።

ሊረዳው ፡ ወዶ ፡ በጎቹን ፡ ከፈረሰ ፡ ግንብ፡ አግብቶ ፡ ዘግቶባቸው ፡ ሂዶ ፡ ለጊዜው ፡

እንዳይጠፋበት ፡ ነው ፡ ፍጻሜው ፡ ግን ፡
ጥበብ ፡ እንመረምራለን ፡ ባላችሁ ፡ ጊዜ ፡
ሁለት ፡ ልብ ፡ አትሁኑ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡
ሁኑ ፡ ሲል ፡ ኢትኅፈር ፡ ኀቤሃ ፡ ለጥበብ ፡
በክልኤ ፡ ልብ ፡ አላ ፡ ኩን ፡ ከመ ፡ ዘይዘ
ርዕ ፡ ወየአጽድ ፡ እንዲል ። አንድም፡ ሙ
ሴ ፡ የመናንያን ፡ አምሳል ፡ ነው ፡ እንመ
ንናለን ፡ ባላችሁ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያው ፡ አት
ሂዱ ፡ ገንዘባችሁን ፡ አከናውናችሁ ፡ መጽ
ውታችሁ ፡ ሂዱ ፡ ለማለት ፡ ለአብነት ፡
ሐመልማል፡ የእስራኤል፡ የሰውነታቸው ፡
ነበልባል ፡ የመከራቸው ፡ ሐመልማሉ ፡
ነበልባሉን ፡ አለማጥፋቱ ፡ እስራኤል ፡
መከራውን ፡ ግብር ፡ ገብተን ፡ ቀኖና ፡
ይዘን ፡ እናርቀው ፡ አላሉምና ፡ ነበልባሉ ፡
ሐመልማሉን ፡ አለማቃጠሉ ፡ መከራው ፡
እስራኤልን ፡ ፈጽሞ ፡ አላጠፋቸውምና ።
አንድም ፡ ሐመልማል ፡ የመቤታችን ፡
ነበልባል ፡ የጌታችን ፡ ቅዱስ ፡ ኤፍሬም ፡
እንደ ፡ መሰለው ። አንድም፡ ሐመልማል ፡
የትስብእት ፡ ነበልባል ፡ የመለኮት ፡ ቅዱ
ስ ፡ ቄርሎስ ፡ እንደ ፡ መሰለው ።

፴፪ ፤ ወነበቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይቤሎ ፡ አነ ፡
ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ አበዊከ ፡ አምላከ ፡
አብርሃም ፡ ወአምላከ ፡ ይስሐቅ ፡ ወአምላከ፡ ያዕቆብ፡

ያባቶችህ ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያ
ዕቆብ ፡ አምላክ ፡ የምሆን ፡ እኔ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ነኝ ፡ አለው ፡ አስተርአዮ ፡ መል
አክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ አልነበረ
ምን ፡ ምነው ፡ ከዚህ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ መልአክ ፡ ካለ ፡
ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እግዚአብሔር ፡
ካለ ፡ ዘንድ ፡ መላክ ፡ አይለይምና ። አን
ድም ፡ ጌታን ፡ ቅሉ ፡ መልአክ ፡ ይለዋል ፡

ወርዕደ ፡ ሙሴ ።

ሙሴም ፡ ደነገጠ ፡

ወስእነ ፡ ጠይቆ ፡

መረዳት ፡ ተሳነው ፡ ዘፀአ ፡ ፫ ፡ ፮ ።

፴፫ ፤ ወይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍታሕ ፡ አሣዕ
ኒከ ፡ እምእገሪከ ፡

እግዚአብሔርም ፡ ጫማህን ፡ ከእግርህ ፡
አውልቅ ፡ አለው ፡

እስመ ፡ ምድር ፡ ኀበ ፡ ትከይድ ፡ ቅድስት ፡ ይእቲ ።

ይህች ፡ የቆምህባት ፡ ምድር ፡ የከበረች ፡
ናትና ፡ ለጊዜው ፡ በዘፈቀደ ፡ ታይቶባ
ታል ፡ ፍጻሜው ፡ ግን ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡
የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምሳሌ ፡ ናት ፡ ከቤተ
ክርስቲያን ፡ በጫማ ፡ መግባት ፡ አይገ
ባም ፡ ሲል ፡ ያም ፡ የሥጋዊ ፡ አምሳል ፡
ነው ፡ የሥጋዊ ፡ ነገር ፡ ከሚነገርበት ፡
በጫማ ፡ ሁኖ ፡ መግባት ፡ አይገባም ፡
ሲል ። አንድም ፡ ተልከህ ፡ የምትሄድባት፡
ግብፅ ፡ ጽንዕት ፡ ናትና ፡ አሣዕነ ፡ ፍርሃ
ትን ፡ ከልቡናህ ፡ አርቅ ፡ ሲለው ፡ ነው ።
አንድም ፡ ከግብፅ ፡ ከተመለስህ ፡ በኋላ ፡
የምትሠራልህ ፡ ሕግ ፡ ደግ ፡ ናትና ፡ ሊማ
ደ ፡ የዮቶርን ፡ ተው ፡ ሲለው ፡ ነው ። አን
ድም ፡ ፋል ፡ የሚባል ፡ ጥንቆላ ፡ ነበረው ፡
ተው ፡ ሲለው ፡ ነው ።

፴፬ ፤ ርእየ ፡ ርኢኩ ፡ ሕማሞሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ ወሰ
ማዕኩ ፡ ገዓሮሙ ፡ ወወረድኩ ፡ አድኅኖሙ ።

የወገኖቼ ፡ የእስራኤልን ፡ መከራቸውን ፡
አይቼ ፡ ኀዘናቸውን ፡ ሰምቼ ፡ ላድናቸው፡
መጣሁ ፡ ወረድኩ ፡ በረድኤት ፡ የቀደ
መች ፡ ራሔል ፡ ናት ፡ ባሏ ፡ ሮቤልም ፡
ስምዖንም ፡ ይሉታል ፡ ታሞ ፡ ሙቶም ፡
ቢሉ ፡ በሱ ፡ ምትክ ፡ ጡብ ፡ እርገጭ ፡
ብሎ ፡ ገፍቶ ፡ ጣላት ፡ ብትደነግጥ ፡ ሁለ
ት ፡ ፅንስ ፡ አስወረዳት ፡ አንሸው ፡ ይለ
ኛል ፡ መስሏት ፡ ቀና ፡ ብላ፡ አየች፡ የሰው፡
ደም ፡ ያጸናዋል ፡ እንጅ ፡ ምን ፡ ይለዋል ፡



አብረሽ ፡ እርገጭው ፡ አላት ፡ በዚህ ፡
ጊዜ ፡ ኢሀሎኑ ፡ አምላከ ፡ እስራኤል ፡
በዝ ፡ ሰማይ ፡ ብላ ፡ እንባዋን ፡ ሽቅብ ፡
ረጭታዋለች ፡ የሷን ፡ እንባ ፡ ሠረገላ ፡
አድርጎ ፡ እስራኤልን ፡ ከግብፅ ፡ አውጥ
ቷቸዋልና፡ ሰማዕኩ፡ ገዓሮሙ፡ ለሕዝብየ፡
ወወረድኩ ፡ አድኅኖሙ ፡ ያሰኘው ፡ ይህ ፡
ነው ፡ አብርሃምም ፡ በነፍስ ፡ ይካሰስላ
ቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያጠይቃል ፡

ወይእዜኒ ፡ ነዓ ፡ እፈኑከ ፡ ብሔረ ፡ ግብፅ ።

አሁንም ፡ ና ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ልላክህ ፡ አለ
ው ፡ ንጉሣዊ ፡ አነጋገር ፡ ንጉሥ ፡ ከባጠ
ገቡ ፡ ያለውን ፡ ና ፡ ልላክህ ፡ እንዲል ፡
አዒ ፡ ይላል ፡ ነዓ ፡ እፈኑከ ፡ ማለት ፡ ነው፡
(ታሪክ)፡ ጌታ ፡ ሙሴን፡ ሂደህ ፡ ፈርዖንን ፡
ፈንዎሙ ፡ ለሕዝብየ ፡ ይግበሩ ፡ በዓልየ ፡
ብሎሃል ፡ በለው ፡ አለው፡ ኅሥሥ፡ ባዕደ፡
ዘትልእክ ፡ እስመ ፡ ላዕላዓ ፡ ልሳን ፡ አነ ፡
ድዳ ፡ ነኝ ፡ መናገር ፡ አይሆንልኝምና ፡
ሌላ ፡ ላክ ፡ አለው ፡ መኑ ፡ ወሀበ ፡ አፈ ፡
ለእጓለ ፡ እመሕያው ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ አን
ደበትን ፡ የፈጠረ ፡ ማን ፡ ይመስልሃል ፡
እኔ ፡ አይደለሁምን ፡ በዚያውም ፡ ላይ ፡
አሮን ፡ እኁከ ፡ ይኩንከ ፡ አፈ ፡ አንተ ፡
ከኔ ፡ እየሰማህ ፡ ለወንድምህ ፡ ለአሮን ፡
ንገረው ፡ እሱ ፡ ካንተ ፡ እየሰማ ፡ ለነሱ ፡
ይንገራቸው ፡ አለው ፡ ማን ፡ አለህ ፡ ቢለ
ኝሳ ፡ አለው ፡ አህያ ፡ ሸራህያ ፡ አልሻዳይ፡
በለው ፡ አለው ፡ አህያ ፡ ሸራህያ ፡ ዘሀሎ ፡
ወይሄሉ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አልሻዳይ ፡ አም
ላከ ፡ ዕብራውያን ፡ አምላክ ፡ ተስፋ ፡ ማ
ለት ፡ ነው ፡ ምን ፡ ምልክት ፡ አለህ ፡ ቢሉ
ኝሳ ፡ አለው ፡ ምንት ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡
በጅህ ፡ ምን ፡ ይዘሃል ፡ አለው ፡ ሊነግ
ረው ፡ ቢሻ ፡ በትር ፡ አለው ፡ ግድፎ ፡ ጣ
ለው ፡ አለው ፡ ቢጥለው ፡ እባብ ፡ ሆነ ፡
ፈርቶ ፡ ይበላኛል ፡ ብሎ ፡ ሸሸ ፡ ንሥአ ፡
በዘነቡ ፡ ጫፉን ፡ ይዘህ፡ አንሣው፡ አለው፡
ቢያነሣው ፡ በትር ፡ ሆኗል ፡ ምሳሌ ፡ ነው፡
ቢጥለው ፡ እባብ ፡ መሆኑ ፡ እስራኤል ፡
ግብፅ ፡ ወርደው ፡ በመከራው ፡ ለመለወ
ጣቸው ፡ ቢያነሣው ፡ በትር ፡ መሆኑ ፡
በሙሴ ፡ ሥልጣን ፡ እስራኤል ፡ ከግብጽ፡
ለመውጣታቸው ፡ ሁለተኛ ፡ እጅህን ፡
ከብብትህ ፡ አግብተህ ፡ አውጣው ፡ አለው
አግብቶ ፡ ቢያወጣው ፡ ለምፅ ፡ ሆነ ፡
መልሰህ ፡ አግብተህ ፡ አውጣው ፡ አለው ፡
አግብቶ ፡ ቢያወጣው ፡ ደህና ፡ ሆነ ፡ ለም
ፅ ፡ መሆኑ ፡ እስራኤል ፡ ግብፅ ፡ ወርደው፡
በመከራው ፡ ለመለወጣቸው ፡ ምሳሌ ፡
አግብቶ ፡ ቢያወጣው ። ደህና ፡ መሆኑ ፡
እስራኤል ፡ ከግብፅ ፡ ለመውጣታቸው ፡
ምሳሌ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ኑ
ሯል ፡ ሂድ ፡ አላልሁህም ፡ ብሎታል ፡
ደንግጦ ፡ ምሽቱን ፡ ልጆቹን ፡ ይዞ ፡ ተነ
ሣ ፡ በመንገድ ፡ ለምሽቱ ፡ መላክ ፡ ሰይ
ፉን ፡ መዞ ፡ ታያት ፡ ሊጣላው ፡ ነው ፡
ብላ ፡ የሷ ፡ ፈንታ ፡ ኤልዛር ፡ አልተገዘ
ረም ፡ ነበረና ፡ ናሁ ፡ ደመ ፡ ግዝሮሁ ፡
ለወልድየ ፡ ይኩን ፡ ቤዛ ፡ ምትየ ፡ ብላ ፡
ገዝራዋለች ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለሱም ፡ ተገ
ልጦለታል ፡ ምነው ፡ ከሰልፍ ፡ የሚገባ ፡
ሰው ፡ ጓዝ ፡ ይዞ ፡ ነው ፡ የሚሄደው ፡ አለ
ው ፡ እኔማ ፡ እኔ ፡ ከሄድሁ ፡ ወጥቶ ፡ ወር
ዶ ፡ የሚመግባቸው ፡ የለም ፡ ብዬ ፡ ነው ፡
እንጅ ፡ አለው ፡ በል ፡ እጅህን ፡ ከዚህ ፡
ባሕር ፡ ስደደው ፡ አለው ፡ እጁን ፡ ሰደደ ፡
ያገኘኸውን፡ ይዘህ ፡ ውጣ ፡ አለው ፡ ደን
ጊያ ፡ ይዞ ፡ ወጣ ፡ ስበረው ፡ አለው ፡ ቢሰ
ብረው ፡ ከደንጊያ ፡ ውስጥ ፡ መንታ ፡
ዕፅ ፡ በቅላ ፡ አንድ ፡ ወገኗ ፡ ሲደርቅ ፡
አንድ ፡ ወገኗ ፡ እየለመለመ ፡ ትል ፡ ሲመ

www.ethiopianorthodox.org

ገብ ፡ አይቶ ፡ ይህን ፡ የሚመግብ ፡ ማን ፡
ይመስልሃል ፡ አለው ፡ ምሽቱን ፡ ልጆ
ቹን ፡ ትቶ ፡ ሂዷል ፡ ሙሴ ፡ ከምድያም ፡
አሮን ፡ ከጌሤም ፡ ተራከቡ ፡ በደብረ ፡
እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ በአንቀጸ ፡ ግብፅ፡
ተገናኝተዋል ፡ ነገረ ፡ እግዚአብሔርን ፡
ስለ ፡ ተጨዋወቱባት ፡ ደብረ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ተብላለች ።

## ክፍል ፡ ፲፪ ፡

፴፭ ፤ ለውእቱ ፡ ሙሴ ፡ ዘክሕድዎ ፡ ወይቤልዎ ፡
መኑ ፡ ሤመከ ፡ መልአከ ፡ ወመኰንነ ፡ ላዕሌነ ፡
ኪያሁ ፡ ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልአከ ፡ ወመድ
ኅነ ፡ በእደ ፡ መልአኩ ።

በኛ ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ ፈራጅ ፡ አድርጎ ፡ ማን ፡
ሹሞሃል ፡ ያሉት ፡ ሙሴ ፡ ነው ፡ ያሉት ፡
ሙሴን ፡ እግዚአብሔር ፡ የድኅነት ፡ ምክ
ንያት ፡ አድርጎ ፡ ላከው ፡

ዘአስተርአዮ ፡ በኀበ ፡ ዕፀ ፡ ጳጦስ ፡

በዕፀ ፡ ጳጦስ ፡ አጠገብ ፡ በታየው ፡ በተነ
ጋገረው ፡ በመልአኩ ፡ ባልደረብነት ።
አንድም ፡ በመባሕተ ፡ መኑ ፡ ትገብር ፡
ዘንተ ፡ ያሉት ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ ያሉት ፡
ጌታን ፡ እግዚአብሔር ፡ የድኅነት ፡ ምክ
ንያት ፡ አድርጎ፡ ላከው ፡ በእመቤታችን ፡
አጠገብ ፡ በታየ ፡ በገብርኤል ፡ ቃል ፡
ዘፀአ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ።

፴፮ ፤ ወውእቱ ፡ አውፅኦሙ ፡ እንዘ ፡ ይገብር ፡
ተአምረ ፡ ወመንክረ ፡ በምድረ ፡ ግብፅ ።

በግብፅ ፡ ተአምራት ፡ እያደረገ ፡ እስራ
ኤልን ፡ ከግብፅ ፡ ያወጣቸው ፡ ሙሴ ፡
ነው ፡ ያወጣቸው ፡ ሙሴን ፡ ላከው ፡ ዘጠ
ኝ ፡ መቅሠፍት ፡ ዐሥረኛ ፡ ሞተ ፡ በኵር፡
አድርጎ ፡ ጌታም ፡ ድውይ ፡ እየፈወሰ ፡
ምውት ፡ እያስነሣ ፡ ጋኔን ፡ እያስወጣ ፡
ያዳናቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ያዳናቸው ፡ እ
ሱን ፡ ላከው ፡

ወበባሕረ ፡ ኤርትራ ፡

ባሕር ፡ እየከፈለ ፡ ያሻገራቸው ፡ ሙሴ ፡
ነው ፡ ሙሴን ፡ ላከው ፡ ጌታም ፡ ባሕረ ፡
እሳትን ፡ ከፍሎ ፡ ነፍሳትን ፡ ያሻገረ ፡
እሱ ፡ ነው ፡ እሱን ፡ ላከው ፡

ወበገዳም ፡ አርብዓ ፡ ዓመተ ፡

አርባ ፡ ዘመን ፡ በበረሃ ፡ ውኃ ፡ ከድንጋይ፡
እያፈለቀ ፡ መና ፡ ከደመና ፡ እያወረደ ፡
እስራኤልን ፡ የመገበ ፡ ሙሴ ፡ ነው ፡ ሙ
ሴን ፡ ላከው ፡ ጌታም ፡ በገዳም ፡ ኅብስት ፡
አበርክቶ ፡ ያበላቸው ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ያበ
ላቸው ፡ ጌታን ፡ ላከው ፡ ዘፀአ ፡ ፯፡ ፲፡ ፲፬፡
፳፩ ።

፴፯ ፤ ወውእቱ ፡ ሙሴ ፡ ይቤሎሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስ
ራኤል ፡ ነቢየ ፡ ያነሥእ ፡ ለክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡
እምአኃዊክሙ ፡ ዘከማየ ፡

ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከወገኖቻችሁ ፡ እን
ደኔ ፡ ያለ ፡ ነቢይ ፡ ያስነሣላችኋል ፡

ሎቱ ፡ ስምዕዎ ፡

ትምህርቱን ፡ ተቀበሉት ፡ ብሎ ፡ የተና
ገረ ፡ ሙሴ ፡ ነው ፤ የተናገረ ፡ ሙሴን ፡
ላከው ፡ ዘዳግ ፡ ፲፰ ፡ ፲፭ ።

፴፰ ፤ ውእቱኬ ፡ ዘዐቀበ ፡ ተዓይኒሆሙ ፡ በገ
ዳም ፡ ምስለ ፡ ውእቱ ፡ መልአክ ፡ ዘተናገሮ ፡ በደ
ብረ ፡ ሲና ።

በደብረ ፡ ሲና ፡ ከተነጋገረው ፡ ከዚያ ፡
መልአክ ፡ ጋራ ፡ በበረሃ ፡ የእስራኤልን ፡
ሠራዊት ፡ የጠበቀ ፡ ሙሴ ፡ ነው ፤ የጠ
በቀ ፡ ሙሴን ፡ ላከው ፤ ጌታም ፡ ምእመና
ንን ፡ የጠበቀ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ የጠበቀ ፡
ጌታን ፡ ላከው ፡

ወዘተናገሮሙ ፡ ለአበዊነ ፡

አባቶቻችነንም ፡ የተነጋገራቸው ፡ እሱ ፡
ነው ፡



ወውእቱ ፡ ዘተመጠወ ፡ ቃለ ፡ ሕይወት ፡

ድኅነት ፡ የሚገኝባት ፡ ኦሪትን ፡ የተቀ
በለ ፡ ሙሴ ፡ ነው ፤ ሙሴን ፡ ላከው ፡

ከመ ፡ የሀበነ ።

ለኛ ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ወን
ጌልን፡ የሠራ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ የሠራ ፡ ጌታን፡
ላከው ፡ እኛን ፡ ይመክረን ፡ ያስተምረን ፡
ዘንድ ፡ ዘፀአ ፡ ፲፱ ፡ ፫ ።

፴፱ ፤ ወአበዩ ፡ አበዊነ ፡ ተአዝዞ ፡ ሎቱ ፡ ወዐለዉ ፡

አባቶቻችን ፡ ግን ፡ አናምንም ፡ አሉ ፡

ወሜጡ ፡ ልቦሙ ፡ ብሔረ ፡ ግብፅ ።

በግብፅ ፡ ወንድ ፡ ወንዱ ፡ አልቆ ፡ ሴት ፡
ሴቱ ፡ ቀርቷል ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡ ተመልሰን፡
ምሽት ፡ አግብተን ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ገዝ
ተን ፡ ሕፃናት ፡ ወልደን ፡ እንኖራለን ፡
ብለው ።

፵ ፤ ወይቤልዎ ፡ ለአሮን ፡ ግበር ፡ ለነ ፡ አማልክተ ፡
እለ ፡ የሐውሩ ፡ ቅድሜነ ፡ ወዘይፀብኡ ፡ ፀረነ ።

አሮንን፡ በፊት ፡ በፊታችን፡ የሚሄዱልን ፡
ጠላታችነን ፡ የሚያጠፉልን ፡ አማልክት፡
ሥራልን ፡ አሉት ።

እስመ ፡ ዝኩ ፡ ሙሴ ፡ ዘአውፅአነ ፡ እምድረ ፡ ግብፅ ፡
ኢናአምር ፡ ምንተ ፡ ኮነ ፡

ከግብፅ ፡ ያወጣን ፡ ሙሴ ፡ አመሌ ፡ አመ
ሌ ፡ ሲል ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ያያት ፡ እሳት ፡
አቃጥላውም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ግብፅ ፡
ሲመለስ ፡ ኤርትራ ፡ አስጥሞት ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ አናውቅምና ፡ ዘፀአ ፡ ፴፪ ፡ ፩ ፡ ፬ ።

፵፩ ፤ ወገብሩ ፡ ላህመ ፡ ውእተ ፡ አሚረ ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ በላም ፡ አምሳል ፡ የተሠራ ፡
ጣዖትን ፡ አቆሙ ።

ወአዕረጉ ፡ መሥዋዕተ ፡ ለጣዖት ፡

ለጣዖት ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ፡

ወተፈሥሑ ፡ በግብረ ፡ እደዊሆሙ ፡

በጃቸው ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡

፵፪ ፤ ወተመይጠ ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርም ፡ ከምሕረት ፡ ወደ ፡
መዓት ፡ ተመልሰ ፡

ወኀደጎሙ ፡ ያምልኩ ፡ ኮከበ ፡ ሰማይ ፡

ኮከብ ፡ ያመልኩ ፡ ዘንድ ፡ በረድኤት ፡
ተለያቸው ፡

በከመ ፡ ይብል ፡ መጽሐፈ ፡ ነቢያት ፡ ቦኑ ፡ መሥዋ
ዕተ ፡ ወቍርባነ ፡ ዘአባእክሙ ፡ ሊተ ፡ አርብዓ ፡ ዓመ
ተ ፡ በገዳም ፡ አ ፡ ቤተ ፡ እስራኤል ፡

ቤተ ፡ እስራኤል ፡ አርባ ፡ ዘመን ፡ በገዳም፡
ያቀረባችሁልኝ ፡ ቍርባን ፡ መሥዋዕት ፡
አለን ፡ መሥዋዕት ፡ ቍርባን ፡ አቀረባች
ሁልኝን ፡ ያቀረባችሁልኝ ፡ ማቅረብ ፡
አለን ፡ ብሎ ፡ አሞጽ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡
ኀደጎሙ ፡ ላለው ፡ ሐተታ ፡ መሥዋዕት ፡
የላሙ ፡ ቍርባን ፡ የበጉ ፡ የፍየሉ ። አን
ድም ፡ መሥዋዕት ፡ የላሙ ፡ የበጉ ፡ የፍ
የሉ ፡ ቍርባን ፡ የስንዴ ፡ የወይኑ ። አን
ድም ፡ መሥዋዕት ፡ የሚባለው ፡ ቍርባን፡
የሚጤሰው ፡ ኤር፡ ፲፱፡ ፲፫። ዓሞ፡ ፭፡ ፳፭።

፵፫ ፤ አላ ፡ ነሣእክሙ ፡ ደብተራ ፡ ሞሎሕ ፡

የሞአብን ፡ ጣዖት ፡ አቆማችሁ ፡ እንጅ ፡
ደብተራ ፡ ሞሎክ ፡ ይላል ፡ የጣዖት ፡ ትር
ሽማን ፡ አቆማችሁ ፡ እንጅ ፡

ወኮከበ ፡ አምለክሙ ፡ ዘስሙ ፡ ሬፋን ፡

ዙኃል ፡ የሚባል ፡ ኮከብ ፡ አመለካችሁ ፡
እንጅ ፡

ወገበርክሙ ፡ አምሳሊሁ ፡ ከመ ፡ ትስግዱ ፡ ሎቱ ፡

ትሰግዱለትም ፡ ዘንድ ፡ ምስሉን ፡ የሠ
ራችሁለት ፡

ወአፍለስክሙ ፡ ውስተ ፡ ባቢሎን ።

ከባቢሎን ፡ ያመጣችሁት ፡ ብሎ ፡ ለም

www.ethiopianorthodox.org

ስሉ ፡ ይቀጥላል ። አንድም ፡ አፈልሰክሙ ውስተ ፡ ባቢሎን ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ አስ ማርኬ ፡ እሰዳችኋለሁ ፡ እምባቢሎን ፡ ከባቢሎን ፡ ወዲያ ፡ አስማርኬ ፡ እሰዳች ኋለሁ ።

## ክፍል ፡ ፲፫ ፡

፵፬ ፤ ወደብተራ ፡ ስምዕ ፡ እንተ ፡ ነበረት ፡ ኀበ ፡ አበዊነ ፡ በገዳም ፡

ደብተራ ፡ ስምዕ ፡ ደብተራ ፡ ዘመን ፡ ደብ ተራ ፡ ሕግ፡ ደብተራ ፡ ብርሃን ፡ ደብተራ ፡ መርጡል ፡ ይላል ፡ ደብተራ ፡ ስምዕ ፡ አም ልኮቱ ፡ ይመሰከርበታልና ፡ ደብተራ ፡ ዘመን ፡ በዘመን ፡ ተሠርታለችና ፡ ደብተ ራ ፡ ሕግ ፡ ሕጉ ፡ ይነገርባታልና ፡ ደብተ ራ ፡ ብርሃን ፡ ብርሃን ፡ ሠፍሮ ፡ ታይቶባታ ልና ፡ ደብተራ ፡ መርጡል ፡ ሰቀለኛ ፡ ናትና ፡ በገዳም ፡ ለአባቶቻችን ፡ የተሠ ራች ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡

በከመ ፡ አዘዞ ፡ ለሙሴ ፡ ዘተናገሮ ፡ ይግበራ ፡ በአር አያ ፡ ዘአርአዮ ።

ምሳሌዋን ፡ ባሳየው ፡ በሰማያዊት ፡ ደብ ተራ ፡ ብርሃን ፡ አምሳል ፡ ይሠራት ፡ ዘን ድ ፡ ለተነጋገረው ፡ ለሙሴ ፡ እንዳዘዘው ፡ የተሠራች ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡ ዘፀአ ፡ ፳፭ ፡ ፵ ። ፳፯ ፡ ፴ ።

፵፭ ፤ ወአብእዋ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ሶበ ፡ ተመጠውዋ ፡ አበዊነ ፡ ወኢያሱ ፡ ውስተ ፡ በሐውርተ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ አውጽኦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምቅድመ ፡ ገጾሙ ፡ ለአበዊነ ፡

እንተ ፡ ነበረት ፡ ወእንተ ፡ አብእዋ ፡ አባቶ ቻችንና ፡ ኢያሱ ፡ ተቀብለው ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ካባቶቻችን ፡ ፊት ፡ ያራቃቸው ፡ አሕዛብ ፡ ወርሰዋት ፡ ወደ ፡ ነበረች ፡ ወደ፡ ከነዓን ፡ ይዘዋት፡ የገቡ፡ ደብተራ ፡ አሪት ፡

እስከ ፡ አመ ፡ መዋዕለ ፡ ዳዊት ፡

ነበረት ፡ እስከ ፡ አመ ፡ መዋዕለ ፡ ዳዊት ፡ እስከ ፡ ዳዊት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ነበረች ፡ ኤር ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

፵፮ ፤ ዘረከበ ፡ ሞገሰ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡

ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ባለሟልነትን ፡ ያገኘ ፡

ወሰአለ ፡ ይርከብ ፡ ማኅደሮ ፡ ለአምላከ ፡ ያዕቆብ ።

የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ ማደሪያን ፡ ሊያውቅ ፡ የወደደ ፡ ታሪክ ፡ ዳዊት ፡ ኢያውሴዎንን ፡ ወግቶ ፡ ደብረ ፡ ጽዮንን ፡ አቅንቶ ፡ እሱ ፡ በጥድ ፡ በዝግባ ፡ ከተሠራ ፡ አዳራሽ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ ሊጠይ ቀው ፡ መጣ ፡ አዝኖ ፡ ቢያየው ፡ ምን ፡ ሁነህ ፡ አዝነሃል ፡ አለው ፡ እኔ ፡ አላዝን ፡ ማን ፡ ይዘን ፡ እኔ ፡ በጥድ ፡ በዝግባ ፡ ከተ ሠራ ፡ አዳራሽ ፡ ተቀምጬ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮ ን ፡ ከደጅ ፡ በድንኳን ፡ እየኖረች ፡ አለው፤ ምነው ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ አትሠራምን ፡ አለው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ካላመለ ከቱ ፡ ይሆናልን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አታመለክትልኝም ፡ አለው ፡ ተያይዘው ፡ ቀኖና ፡ ገቡ ፡ ለናታን ፡ ዳዊት ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ እንዳይሠራ ፡ ልጁ ፡ ሰሎሞን፡ እንዲሠራ ፡ ገልጦለት ፡ አኮ ፡ አንተ ፡ ዘትነድቅ ፡ ሊተ ፡ አላ ፡ ወልድከ ፡ ዘይወ ፅእ ፡ እምሐቌከ ፡ ውእቱ ፡ ይነድቅ ፡ ሊተ ፡ ቤተ ፡ ብሎታል ፡ ለዳዊት ፡ ግን ፡ ጌታ ፡ ጥቂት ፡ ነገር ፡ ቢሹ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ መግ ለጥ ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡ የበለጠ ፡ የሥጋ ዌን ፡ ነገር ፡ ገልጦለት ፡ ናሁ ፡ ሰማዕናሁ ፡ በኤፍራታ ፡ ብሏል ፡ ዳንኤል ፡ ሚጠተ ፡ እስራኤልን ፡ ሲሻ ፡ ቀኖና ፡ ቢገባ ፡ የሥ ጋዌ ፡ ነገር ፡ ተገልጦለት ፡ መቅደስ ፡ ትት ሐነጽ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ፡ ንጉሥ ፡ ወእም ዝ ፡ ትትመዘበር ፡ እንዳለ ። ዕዝራም ፡ ሚጠተ ፡ እስራኤልን ፡ ሲሻ ፡ ቀኖና ፡ ቢገ



ባ ፡ የሥጋዌ ፡ ነገር ፡ ተገልጦለት ፡ አን በሳ ፡ ተንሥአ ፡ እምገዳም ፡ ውእቱኬ ፡ ወልድ ፡ ውእቱ ፡ ብሏል ፡ የበለጠ ፡ የመን ግሥቱ ፡ ሰማያትም ፡ ነገር ፡ ተገልጦለት ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ ዝንቱ ፡ ዓቢይ ፡ እንዳለ፡ ፪ ፡ ሳሙኤ ፡ ፯ ፡ ፪ ። መዝ ፡ ፻፴፪ ፡ ፭ ።

፵፯ ፤ ወዳዕሙ ፡ ሰሎሞን ፡ ሐነጸ ፡ ሎቱ ፡ ቤተ ፡

ሰሎሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ሠራ ፡ እንጅ፡ ነበረት ፡ እስከ ፡ አመ ፡ መዋዕለ ፡ ዳዊት ፡ ላለው ፡ ፩ ፡ ነገሥ ፡ ፮ ፡ ፩ ።

፵፰ ፤ ወአኮሰ ፡ ዘየኅድር ፡ ልዑል ፡ ውስተ ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡

ሰሎሞን ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ መሥራቱ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ተወስኖ ፡ የሚኖር ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ፡

እስመ ፡ ከመ ፡ ዝ ፡ ይቤ ፡ ነቢይ ፡

ነቢይ ፡ እንዲህ ፡ ብሏልና ።

፵፱ ፤ ሰማይኒ ፡ መንበርየ ፡

ሰማይ ፡ ዙፋኔ ፡ ነው ፡

ወምድርኒ ፡ መከየደ ፡ እገርየ ፡

ምድርም ፡ መቋሚያየ ፡ ናት ፡

አየኑ ፡ ቤተ ፡ ተሐንጹ ፡ ሊተ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡

ምን ፡ ቤት ፡ ትሠሩልኛላችሁ ፡ አለ ፡ እግ ዚአብሔር ፡

ወዓይኑ ፡ መካን ፡ ውእቱ ፡ መካነ ፡ ምዕራፍየ ፡

የማርፍበትስ ፡ ቦታ ፡ ምን ፡ ቦታ ፡ ነው ፡ ኢሳ ፡ ፷፮ ፡ ፩ ።

፶ ፤ አኮኑ ፡ እደውየ ፡ ገብራ ፡ ዘ ፡ ኵሎ ፡

ይህን ፡ ሁሉ ፡ እጆቼ ፡ ሠርተውት ፡ የለ ምን ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ነቢይ፡ ተናግሯልና ፡ አኮ ፡ ዘየኅድር ፡ ላለው ፡ ይህን ፡ ለምን ፡ ይሻዋል ፡ ቢሉ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ትፈርሳለች ፡ ይላል ፡ ላሉት ፡ አመጣ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ይህ ፡ ዕንጨት፡ ደንጊያው ፡ ይመስላችኋል ፡ ሕንፃ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ማኅደረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ነታችሁ ፡ እንጅ ፡ ነው ፡ ለማለት ።

፶፩ ፤ አ ፡ ጽኑዓነ ፡ ክሣድ ፡

ክሣደ ፡ ልቡናችሁ ፡ የጸና ፡

ወጽሉላነ ፡ ልብ ፡

ልቡናችሁ ፡ የገዘፈ ፡

ወጽሙማነ ፡ እዝን ፡

ዕዝነ ፡ ልቡናችሁ ፡ የደነቈረ ፡

እለ ፡ ዘልፈ ፡ ታምዕዕዎ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡

መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የምታ ሳዝኑት ፡ አለ ፡ አድሮባችሁ ፡ ያለ ፡ መን ፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ኃጢአት ፡ ሠርታችሁ ፡ እንዲለያችሁ ፡ የምታደርጉ ፡

ከመ ፡ አበዊክሙ ፡ አንትሙሂ ፡

እናንተም ፡ እንደ ፡ አባቶቻችሁ ፡ ናችሁ ፡ ትምህርቱን ፡ አስቀድሞ ፡ ዘለፋውን ፡ ወደ፡ ኋላ፡ አመጣ፡ ዘለፋውን፡ አስቀድሞ ፡ ትምህርቱን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አድርጎት ፡ ቢሆን ፡ እሱን ፡ በደንጊያ ፡ ወግረው ፡ በገ ደሉት ፡ ነበር ፡ ትምህርቱም ፡ በቀረ ፡ ነበ ርና ፡ ትምህርቱን ፡ አስቀድሞ፡ ዘለፋውን፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አመጣ ፡ ቢወዱ ፡ ይቀበሉት ፡ ባይወዱ፡ ይተዉት ፡ ብሎ ፡ ዘፀአ ፡ ፴፪፡፱ ፡

፶፪ ፤ መኑ ፡ እምነቢያት ፡ ዘኢሰደድዎ ፡ ወኢቀተ ልዎ ፡ አበዊክሙ ፡

ከነቢያት ፡ ወገን ፡ አባቶቻችሁ ፡ መከራ ፡ ያላጸኑበት ፡ አገር ፡ አስጥለው ፡ ያልሰደ ዱት ፡ ማን ፡ ነው ፡

ወቀተልዎሙ ፡ ለእለ ፡ አቅደሙ፡ ወዜነውዎሙ ፡ በእ ንተ ፡ ምጽአቱ ፡ ለጻድቅ ፡ ዘአንትሙ ፡ ዓሎክምዎ ፡ ወቀተልክምዎ ፡

እናንት ፡ አምፃችሁ ፡ ሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ብላ

www.ethiopianorthodox.org

ችሁ ፡ ሰቅላችሁ ፡ የገደላችሁት ፡ ጻድቅ ፡
ባሕርይ ፡ የሚሆን ፡ የሱን ፡ መምጣት ፡
አስቀድመው ፡ የነገሯቸው ፡ ነቢያትን ፡
የገደሏቸው ፡ አይደለምን ፡ ፪ ፡ ዜና ፡
፴፯ ፡ ፲፮ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፴፩ ።

፶፫ ፤ ወነሣእክሙ ፡ ኦሪተ ፡ በሥርዐተ ፡ መላእክት፡ ኢዐቀብክሙ ፡

ኦሪት ፡ በሥርዐት ፡ መላእክት ፡ መላእክት ፡ እየተራዱት ፡ በሙሴ ፡ ቃል ፡ የተሠራች ፡ ኦሪትን ፡ ተቀብላችሁ ፡ አልጠበቃችሁም ። ነሣእክሙ ፡ በሥርዐተ ፡ መላእክት ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ እንደ ፡ ተቀበሉ ፡ ተቀብላችሁ ። ኢዐቀብክሙ ፡ በሥርዐተ ፡ መላእክት ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ እንደ ፡ ጠበቁ፡ አልጠበቃችሁም ። አንድም ፡ ሐና ፡ ቀያፋ ፡ እንዳልጠበቁ ፡ አልጠበቃችሁም ። ዘፀአ ፡ ፳ ፡ ፩ ። ገላት ፡ ፫ ፡ ፲፱ ፡ ዕብ ፡ ፪፡፪።

፶፬ ፤ ወዘንተ ፡ ሰሚያሙ ፡ ተምዕዑ ፡

ወነሣእክሙ ፡ ኦሪተ ፡ በሥርዐተ ፡ መላእክት ፡ ኢዐቀብክሙ ፡ ቢላቸው ፡ ዛሬስ ፡ አለ ፡ አለና ፡ እሱን ፡ አልጠበቅህም ፡ ብንለው ፡ ከኩተት ፡ እስከ ፡ ሽበት ፡ የኖርን ባትን ፡ ሕግ ፡ አልጠበቃችሁም ፡ ይለናል፡ ብለው ፡ ተበሳጩ ።

ወአብደ ፡ ልቦሙ ፡

ልባቸው ፡ ተነሣሳ ፡ (ጥቅ) ፡ ወአብደ ፡ ዳቤላ ፡ ጠሊ ፡ እንዲል ፡

ወሐቀዩ ፡ ስነኒሆሙ ፡ ላዕሌሁ ።

ጥርሳቸውን ፡ አፋጩ ፡ አለ ፡ ትእምርተ ፡ ጸብእ ፡ ነው ፡ አጽንተው ፡ ተጣሉት ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፴፫ ።

፶፭ ፤ ወመልአ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ላዕለ፡ እስጢፋኖስ ፡

በእስጢፋኖስም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አደረበት ፡ ተለይቶትን ፡ ያውቃል ፡ ቢሉ ፡ ምስጢር ፡ ገለጠለት ፡ ሲል ፡ ነው ፡

ወነጸረ ፡ ሰማየ ፡ ርኅወ ፡

ሰማይ ፡ ሲከፈት ፡ አየሁ ፡ ሐተታ ፡ አሁን በሰማይ ፡ መከፈት ፡ መዘጋት ፡ኖሮበት ፡ አይደለም ፡ የተዘጋ ፡ ደጅ ፡ በተከፈተ ፡ ጊዜ ፡ ያልታየ ፡ ዕቃ ፡ እንዲታይ ፡ ያልተገለጠ ፡ ምስጢር ፡ ተገለጠ ፡ ሲል ፡ ነው ፡

ወርእየ ፡ ስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡

የእግዚአብሔርን ፡ ጌትነት ፡ አየ ፡

ወኢየሱስ ፡ ይቀውም ፡ በየማነ ፡ እግዚአብሔር ፡

ኢየሱስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ቀኝ ፡ ተቀምጦ ፡ አየ ።

፶፮ ፤ ወይቤ ፡ ናሁ ፡ እሬኢ ፡ ተርኅወ ፡ ሰማይ ፡

ሰማይ ፡ የተከፈተ ፡ ሆኖ ፡ አየሁ ፡

ወወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ይቀውም ፡ በየማነ ፡ እግዚአብሔር ፡

ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ቀኝ ፡ ተቀምጦ ፡ አያለሁ ፡ አለ ፡ ይኸውም ፡ ምስጢረ ፡ ገድሉ ፡ ነው ።

፶፯ ፤ ወከልሑ፡በዐቢይ፡ ቃል ፡ ወከደኑ፡ እዘኒሆሙ ፡

ከፊቱ ፡ የኋላው ፡ ይባስ ፡ ዛሬስ ፡ ለሰማይ፡ ደጅ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አበጀለት ፡ ያን ፡ ጠልተን ፡ ሰቅለን ፡ የገደልነውን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ በአብ ፡ ቀኝ ፡ አየሁት ፡ ይለናል ፡ ይኸን ፡ የሰማ ፡ ጆሮ ፡ ይበጣጠስ ፡ ብለው ፡ ጆሯቸውን ፡ ይዘው ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ ጮሁ ፡

ወሮድዎ ፡ ኅቡረ ፡ ወሰሐብዎ ።

አንድ ፡ ሁነው ፡ ከበው ፡ እየጐተቱ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ፳ ።

፶፰ ፤ ወአውፅእዎ ፡ አፍአ ፡ እምሀገር ፡ ወወገርዎ ፡

ከከተማው ፡ ወደ ፡ አፍአ ፡ አውጥተው ፡ ድንጋይ ፡ ጣሉበት ፡



ወእለሰ ፡ ቀተልዎ ፡ አዕቀቡ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ወአንበሩ ፡ ኀበ ፡ እገሪሁ ፡ ለወሬዛ ፡ ወልድ ፡ ዘሰሙ ፡ ሳውል ።

የገደሉትም ፡ ሰዎች ፡ ልብሳቸውን ፡ ሳውል ፡ ከሚባል፡ ብላቴና፡ ከእግሩ፡ በታች ፡ አኑረው ፡ አስጠበቁ ፡ ሐተታ ፡ ሕፃን ፡ ነውና ፡ ደም ፡ ይፈራል ፡ ብለው ። አንድም፡ ጐበዝ ፡ ነውና ፡ አያስነጥቅም ፡ ብለው ።

፶፱ ፤ ወወገርዎ ፡ ለእስጢፋኖስ ፡ እንዘ ፡ ይጼሊ ፡ ወይብል ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ተመጠዋ ፡ ለነፍስየ ፡

ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥልጣንህ ነፍሴን ፡ ከሥጋዬ ፡ ለይተህ ፡ ተቀበላት ፡ እያለ ፡ ሲጸልይ ፡ ደንጊያ ፡ ጣሉበት ፡ መዝ ፡ ፴፩ ፡ ፮ ። ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፵፮ ።

፷ ፤ ወሶበ ፡ ሰገደ ፡ ከልሐ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ፡

ዘለፍ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ ጮኸ፡

ወይቤ ፡ እግዚኦ ፡ ስረይ ፡ ሎሙ ፡ ዘንተ ፡ ኃጢአቶሙ፡

አቤቱ፡ኃጢአታቸውን፡ ይቅር፡ በላቸው ።

ወኢትረሲ ፡ ቦሙ ፡ ጌጋየ ፡

ዕዳ ፡ አታድርግባቸው ፡ እያለ ፡ ጸለየ ፡

ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ኖመ ፡

ይህን ፡ ተናግሮ ፡ አረፈ ፡ ሐተታ ፡ በሞቱም ፡ ጌታውን ፡ መስሎታል ፡ ጌታ ፡ አባ፡ አመሐፅን ፡ ነፍስየ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ እንዳለ። እሱም፡ አ ፡ እግዚእየ፡ ተመጠዋ፡ ለነፍስየ ፡ ብሏል ፡ ጌታ ፡ አባ ፡ ሥረይ፡ ሎሙ ፡ እንዳለ ፡ እሱም፡ አ፡ እግዚኦ፡ ሥረይ ፡ ሎሙ ፡ ዘንተ ፡ ወኢትረሲ፡ ቦሙ ፡ ጌጋየ ፡ ብሏል ፡ ዛሬም ፡ መከራ ፡ የሚቀበል ፡ ሰው ፡ ከላይ ፡ ጌታን ፡ ከታች ፡ እስጢፋኖስን ፡ አብነት፡ ካላደረገ ፡ መከራው፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ እንደ ፡ ወንበዴ ፡ መከራ ፡ ይሆንበታል ፡

ወሳውልኒ ፡ ኮነ ፡ ኅቡረ ፡ ውእቱ ፡ ውስተ ፡ ቀቲለ ፡ ዚአሁ ፡

ሳውልም ፡ በሞተ ፡ እስጢፋኖስ ፡ በነገሩ ፡ ነበረበት ፡ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፴፮ ። ም ፡ ፯ ፡ ፶፯ ።

## ምዕራፍ ፡ ፰ ፡ ክፍል ፡ ፲፬ ፡

፩ ፤ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ ኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ምንዳቤ ፡ ወሁከት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ባሉ ፡ ምእመናን ፡ ላይ ፡ ጽኑ ፡ መከራ ፡ ሽብር ፡ ሆነ ፡

ወተዘርዉ ፡ ኵሎሙ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርተ ፡ ይሁዳ ፡ ወሰማርያ ፡ ወገሊላ ፡

ሁሉም ፡ በይሁዳ ፡ በሰማርያ ፡ በገሊላ ፡ አውራጃዎች ፡ ተበተኑ ፡

ዘእንበለ ፡ ሐዋርያት ፡ ባሕቲቶሙ ፡ ዘነበሩ ፡ በኢየሩሳሌም ፡

በኢየሩሳሌም ፡ ከነበሩ ፡ ከሐዋርያት ፡ በቀር ። አንድም ፡ ሐዋርያት ፡ ሳይቀሩ ፡ ተበተኑ ፡ አውራ ፡ የሌለው ፡ ንብ ፡ አለቃ ፡ የሌለው ፡ ሕዝብ ፡ እንዲሉ ፡ ምነው ፡ እሱንስ ፡ ቢያስነሣላቸው ፡ ሌላስ ፡ ቢተካላቸው ፡ ይሆን ፡ የለም ፡ ቢሉ ፡ እሱንም ፡ ቢያስነሣላቸው ፡ ሌላም ፡ ቢተካላቸው ፡ ይሆን ፡ ነበረ ፡ ውስጡ ፡ ጥበበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ስምንቱ ፡ ሽሕ ፡ ማኅበር ፡ ባንድነት ፡ ቢሆኑ ፡ ሃይማኖት ፡ ይጸናል ፡ እንጅ ፡ አይሰፋም ፡ የተበተኑ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ በየሄዱበት ፡ ያስተምራሉ ፡ ሃይማኖት ፡ ይሰፋልና ፡ (ጥቅ) ፡ እስመ ፡ ብዝኃ ፡ ጠበብት ፡ መድኃኒተ ፡ ዓለም ፡ ውእቱ ፡ ወዕደ ፡ ብዙኅ ፡ እክል ፡ ይትወዐቅ ፡ እምኃይለ ፡ ላሕሙ ፡ እንዲል፡

www.ethiopianorthodox.org

እንደ ፡ መስኖ ፡ ውኃ ፡ የመስኖ ፡ ውኃ ፡ ባንድ፡ ወገን፡ ባንድ ፡ መሸረብ፡ የወሰዱት፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሄደበትን ፡ ብቻ ፡ ይጠቅ ማል ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ በብዙ ፡ መሸረብ ፡ የወሰዱት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ ለብዙ ፡ አዝርዕት ፡ ለብዙ ፡ አትክልት ፡ ይጠቅ ማልና ፡ የአይሁድ ፡ ግን ፡ መቸም ፡ መች፡ ተምኔታቸው ፡ አልተፈጸመላቸውም፡ቀድ ሞ ፡ ጌታን ፡ ሰቅለው ፡ ገለው ፡ ወንጌል ፡ ትጠፋለች፡ ኦሪት ፡ ትሰፋለች ፡ ብለው ፡ ነበረ ፡ እሱ ፡ ሳለ ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ያስተምር፡ ነበር ፡ እሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ መቶ ፡ ኻያው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ሁሉ ፡ በያሉበት ፡ የሚያስተምሩ ፡ ሆነዋል ፡ ኋላም ፡ እስጢ ፋኖስን ፡ በደንጊያ ፡ ወግረው ፡ ገለው ፡ ወንጌል ፡ ትጠፋለች ፡ ኦሪት ፡ ትሰፋለች ፡ ብለው ፡ ነበር ፡ እስጢፋኖስ ፡ ሳለ ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ያስተምር ፡ ነበር ፡ እሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ስምንቱ ፡ ሺሕ ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ በያሉበት ፡ የሚያስተምሩ ፡ ሆነዋ ልና ፡ መቸም ፡ መች ፡ ተምኔታቸው ፡ አል ተፈጸመላቸውም ፤ ም ፡ ፲፩፡፲፱ ።

፪ ፤ ወለእስጢፋኖስሰ ፡ ነሥእዎ ፡ ዕደው ፡ ጻድቃን ፡ ወቀበርዎ ፡ ወላሐውዎ ፡ ዐቢየ ፡ ላሐ ።

እስጢፋኖስንም ፡ ደጋግ ፡ ሰዎች ፡ ልቡ ፡ ለጻድቅ ፡ ውኩል ፡ ከመ ፡ አንበሳ ፡ እን ዲል ፡ እሱን ፡ ያገኘ ፡ ያገኘናል ፡ ሳይሉ ፡ አንሥተው ፡ ጽኑ ፡ ልቅሶ ፡ አልቅሰው ፡ ቀበሩት ፡ ማቴ ፡ ፲፬ ፡ ፲፪ ።

፫ ፤ ወሳውልሰ ፡ ዓዲሁ ፡ ይትቄየም ፡ አብያተ ፡ ክር ስቲያናት ፡

ሳውል፡ግን፡ገና፡ምእመናንን፡ይጣላ፡ ነበር ፡

ወይደቢ ፡ አብያተ ፡ ሰብእ ፡

የሰውን ፡ ሁሉ ፡ ቤት ፡ ይወር ፡ ይዘርፍ ፡ ይከብ ፡ ነበር ፡

ወይስሕብ ፡ ዕደወ ፡ ወአንስተ ፡ ወይሞቅሖ ።

ሴቶችንም ፡ ወንዶችንም ፡ እያሠረ ፡ ይወ ስድ ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፩ ። ፳፪ ፡ ፬ ።

፬ ፤ ወእለሰ ፡ ተዘርዉ ፡ አንሶሰዉ ፡ ወመሐሩ ፡ ወሰ በኩ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።

ወውእተ ፡ አሚረ ፡ ኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ምንዳቤ፡ ወሁከት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኢየሩ ሳሌም ፡ ወተዘርዉ ፡ ኵሎሙ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርተ ፡ ይሁዳ ፡ ወሰማርያ ፡ ወገሊላ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ በይሁዳ ፡ በሰማ ርያ ፡ በገሊላ ፡ የተበተኑ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ፡ ማኅበር ፡ ሔሩ ፡ ወመሐሩ ፡ ያላት ፡ ወን ጌልን ፡ ዞረው ፡ አስተማሩ ።

፭ ፤ ወወረደ ፡ ፊልጶስ ፡ ሀገረ ፡ ሰማርያ ፡ ወሰበከ ፡ ሎሙ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡

ፊልጶስም ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ሂዶ ፡ የክርስ ቶስን ፡ ነገር ፡ አስተማራቸው ፤ ም ፡ ፯፡ ፭።

፮ ፤ ወአፅምእዎ ፡ ሕዝብ ፡ ዘይነግሮሙ ፡ ፊልጶስ ፡

ፊልጶስ ፡ ያስተማራቸውን ፡ ነገር ። አን ድም ፡ ፊልጶስ ፡ ያስተማራቸው ፡ ሕዝቡ ፡ ተቀበሉ ፡

ወሰምዕዎ ፡ ኅቡረ ፡

አንድ ፡ ሁነው ፡ ተቀበሉት ፡

ወያነክሩ ፡ ወይሬእዩ ፡ ተአምረ ፡ ወመንክረ ፡ ዘይ ገብር ፡

የሚያደርገውን ፡ ተአምራት ፡ እያዩ ፡ ያደ ንቁ ፡ ነበርና ።

፯ ፤ ወብዙኃን ፡ አጋንንት ፡ እኩያን ፡ ይኬልሑ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ፡ ወይወፅኡ ፡

ብዙ ፡ አጋንንትም ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ እየ ጮሁ ፡ ይወጡ ፡ ነበር ፡

ወብዙኃን ፡ ፅውሳን ፡ ወሐንካሳን ፡ የሐይዉ ።

ብዙ ፡ ልምሾ ፡ የሆኑ ፡ ሐንካሶችም ፡ ይድ ኑ ፡ ነበር ፡ ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ።



፰ ፤ ወኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ፍሥሐ ፡ በይእቲ ፡ ሀገር ።

በሰማርያ ፡ ፍጹም ፡ ደስታ ፡ ሆነ ፡ ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፵ ።

፱ ፤ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ በይእቲ ፡ ሀገር ፡ ዘስሙ ፡ ሲሞን ፡

በሰማርያ ፡ ሲሞን ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡

ወያስሕቶሙ ፡ ለሕዝበ ፡ ሰማርያ ፡

የሰማርያን ፡ ሰዎች ፡ ያስታቸው ፡ ነበር ፡

ዘሥራይ ፡ ብእሲሁ ፡

ሰውየውም ፡ ሥራየኛ ፡ ነበር ፡ ሲአምኑ ፡ አይቶ ፡ አመንሁ ፡ አለ ፡ ሲጠመቁ ፡ አይቶ ተጠመቀ ፡ ለማለት ፡ ያመጣዋል ፡

ወይሬሲ ፡ ርእሶ ፡ ዐቢየ ፡

አምላክ ፡ ነኝ ፡ ይል፡ ነበር ። ነቢየ፡ ይላል፡ አዋቂ ፡ ነኝ ፡ ይል ፡ ነበር ።

፲ ፤ ወይትአመንዎ ፡ ንዑሶሙ ፡ ወዐቢዮሙ ፡ ወይ ብሉ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐቢይ ።

ታናሹም ፡ ታላቁም ፡ ይህ ፡ ዐቢይ ፡ እግዚ አብሔር ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ነው ። አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረበት ፡ ነቢይ ፡ ነው ፡ እያሉ ። አንድም ፡ ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢይ ፡ አድሮ ፡ የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ነገሩን ፡ ያምኑት ፡ ነበር ።

፲፩ ፤ ወያፀምእዎ ፡

ይቀበሉት ፡ ነበር ፡

እስመ ፡ ጉንዱይ ፡ መዋዕል ፡ እምዘ ፡ አስሐቶሙ ፡ በሥራዩ ፡

በሥራዩ ፡ ካሳታቸው ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሆኖት ፡ ነበርና ፡ (ጥቅ) ፡ ወበርኅቀተ ፡ መዋዕል ፡ ኮነ ፡ ልማደ ፡ እብሰት ፡ እን ዲል ።

፲፪ ፤ ወሶበ ፡ አምንዎ ፡ ለፊልጶስ ፡ ዘሰበከ ፡ ሎሙ ፡ በእንተ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በስመ ፡ ኢየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዕድ ፡ ወአንስት ፡ ይጠመቁ ።

ፊልጶስ ፡ የነገራቸውን ፡ የወንጌልን ፡ ነገ ር ። አንድም ፡ የወንጌልን ፡ ነገር ፡ የነገራ ቸውን ፡ ፊልጶስን ፡ ከተቀበሉ፡ በኋላ፡ ሴቶ ችም ፡ ወንዶችም ፡ በጌታችን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እያመኑ ፡ ጥምቀተ ፡ ዮ ሐንስ ፡ ይጠመቁ፡ ነበር፡ ማቴ፡ ፳፰፡ ፲፱ ።

፲፫ ፤ ወሲሞንሂ ፡ አምነ ፡ ወተጠምቀ ፡

ሲሞንም ፡ ሲያምኑ ፡ አይቶ ፡ አመንሁ ፡ አለ ፡ ሲጠመቁ ፡ አይቶ ፡ ተጠመቀ ፡

ወነበረ ፡ ይፀመዶ ፡ ለፊልጶስ ፡

ፊልጶስንም ፡ ሲያገለግል ፡ ኖረ ፡ ከፊል ጶስ ፡ ሲማር ፡ ኖረ ፡

እስመ ፡ ይሬኢ ፡ ተአምረ ፡ ወመንክረ ፡ ዘይከውን ፡ በእደዊሁ ፡ ወያነክር ፡ ወይዴመም ፡

በፊልጶስ ፡ ሥልጣን ፡ የሚደረገውን፡ ተአ ምራት ፡ እያየ ፡ ያደንቅ ፡ ነበርና ።

ክፍል ፡ ፲፭ ።

፲፬ ፤ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ሐዋርያት ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ኢየ ሩሳሌም ፡ ከመ ፡ ተወክፉ ፡ ሰብአ ፡ ሰማርያ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡

በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ ሐዋርያትም ፡ የሰ ማርያ ፡ ሰዎች ፡ ወንጌልን ፡ እንደ ፡ ተቀ በሉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡

ፈነዉ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ጴጥሮስሃ ፡ ወዮሐንስሃ ።

ጴጥሮስንና ፡ ዮሐንስን ፡ ትምህርት ፡ እገዙ ፡ ብለው ፡ ወደነሱ ፡ላኩ ።

፲፭ ፤ ወወረዱ ፡ ወጸለዩ ፡ ላዕሌሆሙ ፡

እነሱም ፡ ሂደው ፡ ጸለዩላቸው ፡ ጸሎተ ፡ ጥምቀት ፡ ነው ፡

ከመ ፡ ይንሥኡ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ።

ልጅነትን ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፮ ፤ እስመ ፡ ዓዲ.ሁ ፡ ኢ.ወረደ ፡ ወኢ.ዲበ ፡ አሐዱሂ ፡ እምውስቴቶሙ ፡

ከነሱ ፡ ላንዱ ፡ ስንኳ ፡ ገና ፡ ልጅነት ፡ አል ተሰጠም ፡ ነበረና ፡

ዳእሙ ፡ ተጠምቁ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡

በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አምነው ፡ ጥምቀተ ፡ ዮሐንስ ፡ ተጠምቀው፡ነበረ፡እንጅ፡ዓዲ.ሁ፡ኢ.ወረደ፡ላለው ።

፲፯ ፤ ወእምዝ ፡ ወደዩ ፡ እደዊሆሙ ፡ ላዕሌሆሙ ፡

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እጃቸውን ፡ ጫኑባቸው፡

ወነሥኡ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ።

ልጅነትን ፡ ተቀበሉ ፡

፲፰ ፤ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ሲ.ሞን ፡ ከመ ፡ ኀበ ፡ ወደዩ ፡ እደዊሆሙ ፡ ሐዋርያት ፡ ይወርድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡

ሲ.ሞንም ፡ ሐዋርያት ፡ እጃቸውን ፡ በጫኑበት ፡ ላይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዲያድር ፡ አለ ፡ ልጅነት ፡ ሲሰጥ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡

አምጽአ ፡ ሎሙ ፡ ንዋየ ፡

ገንዘብ ፡ አምጥቶ ፡

፲፱ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አብሑኒ ፡ ሊ.ተኒ ፡ ወሀቡኒ ፡ ከመ፡ኀበ ፡ ወደይኩ፡ እዴየ፡ ይረድ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ ፡

እጄን ፡ ከጫንሁበት ፡ ላይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያድር ፡ ዘንድ ፡ እኔንም ፡ እዘዙኝ፡ ሹሙኝ ፡ አላቸው ።

፳ ፤ ወይቤሎ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወርቅከ ፡ ወብሩርከ ፡ ምስሌከ ፡ ለይኩንከ ፡ ለሕርትምና ፡

ጴጥሮስም ፡ ወርቅህ፡ ብርህ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ እንዳንት ፡ ለጥፋት ፡ ይሁንብህ ፡

ይመስለከኑ ፡ ዘበወርቅ ፡ ትሣየጦ ፡ ለጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡

ይሁዳ ፡ አንዱን ፡ አካል ፡ ክርስቶስን ፡ ለሠላሳ ፡ ብር ፡ እንደ ፡ ሸጠው ፡ እኛም ፡ አንዱን ፡ አካል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በወርቅ፡በብር፡ የምንሸጠው፡ ይመስልሃልን ።

፳፩ ፤ አልብከ ፡ መክፈልት፡ ወርስት፡ ውስተ፡ ዝ ፡ ነገር ።

በዚህ ፡ ነገር ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ጽዋ ፡ ተራ ፡ የለህም ፡

እስመ ፡ ኢ.ኮነ ፡ ርቱዐ ፡ ልብከ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ በሚያውቀው ፡ ነገር ፡ ልቡናህ ፡ የቀና ፡ አይደለምና ።

፳፪ ፤ ነስሕ ፡ ይእዜኒ ፡ እምእከይከ ፡

አሁንም ፡ ከክፋትህ ፡ ተመለስ ፡

ወተጋነይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ ለምን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እመን ፡

ለእመ ፡ የኀድግ ፡ ለከ ፡ እከየ ፡ ልብከ ፡

እግዚአብሔር ፡ የልቡናህን ፡ ክፋት ፡ ይቅር ፡ ይልህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ። አንድም ፡ እከየ ፡ ልብከ ፡ ልቡናህ ፡ ክፋቱን ፡ ይተውልህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

፳፫ ፤ እስመ ፡ ከመ ፡ ሕምዝ ፡ መሪር ፡ እሬእየከ ፡

ጽኑ፡ኃጢአትን፡ ተመልተህ፡ አይሃለሁና ፡

ወውስተ ፡ ማእሠረ ፡ ዐመፃ ፡ ሀሎከ ።

በማዕሠረ ፡ ክህደትም ፡ ተይዘህ ፡ አይሃለሁና ፡ አለ ፡

፳፬ ፤ ወተሠጥዎሙ ፡ ሲ.ሞን ፡ ወይቤሎሙ ፡ ሰአሉ፡ ሊ.ተ ፡ አንትሙ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኢ.ይብጽሐኒ ፡ ወኢ.ምንትኒ ፡ እምዘ ፡ ትቤሉኒ ።

ሲ.ሞንም ፡ ከነገራችሁኝ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ እንዳይደርስብኝ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለምኑልኝ ፡ አላቸው ፤ ሐተታ ፡ እንዳልሆነለት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ሮም ፡ ወርዶ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ያስተማራቸውን ፡ ምእመናን ፡ ያስት ፡ ጀመረ ፡ ሮም ፡ ወርዶ ፡ ያስትልሃል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፡ ዮሐንስን ፡ አስከትሎ ፡ ሂዶ ፡ ከበር ፡ ሲደርስ ፡ አንድ ፡ ቅብው ፡ አገኘ ፡ እፍ ፡ ቢለው ፡ ዳነ ፡ ሕዝቡ ፡ ተአምራትስ ፡ ይህታ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ተመልሰዋል ፡ ብለህ ፡ እንዳለፈው ፡ ተርክ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ፰ ። ትርፍ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊ.ቀ ፡ ሐዋርያት ፡ ዝም ፡ ትለዋለህ ፡ አለው ፡ ተወው ፡ በምር ፡ ከፍ፡ ይበል ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ አለው ፡ በምር ፡ ከፍ፡ ሲ.ል ፡ አይቶ ፡ ቢ.ያማትብባቸው ፡ አጋንንት ፡ ትተውት ፡ ሸሹ ፡ ወርዶ ፡ ተንቈጫቍጮ ፡ ሙቷል ።

፳፭ ፤ ወእሙንቱሰ ፡ ሶበ፡ነገሩ ፡ ወአስምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተሠውጡ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወመሀሩ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ብዙኃት ፡ አህጉረ ፡ ሰማርያ ።

እነሱም ፡ ወንጌልን ፡ አስተምረው ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፡ በሰማርያ ፡ መንገድ ፡ ለመንገድ ፡ እያስተማሩ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ።

## ክፍል ፡ ፲፮ ።

፳፮ ፤ ወነበበ፡መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ለፊልጶስ ፡

ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ ለፊልጶስ ፡ ነገረው ፡

ወይቤሎ ፡ ተንሥእ ፡

በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ተነሥተህ ፡

ወሑር ፡ ጊዜ ፡ ቀትር ፡ ፍኖተ ፡ በድው ፡ ዘያወርድ ፡ እምኢ.የሩሳሌም ፡ ለጋዛ ።

ነበቦ ፡ ጊዜ ፡ ቀትር ፡ ከኢ.የሩሳሌም ፡ ወደ፡ ጋዛ ፡ የሚወስደውን ፡ መንገድ ፡ ይዘህ ፡ ሂድ ፡ ብሎ ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ነገረው ።

፳፯ ፤ ወተንሥአ ፡ ወሖረ ፡

ተንሥአ ፡ ጊዜ ፡ ቀትር ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡ ሄደ ፡

ወረከበ ፡ ብእሴ ፡ እምሰብአ ፡ ኢ.ትዮጵያ ፡ ኀፅዋ ፡ ለህንደኬ ፡ ንግሥተ ፡ ኢ.ትዮጵያ ፡

ከኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግሥት ፡ የህንደኬ ፡ ባለሟል ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አገኘ ፡

ወመጋቢ.ሃ ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ መዛግብቲሃ ፡

የቃቤት ፡ በጅሮወንዲ ፡ የሚሆን ፡

ወሖረ ፡ ኢ.የሩሳሌም ፡ ይስግድ ።

ወደ ፡ ኢ.የሩሳሌም ፡ እጅ ፡ ሊ.ነሣ ፡ ሂዶ ፡ ነበር ፡

፳፰ ፤ ወእንዘ ፡ ይገብእ ፡ ነበረ ፡ ዲበ ፡ ሠረገላ ፡

እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ሲ.መለስ ፡ በሠረገላ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡

ወያነብብ ፡ መጽሐፈ ፡ ኢ.ሳይያስ ፡ ነቢ.ይ ።

መጽሐፈ ፡ ኢ.ሳይያስ ፡ ይደግም ፡ ነበር ።

፳፱ ፤ ወይቤሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ለፊልጶስ፡ ሑር፡ ትልዋ ፡ ለዝ ፡ ሠረገላ ።

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፊልጶስን፡ ይኸንን ፡ ባለሠረገላ ፡ ሂድ ፡ ተከተለው ፡ አለው ።

፴ ፤ ወሮጸ ፡ ፊልጶስ ፡ ወበጽሐ ፡

ፈጥኖ ፡ ተከትሎ ፡ ደረሰ ፡

ወሰምዖ ፡ ያነብብ ፡ መጽሐፈ ፡ ኢ.ሳይያስ ፡ ነቢ.ይ ፡

በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ መጽሐፈ ፡ ኢ.ሳይያስ ፡ ሲ.ደግም ፡ ሰማው ፡

ወይቤሎ ፡ ፊልጶስ ፡ ተአምርኑ ፡ እንከ ፡ ዘታነብብ ።

ፊልጶስም፡ የምትደግመውን ፡ ምስጢሩን፡ ታውቀዋለህን ፡ አለው ።

፴፩ ፤ ወይቤሎ ፡ ኀፅው ፡ በአይቴ፡ አአምር፡ ለእመ ፡ አልቦ ፡ ዘመሀረኒ ፡

ያስተማረኝ ፡ ሳይኖር ፡ በምን ፡ አውቀዋለሁ ፡ አለው ።

ወአስተብቍዖ ፡ ለፊልጶስ ፡ ከመ ፡ ይዕርግ ፡ ወይንበር ፡ ኀቡረ ፡ ምስሌሁ ።

ፊልጶስን ፡ ወጥቶ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ና ፡ ወጥተህ ፡ ተቀመጥ ፡ ብሎ ፡ ማለደው ፡



www.ethiopianorthodox.org

፴፪ ፤ ወነገረ ፡ መጽሐፍሰ ፡ ኀበ ፡ ያነብብ ፡ ከመዝ ፡ ይብል ፡

የሚደግመውም ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ነበር ፡

መጽአ ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡ ይጠባሕ ፡

እንደ ፡ በግ ፡ ሊሠዋ ፡ መጣ ፡

ወከመ ፡ በግዕ ፡ ዘኢይነብብ ፡ በቅድመ ፡ ዘይቀርፆ ፡

በግ ፡ ጠጉሩን ፡ በሚሸልተው ፡ ፊት ፡ ከቀን ፡ ሐሩር ፡ ከሌሊት ፡ ቍር ፡ የምጠበቅበትን ፡ ጠጉሬን ፡ በምን ፡ ዕዳዬ ፡ ነው ፡ እንዳይል ፡

ከማሁ ፡ ኢከሠተ ፡ አፉሁ ፡ በሕማሙ ።

ይዘው ፡ አስረው ፡ በገረፉት፡ ጊዜ፡ በምን ፡ ዕዳዬ ፡ ነው ፡ አላለም ፡ የሚል ፡ ነው ። አንድም፡በግ፡በሚያርደው፡በሚአወራርደው፡ ፊት ፡ በምን ፡ ዕዳዬ ፡ ነው ፡ እንዳይል ፡ ይዘው ፡ አስረው ፡ ገርፈው ፡ ሰቅለው ፡ በገደሉት ፡ ጊዜ ፡ በምን ፡ ዕዳዬ ፡ ነው ፡ አላለም ፡ የሚል ፡ ነበር ፡ ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፯ ።

፴፫ ፤ ወተንሥአ ፡ እምኵነኔ ፡ ወእምነ ፡ ሞቅሕ ፡

ተነሥአ ፡ ማሠር ፡ መግረፍ ፡ መፍረድ ፡ መግደል ፡ ገንዘቡን ፡ ተቀማ ። አንድም ፡ ተንሥአ ፡ ይዘው ፡ አስረው ፡ ሰቅለው ፡ ከገደሉት ፡ በኋላ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ተነሣ ፡ የሚል ፡ ነው ፡

ወመኑ ፡ ይነግር ፡ ልደቶ ፡ እስመ ፡ ተአተተ ፡ እምድር ፡ ሕይወቱ ።

አነዋወሩ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ልዩ ፡ ነውና ፡ ምንም ፡ ልዩ ፡ ቢሆን ፡ ሰማያዊ ፡ ልደቱን፡ ማን ፡ ይነግራል ፡ ብለው ፡ (ማን ፡ ይመሰክራል ፡ ማለት ፡ ነው) ። አንድም ፡ ሕይወቱ ፡ ነቢይ ፡ ሕይወቱ ፡ ሐዋርያ ፡ ከዚህ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ተለይቷልና ፡ ምድራዊ ፡ ልደቱን ፡ ማን ፡ ይነግራል ፡ ብለው ፡ ይዘው ፡ አስረው ፡ ሰቅለው ፡ በገደሉት ፡ ጊዜ ፡ በምን ፡ ዕዳዬ ፡ ነው ፡ አላለም ፡ የሚል ፡ ነው ።

፴፬ ፤ ወተመይጠ ፡ ኀበ ፡ ፊልጶስ ፡ ውእቱ ፡ ኅፅው ፡

ያ ፡ ኅፅውም ፡ ወደ ፡ ፊልጶስ ፡ ተመልሶ ፡

ወይቤሎ ፡ ብቍዐኒ ፡ ንግረኒ ፡ በእንተ ፡ መኑ ፡ ይብል ፡ ነቢይ ፡ ከመዝ ፡

ነቢይ ፡ ይህን ፡ የተናገረ ፡ ስለማን ፡ ነው ፡ እስቲ ፡ በጅ ፡ በለኝ ፡ ንገረኝ ፡

በእንተ ፡ ርእሱኑ ፡

ስለ ፡ ራሱ ፡ ነውን ፡

ወሚመ ፡ በእንተ ፡ ካልእ ፡

ወይስ ፡ ለሌላ ፡ አለው ፡

፴፭ ፤ ወከሠተ ፡ አፉሁ ፡ ፊልጶስ ፡

ፊልጶስም ፡ ነገር ፡ ጀመረ ፡ (ጥቅ) ፡ ከሠተ ፡ አፉሁ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከሠተ ፡ አፉሁ ፡ ኢዮብ ፡ እንዲል ፡

ወአኀዘ ፡ ይምሀሮ ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ወይፌክር ፡ሎቱ ፡ በውእቱ ፡ መጽሐፍ ።

ውእተ ፡ መጽሐፈ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ እየተረጐመ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ይነግረው ፡ ጀመረ ።

፴፮ ፤ ወእንዘ ፡ የሐውሩ ፡ በጽሑ ፡ ኀበ ፡ ማይ ፡

እየተረጐመ ፡ እየነገረው ፡ ሲሄዱ፡ ከውኃ፡ ደረሱ ፡ እንዲህ ፡ እያልን ፡ ብናስተምር ፡ ብናጠምቅ ፡ ይከለክሉናል ፡ አለው ፡

ወይቤሎ ፡ ውእቱ ፡ ኅፅው ፡ ነዋ ፡ ማይ ፡ ወመኑ ፡ ይከልአኒ ፡ ተጠምቆ ።

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ ውኃ ፡ አለ ፡ ብጠመቅ ፡ ማን ፡ ይከለክለኛል ፡ ብሎ ።

www.ethiopianorthodox.org



፴፯ ፤ ወይቤሎ ፡ ፊልጶስ ፡ ይደልወከ ፡ ትእመን ፡ በኵሉ ፡ ልቡናከ ፡ ወተመይጠ ፡ ወይቤ ፡ አነ ፡ አአምን ፡ ከመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ውእቱ ፡ ወልዱ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ፊልጶስም ፡ በፍጹም ፡ ልቡናህ፡ ልታምን፡ ይገባሃል ፡ ተመልሶም ፡ እኔ ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አምናለሁ ፡ አለው ፡ ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፲፮ ። ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፮ ።

፴፰ ፤ ወአዘዘ ፡ ያቅሙ ፡ ሠረገላሁ ፡

ሠረገላውን ፡ ግቱልኝ ፡ አለ ፡

ወአቀሙ ፡

ገቱለት ፡

ወወረዱ፡ኅቡረ፡ኀበ፡ ማይ፡ ፊልጶስ፡ ወውእቱ፡ ኅፅው፡

ፊልጶስና ፡ ያ ፡ ኅፅው ፡ ተያይዘው ፡ ወደ ፡ ውኃው ፡ ወረዱ ፡

ወአጥመቆ ፡

አጠመቀው ።

፴፱ ፤ ወወፂአ ፡ እማይ ፡

ተጠምቆ ፡ ከውኃው ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡

መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሠጦ ፡ ለፊልጶስ ፡

ፊልጶስን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕይወት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነጥቆ ፡ ወሰደው ፡ ሐተታ ፡ ቅብዓ ፡ ትፍሥሕት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ ወረደለት ፡ ለማጠየቅ ። አንድም ፡ በደግ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ተጠምቄ ያለሁሳ ፡ ብሎ ፡ ደስ ፡ እንዲለው ፡

ወኢርእዮ ፡ እንከ ፡ ውእቱ ፡ ኅፅው ፡

ያ ፡ ኅፅውም ፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ወዲህ ፡ ፊልጶስን ፡ አላየውም ፡

ወአተወ ፡ ብሔሮ ፡ እንዘ ፡ ይትፌሣሕ ።

ደስ ፡ እያለው ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡ ገባ ፡ በደግ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ተጠምቄያለሁሳ ፡ ለካ ፡ በደግ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ተጠምቄያለሁን ፡ እያለ ፡ ቅብዓ ፡ ትፍሥሕት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብሏልና ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ፩ ፡ ነገሥ ፡ ፲፰ ፡ ፲፪ ።

፵ ፤ ወበጽሐ ፡ ፊልጶስ ፡ ሀገረ ፡ አዛጦን ፡

ፊልጶስም ፡ አዛጦን ፡ ወደሚባል ፡ አገር ፡ ደረሰ ።

ወአንሶሰወ ፡ ወመሀረ ፡ በኵሉ ፡ አህጉር ፡ እስከ፡ በጽሐ ፡ ቂሣርያ ፡

ቂሳርያ ፡ እስቲደርስ ፡ ድረስ ፡ በየሀገሩ ፡ እየዞረ ፡ አስተማረ ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፰ ፡ ፱ ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ፡

፩ ፤ ወሳውልሰ ፡ ዓዲሁ ፡ ይትቄየም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡

ሳውል ፡ ግን ፡ ገና ፡ ምእመናንን ፡ ይጣላ ፡ ነበር ፡

ወይቀትሎሙ ፡ ለአርዳአ ፡ እግዚእነ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡

በጌታችን ፡ ባመኑ ፡ በምእመናን ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ ያጸናባቸው ፡ ነበር ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ሂዶ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ፫ ፡ ፳፪ ፡ ፫—፳፩።

፪ ፤ ወሰአለ ፡ በኀቤሆሙ ፡ መጽሐፈ ፡ መባሕት ፡ ለሀገረ ፡ ደማስቆ ፡ ወለመኳርብት ፡

በደማስቆ ፡ ላሉምኵራባት፡ ቃስድነት ፡ሹመት፡ ተካሰሰ፡እንደ፡ሌባ፡አድም፡ያለ፡ነው

ለእመ ፡ ቦ ፡ ዘይረክብ ፡ በፍኖት ፡ እድ ፡ ወአንስት ፡ ከመ ፡ ያእትዎሙ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መቁሐኒሆሙ ፡

በመንገድ፡ የሚያገኘው ፡ ቢኖር ፡ ሴቶችንም ፡ ወንዶችንም፡ እያሰረ ፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይወስዳቸው ፡ ዘንድ ።

፫ ፤ ወእንዘ ፡ የሐውር ፡ ሶበ ፡ አልጸቀ ፡ ለሀገረ ፡ ደማስቆ ፡ ግብተ ፡ በረቀ ፡ መብረቅ ፡ እምሰማይ ፡ ላዕሌሁ ፡

ቃሰድነት ፡ ሹመት ፡ ተካሶ ፡ ሲሄድ ፡ ደማ ስቆ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ድንገት ፡ ከወደ ፡ ሰማይ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ብርሃን ፡ በራ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፰ ።

፬ ፤ ወወድቀ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡

ወደ ፡ ምድር ፡ ወደቀ ፡

ወሰምዐ ፡ ቃለ፡ዘይቤሎ ፡ ሳውል ፡ ሳውል ፡ ለምንት ፡ ትሰድደኒ ፡

ባገራቸው ፡ ደጊመ ፡ ቃል ፡ ልማድ ፡ ነው፡ አብርሃም ፡ አብርሃም ፡ ማርታ ፡ ማርታ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዳለ ፡ ሳው ል ፡ ከዋልሁበት ፡ አላሳድር ፡ ካደርሁበት፡ አላውል ፡ ለምን ፡ትለኛለህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰማ ፡ የምእመናንን ፡ ስደት ፡ ስደ ት ፡ አድርጎ ፡ ትሰድደኒ ፡ አለ ። አንድም፡ ባንት ፡ በምእመናን፡ እንዳላድር፡ ለምን ፡ ታደርገኛለህ ። አንድም ፡ ትሰድድ ፡ ብየ ፡ ሲል ፡ ነው፡ ምእመናንን ፡ ከዋሉበት ፡ አላ ሳድር ፡ ካደሩበት ፡ አላውል ፡ ለምን ፡ ት ልብኛለህ ፡

ይብእሰከ ፡ ረጊጽ ፡ ውስተ ፡ ቀኖት ፡ በሊኅ ፡

ሰይፍ ፡ የረገጠ ፡ እሱ ፡ ይጐዳል ፡ እንጅ ፡ ሰይፉ ፡ ይጐዳልን ፡ እንደዚህስ ፡ ሁሉ ፡ አንተ ፡ ትጐዳለህ ፡ እንጅ ፡ እኔ ፡እጐዳለ ሁን ። አንድም ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ተደላ ደልህ ፡ እንደ ፡ ተቀማጠልህ ፡ አትቀርም፡ የኔን ፡ ነገር ፡ ስታስተምር ፡ ኔሮን ፡ ቄሣር፡ በሰይፍ ፡ አስመትቶ ፡ ይገልሃል ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰማ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፴፱ ።

፭ ፤ ወይቤሎ ፡ መኑ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ማነህ ፡

ወይቤሎ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ናዝራዊ ፡ ዘአንተ፡ ትሰድደኒ ፡

አንተ ፡ ከዋልሁበት ፡ አላሳድር ፡ ካደርሁ በት ፡ አላውል ፡ የምትለኝ ፡ የናዝሬቱ ፡ ሰው ፡ ኢየሱስ ፡ ነኝ ፡ አለው ፡ ሐተታ ፡ ቍ ፡ ፬ ፡ ተመልከት ።

፮ ፤ ወይቤሎ ፡ እግዚኦ ፡ ምንተኑ ፡ እግበር ፡ አነ ፡

አቤቱ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ አለው ፡

ወይቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ተንሥእ ፡ ወባእ ፡ ሀገረ ፡

ተነሥተህ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ግባ ፡

ወበህየ ፡ ይነግሩከ ፡ ዘይደልወከ ፡ ትግበር ፡

ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ የሚገባህን ፡ በሀገር ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ይነግሩሃል ።

፯ ፤ ወሰብእሰ ፡ እለ ፡ ምስሌሁ ፡ ቆሙ ፡ ያፀምኡ ፡ ነገሮ ፡

ከሱ ፡ ጋራ ፡ ቆመው ፡ የነበሩም ፡ ሰዎች ፡ ነገሩን ፡ ይሰሙ ፡ ነበር ፡

ወአልቦ ፡ ዘይሬእዩ ፡

የሚያዩት ፡ ግን ፡ አልነበረም ፡

፰ ፤ ወተንሥአ ፡ ሳውል ፡ እምድር ፡

ሳውልም ፡ ከወደቀበት ፡ ተነሣ ፡

ወእንዘ ፡ ክሡታት ፡ አዕይንቲሁ ፡ አልቦ ፡ ዘይሬኢ ፡

ዓይኑ ፡ ተገልጦ ፡ ሳለ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሚ ያየው ፡ አልነበረም ፡

ወእንዘ ፡ ይመርሕዎ ፡ አብእዎ ፡ ደማስቆ ፡

እየመሩ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ አገቡት ።

፱ ፤ ወነበረ ፡ ህየ ፡ ሠሉስ ፡ ዕለተ ፡ እንዘ ፡ ኢይሬኢ፡ ወኢይበልዕ ፡ ወኢይሰቲ ፡

በደማስቆም ፡ ብርሃን ፡ ሳያይ ፡ እህል ፡ ውኃ ፡ ሳይቀምስ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሰነበተ ።

፲ ፤ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ በሀገረ ፡ ደማስቆ ፡ ዘእምውስተ ፡ አርድእት ፡ ዘስሙ ፡ ሐናንያ ፡

አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ ሐናንያ ፡ ደማ



ስቆ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ከሰብዓ ፡ አርድ እት ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡ ሐናንያ ፡ የሚባል፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡

ወአስተርአዮ ፡ እግዚእነ ፡ በራእይ ፡

ጌታችን ፡ ሌሊት ፡ በራእይ ፡ ተነጋገረው ፡

ወይቤሎ ፡ ሐናንያ ፡

ሐናንያ ፡ አለው ፡

ወይቤ ፡ ነየ ፡ እግዚኦ ፡

አቤት ፡ እነሆ ፡ አለው ።

፲፩ ፤ ወይቤሎ ፡ እግዚእነ ፡ ተንሥእ ፡ ወሑር ፡ ሰኰተ ፡ እንተ ፡ ይብልዋ ፡ ርትዕት ፡

ተነሥተህ ፡ ርትዕት ፡ ስሟ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ርትዕት ፡ ወደሚሏት ። አንድም ፡ የቀ ናች ፡ ወደምትሆን ፡ አደባባይ ፡ ሂድ ፡ አለው ፡

ወኅሥሥ ፡ በቤተ ፡ ይሁዳ ፡ ዘስሙ ፡ ሳውል ፡ ዘሀገረ ፡ ጠርሴስ ፡

በቤተ ፡ ይሁዳ ፡ የጠርሴስ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የሚሆን፡ ሳውል፡ የሚባል፡ ሰው ፡ ጠይቅ ፡ አለው ፡ (ዕርቅ) ፡ ስንክሳር ፡ በቤተ ፡ ገብ ርኤል ፡ ይላል ፡ ከዚህ ፡ በቤተ ፡ ይሁዳ ፡ አለ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡ ስም ፡ አለውና ። አንድም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ካንዱ ፡ ቤት ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ካንዱ ፡ ቤት ፡ አድሯልና ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ናሁ ፡ ይጼሊ ፡

እሱ ፡ አሁን፡ ይጸልያልና፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፴፱ ።

፲፪ ፤ ወእንዘ ፡ ይጼሊ ፡ ሳውል ፡ አስተርአዮ ፡ ብእ ሲ ፡ በአምሳለ ፡ ሐናንያ ፡

ሳውልም ፡ ሲጸልይ ፡ ጌታ ፡ ሐናንያን ፡ መስሎ ፡ ታየው ፡ ተነጋገረው ፡

ቦአ ፡ ኀቤሁ ፡

ወደሱ ፡ ገባ ፡

ወወደየ ፡ እዴሁ ፡ ዲቤሁ ፡

በላዩ ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ጫነበት ፡

ከመ ፡ ይርአይ ፡

ብርሃን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ።

፲፫ ፤ ወአውሥአ ፡ ሐናንያ ፡ ወይቤ ፡ እግዚኦ ፡ ሰማዕኩ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ በኀበ ፡ ብዙኃን ፡

አውሥአ ፡ ለላይኛው ፡ ነው ፡ ሐናንያም ፡ የዚያን ፡ ሰው ፡ ነገር ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰምቻለሁ ፡

ኵሎ ፡ ዘይገብር ፡ እኩየ ፡ ዲበ ፡ ቅዱሳኒከ ፡ በኢየሩ ሳሌም ፡

በኢየሩሳሌም ፡ ባሉ ፡ ምእመናን ፡ ላይ ፡ ይሠራው ፡ የነበረውን ፡ ክፉ ፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰምቻለሁ ፡

፲፬ ፤ ወዝየኒ ፡ አስተበዊሖ ፡ በኀበ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ መጽአ ፡

ከሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ዘንድ ፡ ሂዶ ፡ ቃሰድ ነት ፡ ሹመት ፡ ተካሶ ፡ ከዚህ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ሰምቻለሁ ፡

ከመ ፡ ይሞቅሖሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይጼውዑ ፡ ስመከ ፡

ስምህን ፡ የሚጠሩ ፡ በስምህ ፡ ያመኑ ፡ ምእመናንን ፡ እያሠረ ፡ ይወስዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፪ ።

፲፭ ፤ ወይቤሎ ፡ እግዚእነ ፡ ተንሥእ ፡ ወሑር ፡

ጌታም ፡ ተነሣ ፡ ሂድ ፡ አለው ፡

እስመ ፡ ንዋየ ፡ ኅሩየ ፡ ረሰይክዎ ፡ ሊተ ፡

ምርጽ ፡ ዕቃ ፡ አድርጌዋለሁና ፡

ከመ ፡ ይጹር ፡ ስምየ ፡ በቅድመ ፡ አሕዛብ ፡ ወነገሥት ወደቂቀ ፡ እስራኤል ።

ስሜን ፡ በነገሥታተ ፡ አሕዛብ ፡ በመኳ ንንተ፡ አሕዛብ ፡ በነገሥታተ ፡ እስራኤል ፡ በመኳንንተ፡ እስራኤል ፡ ፊት፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ ሐተታ ፡ ሰው ፡ የሚሞትበትን ፡

www.ethiopianorthodox.org

ነፍጥ ፡ ተሸክሞ ፡ እንዲሄድ ፡ እሱም ፡
የጌታን ፡ ነገር ፡ እያስተማረ ፡ ይሞታልና ፡
ከመ ፡ ይጹር ፡ ስምየ ፡ አለ ፡ ም ፡ ፳፭ ፡
፲፫ ። ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፩ ።

፲፮ ፤ ወአነ ፡ አርእዮ ፡ መጠነ ፡ ሀለዎ ፡ ይሕምም ፡ በእንተ ፡ ስምየ ፡

በስሜ ፡ ስላመነ ፡ በስሜ ፡ ስለ ፡ ተጠራ ፡
ስሜን ፡ ስለ ፡ አስተማረ ፡ መከራ ፡ ይቀ
በል ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ ነግሬዋለሁ ፡
ቊ ፡ ፳፫ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫ ።

፲፯ ፤ ወሶቤሃ ፡ ሖረ ፡ ሐናንያ ፡

ሐናንያም ፡ ፈጥኖ ፡ ሂዶ ፡

ወቦአ ፡ ቤቶ ፡

ከቤት ፡ ገብቶ ፡

ወወደየ ፡ እዴሁ ፡ ዲቤሁ ፡

እጁን ፡ ጫነበት ፡

ወይቤሎ ፡ ሳውል ፡ እኁየ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፈነወኒ ፡ ኀቤከ ፡

ሳውል ፡ ወንድሜ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ወዳንተ ፡ ልኮኛል ፡

ዘአስተርአየከ ፡ በፍኖት ፡ እንዘ ፡ ትመጽእ ፡

ስትመጣ ፡ በመንገድ ፡ የተነጋገረህ ፡

ከመ ፡ ትርአይ ፡

ፈነወኒ ፡ ከመ ፡ ትርአይ ፡ ብርሃን ፡ ታይ ፡
ዘንድ ፡ ላከኝ ፡

ወይምላእ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌከ ፡

ልጅነትን ፡ ይሰጥህ ፡ ዘንድ ።

፲፰ ፤ ወሶቤሃ ፡ ተሥዕሳ ፡ እምአዕይንቲሁ ፡ ከመ ፡ ዘሣሬት ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ከዐይኑ ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡
ወተር ፡ ያለ ፡ ተገፎ ፡ ወደቀለት ፡ ከመ ፡
ዘቅሣር ፡ ይላል ፡ እንደ ፡ ዓሣ ፡ ገለፈት ፡
ያለ ፡ ተቀርፎ ፡ ወደቀለት ፡

ወተከሥታ ፡ አዕይንቲሁ ፡

ዐይኑ ፡ በራ ፡

ወርእየ ፡ ሶቤሃ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ብርሃን ፡ አየ ፡

ወተንሥአ ፡ ወተጠምቀ ፡

ተነሥቶ ፡ አመነ ፡ ተጠመቀ ።

፲፱ ፤ ወበልዐ ፡ እክለ ፡ ወጸንዐ ፡

እህል ፡ በልቶ ፡ ጸና ፡

ወነበረ፡ ደማስቆ፡ ኅዳጠ፡ መዋዕለ፡ ምስለ፡ አርድእት ፡

በደማስቆ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከምእመናን ፡
ጋራ ፡ ኖረ ።

፳ ፤ ወሰበከ ፡ በጊዜሃ ፡ በምኵራባት ፡ ወመሀረ ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡

ይህ ፡ ወላምጢ ፡ ይሉኛል ፡ ሳይል ፡ ፈጥ
ኖ ፡ ከምኵራቡ ፡ ገብቶ ፡ ወልደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የጌታችን ፡ የኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡ አስተማረ ።

፳፩ ፤ ወአንከሩ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሰምዑ ፡

ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሲያ
ስተምር ፡ የሰሙት ፡ ሁሉ ፡ አደነቁ ፡

ወይቤሉ ፡ አኮኑ ፡ ዝንቱ ፡ ዘኮነ ፡ ይሰድዶሙ ፡ ለእለ ፡ ይሰምዩ ፡ ዘንተ ፡ ስመ ፡ በኢየሩሳሌም ፡

በኢየሩሳሌም ፡ ይህን ፡ ስም ፡ የሚጠሩ
ትን ፡ ሰዎች ፡ ከዋሉበት ፡ አላሳድር ፡ ካደ
ሩበት ፡ አላውል ፡ ይል ፡ የነበረው ፡ አይ
ደለምን ፡

ወዝየኒ ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ መጽአ ፡ ከመ ፡ ይሞቅሖሙ ፡ ወይሰዶሙ ፡ ኀበ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡

እያሰረ ፡ ከሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ይወስዳቸው ፡
ዘንድ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ቃስድነት ፡ ሹመ
ት ፡ ተካሶ ፡ ከዚህ ፡ መጥቶ ፡ የነበረው ፡
አይደለምን ፡ ብለው ፡ አደነቁ ፤ ቊ ፡ ፩ ፡
፲፬ ። ም ፡ ፰ ፡ ፩ ፡ ፳፯ ፡ ፲ ።

ግብረ ፡ ሐዋርያት ። ፹፱

፳፪ ፤ ወሳውልሰ ፡ ፈድፋደ ፡ ይጸንዖሙ ፡ ወይመውእሙ ፡ ለአይሁድ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ደማስቆ ፡

ሳውል ፡ ግን ፡ በደማስቆ ፡ ያሉ ፡ አይሁ
ድን ፡ እየተከራከረ ፡ ምላሽ ፡ ያሳጣቸው ፡
ነበር ፡

ወያበጽሕ ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡

መቅደስ ፡ ትትሐነጽ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ፡
ንጉሥ ፡ ወእምዝ ፡ ትትመዘበር ፡ ተብሎ ፡
ተነግሮለት ፡ የመጣው ፡ እሱ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ ያስረዳቸው ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፳፰ ።

፳፫ ፤ ወእምድኅረ ፡ ብዙኅ ፡ መዋዕል ፡ ተማከሩ ፡ አይሁድ ፡ ይቅትልዎ ፡ ለሳውል ፡

ከብዙ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሳውልን ፡ ይገድ
ሉት፡ዘንድ፡እንግደለው፡ ብለው፡ መከሩ ።

፳፬ ፤ ወአእመሮሙ ፡ ሳውል ፡ ምክሮሙ ፡ ዘይፈቅዱ ፡ ይግበሩ ፡ ላዕሌሁ ፡

ሳውልም ፡ ሊገሉት ፡ እንደ ፡ መከሩ ፡
አውቆባቸው ፡ ነበር ፡

ወየዐቅቡ ፡ አናቅጸ ፡ ሀገር ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ከመ ፡ ይቅትልዎ ፡

ይገሉት ፡ ዘንድ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊ
ትም ፡ በሩን ፡ ይዘው ፡ ይጠብቁት ፡ ነበር።

፳፭ ፤ ወነሥእዎ ፡ አርድእት ፡ ሌሊተ ፡

ምእመናን ፡ ግን ፡ ሌሊት ፡ ሰርቀው ፡

ወአውረድዎ ፡ በአስፈሬድ ፡ እንተ፡ ተድባበ፡ ቅጽር ፡

በመስኮት ፡ አውጥተው ፡ ከቀጸላው ፡
በዝንግሬር ፡ አውርደው ፡ አሸሸተው ፡
ሰደዱት ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፴፪ ፡ ፴፫ ።

፳፮ ፤ ወበጺሖ ፡ ሳውል ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኀሠሦሙ ፡ ለአርድእት ፡ ይትራከቦሙ ፡

ሳውልም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡
ምእመናንን ፡ ሊገናኛቸው ፡ ወደደ ፡

ወፈርህዎ ፡ ኵሎሙ ፡

እነሱ ፡ ግን ፡ ፈርተው ፡ አንገናኝም ፡ አሉ፡

ወኢአምንዎ ፡ ከመ ፡ ገብአ ፡ ኀበ ፡ አርድእት ፡

ወደ ፡ እነሱ ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ አላመ
ኑም ፡ ነበርና ፡ ገላት ፡ ፩ ፡ ፲፯ ።

፳፯ ፤ ወነሥኦ ፡ በርናባስ ፡ ወወሰዶ ፡ ኀበ ፡ ሐዋርያት ፡

በርናባስም ፡ ወስዶ ፡ ከሐዋርያት ፡ አገ
ናኘው ፡

ወነገሮሙ ፡ ጳውሎስ ፡ ዘከመ ፡ አስተርአዮ ፡ እግዚእነ ፡ በፍኖት ፡

ጌታ ፡ በመንገድ ፡ እንደታየው ፡

ወዘከመ ፡ ተናግሮ ፡

እንደ ፡ ተነጋገረው ፡ ነገራቸው ፡

ወዘከመ ፡ መሀረ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ በደማስቆ ።

በደማስቆ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክር
ስትስ ፡ ስም ፡ እንዳስተማረ ፡ አለ ፡ ስሙ ፡
ሕይወት ፡ መድኃኒት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እን
ዳስተማረ ፡ ነገራቸው ፡ ቊ ፡ ፳ ።

፳፰ ፤ ወነበረ ፡ ይበውእ ፡ ወይወፅእ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በኢየሩሳሌም ፡

በኢየሩሳሌም ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ እየወጣ ፡
እየገባ ፡ እያስተማረ ፡ ኖረ ፡

ወይሜህር ፡ ክሡተ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ።

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ስም ፡
ገልጦ ፡ እያስተማረ ፡ ኖረ ፡

፳፱ ፤ ወይትዋቀሥሙ ፡ ለአረሚ ፡

ከዕርዕ ፡ የመጡ ፡ አረማውያንንም ፡ ይከ
ራከራቸው ፡ ነበር ፡

ወፈቀዱ ፡ ካዕበ ፡ እሙንቱ ፡ ይቅትልዎ ፡

ካዕበ ፡ ለላይኛው ፡ ነው ፡ ዳግመኛ ፡ ሊገ
ሉት ፡ ወደዱ ።

፴ ፤ ወአእሚሮሙ ፡ ቢጹ ፡ አውረድዎ ፡ ቂሣርያ ፡

ሊገሉት ፡ እንደ ፡ ወደዱ ፡ አውቀው ፡ ም
እመናን ፡ አሸሸተው ፡ ወደ ፡ ቂሳርያ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ሰደዱት ፡ ምርጽ ፡ ዕቃ ፡ ብሎታልና ፡ ያሸሹታል ፡ ሆነ ፡

ወእምዝ ፡ ፈነውዎ ፡ ጠርሴስ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጠርሴስ ፡ ሸኙተው ፡ ሰደዱት ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፳፫ ።

፴፩ ፤ ወነበራ ፡ ኵሎን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በሰላም ፡ ዘይሁዳ ፡ ወሰማርያ ፡ ወገሊላ ፡

በይሁዳ ፡ በሰማርያ ፡ በገሊላ ፡ ያሉ ፡ ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ባንድነት ፡ በዕረፍት ፡ ኖሩ ፡

ወተሐንጸ ፡ ወሖራ ፡ በፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ ጸንተው ፡ ኖሩ ፡

ወበዝኁ ፡ ሕዝብ ፡ በትምህርተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡

ሕዝቡም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በገለጸው ፡ በወንጌል ፡ ትምህርት ፡ ፍጹማን ፡ ሆኑ ።

፴፪ ፤ ወእምዝ ፡ አንሶሰወ ፡ ጴጥሮስ ፡ በኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ልዳ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጴጥሮስ ፡ በልዳ ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ እየዞረ ፡ አስተማረ ።

፴፫ ፤ ወረከበ ፡ በህየ ፡ ብእሴ ፡ ዘስሙ ፡ ኤንያ ፡

በልዳም ፡ ኤንያ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ አገኘ ፡

ወሰመንቱ ፡ ዓመቱ ፡ እምዘ ፡ ደወየ ፡ ወሰከበ ፡ ውስተ ፡ ዐራት ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ መፃጕዕ ፡

ከታመመ ፡ አለ ፡ በደዌ ፡ ዳኛ ፡ በአልጋ ፡ ቍራኛ ፡ ከተያዘ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ሁኖት ፡ ነበር ፡ ዘሠላሳ ፡ ወሰመንቱ ፡ ዓመቱ እምዘ ፡ ደወየ ፡ ይላል ፡ ከታመመ ፡ አለ ፡ በደዌ ፡ ዳኛ ፡ ባልጋ ፡ ቍራኛ ፡ ከተያዘ ፡ ሠላሳ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ የሆነው ፡ ድውይ ፡ ነበር ፡ መፃጕዕ ፡ ነውና ፡ ሰከበ ፡ ሐተታ ፡ የቀደመ ፡ መፃጕዕ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ሠላሳ ፡ ስምንት ፡ ቢል ፡ የተመቸ ፡ ስምንት ፡ ቢል ፡ የጸናበትን ፡ ለይቶ ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ስምንት ፡ ቢል ፡ የተመቸ ፡ ሠላሳ፡ስምንት ፡ ቢል ፡ የሠላሳ ፡ ስምንት፡ ዓመት ፡ ድውይ ፡ በተፈወሰበት ፡ ኃይል ፡ ከተፈወሰ ፡ ብሎ ።

፴፬ ፤ ወይቤሎ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኤንያ ፡ ተሣሃለከ ፡ ያሕዩከ ፡ ኢያሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ጴጥሮስም ፡ የቀደመ ፡ መፃጕዕ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ኤንያ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ይቅር፡ ብሎህ ፡ ነበር ፡ ይለዋል ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይቅር ፡ አለህ ፡ ይለዋል ፡

ተንሥእ ፡ ወንሣእ ፡ ዐራተከ ፡

ተነሥተህ ፡ አልጋህን ፡ ተሸክመህ ፡ ሂድ፡ ብሎህ ፡ ነበር ፡ ይለዋል ፡ ተነሥተህ ፡ አልጋህን ፡ ተሸክመህ ፡ ሂድ ፡ አለው ፡

ወተንሥአ ፡ ሶቤሃ ፡ ወነሥአ ፡ ዐራቶ ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡ አልጋውን ፡ ተሸክሞ ፡ ሄደ ።

፴፭ ፤ ወርእይዎ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ልዳ ፡ ወሲዶና ፡ ወተመይጡ ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ ፡

በልዳ ፡ በሲዶና ፡ የሚኖሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች፡ ባዩት ፡ ጊዜ፡ በጌታችን፡ እያመኑ፡ ከገቢረ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመለሱ ።

፴፮ ፤ ወበሀገረ ፡ ኢዮጴ ፡ ሀለወት ፡ አሐቲ ፡ ረድእት ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ጣቢታ ፡

ኢዮጴ ፡ በሚባል ፡ ሀገር ፡ ጣቢታ ፡ የምትባል ፡ አንዲት ፡ ምእመን ፡ ነበረች ፡

ዘበትርጓሜሁ ፡ ይብልዋ ፡ ዶርቃስ ፡

ባንድ ፡ ልሳን ፡ ዶርቃስ ፡ የሚሏት ፡

ወይጠል ፡ ብሂል ፡

ትርጓሜውም ፡ ወይጠል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አለ ፡ ፈጣን ፡ ማለት ፡ ነው ፡



ወብዙኀ ፡ ምግባረ ፡ ሠናየ ፡ ትገብር ፡ ምጽዋተ ፡

ምጽዋት ፡ አድርጋ ፡ ብዙ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ትሠራ ፡ ነበር ።

፴፯ ፤ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ ሞተት ፡ ደውያ ፡

ጴጥሮስ ፡ በልዳ ፡ እየዞረ ፡ ባስተማረበት ፡ ወራት ። አንድም ፡ ኤንያ ፡ በተፈወሰበት፡ ወራት ፡ ታማ ፡ ሞተች ፡

ወሐፀብዋ ፡ በድና ፡ ወአስከብዋ ፡ ውስተ ፡ ጽርሕ ።

ሥጋዋን ፡ አጥበው ፡ አጐናጽፈው ፡ ከሰገነት ፡ አስተኟት ።

፴፰ ፤ ወቅሩብ ፡ ሀገረ ፡ ልዳ ፡ ለኢዮጴ ፡

ልዳም ፡ ለኢዮጴ ፡ ቅርብ ፡ ነበር ፡

ወሰሚዖሙ፡ አርድእት፡ ከመ፡ ሀሎ፡ ጴጥሮስ፡ ህየ ፡

ምእመናንም ፡ ጴጥሮስ ፡ ከዚያ ፡ እንዳለ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡

ለአኩ ፡ ክልኤተ ፡ ዕደወ ፡ ያስተብቍዕዎ ፡ ኢይትሀከይ ፡ በጺሐቶሙ ፡

ነግ ፡ ሠልስት ፡ ሳይል ፡ ማልደው ፡ ያመጡት ፡ ዘንድ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ላኩ፡ ማልዳችሁ ፡ አምጡት ፡ ብለው ።

፴፱ ፤ ወተንሥአ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወሖረ ፡ ምስሌሆሙ ፡

ጴጥሮስም ፡ ነግ ፡ ሠልስት ፡ ሳይል ፡ ተነሥቶ ፡ አብሯቸው ፡ ሄደ ፡

ወበጺሖ ፡ አዕረግዎ ፡ ጽርሐ ።

ኢዮጴ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሰገነት ፡ አወጡት ፡

ወመጽኣ ፡ ኀቤሁ ፡ ኵሎን ፡ እቤራት ፡ ወቆማ ፡ ቅድሜሁ ፡ ይብክያሃ ፡

ባልቴቶችም ፡ ወደሱ ፡ መጥተው ፡ ከፊቱ፡ ቁመው ፡ አለቀሱ ፡

ወአርአያሁ ፡ አልባሰ ፡ ወከዳናተ ፡ ዘዐዕረዘቶን ፡ ዶርቃስ ፡ እንዘ ፡ ሀለወት ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ።

ዶርቃስ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳለች ፡ ፈትላ ፡ ያለበሰቻቸውን ፡ ቀሚስ ፡ መጐናጸፊያ ፡ አሳዩት ። አንድም ፡ ዘዐራዛቶን ፡ ዶርቃሰ ፡ የልብሳቸውን ፡ ጁህ ፡ ጀባነት ፡ አሳዩት ፡ እየው ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ታለብሰን ፡ ነበር ፡ እያሉ ።

፵ ፤ ወሰደደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኵሎ ፡

ጴጥሮስም ፡ ተመለሱ ፡ አለ ፡

ወሰገደ ፡ ወጸለየ ፡

እየሰገደ ፡ ጸለየ ፡ እየጸለየ ፡ ሰገደ ፡

ወተመይጠ ፡ መንገለ ፡ በድና ፡ ወይቤላ ፡ ጣቢታ ፡ ተንሥኢ ፡

ወደርስዋ ፡ ተመልሶ ፡ ጣቢታ ፡ ተነሽ ፡ አላት ፡

ወከሠተት ፡ አዕይንቲሃ ፡

ዐይኗን ፡ ግልጥ ፡ አድርጋ ፡

ወሶቤሃ ፡ ርእየቶ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ወነበረት ።

ባየችው ፡ ጊዜ ፡ ተነሥታ ፡ ተቀመጠች ፡ ማር፡ ፭ ፡ ፵፩ ። ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፲፬ ።

፵፩ ፤ ወመጠዋ ፡ እዴሁ ፡ ወአንሥኣ ፡

በጁ ፡ ይዞ ፡ አስነሣት ፡ እጅዋን ፡ ይዞ ፡ አስነሣት ፡

ወጸውዖሙ ፡ ለቅዱሳንሂ ፡ ወለእቤራትሂ ፡ ወአወፈያ፡ ኪያሃ ፡ ሕይወታ ።

ምእመናንን ፡ ባልቴቶችን ፡ ጠርቶ ፡ አውፈያ ፡ ኪያሆን ፡ እነሱን ፡ ለሷ ፡ ሰጣት ፡ እርጃቸው ፡ አጥቢያቸው ፡ ብሎ ። አውፈዮን ፡ ኪያሃ ፡ እሷን ፡ ለነሱ ፡ ሰጣቸው ፡ ትርዳችሁ ፡ ታጥባችሁ ፡ ብሎ ።

፵፪ ፤ ወሰምዑ ፡ ኵሉ ፡ ኢዮጴ ፡ ወአምኑ ፡ ብዙኃን ፡ በእግዚእነ ።

በኢዮጴ ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡ መነሣቷን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በጌታችን ፡ አመኑ ፡ ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፴ ። ፲ ፡ ፵፪ ።

www.ethiopianorthodox.org

፵፫ ፤ ወነበረ፡ጴጥሮስ፡ብዙኀ፡መዋዕለ፡በሀገረ፡ኢዮጴ።

ጴጥሮስም ፡ ኢዮጴ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ እያስተማረ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ኖረ ፡

ወኀደረ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ስምዖን ፡ ሰፋዪ ።

ሲያስተማር ፡ እየዋለ ፡ ከስምዖን ፡ሰፋዪ ፡ ቤት ፡ ያድር ፡ ነበር ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

፩ ፤ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ በሀገረ ፡ ቂሣርያ ፡ ዘስሙ ፡ ቆርኔሌዎስ ።

በቂሣርያ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡

ሐቢ ፡ ውእቱ ፡ ለሕዝበ ፡ ሰጲራ ፡

ሰጲራ ፡ ለሚባል ፡ ጭፍራ ፡ ሹም ፡ ነበር ፡

እንተ ፡ ይብልዋ ፡ ኢጣሊቄ ፡

ባንድ ፡ ልሳን ፡ ኢጣሊቄ ፡ የሚሉት ፡ ጨፈንታ ፡ ጋዲሳ ፡ ድንስር ፡ ቡርሳ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ማቴ ፡ ፳ ፡ ፳፭ ።

፪ ፤ ጻድቅ ፡ ወፈራሄ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብአ ፡ ቤቱ ፡

ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ደግ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ፈራሄ ፡ እግዚአብሔርነቱ ፡ የምግባር ፡ ነው ፡

ወይገብር ፡ ብዙኀ ፡ ምጽዋተ ፡ ለሕዝብ ፡

ለሕዝቡ ፡ ብዙ፡ ምጽዋት፡ ያደርግ፡ ነበር ፡

ወይጼሊ ፡ ወትረ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

ሁል ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጸልይ ፡ ነበር ፡ ዳን ፡ ፮ ፡ ፳፮ ።

፫ ፤ ወአስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሡተ ፡ ጊዜ ፡ ተሡዓት ፡ ሰዓት ፡ ዘመዓልት ፡

በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መላክ ፡ ታየው ፡ ተነጋገረው ፡ ዘሌሊት፡አለና፡ከዚያ፡ሲለይ፡ዘመዓልት፡ አለ ፡

ቦአ ፡ ኀቤሁ ፡

ወደሱ ፡ ገባ ፡ አለ ፡ የቦታ ። አንድም ፡ ባሕርዩን ፡ መሰለለት ፡

ወይቤሎ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡

ቆርኔሌዎስ ፡ አለው ።

፬ ፤ ወነጸረ ፡ ኀቤሁ ፡

ወደሱ ፡ ተመለከተ ፡

ወፈርሀ ፡

ባየው፡ ጊዜ፡ ፈራ፡ አለ፡ፍርሃት፡አደረበት፡

ወይቤ ፡ ምንተ ፡ ትብል ፡ እግዚእ ፡

አቤቱ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ አለው ፡

ወይቤሎ ፡ ጸሎትከ ፡ ወምጽዋትከ ፡ ዐርገ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተዘካረ ፡ ሠናየ ።

ጸሎትህ ፡ ምጽዋትህ ፡ በጎ ፡ መታሰቢያ ፡ ሆኖ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ደርሶልሃል ፡ አለው ።

፭ ፤ ወይእዜኒ ፡ ፈኑ ፡ ዕደወ ፡ ሀገረ ፡ ኢዮጴ ፡ ይጸውዕዎ ፡ ለከ ፡ ለስምዖን ፡ ጴጥሮስ ።

አሁንም ፡ ጴጥሮስ ፡ የተባለ ፡ ስምዖንን ፡ ይጠሩልህ ፡ ዘንድ ፡ ወደ፡ ኢዮጴ፡ ሰዎችን፡ ላክ ።

፮ ፤ ዘየኀድር ፡ ቤተ ፡ ስምዖን ፡ ሰፋዪ፡

ከስምዖን ፡ ሰፋዪ ፡ ቤት ፡ የሚያድር ፡

ዘመንገለ ፡ ባሕር ፡

በባሕር ፡ ዳር ፡ ያለ ፡ አለ ፡ ጀን ፡ አርሳሚ ፡ ግምጃ ፡ ጠቃሚ ፡ ነውና ፡ ለመንከር ፡ እንዲመቸው ፡

ወውእቱ ፡ ይነግረከ ፡ በዘተሐዩ ፡ አንተ ፡ ወኵሉ ፡ ቤትከ ።

አንተም ፡ ቤተ ፡ ሰቦችህም ፡ በምትድኑ ፡ ገንዘብ ፡ የምትድኑበትን ፡ እሱ ፡ ይነግርሃል ፡ አለው ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፵፫ ። ም ፡ ፪፡፴፯ ።

፯ ፤ ወኀሊፎ ፡ መልአክ ፡ ዘተናገሮ ፡

የነገረውም ፡ መልአክ ፡ አልፎ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡

ጸውዐ ፡ ክልኤተ ፡ እምወዓልያኒሁ ፡

ከባለሟሎቹ ፡ ሁለቱን ፡

ወአሐደ ፡ ኄረ ፡ እምፀማዱ ፡

ከጃን ፡ ገብሩ ፡ አንዱን ፡ ጠርቶ ። አንድም ፡ በአፍአ ፡ ካሉ ፡ ብላቴኖቹ ፡ ሁለቱን ፡ ከባለሟሎቹ ፡ አንዱን ፡ ጠርቶ ።

፰ ፤ ወነገሮሙ ፡ ኵሎ ፡ ወለአኮሙ ፡ ሀገረ ፡ ኢዮጴ ፡

የነገረውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ነግሮ ፡ ወደ ፡ ኢዮጴ ፡ ላካቸው ።

## ክፍል ፡ ፲፰ ።

፱ ፤ ወበሳኒታ ፡ እንዘ ፡ የሐውሩ ፡ በጽሑ ፡ ኢዮጴ ፡ ኀበ ፡ አንቀጸ ፡ ሀገር ፡

በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ሲሄዱ ፡ ኢዮጴ ፡ ከከተማው ፡ በር ፡ ደረሱ ፡

ወጴጥሮስኒ ፡ ዐርገ ፡ ናሕሰ ፡ ጸሊ ፡ ጊዜ ፡ ቀትር ።

ጴጥሮስም ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ከሰገነት ፡ ወጥቶ ፡ ይጸልይ ፡ ነበር ።

፲ ፤ እስመ ፡ ርኁበ ፡

ተርቦ ፡ ነበርና ፡

ወፈቀደ ፡ ይምሳሕ ፡

ሊመገብ ፡ ወዶ ፡ ሳለ ፡

ወእንዘ ፡ ያስተዳልዉ ፡ እሙንቱ ፡ መጽአ ፡ ድንጋጼ ፡ ላዕሌሁ ፡

ምግቡን ፡ እስቲአዘጋጁለት ፡ ድረስ ፡ ተደሞ ፡ መጣበት ።

፲፩ ፤ ወርእየ ፡ ሰማየ ፡ ርኁወ ፡

ሰማይ፡ የተከፈተ፡ ሆኖ፡ አየ፡ ሐተታ፡ አሁን፡ በሰማይ፡ መከፈት፡ መዘጋት፡ ኑሮበት ፡ አይደለም ፡ የተዘጋ ፡ ደጅ፡ በተከፈተ ፡ ጊዜ ፡ ያልታየ ፡ ዕቃ ፡ እንዲታይ ፡ ያልተገለጠ ፡ ምስጢር ፡ ተገለጠ ፡ ሲል ፡ ነው ፡

ወይወርድ ፡ ከመ ፡ ዘሞጣሕት ፡ ዓቢይ ፡ ዲበ ፡ ምድር፡ እኁዝ ፡ በአርባዕቱ ፡ ጽነፊሁ ።

ባራት ፡ ወገን ፡ የተያዘ ፡ ሰፌ ፡ መጋረጃ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ሲወርድ ፡ አየ ፡ ም ፡ ፲፩፡፯። ሉቃ ፡ ፲፫ ፡ ፳፱ ።

፲፪ ፤ ወቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ኵሉ ፡ እንስሳ ፡

በውስጡም ፡ ሥዕለ ፡ እንስሳ ፡

ወአራዊተ ፡ ገዳም ፡

ሥዕለ ፡ አራዊት ፡

ወአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡

ሥዕለ ፡ አዕዋፍ ፡ ተሥሎበት ፡ አየ ፡

፲፫ ፤ ወነበቦ ፡ ቃል ፡

ቃል ፡ ነገረው ፡

ወይቤሎ ፡ ተንሥእ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኀርድ ፡ ወብላዕ ።

እሪያውን ፡ እያሳየ ፡ ጴጥሮስ ፡ ተነሣ ፡ እሪያውን ፡ አርደህ ፡ ብላ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

፲፬ ፤ ወይቤሎ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐሰ ፡ ሊተ ፡ እግዚእ ።

ጴጥሮስም ፡ አቤቱ ፡ አይገባም ፡ አለው ፡

ግሙራ ፡ ኢቦአ ፡ ርኩስ ፡ ውስተ ፡ አፉየ ፡

ርኩስ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ ካፌ ፡ ገብቶ፡ አያውቅም ፡

ወኢበላዕኩ ፡ ዘኢኮነ ፡ ንጹሐ ።

ንጹሕ ፡ ያልሆነ ፡ ነገር ፡ በልቼ ፡ አላውቅም ፡ አለው ፡ ሕዝ ፡ ፬ ፡ ፲፬ ። ዘሌዋ ፡ ፲፩ ፡ ፯ ፡ ፲፫ ፡ ፳፫ ።

፲፭ ፤ ወነበቦ ፡ ዳግመ ፡ ወይቤሎ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ አንጽሐ ፡ አንተ ፡ ኢታስተራኵስ ።

ዳግመኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጹሕ ፡ አድ



www.ethiopianorthodox.org

ርጎ ፡ የፈጠረውን ፡ ፍጥረት ፡ አንተ ፡ አት
ጸየፍ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፡ ማቴ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ።

፲፮ ፤ ወከመዝ ፡ ይቤሎ ፡ ሥልሰ ፡

ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ ነግሮት ፡

ወዕሶ ፡ ተመይጠ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡

ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲዐርግ ፡ አየ ፡ ሰፊ ፡ መጋረጃ ፡ የወንጌል ፡ ባራት ፡ ወገን፡ መያዟ ፡ ወንጌል ፡ ባራቱ ፡ መዓዝን፡ ለመ ነገሯ ፡ አራት ፡ ክፍል ፡ ሁና ፡ ለመጻፍዋ ፡ ምሳሌ ። ሥዕለ ፡ አዕዋፍ ፡ የነቢያት ፡ የካ ህናት ፡ ሥዕለ ፡ አራዊት ፡ የምእመናን ፡ አሕዛብ ፡ ሥዕለ ፡ እንስሳ ፡ የምእመናን ፡ እስራኤል ፡ እሪያውን ፡ እያሳየ ፡ ኀርድ ፡ ወብላዕ ፡ ማለቱ ፡ አሕዛብን ፡ አስተምር ፡ ሲለው ፡ ነው ፡ ግሙራ ፡ ኢቦአ ፡ ርኩስ ፡ ውስተ ፡ አፉየ ፡ ወኢበላዕኩ ፡ ዘኢኮነ ፡ ንጹሐ ፡ ማለቱ ፡ እስራኤል ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ አይገናኙም ፡ ነበረና ፡ ዘእግዚአብ ሔር ፡ አንጽሐ ፡ አንተ ፡ ኢታስተራኩስ፡ ማለቱ ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ሆነዋልና ። ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ መናገሩ ፡ የሦስ ትነት ፡ ቃሉ ፡ አለመለወጡ ፡ ያንድነት ፡ ሦስት፡ ጊዜ፡ መላልሶ፡ ነግሮት፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲዐርግ ፡ ማየቱ ፡ እሊህ ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ በወንጌል ፡ አምነው ፡ ወደ፡ ገነት ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ለመ ግባታቸው ፡ ምሳሌ ።

፲፯ ፤ ወእንዘ ፡ ይጼሊ ፡ ጴጥሮስ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ዘአስተርአዮ ፡ በጽሑ ፡ ዕደው ፡ እለ ፡ ተፈነዉ ፡ እም ኀበ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ እንዘ ፡ የኀሥሡ ፡ ቤቶ ፡ ለስም ዖን ፡

ጴጥሮስም ፡ የታየው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ ሲያወጣ፡ ሲያወርድ ፡ ከቆርኔሌዎስ ፡ ዘንድ ፡ ተልከው ፡ የሄዱ ፡ ሰዎች ፡ የስም ዖንን ፡ ቤት ፡ እየጠየቁ ፡ ደረሱ ።

፲፰ ፤ ወቆሙ ፡ ኀበ ፡ ዴዴ ፡ ወጸርሑ ፡ ወሐተቱ ፡ እምህየ ፡ ኀበ ፡ የኀድር ፡ ጴጥሮስ ።

ከበር ፡ ቁመው ፡ ጴጥሮስ ፡ የሚያድርበ ትን ፡ ቤት ፡ ጠየቁ ።

፲፱ ፤ ወእንዘ፡ይሔሊ፡ጴጥሮስ፡በእንተ፡ዘአስተርአዮ፡

የታየው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሲያ ወጣ ፡ ሲያወርድ ፡

ይቤሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ናሁ ፡ ሠለስቱ ፡ ዕደው ፡ የኀሥሡከ ።

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ይሹ ሃል ፡ አለው ።

፳ ፤ ተንሥእ ፡ ወረድ ፡ ወሑር ፡ ምስሌሆሙ ፡ እንዘ ፡ ኢትናፍቅ ፡ ወኢምንተኒ ፡

ተነሥተህ ፡ ወርደህ ፡ በምንም ፡ በምን ፡ ሳትጠራጠር ፡ አብረሃቸው ፡ ሂድ ፡ አለው፡

እስመ ፡ አነ ፡ ፈነውክዎሙ ፡

እኔ ፡ ሰድጃቸዋለሁና ።

፳፩ ፤ ወወረደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኀበ ፡ እሙንቱ ፡ ዕደው ፡

ጴጥሮስም ፡ ከሰገነት ፡ እነሱ ፡ ወዳሉበት ፡ ወርዶ ፡

ወይቤሎሙ ፡ ነየ ፡ አነ ፡ ዘተኀሥሡኒ ፡

የምትሹኝ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡

በእንተ ፡ ምንት ፡ መጻእክሙ ፡

ስለምን ፡ መጥታችኋል ፡ አላቸው ።

፳፪ ፤ ወይቤልዎ ፡ እሙንቱ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ሐቢ ሹሙ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ልኮናል ፡

ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡

ደግ ፡ ሰው ፡

ወፈራሄ ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡

ወያአምርዎ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝበ ፡ አይሁድ ፡

የአይሁድ ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ደግነቱን ፡ ያውቁለታል ፡



አስተርአዮ ፡ መልአክ ፡ ቅዱስ ፡ ወይቤሎ ፡

ክቡር ፡ መልአክ ፡ ታየው ፡ ተነጋገረው ፡

ከመ ፡ ይጸውዕከ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡

ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይጠራህ ፡ ዘንድ ፡

ወይስማዕከ ፡ ዘትነግሮ ፡

የምትነግረውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይሰማህ ፡ ዘንድ ፡ ጥራው ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

፳፫ ፤ ወውእቱ ፡ ጸውዖሙ ፡ ወአኀደሮሙ ፡

እሱም ፡ ኑ ፡ ብሎ ፡ ወስዶ ፡ ካለበት ፡ ቤት፡ አሳደራቸው ፡

ወበሳኒታ ፡ ተንሥአ ፡ ወሖረ ፡ ምስሌሆሙ ፡

በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ አብሯቸው ፡ ሄደ ።

ወቦ ፡ እምቢጹ ፡ እምሀገረ ፡ ኢዮጴ ፡ እለ ፡ ሖሩ ፡ ምስሌሁ ፡

ኢዮጴ ፡ በሚባል ፡ ሀገር ፡ ካሉ ፡ ምእመ ናን ፡ ጴጥሮስን ፡ ተከትለውት ፡ የሄዱ ፡ ነበሩ ፡ ስድስት ፡ ብሎ ፡ ኋላ ፡ ያመጣቸ ዋል ፡

፳፬ ፤ ወበሳኒታ ፡ ቦአ ፡ ሀገረ ፡ ቂሣርያ ፡

ባራተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ገቡ ፡

ወሀሎ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ይጸንሖሙ ፡ ወጸውዐ ፡ አዝማ ዲሁ ፡ ወማኅፈሮ ።

ቆርኔሌዎስም ፡ ዘመዶቹን ፡ አምቾቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ይጠብቃቸው ፡ ነበር ።

፳፭ ፤ ወበዊአ ፡ ጴጥሮስ ፡ ተቀበሎ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡

ጴጥሮስም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ከቤት ፡ ወጥቶ ፡ ተቀበለው ፡

ወሰገደ ፡ ሎቱ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ።

ከእግሩ ፡ በታች ፡ ወድቆ ፡ ሰገደለት ፡ የአ ክብሮ ፡ ስግደት ፡ ነው ፡ ሐተታ ፡ ቄስ ጠንጢኖስ ፡ ለሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ዮሐንስ፡ ለመላኩ ፡ እንደ ፡ ሰገዱ ፡

፳፮ ፤ ወአንሥኦ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወይቤሎ ፡ ተንሥእ ፡ አነሂ ፡ ከማከ ፡ ሰብእ ፡

እንዳንት ፡ ያለሁ ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ አይ ደለሁምን ፡ ለኔ ፡ ለምን ፡ ትሰግዳለህ ፡ ብሎ ፡ አስነሣው ፡ ም፲፬ ፡ ፲፭ ። ራእ ፡ ፲፱ ፡ ፲ ።

፳፯ ፤ ወቦኡ ፡ እንዘ ፡ ይትናገሩ ፡

እየተጠያየቁ ፡ ገቡ ፡

ወረከበ ፡ ብዙኃነ ፡ ሰብአ ፡ እለ ፡ መጽኡ ፡

በገባም ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስ በው ፡ አገኘ ።

፳፰ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ጴጥሮስ፡ ተአምሩ ፡ ለሊክሙ ፡ ከመ ፡ ኢይከውኖ ፡ ለብእሲ ፡ አይሁዳዊ ፡ ከመ ፡ ይሖር ፡ ወይባእ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ሕዝብ ።

ለአይሁዳዊ ፡ ሰው ፡ ትውልዱ ፡ ነገዱ ፡ ካልእ ፡ ወደሚሆን ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ መግ ባት ፡ እንዳይገባው ፡ አለ ፡ መገናኘት ፡ እንዳይገባው ፡ ታውቃላችሁ ፡

ወሊተሰ ፡ አርአየኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኢያስተ ራኵሶ ፡ ለሰብእ ፡ ወኢለመኑሂ ።

ለኔ ፡ ግን ፡ ሰውን ፡ ማነንም ፡ ማነን ፡ እ ንዳልጸየፍ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነግሮኛል ።

፳፱ ፤ ወይእዜኒ ፡ ኢናፈቅየ ፡ መጻእኩ ፡ ኀቢክሙ ፡ በዘለአክሙ ፡

አሁንም ፡ በላካችሁብኝ ፡ ገንዘብ ፡ ሳልጠ ራጠር ፡ ወደናንት ፡ መጥቻለሁ ፡

እስኩ ፡ አይድዑኒ ፡ ምንትኑ ፡ በዘጸዋዕክሙኒ ።

እኔን ፡ የጠራችሁበት ፡ ነገሩ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ እስቲ ፡ ንገሩኝ ፡ አላቸው ።

፴ ፤ ክፍል ፡ ፲፱ ። ወይቤሎ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ረቡዕ ፡ ዮም ።

ቆርኔሌዎስም፡ ዛሬ፡ አራተኛ፡ ቀን ፡ ነው ፡

እንዘ ፡ እጼሊ ፡ በጊዜ ፡ ተሱዓት ፡ ሰዓት ፡ በቤትየ ፡

በቀትር ፡ ጊዜ ፡ በቤቴ ፡ ስጸልይ ፡

www.ethiopianorthodox.org

አስተርአየኒ ፡ ብእሲ ፡ ይቀውም ፡ ቅድሜየ ፡ ወይለ
ብስ ፡ ብርሃነ ፡

ብሩህ ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡ ከፊቴ ፡ ቁሞ ፡ ታየኝ ፡ አለው ፤ መልአክ ፡ ነው ።

፴፩ ፤ ወይቤለኒ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ተሰምዐ ፡ ጸሎትከ ፡ ወምጽዋትከ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡

ቆርኔሌዎስ ፡ ጸሎትህ ፡ ምጽዋትህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ደርሶልሃል ፡

ተዘከሩከ ።

ፍትሑ ፡ ርቱዕ ፡ ሥላሴ ፡ በምሕረት ፡ አሰቡህ ፡ አዘከሩከ ፡ መላእክት ፡ አሳሰቡህ ። አንድም ፡ ጸሎትህ ፡ ምጽዋትህ ፡ አሳሰቡኽ ።

፴፪ ፤ ወይእዜኒ ፡ ለአክ ፡ ሀገረ ፡ ኢዮጴ ፡ ይጸውዕዎ ፡ ለከ ፡ ለስምዖን ፡ ዘተሰምየ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘየኀድር ቤተ ፡ ስምዖን ፡ ሰፋዪ ፡

አሁንም ፡ ከስምዖን ፡ ሰፋዪ ፡ ቤት ፡ ያድር ፡ የነበረ ፡ ጴጥሮስ ፡ የተባለ ፡ ስምዖንን ፡ ይጠሩልህ ፡ ዘንድ ፡ ኢዮጴ ፡ ወደሚባል ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ላክ ፡

ዘመንገለ ፡ ባሕር ፡

በባሕር ፡ አጠገብ ፡ ያለ ፡

ወውእቱ ፡ ይነግረከ ፡ በዘተሐዩ ፡ አንተ ፡ ወኵሉ ፡ ቤትከ ።

አንተም ፡ ቤተ ፡ ሰቦችህም ፡ በምትድኑ ፡ ገንዘብ ፡ የምትድኑበትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እሱ ፡ ይነግርሃል ፡ አለኝ ።

፴፫ ፤ ወሶቤሃ ፡ በእንቲአሁ ፡ ለአኩ ፡ ኀቤከ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኜ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ወዳንተ ፡ ላክሁ ፡

ወሠናየ ፡ ገበርከ ፡ ዘመጻእከ ፡

መምጣትህ ፡ በጎ ፡ አደረግህ ፡

ወይእዜኒ ፡ ሀሎነ ፡ ኵልነ ፡ ቅድሜከ ።

አሁንም ፡ ሁላችንም ፡ በፊትህ ፡ አለንና ፡ አለ ፡ ያዘዝኽንን ፡ ነገር ፡ እንሰማለንና ፡

ንግረነ ፡ ኵሎ ፡ ዘአዘዘከ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ያዘዘህን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ንገረን ፡ አለው ።

፴፬ ፤ ወከሠተ ፡ አፉሁ ፡ ጴጥሮስ ፡

ጴጥሮስም ፡ ነገር ፡ ጀመረ ፡ (ጥቅ) ፡ ወከሠተ ፡ አፉሁ ፡ ኢዮብ ፡ ወከሠተ ፡ አፉሁ ፡ ፊልጶስ ፡ እንዲል ፡

ወይቤ ፡ አማነ ፡ ርኢኩ ፡ ከመ ፡ ኢያደሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለገጽ ፡ በኵሉ ፡ አሕዛብ ።

እግዚአብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ እንዳያደላ ፡ በውነት ፡ አወቅሁ ፡ ተረዳሁ ፡ ፩ ፡ ሳሙኤ ፡ ፲፮ ፡ ፯ ። ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።

፴፭ ፤ አላ ፡ ዘፈርሆ ፡ ወገብረ ፡ ጽድቀ ፡ ኅሩይ ፡ ውእቱ ፡ በኀቤሁ ።

የሚፈራው ፡ የሚያመልከው ፡ ትእዛዙን ፡ የሚፈጽም ፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡ የተመረጠ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፲፮ ።

፴፮ ፤ ወፈነወ ፡ ቃሎ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡

ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ በሙሴ ፡ ቃል ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዐሥሩ ፡ ቃላትን ፡ ሠራ ፡

ወዜነዎሙ ፡ ሰላመ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘውእቱ ፡ እግዚእ ፡ ለኵሉ ፡

ለሁሉ ፡ ገዥ ፡ በሚሆን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ሕልው ፡ ሆኖ ፡ ሕዝብና ፡ አሕዛብን ፡ አንድ ፡ የምታደርግ ፡ ወንጌልን ፡ አስተምራቸው ። አንድም ፡ አካላዊ ፡ ቃልን ፡ ሰደደ ፡ ለሁሉ ፡ ገዥ ፡ በሚሆን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሕልው ፡ ሁኖ ፡ ልጅነትንም ፡ ሰጣቸው ፡ ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፰ ።

፴፯ ፤ ተአምሩ ፡ ለሊክሙ ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡ ዘኮነ ፡ በይሁዳ ፡ እኂዞ ፡ እምገሊላ ።

ከገሊላ ፡ ጀምሮ ፡ በይሁዳ ፡ የተደረገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እናንተ ፡ ቅሉ ፡ ታውቃላችሁ ፡ ማቴ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ።



፴፰ ፤ እምድኅረ ፡ ጥምቀት ፡ ዘሰበከ ፡ ዮሐንስ ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘእምናዝሬት ፡

ዮሐንስ ፡ ስለ ፡ ናዝሬቱ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ካስተማረው ፡ ጥምቀት ፡ በኋላ ፡

ዘቀብኦ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ ወኃይለ ፡

እግዚአብሔርነቱ ፡ ኃይሉ ፡ ሕይወቱ ፡ በሚሆን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የመረጠው ፡ (የሾመው) ፡

ውእቱ ፡ መጽአ ፡

ከገሊላ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ በመምህርነት ፡ መጥቶ ፡

ወረድአሙ ፡ ለእለ ፡ ይትዔገሎሙ ፡ ሰይጣን ፡

ሰይጣን ፡ ድል ፡ አድርጓቸው ፡ የነበሩትን ፡ እንዳዳነ ፡ ታውቃላችሁ ፡ (ጥቅ) ፡ እስመ ፡ በዘአመከርዎ ፡ ወአሕመምዎ ፡ ክህለ ፡ ረድኤቶሙ ፡ ለሕሙማን ፡ ወረድነ ፡ በከመ ፡ ምክረ ፡ ፈቃዱ ፡ እንዲል ፡

እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌሁ ፡

እግዚአብሔር ፡ በሕልውናው ፡ ነውና ፡ ኢሳ ፡ ፷፩ ፡ ፩ ።

፴፱ ፤ ወንሕነ ፡ ኵልነ ፡ ሰማዕቱ ፡ በዘገብረ ፡ በይሁዳ ፡ ወበኢየሩሳሌም ።

እኛ ፡ ግን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በይሁዳ ፡ ባደረገው ፡ ሁሉ ፡ ምስክሮቹ ፡ ነን ፡ ባስተማረው ፡ ትምህርት ፡ በሠራው ፡ ትሩፋት ፡ ባደረገው ፡ ተአምራት ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡

ወቀተልዎ ፡ ሰቂሎሙ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ፡

በዕንጨት ፡ ሰቅለው ፡ እንደ ፡ ገደሉት ።

፵ ፤ ወእግዚአብሔር ፡ አንሥኦ ፡ እሙታን ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፡

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ እንዳስነሣው ፡ እኛ ፡ ምስክሮቹ ፡ ነን ፡

ወወሀቦ ፡ ከመ ፡ ያስተርኢ ፡ ገሃደ ፡

ፈጽሞ ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ መገለጥን ፡ ሰጠው ።

፵፩ ፤ ወአኮሰ ፡ ለኵሉ ፡ ሕዝብ ፡

መገለጡ ፡ ግን ፡ ለሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ አይደለም ፡

አላ ፡ ዳእሙ ፡ ለእለ ፡ ይከውኑ ፡ ስምዐ ፡ እለ ፡ ኀረዮሙ ፡ እምትካት ፡

ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ለመረጣቸው ፡ ትንሣኤውን ፡ ለሚመሰክሩ ፡ ለመቶ ፡ ኻያው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡

ወንሕነ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ በላዕነ ፡ ወሰተይነ ፡ ምስሌሁ ፡ እምድኅረ ፡ ተንሥአ ፡ እሙታን ፡ አርብዓ ፡ ዕለተ ።

ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ አብረን ፡ የበላን ፡ የጠጣን ፡ እኛ ፡ ነን ፡ ሐተታ ፡ ምነው ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ አይደለም ፡ ቢሉ ፡ ከዚያው ፡ ገብቶ ፡ ከተቆጠረ ፡ ብሎ ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፳፪ ፡ ፲፫ ፡ ፳፯ ።

፵፪ ፤ ወአዘዘነ ፡ ከመ ፡ ንስብክ ፡ ወንንግር ፡ ለሕዝብ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ዘተሠይመ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ መኰንነ ፡ ሕያዋን ፡ ወሙታን ።

በሕያዋን ፡ በሙታን ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ሕያዋንን ፡ ሙታንን ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ፈራጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሕዝቡ ፡ እናስተምር ፡ ዘንድ ፡ ሑሩ ፡ ወመሐሩ ፡ ብሎ ፡ ያዘዘን ፡ እኛ ፡ ነን ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፴፩ ።

፵፫ ፤ ወኵሎሙ ፡ ነቢያት ፡ ሰማዕቱ ፡

ነቢያትም ፡ ምስክሮቹ ፡ ናቸው ፡

ከመ ፡ በስመ ፡ ዚአሁ ፡ ይትኀደግ ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ፡ የአምኑ ፡ ቦቱ ።

ስሙ ፡ ሕይወት ፡ መድኀኒት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሚያምኑበት ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአታቸው ፡ እንዲሠረይላቸው ፡ ምስክሮቹ ፡ ናቸው ፡ (ጥቅ) ፡ ወይቄርዎን ፡ ለኃጣውኢነ ፡ ወያሠጥሞን ፡ ውስተ ፡ ቀላየ ፡ ባሕር ። ወለብ

www.ethiopianorthodox.org

ዞኃን ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ውእቱ ፡ ይደመስስ፡ እንዲል ፡ ኢሳ ፡ ፶፫ ፡ ፯ ። ኤር ፡ ፴፩፡ ፴፬ ። ሕዝ ፡ ፴፮ ፡ ፲፮ ። ዳን ፡ ፱ ፡ ፳፬ ። ሆሴ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ። ሚክ ፡ ፯ ፡ ፲፰ ።

፵፬ ፤ ክፍል ፡ ፰ ። ወእንዘ ፡ ይነግሮሙ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡

ጴጥሮስም ፡ ይህን ፡ ሲያስተምራቸው ፡

ወረደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዲበ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሰምዑ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡

ይህን ፡ በሰሙ ፡ ሰዎች ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ፡ አደረባቸው ።

፵፭ ፤ ወደንገፁ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ እምውስተ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ መጽኡ ፡ ምስለ ፡ ጴጥሮስ ፡

ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ የሚሆኑ ፡ ጴጥሮስን ፡ ተከትለው ፡ የመጡ ፡ ሰዎች ፡ የአንክሮ ፡ ድንጋጤ ፡ ደነገጡ ፡

እስመ ፡ ዲበ ፡ አሕዛብኒ ፡ ወረደ ፡ ጸጋሁ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸጋው ፡ ለአሕዛብም ፡ ተሰጥቷልና ፡ ዋዌው ፡ ለሐዋርያት ፡ ነው።

፵፮ ፤ ወሰምዕዎሙ ፡ ይነብቡ ፡ በነገረ ፡ በሐውርት፡

በየሀገሩ ፡ ቋንቋ ፡ ሲናገሩ ፡ ሰምተዋቸዋልና ።

ወይሴብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርንም ፡ ሲያመሰግኑ ፡ ሰምተዋቸዋልና ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፬ ። ማር ፡ ፲፮ ፡ ፲፯ ።

፵፯ ፤ ወይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡ መኑ ፡ እንከ ፡ ይክል ፡ ይከልአሙ ፡ ማየ ፡ ከመ ፡ ኢይጠመቁ ፡ እምድኅረ ፡ ነሥኡ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ ከማነ ።

ጴጥሮስም ፡ እንደኛ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ገንዘብ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ በውኃ ፡ እንዳይ ጠመቁ ፡ የሚከለክል ፡ ማነው ፡ ብሎ ።

፵፰ ፤ ወአዘዞሙ ፡ ይጠመቁ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አምናችሁ ፡ ተጠመቁ ፡ አላቸው ፡

ወእምዝ ፡ አስተብቍዕዎ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ኀቤሆሙ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ሰንብት ፡ ብለው ፡ ማለዱት ፡ ዮሐ ፡ ፬፡ ፵።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡

፩ ፤ ወሰምዑ ፡ ሐዋርያት ፡ ወቢጸሙሂ ፡ እለ ፡ ብሔረ ፡ ይሁዳ ፡ ከመ ፡ ተወክፉ ፡ አሕዛብ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡

ሐዋርያት ፡ በብሔረ ፡ ይሁዳ ፡ ያሉ ፡ ምእመናንም ፡ አሕዛብ ፡ ወንጌልን ፡ አክብረው ፡ እንደ ፡ ተቀበሉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

፪ ፤ ክፍል ፡ ፳፩ ። ወአመ ፡ ዐርገ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተዋቀሥዎ ፡ ቢጹ ፡ እለ ፡ እምአይሁድ ።

ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ የሚሆኑ ፡ ምእመናን ፡ ተከራከሩት ፡ ም ፡ ፲ ፡ ፵፰ ።

፫ ፤ ወይቤልዎ ፡ ቦእከ ፡ ኀበ ፡ ዕደው ፡ እለ ፡ ኢኮኑ ፡ ግዙራነ ፡ ወበላዕከ ፡ ምስሌሆሙ ።

ግዙራን ፡ ወዳልሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሂደህ ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ በልተሃል ፡ ብለው ፡ ተከራከሩት ፡ ገላት ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።

፬ ፤ ወአኀዘ ፡ ጴጥሮስ ፡ ይንግሮሙ ፡ እምጥንቱ ።

ጴጥሮስም ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እየተረከ ፡ ይነግራቸው ፡ ጀመረ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ፲ ።

፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ እንዘ ፡ ሀለውኩ ፡ ሀገረ ፡ ኢዮጴ ፡ እንዘ ፡ እጼሊ ፡ ደንገፅኩ ።

በኢዮጴ ፡ ሳለሁ ፡ ስጸልይ ፡ ተደሞ ፡ መጣብኝ ፡

www.ethiopianorthodox.org



ወርኢኩ ፡ ከመ ፡ ዘሞጣሕት ፡ ዐቢይ ፡ ዘይወርድ ፡ እምሰማይ ፡ ወእኁዝ ፡ በአርባዕቱ ፡ ጽነፊሁ ፡ ወመጽአ ፡ መንገሌየ ።

ከወደ ፡ ሰማይ ፡ ባራቱ ፡ መዓዝን፡ የተያዘ፡ ሰፊ ፡ መጋረጃ ፡ ወደኔ ፡ ሲመጣ ፡ አየሁ ።

፮ ፤ ወነጸርኩ ፡ ወርኢኩ ፡ በውስቴቱ ፡ እንስሳ ፡ ወአርዌ ፡ ገዳም ፡ ወአዕዋፈ ፡ ሰማይ ።

በውስጡ ፡ ሥዕለ ፡ እንስሳ ፡ ሥዕለ ፡ አራዊት ፡ ሥዕለ ፡ አዕዋፍ ፡ ተሥለውበት ፡ አየሁ ።

፯ ፤ ወሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ ዘይቤለኒ ፡ ተንሥእ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኅርድ ፡ ወብላዕ ።

ጴጥሮስ ፡ ተነሥተህ ፡ እሪያውን ፡ አርደህ፡ ብላ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰማሁ ።

፰ ፤ ወእቤ ፡ ሐሰ ፡ እግዚኦ ፡ ግሙራ ፡ ኢቦአ ፡ ርኩስ ፡ ውስተ ፡ አፉየ ፡ ዘኢኮነ ፡ ንጹሐ ።

አቤቱ ፡ አይገባም ፡ ከቶ ፡ ንጹሕ ፡ ያል ሆነ ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ በአፌ ፡ ገብቶ ፡ አያውቅም ፡ አልሁ ።

፱ ፤ ወይቤለኒ ፡ ዳግመ ፡ ቃል ፡ እምሰማይ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ አንጽሐ ፡ አንተ ፡ ኢታስተራኵስ ።

ዳግመኛ ፡ ከወደ ፡ ሰማይ ፡ ቃል ፡ ተሰምቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጹሕ ፡ አድርጎ ፡ የፈጠረውን ፡ አንት ፡ አትጸየፍ ፡ አለኝ ።

፲ ፤ ወከመዝ ፡ ይቤለኒ ፡ ሠልሰ ፡ ወተሠውጠ ፡ ካዕበ ፡ ኵሉ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ።

እንዲህ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መላልሶ ፡ ከነገረኝ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ሰማይ፡ ሲዐርግ ፡ አየሁ ፡ አላቸው ።

፲፩ ፤ ወበይእቲ ፡ ሰዓት ፡ በጽሑ ፡ ዕደው ፡ ሠለስቱ ፡ እለ ፡ ተፈነዉ ፡ ኀቤየ ፡ እምቂሣርያ ።

በዚያች ፡ ሰዓት ፡ ከቂሣርያ ፡ ወደኔ፡ ተልከው ፡ የመጡ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ደረሱ ፡

ወቆሙ ፡ ኀበ ፡ ኆኅተ ፡ ዐጸድ ፡ ኀበ ፡ ሀለውኩ ።

ከበር፡ቆመው፡ ያለሁበትን፡ ቤት፡ ጠየቁ ።

፲፪ ፤ ወይቤለኒ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሑር ፡ ምስሌሆሙ ፡ እንዘ ፡ ኢትናፍቅ ፡

መንፈስ፡ ቅዱስም፡ በምንም፡ በምን ፡ ሳት ጠራጠር ፡ አብረሃቸው ፡ ሂድ ፡ አለኝ ፡

ወመጽኡ ፡ ምስሌየ ፡ እሉሂ ፡ ስድስቱ ፡ አኀዊነ ።

ከኢዮጴም ፡ እሊህ ፡ ስድስቱ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ተከትለውኝ ፡ መጡ ፡

ወቦእነ ፡ ቤቶ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ።

ከቆርኔሌዎስ ፡ ቤት ፡ በገባን ፡ ጊዜ ።

፲፫ ፤ ወነገረነ ፡ ዘከመ ፡ ርእየ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቤቱ ፡ እንዘ ፡ ይቀውም ፡

ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ በቤቱ ፡ ቁሞ ፡ እንዳየ ፡

ወዘይቤሎ ፡ ፈኑ ፡ ሀገረ ፡ ኢዮጴ ፡ ይጸውዕዎ ፡ ለከ ፡ ለስምዖን ፡ ዘተሰምየ ፡ ጴጥሮስ ።

ጴጥሮስ ፡ የተባለ ፡ ስምዖንን ፡ ይጠሩልህ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢዮጴ ፡ ሰዎች ፡ ላክ ።

፲፬ ፤ ወውእቱ ፡ ይነግረከ ፡ ነገረ ፡ በዘተሐዩ ፡ አንተ ወኵሉ ፡ ቤትከ ።

አንተም ፡ ቤተ ፡ ሰቦችህም ፡ በምትድኑ ፡ ገንዘብ ፡ የምትድኑበትን ፡ ነገር ፡ እሱ ፡ ይነግርሃል ፡ ብሎ ፡ ነገረኝ ፡ አላቸው ፡ ም ፡ ፲ ፡ ፳ ።

፲፭ ፤ ወሶበ ፡ አኀዝኩ ፡ እንግሮሙ ፡ ወረደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዲቤሆሙ ፡ ዘከመ ፡ ወረደ ፡ ቀዲሙ ፡ ዲቤነ ።

ልነግራቸው ፡ በጀመርሁ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቀድሞ ፡ በኛ ፡ እንዳደረ ፡ አደረባቸው ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፬ ።

፲፮ ፤ ወተዘከርኩ ፡ ቃሎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ዘይቤ ፡ ዮሐንስ ፡ አጥመቀ ፡ በማይ ፡ ወአንትሙሰ ፡ ትጠመቁ ፡ (ታጠምቁ) ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

ዮሐንስ ፡ በውኃ ፡ ብቻ ፡ አጠመቀ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ታጠምቃላችሁ ፡ ብሎ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክር

ስቶስ ፡ የተናገረውን ፡ አሰብሁ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፭ ። ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

፲፯ ፤ ወሶበ ፡ እንከ ፡ ዕሩየ ፡ ወሀቦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋሁ ፡ ከማነ ፡ እስመ ፡ አምኑ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምነዋልና ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደኛ ፡ አስተካክሎ ፡ ልጅነትን ፡ ከሰጣቸው ፡ በኋላ ፡

መኑ ፡ እንከ ፡ አነ ፡ ዘእክል ፡ ከሊኦቶ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ እንዳያድርባቸው ፡ የምከለክል ፡ እኔ ፡ ምንድን ፡ ነኝ ። አንድም ፡ እከለክል ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ማነኝ ፡ አላቸው።

፲፰ ፤ ወዘንተ ፡ ሰሚዖሙ ፡ አርመሙ ፡

ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ክርክሩን ፡ ተዉ ፡

ወአእኰትዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገኑት ፡

ወይቤሉ ፡ እንዳዒ ፡ ለእመ ፡ ወሀቦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአሕዛብ ፡ ከመ ፡ ይነስሑ ፡ ለሕይወት ።

ድኅነትን ፡ ለማግኘት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ለአሕዛብ ፡ መመለሱን ፡ ይሰጣቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማን፡ ያውቃል ፡ ብለው ፡ አመሰገኑ ፡ ሐተታ ፡ አሁን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መስጠት ፡ መጠራጠር ፡ አይደለም ፡ የነሱን ፡ መመለስ ፡ መጠራጠር ፡ ነው ።

፲፱ ፤ ክፍል ፡ ፳፪ ። ወእለሰ ፡ ተዘርዉ ፡ በእንተ ፡ ቅትለተ፡ እስጢፋኖስ ፡ ወሐሩ ፡ ወበጽሑ ፡ ቆጵሮስ ፡ ወፍንቂስ ፡ ወአንጾኪያ ፡

በሞተ ፡ እስጢፋኖስ ፡ የተበተኑት ፡ ስምንቱ ፡ ሽሕ ፡ ማኅበር ፡ ቆጵሮስ ፡ ፍንቂስ ፡ አንጾኪያ ፡ ደረሱ ፡

እንዘ ፡ ኢይነግሩ ፡ ቃሎሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ለአይሁድ ፡ ለባሕቲቶሙ ፡

ለአይሁድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ከአይሁድ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ወንጌልን ፡ ለአሕዛብ ፡ ሳያስተምሩ ፡ ደረሱ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ፩ ።

፳ ፤ ወቦ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ሰብአ ፡ ቆጵሮስ ፡ ወቀሬናውያን ፡ እለ ፡ ሐሩ ፡ አንጾኪያ ፡ ወነገርዎሙ ፡ ለአረማውያን ፡

ከነሱም ፡ ወገን ፡ የቆጵሮስ ፡ ሰዎች ፡ ቀሬናውያን ፡ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ሂደው ፡

ወመሀርዎሙ፡ በእንተ፡ እግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ለአረማውያን ፡ ያስተማሩ ፡ አሉ ።

፳፩ ፤ ወእደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌሆሙ ፡

ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አድሮባቸዋልና ።

ወበዝኀ ፡ ኍልቆሙ ፡ ለእለ ፡ አምኑ ፡ ወተመይጡ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

እያመኑ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተመለሱትም ፡ ቍጥራቸው ፡ በዛ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፴፯ ።

፳፪ ፤ ወተሰምዐ ፡ ዝ፡ ነገር ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡ በእንቲአሆሙ ፡

በእንቲአሆሙና፡ ዝ ፡ ነገር፡ አንድ፡ ወገን ፡ የሳቸውም ፡ ነገር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ባሉ ፡ በምእመናን ፡ ዘንድ ፡ ደርሶ ፡ ተሰማ ፡

ወፈነውዎ ፡ ለበርናባስ ፡ አንጾኪያ ።

በርናባስንም ፡ ትምህርት ፡ እገዝ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ሰደዱት ።

፳፫ ፤ ወበጺሖ ፡ ርእየ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ።

አንጾኪያ ፡ ደርሶ ፡ ወንጌል ፡ መልታ ፡ ሰፍታ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡

ወተፈሥሐ ፡

ደስ ፡ አለው ፡

ወመሀሮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ይትመየጡ ፡ በኵሉ ፡ ልቦሙ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

በፍጹም ፡ ልቡናቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ለሁሉም ፡ አስተማራቸው ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፵፫ ።



፳፬ ፤ እስመ ፡ ብእሲ ፡ ጻድቅ ፡ ውእቱ ።

ደግ ፡ ሰው ፡ ነውና ፡ ተፈሥሐ ፡

ወምሉእ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያደረበት ፡ ነውና ፡

ወሃይማኖት ፡

ሃይማኖቱ ፡ ፍጹም ፡ ነውና ፡ መሐሮሙ ። ላለው ፡

ወተወሰኩ ፡ ብዙኃን ፡ አሕዛብ ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ ።

ብዙ ፡ አሕዛብ ፡ በጌታችን ፡ እያመኑ ፡ ተጨመሩ ፡ ተወሰኩ ፡ በስምንቱ ፡ ሽሕ ፡ ማኅበር ፡ ላይ፡ ነው፡ ም፡ ፮፡ ፭፡ ም፡ ፭፡ ፲፬።

፳፭ ፤ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ በርናባስ ፡ ጠርሶን ፡ ይኅሥሥ ፡ ለሳውል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በርናባስ ፡ ሳውልን ፡ እየፈለገ ፡ ወደ ፡ ጠርሶን ፡ ሄደ ፡ ከዚህ ፡ ምርት ፡ ይፈስለት ፡ እንጅ ፡ ብሎ ።

ወረከቦ ፡ ወወሰዶ ፡ አንጾኪያ ።

ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ወሰደው ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፴ ።

፳፮ ፤ ወነበሩ ፡ አሐተ ፡ ዓመተ ፡ ኅቡረ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘአንጾኪያ ፡

በአንጾኪያ ፡ ጉባኤ ፡ ዓመት ፡ በኅብረት ፡ እያስተማሩ ፡ ኖሩ ፡

ወመሐሩ ፡ ለብዙኃን ፡ አሕዛብ ።

ለብዙ ፡ ምእመናን ፡ አስተማሩ ፡

ወተሰምዩ ፡ አርድእት ፡ ክርስቲያነ ፡ በአንጾኪያ ፡ ቀዲሙ ፡

ምእመናንም ፡ መጀመሪያ ፡ በአንጾኪያ ፡ ክርስቲያን ፡ ተባሉ ፡ ከዚያ ፡ አስቀድሞ ፡ ምን ፡ ይባሉ ፡ ኑሯል ፡ ቢሉ ፡ ቢጽ ፡ ሕዝብ ፡ ኅሩያን ፡ አርድእት ፡ ይባሉ ፡ ነበር ፡ ገላት ፡ ፪ ፡ ፲፩ ።

፳፯ ፤ ክፍል ፡ ፳፫ ። ወውእተ ፡ አሚረ ፡ ወረዱ ፡ ነቢያት ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ ለአንጾኪያ ።

ወተሰምዩ ፡ አርድእት ፡ ክርስቲያነ ፡ በአንጾኪያ ፡ ቀዲሙ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡አርድእት ፡ ክርስቲያን ፡ በተባሉበት ፡ ወራት ፡ መምህራን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ሄዱ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፩ ። ፲፭ ፡ ፴፪ ።

፳፰ ፤ ወተንሥአ ፡ አሐዱ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ዘስሙ ፡ አጋቦስ ፡ ወነገረ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ይመጽእ ፡ ረኃብ ፡ ዐቢይ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ።

ከነሱም ፡ ወገን ፡ አጋቦስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተነሥቶ ፡ ባራቱ ፡ መዓዝን፡ ጽኑ ፡ ረኃብ ፡ እንዲሆን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገልጦለት ፡ ተናገረ ፡

ወዝ ፡ ዘኮነ ፡ በመዋዕለ ፡ ቀላውዴዎስ ።

ይኸውም ፡ በቀላውዴዎስ ፡ ዘመን ፡ የሆነው ፡ ነው ። አንድም ፡ ዘእንበለ ፡ ዘኮነ ፡ ይላል ፡ በቀላውዴዎስ ፡ ዘመን ፡ ከሆነው፡ ሌላ ፡ ጽኑ ፡ ረኃብ ፡ እንዲሆን ፡ ተናገረ ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፲ ።

፳፱ ፤ ወእምዝ ፡ አስተዋፅኡ ፡ አርድእት ፡ መጠነ ፡ ይክሉ ፡ ወፈነዉ ፡ ለቢጾሙ ፡ ለእለ፡ ይነብሩ፡ ብሔረ ፡ ይሁዳ ፡ ምስለ ፡ በርናባስ ፡ ወሳውል ፡ ኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ ቀሲሳን ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ምእመናን ፡ የሚቻላቸውን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ አወጣጥተው ፡ በብሔረ ፡ ይሁዳ ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ ለበርናባስና ፡ ለሳውል ፡ አስይዘው ፡ ከቀሳውስት ፡ ዘንድ ፡ ላኩ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፡ ፲፪ ። ክፍል ፡ ፳፬ ።

፩ ፤ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ አኀዘሙ ፡ ሄሮድስ ፡ ለሥ
ዩማነ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአሕመሞሙ ።

በዚያ ፡ ወራት ፡ ሄሮድስ ፡ በምእመናን ፡ ላይ ፡ የተሾሙ ፡ ሐዋርያትን ፡ ይዞ ፡ መከራ ፡ አጸናባቸው ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፫ ።

፪ ፤ ወቀተሎ ፡ ለያዕቆብ ፡ እኁሁ ፡ ለዮሐንስ ፡ በሰ
ይፍ ፡

የዮሐንስ ፡ ወንድም ፡ ያዕቆብንም ፡ በሰይፍ ፡ አስመታው ።

፫ ፤ ወርእዮ ፡ ከመ ፡ ተፈሥሑ ፡ አይሁድ ፡ አኀዞ ፡
ካዕበ ፡ ለጴጥሮስ ።

አይሁድም ፡ በያዕቆብ ፡ ሞት ፡ ደስ ፡ እንዳላቸው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ዳግመኛ፡ ጴጥሮስን፡ ያዘው ፡ ሐተታ ፡ በጭፍራው ፡ ሞት ፡ ይህን፡ ያህል፡ ደስ ፡ ያላቸው፡ ባለቃውማ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ብሎ ።

፬ ፤ ወበዓለ ፡ ፋሲካ ፡ ውእተ ፡ አሚረ ፡ ወእኂዞ ፡
ሞቅሖ ፡

ያን ፡ ጊዜም ፡ በዓለ ፡ ፋሲካ ፡ ነበርና፡ ይዞ ፡ አስሮ ፡

ወወሀቦሙ ፡ ለዐሠርቱ ፡ ወስድስቱ ፡ ሠገራት ፡ እለ ፡
የዐቅብዎ ፡

ለሚጠብቁት ፡ ላሥራ ፡ ስድስት ፡ ሠገራት ፡ ሰጠው ፡

ወፈቀደ ፡ እምድኅረ ፡ ፋሲካ ፡ ያቅርቦ ፡ ኀበ፡ ሕዝብ፡

ከፋሲካ ፡ በኋላ ፡ ለሕዝቡ ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠው ፡ ወዶ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፳፬ ።

፭ ፤ ወየዐቅብዎ ፡ ለጴጥሮስ ፡ በቤተ ፡ ሞቅሕ ።

ጴጥሮስንም ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ ይጠብቁት፡ ነበር ፡

ወይጼልዩ ፡ ወትረ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንቲ
አሁ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ።

ምእመናንም ፡ ስለሱ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ባንድነት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጸልዩለት ፡ ነበር ።

፮ ፤ ወበይእቲ ፡ ሌሊት ፡ እንተ ፡ ጸቢሖ ፡ ፈቀደ ፡
ሄሮድስ ፡ ከመ ፡ ይመጥዎ ፡ ለአይሁድ ።

(ግጥም) ፡ ጸቢሖ ፡ በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ ፈቀደ ፡ በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ ሌሊቱ ፡ በነጋ፡ ጊዜ ፡ ለአይሁድ ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠው ፡ ወደደ ፡

ወእንዘ ፡ ይነውም ፡ ጴጥሮስ ፡ ማዕከለ ፡ ክልኤቱ ፡
ሠገራት ።

ይነውም ፡ በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ከሁለት ፡ ሠገራት ፡ መካከል ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፡ ምነው ፡ ሐተታ ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ብሎ ፡ የለም ፡ ማዕከለ ፡ ክልኤቱ ፡ ሠገራት ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ዐሥራ ፡ አራቱ ፡ ከደጅ ፡ ሁነው ፡ ይጠብቃሉ ፡ ሁለቱ ፡ ከውስጥ ፡ ይዘውት ፡ ተኝተው ፡ ነበርና ። አንድም ፡ ስምንቱ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ስምንቱ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ሁነው ፡ እሱን ፡ ከመካከል ፡ አድርገው ፡ ይዘውት ፡ ተኝተው ፡ ነበርና ፡ ማዕከለ ፡ ክልኤቱ ፡ ሠገራት ፡ አለ ፡

ወሙቁሒት ፡ ክልኤሆን ፡ እደዊሁ ፡ በሰናስል ።

ሁለቱም ፡ እጆቹ ፡ በሰንሰለት ፡ ታስረው ፡ ነበር ፡

ወዐቀብት ፡ የዐቅቡ ፡ አናቅጸ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ።

ጭፍሮቹም ፡ በሩን ፡ ይዘው ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ።

፯ ፤ ወወረደ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወቆመ ፡
ኀቤሁ ።

ወርዶ ፡ በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መላክ ፡ ወርዶ ፡ ካጠገቡ ፡ ቆመ ፡



ወአብርሃ ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ ቤት ።

ቤቱም ፡ ብርሃን ፡ ሆነ ፡

ወጐድኦ ፡ መልአክ ፡ ገቦሁ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ወአንቅሖ ።

መልአኩ ፡ ጴጥሮስን ፡ ጐኑን ፡ ጐንጦ ፡ አስነሣው ።

ወይቤሎ ፡ ተንሥእ ፡ ፍጡነ ።

ፈጥነህ ፡ ተነሥ ፡ ብሎ ።

ወወድቃ ፡ መዋቅሕት ፡ እምእደዊሁ ።

ሰንሰለቶቹም ፡ ከእጁ ፡ ወልቀው ፡ ወደቁ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ፲፱ ።

፰ ፤ ወይቤሎ ፡ ውእቱ ፡ መልአክ ፡ ቅንት ፡ ሐቋከ ፡
ወተሠአን ፡ አሣእኒከ ።

መልአኩም ፡ ወገብህን ፡ ታጠቅ ፡ ጫማህን ፡ አድርግ ፡ አለው ፡

ወገብረ ፡ ከማሁ ፡

እንዳለው ፡ አደረገ ።

ወይቤሎ ፡ ተዐጸፍኬ ፡ ልብሰከ ፡ ወነዓ ፡ ትልወኒ ።

ልብስህን ፡ ለብሰህ ፡ ና ፡ ተከተለኝ ፡ አለው ። ሐተታ ፡ ተከተለኝ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ደንግጦ፡ ሲነሣ ፡ ልብሱ ፡ ወድቆበታልና። አንድም፡ የሱን፡ ልብስ፡ አኑረው፡የነሱን ፡ ልብስ ፡ አልብሰው ፡ ይዘውት፡ ተኝተው ፡ ነበርና ፡ ተዐፀፍኬ ፡ ልብሰከ ፡ አለው ።

፱ ፤ ወወጽአ ፡ ወተለዎ ፡

ከቤት ፡ ወጥቶ ፡ ተከተለው ፡

ወኢያእመረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከመ ፡ ዘእሙን ፡ አስተር
አዮ ፡ መልአክ ፡

በውነት ፡ የታየው ፡ መልአክ ፡ እንደ ፡ ሆነ አላወቀም ፡ አለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ አልመሰለውም ፡ ነበር ፡

አላ ፡ ሕልመ ፡ ዘየሐልም ፡ ይመስሎ ፡

ሕልም ፡ የሚያልም ፡ ይመስለው ፡ ነበር ፡ እንጅ ።

፲ ፤ ወወፂአሙ ፡ ቀዳማዌ ፡ ዓጸደ ፡ ወካልአ ፡ በጽ
ሑ ፡ ኀበ ፡ ኆኅተ ፡ ኀጺን ፡ ወተርኀወት ፡ ሶቤሃ ፡
ለሊሃ ።

አንዱን ፡ በር ፡ ሁለተኛውን ፡ በር ፡ ወጥተው ፡ የብረት ፡ ሣንቃ ፡ካለበት ፡ በር ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥና ፡ በገዛ ፡ እጅዋ ፡ ተከፈተች ።

ወወጺአሙ ፡ ሐሩ ፡ አሐተ ፡ ሰኰተ ።

በሩን ፡ ወጥተው፡ አንድ፡ ሜዳ፡ባንድነት ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡

ወኀደጎ ፡ ዝኩ ፡ መልአክ ፡ ለጴጥሮስ ።

ያ ፡ መልአክ ፡ ጴጥሮስን ፡ ተለየው ።

፲፩ ፤ ወገብአ ፡ ልቡ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ሶቤሃ ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ የጴጥሮስ ፡ ልቡ ፡ ተመለሰ ፡ አለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አወቀ ።

ወይቤ ፡ ይእዜ ፡ አእመርኩ ፡ ከመ ፡ በአማን ፡ ፈነወ ፡
እግዚአብሔር ፡ መልአኮ ፡ ወአድኀነኒ ፡ እምእዴሁ ፡
ለሄሮድስ ፡

በውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ መላክተኛውን፡ ሰዶ ፡ ከሄሮድስ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ አዳነኝ ፡ አወቅሁ ፡

ወእምኵሉ ፡ ተስፋሆሙ ፡ ለሕዝበ ፡ አይሁድ ።

ከአይሁድ ፡ ወገኖች ፡ ተስፋ፡ ሁሉ፡ እንደ፡ አዳነኝ ፡ አወቅሁ ፡ ሐተታ ፡ ምን ፡ ተስፋ፡ ነበራቸው ፡ ቢሉ ፡ እንገለዋለን ፡ የማለት ፡ ተስፋ ፡ ነበራቸው ።

## ክፍል ፡ ፳፭ ።

፲፪ ፤ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ ቤተ ፡ ማርያም ፡ እሙ ፡ ለዮ
ሐንስ ፡ ዘተሰምየ ፡ ማርቆስ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ማርቆስ ፡ የተባለ ፡ የዮሐንስ ፡ እናት ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ ማርያም ፡ ቤት ፡ ሄደ ፡ ብዙ ፡ ማርያም ፡ አለና፡ ከዚያ ፡ ሲለይ ፡ እሙ ፡ ለዮሐንስ ፡ ብዙ ፡ ዮሐንስ፡ አለና ፡ ዘተሰምየ፡ ማርቆስ ፡ አለ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኀበ ፡ ሀለዉ፡ ብዙኃን፡ አኃው፡ ጉቡአን፡ወይጼልዩ።

ብዙ ፡ ምእመናን ፡ ተሰብስበው ፡ ወደሚ ጸልዩበት ፡ ሄደ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፴፯ ።

፲፫ ፤ ወጐድጐደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኆኅተ ፡

ጴጥሮስም ፡ ሂዶ ፡ ደጅ ፡ መታ ፡

ወመጽአት ፡ ወለት ፡ ታርኅዎ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ሩዳ።

ወለት ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ሩዳ ፡ ሩዳ፡ የምት ባል ፡ ብላቴና ፡ ልትከፍትለት ፡ መጣች ።

፲፬ ፤ ወአእሚራ ፡ ቃለ ፡ ጴጥሮስ ፡ እምትፍሥሕት፡ ኢያርኀወት ።

ጴጥሮስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቃሉ ፡ አውቃ ፡ ከደስታዋ ፡ የተነሣ ፡ ሳትከፍትለት ፡

ወሮጸት ፡ ወነገረቶሙ ፡ እንዘ ፡ ይቀውም ፡ ጴጥሮስ ፡ ኀበ ፡ ኆኅት ።

ፈጥና ፡ ሂዳ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከበር ፡ ቁሟል ፡ ብላ ፡ ነገረቻቸው ።

፲፭ ፤ ወይቤልዋ ፡ ተዐብዲኑ ፡ ተዐገሢ ፡ ምዕረ ፡

ክልፍ ፡ ክልፍ ፡ ስትል ፡ አይተው ፡ አእ ምሮዋ ፡ ተሥቷታልን ፡ እስቲ ፡ ጸጥ ፡ በይ፡ አሏት ፡

ወጐድጐደ ፡ በሕቁ ፡

ጴጥሮስም ፡ መላልሶ ፡ ደጅ ፡ መታ ፡

ወይቤሉ ፡ መልአክኑ ፡ እንጋ ፡ ውእቱ ።

ጴጥሮስ ፡ እግሩን ፡ እጁን ፡ ታሥሮ ፡ ዐሥ ራ ፡ ስድስት ፡ ሠገራት ፡ እየጠበቁት ፡ የሚ መጣ ፡ መልአክ ፡ ነውን ። አንድም ፡ መል አክ ፡ ዑቃቢዋ ፡ ታይቷት ፡ ይሆን ፡ አሉ ፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፴፯ ።

፲፮ ፤ ወጐንደየ ፡ ጴጥሮስ ፡ እንዘ ፡ ይጐደጕድ ፡

ጴጥሮስም፡ መላልሶ፡ ደጅ፡ ሲመታ፡ ቆየ ፡

ወሶበ ፡ አርኀውዎ ፡ ወርእይዎ ፡ ደንገፁ ፡

ከፍተው ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ የደስታ ፡ ድን ጋጤ ፡ ደነገጡ ።

፲፯ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አርምሙ ፡

ዝም ፡ በሉ ፡ አላቸው ።

ወነገሮሙ ፡ ዘከመ ፡ አውፅአ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምነ፡ ሞቅሕ ፡

እግዚአብሔር ፡ ከእሥር ፡ ቤት ፡ እንዳወ ጣው ፡ ነገራቸው ፡

ወይቤሎሙ ፡ ንግርዎሙ ፡ ለያዕቆብ ፡ ወለኵሎሙ ፡ አኀዊነ ፡ ዘንተ ፡ ወወፅአ ፡

ለያዕቆብ ፡ ለወንድሞቻችን ፡ ይህን ፡ ነገር ንገሯቸው ፡ ብሎ ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡

ወሖረ ፡ ካልአ ፡ ቤተ ።

ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ሄደ ።

፲፰ ፤ ወጸቢሖ ፡ ተሀውኩ ፡ ሠገራት ፡ ፈድፋደ ፡

በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ጭፍሮች ፡ እጅግ ፡ ተጨ ነቁ ።

ወይቤሉ ፡ ምንተ ፡ ኮነ ፡ እንከ ፡ ጴጥሮስ ።

ጴጥሮስ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ዐየረ ፡ ዐየራትን ፡ ወጣ ፡ ዕመቀ ፡ ዕመቃትን ፡ ወረደ፡ እያሉ። አንድም ፡ ሰውን ፡ ላድን ፡ መጥቻለሁ ፡ ይል ፡ አልነበረምን ፡ ይፍጃቸው ፡ ብሎ ፡ ነውን ፡ እያሉ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ።

፲፱ ፤ ወኀሠሦ ፡ ሄሮድስ ፡ ወኀጢኦ ፡ ኰነኖሙ ፡ ለሠ ገራት ፡

ሄሮድስም ፡ አስፈልጎ ፡ ባጣው ፡ ጊዜ ፡ በጭፍሮች ፡ ቅጣት ፡ ፈረደባቸው ፡

ወአዘዘ ፡ ይቅትልዎሙ ፡

ግደሉ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፳ ፤ ወእምዝ ፡ ወረደ ፡ እምይሁዳ ፡ ለቂሣርያ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከይሁዳ ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ሄደ ፡

እስመ ፡ ተምዐ ፡ ላዕለ ፡ ሰብአ ፡ ጢሮስ ፡ ወሲዶና ፡

በጢሮስ ፡ በሲዶና ፡ ሰዎች ፡ ተቆጥቶ ፡ ነበርና ፡ ከቀጠ ፡ ለዩ ፡ ቁጣ ፡ ኢየይዞ ፡



ወመጽኡ ፡ ኅቡረ ፡ ኀቤሁ ፡ ወአስተብቍዕዎ ፡ ለብ ላስጦን ፡ መጋቤ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡ ይዕርቆሙ ።

አንድ ፡ ሁነው ፡ መጥተው ፡ የንጉሡ ፡ ባለሟል ፡ ብላስጦንን ፡ አስታርቀን ፡ ብ ለው ፡ ማለዱት ፡

እስመ ፡ ትእዛዘ ፡ ብሔሮሙ ፡ ኮነ ፡ እምሄሮድስ ፡ ንጉሥ ፡

ከሄሮድስ ፡ ተሹሞ ፡ ያገራቸው ፡ ምዝክር፡ ነበርና ። አንድም ፡ ያገራቸው ፡ ግብር ፡ በሱ ፡ እጅ ፡ ወጥቶ ፡ ከሄሮድስ ፡ ዘንድ ፡ ደርሶ ፡ ወደ ፡ ቄሣር ፡ ያልፍ ፡ ነበርና ። አንድም ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይሴሲ ፡ ማ ዕደ ፡ ንጉሥ ፡ የንጉሥ ፡ ግብር ፡ አግቢ ፡ ነበርና ። አንድም ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይሴስዩ ፡ ማዕደ ፡ ንጉሥ ፡ የንጉሥ ፡ ግብ ር ፡ አግቦች ፡ ነበሩና ፡ ግብር፡ አስቀርተው፡ እንደ ፡ ጭልጋ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይሴ ሰዩ ፡ እማዕደ ፡ ንጉሥ ፡ የንጉሥ ፡ ግብረ ፡ በሎች ፡ ነበሩ ፡ ገበታ ፡ ረግጠው ፡ ነበ ርና ። አንድም ፡ እስመ ፡ ደቀ ፡ ጽርሑ፡ ይላል ። ባለሚሉ ፡ ነበርና ፡ አስታርቀን ፡ ብለው ፡ ማለዱት ፡ ፩ ፡ ነገሥ ፡ ፳ ፡ ፱ ፡ ፲፩ ። ሕዝ ፡ ፳፯ ፡ ፲፯ ።

፳፩ ፤ ወእምዝ ፡ አሐተ ፡ ዕለተ ፡ ለብሰ ፡ ሄሮድስ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥቱ ፡ ወነበረ ፡ ዐውደ ፡

ከዕለታት ፡ ባንድ ፡ ዕለት ፡ ሄሮድስ ፡ አር ድ ፡ አንቀጥቅጥ ፡ የሚባል ፡ ልብሰ ፡ መን ግሥቱን፡ለብሶ፡በአደባባይ፡በነገር፡ተገኘ ፡

ወአኀዘ ፡ ይኰንኖሙ ።

ቅጣት ፡ ጀመረ ።

፳፪ ፤ ወዐውየዉ ፡ ሕዝብ ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአኮ ፡ በቃለ ፡ ሰብእ ፡

ሕዝቡም ፡ ጃንሆይ ፡ ጃንሆይ ፡ ብለው ፡ ያይደለ ፡ አምላክ ፡ አምላክ ፡ ብለው ፡ ጮሁ ፡ ሕዝ ፡ ፳፰ ፡ ፪ ።

፳፫ ፤ ወቀሠፎ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሶቤሃ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ ቀሠፈው ፡

እስመ ፡ ኢያእኰቶ ፡ ለእግዚአብሔር ።

አምላክ ፡ አምላክ ፡ ቢሉት ፡ አይደለሁም፡ አላለምና ። አንድም ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ብለህ ፡ ያይደለ ፡ ስለ ፡ አምላክ ፡ ተወን ፡ ብለው ፡ ለመኑት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መላ ክ ፡ ቀሠፈው ፡ ስለ ፡ አምላክ ፡ ተወን ፡ ቢሉት ፡ አልተዋቸውምና ፡

ወዐጼዮ ፡ ሞተ ፡

ዐጼዮ ፡ ተልቶ ፡ ጸይዖ ፡ ሸቶ ፡ አንጺዎ ፡ ኳ ፡ ደርቋ ፡ ብሎ ፡ አጺዎ ፡ ደጅ ፡ ዘግቶ ፡ የገዛ ፡ አካሉን ፡ እየነጨ ፡ ሞተ ።

፳፬ ፤ ወቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐብየ ፡ ወበዝኀ ፡

እንዲህ ፡ ባለ ፡ ነገር ፡ ወንጌል ፡ ከሁሉ ፡ ደረሰ ።

፳፭ ፤ ወገብኡ ፡ በርናባስ ፡ ወሳውል ፡ እምኢየሩ ሳሌም ፡ ፈጺሞሙ ፡ መልእክቶሙ ።

በርናባስና ፡ ሳውልም ፡ አስተዋጽአውን ፡ አድርሰው ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ፡

ወነሥእዎ ፡ ለዮሐንስ ፡ ዘተሰምየ ፡ ማርቆስ ።

ማርቆስ ፡ የተባለ ፡ ዮሐንስን ፡ አስከት ለው ፡ ተመለሱ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ። ክፍል ፡ ፳፯ ።

፩ ፤ ወሀለዉ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘአንጾኪያ ፡ ነቢያት ፡ ወሊቃውንት ።

በአንጾኪያ ፡ ጉባኤ ፡ መምህራን ፡ ሊቃውንት ፡ ነበሩ ፡ ነቢያት ፡ ሊቃውንት ፡ ብሎ፡ ሁለት ፡ አርእስት ፡ ተናግሯል ፡ ለሁለቱም ፡ ያመጣል ፡

በርናባስ ፡

በርናባስ ፡ ነቢያት ፡ ላለው ፡ አመጣ ፡

ወስምዖን ፡ ዘተሰምየ ፡ ኔጎር ፡

ኔጎር ፡ የተባለ ፡ ስምዖንም፡ ነበር፡ ጸሊመ፡ መልክዕ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሊቃውንት ፡ ላለው ፡

ወሉቅዮስ ፡ ቀሬናዊ ፡

የቀሬን ፡ ሰው ፡ የሚሆን ፡ ሉቅዮስም ፡ ነበር ፡

ወምናሔ ፡ ወልደ ፡ ሐፃኒቱ ፡ ለሄሮድስ ፡ ንጉሥ ፡

የሄሮድስ ፡ የሞግዚቱ ፡ ልጅ ፡ ምናሔም ፡ ነበር ፡

ወሳውል ፡

በርናባስ ፡ ወሳውል ፡ በርናባስና ፡ ሳውል ፡ ነበሩ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፳፯ ፡ ፳፩ ፡ ፲ ።

፪ ፤ ወእንዘ ፡ ይገብሩ ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ፡

እሊህ ፡ ሁሉ ፡ ባንድነት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡

ወይጸውሙ ፡ ወይጼልዩ ፡

ግብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡ አመጣ፡ ሲጾሙ ፡ ሲጸልዩ ፡

ይቤሎሙ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍልጥዎሙ ፡ ሊተ ፡ ለበርናባስ ፡ ወለሳውል ፡ ለግብር ፡ ዘፈቀድክዎሙ ።

መንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ሳውልንና፡ በርናባስን ፡ እኔ ፡ እሱን ፡ ለመረጥሁላቸው ፡ ግብር ። አንድም ፡ ለግብር ፡ ዘፈቀድክዎ ፡ እነሱን፡ ለመረጥሁለት ፡ ግብር፡ ለዩልኝ፡ አላቸው፡ ም ፡ ፱ ፡ ፲፭ ።

፫ ፤ ወእምዝ ፡ ጾሙ ፡ ወጸለዩ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጾም ፡ ጸሎት ፡ አደረጉ ፡

ወወደዩ ፡ እደዊሆሙ ፡ ዲቤሆሙ ፡ ወፈነውዎሙ ፡

እጃቸውን ፡ ጫኑባቸው ፡ ሾሚቸው ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ፳፫ ። ም ፡ ፮ ፡ ፮ ።

፬ ፤ ወተፈኒዎሙ ፡ እምኀበ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወረዱ ፡ ሴሌውንቅያ ፡

ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተሹመው፡ ተልከው፡ ወደ ፡ ሴሌውንቅያ ፡ ሄዱ ፡

ወእምህየ ፡ ነገዱ ፡ ቆጵሮስ ።

ከዚያም ፡ ወደ ፡ ቆጵሮስ ፡ ሄዱ ።

፭ ፤ ወበዊኦሙ ፡ ሀገረ ፡ ስልማና ፡ ነገሩ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በምኲራባቲሆሙ ፡ ለአይሁድ ፡

ከዚያም ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ስልማና ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በአይሁድ ፡ ምኲራብ ፡ ገብተው ፡ አስተማሩ ።

ወሀሎ ፡ ዮሐንስ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ይትለአኮሙ ፡

ዮሐንስ ፡ ዘተሰምየ ፡ ማርቆስም ፡ ዕንጨት ፡ እየሰበረ ፡ ውኃ ፡ እየቀዳ ፡ ያገለግላቸው ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ፲፪ ፡ ፳፭ ።

፮ ፤ ወሶበ ፡ አንሶሰዉ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ደስያት ፡ በጽሑ ፡ ሀገረ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ጳፉ ።

በደሴቱ ፡ ሁሉ ፡ እየዞሩ ፡ ካስተማሩ ፡ በኋላ ፡ ጳፉ ፡ ከምትባል ፡ አገር ፡ ደረሱ ፡

ወረከቡ ፡ በህየ ፡ ብእሴ ፡ ዘሥራይ ፡ አይሁዳዌ ፡

በጳፉ ፡ ትውልዱ ፡ ነገዱ ፡ ከአይሁድ ፡ ወገን፡የሚሆን፡አንድ፡ሥራየኛ፡ሰው፡አገኙ

ሐሳዌ ፡ ነቢየ ፡

ሐሰተኛ ፡ ነቢይ ፡ የሚሆን ፡ ሐሳዌ ፡ ነቢይ ፡ በነቢይ ፡ የሚያብል ፡



ወስሙ ፡ በርያሱስ ፡

ስሙም ፡ በርያሱስ ፡ ይባል ፡ ነበር ።

፯ ፤ ዘሀሎ ፡ ኀበ ፡ መልአክ ፡ ሰርግዮስ ፡ ጳውሎስ ፡ ብእሲ ፡ ጠቢብ ፡

ብልህ ፡ አዋቂ ፡ ከሚሆን ፡ ከሹሙ ፡ ከሰርግዮስ ፡ ጳውሎስ ፡ ዘንድ ፡ የነበረ ፡

ወፈቀደ ፡ ይስማዕ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።

ወንጌልን ፡ ሊማር ፡ ወዶ ፡

ወጸውዖሙ ፡ ለበርናባስ ፡ ወለሳውል ።

ሳውልንና ፡ በርናባስን ፡ ጠራቸው ።

፰ ፤ ወይትዋቀሥዎሙ ፡ ውእቱ ፡ ዘሥራይ ፡ ዘይብልዎ ፡ ኤልማስ ፡

ኤልማስ ፡ የሚሉት ፡ ያ ፡ ሥራየኛም ፡ ይከራከራቸው ፡ ነበር ።

እስመ ፡ ከመዝ ፡ ትርጓሜ ፡ ስሙ ።

የስሙ ፡ ትርጓሜ ፡ ይህ ፡ ነውና ፡ ለምንት፡ መከልእ ፡ ማለት ፡ ነውና ፡

ወፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይክልኦ ፡ ለመልአክ ፡ አሚነ ፡

ሹሙን ፡ ከማመን ፡ ሊከለክለው ፡ ወደደ ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፰ ።

፱ ፤ ወመልአ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕለ ፡ ሳውል ፡

በሳውልም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አደረበት፡ ተለይቶትን ፡ ያውቃል ፡ ሥራ ፡ አሠራው፡ ሲል ፡ ነው ፡

ዘውእቱ ፡ ጳውሎስ ፡

ይኸውም ፡ ጳውሎስ ፡ ነው ፡

ወነጸሮ ፡

እሱን ፡ በመዓት ፡ ዐይን ፡ አይቶ ።

፲ ፤ ወይቤሎ ፡ ኦ ፡ ጽጉበ ፡ ኃጢአት ፡

ኃጢአትን ፡ የተመላህ ፡

ወኵሉ ፡ እከይ ፡

ክፋትን ፡ ሁሉ ፡

ወልዱ ፡ ለሰይጣን ፡

የሰይጣን ፡ የግብር ፡ ልጁ ፡

ፀሩ ፡ ለኵላ ፡ ጽድቅ ፡

የሃይማኖት ፡ ደመኛዋ ፡

አበይከ ፡ ትኅድግ ፡ እንዘ ፡ ተዐሉ ፡ ፍኖተ፡ እግዚአብሔር ፡ ርቱዐ ።

የቀናውን ፡ ሕግ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያጣመምህ ፡ አልመለስም ፡ አልህን ።

፲፩ ፤ ወይእዜኒ፡ ናሁ፡ እደ፡ እግዚአብሔር፡ላዕሌከ ፡

አሁንም ፡ እነሆ ፡ ሥልጣነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልታጠፋኽ ፡ ተቃጥታለች ፡

ወተዐውር ፡ አእይንቲከ ፡

ዐይንህ ፡ ከማየት ፡ ይከለከላል ፡

ወኢትሬኢ ፡ ፀሓየ ፡ ወወርኃ ፡

በመዓልት ፡ ፀሓይን ፡ በሌሊት ፡ ጨረቃን ፡ አታይም ፡

እስከ ፡ አመ ፡ ይበጽሕ ፡ ዕድሜከ ፡

እስክትሞት ፡ ድረስ ፡ አለው ፡

ወተጸለለ ፡ ሶቤሃ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ዐይኑ ፡ ጠፋ ፡

ወጸልመ ፡

ብርሃን ፡ ከማየት ፡ ተከለከለ ፡

ወኀሠሠ ፡ ዘይመርሖ ፡

የሚመራው ፡ ሻ ፡ አለ ፡ ምሩኝ ፡ አለ ።

፲፪ ፤ ወርእዮ ፡ መልአክ ፡ ዘኮነ ፡ ደንገፀ ፡

ሹሙም ፡ የተደረገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የአንክሮ ፡ ድንጋጤ ፡ ደነገጠ።

ወአምነ ፡ በእግዚእነ ፡

ደንግጦም ፡ በጌታችን ፡ አመነ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ስሙን ፡ አበርክቶታል ፡ የበረያሱስን ፡ ዐይነ ፡ ሥጋውን ፡ በተአምራት ፡ ሲያጠፋበት ፡ የሱን ፡ ዐይነ ፡ ሕሊናውን ፡ በትምህርት ፡ ሲያበራለት ፡ አይቶ ፡ እኔ ፡

www.ethiopianorthodox.org

አፍአዊውን፡ አእምሮ፡ በአፍአዊ ፡ ጥበብ፡ ብሩህ ፡ ባደርግ ፡ እናት ፡ አባቴ ፡ ጳውሎ ስ ፡ ብለውኝ ፡ ነበረ ፡ ውሣጣዊውን ፡ አእ ምሮ ፡ በውሣጣዊ ፡ ጥበብ ፡ ብሩህ ፡ ለም ታደርግ ፡ ላንት ፡ ጳውሎስ ፡ መባል ፡ ይገ ባሃል ፡ ብሎ ፡ አበርክቶታል ፡ እንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ጳውሎስ ፡ እያለው ፡ ይሄዳል ።

፲፫ ፤ ወእምዝ ፡ ኀለፉ ፡ በባሕር ፡ እለ ፡ ጳውሎስ ፡ እምነ ፡ ጳፉ ፡ ሀገር ፡

ወሶበ ፡ አንሶሰዉ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ደስ ያት ፡ በጵሑ ፡ ሀገረ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ጳፉ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ እለ ፡ ጳውሎስ ፡ በባሕር ፡ በመርከብ ፡ ተጭነው ፡ ጳፉ ፡ ከምትባል ፡ አገር ፡ ወጥተው ፡ ሄዱ ፡

ወበጵሑ ፡ ጴርጌን ፡ ዘጵንፍልያ ፡

የጵንፍልያ ፡ አውራጃ ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ ጴርጌን ፡ ደረሱ ፡

ወኀደጎሙ ፡ ዮሐንስ ፡ ወተሠውጠ ፡ ኢየሩሳሌም ፡

ማርቆስ ፡ የተባለ ፡ ዮሐንስም ፡ ተለይቷ ቸው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሰ ፡ ሕፃን ፡ ነውና ፡ መከራውን ፡ ተሰቆ ፡ ም ፡ ፲፭ ፡ ፴፰ ።

፲፬ ፤ ወእሙንቱሰ ፡ ኀለፉ ፡ እምጴርጌን ፡

እነሱ ፡ ግን ፡ ከጴርጌን ፡ ወጥተው ፡ ሄዱ ፡

ወበጵሑ ፡ አንጾኪያ ፡ ዘጲስድያ ፡

የጲስድያ ፡ አውራጃ ፡ ወደምትሆን ፡ አን ጾኪያ ፡ ደረሱ ፡

ወቦኡ ፡ ምኵራብ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ወነበሩ ፡

ቅዳሜ ፡ ቀን ፡ ከምኵራብ ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ።

፲፭ ፤ ወእምድኅረ ፡ አንበቡ ፡ ኦሪተ ፡ ወነቢያተ ፡ ለአኩ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡

ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ኦሪትን ፡ ነቢያትን ፡ ካነበቡ ፡ በኋላ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ለነ ፡ ጳው ሎስ ፡ ነው ፡ በነጳውሎስ ፡ ላኩባቸው ። አንድም ፡ በእንግዳ ፡ ልማድ ፡ አንቡ ፡ ብለው፡ ሰጠዋቸዋል ፡ እለ፡ ጳውሎስ፡ ኦሪ ትን ፡ ነቢያትን ፡ ካነበቡ ፡ በኋላ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ በነጳውሎስ ፡ ላኩባቸው ፡

ወይቤልዎሙ ፡ አንትሙ ፡ አኃዊነ፡ ለእመ፡ ቦ፡ እም ውስቴትክሙ ፡ ዘይክል ፡ ሠናየ ፡ ነገረ ፡ አይድዕዎ ሙ ፡ ለሕዝብ ፡

ወንድሞቻችን ፡ ከናንተ ፡ ወገን ፡ ትር ጓሜ ፡ የሚያውቅ ፡ እንዳለ ፡ ለሕዝቡ ፡ ተርጕማችሁ ፡ ንገሯቸው ፡ ብለው ።

፲፮ ፤ ክፍል ፡ ፳፯ ፡ ወተንሥአ ፡ ጳውሎስ ፡

ወዶ፡ ጳውሎስ፡ ይህን፡ ሲያገኝ ፡ ተነሥቶ ፡

ወአዘዘ ፡ ያርምሙ ፡

ዝም ፡ በሉ ፡ አላቸው ፡

ወይቤሎሙ ፡ ስምዑ ፡ ሰብአ ፡ እስራኤል ፡

እናንት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ስሙ ፡ ዕወቁ ፡

ወእለኒ ፡ ትፈርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ የምትፈሩ ፡ የምታመ ልኩ ።

፲፯ ፤ አምላኮሙ ፡ ለሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ኀረዮሙ ፡ ለአበዊነ ፡

የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ አባቶቻችንን ፡ መር ጧቸዋል ፡ እንደ ፡ መረጣቸው ፡ ዕወቁ ፡

ወአዕበዮሙ ፡ ለሕዝቡ ፡ በኀበ ፡ አፍለሶሙ ፡ በም ድረ ፡ ግብፅ ።

ተሰደው ፡ በሄዱበት ፡ አገር ፡ በግብፅ ፡ አበዛቸው ፡ እንዳበዛቸው ፡ ዕወቁ ፡

ወበመዝራዕቱ ፡ ልዑል ፡ አውፅአሙ ፡ እምህየ ።

በጽኑ ፡ ሥልጣኑ ፡ ከግብፅ ፡ አወጣቸው ፡ ዘጠኝ ፡ መቅሠፍት ፡ ዐሥረኛ ፡ ሞተ ፡ በኵር ፡ አድርጎ ፡ እንዳወጣቸው ፡ ዕወቁ ፡ ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፪። ዘፀአ ፡ ፲፪ ፡ ፴፯ ፡ ፵፩ ።



፲፰ ፤ ወሴሰዮሙ ፡ በገዳም ፡ አርብዓ ፡ ዓመተ ።

አርባ ፡ ዘመን ፡ መና ፡ ከደመና ፡ እያወ ረደ ፡ ውኃ ፡ ከደንጊያ ፡ እያፈለቀ ፡ መገ ባቸው ፡ ዘፀአ ፡ ፲፮ ፡ ፴፭ ። ዘኍል ፡ ፲፬ ፡ ፴፬ ። ዘዳግ ፡ ፩ ፡ ፴፩ ።

፲፱ ፤ ወአእተተ ፡ ሰብዐተ ፡ አሕዛበ ፡ ከነዓን ፡ ወአ ውረሶሙ ፡ ምድሮሙ ፡

ሰባቱን ፡ የከነዓን ፡ ነገሥታት ፡ አጥፍቶ ፡ ምድሮሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ነው ፡ የአሕዛ ብን ፡ ምድራቸውን ፡ ለእስራኤል ፡ አወረ ሳቸው ። አንድም ፡ ምድሮሙ ፡ ለእስራ ኤል ፡ ነው ፡ በተስፋ ፡ ወርሰዋት፡ ነበርና ፡ ሐተታ ፡ ምነው ፡ ሰባት ፡ አለ ፡ ሠላሳ ፡ ሁ ለት ፡ አይደሉም ፡ ቢሉ ፡ ሰባቱ ፡ አሞሬ ዎን ፡ ኬጤዎን ፡ ጌርጌሴዎን ፡ ኢዌዎን ፡ ፍሬርዜዎን ፡ ኢያውሴዎን ፡ ከናኔዎን ፡ ሠላሳ ፡ ሁለቱን ፡ ወልደዋል ፡ ሦስቱን ፡ ሙሴ ፡ አጥፍቷቸዋል ፡ ኻያ ፡ ዘጠኙን ፡ ኢያሱ ፡ አጥፍቷቸዋል ፡ ዘዳግ ፡ ፯ ፡ ፩ ። ኢሳ ፡ ፲፬ ፡ ፪ ።

፳ ፤ ወእምድኅረ፡ ዝ ፡ ሤመ ፡ ሎሙ፡ መሳፍንተ ፡ አርባዕተ ፡ ምእተ ፡ ወኀምሳ ፡ ዓመተ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ሳሙኤል ፡ ነቢይ ።

ካወረሳቸው ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ሳሙኤል ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ዘመን ፡ መሳፍንትን ፡ ሾመላቸው ፡ የሙ ሴ ፡ አርባ ፡ የኢያሱ ፡ አርባ ፡ ሰማንያ ፡ የፊንሐስ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዐሥር ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ የኤሊ ፡ አርባ ፡ የሳሙኤል፡ ኻያ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ይሆናል ፡ ምነው ፡ ሙሴማ ፡ የቀረ ፡ በናባው ፡ አይ ደለም ፡ መች ፡ አወረሳቸውና ፡ አውረ ሰሙ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ማውጣቱ ፡ ለማው ረስ ፡ ከሆነ ፡ ብሎ ። አንድም ፡ በዮርዳ ኖስ ፡ ማዶ ፡ የቀሩትን ፡ ሁለቱን ፡ ነገድ ፡ ካወረሰ ፡ ብሎ ፡ ይህስ ፡ አውረሶሙ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ሤመ ፡ ሎሙ ፡ ያለ ፡ ብሎ ፡ የኢያሱ ፡ አርባ ፡ የኤሊ ፡ አርባ ፡ ሰማንያ ፡ የመሳፍንተ ፡ እስራኤል ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ አምስት ፡ የመሳፍንተ ፡ አሕዛብ ፡ ሰማንያ ስምንት ፡ አራት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሦስት ፡ የሳሙኤል ፡ ሰባት ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ፡ ይሆናልና ፡ አርባዕተ ፡ ምእተ ፡ ወሃምሳ ፡ ዓመተ ፡ አለ ፡ መሳ ፡ ፪ ፡ ፲፮ ። ፫ ፡ ፱ ።

፳፩ ፤ ወእምዝ ፡ እንከ ፡ ሰአሉ ፡ ያንግሥ ፡ ሎሙ ፡ ወአንገሠ ፡ ሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳኦልሃ ፡ ወልደ ፡ ቂስ ፡ ብእሴ ፡ ዘእምሕዝበ ፡ ብንያም ፡ አርብዓ ፡ ዓመተ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንግሥ ፡ ለነ ፡ ንጉሠ ፡ ዘይቀንየነ ፡ ብለው ፡ ቢዘበዝቡት ፡ ዘመነ፡ መንግሥት ፡ ሳይደርስ ፡ የይነቅኸ ፡ መን ግሥት ፡ ከብንያም ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡ የቂስ ፡ ልጅ ፡ ሳኦልን ፡ አነገሠላቸው ፡ ፩ ፡ ሳሙኤል ፡ ፲ ፡ ፳፩ ።

፳፪ ፤ ወሠዐሮ ፡ ኪያሁኒ ፡

እሱንም ፡ በሞት ፡ አሳለፈው ፡ ዋዌው ፡ ለመሳፍንተ ፡ አሕዛብ ፡ ነው ።

ወእምድኅሬሁ ፡ አንገሠ ፡ ሎሙ ፡ ደዊትሃ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቀን ፡ ቢደርስ ፡ አምባ ፡ ይፈርስ ፡ እንዲሉ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ቢደርስ ፡ ዳዊትን ፡ አነገሠላቸው ፡

ወሰማዕተ ፡ ኮኖ ፡

መሰከረለት ፡

ወይቤ ፡ ረከብክዎ ፡ ለዳዊት ፡ ወልደ ፡ ዕሤይ ፡ ብእሴ፡ ምእመነ ፡ ዘከመ ፡ ልብየ ።

የዕሤይ ፡ ልጅ ፡ ዳዊትን ፡ ልቡናዬ ፡ እን ደሚወደው ፡ (የታመነ) ፡ ሆኖ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዘይገብር ፡ ኵሎ ፡ ፈቃድየ ፡

ፈቃዴንም ፡ የሚፈጽም ፡ ሁኖ ፡ አገኘ ሁት ። ፩ ፡ ሳሙኤ ፡ ፲፮ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ።

፳፫ ፤ ወእምዘርዐ ፡ ዚአሁ ፡ አምጽአ ፡ ሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኀኒተ ፡ ለእስራኤል ፡ ኢየሱስሃ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከዳዊት ፡ ባሕርይ ፡ ከዳ ዊት ፡ ወገን ፡ ለእስራኤል ፡ መድኃኒት ፡ አድርጎ ፡ ኢየሱስን ፡ አስነሣላቸው ።

በከመ ፡ አሰፈዎሙ ፡

እስመ ፡ እምፍሬ ፡ ከርሥከ ፡ አነብር ፡ ዲበ መንበርከ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ እንዳናገረላ ቸው ፡ ኢሳ ፡ ፲፩ ፡ ፩ ።

፳፬ ፤ ወሰበከ ፡ ሎሙ ፡ ዮሐንስ ፡ ጥምቀተ ፡ ለኵሉ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ከመ ፡ ይነስሑ ፡ እምቅድመ ፡ ምጽአተ ፡ ዚአሁ ፡

ዮሐንስ ፡ ከጌታ ፡ መምጣት ፡ አስቀድሞ ፡ ንስሐ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ለእስራኤል ፡ የጌ ታን ፡ ጥምቀት ፡ አስተማራቸው ፡ አን ሰኬ ፡ አጠምቀክሙ ፡ በማይ ፡ ለንስሐ ፡ ውእቱሰ ፡ ያጠምቀክሙ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወበእሳት ፡ ብሎ ፡ ማቴ ፡ ፫ ፡ ፩ ።

፳፭ ፤ ወፈጺሞ ፡ ዮሐንስ ፡ መልእክቶ ፡

ዮሐንስም ፡ ወንጌልን ፡ አስተምሮ ፡ ከፈ ጸመ ፡ በኋላ ፡

ይቤሎሙ ፡ ምንትኑ ፡ ትትሐዘቡኒ ፡ ኪያየ ፡

እኔን ፡ ክርስቶስ ፡ ነው፡ እያላችሁ፡ ለምን፡ ትጠረጥሩኛላችሁ ፡

አንሰ ፡ ኢኮንኩ ፡ ኪያሁ ፡

እኔ ፡ ክርስቶስ ፡ አይደለሁም ፡

ናሁ ፡ ይመጽእ ፡ እምድኅሬየ ፡ ዘኢይደልወኒ ፡ እፍ ታሕ ፡ ቶታነ ፡ አሣእኒሁ ፡ እምእገሪሁ ።

የእግሩን ፡ ጫማ ፡ ልይዝ ፡ የማልበቃ ፡ እሱ ፡ ከኔ ፡ በኋላ ፡ ይመጣል ፡ አላቸው ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፳ ። ማር ፡ ፩ ፡ ፯ ። ሉቃ ፡ ፫፡፲፮።

፳፮ ፤ አንትሙ ፡ አኃዊነ ፡ ትውልደ ፡ ዘመደ ፡ አብ ርሃም ፡

እናንት ፡ ወንድሞቻችን ፡ የአብርሃም ፡ ልጆች ፡ ናችሁና ፡ ሐተታ ፡ ዘመድ ፡ ይስ ሐቅ ፡ ያዕቆብ ፡ ትውልድ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለ ቱ ። አንድም ፡ ዘመድ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ትውልድ ፡ አይሁድ ፡

ወእለ ፡ ትፈርህዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ የምትፈሩት ፡ የምታመ ልኩት ፡

ለክሙ ፡ ተፈነወ ፡ ዝ ፡ ነገረ ፡ ሕይወት ፡

ይህ ፡ የድኅነት ፡ ነገር ፡ ለናንት ፡ ታዝ ዟል ፡ ቍ ፡ ፵፮ ።

፳፯ ፤ ወእለሰ ፡ ይነብሩ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወመላእክ ቲሆሙ ፡ አብዱ ፡

በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ ግን ፡ አለቆቻ ቸውም፡ሰነፉ፡ አለ፡ አእምሯቸውን፡ አጡ፡

ወኢያእመርዎ ፡ ለዝንቱ ፡

ይህን ፡ ነገር ፡ ስለሱ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ አላወቁትም ፡

ወኢለበዉ ፡ መጻሕፍተ ፡ ነቢያት ፡ እንዘ ፡ ያነብብዎ ፡ በኵሉ ፡ ሰናብት ።

መጻሕፍተ ፡ ነቢያትን ፡ ቅዳም ፡ ቅዳም ፡ ሲመለከቱ ፡ የሚናገሩትን ፡ ምስጢሩን ፡ አልተረዱትም ፡

አላ ፡ ፈትሑ ፡ ላዕሌሁ ፡

ይሞት ፡ በቃ ፡ ፈረዱበት ፡ እንጅ ፡

ወፈጸሙ ፡ ኵሎ ፡ ዘተጽሕፈ ፡ በእንቲአሁ ።

ስለሱ ፡ የተጻፈውን ፡ ሁሉ ፡ ፈጸሙ ፡ አስ ገደሉት ።

፳፰ ፤ ወሶበ ፡ ኢረከቡ ፡ ሎቱ ፡ ጌጋየ ፡ ወኢምንተኒ ፡ በዘይቀትልዎ ፡

ሰቅለው ፡ በሚገሉት ፡ ገንዘብ ፡ የሚገሉ በት ፡ ምክንያት ፡ ባያገኙ ፡



ሰአልዎ ፡ ለጲላጦስ ፡ ከመ ፡ ይቅትሎ ።

ጲላጦስን ፡ ስቀልልን ፡ ብለው ፡ ተካሰሱ ፡ ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።

፳፱ ፤ ወሶበ ፡ ፈጸሙ ፡ ኵሎ ፡ ዘተጽሕፈ ፡ በእንቲ አሁ ።

ስለሱ ፡ ስቅለተ ፡ ትሬኢያ ፡ እስራኤል ፡ ለሕይወትከ ፡ ተብሎ ፡ የተነገረውን ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ማለት ፡ ሰቅለው ፡ ከገ ደሉት ፡ በኋላ ፡

አውረድዎ ፡ እምዕፅ ፡ ወወደይዎ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡

ከነሱ ፡ ወገን ፡ ደጋግ ፡ ሰዎች ፡ ዮሴፍ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ ናቸው ፡ ሥጋውን ፡ ከመስ ቀል፡አውርደው፡ ቀበሩት፡ ማቴ፡ ፳፯፡ ፶፱።

፴ ፤ ወእግዚአብሔር ፡ አንሥኦ ፡ እሙታን ።

እግዚአብሔርም ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ አስነሣው ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፲፭ ፡

፴፩ ፤ ወአስተርአዮሙ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ እም ድኅረ ፡ ተንሥአ ፡ ለእለ ፡ ዐርጉ ፡ ምስሌሁ ፡ እምገ ሊላ ፡ ለኢየሩሳሌም ።

ከሙታንም ፡ ተለይቶ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ከገሊላ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እሱን ፡ ተከ ትለው ፡ ለመጡ ፡ ለመቶ ፡ ኻያው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ታያቸው ፡

ወእሙንቱ ፡ ኮንዎ ፡ ሰማዕተ ፡ በኀበ ፡ ሕዝብ ፡

እነሱም ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ መሰከሩለት ፡ ም ፡ ፩ ፡ ፫ ።

፴፪ ፤ ወንሕነኒ ፡ ንዜንወክሙ ፡ ዘአሰፈዎሙ ፡ እ ግዚአብሔር ፡ ለአበዊነ ፡

እኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ ላባቶቻችን ፡ ያናገረውን ፡ ተስፋ ፡ እንነግራችኋለን ፡ ቍ ፡ ፳፫ ።

፴፫ ፤ ወወሀቦሙ ፡ ለውሉዶሙ ፡

ለልጆቻቸውም ፡ ያደረገውን ፡ ነገር ፡ እን ነግራችኋለን ፡

ወአንሥኦ ፡ ለኢየሱስ ።

ኢየሱስን፡እንዳስነሣው፡እንነግራችኋለን ፡

በከመ ፡ ይቤ ፡ ውስተ ፡ መዝሙር ፡ ዘከልኤቱ ፡ ወል ድየ ፡ አንተ ፡ ወአነ ፡ ዮም ፡ ወለድኩከ ።

ወልድየ ፡ አንተን ፡ አይሻውም ፡ በሁለተ ኛው ፡ መዝሙር ፡ ወአነ ፡ ዮም ፡ ወለድ ኩከ ፡ እንዳለ ፡ አንሥኦ ፡ መዝ ፡ ፪ ፡ ፯ ።

፴፬ ፤ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንሥኦ ፡ እሙታን ፡ ከመ ፡ ኢይገብእኒ ፡ ውስተ ፡ ሙስና ።

ሙስና ፡ መቃብር ፡ እንዳያገኘው፡ ከሙታ ን ፡ ለይቶ ፡ ስላስነሣው ፡ ወአነ ፡ ዮም ፡ ወለድኩከ ፡ እንዳለ ፡ አንሥኦ ፡ ላለው ፡

ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እሁበክሙ ፡ ጽድቆ ፡ ለዳዊት ፡ ዘእ ሙን ።

ጽድቅ ፡ ዘእሙን ፡ የዳዊትንም ፡ የታመነ ፡ እውነተኛ ፡ ነገሩን ፡ እነግራችኋለሁ ፡ ወ አነ ፡ ዮም ፡ ወለድኩከ ፡ ብሏል ፡ ብዬ ፡ ኢሳ ፡ ፶፭ ።

፴፭ ፤ ወውስተ ፡ ካልእኒ ፡ ይብል ፡

በሌላውም ፡ አንቀጽ ፡ ኢትሁቦ ፡ ለጻድ ቅከ ፡ ይርአይ ፡ ሙስና ፡ ብሏል ፡ ብዬ ፡ እነግራችኋለሁ ። አንድም ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ ስላስነሣው ፡ ወአነ ፡ ዮም ፡ ወለ ድኩከ ፡ እንዳለ ፡ አንሥኦ ፡

ኢትሁቦ ፡ ለጻድቅከ ፡ ይርአይ ፡ ሙስና ፡

ሙስና ፡ መቃብርም ፡ እንዳያገኘው ፡ በሌ ላው ፡ አንቀጽ ፡ ኢትሁቦ ፡ ለጻድቅከ ፡ ይርአይ ፡ ሙስና ፡ ብሏል ፡ ብዬ ፡ እነግራ ችኋለሁ ፡ መዝ ፡ ፲፭ ፡ ፲ ።

፴፮ ፤ ወዳዊትኒ ፡ ተልእከ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለትእ ዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኖመ ፡

ዳዊትም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ በዘመኑ ፡ ትንቢት ፡ ተናግሮ ፡ አረፈ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወተቀብረ ፡ ኀበ ፡ አበዊሁ ፡

ካባቶቹ ፡ መቃብር ፡ ተቀበረ ፡

ወርእየ ፡ ሙስና ፡

ሙስና ፡ መቃብር ፡ አገኘው ፡ ም፡ ፪፡ ፳፱።

፴፯ ፤ ወዘሰ ፡ አንሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ኢርእየ ፡ ለሙስና ።

ወአኑ፡ዮም፡ ወለድኩከ፡ እንዳለ፡ እግዚአብ ሔር፡ ከሙታን፡ ለይቶ፡ ያስነሣው፡ክርስቶ ስን፡ ግን፡ ሙስና፡ መቃብር፡ አላገኘውም። አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ ያስነሣው ፡ ክርስቶስን ፡ ኢትሁብ፡ ለጻድቅከ ፡ ይርአይ ፡ ሙስና ፡ እንዳለ ፡ ሙስና ፡ መቃብር ፡ አላገኘውም ።

፴፰ ፤ አእምሩ ፡ እንከ ፡ አኃዊነ ፡ ከመ ፡ በእንቲአሁ ይትኀደግ ፡ ለክሙ ፡ ኃጢአትክሙ ፡ ዘአሰፈወክሙ ።

ከአሕዛብ ፡ አስቀድሞ ፡ ከአሕዛብ ፡ ለይ ቶ ፡ እምጽዮን ፡ ይወፅእ ፡ መድኅን ፡ ወየ አትት ፡ ኃጢአተ ፡ እምእስራኤል ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ያናገረላቸሁ ፡ ወንድሞቻችን ፡ በሱ ፡ ስላመናችሁ ፡ ኃጢአታችሁ ፡ እን ዲሠረይላችሁ ፡ ዕወቁ ፡

፴፱ ፤ እምኵሉ ፡ ዘተስእንክሙ ፡ ጸዲቅ ፡ በሕገ ፡ ኦሪተ ፡ ሙሴ ።

በሙሴ ፡ ሕግ ፡ በኦሪት ፡ መክበር ፡ የተሳ ናችሁ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ኃጢአታችሁ ፡ እንዲሠረይላችሁ ፡ ዕወቁ ።

ወቦቱሰ ፡ ኵሉ ፡ ዘአምነ ፡ ይጸድቅ ።

በሱ፡ ያመነ፡ ግን፡ ይከብራል፡ ሮሜ፡ ፲፡ ፬ ።

፵ ፤ ዑቁ ፡ እንከ ፡ ኢይርከብክሙ ፡ ቃለ ፡ ነቢይ ፡ ዘይቤ ።

እንዲህም ፡ ከሆነ፡ ነቢይ ፡ የተናገረው ፡ ነ ገር፡እንዳይደርስባችሁ፡ዕወቁ፡እንባ፡፩፡፫ ።

፵፩ ፤ ናሁ ፡ ርእዩ ፡ እለ ፡ ታስተሐቅሩ ፡ ወአንክሩ ፡

እንሆ ፡ የምትንቁ ፡ የምታቃልሉ፡ እመኑ ፡

ወትማስኑ ፡

ባታምኑ ፡ ግን ፡ ትጠፋላችሁ ፡

እስመ ፡ አነ ፡ እገብር ፡ ግብረ ፡ በመዋዕሊክሙ ፡ ዘኢ ተአምርዎ ፡

በዘመናችሁ ፡ እናንት ፡ የማታውቁት ፡ እኔ ፡ የምሠራው ፡ ሥራ ፡ አለና ፡ አለ ፡ ሥጋዌ ፡ ነው ፡

ለእመ ፡ ቦ ፡ ዘነገረክሙ ፡

የነገራችሁ ፡ ቢኖር ፡ እመኑ ፡ ባታምኑ ፡ ግን ፡ ትጠፋላችሁ ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ዕወቁ ።

፵፪ ፤ ወአስተብቍዕዎሙ ፡ ከመ ፡ ይንግርዎሙ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ በካልእት ፡ ሰንበት ።

ይህነንስ ፡ ነገር ፡ በሁለተኛ ፡ ሱባኤ ፡ በሁ ለተኛው ፡ ጉባኤ ፡ ትነግሩናላችሁ ፡ ብለ ው ፡ ማለዷቸው ።

፵፫ ፤ ወወፂአሙ ፡ እምኵራብ ፡ ተለውዎሙ ፡ ብዙ ኃን ፡ እምአይሁድ ፡ ወኄራቶሙ ፡ ለጳውሎስ ፡ ወለ በርናባስ ።

ከምኵራቡም ፡ ወጥተው ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ደጋጎ ች፡ጳውሎስንና፡በርናባስን፡ ተከተሏቸው ፡

ወነገርዎሙ ፡

እነሱም ፡ መንገድ ፡ ለመንገድ ፡ አስተማ ሯቸው ፡

ወአምኑ ፡ ወተመይጡ ፡ በጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡

በጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ በወንጌል ፡ እያ መኑ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመለሱ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፳፫ ።

## ክፍል ፡ ፳፰ ።

፵፬ ፤ ወበካልእት ፡ ሰንበት ፡ ተጋብኡ ፡ ኵሉ ፡ ሀገ ር ፡ ይስምዑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡

ወአስተብቍዕዎሙ ፡ ከመ ፡ ይንግርዎሙ፡ ዘንተ ፡ በካልዕት ፡ ሰንበት ፡ ብሎ ፡ ነበርና



ብሁለተኛው ፡ ሱባኤ ፡ በሁለተኛው ፡ ጉ ባኤ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ሔሩ ፡ ወመሐሩ ፡ ያላት፡ወንጌልን፡ይሰሙ፡ዘንድ፡ተሰበሰቡ።

፵፭ ፤ ወርእዮሙ ፡ ካህናተ ፡ አይሁድ ፡ ብዙኀ ፡ ጉባ ኤ ፡ ሕዝብ ፡ ቀንኡ ፡ ላዕሌሆሙ ።

የአይሁድም ፡ ካህናት ፡ የጉባኤውን ፡ ስ ፋት ፡ የሕዝቡን ፡ ብዛት ፡ አይተው ፡ ላዕሌሆሙ ፡ በነጳውሎስ ፡ ቀኑባቸው ፡

ወተዋቀሥዎሙ ፡ ለጳውሎስ ፡ ወለበርናባስ ፡

ጳውሎስንና ፡ በርናባስን ፡ ተከራከሯቸው፡ ወንጌል ፡ እንበለ ፡ ኦሪት ፡ ጥምቀት ፡ እን በለ ፡ ግዝረት ፡ አትረባም ፡ አትጠቅምም፡ ብለው ፡

ወፀረፉ ፡

ክርስቶስን፡ዕሩቅ፡ብእሲ፡ወንጌልን፡ዲቃላ፡ ሕግ፡ ብለው፡ ነቀፉ፡ ቀኍ፡ ፶። ም፡ ፲፬ ፡ ፪ ።

፵፮ ፤ ወነገርዎሙ ፡ ጳውሎስ ፡ ወበርናባስ ፡

ጳውሎስና ፡ በርናባስም ፡ አስተማሯቸው ፡

ወይቤልዎሙ ፡ ለክሙ ፡ ርቱዕ ፡ ንቅድም ፡ ንንግር ክሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡

አስቀድሞ ፡ ወንጌልን ፡ መማር ፡ ለናንት፡ ይገባ ፡ ነበር ፡

ወእመሰ ፡ ትክህዱ ፡

ባታምኑ ፡ ግን ፡

ወኢትሬስዩ ፡ ርእሰክሙ ፡ ለሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡

ራሳችሁንም ለዘለዓለም፡ድኅነት፡ባታበቁ።

ናሁ ፡ ንትመየጥ ፡ መንገለ ፡ አሕዛብ ፡

ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ሂደን ፡ አሕዛብን ፡ እናስ ተምራለን ፡ ብለው፡ አስተማሯቸው ። ም፡ ፫ ፡ ፳፮ ። ማቴ ፡ ፲ ፡ ፮ ።

፵፯ ፤ እስመ ፡ ከማሁ ፡ ይብል ፡ መጽሐፍ ፡ ረሰይ ኩከ ፡ ብርሃኖሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ከመ ፡ ትኩኖሙ ፡ ሕይወቶሙ ።

ለአሕዛብ ፡ መምህራቸው ፡ ዕውቀታቸው፡ አደረግሁህ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡

እስከ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ።

ለአሕዛብ ፡ እስከ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ፡ ጽ ንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ላሉ ፡ አሕዛብ ፡ የድ ኅነት ፡ ምክንያት ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ መም ህራቸው ፡ ዕውቀታቸው ፡ አደረግሁህ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ኢሳ ፡ ፵፱ ፡ ፮ ።

፵፰ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ አሕዛብ ፡ ዘንተ ፡ ተፈሥሑ ፡

አሕዛብም ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ፡ ለኛም፡ ትንቢት ፡ ተነግሮልናልሳ ፡ ለካ ፡ ለኛም ፡ ትንቢት ፡ ተነግሮልናልን ፡ ብለው ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ወሰብሑ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።

ወንጌልን ፡ አክብረው ፡ ተቀበሉ ፡

ወአምኑ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ከፈሎሙ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለ ዓለም ።

የዘለዓለም ፡ ድኅነትን ፡ ያደላቸውም ፡ ሁሉ ፡ አመኑ ፡ ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፱ ።

፵፱ ፤ ወበጽሐ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርት ።

ወንጌል ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ ነገር ፡ ከሁሉ ፡ ደረሰ ።

ወወሀክዎን ፡ አይሁድ ፡ ለአንስት ፡ ወለዐበይተ ፡ ሀ ገር፡ ወለኄራተ ፡ ሀገር ።

አይሁድ ፡ ግን ፡ ሴቶቹን ፡ ደጋጎቹን ፡ ወይዛዝሩን ፡ አነሳሷቸው ።

፶ ፤ ወአንሥኡ ፡ መራደ ፡ ላዕለ ፡ ጳውሎስ ፡ ወበር ናባስ ።

በጳውሎስና ፡ በበርናባስ ፡ ወራሪ ፡ ፈቱ ባቸው ፡

ወሰደድዎሙ ፡ እምብሔሮሙ ።

ከሀገራቸውም ፡ አስወጥተው፡ ሰደዷቸው፡

www.ethiopianorthodox.org

፶፩ ፤ ወነገፉ ፡ ጸበለ ፡ እገሪሆሙ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወኀ ለፉ ፡ ኢቆንዮን ።

ሐዋርያትም ፡ የእግራቸውን ፡ ትቢያ ፡ አራግፈው ፡ ወደ ፡ ኢቆንዮን ፡ ሄዱ ፡ ሐ ተታ ፡ እኛ ፡ ደከምንላችሁ ፡ በእንቢተኛ ነታችሁ ፡ ቀረባችሁ ፡ ፍዳችሁ ፡ በራሳ ችሁ ፡ ነው ፡ ለማለት ። አንድም ፡ ይህ ፡ ከኛ ፡ እንደ ፡ ተለየ ፡ እናንተም ፡ ከኛ ፡ ልዩ ፡ ናችሁ ፡ እኛም ፡ ከከብታችሁ ፡ ልዩ፡ ነን ፡ ለማለት ። አንድም ፡ ሥጋችሁ ፡ በመቃብር ፡ ነፍሳችሁ ፡ በሲኦል ፡ እን ዲህ ፡ ይርገፍ ፡ ለማለት ። አንድም፡ በቄ ሣር ፡ ልማድ ፡ የተበደለ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ሣር ፡ ቋጥሮ ፡ ደንጊያ ፡ ኰልኵሎ ፡ ይን ገር ፡ ብሎ ፡ ሥርዐት ፡ ሠርቶ ፡ ነበርና ፡ በዚያ ፡ ልማድ ፡ ም ፡ ፲፰፡፮። ማቴ፡፲፡፲፬።

፶፪ ፤ ወመልአ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዲበ ፡ ሐዋርያት፡

በሐዋርያትም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አደረ ባቸው ፡ ተለይቷቸው ፡ ያውቃልን ፡ ሥራ፡ አሠራቸው ፡ ሲል ፡ ነው ፡

ወተፈሥሑ ፡

በመከራው ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፬ ።

፩ ፤ ወበሀገረ ፡ ኢቆንዮን ፡ ቦኡ ፡ ምኵራበ ፡ አይ ሁድ ፡ ወአረሚ ፡

ኢቆንዮን ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ከአይሁድና ፡ ከአረሚ ፡ ምኵራብ ፡ ገብተው ፡

ወነገሩ ፡ ከመ ፡ ይነግሩ ፡ ዘልፈ ፡

ቀድሞ ፡ እንዳስተማሩ ፡ አስተማሩ ፡ ሐተ ታ ፡ አንድ ፡ ወገኑ ፡ የአረሚ ፡ አንድ ፡ ወገኑ ፡ የአይሁድ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ፈረቃ ፡ ቤት ። አንድም ፡ በፊት ፡ የአረሚ ፡ ሆኖ ፡ ኋላ ፡ የአይሁድ ፡ ሆኗል ፡

እስመ ፡ አምኑ ፡ ብዙኃን ፡ ጥቀ ፡ እምአይሁድ ፡ ወእ ምአረሚኒ ።

ከአይሁድም ፡ ከአረሚም ፡ ወገን ፡ እጅግ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ እስቲያምኑ ፡ ድረስ ፡ አስ ተማሩ ።

፪ ፤ ወቢጸ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ አበዩ ፡ ተበአሱ ፡ ም ስለ ፡ አሕዛብ ፡ ወምስለ ፡ ሐዋርያት ፡

ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ በወንጌል ፡ አናም ንም ፡ ያሉት ፡ ቢጽ፡ ሐሳውያን፡ ግን፡ ካ መኑ፡ከአሕዛብ፡ከሐዋርያት፡ጋራ፡ተጣሉ ፡

ወአጸዐርዋ ፡ ለነፍሶሙ ፡

ሰውነታቸውን ፡ በመከራው ፡ አስጨነ ቋት ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፵፭ ።

፫ ፤ ወነበሩ ፡ ጉንዱየ ፡ መዋዕለ ፡ እንዘ ፡ ይነግሩ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡

ሐዋርያትም ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክር ስቶስ ፡ ስሙ ፡ ሕይወት ፡ መድኃኒት ፡ እን ደ ፡ ሆነ ፡ እያስተማሩ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ኖሩ ፡

እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ያርኢ ፡ ስማዕተ ፡ ቃለ ፡ ጸጋሁ ፡

በለጋስነት ፡ የሠራት ፡ ወንጌልን ፡ በምስ ክር ፡ እያስረዳላቸው ፡

ወይገብር ፡ ተአምረ ፡ ወመንክረ ፡ በእደዊሆሙ ።

በነሱ ፡ ቃል ፡ በነሱ ፡ ሥልጣን ፡ ተአም ራት ፡ እያደረገላቸው ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፲፩ ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፬ ።

፬ ፤ ወተናፈቁ ፡ ኵሉ ፡ ሀገር ፡

ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ተለያዩ ፡

መንፈቆሙ ፡ መንገለ ፡ አይሁድ ፡

እኩሌቶቹ ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡



ወቦ ፡ እለሂ ፡ ኀበ ፡ ሐዋርያት ፡

እኩሌቶቹ ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡ ሆነው ፡ ተለያዩ ። አንድም ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ የ ሆኑ ፡ አሉ ። ወደ ፡ ሐዋርያትም ፡ የሆኑ ፡ አሉ ፡

፭ ፤ ወተበአሱ ፡ አይሁድ ፡ ወአረሚ ፡ ምስለ ፡ መላ እክቲሆሙ ፡

አይሁድና፡ አረሚም፡ ካለቆቻቸው፡ ጋራ ፡ ተከራከሩ ፡

ወአኀዙ ፡ ይጸአሉ ፡ ወይትዋገሩ ፡

ይጸአሉ፡ ስድብ፡ ጀመሩ ፡ ይጸልዑ ፡ ጠብ ፡ ጀመሩ ፡ ደንጊያም ፡ ተጣጣሉ ፡ ቍ ፡ ፲፱ ፡ ፪ ። ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

፮ ፤ ወርእዮሙ ፡ ሐዋርያት ፡

ሐዋርያትም ፡ ይህን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ሁነን ፡ የላይ ፡ ፈሪ ፡ የታች ፡ ፈሪ ፡ እያ ልን ፡ እናጣላለን ፡ ብለው ።

ጐዩ ፡ ውስተ ፡ አህጉረ ፡ ሊቃኦንያ ፡

ሊቃኦንያ ፡ ወደሚባል ፡ አገር ።

ወልስጥራን ፡ ወደርቤን ፡

ልስጥራን ፡ ደርቤን ፡ ወደሚባል ፡ አገር ።

ወውስተ ፡ አድያም ፡

ወደነዚህ ፡ አገሮች ፡ አውራጃ ፡ ሸሽተው ፡ ሄዱ ።

፯ ፤ ወመሀሩ ፡ በህየ ፡

በየደረሱበት ፡ አስተማሩ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።

፰ ፤ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ በሀገረ ፡ ልስጥራን ፡ ዘዕውስ ፡ እገሪሁ ፡ ከማሁ ፡ ተወልደ ፡ እምከርሠ ፡ እሙ ።

በልስጥራንም ፡ ከናቱ፡ ማኅፀን፡ ጀምሮ ፡ ልምሾ ፡ ሁኖ ፡ የተወለደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ወዳእሙ ፡ ይነብር ፡ ግሙራ ፡ ወእምአመ ፡ ኮነ ፡ ኢ ሖረ ፡

ተቀምጦ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፡ እንጅ ፡ ከተወ ለደ ፡ ጀምሮ ፡ ከቶ ፡ ቁሞ ፡ ሂዶ ፡ አያው ቅም ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፪ ።

፱ ፤ ወሰምዖ ፡ ለጳውሎስ ፡ እንዘ ፡ ይነግር ።

ጳውሎስን ፡ ሲያስተምር ፡ በሰማው ፡ ጊዜ፤

ወነጸሮ ፡ ጳውሎስ ፡

ጳውሎስም ፡ ነቅቶ ፡ እሱን ፡ ሲመለከት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ።

ወርእዮ ፡ ከመ ፡ ቦ ፡ ሃይማኖት ፡ ወየሐዩ ፡

አምኖ፡ እንዲድን፡ አውቆ፡ ማቴ ፡፱፡ ፳፰ ።

፲ ፤ ወይቤሎ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ፡ ለከ ፡ እብለከ፡ በስ ሙ ፡ ለኢየሱስ ።

በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አምነህ ።

ተንሥእ ፡ ወቁም ፡ በእገሪከ ፡

በግርህ ፡ ቀንተህ ፡ ቁም ፡ እልሃለሁ፡ ብሎ፡ በታላቅ ፡ ቃል፡ ነገረው ፡ ሐተታ፡ በምን ፡ ይቆም ፡ ኑሯል ፡ ቢሉ ፡ ጥግ ፡ መቋሚያ ፡ ሳይሻ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ወሶቤሃ ፡ ተንሥአ ፡ ወሖረ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡ ሄደ ።

፲፩ ፤ ወርእዮሙ ፡ አሕዛብ ፡ ዘገብረ ፡ ጳውሎስ ፡

አሕዛብም ፡ ጳውሎስ ፡ ያደረገውን ፡ ተአ ምራት ፡ ባዩ፡ ጊዜ ።

ከልሑ ፡ በነገረ ፡ ሊቃኦንስጦ ፡

ሊቃኦንስጦ ፡ በሚባል ፡ ቋንቋ ። አንድም፡ ሊቃኦንስጦ ፡ በሚባል ፡ ሰው ፡ ቃል ፡ ጮኸው ፡ ተናገሩ ።

ወይቤሉ፡አማልክት፡ሰብአ፡ተመሰሉ፡ወወረዱ፡ኀቤነ፡

አማልክት ፡ ሰው ፡ መስለው ፡ ወደኛ ፡ መጥተዋል ፡ ብለው ፡ ም ፡ ፳፰ ፡ ፮ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪ ፤ ወሰመይዎ ፡ ለበርናባስ ፡ ድያ ፡

በርናባስን ፡ ድያ ፡ አሉት ፡ መሽተሪ ፡
ብሎ ፡ ሊቁ ፡ ያነበዋል ።

ወለጳውሎስ ፡ ሄርሜን ፡

ጳውሎስንም ፡ ሄርሜን ፡ አሉት ፡ ዙሐል ፡
ብሎ ፡ ሊቁ ፡ ያነበዋል ፡

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ትምህርቱ ፡

የትምህርቱ ፡ አበጋዝ ፡ እሱ ፡ ነውና ።

፲፫ ፤ ወአምጽኡ ፡ ማሬ ፡ ዘድያስ ፡

ካህን ፡ ጣዖት ፡ አመጡለት ፡

ዘሀሎ ፡ ቅድመ ፡ ሀገር ፡

እንደፊት ፡ አቦ ፡ ባለ ፡ አገር ፡ ያለ ። አን
ድም ፡ የሀገር ፡ ቀንድ ፡ የሚሆን ። አን
ድም ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡
አረጋዊ ፡ ነውና ፡ አምጽኡ ፡ ቅድመ ፡
ሀገር ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ አመ
ጡለት ፡

ምስለ ፡ አልህምት ፡ ወመሣውዕ ፡ ኀበ ፡ አንቀጸ ፡ ዐጸ
ደ ፡ ማኅደሮሙ ፡ ምስለ ፡ ሕዝቢሆሙ ።

የሚሠውትን ፡ ላም ፡ ነድተው ፡ ላሙን ፡
የሚያርዱበትን ፡ ወቅለምት ፡ ደሙን ፡
የሚቀበሉበትን ፡ ብርት ፡ ሥጋውን ፡ የሚ
ቀቅሉበትን ፡ ድስት ፡ ይዘው ፡ ሐዋርያት፡
ወደሚያድሩበት ፡ ቤት ፡ በር ፡ ሕዝቡን ፡
ሰብስበው ፡ መጡ ፡

ወፈቀዱ ፡ ከመ ፡ ይሡዑ ፡ ሎሙ ፡

ሊሠውላቸው ፡ ወደው ፡ መጡ ።

፲፬ ፤ ወሰሚያሙ ፡ ሐዋርያት ፡ በርናባስ ፡ ወጳው
ሎስ ፡ ሰጠጡ ፡ አልባሲሆሙ ፡

ጳውሎስና ፡ በርናባስም ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡
ጊዜ ፡ ልብሳቸውን ፡ ቀደዱ ፡ ትእምርተ ፡
ኀዘን ፡ ነው ። አንድም ፡ አሪት ፡ ሊቀ ፡
ካህናቱ ፡ ልብሱን ፡ የቀደደ ፡ ጽሕሙን ፡
የላጨ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ፡
ትላለች ፡ ይህ ፡ ግን ፡ ጥቅም ፡ ያለበት ፡
ነውና ።

ወሖሩ ፡ ኀበ ፡ አሕዛብ ፡

ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ሂደው ፡

፲፭ ፤ ወከልሑ ፡ ሎሙ ፡ ወይቤልዎሙ ፡ አንትሙ ፡
ሰብእ ፡ ምንትኑ ፡ ዝ ፡ ነገር ፡

እየጮሁ ፡ እናንት ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡ ነገር ፡
ምንድን ፡ ነው ፡

አኮኑ ፡ ከማክሙ ፡ ሰብእ ፡ ንሕነ ፡ ዘንመውት ፡

እንደናንት ፡ ያለን ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡
ሰዎች ፡ አይደለንምን ።

ወንሜህረክሙ ፡ ከመ ፡ ትኅድጉ ፡ ዘንተ ፡ ከንቶ ፡ ወት
ትመየጡ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ።

ይህን ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ትታችሁ ፡ እግዚአ
ብሔርን ፡ ወደ ፡ ማምለክ ፡ ትመለሱ ፡
ዘንድ ፡ የምናስተምራችሁ፡ አይደለንምን፡

ዘገብረ ፡ ሰማየ ፡ ወምድረ ፡

ሰማይን ፡ ምድርን ፡ የፈጠረ ፡

ወባሕረ ፡

ባሕሩን ፡ የፈጠረ ፡

ወኵሎ ፡ ዘውስቴቶሙ ፡

በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ፀሓይ ፡ ጨረቃን ፡ ከዋ
ክብትን ፡ መላእክትን ፡ በምድር ፡ ያሉ ፡
ደቂቀ ፡ አዳምን ፡ እንስሳት ፡ አራዊትን ፡
ዕፀው ፡ አዕባንን ። በባሕር ፡ ያሉ ፡ ዓሣ ፡
አንበሪን ፡ አዞ ፡ ጉማሬን ፡ የፈጠረ ፡
ም ፡ ፲ ፡ ፳፮ ።

፲፮ ፤ ወኀደጎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ይሖሩ ፡
በግዕዞሙ ፡ በዘቀዲሙ ፡ መዋዕል ፡

ለአሕዛብ ፡ በዘቀዲሙ ፡ መዋዕል ፡ ይሑ
ሩ፡ በግዕዞሙ፡ በዘቀዲሙ ፡ (ግጥም) ፡ በቀ
ድሞ ፡ ዘመን ፡ [illegible] ፡ አሕዛብን ፡ በቀ



ደመ ፡ ዕውቀታቸው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ በተ
ዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፴ ።

፲፯ ፤ እንዘ ፡ ኢየኀድግ ፡ ርእሶ ፡ ዘእንበለ ፡ ሰማዕት ፡

ጌትነቱን ፡ ያለ ፡ ምስክር ፡ ሳይተው ፡

ወይገብር ፡ ሠናይቶ ፡

በጎ ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ አለ ፡ የቸርነቱን ፡
ሥራ ፡ እየሠራ ፡

ወይሁብ ፡ እምሰማይ ፡ ዝናመ ፡

ከሰማይ ፡ ዝናም ፡ እያዘነመ ፡ ጠል ፡ ለመ
ከር ፡ እየሰጠ ፡

ወያከርም ፡ በበዓመት ፡

በጋንና፡ክረምትን፡መዓልትንና፡ ሌሊትን፡
እያፈራረቀ ።

ወያፈሪ ፡

ፍሬ ፡ እያፈራ ።

ወያሠምር ፡ ከመ ፡ ያጽግበነ ፡ ወያስተፍሥሕ ፡ ልበነ ፡

እኛን ፡ ለመመገብ ፡ ልቡናችንን ፡ ደስ ፡
ለማሰኘት ፡ ፍሬ ፡ እያፈራ ፡ እያበዛ ፡ ጌት
ነቱን ፡ ያለ ፡ ምስክር ፡ ሳይተው ፡ የተዋ
ቸው ፡ አሕዛብ ፡ ያመልኩት ፡ የነበረ ፡
ጣዖትን ፡ ትታችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡
ወደ ፡ ማምለክ ፡ ትመለሱ ፡ ዘንድ ፡ የም
ናስተምራችሁ ፡ አይደለምን ፡ መዝ ፡
፻፵፯ ፡ ፰ ። ኤር ፡ ፭ ፡ ፳፬ ።

፲፰ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎሙ ፡ በዕፁብ ፡ አኀደግዎሙ ፡
ለአሕዛብ ፡ ኢይሡዑ ፡ ሎሙ ፡

ይህን ፡ ተናግረው ፡ እንዳይሠውላቸው ፡
አሕዛብን ፡ በጭንቅ ፡ አስተውዋቸው ።

፲፱ ፤ ወእንዘ ፡ እሙንቱ ፡ ይሜህሩ ፡ በህየ ፡ መጽኡ፡
አይሁድ ፡ እምአንጾኪያ ፡ ወኢቆንያ ።

በልስጥራን ፡ በደርቤን ፡ በሊቃኦንያ ፡
ሳሉ ፡ ሲያስተምሩ ፡ አይሁድ ፡ ከአንጾ
ኪያ ፡ ከኢቆንዮ ፡ መጥተው ፡
ወየውህዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ከመ ፡ ያሕሥሙ ፡ ልቦ
ሙ ፡ ላዕሌሆሙ ፡

ልባቸውን ፡ አጽንተው ፡ ይጣሏቸው ፡
ዘንድ ፡ አሕዛብን ፡ አባበሏቸው ፡

ወወገርዎ ፡ ለጳውሎስ ፡ ወሰሐብዎ ፡ ወአውፅእዎ ፡
አፍአ ፡ እምሀገር ፡

ጳውሎስን ፡ እየገጐተቱ ፡ ከከተማ ፡ በአ
ፍአ ፡ አውጥተው ፡ ድንጋይ ፡ ጣሉበት ፡

ወመሰሎሙ ፡ ዘሞተ ፡ ወኦድዎ ፡ አርጻኢሁ ፡

አይሁድ ፡ የሞተ ፡ መስሏቸው ፡ ትተውት፡
ሄዱ ። አንድም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ የሞ
ተ ፡ መስሏቸው ፡ ሊቀብሩት ፡ ቀረቡ ፡
፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭ ። ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

፳ ፤ ወተንሥአ ፡ ወቦአ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ሀገረ ፡

ወዶ ፡ ጳውሎስ ፡ ይህን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡
ብሎት ፡ ተነሥቶ ፡ አሕዛብን ፡ በኋላ ፡
በኋላ ፡ ተከትሏቸው ። አንድም ፡ ደቀ ፡
መዛሙርቱን፡አስከትሎ፡ ወደ፡ ሀገር፡ ገባ ፡

ወበሳኒታ ፡ ሖረ ፡ ምስለ ፡ በርናባስ ፡ ሀገረ ፡ ደርቤን ፡

በነጋው ፡ ከበርናባስ ፡ ጋራ ፡ ደርቤን ፡
ወደሚባል ፡ አገር ፡ ሄደ ።

፳፩ ፤ ወመሐሩ ፡ በይእቲ ፡ ሀገር ፡

በርናባስና ፡ ጳውሎስም ፡ በዚያች ፡ አገር ፡
አስተማሩ ፡

ወአብኡ ፡ ብዙኃነ ፡

ብዙ ፡ ምእመናንን ፡ አሳመኑ ፡ አጠመቁ ፡

ወገብኡ፡ሀገረ፡ ልስጥራን፡ ወኢቆንዮን፡ ወአንጾኪያ ፡

ብዙ ፡ ምእመናንን ፡ ካስተማሩ ፡ ካጠ
መቁ ፡ በኋላ ፡ ልስጥራን ፡ ኢቆንዮን ፡
አንጾኪያ ፡ ወደሚባል ፡ አገር ፡ ተመለሱ።

፳፪ ፤ ወአጽንዕዎሙ ፡ ነፍሶሙ ፡ ለሕዝብ ፡

ሕዝቡምን ፡ መክረው ፡ አስተምረው ፡ በሃ
ይማኖት ፡ አጸኗቸው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወመሀርዎሙ ፡ ያጥብዑ ፡ በሃይማኖት ፡

በሃይማኖት ፡ ጸንተው ፡ መከራውን ፡ ለመ ቀበል ፡ ይጨክኑ፡ ዘንድ ፡ ጨክኑ፡ ብለው፡ አስተማሯቸው ፡

እስመ ፡ በብዙኅ ፡ ሕማም ፡ ሀለወነ ፡ ንባእ ፡ ለመንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ።

በብዙ ፡ ጻር፡ መንግሥተ፡ ሰማይን ፡ እንገ ባታለንና ። አንድም ፡ በብዙ ፡ ጻር ፡ መንግ ግሥተ ፡ ሰማይን ፡ እንገባታለንና ፡ ይላል፡ ሉቃስ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፳፫ ። ፩ ፡ ተሰ ፡ ፫፡፫ ።

፳፫ ፤ ወሢሞሙ ፡ ቀሲሳነ ፡ ላዕለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡

ለምእመናንም ፡ ቀሳውስትን ፡ ሾሙላ ቸው ፡

ወጸለዩ ፡ ወጾሙ ፡

የመሰነባበቻ ፡ ጾም ፡ ጸሎት ፡ አደረጉ ፡

ወአማኅፀንዎሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘኪያሁ ፡ ተአመኑ ፡

ያመናችሁበት ፡ እግዚአብሔር ፡ አይለያ ችሁ ፡ ብለው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አደራ ፡ ሰጧቸው ። አንድም ፡ ያመናችሁበት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አትካዱ ፡ ብለው ፡ አደ ራ ፡ አሏቸው ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፫ ።

፳፬ ፤ ወኀሊፎሙ ፡ እምጲስድያ ፡ ወበጽሑ ፡ ጵንፍልያ ፡

ከጲስድያ ፡ ወጥተው ፡ ጵንፍልያ ፡ ደረሱ።

፳፭ ፤ ወነገሩ ፡ ቃሎሙ ፡ በሀገረ ፡ ጴርጌን ።

ጴርጌን ፡ በምትባል ፡ አገር ፡ ወንጌልን ፡ አስተማሩ ፡

ወወረዱ ፡ አጣልያ ፡

ከዚያም ፡ ወደ ፡ አጣልያ ፡ ሄዱ ።

፳፮ ፤ ወእምህየ ፡ ነገዱ ፡ አንጾኪያ ፡ በኀበ ፡ ተውህበ ፡ ሎሙ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ግብር ፡ ዘይገብሩ ።

ከአጣልያም ፡ ወጥተው ፡ ስለሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ተሰጠ ችባቸው ፡ አገር ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ሄዱ ፡ ማለት ፡ ፍልጥዎሙ ፡ ሊተ ፡ ለሳውል ፡ ወለበርናባስ ፡ ወደ ፡ ተባሉበት ፡ አገር ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ሄዱ ። አንድም ፡ ወተ ሰምዩ ፡ አርድእት ፡ ክርስቲያነ ፡ በአንጾ ኪያ፡ ቀዲሙ፡ እንዲል፡ ክርስቲያን፡ ወደ፡ ተባሉበት ፡ አገር፡ ሄዱ ፡ ም ፡ ፲፫፡ ፩ ፡ ፪ ።

፳፯ ፤ ወበጺሖሙ ፡ አስተጋብኡ ፡ ኵሎ ፡ ሕዝበ ፡ ወነገሩ ፡ ኵሎ ፡ ዘገብረ ፡ ሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡

ከዚያም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ፡ ሰብስበው ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአሕዛብ ፡ ያደረገላቸውን ፡ ትምህርት ፡ ተአምራት ፡ ነገሯቸው ፡

ወዘከመ ፡ አርኀወ ፡ ሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ አናቅጸ፡ ሃይማኖት ፡ ለአሕዛብ ።

ለአሕዛብ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሃይማኖትን፡ ምስጢር ፡ እንደ ፡ ገለጠላቸው ፡ ነገሯ ቸው ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፱ ።

፳፰ ፤ ወነበሩ ፡ ጉንዱየ ፡ መዋዕለ ፡ ምስለ ፡ አርድእት ፡

በዚያም ፡ ከምእመናን ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ቀን፡ ኖሩ ።



## ምዕራፍ ፡ ፲፭ ።

፩ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ ወረዱ ፡ እምብሔረ ፡ ይሁዳ ፡ ወመ ሀርዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡

ከብሔረ ፡ ይሁዳ ፡ ሂደው ፡ ለሕዝቡ ፡ ያስ ተማሩ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያንም ፡ አሉ ፡

ወይቤልዎሙ ፡ እምከመ ፡ ኢትትገዘሩ ፡ በሕገ ፡ ሙሴ ፡ ኢትክሉ ፡ ሐይወ ።

በሙሴ ፡ ሥርዐት ፡ ካልተገዘራችሁ ፡ መ ዳን ፡ አይቻላችሁም ፡ ብለው ፡ ገላት ፡ ፭ ፡ ፪ ።

፪ ፤ ወተሀውኩ ፡ ሕዝብ ፡ ፈድፋደ ፡

ሕዝቡም ፡ እጅግ ፡ ታወኩ ፡ በአምሳ ፡ ዓመት ፡ ግዝረት ፡ ብለው ። አንድም ፡ ት ምህርት ፡ ተከፋፍሎብናል ፡ ብለው ፡ ታወኩ ፡

ወተዋቀሥዎሙ ፡ ለጳውሎስ ፡ ወለበርናባስ ፡

ጳውሎስንና ፡ በርናባስን ፡ ተከራከሯቸው ፡ ሐተታ ፡ ወንጌል ፡ እንበለ ፡ አሪት ፡ ጥም ቀት ፡ እንበለ ፡ ግዝረት ፡ አትረባም ፡ አት ጠቅምም ፡ ብለው ፡

ወመከሩ ፡ ከመ ፡ ይፈንውዎሙ ፡ ለጳውሎስ ፡ ወለበር ናባስ ፡ ወለቢጾሙኒ ፡ ኀበ ፡ ሐዋርያት ፡ ወቀሲሳን ፡ እለ ፡በኢየሩሳሌም ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ነገር ።

ምእመናንም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ በኢየሩ ሳሌም ፡ ካሉ ፡ ከቀሳውስት ፡ ከሐዋርያት ፡ ዘንድ ፡ ጳውሎስንና ፡ በርናባስን ፡ ከባል ንጀሮቻቸው ፡ ጋራ ፡ አያይዘው ፡ ይሰዷ ቸው ፡ ዘንድ ፡ መከሩ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፴ ። ገላት ፡ ፪ ፡ ፩ ።

፫ ፤ ወተፈኒዎሙ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡

ጳውሎስና ፡ በርናባስም ፡ ከምእመናን ፡ ተልከው ። አንድም ፡ ተፋኒዎሙ ፡ ከም እመናን ፡ ተሰናብተው ፡ ሄዱ ፡

በጽሑ ፡ ፊንቂ ፡ ወሰማርያ ፡ ወነገርዎሙ ፡ ዘከመ ፡ ተመይጡ ፡ አሕዛብ ።

ፊንቂ ፡ ሰማርያ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ፡ አሕዛብ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እ ግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፡ ነገሯ ቸው ፡

ወገብሩ ፡ ዐቢየ ፡ ፍሥሓ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ ቢጾሙ ፡

ከምእመናን ፡ ጋራ ፡ ፍጹም ፡ ተድላ ፡ ደስ ታን ፡ አደረጉ ።

፬ ፤ ክፍል፡ ፳፱ ። ወበጺሖሙ ፡ ኢየሩሳሌም፡ ተቀበ ልዎሙ፡ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወሐዋርያት ፡ ወቀሲሳን ፡

ኢየሩሳሌም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ሐዋርያ ትና ፡ ቀሳውስት ፡ ተቀበሏቸው ፡

ወዜነውዎሙ ፡ ኵሎ ፡ ዘከመ ፡ ገብረ ፡ ሎሙ ፡ እግዚ አብሔር ፡ በውስተ ፡ አሕዛብ ።

እግዚአብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ለነሱ፡ ያደረገላቸውን ፡ ትምህርት ፡ ተአምራት ፡ ነገሯቸው ። አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአሕዛብ ፡ ያደረገላቸውን ፡ ትምህርት ፡ ተአምራት ፡ ነገሯቸው ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ፳፯ ።

፭ ፤ ወቦ፡ እለ፡ ተንሥኡ፡ እምሕዝበ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ቢጽ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ ወይቤልዎሙ ፡ ርቱዕ ፡ ይት ገዘሩ ፡

ከፈሪሳውያን ፡ ወገን ፡ አመን ፡ ያሉት ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ግን ፡ ተነሥተው ፡ ሊገዘሩ ፡ ይገባል ፡

ወነአዝዞሙ ፡ ይዕቀቡ ፡ ሕገ ፡ ሙሴ ። ፡

ነአዝዞሙ ፡ ሕገ ፡ ሙሴ ፡ ይዕቀቡ ፡ ሕገ ፡ ሙሴ ፡ ግጥም ፡ የሙሴን ፡ ሥርዐት ፡ ይጠ ብቁ ፡ ዘንድ ፡ የሙሴን ፡ ሥርዐት ፡ ልናዝ ዛቸው ፡ ይገባል ፡ ያሉ ፡ አሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

፮ ፤ ወአንገለጉ ፡ ሐዋርያት ፡ ወቀሲሳን ፡ ከመ ፡ ይርአዩ ፡ ዘይገብሩ ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ ነገር ፡

ሐዋርያትና ፡ ቀሳውስትም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የሚሠሩትን ፡ ሥርዐት ፡ ይበይኑ ፡ ዘንድ ፡ ጉባኤ ፡ አደረጉ ።

፯ ፤ ወእምድኅረ፡ተዋቀሥዎሙ፡ተንሥአ፡ ጴጥሮስ፡

ጳውሎስንና ፡ በርናባስን ፡ ከተከራከሯቸው ፡ በኋላ ፡ ጴጥሮስ ፡ ተነሥቶ ፡

ወይቤሎሙ ፡ ስምዑ ፡ አኀዊነ ፡

ወንድሞቻችን ፡ ስሙ ፡

ለሊከሙ ፡ ተአምሩ ፡ ከመ፡ እምትካት ፡ ኀረየኒ ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔር ፡ ከጥንተ ፡ ስብከት ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ መረጠኝ ፡ ታውቃላችሁ ፡

ከመ ፡ አስምዖሙ ፡ ቃለ ፡ አፉየ ፡ ለአሕዛብ ፡

በቃል ፡ ጠይቄው ፡ የነገረኝን ፡ ከራሴ ፡ አንቅቼ ፡ ለአሕዛብ፡ እነግራቸው ፡ ዘንድ ፡

ወትምህርተ ፡ ወንጌሉ ፡ ወይእመኑ ፡

ሊያምኑም፡ በወንጌል፡ ያስተማረኝን፡ ትምህርት ፡ ለአሕዛብ ፡ እነግራቸው፡ ዘንድ፡ እንደ፡መረጠኝ፡ታውቃላችሁ፡ ም፡ ፲፩፡ ፲፰።

፰ ፤ ወእግዚአብሔር ፡ ማእመረ ፡ ልብ ፡ ሰማዕተ ፡ ኮኖሙ ፡

ልቡና ፡ ያሰበውን ፡ ኅላሊት ፡ ያመላለሰውን ፡ የሚያውቅ ፡ እግዚአብሔርም ፡ መሰከረላቸው ፡ እንደ ፡ መሰከረላቸው ፡ ታውቃላችሁ ።

ወወሀቦሙ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ ከማነ ።

እንደኛ ፡ ልጅነትን ፡ ሰጣቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አሳደረባቸው ።

፱ ፤ ወኢፈለጠሙ ፡ እምኔነ ፡ አንጺሐ ፡ ልቦሙ ፡ በሃይማኖት ፡

ልቡናቸውን ፡ በሃይማኖት ፡ አጽንቶ ፡ ከኛ ፡ አለያቸውም ፡ ም ፡ ፲ ፡ ፴፬ ።

፲ ፤ ወይእዜኒ ፡ ኢታመክርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

አሁንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አትፈታተኑት ፡

ወኢታስከምዎሙ ፡ አርዑተ ፡ ዲበ ፡ ክሳውዲሆሙ ፡ ለአሕዛብ ፡

ጽኑ ፡ ሥርዐት ፡ ሠርታችሁ ፡ አሕዛብን ፡ በመትከፈ ፡ ልቡናችሁ ፡ ጠብቁ ፡ አትበሏቸው ፡

ዘኢክህልነ ፡ ጸዊሮቶ ፡ ንሕነ ፡ ወኢአበዊነ ፡

እኛ ፡ ልንፈጽመው ፡ የማይቻለንን ፡ አባቶቻችንም ፡ ሊፈጽሙት ፡ ያልተቻላቸውን ፡ ገላት ፡ ፫ ፡ ፲ ። ፭ ፡ ፩ ።

፲፩ ፤ ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ ንሕነ ፡ በጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ንትአመን ፡

በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ቸርነት ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቸርነት ፡ እንድንን ፡ ዘንድ ፡ እናምናለን ፡ እንጅ ፡ እንመን ፡ እንጅ ፡

ወከማሁ ፡ እሙንቱሂ ፡

እኛ ፡ እንደ ፡ ዳንን ፡ እነሱም ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ፡ ኤፌ ፡ ፪ ፡ ፬—፲ ።

፲፪ ፤ ወሶቤሃ ፡ አርመሙ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ወአፅምእዎሙ ፡ ለጳውሎስ ፡ ወለበርናባስ ፡

ያንጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ጳውሎስንና ፡ በርናባስን ፡ ጸጥ ፡ ብለው ፡ አደመጧቸው ፡

እንዘ ፡ ይነግሩ ፡ ኵሎ ፡ ዘገብረ ፡ ሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተአምረ ፡ ወመንክረ ፡ በውስተ ፡ አሕዛብ ፡

እግዚአብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ለነሱ ፡ ያደረገላቸውን ፡ ትምህርት ፡ ተአምራት ፡ ሲነግሯቸው ። አንድም ፡ ለአሕዛብ ፡ ያደረገላቸውን ፡ ትምህርት ፡ ተአምራት ፡ ሲነግሯቸው ፡ ጸጥ ፡ ብለው ፡ አደመጧቸው ።



፲፫ ፤ ክፍል ፡ ፴ ። ወእምድኅረ ፡ አርመሙ ፡ ተሠጥወ ፡ ያዕቆብ ፡

ጳውሎስና ፡ በርናባስም ፡ ተናግረው ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ያዕቆብ ፡ ተናገረ ፡ (ጥቅ)፡ ተሠጥወ ፡ ዲሙቅላስ ፡ እንዲል ፡

ወይቤ ፡ ስምዑ ፡ አኀዊነ ፡

ወንድሞቻችን ፡ ስሙ ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፲፰ ።

፲፬ ፤ ስምዖንሂ ፡ ነገረ ፡ ዘከመ ፡ አቅደመ ፡ ተሣሀሎ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአሕዛብ ፡

ስምዖንሂ ፡ ቢል ፡ ስምዖን ፡ አረጋዊም ፡ አሕዛብን ፡ ይቅር ፡ እንዳላቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ተናግሯል ፡ ከመ ፡ ትክሥት ፡ ብርሃነ ፡ ለአሕዛብ ፡ ብሎ ። አንድም ፡ ስምዖን ኬ ፡ ይላል ፡ ስምዖን ፡ ኬፋም ፡ አሕዛብን ፡ ይቅር ፡ እንዳላቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ተናግሯል ፡ ወወሀቦሙ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ ከማነ ፡ ወኢፈለጠሙ ፡ እምኔነ ፡ አንጺሐ፡ ልቦሙ ፡ በሃይማኖት ፡ ብሎ ፡

ወነሥአ ፡ ሕዝበ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ለስሙ ፡

በስሙ ፡ ለመጠራት ፡ አለ ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመባል ፡ ከነሱ ፡ ወገን ፡ ምእመናንን ፡ እንደ ፡ መረጠ ፡ አስቀድሞ ፡ ተናግሯል ።

፲፭ ፤ ወየኀብሩ ፡ ቃለ ፡ ነቢያት ፡ በዝንቱ ፡ በከመ ፡ ይብል ፡ መጽሐፍ ፡

ይህን ፡ ነገር ፡ በመናገር ፡ ነቢያት ፡ አንድ፡ ሆኑ ፡ ወየኀብር ፡ ቃለ ፡ ነቢያት ፡ በዝንቱ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በመናገር ፡ የነቢያት ፡ ቃል፡ አንድ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ።

፲፮ ፤ እምድኅረ ፡ ዝ ፡ አገብእ ፡ ወአሐንጽ ፡ ለቤተ ፡ ዳዊት ፡ ዘወድቀት ፡

ተፈታ ፡ የነበረች ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከሰባ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ መልሼ ፡ አቀናታለሁ ፡

ወእነድቅ ፡ መዝበራ ፡

የፈረሰውንም ፡ እሠራለሁ ፡ ዓሞ ፡ ፱ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ።

፲፯ ፤ ከመ ፡ ይኅሥሥዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡

ከእምቢታ ፡ የቀሩ ፡ እስራኤል ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮ ፡ ይሹት ፡ ዘንድ ፡

ወኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ ተሰምየ ፡ ዲቤሆሙ ፡ ስምየ ፡

ስሜ ፡ የተጠራባቸው ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባሉ ፡ አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልኮት ፡ ይሹት ፡ ዘንድ ።

፲፰ ፤ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘገብረ ፡ ዘንተ ፡ ዘኢይትዐወቅ ፡ ዘእምፍጥረተ ፡ ዓለም ፡

እግዚአብሔርና ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ጴዋዌ ፡ ሥጋውን ፡ ሚጠተ ፡ ሥጋውን ፡ ያደረገ ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ታይቶ ፡ የማያውቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ የኀብሩ፡ ቃለ፡ ነቢያት፡ በዝንቱ ፡ ላለው ። አንድም፡ ወእምድኅረ፡ዝ፡ካምስት ፡ ሺሕ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በአዳም ፡ የሄደችውን ፡ ልጅነት ፡ እመልሳታለሁ ፡ (ወእነድቅ ፡ መዝበራ) ፡ ገነት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ እንድትሰጥ ፡ አደርጋለሁ ፡ (ከመ ፡ ይኅሥሥዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው) ፡ አንድም ፡ ከእንቢታ ፡ ከክህደት ፡ የቀሩ ፡ እስራኤል ፡ እግዚአብሔርን ፡ በወንጌል ፡ በሃይማኖት ፡ ይሹት ፡ ዘንድ ፡ (ወኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ ተሰምየ ፡ ዲቤሆሙ ፡ ስምየ) ፡ በወልድ ፡ ውሉድ ፡ በክርስቶስ ፡ ክርስቲያን ፡ የተባሉ ፡ አሕዛብ

www.ethiopianorthodox.org

ም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በወንጌል ፡ በሃይማኖት ፡ ይሹት ፡ ዘንድ ፡ (ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘገብረ ፡ ዘንተ ፡ ዘኢይትዐወቅ ፡ ዘእምፍጥረተ ፡ ዓለም) ፡ ጼዋዌ ፡ ነፍሱን ፡ ሚጠተ፡ ነፍሱን፡ ያደረገ፡ ዓለም፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ታይቶ ፡ የማያውቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ የኀብሩ ፡ ቃለ ፡ ነቢያት ፡ በዝንቱ ፡ ላለው ።

፲፱ ፤ ወይእዜኒ ፡ እብለክሙ ፡ ኢታክብዱ ፡ ላዕለ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ ተመይጡ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

አሁንም ፡ እምነው ፡ ከአምልኮ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በተመለሱ ፡ አሕዛብ ፡ ሥርዐት፡ አታጽኑባቸው፡ እላችኋለሁ ፡

፳ ፤ ዳዕሙ ፡ አዝዝዎሙ ፡ ይርሐቁ ፡ እምዘ ፡ ይዘብሑ ፡ ለአማልክት ።

ለጣዖት ፡ መሥዋዕት ፡ ከመሠዋት ፡ ይከለከሉ ፡ ዘንድ ፡ አዝዟቸው ፡ እንጂ ።

ወእማውታ ፡

ሙቶ ፡ የተገኘውን ።

ወደም ፡

ደም ፡ ከመብላት ፡ ይከለከሉ ፡ ዘንድ ፡ ሐተታ ፡ ደሙ ፡ ሲረጋ ፡ አንፍረው ፡ ቆልተው ፡ ይበሉታልና ።

ወእምዝሙት ፡

ከዝሙት ፡ ይከለከሉ ፡ ዘንድ ።

ወዘይጸልኡ ፡ ለርእሶሙ ፡ ኢይግበሩ ፡ ዲበ ፡ ቢጾሙ ፡

ለራሳቸው ፡ የሚጠሉትን ፡ በባልንጀሮቻቸው፡ እንዳያደርጉ፡ ይከለከሉ፡ ዘንድ፡ እዘዟቸው፡እንጅ፡ ዘፍጥ፡ ፱፡፬።ዘሌዋ፡፫፡፲፯።

፳፩ ፤ ወሙሴሂ ፡ ቦ፡እምቀዲሙ ፡ ዘይሰብክ፡ሎሙ ፡ በበአህጉር ፡

ሙሴም ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በየሀገሩ ። አንድም ፡ በየአንቀጹ ፡ የሚያስተምራቸው ፡ ይህን ፡ ነበር ፡ይህን፡ ያስተምራቸው፡ ነበር ፡ የሚያስተምራቸው ፡ ሙሴ ፡ ነበር።

ወያነብብዎ ፡ በመኳርብት ፡ በኵሉ ፡ ሰናብት ፡

ቅዳም ፡ ቅዳም ፡ በምኵራብ ፡ ይመለከቱት ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፲፭ ።

፳፪ ፤ ወእምዝ ፡ ኀብሩ ፡ ሐዋርያት ፡ ወቀሲሳን ፡ ወኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ከመ ፡ ይኅረዩ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ዕደወ ፡ ዘይፌንዉ ፡ አንጾኪያ ፡ ምስለ ፡ ጳውሎስ ፡ ወበርናባስ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሐዋርያትና ፡ ቀሳውስት ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ከጳውሎስና ፡ ከበርናባስ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ የሚሰዷቸውን ፡ ሰዎች ፡ ከነሱ ፡ ወገን ፡ ይመርጡ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ።

ወኀረዩ ፡ ይሁዳሃ ፡ ዘተሰምየ ፡ በርስያን ፡ ወሲላስሃ ፡ ዕደወ ፡ ሊቃውንተ ፡ በውስተ ፡ ቢጾሙ ፡

አንድ ፡ ሆነውም ፡ ከወገኖቻቸው፡ ይልቅ፡ የተማሩ ፡በወገኖቻቸው ፡ ዘንድ ፡ የከበሩ፡ ሲላስንና፡በርስያን ፡ የተባለ ፡ ይሁዳን ፡ መረጡ ።

፳፫ ፤ ወጸሐፉ ፡ በእደዊሆሙ ፡ መልእክተ ፡ እንተ ፡ ትብል ፡ ከመዝ ፡

በጃቸውም፡እንዲህ፡ የምትል፡ ክታብ፡ጻፉ።

እምልኡካን ፡ ወቀሲሳን ፡

ከሐዋርያት ፡ ከቀሳውስት ፡ የተላከች ፡ ክታብ ።

ለአኀው ፡ ለእለ ፡ በአንጾኪያ ፡ ወሶርያ ፡ ወቂልቅያ ፡ አኀዊነ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ እምውስተ ፡ አሕዛብ ፡

ከአሕዛብ ፡ ወገን ፡ ላመኑ ፡ በአንጾኪያ ፡ በሶርያ፡ በቂልቅያ ፡ ላሉ ፡ ለወንድሞቻችን ፡ ትድረስ ።

ሰላም ፡ ለክሙ ፡

ቸር ፡ አላችሁ [illegible]



ወትፍሥሕት ፡

ደስታ ፡ ይደረግላችሁ ፡ አለ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ።

፳፬ ፤ እስመ ፡ ሰማዕነ ፡ ከመቦ ፡ እለ ፡ ወፅኡ ፡ እምኔነ ፡ ወሆክዋ ፡ ለነፍስክሙ ፡ በነገር ፡

ከኛ ፡ ተለይተው ፡ ሂደው ።

እንዘ ፡ ይብሉክሙ ፡ ተገዘሩ ፡

ተገዘሩ ።

ወዕቀቡ ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡

የኦሪትን ፡ ሥርዐት ፡ ጠብቁ ፡ እያሉ ፡ ሰውነታችሁን ፡ በነገር ፡ ያስጨነቋት ፡ ሰዎች፡ እንዳሉ ፡ ሰምተናልና ።

ዕደው ፡ እለ ፡ ኢአዘዝናሆሙ ፡ ወኢበአሐቲኒ ፡ እምዝንቱ ፡ ነገር ፡ ዘይቤሉክሙ ፡

ከዚህ ፡ ከነገሯችሁ ፡ ነገር ፡ ባንዱ ፡ ስንኳ፡ ያላዘዝናቸው ፡ ሰዎች ፡ እንዳሉ ፡ ሰምተናልና ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፴ ። ገላት ፡ ፪ ፡ ፬ ።

፳፭ ፤ ወርኢነ ፡ እምድኅረ ፡ ተጋባእነ ፡ ኵልነ ፡ በአሐዱ ፡ ምክር ፡

ጉባኤ ፡ካደረግነ ፡ በኋላ ፡ እንዳንድ ፡ ልብ፡ መካሪ ፡እንዳንድ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ሁነን ፡ በየነ ።

ወኀቢረነ ፡ ኀረይነ ፡ ዕደወ ፡ ዘንፌኑ ፡ ኀቤክሙ ፡ ምስለ ፡ አኀዊነ ፡ በርናባስ ፡ ወጳውሎስ ።

አንድ ፡ ሁነንም ፡ ከወንድሞቻችን ፡ ከጳውሎስና ፡ ከበርናባስ ፡ ጋራ ፡ ወደናንት ፡ የምንሰዳቸውን ፡ ሰዎች ፡ መረጥነ ።

፳፮ ፤ ዕደው ፡ እለ ፡ መጠዉ ፡ ነፍሶሙ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ስለ ፡ ተጠሩ ፡ ስላመኑ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ስም ፡ ስላስተማሩ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ለመከራው ፡ አሳልፈው፡ የሰጡ ።

፳፯ ፤ ወፈነውነ ፡ ይሁዳሃ ፡ ወሲላስሃ፡ እሙንቱ ፡ ያጠይቁክሙ ፡ በቃሎሙ ፡ ዘንተ ፡

ይህነን ፡ ነገር ፡ እነሱ ፡ በቃላቸው ፡ ነግረው ፡ ያስረዷችሁ ፡ ዘንድ ፡ የመረጥናቸው ፡ ሲላስንና ፡ ይሁዳን ፡ ሰደድነ ።

፳፰ ፤ እስመ ፡ ኀብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምስሌነ ፡

መንፈስ ፡ ቅዱስ፡ በኛ ፡ አድሮ ፡ ሥርዐት ፡ ሠርቷልና ።

ከመ ፡ ኢናክብድ ፡

በናንት ፡ ላይ ፡ ሥርዐት ፡ እንዳናጸና ።

ወኢንወስክ ፡ ባዕደ ፡

ሌላ ፡ ሥርዐትም ፡ እንዳንሠራ ።

፳፱ ፤ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ዘንተ ፡ ዘተኀድጉ ፡ በግብር ፡ ዝቡሐ ፡ ለአማልክት ፡

ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ መሥዋዕት ፡ በግድ ፡ ከመብላት ፡ ትከለከሉ ፡ ዘንድ ፡ የምትከለከሉትን ፡ ይህን ፡ ብቻ ፡ እናዝዛችኋለን ፡ እንጅ ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ሥርዐት፡ እንዳንሠራ ።

ወኢትብልዑ ፡ ማውታ ፡

ሙቶ ፡ የተገኘውን ።

ወደመ ፡

ደም ፡ እንዳትበሉ ፡ ትከለከሉ ፡ ዘንድ ። ሐተታ ፡ ደሙ ፡ ሲረጋ ፡ አንፍረው ፡ ቆልተው ፡ ይበሉታልና ፡

ወትርኀቁ ፡ እምዝሙት ፡

ዝሙት ፡ ከመሥራት ፡ ትከለከሉ ፡ ዘንድ ፡

ወእማውታ ፡ ወደም ፡ ወትርሐቁ ፡ እምዝሙት ፡

ሙቶ፡ያደረውን፡ደም፡ከመብላት፡ከዝሙት

ወዘትጸልኡ፡ለርእስክሙ፡ኢትግበሩ፡ዲበ፡ ቢጽክሙ ፡

በራሳችሁ ፡ የምትጠሉትንም ፡ በወንድሞቻችሁ ፡ እንዳታደርጉ ፡ ትከለከሉ ፡ ዘንድ፡ ይህን ፡ ብቻ ፡ እናዝዛችኋለን ፡እንጅ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወለእመ ፡ ዐቀብክሙ ፡ ነፍሰክሙ ፡ እምእሉ ፡ ምግባራት ፡ ትሄልዉ ፡ በሰላም ፡

ከዚህ ፡ ከክፉው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ሰውነታችሁን ፡ ብትጠብቁ ፡ በዕረፍት ፡ ትኖራላችሁና ፡ ትኖራላችሁ ፡ የምትል ፡ ክታብ፡ ጽፈው ፡ ሰጧቸው ።

፴ ፤ ወተፈኒዎሙ ፡ እሙንቱ ፡ ወረዱ ፡ አንጾኪያ ፡

እሙንቱ ፡ ሲላስና ፡ በርናባስ ፡ ናቸው ፡ ተልከው ፡ ተሰናብተው፡ ወደ፡ አንጾኪያ ፡ ሄዱ ፡

ወአስተጋብኡ ፡ ሕዝበ ፡ ወመጠውዎሙ ፡ መጽሐፈ ፡ መልእክት ፡

ሕዝቡንም ፡ ሰብስበው ፡ ክታቡን ፡ ሰጧቸው ።

፴፩ ፤ ወአንቢቦሙ ፡ ተፈሥሑ ፡ ዐቢየ ፡ ፍሥሓ ፡ ወተናዘዙ ፡

ሕዝቡም ፡ ተመልክተው ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ጸኑ ፡ ምዕ ፡ ፲፫ ፡ ፵፰ ።

፴፪ ፤ ወአጽንዖ ፡ አኃወ ፡ በነገር ፡ ዘተርፈ ፡ በቃሎሙ ፡

ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ ግን ፡ በቃል ፡ ነግረው ፡ አጸኗቸው ።

ወመሀርዎሙ ፡ ይሁዳ ፡ ወሲላስ ፡

ይሁዳና ፡ ሲላስም ፡ ብዙ ፡ ትምህርት ፡ አስተማሯቸው ።

እስመ ፡ ነቢያት ፡ እሙንቱ ፡

መምህራን ፡ ነበሩና ፡ መሀርዎሙ ።

ወአጽንዕዎሙ ፡ ለቢጾሙ ፡ በቃሎሙ ፡

በቃል ፡ ነግረው ፡ ምእመናንን ፡ አጸኗቸው ፡ ምዕ ፡ ፲፩ ፡ ፳፮ ። ፲፫ ፡ ፩ ።

፴፫ ፤ ወጐንድዮሙ ፡ ፈነውዎሙ ፡ በሰላም ፡ ቢጾሙ ፡ ኀበ ፡ ልኡካን ፡

ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከነሱ ፡ ዘንድ ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ በፍቅር ፡ ሸኝተው ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡ ሰደዷቸው ።

፴፬ ፤ ወአጥብዐ ፡ ሲላስ ፡ ይንበር ፡ ሀየ ፡

ሲላስ ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ ሊኖር ፡ ወዶ ፡ ቀረ ።

፴፭ ፤ ወጳውሎስ ፡ ወበርናባስ ፡ ጐንደዩ ፡ አንጾኪያ

ጳውሎስና ፡ በርናባስም ፡ በአንጾኪያ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ኖሩ ፡

ወመሀሩ ፡ ወሰበኩ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ ባዕዳን ፡ ብዙኃን ፡

ለሌሎች ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወንጌልን ፡ አስተማሩ ።

፴፮ ፤ ክፍል ፡ ፴፩ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ይቤሎ ፡ ጳውሎስ፡ ለበርናባስ ፡ ንሰወጥ ፡ እንከሰ ፡ ወነሐውጾሙ፡ ለኵሎሙ፡ቢጽነ፡ እለ ፡ መሀርናሙ ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር ።

ጳውሎስ ፡ ወበርናባስ ፡ ጐንደዩ ፡ አንጾኪያ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ፡ ጳውሎስ፡ በርናባስን፡ ዘርዕ፡ የዘራ ፡ ሰው፡ ካላረመው ፡ ካልኰተኰተው፡ ይሆናል፡ በየሀገሩ፡ ወንጌልን፡ ያስተማርናቸው፡ ምእመናንን፡ እየዞርን ፡ እንጐብኝ፡ አለው፡

ወናእምር ፡ ዘከመ ፡ ሀለዉ ፡

በምን ፡ አኳሆን ፡ እንዳሉ ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ አለ ፡ በጽድቅም ፡ በኃጢአትም ፡ በሃይማኖትም ፡ በክህደትም ፡ እንዳሉ ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ፩ ፡ ተሰ ፡ ፫ ፡ ፮ ።

፴፯ ፤ ወፈቀደ ፡ በርናባስ ፡ ይንሥእ ፡ ለዮሐንስ ፡ ዘተሰምየ ፡ ማርቆስ ፡

በርናባስ ፡ ማርቆስ ፡ የተባለ ፡ ዮሐንስን፡ አስከትሎ ፡ ሊሄድ ፡ ወደደ ፡ ምዕ ፡ ፲፪ ፡ ፲፪ ፡ ፳፭ ።

፴፰ ፤ ወኢፈቀደ ፡ ጳውሎስ፡ ይንሥኦ፡ ምስሌሆሙ፡

ጳውሎስ ፡ ግን ፡ አስከትሎት ፡ ሊሄድ ፡ አልወደደም ።

እስመ ፡ ኀደጎሙ ፡ እንዘ ፡ እሙንቱ፡ በጵንፍልያ ፡

ብጵንፍልያ ፡ ሳሉ ፡ ተለይቷቸው ፡ ሂዶ ፡ ነበርና ፡

ወሖረ ፡ ወኢመጽአ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ውስተ ፡ ግብር ፡

ለመርዳት ። አንድም ፡ ለማስተማር ፡ ከእነሱ ፡ ጋራ ፡ አልመጣም ፡ ነበርና ፡ ምዕ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ።

፴፱ ፤ ወበእንተ፡ዝ፡ተምዑ፡ወተፋለጡ፡ዘዘዚአሆሙ፡

ስለዚህ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተከራርረው ፡ ተለያዩ ፡ ሐተታ ፡ አሁን ፡ በሁለቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ተቃኅዎ ፡ኑሮባቸው ፡ አይደለም ፡ ውስጡ ፡ ጥበበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ሁለቱ ፡ አበጋዞች ፡ ባንድነት ፡ ቢሆኑ ፡ ሃይማኖት ፡ ይጸናል ፡ እንጅ ፡ አይሰፋም ፡ በየራሳቸው ፡ የሆኑ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ በያሉበት ፡ ያስተምራሉ ፡ ሃይማኖት ፡ ይሰፋልና ፡

በርናባስ ፡ ነሥአ ፡ ለማርቆስ ፡ ወነገደ ፡ ቆጵሮስ ፡

በርናባስ ፡ ማርቆስን ፡ አስከትሎ ፡ ወደ ፡ ቆጵሮስ ፡ ሄደ ።

፵ ፤ ጳውሎስ ፡ ኀረየ ፡ ለሲላስ ፡ ወሖረ ፡

ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ሲላስን፡ አስከትሎ፡ ሄደ ፡

ወአማኅፀንዎ ፡ ቢጹ ፡ በጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡

ምእመናንም ፡ ጳውሎስን ፡ አደራ፡ አሉት፡ አለ ፡ ያመንህበት ፡ እግዚአብሔር ፡ አይለይህ ፡ አሉት ።

፵፩ ፤ ወያደ ፡ ሶርያ ፡ ወቂልቅያ ፡ ወአጽንዐ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ።

በቂልቅያ ፡ በሶርያ ፡ እየዞረ ፡ አስተማረ ፡ ምእመናንን ፡ በሃይማኖት ፡ አጸና ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፮ ፡

፩ ፤ ወበጽሐ ፡ ሀገረ ፡ ደርቤን ፡ ወልስጥራን ፡

እስከ ፡ ደርቤን ፡ እስከ ፡ ልስጥራን ፡ ድረስ አስተማረ ፡

ወረከበ ፡ አሐደ ፡ ረድአ ፡ ዘስሙ ፡ ጢሞቴዎስ ፡

በልስጥራን ፡ ጢሞቴዎስ ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ምእመን ፡ አገኘ ፡

ወእሙሰ ፡ አይሁዳዊት ፡

እናቱ ፡ አይሁዳዊት ፡ ነበረች ፡

ወአምነት ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ በሱ ፡ ስብከት ፡ አመነች ፡

ወአቡሁሰ ፡ አረማዊ ፡

አባቱ ፡ ግን ፡ አረማዊ ፡ ነበር ፡ ምዕ ፡ ፲፯ ፡ ፲፬ ። ፲፱ ፡ ፳፪ ።

፪ ፤ ወይንእድዎ ፡ ኵሉ ፡ ቢጹ ፡ እለ ፡ በልስጥራን ፡ ወደርቤን ፡ ወኢቆንዮን ፡

በልስጥራን ፡ በደርቤን ፡ በኢቆንዮን ፡ ያሉ ፡ ወገኖቹ ፡ ሁሉ ፡ ያከብሩት ፡ ነበርና፡ አላመነም ፡ ምዕ ፡ ፯ ፡ ፫ ።

፫ ፤ ወአፍቀረ ፡ ጳውሎስ ፡ ይንሥአ ፡ ምስሌሁ ፡ ወይሑር ፡ ወነሥአ ፡

ጳውሎስም ፡ ጢሞቴዎስን ፡ አስከትሎት ፡ ሊሄድ ፡ ወደደ ፡ ሐተታ ፡ በጎ ፡ብላቴንነቱን ፡ አይቶ ፡ ሲሻው ፡ አይቶ ፡ ኋላ ፡ ከፍጹምነት ፡ እንዲደርስ ፡ አውቆ ።

ወገዘሮ ፡ በእንተ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ ብሔር ፡

በዚያ ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ አይሁድን ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፡ ብሎ ፡ ገዝሮ፡ አስከትሎታል ፡

እስመ ፡ የአምርዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ከመ፡ አረማዊ፡ አቡሁ፡

አባቱ ፡ አረማዊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሁሉም ፡ ያውቁ ፡ ነበርና ፡ ገዝሮ ፡ ላለው ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፭ ።



www.ethiopianorthodox.org

፬ ፤ ወሖሩ ፡ አህጉረ ፡ ወመሀረዎሙ ፡ ሥርዐተ ፡ ሐዋርያት ፡ ዘአዘዙ ፡ ኅቢሮሙ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ምስለ ፡ ቀሲሳን ፡

በየሀገሩ ፡ እየዞሩ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከቀሳውስት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ የሠሩትን፡ የሐዋርያትን ፡ ሥርዐት፡ አስተማሯቸው። አንድም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከቀሳውስት ፡ ጋራ ፡ ሐዋርያት ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ የሠሩትን ፡ ሥርዐት ፡ አስተማሯቸው ፡ ም ፡ ፲፭ ፡ ፳—፳፱ ።

፭ ፤ ወጸንዑ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በሃይማኖት

ምእመናንም ፡ በሃይማኖት ፡ ጸኑ ፡

ወእንተ ፡ ጸብሐት ፡ ይበዝኁ ፡ ሕዝብ ፡

የሚያምኑትም፡ዕለት፡ዕለት፡ይበዙ፡ነበር ።

፮ ፤ ወሖሩ ፡ ፍርግያ ፡ ወብሔረ ፡ ገላትያ ፡

ከዚያ ፡ ወጥተው ፡ ወደፍርግያ ፡ ወደ፡ ገላትያ ፡ አገር ፡ ሄዱ ።

ወከልአሙ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኢይንግሩ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእስያ ፡

በእስያ ፡ ወንጌልን፡ እንዳያስተምሩ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከለከላቸው ፡ ጊዜው ፡ ባይደርስ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፳፫ ።

፯ ፤ ወበጺሖሙ ፡ ሚስያ ፡ ፈቀዱ ፡ ይሑሩ ፡ ቢታንያ ፡ ወኢያብሖሙ ፡ መንፈሱ ፡ ለኢየሱስ ።

ሚስያ ፡ ደርሰው ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ ሊሄዱ፡ ወደዱ ። ከዚያም ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሕይወት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ግን ፤ አላሰናበታቸውም ።

፰ ፤ ወኀሊፎሙ፡እምነ፡ ሚስያ፡ ወረዱ፡ ጢሮአዳ ፡

ከሚስያ፡ ወጥተው፡ ወደ፡ ጢሮአዳ፡ ሄዱ ።

፱ ፤ ወአስተርአዮ፡ ለጳውሎስ፡በሌሊት፡ብእሲ፡መቄዶናዊ ፡ ይቀውም ፡ ወያስተበቊዖ ፡ ወይቤሎ ፡ ኅልፍ፡ እንተ ፡ መንገሌነ ፡ ለመቄዶንያ ፡ ወነዓ ፡ ርድአነ ።

በአምሳለ ፡ መኰንን ፡ መቄዶንያዊ ፡ ሌሊት ፡ ለጳውሎስ ፡ ታይቶ ፡ በኛ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ። አንድም ፡ እኛ ፡ ወደ ለንበት ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ መጥተህ ፡ ትምህርት ፡ እገዘን ፡ ብሎ ፡ ማለደው ።

፲ ፤ ወርእዮ ፡ ዘንተ ፡ ፈቀድነ ፡ ንሑር ፡ እንተ ፡ መቄዶንያ ፡

ይህንም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ ልንሄድ ፡ ወደድን ፡

እስመ ፡ ጸውዐነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንምሀሮሙ ፡ ሃይማኖተ ፡

ሃይማኖትን ፡ ልናስተምራቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ አዝዞናልና ።

፲፩ ፤ ወወፂእነ ፡ እምጢሮአዳ ፡ አፍጠነ ፡ ወበጸሕነ ፡ አሞትራቄ ።

ከጢሮአዳ ፡ ወጥተን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ አሞትራቄ ፡ ደረስን ፡

ወበሳኒታ ፡ ሖርነ ፡ ሀገረ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ብና ።

በነጋው ፡ ከዚያ ፡ ወጥተን ፡ ብና ፡ ወደምትባል ፡ አገር ፡ ሄድን ።

፲፪ ፤ ወእምህየ ፡ ፊልቁስ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ቀዳሚት ፡ ዘመቄዶንያ ፡

ከዚያም ፡ ወጥተን ፡ የመቄዶንያ ፡ መዲና፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ሄድን ፡

ወይእቲ ፡ ሀገር ፡ ቆሎንያ ፡

በቆላስይስ ፡ አጠገብ ፡ ያለች ።

፲፫ ፤ ወነበርነ ፡ በይእቲ ፡ ሀገር ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ።

በይእቲ ፡ ሀገር ፡ በፊልጵስዩስ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ኖርን ፡

ወወፃእነ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ እምአንቀጸ ፡ ሀገር ፡ መንገለ ፡ ድንጋገ ፡ ፈለግ ፡

ቅዳሜ ፡ ቀን ፡ ከከተማው ፡ በር ፡ ወጥተን፡ ወደ ፡ ወንዙ ፡ ዳር ፡ ሄድን ፡

እስመ ፡ ቤተ ፡ ጸሎት ፡ ሀየ ፡ ሀሎ ፡

ከዚያ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ነበረና ፡



ወነበርነ ፡ ወአኅዝነ ፡ ከመ ፡ ንንግር ፡ ለአንስት ፡ እለ፡ ተጋብአ ፡ ህየ ።

ከዚያ ፡ ለተሰበሰቡት ፡ ሴቶች ፡ ጉባኤ ፡ ሠርተን ፡ አስተማርን ።

፲፬ ፤ ወሀለወት ፡ ማዕከሎን ፡ አሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ሠያጢተ ፡ አጌ ፡

በመካከላቸው ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ የሐር ፡ ኩብ፡ የምትሸጥ፡ አንዲት፡ ሴት፡ ነበረች ።

እንተ ፡ ሀገረ ፡ ትያጢሮን ፡

ሀገሯ ፡ ትያጢሮን ፡ የሚሆን ፡

ፈራሂተ ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን፡የምትፈራ፡የምግባር፡ ነው

ወታፀምዕ ፡ እስመ ፡ ከሠተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እዝና ፡

እግዚአብሔር ፡ እዝነ ፡ ልቡናዋን ፡ ስለ ፡ ገለጠላት ፡ ትምህርቱን ፡ ትሰማ ፡ ነበር ፡

ወስማ ፡ ልድያ ፡

ስሟም ፡ ልድያ ፡ ይባል ፡ ነበር ፡ ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፵፬ ።

፲፭ ፤ ወተጠምቀት ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብአ ፡

ከቤተ ፡ ሰቦችዋ ፡ ጋራ ፡ አምና ፡ ተጠመቀች ።

ወአስተብቍዐተነ ፡ ወትቤለነ ፡ ለእመሁ ፡ ረሰይክሙኒ ፡ መሃይምንተ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ባኡ ፡ ቤትየ ፡ ወኅድሩ ፡

የእግዚአብሔርስ ፡ አማኒ(ኝ) ፡ ካደረጋችሁኝ፡ከቤቴ ፡ ገብታችሁ ፡ እደሩ ፡ ብላ ፡ ማለደችን ፡

ወአገበረተነ ፡ ብዙኀ ፡

መላልሳ ፡ ግድ ፡ አለችን ፡ አደርን ።

፲፮ ፤ ክፍል ፡ ፴፪ ። ወእንዘ ፡ ነሐውር ፡ ለጸሎት ፡

ከዚያ ፡ አድረን ፡ በነጋው ፡ ለጸሎት ፡ ስንሄድ ፡

ረከበተነ ፡ አሐቲ ፡ ወለት ፡ እንተ ፡ ይትዋረዳ፡ ጋኔን ።

ጋኔን ፡ የሚያዘፍናት ፡ አንዲት ፡ ብላቴና ፡ ሴት ፡ አገኘችን ፡

ወታገብእ ፡ ለአጋእዝቲሃ ፡ ብዙኀ ፡ ብነተ ፡ እምዘ ፡ ትነሥእ ፡ ሐፍሣ ፡

ለጌቶችዋ ፡ ብዙ፡ ግብር ፡ ታገባ ፡ ነበር ፡ ሐፍሣ ፡ ስሟ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከያዘችው ፡ ሐፊሣ ፡ ቢል ፡ ዘግና ፡ ከያዘችው ። አንድም፡ እምሐፍሣ፡ ዘትነሥእ ፡ ከጥርኝዋ ፡ ከዝግኝዋ ፡ ለጌቶችዋ ፡ ግብር ፡ ታገባ፡ ነበር ፡ (ጥቅ)፡ ሐፍሰ ፡ ወይኑ፡ ዘቢብ ፡ እንዲል ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፳፬ ።

፲፯ ፤ ወእምዝ ፡ ተለወት ፡ ድኅሬሁ ፡ ለጳውሎስ፡ ወድኅሬነ ፡ እንዘ ፡ ትኬልሕ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ በጳውሎስ ፡ ኋላ ፡ በኛም ፡ በኋላ ፡ በኋላችን ፡ እየጮኸች ፡ ተከተለች ፡

ወትብል ፡ እሉ ፡ ዕደው ፡ አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ እሙንቱ ፡

እሊህ ፡ ሰዎች ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ ናቸው ፡

ወይሜህሩክሙ ፡ ፍኖተ ፡ ሕይወት ፡

ድኅነት ፡ የምታገኙበትን ፡ ነገር ፡ ያስተምሯችኋል ፡ እያለች ፡ ማር ፡ ፩ ፡ ፳፬ ።

፲፰ ፤ ወከመ ፡ ዝ ፡ ትገብር ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡

ብዙ ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ እያለች ፡ ትጮኽ፡ ነበር ፡

ወአጽሀቀቶ ፡ ለጳውሎስ ፡

እንዲህ ፡ እያለች ፡ እየጮኸች ፡ ጳውሎስን ፡ አሳዘነችው ፡ አተጋችው ፡

ወተመይጠ ፡ ወይቤሎ ፡ ለውእቱ ፡ መንፈስ ፤ እኤዝዘከ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ትፃእ ።

ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ከሷ ፡ ትወጣ ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አዝዝሃለሁ ፡ አለው ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወኀደጋ ፡ በጊዜሃ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ተለይቷት ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ ፡ ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ ።

፲፱ ወርእዮሙ ፡ አጋእዝቲሃ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ እም ኀበ ፡ ታገብእ ፡ ብንታ ፡

ጌቶቿዋም ፡ የምታገባላቸው ፡ ግብር ፡ እን ደ ፡ ቀረ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ።

አኀዝዎሙ ፡ ለጳውሎስ ፡ ወለሲላስ ፡ ወሰሐብዎሙ ፡ እንተ ፡ ምሥያጥ ፡

ጳውሎስንና ፡ ሲላስን ፡ ይዘው ፡ በአደ ባባይ ፡ እየጐተቱ ፡

፳ ወአብጽሕዎሙ ፡ ኀበ ፡ መኳንንት ።

ወደ ፡ ሹማምቱ ፡ አደረሷቸው ፡

ወይቤሉ ፡ እሉ ፡ ዕደው ፡ የሀውኩ ፡ ለነ ፡ ሀገረ ፡

እሊህ ፡ ሰዎች ፡ አገራችነን ፡ ያሸብሩብ ናል ፡

ወአይሁድ ፡ እሙንቱ ፡

ወዲህም ፡ አይሁድ ፡ ናቸው ፡ ም ፡ ፲፯፡ ፮ ።

፳፩ ወይሜህሩ ፡ ለነ ፡ ሕገ ፡ ዘኢይከውነነ ፡ ለገ ቢር ፡ እንዘ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ ንሕነ ።

የሮም ፡ ሰዎች ፡ ስንሆን ፡ ልንሠራው ፡ የማይገባነን ፡ ሥርዐት ፡ ያስተምሩብናል ፡ እያሉ ፡ አብጽሕዎሙ ፡ ላለው ።

፳፪ ወተጋብኡ ፡ ሕዝብ ፡ ወመኳንንት ፡ ወአኀዙ፡ ይዝብጥዎሙ ፡ በበትር ።

ሕዝቡም ፡ መኳንንቱም ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ተሰብስበው ፡ በበትር ፡ ደበደቧቸው ፡

ወሰጠጡ ፡ አልባሲሆሙ፡

ደብዳቦቹም ፡ ልብሳቸውን ፡ አሰለቡ ። አን ድም ፡ የነጳውሎስን ፡ ልብሳቸውን ፡ ገ ፈፉ ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭ ። ፊል ፡ ፩ ፡ ፴ ። ፩ ፡ ተሰ ፡ ፪ ፡ ፪ ።

፳፫ ወዘበጥዎሙ ፡ ብዙኀ ፡ ወሞቅሕዎሙ ፡

መላልሰው ፡ ደብድበው ፡ አሠሯቸው ፡

ወአዘዝዎ ፡ ለዐቃቤ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ያጽንዕ ፡ ዐቂቦቶሙ ፡

የሥር ፡ ቤት ፡ ጠባቂውንም ፡ አጽንቶ ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቅ ፡ አሉት ፡

፳፬ ወተአዚዞ ፡ ሞቅሖሙ ፡ ውስተ ፡ ውሳጤ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ።

እሽ ፡ በጄ ፡ ብሎ ፡ ተቀብሎ ፡ ከምድር ፡ ቤት ፡ አሠራቸው ፡

ወአጽንዐ ፡ እገሪሆሙ ፡ ውስተ ፡ ጕንድ ።

እግራቸውን ፡ ከፍልፍል ፡ ግንድ ፡ አግ ብቶ ፡ እሥራት ፡ አጸናባቸው ።

፳፭ ወጊዜ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ጸለዩ ፡ ጳውሎስ ፡ ወሲላስ ፡

መንፈቀ ፡ ሌሊትም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ጳው ሎስና ፡ ሲላስ ፡ ጸሎት ፡ ጸለዩ ፡

ወሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርንም ፡ ለመኑት ፡

ወሙቁሓን ፡ ይሰምዕዎሙ ፡

እሥረኞችም ፡ ይሰሟቸው ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፴፩ ፡ ፳ ፡ ፵፩ ።

፳፮ ወሶቤሃ ፡ አድለቅለቀ ፡ ዐቢይ ፡ ድልቅልቅ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ፍጹም ፡ መነዋወጥ ፡ ሆነ ፡

ወአንቀልቀለ ፡ መሠረታተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ።

የእሥሩ፡ ቤት፡ መሠረት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ተነ ዋወጠ ፡ በድረግ ፡ አለ ፡ ትእምርተ ፡ ኀል ፈተ ፡ ዓለም ፡ ትእምርተ ፡ ኀልፈተ ፡ ምኵ ራብ ፡ ትእምርተ ፡ ምዝባሬ ፡ ቤተ ፡ መቅ ደስ ፡ ትእምርተ ፡ ዕርገተ ፡ጸሎት ፡ የሰ ውን ፡ ሁሉ ፡ ልቡና ፡ እንዲህ ፡ አሸብርላ ችኋለሁ ፡ ሲል ፡

ወተርኀወ ፡ በጊዜሃ ፡ ኵሉ ፡ አንቀጽ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ በሩ ፡ ሁሉ ፡ ተከፈተ ።

ወተፈትሐ ፡ መዋቅሕቲሆሙ ፡ ለኵሎሙ ፡

ሰንሰለቶች ፡ ከእጃቸው ፡ እየወለቁ ፡ ወ ደቁ ።

፳፯ ወሶበ ፡ ነቅሀ ፡ ዐቃቤ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ርእየ ፡ ርኅወ ፡ ኵሎ ፡ አናቅጸ ፡

የእሥር ፡ ቤት ፡ ጠባቂም ፡ ከእንቅልፉ፡ በነቃ ፡ ጊዜ ፡ በሩ ፡ ሁሉ ፡ ተከፍቶ ፡ አየ ፡

ወመልሐ ፡ መጥባሕቶ ፡ ወፈቀደ ፡ ይትረገዝ ፡ ለሊሁ፡

ሾተሉን ፡ መዞ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ታርዶ ፡ ሊ ሞት ፡ ወደደ ፡

እስመ ፡ መሰሎ ፡ ዘአምሠጡ ፡ ሙቁሓን ፡

እሥሮች፡ ያመለጡ ፡ መስሎት ፡ ነበርና ።

፳፰ ከልሐ ፡ ሎቱ ፡ ጳውሎስ ፡ ወይቤሎ ፡ ኢት ግበር ፡ እኩየ ፡ ዲበ ፡ ነፍስከ ፡

በሰውነትህ ፡ ክፉ ፡ ሥራ፡ አትሥራ፡ ብሎ፡ ጳውሎስ ፡ ድምፅ ፡ አሰማው ፡ በገዛ ፡ እጅህ ፡ ታርደህ ፡ አትሙት ፡ አለው ፡

ሀሎነ ፡ ኵልነ ፡ ዝየ ፡

ሁላችንም ፡ ከዚህ ፡ አለንና ።

፳፱ ወአምጽአ ፡ ማኅቶተ ፡ ወሖረ ፡ እንዘ ፡ ይር ዕድ ፡

መብራት ፡ አብርቶ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ሂዶ ፡

ወሰገደ ፡ ኀበ ፡ ጳውሎስ ፡ ወሲላስ ፡

ከጳውሎስና ፡ ከሲላስ ፡ ከእግራቸው ፡ በ ታች ፡ ወድቆ ፡ ሰገደ ።

፴ ወአውፅኦሙ ፡ አፍአ ፡ ወይቤሎሙ ፡ አጋእዝ ትየ ፡ ምንተ ፡ እግበር ፡ ከመ ፡ እድኅን ፡

ወደ ፡ አፍአ ፡ አውጥቶ ፡ ጌቶቼ ፡ እድን ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ አላቸው ፡ ም ፡ ፪ ፡ ፴፯ ። ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፲ ።

፴፩ ወይቤልዎ ፡ እመን ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

ብጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እመን ፡

ወተሐዩ ፡ አንተ ፡

አንተም ፡ ትድናለህ ፡

ወኵሉ ፡ ቤትከ ፡

ቤተ ፡ ሰቦችህም ፡ ሁሉ ፡ ይድናሉ፡ አሉት፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።

፴፪ ወነገርዎ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡

ወንጌልን ፡ አስተማሩት ፡

ወለኵሉ ፡ ሰብኡ ፡

ለቤተ ፡ ሰቦቹም ፡ አስተማሯቸው ።

፴፫ ወነሥኦሙ ፡ ሶቤሃ ፡ በሌሊት ፡ ወኀፀቦሙ ፡ እምቅሥፈቶሙ ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ በሌሊት ፡ ወስዶ ፡ ግርፋታቸ ውን ፡ አጠባቸው ፡ ሐተታ ፡ የተገረፈ ፡ ሰው ፡ ሲያጥቡት ፡ ይቀለዋል ፡ ይባላልና

ወተጠምቀ ፡ ውእቱኒ ፡

እሱም ፡ ተጠመቀ ።

ወኵሉ ፡ ሰብኡ ፡ በጊዜሃ ፡

ቤተ ፡ ሰቦቹም ፡ አምነው ፡ ተጠመቁ ።

፴፬ ወአዕረጎሙ፡ ውስተ፡ ቤቱ ፡ ወሠርዐ ፡ ማዕደ፡

ከቤቱ ፡ ወስዶ ፡ ግብር ፡ አገባላቸው ፡

ወተፈሥሐ ፡ ውእቱ ፡

እሱም ፡ ደስ ፡ አለው ፡

ወኵሉ ፡ ቤቱ ፡ በአሚነ ፡ እግዚእነ ፡

ቤተ ፡ ሰቦቹም ፡ በጌታችን ፡ በማመን ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡

፴፭ ወጸቢሖ ፡ ለአኩ ፡ መኳንንት ፡ ወዓልያኒ ሆሙ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ፍትሕዎሙ ፡ ለእሉ ፡ ዕደው ፡ ወኅድግዎሙ ፡ ይሑሩ ፡

በነጋ ፡ ጊዜ ፡ ሹማምቱ ፡ እሊያን ፡ ሰዎች፡ ፈትታችሁ ፡ ተዋቸው ፡ ይሂዱ ፡ ብለው ፡ ብላቴኖቻቸውን ፡ ላኩ ።

፴፮ ወሰሚዖ ፡ ዐቃቤ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡

የሥር ፡ ቤት ፡ ጠባቂው፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ነገሮሙ ፡ ዘ ፡ ነገረ ፡ ለጳውሎስ ፡ ወለሲላስ ፡

ይኸን ፡ ነገር ፡ ለጳውሎስና ፡ ለሲላስ ፡ ነገ
ራቸው ፡

ከመ ፡ ለአኩ ፡ መኳንንት ፡ ይኅድግዎሙ ፡

ፈትታችሁ ፡ ተዋቸው ፡ ይሂዱ ፡ ብለው ፡
እንደ ፡ ላኩ ።

፴፮ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ሑሩ ፡ በሰላም ፡

አሁንም ፡ ሂዱ ፡ በደህና ፡ አላቸው ፡

ወይቤልዎ ፡ ቀሠፉነ ፡ ገሃደ ፡ ዘአልብነ ፡ አበሳ ፡
እንዘ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ ንሕነ ፡ ወሞቅሑነ ፡

የሮም ፡ ሰዎች ፡ ስንሆን ፡ በደል ፡ ሳይኖ
ርብን ፡ ገርፈው ፡ አስረውናል ፡

ወይእዜኒ ፡ ጽሚተ ፡ ያውፅኡነ ፡ ይፈቅዱ ፡

አሁን ፡ ግን ፡ ሠውረው ፡ ሊያስወጡን ፡
ይወዳሉ ፡

ጽሚተሰኬ ፡ አበይነ ፡

ተሰውረንስ ፡ አንሄድም ፡

ይምጽኡ ፡ ለሊሆሙ ፡ ያውፅኡነ ፡

እነሱ ፡ መጥተው ፡ ያስወጡን ፡ እንጅ ፡
አሏቸው ፡ ም ፡ ፳፱ ፡ ፳፰ ።

፴፰ ፤ ወሐሩ ፡ ወነገርዎሙ ፡ ወዓልያኒሆሙ ፡ ዘንተ
ነገረ ፡ ለመኳንንት ፡

ብላቴኖቻቸውም ፡ ሂደው ፡ ይህንን ፡ ነገር
ለሹማምቱ ፡ ነገሯቸው ፡

ወፈርሁ ፡ ሰሚዖሙ ፡ ከመ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ እሙንቱ፡

የሮም ፡ ሰዎች ፡ ነን ፡ ያሉትን ፡ በሰሙ ፡
ጊዜ ፡ ፍርሃት ፡ አደረባቸው ።

፴፱ ፤ ወመጽኡ ፡ ወአስተብቍዕዎሙ ፡ ከመ ፡ ይፃ
ኡ ፡ እምብሔሮሙ ፡

መጥተው ፡ ከሀገራችን ፡ ውጡልን ፡ ብለ
ው ፡ ማለዷቸው ፡ ማቴ ፡ ፰ ፡ ፴፬ ።

፵ ፤ ወወፂአሙ ፡ እምቤተ ፡ሞቅሕ ፡ ቦኡ ፡ ቤተ፡
ልድያ ፡

ከሥሩ ፡ ቤት ፡ ወጥተው ፡ ከልድያ ፡ ቤት ፡
ገቡ ፡

ወረከቡ ፡ ቢጾሙ ፡

ምእመናንን ፡ አገኙ ፡

ወመሀርዎሙ ፡

አስተማሯቸው ፡

ወወፅኡ ፡

ከልድያ ፡ ቤት ፡ ወጥተው ።

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

ክፍል ፡ ፴፫ ።

፩ ፤ ወሐሩ ፡ አንፊጶል ፡ ወአጶሎንያ ፡ አህጉረ ፡

ወደ፡አንፊጶል፡ወደ፡አጶሎንያ፡አገር፡ ሄዱ ፡

ወበጽሑ፡ ተሰሎንቄ፡ ኀበ፡ ሀሎ፡ምኵራብ፡ አይሁድ ፡

ከዚያም ፡ ወጥተው ፡ የአይሁድ ፡ ምኵ
ራብ ፡ ካለበት ፡ ተሰሎንቄ ፡ ደረሱ ፡ ፩ ፡
ተሰ ፡ ፪ ፡ ፪ ።

፪ ፤ ወቦአ ፡ ጳውሎስ ፡ ኀቤሆሙ ፡ በከመ ፡ ያለምድ፡
ወነበረ፡ይትዋቀሥሙ፡ሠለስተ፡ሰናብተ፡እመጻሕፍት ፡

ጳውሎስም ፡ እንደለመደ ፡ እነሱ ፡ ወዳሉ
በት ፡ ምኵራብ ፡ ገብቶ ፡ ከመጻሕፍት ፡
እየጠቀሰ ፡ ሦስት ፡ ሱባኤ ፡ ሲከራከራ
ቸው ፡ ኖረ ።

፫ ፤ ወይፌክር ፡ ሎሙ ፡

እየተረጐመላቸው ፡

ወያበጽሕ ፡ ከመሂ ፡ ይትቀተል ፡ ክርስቶስ ፡

ክርስቶስ ፡ እንዲሞት ፡

ወከመሂ ፡ ይትነሣእ ፡ እምውታን ፡

ከሙታንም ፡ ተለይቶ ፡ እንዲነሣ ፡ ሲያስ
ረዳቸው ፡ ኖረ ።



ወከመ ፡ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘአነ ፡ ነገርኩ
ክሙ ፡

ይህም ፡ እኔ ፡ የነገርኋችሁ ፡ ኤርምያስ ፡
ለሊሁ ፡ ኢየሱስ ፡ አምላክ ፡ ወልደ ፡ አም
ላክ ፡ ይመጽእ ፡ ብሎ ፡ የተናገረለት ፡ኢየ
ሱስ ፡ ዳንኤል ፡ መቅደስ ፡ ትትሐነጽ፡ እስ
ከ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ ብሎ ፡ የተናገረ
ለት ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። አንድም ፡ ዳን
ኤል ፡ መቅደስ ፡ ትትሐነጽ ፡ እስከ ፡
ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ ብሎ ፡ የተናገረለት ፡
ክርስቶስ ፡ኤርምያስ ፡ ለሊሁ ፡ ኢየሱስ ፡
አምላክ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ይመጽእ ፡
ብሎ ፡ የተናገረለት ፡ ኢየሱስ ፡ ነው ፡ እ
ያለ ፡ ሲያስረዳቸው ፡ ኖረ ፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡
፳፯ ፡ ፵፫ ።

፬ ፤ ወቦ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ ወተለው
ዎሙ ፡ ለጳውሎስ ፡ ወለሲላስ ፡ ቢጽ ፡

ከነዚያም፡ ወገን፡ አምነው ፡ ጳውሎስንና ፡
ሲላስን ፡ የተከተሉ ፡ ነበሩ ፡

ወኄራቶሙ ፡ ለአረማውያን ፡ ብዙኃን፡ ወአንስትኒ ፡

ከአረማውያንም ፡ ወገን ፡ አምነው ፡ የተ
ከተሉ ፡ ብዙ ፡ ደጋግ ፡ ሴቶችም ፡ ወንዶ
ችም ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡

ወዐበይቶሙ ፡ ብዙኃን ፡

ወይዛዝሩም ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ።

፭ ፤ ወቀንኡ ፡ አይሁድ ፡ ላዕሌሆሙ ፡

አይሁድ ፡ ግን ፡ ቀኑባቸው ፡

ወአስተጋብኡ ፡ ሰብአ ፡ ምሥያጥ ፡ ቢጸ ፡ እኩያነ ፡

ሰብአ ፡ ምስያጥ ፡ ቢጽ ፡ እኩያንን ፡ ቢጽ ፡
እኩያን ፡ ሰብአ ፡ ምስያጥን ፡ ሰበሰቡ ፡

ወበጽሑ ፡ ወሆከዋ ፡ ለሀገር ፡ ወኀሠሥዎሙ ፡

በዝተው፡አገሪቱን፡ደረፁዋት፡ፈለጓቸው ።

ወደበዩ ፡ ቤተ ፡ ኢያሶን ፡

... ዘረፉ ፡

ወፈቀዱ ፡ ያውፅእዎሙ ፡ ኀበ ፡ ሕዝብ ፡

ለሕዝቡ ፡ አሳልፈው፡ ይሰጧቸው፡ዘንድ፡
ወደው ።

፮ ፤ ወኀጢአሙ ፡ ሰሐብዎ ፡ ለኢያሶን፡ ወለቢጹሂ ፡
እለ ፡ ሀለዉ ፡ ህየ ፡ ወወሰድዎሙ፡ ኀበ ፡ መኳንንት ፡

ፈልገው ፡ ባያገኙዋቸው ፡ ኢያሶንን ፡ ከ
ዚያ ፡ ያሉ ፡ ምእመናንም ፡ እየጐተቱ ፡
ወደ ፡ ሹማምቱ ፡ አደረሷቸው ፡

እንዘ ፡ የዐወይዉ ፡ ወይብሉ፡ እሉ ፡ እሙንቱ፡ እለ ፡
የሀውክዋ ፡ ለዓለም ፡

ዓለምን ፡ የሚያሸብሯት ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡
እያሉ ፡ እየጮሁ ፡

ወመጽኡ ፡ ዝየኒ ፡

ከዚህም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ፳ ።
፩ ፡ ነገሥ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯ ።

፯ ፤ ወተወክፎሙ ፡ ዝ ፡ ኢያሶን ፡

ይህ ፡ ኢያሶን ፡ ተቀብሏቸዋል ፡

ወእሙንቱ ፡ ይገብሩ ፡ ማዕሌተ ፡ ቄሣር ፡

በቄሣር ፡ ላይ ፡ አመፅን ፡ ያደርጋሉ ፡ የሚ
ያደርጉ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።

ወይሜህሩ ፡ ካልአ ፡ ሕገ ፡

ከአሪት ፡ ካልእ ፡ የሚሆን ፡ ወንጌልን ፡
ያስተምራሉ ፡

ወይቤሉ ፡ ኢየሱስ ፡ ካልእ ፡ ንጉሥ ፡

ኢየሱስ ፡ ወሬኛ ፡ ንጉሥ ፡ ነው፡ እያሉ፡
በቄሣር ፡ አመፅን ፡ ያደርጋሉ ፡ የሚያ
ደርጉ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፪ ።

፰ ፤ ወተሀውኩ ፡ ሕዝብ ፡ ወመኳንንት ፡ ዘንተ ፡
ሰሚዖሙ ፡

ሕዝቡም ፡ ሹማምቱም ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡
ጊዜ ፡ ተቸገሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

፬ ፤ ወብዙኅ ፡ ተሐልዮሙ ፡ እምኅበ ፡ ኢያሶን ፡ ወእምኅበ ፡ ቢጹ ፡ ኅደግዎሙ ፡

ከኢያሶን ፡ ከምእመናንም ፡ ብዙ ፡ መማ ለጃ ፡ ተቀብለው ፡ ሰደዷቸው ።

፲ ፤ ወቢጸሙሰ ፡ ፈነውዎሙ ፡ በሌሊት ፡ ለጳውሎስ ፡ ወለሲላስ ፡ ውስተ ፡ ቤርያ ፡

ምእመናን ፡ ግን ፡ ጳውሎስንና ፡ ሲላስን ፡ ሌሊት ፡ አሸሽተው ፡ ወደ ፡ ቤርያ ፡ ሰደ ዷቸው ፡

ወቦኡ ፡ ምኵራበ ፡ አይሁድ ፡

በቤርያ ፡ ከአይሁድ ፡ ምኵራብ ፡ ገብተው፡ አስተማሩ ።

፲፩ ፤ ወእሙንቱ ፡ ይኄይሱ ፡ እምእለ ፡ በተሰሎንቄ ፡

በተሰሎንቄ ፡ ካሉ ፡ አይሁድ ፡ በቤርያ ፡ ያሉ ፡ አይሁድ ፡ ይሻሉ ፡ ነበርና ፡

ወተወክፉ ፡ ቃሎሙ ፡ በኵሉ ፡ ትፍሥሕት ፡

በፍጹም ፡ ደስታ ፡ ትምህርታቸውን ፡ ተቀበሏቸው ፡

ወኵሎ ፡ አሚረ ፡ የኀሥሡ ፡ በውስተ ፡ መጻሕፍት ፡

ሁል ፡ ጊዜ ፡ መጻሕፍትን ፡ ይሹ ፡ ይመረ ምሩ ፡ ነበር ፡

ለእመ ፡ ከማሁ ፡ ውእቱ ፡

መጻሕፍት ፡ እንደ ፡ ተናገሩት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለመረዳት ፡ ኢሳ ፡ ፴፬ ፡ ፲፮ ። ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፳፱ ። ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፴፱ ።

፲፪ ፤ ወብዙኃን ፡ እምውስቴቶሙ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡

ከነዚያም ፡ ወገን ፡ ያመኑ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡

ወአንስትኒ ፡ ብዙኃት ፡ አረማውያት ፡ ኄራት ፡ ወዕ ደውኒ ፡ ብዙኃን ፡

ከአረማውያንም ፡ ወገን ፡ ያመኑ ፡ ብዙ ፡ ደጋግ ፡ ሴቶችም ፡ ነበሩ ፡ ወንዶችም ፡ ያመኑ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ።

፲፫ ፤ ወአእሚሮሙ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ በተሰሎንቄ ፡ ከመ ፡ መሀረ ፡ ጳውሎስ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቤ ርያ ፡

በተሰሎንቄ ፡ ያሉ፡ አይሁድም፡ ጳውሎስ፡ ወንጌልን ፡ በዚያ ፡ እንዳስተማረ፡ በሰሙ፡ ጊዜ ፡ ከዚያስ ፡ ማን ፡ አሰናብቶት ፡ ነው፡ ብለው ፡

ወመጽኡ ፡ ህየኒ ፡ ወሆከዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡

ሂደው ፡ ሕዝቡን ፡ አስቸገሯቸው ፡ ፩ ፡ ተሰ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ።

፲፬ ፤ ወፈነውዎ ፡ ለጳውሎስ ፡ ቢጽ ፡ ሶቤሃ ፡ ወአ ብጽሕዎ ፡ መንገለ ፡ ባሕር ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ምእመናን ፡ ጳውሎስን ፡ እየተ ከተሉ ፡ እየሸኙ ፡ እስከ ፡ ባሕሩ ፡ ድረስ ፡ አደረሱት ፡

ወነበሩ ፡ ሲላስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡

ሲላስና ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ግን ፡ በቤርያ ፡ ቀሩ ።

፲፭ ፤ ወእለሰ ፡ አስተፋነውዎ ፡ ለጳውሎስ ፡ መጽኡ ምስሌሁ ፡ እስከ ፡ ሀገረ ፡ አቴና ፡

ጳውሎስን ፡ የሸኙት ፡ ሰዎችም ፡ እስከ ፡ አቴና ፡ ድረስ ፡ ተከትለው ፡ መጡ ፡

ወለአኮሙ ፡ ኀበ ፡ ሲላስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡ ፍጡነ ፡ ይትልውዎ ፡

ፈጥነው ፡ ይከተሉት ፡ ዘንድ ፡ ተከተሉኝ ፡ በሏቸው፡ ብሎ፡ ከሲላስና ፡ ከጢሞቴዎስ ፡ ዘንድ ፡ ላካቸው ፡

ወሐሩ ፡

ተሰነባብተው ፡ ሄዱ ።

፲፮ ፤ ወእንዘ ፡ ይጸንሖሙ ፡ ጳውሎስ ፡ በአቴና ፡ ተምዕዐ ፡ መንፈሱ ፡ ሶበ ፡ ርእየ ፡ ያጣዕዉ ፡ ኵሉ ፡ ሀገር ፡

ወለአኮሙ ፡ ኀበ ፡ ሲላስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡ ፍጡነ ፡ ይትልውዎ ፡ ወሐሩ ፡ ብሎ ፡ ነበ ርና ፡ ጳውሎስ፡ በአቴና፡ ሆኖ ፡ ሲላስንና ፡ ጢሞቴዎስን ፡ ሲጠብቅ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ጣዖት ፡ ሲያመልኩ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ናው ፡ አዘነበት ።

፲፯ ፤ ወይትዋቀሦሙ ፡ ለአይሁድ ፡ በምኵራብ ፡

አይሁድን ፡ በምኵራቡ ፡ ይከራከራቸው ፡ ነበር ፡

ወበምሥያጥ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ፡ ለዘተራከቦሙ ፡

ባደባባዩም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያገኛቸውን ፡ ሁሉ ፡ ይከራከራቸው ፡ ነበር ።

፲፰ ፤ ወቦ ፡ እምውስተ ፡ ጠቢባን ፡ እለ ፡ እምትም ህርተ ፡ አፌቆሮስ ፡

አፌቆሮስ ፡ ከሚባል ፡ ሰው ፡ ከተማሩ ፡ ከፈላስፎች ፡ ወገን ፡

ወካልአን ፡ ይሰመዩ ፡ ረቃይያነ ፡

ረቃይያን ፡ ከሚባሉ ፡ ማለት ፡ ጨጨ ፡ ጆ ፡ ጆ ፡ እያሉ፡ እየደገሙ ፡ ከሚረጩ ። አንድም ፡ ቅጠል ፡ እየዘፈዘፉ ፡ ከሚረጩ፡ ከሌሎችም ፡ ወገን ፡

እለ ፡ ተአኀዝዎ ፡

ቦእለ፡ተአኀዝዎ፡ግጥም፡የተከራከሩት፡አሉ

ወመንፈቆሙ ፡ ይብሉ ፡ ምንተ ፡ ይፈቅድ ፡ ዝ ፡ ዘራ ዔ ፡ ነቢብ ፡

እኵሌቶቹ ፡ ይህ ፡ አፈ ፡ ዝናም ፡ ምን ፡ ይሻል ፡ አሉ ፡

ወካልአን ፡ ይቤሉ ፡ ትምህርተ ፡ አምላክ ፡ ሐዲስ ፡ ይሜህር ፡

ሌሎቹም ፡ እንግዳ ፡ የሚሆን ፡ የአምላ ክን ፡ ትምህርት ፡ ያስተምራል ፡ አሉ ፡ ሐዲስን ፡ ለትምህርትም ፡ ለአምላክም ፡ መቀጠል ፡ ነው ፡

እስመ ፡ ሰበከ ፡ ሎሙ ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡ አስተምሯቸዋልና ፡



ወትንሣኤሁ ፡ እሙታን ፡

ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ የመነሣቱንም ፡ ነገ ር ፡ አስተምሯቸዋልና ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ።

፲፱ ፤ ወወሰድዎ ፡ ቤተ ፡ ምኵናን ፡ ዘይሰመይ ፡ አር ዮስፋጎስ ፡

አርዮስፋጎስ ፡ ወደሚባል ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወሰዱት ፡ አርዮስፋጎስ ፡ ማለት ፡ መካነ ፡ ፍትሕ ፡ መካነ ፡ ጣዖት ፡ መካነ ፡ ጠቢባን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ምስትጉቡአ ፡ ጠቢባንም ፡ ይላል ፡ መካነ ፡ ጠቢባን ፡ ፈላስፎች ፡ ይሰበሰቡበታልና ፡ መካነ ፡ ጣዖት ፡ ጣዖት ፡ አቁመውበታል ፡ መካነ ፡ ፍትሕ ፡ ታሪክ ፡ እልፍርንዮስ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ምሽቱ ፡ ተሙዝ ፡ ትባላለች፡ አርዮስ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ለመዳት ፡ አን ድ ፡ ቀንም ፡ እሱ ፡ በሌለበት ፡ ገብቶ ፡ ሲወጣ ፡ ልጁ ፡ አየው ፡ ሳይነግርብኝ ፡ አይቀርም ፡ ብሎ ፡ ገደለው ፡ ቢመለስ ፡ ሙቶ ፡ አገኘው ፡ ይዞ ፡ ባደባባይ ፡ አስፈ ርዶ ፡ ገሎታልና ፡

ወይቤልዎ ፡ እስኩ ፡ ንግረነ ፡ ምንትኑ ፡ ዝ ፡ ነገር ፡ ዘትሜህር ፡ ትምህርተ ፡ ሐዲሰ ፡

ይህ ፡ የምታስተምረው ፡ እንግዳ ፡ ትም ህርት ፡ ምንድነው ፡ እስቲ ፡ ንገረን ።

፳ ፤ ንፈቅድ ፡ ንጠይቀ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡

ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልንረዳው ፡ እንወዳ ለን ፡ አሉት ፡

፳፩ ፤ ወሰብእ ፡ አቴናሰ ፡

የአቴና ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡

ወእለ ፡ ይነግዱ ፡ ኵሎሙ ፡ ህየ ፡ ባዕድ ፡ ትካዝ ፡ አልቦሙ ፡

ወደዚያ ፡ የሚሄዱትም ፡ ሌላ ፡ ግዳጅ ፡ አልነበራቸውም ፡

ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ለአፅምኦ ፡ ባሕቲቱ ፡

ትምህርቱን ፡ ለመስማት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንጅ ። አንድም ፡ ለመስማት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ እንሠራዋለን ፡ ብለው ፡ አያስቡም ፡ ነበር ፡

ወየኀሥሡ ፡ ዘይብሉ ፡ ወዘይሰንብቡ ፡

የሚመልሱትን ፡ ምላሽ ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር።

፳፪ ፤ ወቆመ ፡ ጳውሎስ ፡ ውስተ ፡ አርዮስፋጎስ ፡

ጳውሎስም ፡ አርዮስፋጎስ ፡ በሚባል ፡ ቦታ ፡ ቁሞ ፡

ወይቤሎሙ ፡ አንትሙ ፡ ሰብአ ፡ አቴና ፡ እሬእየክሙ ፡ ተአብዱ ፡ በኵሉ ፡

እናንት ፡ የአቴና ፡ ሰዎች ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ አእምሯችሁን ፡ አጥታችሁ ፡ አያችኋለሁ ።

፳፫ ፤ ወበጸሐየ ፡ ዝየ ፡ ርኢኩ ፡ ጣዖተክሙ ፡ ወምሥዋኢክሙ ፡ ኀበ ፡ ታመልኩ ፡

ከዚያም ፡ ደርሼ ፡ የምታመልኩትን ፡ ጣዖት ፡ የምትሠዉበትን ፡ ምሥዋዕ ፡ ባየሁ ፡ ጊዜ ፡

ወጽሑፍ ፡ ውስቴቱ ፡ ዘይብል ፡

በውስጡ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ተጽፎበታል ።

አንጽሑ ፡ ርእሰክሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ለመሆን ፡ ሰውነታችሁን ፡ ከኃጢአት ፡ ከጣዖት ፡ ልዩ ፡ አድርጉ ፡ የሚል ፡ ተጽፎበታል ። ታሪክ ፡ ጌታ ፡ በተሰቀለ ፡ ጊዜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የተደረገው ፡ ሁሉ ፡ ተአምራት ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ተደርጓል ፡ ዲዮናስዮስ ፡ ፀሐይ ፡ ጨለማ ፡ ሲሆን ፡ ጨረቃ ፡ ደም ፡ ስትሆን ፡ ከዋክብት ፡ ሲረግፉ ፡ ምድር ፡ ስትንቀጠቀጥ ፡ አይቶ ፡ አቀድ ፡ የሚባል ፡ ኮከብ ፡ አለ ፡ ያ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብት ፡ ብርሃናቸውን ፡ ይነሣል ፡ እሱ ፡ ወጥቶ ፡ ይሆን ፡ ብሎ ፡ ቢያይ ፡ ሳይወጣ ፡ አገኘ ። ዐቢይ ፡ ባሕር ፡ በተነዋወጠ ፡ ጊዜ ፡ ምድር ፡ ትንቀጠቀጣለች ፡ እሱ ፡ ተነዋውጦ ፡ ይሆን ፡ ብሎ ፡ ቢያይ ፡ ሳይነዋወጥ ፡ አገኘ ፡ ከዕቃ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ወነሥአ ፡ አርስጣላበ ፡ ዘውእቱ ፡ መጻልወ ፡ አልባብ ፡ ይላል ፡ የፍልስፍና ፡ መጣፍ ፡ አንሥቶ ፡ ሲመለከት ፡ እልመክኑን ፡ ወረደ ፡ ኀበ ፡ እሊዓሁ ፡ ወእሊዓሁ ፡ ሰቀልዎ ፡ የሚል ፡ ተጽፎ ፡ አገኘ ፡ ከወምበሩ ፡ ወርዶ ፡ ምንጣፍ ፡ ለብሶ ፡ ትቢያ ፡ ነስንሶ ፡ ፊቱን ፡ እየጸፋ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመር ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ኡሲፎስ ፡ አርያኖስ ፡ ይባላሉ ፡ አባታችን ፡ ነገሩ ፡ ምንድርነው ፡ ግለጥልን ፡ አሉት ፡ ዝም ፡ አላቸው ፡ ንገረን ፡ እንጅ ፡ እኛም ፡ እንዘንበት ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ አውቀኸው ፡ ቢቀር ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ አሉት ፡ እልመክኑን ፡ ወረደ ፡ ኀበ ፡ እሊዓሁ ፡ ወእሊዓሁ ፡ ሰቀልዎ ፡ አላቸው ፡ ጻፉት ፡ ብሏቸው ፡ በብርት ፡ ሰሌዳ ፡ ጽፈውታል ፡ ይህ ፡ በሆነ ፡ ባሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እያስተማረ ፡ እንደ ፡ ደምቢያ ፡ ሲደርስ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ የሚያስተምር ፡ መጥቷል ፡ አሉት ፡ ወዲህ ፡ አምጡልኝ ፡ አላቸው ፡ አመጡለት ፡ ይህ ፡ የምታስተምረው ፡ የተደረገበት ፡ ዘመኑ ፡ ምን ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ ወርኁስ ፡ ምን ፡ ወርኅ ፡ ነው ፡ ጊዜውስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ቀኑስ ፡ ምን ፡ ቀን ፡ ነው ፡ አለው ፡ ዘመኑ ፡ ዘመነ ፡ ዮሐንስ ፡ ወርኁ ፡ ወርኃ ፡ መጋቢት ፡ ዕለቱ ፡ ዕለተ፡ ዐርብ፡ ጊዜው፡ ቀትር ፡ ነው ፡ አለው ፡ አመንሁ ፡ አጥምቀኝ ፡ አለው ፡ አጥምቆ ፡ ባገሩ ፡ በአቴና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነት ፡ ሹሞት ፡ ሂዷልና፡ ወጽሑፍ፡ ውስቴቱ ፡ ዘይብል ፡ አንጽሑ ፡ ርእሰክሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ [illegible]

ናሁኬ ፡ ርእዩ ፡ ከመ ፡ ዘኢተአምሩ ፡ ታመልኩ ፡

እነሆ ፡ የምታመልኩትን ፡ የማታውቁት ፡ እንደ ፡ ሆነ፡ የማታውቁትን ፡ የምታመልኩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዕወቁ ።

፳፬ ፤ ወአንሰ ፡ እሜህረክሙ ፡ ታምልክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘገብረ ፡ ዓለመ ፡ ወምድረ ፡

እኔ ፡ ግን ፡ ሰማዩን ፡ ምድሩን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታመልኩት ፡ ዘንድ ፡ አስተምራችኋለሁ ፡

ወኵሎ ፡ ዘውስቴቶሙ ፡

በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃን ፡ ከዋክብትን ፡ መላእክትን ፡ በምድር ፡ ያሉ ፡ ዕፀው ፡ አዕባንን ፡ እንስሳት ፡ አራዊትን ፡ ደቂቀ ፡ አዳምን ፡ የፈጠረ ፡

ዘውእቱ ፡ እግዚአ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡

በሰማይ ፡ በምድር ፡ ምሉእ ፡ የሚሆን ፡ ሰማይን ፡ ምድርን ፡ የሚገዛ ፡

ወኢይነብር ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ ዘገብሮ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡

የሰው ፡ እጅ ፡ በሠራው ፡ ቤት ፡ ተወስኖ ፡ የማይኖር ፡ ም ፡ ፮ ፡ ፵፰ ።

፳፭ ፤ ወኢይትለአኮ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡

የሰው ፡ እጅ ፡ ያልፈጠረው ፡

ወውእቱ ፡ ይሁብ ፡ ለኵሉ ፡ ወኢይጽህቅ ፡ ምንተኒ ፡

እሱ ፡ ለሌላው ፡ ይሰጣል ፡ እንጅ ፡ ከሌላው ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የማይሻ ።

ወውእቱ ፡ ይሁብ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ነፍሰ ፡

ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ደመ ፡ ነፍስን ፡

ወሕይወተ ፡

ነባቢት ፡ ነፍስን ፡ የፈጠረ ፡

ወገብረ ፡ ኵሎ ፡ ኀቡረ ፡

ነፍስና ፡ ሥጋን ፡ አዋሕዶ ፡ የፈጠረ ፡

[illegible]

፳፮ ፤ ወኵሎ ፡ አሕዛበ ፡ እምአሐዱ ፡ እጓለ ፡ እመ ሕያው ፡

ካንድ ፡ ከአዳም ፡ ሕዝብና ፡ አሕዛብን ፡ የፈጠረ ፡

ከመ ፡ ይንበሩ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ገጸ ፡ ምድር ፡

ብዝኀ ፡ ወተባዝኁ ፡ ባለው ፡ ቃል ፡ በምድር ፡ በዝተው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ዘዳግ ፡ ፴፪ ፡ ፰ ።

፳፯ ፤ ወሠርዐ ፡ ዕድሜሁ ፡ ወዐመታቲሁ ፡ መጠነ ፡ ይነብሩ ፡ በዘየኀሥሥዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ በሚሹት ፡ ገንዘብ ፡ የሚሹበትን ፡ ያህል ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩትን ፡ ዘመን ፡ ወሰነ ፡ ሰባ ፡ ሰማንያ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ።

እመ ፡ ይረከብዎ ፡ወያደምዕዎ ፡

ምናልባት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚሹት ፡ ሰዎች ፡ ያገኙት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሐተታ ፡ አሁን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መገኘት ፡ መጠራጠር ፡ አይደለም፡ የነሱን ፡ መሻት፡ መጠራጠር ፡ ነው ፡

ወኢኮነ ፡ ርሑቀ ፡ እምኵልነ ፡

እመ ፡ ይረከብዎ ፡ ወያደምዕዎ ፡ ብዬ ፡ ብናገር ፡ ከሁላችን ፡ የራቀ ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ።

፳፰ ፤ እስመ ፡ ቦቱ ፡ ነሐዩ ፡ ወንትሐወስ ፡ ወንሄሉ ፡

በሱ ፡ ሕያዋን ፡ ሆነን ፡ እንኖራለንና ፡ ንትሐወስ ፡ በሞት ፡ ንሄሉ ፡ በመቃብር ። አንድም ፡ ንትሐወስ ፡ በሞት ፡ ንሄሉ ፡ በመቃብር ፡ ነሐዩ ፡ በትንሣኤ ። አንድም ፡ ንሄሉ ፡ በመቃብር ፡ ነሐዩ ፡ በትንሣኤ ፡ ንትሐወስ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ በክብር ፡



www.ethiopianorthodox.org

ወሀለዉ፡ ጠቢባን ፡ ሰብእ ፡ እምውስቴትክሙ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ከመ ፡ ፍጥረትነ ፡ እምኔሁ ፡

ከናንተም ፡ ወገን ፡ ባሕርያችን ፡ ከሱ ፡ እንደ፡ ተገኘ፡ የሚናገሩ፡ ፈላስፎች፡አሉ ።

፳፱ ፤ ወእንዘ ፡ ዘመድነ ፡ እንከ ፡ እምኔሁ ፡ ንሕነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኢርቱዕ ፡ ናስተማስሎ ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ፡ ወበእብን ፡ ዘግሉፍ ፡ በኪነ ፡ እጓለ ፡ እመ ሕያው ፡ ወበአእምሮቱ ።

ባሕርያችንም ፡ ከሱ ፡ ከተገኘ ፡ እግዚአ ብሔርን ፡ በሰው ፡ ዕውቀት ፡ በሰው ፡ ጥ በብ ፡ ከዕንጨት ፡ ከደንጊያ ፡ ተቀርጾ ፡ ከወርቅ ፡ ከብር ፡ ተመትቶ ፡ በተሠራ ፡ ጣዖት ፡ ልንመስለው ፡ አይገባም ።

ኢይደሉኬ ፡ ናስተማስል ፡ መለኮቶ ፡

ጌትነቱን ፡ በጣዖት ፡ ልንመስለው ፡ አይ ገባም ፡ ኢሳ ፡ ፵ ፡ ፲፰ ። ዘፍጥ ፡ ፩ ፡ ፳፯ ።

፴ ፤ ወዘቀዲሙሰ ፡ መዋዕለ ፡ ኢያእምሮ ፡ አሰሰለ ፡ እግዚአብሔር ።

አለማወቅ ፡ ሠልጥኖበት ፡ የነበረ ፡ የቀደ መውን ፡ ዘመን ። አንድም ፡ ኢያእምሮ ፡ መዋዕል ፡ ዘቀዲሙ ፡ በቀደመ ፡ ዘመን ፡ ሠልጥኖ ፡ የነበረ ፡ ድንቁርናን ፡ እግዚአ ብሔር ፡ አሳልፎታልና ፡

ወይእዜ ፡ ባሕቱ ፡ አዘዘ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ይነስሑ ፡ በኵለሄ ፡

ዛሬ ፡ ግን ፡ ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ንስሓ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ነስሑ ፡ ብሎ ፡ አስተማረ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፮ ። ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፵፯ ።

፴፩ ፤ እስመ ፡ ዐቀመ ፡ ዕለተ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ይኴን ን ፡ ዓለመ ፡ በጽድቅ ።

ይኴንን ፡ ዓለመ ፡ በጽድቅ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ዕውነት ፡ ፈርዶ ፡ በዕውነት ፡ ዓለ ሙን ፡ የሚያሳልፍባትን ፡ ቀን ፡ ወስኗ ልና ፡

ላዕለ ፡ እደዊሁ ፡ ለብእሲ ፡ ዘሠርዖ ፡ ወሜጠሙ ፡ ኀበ ፡ ሃይማኖት ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ኪያሁ ፡ በአንሥኦ ፡ እሙታን ፡

ባዋሐደው ፡ እሱን ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ በማስነሣቱ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ከክህደት፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ በመለሰ ፡ በሱ ፡ ሥል ጣን ፡ ይኴንን ፡ ላለው ፡ ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፲፬ ።

፴፪ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ ሕይወተ ፡ እሙታን ፡

ኪያሁ ፡ በአንሥኦ ፡ እሙታን ፡ ያለውን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡

መንፈቆሙሰ ፡ ሰሐቅዎ ፡

እኩሌቶቹ ፡ ሳቁበት ፡ ሰዱቃውያን ፡ ና ቸው ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ የለም ፡ ባዮች ፡ ናቸውና ፡

ወካልአን ፡ ይቤልዎ ፡ ናፀምአከ ፡ በእንተ፡ዝ ፡ ካልአ ፡ ጊዜ ፡

እኩሌቶቹ ፡ ግን ፡ የትንሣኤ ፡ ሙታንንስ ፡ ነገር ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ትነግረናለህ ፡ አሉት፡ ፈሪሳውያን ፡ ናቸው ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ።

፴፫ ፤ ወወፅአ ፡ ጳውሎስ ፡ እማዕከሎሙ ፡

ጳውሎስም ፡ ከመካከላቸው ፡ ተለይቶ ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ ፡

፴፬ ፤ ወቦ ፡ ዕደው ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ ወተለውዎ ፡

ከነዚያም ፡ ወገን ፡ አምነው ፡ የተከተሉት፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡

ወአሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ እመኳንንት ፡ ዘአርዮስፋጎስ ፡

አምነው፡ከተከተሉትም፡አንዱ፡በአርዮስፋ ጎስ ፡ ካሉ ፡ ከፈላስፎች ፡ ወገን ፡ የሚሆን፡ ዲዮናስዮስ ፡ ነው ። አንድም ፡ ዘአርአዮ ፡ ጳጊጢስ ፡ ይላል ፡ በአርዮስፋጎስ ፡ ካሉ ፡ ከፈላስፎች ፡ ወገን ፡ ጳጊጢስ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ያስተማረው ፡ ዲዮናስዮስ ፡ ነው ፡



ወብእሲት ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ድማርስ ፡

ድማርስ ፡ የምትባል ፡ ሚስቱም ፡ ነበ ችረ ፡

ወቦ ፡ ባዕዳንሂ ፡ እለ ፡ ምስሌሆሙ ፡

አምነው ፡ እሱን ፡ የተከተሉ ፡ ከእነሱ ፡ ጋራ ፡ ሌሎችም ፡ ነበሩ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ፡ ክፍል ፡ ፴፬ ፡

፩ ፤ ወእምዝ ፡ ወፅአ ፡ ጳውሎስ ፡ እምአቴና ፡ ወሖረ ቆሮንቶስ ፡

ከዚህ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ ከአቴና ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ሄደ ።

፪ ፤ ወረከበ ፡ አሐደ ፡ አይሁዳዌ ፡ ዘስሙ ፡ አቂላ ፡

በቆሮንቶስም ፡ አቂላስ ፡ የሚባል፡ አንድ ፡ አይሁዳዊ ፡ አገኘ ፡

ወሀገሩ ፡ ጳንጦስ ፡

አገሩ ፡ ጳንጦስ ፡ የሚሆን ፡

ወበጽሐ ፡ ሶቤሃ ፡ እምአጣልያ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ከአጣልያ ፡ ተሰዶ ፡ ወደ ፡ ቆሮንቶስ ፡ መጣ ፡

ወብእሲቱ ፡ ጵርስቅላ ፡

ምሽቱም ፡ ጵርስቅላ ፡ ትባላለች ፡

እስመ ፡ አዘዘ ፡ ቀላውዴዎስ ፡ ይስድዱ ፡ አይሁደ ፡ እምሮሜ ፡

ቀላውዴዎስ፡ አይሁድ፡ (ይሰደዱ)፡ ከሮም፡ ወጥተው ፡ ይሰደዱ ፡ ብሎ ፡ አዋጅ፡ ነግሮ፡ ነበርና ። አንድም ፡ ይስድዱ ፡ አይሁደ ፡ እምሮሜ ፡ አይሁድን ፡ ከሮም ፡ አስወጥ ታችሁ ፡ ስደዱ ፡ ብሎ ፡ አዋጅ ፡ ነግሮ ፡ ነበርና ፡ ሮሜ ፡ ፲፮ ፡ ፫ ።

፫ ፤ ወመጽአ ፡ ኀቤሆሙ ፡

እነሱ ፡ ወዳሉበት ፡ መጣ ፡

እስመ ፡ የኀብር ፡ ግብረ ፡ ሥራሆሙ ፡

በሥራ ፡ ይተባበሩ ፡ ነበርና ፡

እስመ ፡ ገበርተ ፡ ሰቀላ ፡ እሙንቱ ፡

ድንኳን ፡ ሰፎች ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡

ወነበረ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ኀቡረ ፡

በጥበብ ፡ አንድ ፡ ነበሩና ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ኖረ ፡

ወይትጌበሩ ፡ ክዳናተ ፡ ሰቀላ ፡

ድንኳን ፡ ይሰፉ ፡ ነበርና ፡ ሐተታ ፡ ሰቀላ ፡ ስፉ ፡ ክዳናት ፡ ልብስነቱ ። አንድም ፡ ክዳናተ ፡ ወሰቀላ ፡ ሰቀላ ፡ ትርሽማው ፡ ክዳናት ፡ መላጃኑ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ።

፬ ፤ ወጳውሎስ ፡ ይትዋቀሦሙ ፡ በምኵራብ ፡ በኵሉ ፡ ሰናብት ፡

ጳውሎስም ፡ ቅዳም ፡ ቅዳም ፡ ከምኵራቡ ፡ እየገባ ፡ ይከራከራቸው ፡ ነበር ፡

ወያአምኖሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ወለአረሚ ፡

እየተከራከረ ፡ አይሁድንም ፡ አረማውያ ንንም ፡ ያሳምናቸው ፡ ነበር ፡

፭ ፤ ወወረዱ ፡ እመቄዶንያ ፡ ሲላስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡

ሲላስና ፡ ጢሞቴዎስም ፡ ከመቄዶንያ ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ሄዱ ።

ወነገሮሙ ፡ ጳውሎስ ፡ ለአይሁድ ።

ጳውሎስም ፡ ለአይሁድ ፡ አስተማራቸው፡

ወአስምዖሙ ፡ ከመ ፡ ኢየሱስ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ።

ዳንኤል ፡ መቅደስ ፡ ትትሐነጽ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ ብሎ ፡ የተናገረለት ፡ ክርስቶስ ፡ ኤርምያስ ፡ ለሊሁ ፡ ኢየሱስ ፡ አምላክ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ይመጽእ ፡ ብሎ ፡ የተናገረለት ፡ ኢየሱስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ኤርምያስ ፡ ለሊሁ ፡ ኢየሱስ ፡ አም ላክ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ይመጽእ ፡ ብሎ ፡ የተናገረለት ፡ ኢየሱስ ፡ ዳንኤል ፡ መቅ

www.ethiopianorthodox.org

ደስ ፡ ትትሐነጽ ፡ እስከ፡ ክርስቶስ፡ ንጉሥ
ብሎ ፡ የተናገረለት ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ አስረዳቸው ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፲፱ ፡ ፲፰ ።

፮ ፤ ወተዋቀሥዎ ፡

እነሱ ፡ ግን ፡ ተከራከሩት ፡ ወንጌል ፡ እን
በለ ፡ አሪት ፡ ጥምቀት ፡ እንበለ ፡ ግዝረት ፡
አትረባም ፡ አትጠቅምም ፡ ብለው ፡

ወፀረፉ ፡

ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡
ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ አሉ ፡

ወእምዝ ፡ ነገፈ ፡ አልባሲሁ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልብሱን ፡ አራግፎ ፡

ወይቤሎሙ ፡ ደምክሙ ፡ ላዕለ ፡ ርእስክሙ ፡

ፍዳችሁ ፡ በራሳችሁ ፡ ነው ፡

ንጹሕ ፡ አነ ፡ እንከ ፡ እምደመ ፡ ኵልክሙ ፡

ከእንግዴህ ፡ ወዲህ ፡ እኔ ፡ በናንት ፡ ከሚ
መጣው ፡ ፍዳ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ።

እምይእዜሰ ፡ አሐውር ፡ መንገለ ፡ አሕዛብ ፡

እንግዲህስ ፡ ወዲህ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ሂጄ፡
አሕዛብን፡ አስተምራለሁ ፡ ብሎ ፡

፯ ፤ ወኀሊፎ ፡ እምህየ ፡ ቦአ ፡ ቤተ ፡ ቲጦስ ፡

ከዚያ ፡ አልፎ ፡ ከቲጦስ ፡ ቤት ፡ ገባ ፡

ብእሲ ፡ ፈራሄ ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ብሎ ፡ ለቲ
ጦስ ፡ ይቀጥላል ፡

ወቤቱ ፡ ጎረ ፡ ምኵራብ ፡

ፈራሂ ፡ እግዚአብሔርነቱም ፡ ሊታወቅ ፡
ቤቱ ፡ ከምኵራቡ ፡ አጠገብ ፡ ነበር ፡ ሐ
ተታ ፡ ምነው ፡ ከሌላ ፡ ቢሆን ፡ ፈራሄ ፡
እግዚአብሔርነቱን፡ ያስቀርበታል ፡ ብሎ፡
በተጡን ፡ መናገር ፡ ነው ።

፰ ፤ ወቀርስጶስሂ ፡ መጋቤ ፡ ምኵራብ ፡ አምነ ፡ ም
ስለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብአ ፡ ቤቱ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡

የምኵራቡ ፡ ሹም ፡ ቀርስጶስም ፡ ከቤተ ፡
ሰቦቹ ፡ ጋራ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ አመነ ፡

ወብዙኃን ፡ እምሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ አምኑ ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ ወተጠምቁ ።

በቆሮንቶስ ፡ ካሉ ፡ ሰዎችም ፡ በእግዚአ
ሔር ፡ አምነው ፡ የተጠመቁ ፡ ብዙ ፡
ነበሩ ።

፱ ፤ ወይቤሎ ፡ እግዚእነ ፡ ለጳውሎስ ፡ በራእየ ፡
ሌሊት ፡ ኢትፍራህ ፡

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጳውሎ
ስን ፡ ሌሊት ፡ በራእይ ፡ አይዞህ ፡

ንግር ፡ ወኢታርምም ፡

አስተምር ፡ ዝም ፡ አትበል ፡ አለው ፡
፩ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፫ ።

፲ ፤ እስመ ፡ ሀለውኩ ፡ አነ ፡ ምስሌከ ፡

እኔ ፡ በረድኤት ፡ አልለይህምና ፡

ወአልቦ ፡ ዘየሐምመከ ፡

መከራ፡ የሚያጸናብህ፡የለምና፡ኢትፍራህ ፡

እስመ ፡ ብዙኅ ፡ ሕዝብ ፡ ብየ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ሀገር ።

በዚህች ፡ አገር ፡ በኔ ፡ የሚያምኑ ፡ ብዙ ፡
ምእመናን ፡ አሉና፡ ንግር፡ ወኢታርምም፡
አለው ፡ኤር፡ ፩፡፳፫።ሆሴ፡፪፡፳፫።ዮሐ፡፲፡፲፮።

፲፩ ፤ ወነበረ ፡ ጳውሎስ ፡ ዓመተ ፡ ወስድስተ ፡ አው
ራኀ ፡ እንዘ ፡ ይሜህሮሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡
በቆሮንቶስ ።

ጳውሎስ ፡ ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ወንጌ
ልን ፡ እያስተማረ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ኖረ ።

፲፪ ፤ ወተባጽሕዎ ፡ አይሁድ ፡ ለጳውሎስ ፡ ኅበ ፡
ጋልዩስ ፡ መልአከ ፡ አካይያ ፡

አይሁድም ፡ ጳውሎስን ፡ አቅ...

ው ፡ ወደ ፡ አካይያው ፡ ሹም ፡ ወደ ፡ ጋል
ዩስ ፡ አደረሱት ፡

ወአምፅእዎ ፡ ኀበ ፡ ዐውድ ።

ወደ ፡ አደባባይ ፡ አመጡት ።

፲፫ ፤ ወይቤልዎ ፡ በዘአልቦ ፡ ሕግ ፡ ይሜህር ፡ ለሰ
ብእ ፡ ያምልክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ ያመልኩት ፡ ዘንድ ፡
የማይገባ ፡ ሥራት ፡ ያስተምራል ። አን
ድም ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማይገባ ፡ ሥ
ራት ፡ ያመልኩት ፡ ዘንድ፡ ያስተምራል ፡
አሉት ።

፲፬ ፤ ወፈቂዶ ፡ ጳውሎስ ፡ይክሥት ፡ አፉሁ ፡ወይ ፡
ንግሮሙ ፡

ጳውሎስም ፡ ሊናገር ፡ ወዶ ፡ ሳለ ፡

ወአውሥአ ፡ መልአክ ፡ ጋልዩስ ፡ ለአይሁድ ።

ሹሙ ፡ ጋልዩስ፡ ለአይሁድ ፡ መለሰ ፡

ወይቤሎሙ፡አንትሙ፡አይሁድ፡ለእመቦ፡ዘገፍዐክሙ፡

እናንት ፡ አይሁድ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የቀማ
ችሁ ፡ መቀማት ፡ ቢኖር ፡

ወቦ ፡ ጌጋይ ፡ እምአስተዋቀሥኩክሙ ፡

የበደላችሁ ፡ በደል ፡ ቢኖር ፡ ባበባልኋ
ችሁ ፡ ነበር ፡

ወእምአፅማዕኩክሙ ፡

ዳኝነትም ፡ በሰማኋችሁ ፡ ነበር ። ብሎ ፡
መለሰላቸው ፡

፲፭ ፤ ወእመሰ ፡ ትትካሐዱ ፡ በእንተ ፡ ሕግክሙ ፡

ስለ ፡ ሕጋችሁ ፡ ግን ፡ አሪት ፡ ትበልጣ
ለች ፡ ወንጌል ፡ ትበልጣለች ፡ እያላሁች ፡
የምትከራከሩ ፡ ከሆነ ፡

ወበእንተ ፡ አስማተ ፡ ሰብእ ፡ ለሊክሙ ፡ አእምሩ ፡

ሙሴ ፡ ይበልጣል ፡ ክርስቶስ ፡ ይበልጣል፡
እያላችሁ ፡ የምትከራከሩ ፡ ከሆነ ፡ ራሳ
ችሁ ፡ ዕወቁ ።

አንሰ ፡ ኢይፈቅድ ፡ እስማዕ ፡ ዘከመ ፡ ዝ ፡ ነገረ ፡

እኔ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ልሰማ ፡ አል
ወድም ፡ አላቸው ፡ ሐተታ ፡ የሃይማኖት ፡
ዳኝነት ፡ ኩርማን ፡ አጋማሽ ፡ አሞሌ ፡
ግማሽ ፡ የለውምና ፡ ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፳፱ ።
ዮሐ ፡ ፲፰ ፡ ፴፩ ።

፲፮ ፤ ወሰደድዎሙ ፡ እምኀበ ፡ ዐውድ ፡

ከአደባባይ ፡ አስወጥተው ፡ ሰደዷቸው ።

፲፯ ፤ ወአኀዝዎ ፡ ኵሎሙ ፡ አረማውን ፡ ለስቴንስ ፡
መጋቤ ፡ ምኵራብ ፡ ወዘበጥዎ ፡ በኀበ ፡ ዐውድ ፡

አረማውያንም ፡ ሁሉ ፡ የምኵራቡን ፡
ሹም ፡ ስቴንስን ፡ ይዘው ፡ በአደባባይ ፡
ደበደቡት ፡

ወኢየሐዝኖ ፡ ለጋልዩስ ፡ ወኢምንተኒ ፡ በእንቲአሁ ፡

ለጋልዩስም ፡ የስቴንስ ፡ መደብደብ ፡ አላ
ሳዘነውም ፡ ሐተታ ፡ የሹመት ፡ ጎባኑ ፡
ነውና ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፩ ።

፲፰ ፤ ወነበረ ፡ ጳውሎስ ፡ ዓዲ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ፡
ኀበ ፡ ቢጹ ፡

ጳውሎስም ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከምእመናን ፡
ዘንድ ፡ ኖረ ፡

ወፈነውዎ ፡ በሰላም ፡

ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ በፍቅር ፡
ሸኙተው ፡ ሰደዱት ፡

ወነገደ ፡ በባሕር ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ሶርያ ፡

በባሕር ፡ በመርከብ ፡ ተጭኖ ፡ ወደ ፡
ሶርያ ፡ ሄደ ፡

ወሀለዉ ፡ ምስሌሁ ፡ ጵርስቅላ ፡ ወአቂላ ፡

ጵርስቅላና ፡ አቂላም ፡ አብረውት ፡ ነበሩ ፡

ወተላፀየ ፡ ርእሶ ፡ ውስተ ፡ ፍንክራኦስ ፡

በፍንክራኦስም፡ በዓለ ፡ አንጽሖ፡ አደረገ ፡

እስመ ፡ ብፅዓት ፡ ቦ ፡

ብፅዓት ፡ ነበረበትና፡ ሐተታ፡ ብፅዓት ፡



www.ethiopianorthodox.org

ያለበት ፡ ሰው ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ጠጉሩን ፡ ተላጭቶ ፡ ገላውን ፡ ታጥቦ ፡ ልብሱን ፡ አንጽቶ ፡ መሥዋዕት ፡ አሠውቶ ፡ ማየ ፡ ምንዛሕ ፡ ተረጭቶ ፡ ከሰው፡ ይገናኛልና ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፳፬ ። ዘኍል ፡ ፮ ፡ ፱ ፡ ፲፰ ።

፲፱ ፤ ወበጽሑ ፡ ኤፌሶን ፡

ከክንክራኦስ ፡ ወጥተው ፡ ኤፌሶን ፡ ደረሱ፡

ወውእቱሰ፡ ቦአ፡ ምኵራበ፡ ወተዋቀሦሙ፡ ለአይሁድ፡

እሱም ፡ ከምኵራቡ ፡ ገብቶ ፡ ተከራክሮ ፡ አይሁድን ፡ አሳመናቸው ።

፳ ፤ ወአስተብቍዕዎ ፡ ይንበር ፡ ብዙኃ ፡ መዋዕለ ፡

ብዙ ፡ ቀን ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ሰንብት ፡ ብለው ፡ ማለዱት ፡

ወኢፈቀደ ፡

እሱ ፡ ግን ፡ ሊሰነብት ፡ አልወደደም ።

፳፩ ፤ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ፈነውዎ ፡ ይቤሎሙ ፡ እገብእ ፡ ካዕበ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እየተከተሉ ፡ በማለዱት ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢፈቅድልኝ ፡ ዳግመኛ ፡ ወደናንት ፡ እመለሳለሁ ፡

ወባሕቱ ፡ ይእዜሰ ፡ እፈቅድ ፡ ከመ ፡ እግበር ፡ በዓለ ፡ ዘይመጽእ ፡ በኢየሩሳሌም ፡

ዛሬ ፡ ግን ፡ የሚመጣውን ፡ በዓለ ፡ ሃምሳ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላከብር ፡ እወዳለሁ ፡

ወእመ ፡ ሠምረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እገብእ ፡ ኀቤክሙ፡ ለጵርስቅላ ፡ ወለአቂላ ፡ ኀደጎሙ ፡ ኤፌሶን ፡

እግዚአብሔር ፡ ቢፈቅድልኝ ፡ ወደናንት ፡ እመለሳለሁ ፡ ብሎ ፡ ጵርስቅላንና ፡ አቂላንን ፡ በኤፌሶን ፡ ትቷቸው ፡ ፩ ፡ ቆሮ፡ ፬ ፡ ፲፱ ። ያዕ ፡ ፬ ፡ ፳ ። ዕብ ፡ ፮ ፡ ፫ ።

፳፪ ፤ ወነገደ ፡ በባሕር ፡ ወወረደ ፡ ቂሣርያ ፡

በባሕር ፡ በመርከብ ፡ ተጭኖ ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ሄደ ፡

ወዐርገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወተአምኆሙ ፡

በቂሣርያም ፡ ምእመናን ፡ ካሉበት ፡ ገብቶ ፡ ተገናኛቸው ።

፳፫ ፤ ክፍል ፡ ፴፰ ። ወሖረ ፡ አንጾኪያ ፡

ከተገናኛቸውም ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ሄደ ፡

ወነበረ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ፡

በአንጾኪያም ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ኖረ ።

ወወፅአ ፡ ወሖረ ፡ ወኀለፈ ፡ በበንስቲት ፡ በብሔረ ፡ ፍርግያ ፡ ወገላትያ ፡

ከዚያም ፡ ወጥቶ ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ እያለ ፡ እያስተማረ ፡ ወደ ፡ ፍርግያ ፡ ወደ ፡ ገላትያ ፡ ሄደ ፡

ወአጽንዖሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አርድእት ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ህየ ፡ ላዕለ ፡ አሚን ፡ በእግዚእነ ፡ ክርስቶስ ።

ከዚያ ፡ ያሉ ፡ ምእመናንን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባመኑት ፡ እምነት፡ አጸናቸው ።

፳፬ ፤ ክፍል ፡ ፴፱ ። ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ አይሁዳዊ ፡ ዘስሙ ፡ አጵሎስ ፡ ዘእስክንድርያ ፡

የእስክንድርያ ፡ ሰው ፡ የሚሆን ፡ አጵሎስ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡

ብእሲ ፡ ጠቢብ ፡

ብልህ ፡ ዐዋቂ ፡

ወየአምር ፡ መጽሐፈ ፡

ነገር ፡ ያውቅ ፡ ነበር ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፮ ።

፳፭ ፤ ወበጽሐ ፡ ኤፌሶን ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ተሰዶ ፡ ኤፌሶን ፡ ደረሰ ፡

ወይክል ፡ ተናግሮ ፡

ምላሽ ፡ ያውቅ ፡ ነበር ፡

ወምሁር ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡

አሪትን ፡ የተማረ ፡ ነበር ፡



ወጸሃቂ ፡ በመንፈሱ ፡ ይንግር ፡ ወይምህር ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡

የጌታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ነገር፡ ያስተምር፡ዘንድ፡ይተጋ፡ነበር።አንድም፡ የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ነገር፡ተግቶ፡ያስተምር፡ ነበር፡ ይወርዳል፡ ይወለዳል፡እያለ፡

ወዳዕሙ ፡ በጥምቀተ ፡ ዮሐንስ ፡ ተጠምቀ ፡

ጥምቀተ፡ዮሐንስ፡ተጠምቆ፡ነበረ፡እንጅ፡እንደ፡ወረደ፡እንደ፡ተወለደ፡አላመነም፡ ነበር

፳፮ ፤ ወውእቱ፡ አኀዘ፡ ይንግር፡ ገሃደ፡ በምኵራብ፡

ገልጦ ፡ በምኵራብ ፡ ማስተማር ፡ ጀመረ ፡ ይወርዳል ፡ ይወለዳል ፡ እያለ ፡

ወሰምዕዎ ፡ ጵርስቅላ ፡ ወአቂላ ፡

ጵርስቅላና ፡ አቂላም ፡ ይወርዳል ፡ ይወለዳል፡ እያለ፡ ሲያስተምር፡ በሰሙት፡ጊዜ ፡

ወአቅረብዎ ፡ ኀበ ፡ ማኅደሮሙ ፡

ወደሚያድሩበት ፡ ቤት ፡ አስጠግተው ፡

ወአጠየቅዎ ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጹመ ።

የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ አስረዱት ፡ አለ፡ ይወርዳል ፡ ይወለዳል ፡ ብለህ ፡ የምታስተምርለት ፡ ወርዷል ፡ ተወልዷል ፡ ብለው፡ ፈጽመው ፡ አስረዱት ።

፳፯ ፤ ወፈቀደ ፡ ይሑር ፡ አካይያ ፡

ወደ ፡ አካይያ ፡ ሊሄድ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡

ወአብጽሕዎ ፡ ቢጹ ፡ ወጸሐፉ ፡ ሎቱ ፡ ኀበ ፡ አርድእት ፡ ይትወከፍዎ ፡

ቢጹ ፡ አቂላና ፡ ጵርስቅላ ፡ ናቸው ፡ ከምእመናን ፡ ዘንድ ፡ ተቀበሉት ፡ ብለው፡ ክታብ ፡ ጽፈው ፡ ሰደዱት ፡

ወበጺሖ ፡ ኀቢሆሙ ፡ ነገሮሙ ፡ ብዙኀ ፡ ለእለ ፡ አምኑ ፡ በጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡

ወደነሱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በወንጌል ፡ ላመኑት፡ ፍጹም፡ ትምህርት፡ አስተማራቸው ፡

ወረድኦሙ ፡ ለመሃይምናን ፡ ዐቢየ ፡ ረድኤተ ፡

ምእመናንንም፡ በብዙ፡ ወገን ፡ ረዳቸው ።

፳፰ ፤ እስመ ፡ ይትጋደሎሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ፈድፋደ ፡ በቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ እንዘ ፡ ሀለዉ ፡ ጉቡአን ፡ ገሃደ ፡

ይልቁንም ፡ ተሰብስበው ፡ ሳለ ፡ በጉባኤ ፡ ገልጦ ፡ እየተከራከረ ፡ አይሁድን ፡ ይረታቸው ፡ ነበርና ፡

ወያበጽሕ ፡ ሎሙ ፡ እምውስተ ፡ መጻሕፍት ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ።

ዳንኤል ፡ መቅደስ ፡ ትትሐነጽ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ ብሎ ፡ የተናገረለት ፡ ክርስቶስ ፡ ኤርምያስ ፡ ለሊሁ ፡ ኢየሱስ ፡ አምላክ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ይመጽእ ፡ ብሎ፡ የተናገረለት ፡ ኢየሱስ፡ እንደ፡ሆነ። አንድም፡ኤርምያስ፡ለሊሁ፡ኢየሱስ፡አምላክ ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ይመጽእ ፡ ብሎ ፡ የተናገረለት ፡ ኢየሱስ ፡ ዳንኤል ፡ መቅደስ ፡ ትትሐነጽ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ ብሎ ፡ የተናገረለት ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከመጻሕፍት ፡ እየጠቀሰ ፡ ያስረዳቸው ፡ ነበርና ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፳፪ ፡ ፲፯ ፡ ፫ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

፩ ፤ ወእምዝ ፡ እንዘ ፡ አጵሎስ ፡ ሀሎ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ኀለፈ ፡ ጳውሎስ ፡ እንተ ፡ ላዕላይ ፡ ዐጸድ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አጵሎስ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ሳለ ፡ ጳውሎስ ፡ ደጋ ፡ ደጋውን ፡ ሄደ ፡

ወበጽሐ፡ኤፌሶን፡ወረከበ፡ በህየ፡ ኅዳጣነ፡ አርድእተ ፡

ኤፌሶንም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ ጥቂቶች፡ምእመናንን፡ አገኘ ፡ ዐሥራ፡ ሁለት ፡ ብሎ ፡ ያመጣቸዋል ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ቦኑ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ መንፈሰ ፡ ቅዱሰ ፡ እምዘአመንክሙ ፤

ካመናችሁ ፡ ጀምሮ ፡ በውኑ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብላችኋልን ፡ የተቀበላችሁት ፡ መቀበል ፡ አለን ፡ አላቸው ፡

ወይቤልዎ፡ኢ.ሰማዕናሁ፡ጥቀ፡ከመ፡ቦ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡

እኛስ ፡ ስንኳን ፡ መቀበል ፡ መኖሩንም ፡ ሰምተን ፡ አናውቅም ፡ አሉት ፡ ም ፡ ፲ ፡ ፵፯። ዮሐ ፡ ፯ ፡ ፴፱ ።

፫ ፤ ወይቤሎሙ ፡ በምንትኑ ፡ ተጠመቅሙ ፤

እንኪያ ፡ በምን ፡ ተጠመቃችሁ ፡ አላቸው ፡

ወይቤልዎ ፡ በጥምቀተ ፡ ዮሐንስ ።

በዮሐንስ ፡ ጥምቀት ፡ ነው ፡ አሉት ።

፬ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ጳውሎስ ፡ ዮሐንስ ፡ አጥመቀ ፡ በጥምቀተ ፡ ንስሓ ፡ እንዘ ፡ ይሰብክ ፡ ከመ ፡ ይእመኑ ፡ በዘይመጽእ ፡ እምድኅሬሁ ፡

ጳውሎስም ፡ ዮሐንስ ፡ ከሱ ፡ በኋላ ፡ በሚመጣው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ፡ እያስተማረ ፡ ለጌታ ፡ የሚያበቃ፡ ጥምቀት ፡ አጠመቀ ፡ አላቸው ፡

ዘውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

ይኸውም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

፭ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ ተጠምቁ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡አምነው፡ተጠመቁ።

፮ ፤ ወወደየ ፡ እደዊሁ ፡ ጳውሎስ ፡ ዲቤሆሙ ፡ ወወረደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌሆሙ ፡

እጁንም ፡ በጫነባቸው ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አደረባቸው ፡

ወነበቡ ፡ በነገረ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርት ፡

ሁሉም ፡ በየሀገሩ ፡ ቋንቋ ፡ ተናገሩ ፡

ወተነበዩ ፡

ምስጢር ፡ ተረጐሙ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፲፯ ። ፲ ፡ ፵፮ ፡ ፵፯ ።

፯ ፤ ወየአክሉ፡ኵሎሙ፡ዐሠርተ፡ወክልኤተ፡ዕደወ፡

ሁሉም፡ዐሥራ፡ሁለት፡ያህል፡ይሆኑ፡ነበር፡

፰ ፤ ወቦአ ፡ ጳውሎስ ፡ ምኵራበ ፡ ወነገረ ፡ ገሃደ ፡

ጳውሎስም ፡ ከምኵራቡ ፡ ገብቶ ፡ ገልጦ ፡ አስተማረ ፡

ወነበረ ፡ ሠለስተ ፡ አውራኀ ፡ ይትዋቀሦሙ ፡ ወያአምኖሙ ፡ በእንተ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፡

እየተከራከረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ወንጌልን ፡ እያሳመናቸው ፡ ሦስት፡ ወር ፡ ኖረ ።

፱ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ ክሕዱ ፡ ወተንሥኡ ፡ ወአሕሠሙ ፡ ዲበ ፡ ትምህርት ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ በቅድመ ፡ ጉባኤ ፡ አሕዛብ ።

አናምንም ፡ ብለው ፡ ተነሥተው፡ በጉባኤ፡ የእግዚአብሔር ፡ ትምህርት ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ ያሉ ፡ አሉ ፡

ወኀደጎሙ ፡ ጳውሎስ ፡ ወነሥአሙ ፡ ለአርድእት ፡

ጳውሎስም ፡ ከነዚያ ፡ ተለይቶ ፡ ምእመናንን ፡ አስከትሎ ፡ ሄደ ፡

ወኵሎ ፡ አሚረ ፡ ይነግሮሙ ፡ በመምህረ ፡ ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ ጡራዮስ ፡

ጡራዮስ ፡ በሚባል ፡ ሰው ፡ መምህርነት ፡ ገብቶ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ። አንድም ፡ በምምህረ ፡ ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ ጡራዮስ ፡ ጡራዮስ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ በሚያስተምርበት ፡ ቦታ ፡ ገብቶ ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ፡

ወበምኵናነ ፡ መላእክት ፡

አለቆች ፡ በሚፈርዱበት ፡ ቦታ ፡ ሆኖ ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ፡ ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ። ም ፡ ፱ ፡ ፪ ።



፲ ፤ ወገብረ ፡ ከመዝ ፡ ክልኤ ፡ ዓመተ ፡

እንዲህ፡ እያስተማረ፡ ሁለት፡ ዓመት፡ ኖረ፡

እስከ ፡ ሰምዑ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ እስያ ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር ፡ አይሁድ ፡ ወአረሚ ፡

በእስያ ፡ ያሉ ፡ አይሁድም ፡ አረማውያንም ፡ ሁሉ ፡ ወንጌልን፡ እስኪረዱ፡ ድረስ፡

## ክፍል ፡ ፴፲ ።

፲፩ ፤ ወዐቢየ ፡ ኀይለ ፡ ይገብር ፡ እግዚአብሔር ፡ በእደዊሁ ፡ ለጳውሎስ ።

እግዚአብሔርም ፡ በጳውሎስ ፡ ቃል ፡ በጳውሎስ ፡ ሥልጣን ፡ ደጋግ ፡ ተአምራትን ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ፫ ።

፲፪ ፤ ወይወስዱ ፡ እምጽንፈ ፡ ልብሱ ፡ ወሰበኑ ፡ መቲሮሙ ፡ ወያነብሩ ፡ ዲበ ፡ ድውያን ።

ከልብሱ ፡ ዘርፍ ፡ ከመጠምጠሚያው ፡ እየቀደዱ ፡ ወስደው ፡ በድውያን ፡ ላይ ፡ ይጥሉት ፡ ነበር ፡

ወየሐይዉ ፡

ድውያኑም ፡ ይድኑ ፡ ነበር ፡

ወአጋንንት ፡ እኩያን ፡ ይወፅኡ ፡

አጋንንትም ፡ እየወጡ ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፭ ፡ ፲፭ ።

፲፫ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ አኀዙ ፡ እምአይሁድ ፡ ይዑዱ፡ ወይርቅዩ ፡

ከአይሁድም ፡ ወገን ፡ እየዞሩ ፡ ጨጨ ፡ ጀጀ ፡ እያሉ ፡ እየደገሙ ። አንድም ፡ ቅጠል ፡ እየዘፈዘፉ ፡ የሚረጩ ፡ ነበሩ ፡

ወይጼውዑ ፡ ሎሙ ፡ ለአጋንንት ፡ እኩያን ፡ በስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡

የጌታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስንም፡ ስም፡ በአጋንንት ፡ ይጠሩባቸው ፡ ነበር ፡

ወይቤልዎሙ ፡ ናምሕለክሙ ፡ በስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ዘጳውሎስ ፡ ይሜህር ፡ በስሙ ፡

ጳውሎስ ፡ ስሙ ፡ ሕይወት ፡ መድኃኒት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሚያስተምርለት ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ውጡ ፡ ብለን ፡ እናዝዛችኋለን ፡ እያሉ፡ ሉቃ ፡ ፱ ፡ ፵፱ ።

፲፬ ፤ ወእሉ ፡ እለ ፡ ከመዝ ፡ ይገብሩ ፡ አይሁድ ፡ እሙንቱ ፡ ደቂቀ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ዘስሙ ፡ አስቄዋ ፡

እንዲህም ፡ የሚያደርጉ ፡ አስቄዋ ፡ የሚባል ፡ የሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ልጆች ፡ አይሁድ ፡ ናቸው ፡

ወሰብዐቱ ፡ እሙንቱ ፡

ቍጥራቸውም ፡ ሰባት ፡ ነበር ።

፲፭ ፤ ወተሠጥዎሙ ፡ ውእቱ ፡ ጋኔን ፡ እኩይ ፡

ያ ፡ ቢስ ፡ ጋኔንም ፡ መለሰላቸው ፡

ወይቤሎሙ ፡ በኢየሱስኒ ፡ አአምን ፡

በኢየሱስ ፡ አምናለሁ ፡

ወለጳውሎስኒ ፡ አአምሮ ፡

ጳውሎስንም ፡ አውቀዋለሁ ፡

አንትሙ ፡ እንከ ፡ መኑ ፡ አንትሙ ፡

እናንት ፡ እነማን ፡ ናችሁ ፡ እናንት ፡ ከኔ ፡ ሌላ ፡ ናችሁን ፡ ብሎ ።

፲፮ ፤ ወአብደ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ውእቱ ፡ ዘጋኔን ፡ እኩይ ፡

ተነሣሣባቸው ፡ (ጥቅ) ፡ ወአብደ ፡ ዳቤላ ፡ ጠሊ ፡ እንዲል ፡

ወኀየሎሙ ፡

ተበራታባቸው ፡

ወሞዖሙ ፡

ድል ፡ አደረጋቸው ፡

ወአቍሰሎሙ ፡ ወፈቅአሙ ፡

ገምሶ ፡ አቁስሎ ፡

ወሰደዶሙ ፡ እምውእቱ ፡ ቤት ፡

ከቤት ፡ አስወጥቶ ፡ ሰደዳቸው ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፯ ፤ ወተሰምዐ ፡ ዝ ፡ ነገር ፡ በኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ አይሁድ ፡ ወአረሚ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ኤፌሶን ፡

ይህም ፡ ነገር ፡ በኤፌሶን ፡ በሚኖሩ ፡ በአይሁድና ፡ በአረሚ ፡ ዘንድ፡ ደርሶ፡ ተሰማ፡

ወፈርሁ ፡ ኵሎሙ ፡

በሁሉም ፡ ፍርሃት ፡ አደረባቸው ፡

ወአዕበዩ ፡ ስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡

የጌታችን ፡ የኢየሱስን ፡ ስም ፡ አከበሩ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

፲፰ ፤ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ ይመጽኡ ፡ ወይኔስሑ ፡ በእንተ ፡ ዘገብሩ ፡

ያመኑትም ፡ ሁሉ ፡ እየመጡ ፡ ስለ ፡ ሠሩት ፡ ሥራ ፡ ንስሓ ፡ ይገቡ ፡ ነበር ።

፲፱ ፤ ወብዙኃን ፡ መሠርያን ፡ ያስተጋብኡ ፡ ወያመጽኡ ፡ ወያውዕዩ ፡ ኵሎ ፡ መጻሕፍቲሆሙ ፡ በቅድመ ፡ ኵሉ ፡

ብዙ ፡ ሥራየኞችም ፡ መጣፋቸውን፡ እየሰበሰቡ ፡ እያመጡ ፡ በጉባኤ ፡ ያቃጥሉት ፡ ነበር ፡

ወሐሳበ ፡ ሤጡ ፡ ለዘአውዐዩ ፡ ኀምስት ፡ እልፍ ፡ ድርህመ ፡ ብሩር ፡

ያቃጠሉትም ፡ የመጣፉ ፡ ዋጋ ፡ አምስት ፡ እልፍ ፡ ብር ፡ ይሆን ፡ ነበር ።

፳ ፤ ወከመዝ ፡ ፀንዐ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡

እንዲህ ፡ ባለ ፡ ነገር፡ ወንጌል፡ጸና፡ ተረዳ፡

ወዐብየ ፡ ወኀየለ ፡

ከሁሉ ፡ ደረሰ ፡ ሰፋ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ፯ ።

፳፩ ፤ ክፍል ፡ ፴፰ ። ወእምዝ ፡ ተፈጺሞ ፡ ዝንቱ ፡ ሐለየ ፡ ጳውሎስ ፡ በመንፈሱ ፡ ይኅልፍ ፡ እንተ ፡ መቄዶንያ ፡ ወአካይያ ፡ ወይሑር ፡ ኢየሩሳሌም ፡

ይህ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ በአካይያ ፡ በቆሮንቶስና ፡ በመቄዶንያ ፡ ፊልጵስዩስ ፡ መካከል ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ በልቡናው ፡ ወደደ፤

ወይቤ ፡ በጺሕየ ፡ ህየ ፡ ይደልወኒ ፡ እርአያ ፡ ለሮሜ ።

ኢየሩሳሌም ፡ ደርሼ ፡ ሮሜን ፡ ላያት ፡ ይገባኛል ፡ አለ ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ፲፩ ።

፳፪ ፤ ወፈነወ ፡ ለመቄዶንያ ፡ ክልኤተ ፡ እለ ፡ ይትለአክዎ ፡ ጢሞቴዎስሃ ፡ ወአርስጦስሃ ፡

ወደ ፡ መቄዶንያም ፡ ሁለቱን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት፡ ጢሞቴዎስንና፡ አርስጦስን፡ ላከ፡

ወውእቱሰ፡ ጳውሎስ፡ ነበረ፡ እስያ፡ ብዙኀ፡ መዋዕለ፡

እሱ ፡ ግን ፡ በእስያ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ኖረ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፲፬ ። ሮሜ ፡ ፲፮ ፡ ፳፫ ።

፳፫ ፤ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ዐቢይ ፡ ሁከት ፡ ኮነ ፡ በእንተ፡ ዝ፡ ትምህርት፡ ላዕለ፡ እለ፡ አምኑ፡በእግዚእነ፡

ስለዚህ ፡ ትምህርት ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ በጌታችን ፡ ባመኑ ፡ በምእመናን ፡ ብዙ ፡ጸብ፡ ክርክር ፡ ሆነ ፡ ቈ ፡ ፱ ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፰ ።

፳፬ ፤ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ህየ ፡ ብእሲ፡ ዘስሙ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ነሀቢ ፡ ብሩር ፡

ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ ዐቢይ ፡ ሁከት ፡ ኮነ ፡ በእንተ፡ ዝ፡ ትምህርት ፡ ላዕለ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ በእግዚእነ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ኮነ ፡ ሁከት ፡ ያለውን ፡ ያመጣል ፡ ድሜጥሮስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ አንጥረኛ ፡ ነበር ፡

ወይገብር ፡ ሥዕላተ ፡ ወአምሳላተ ፡ ብሩር ፡ ጣዖተ ፡ ለአርጤምስ ፡

ወርቁን ፡ ብሩን ፡ ሥዕል፡ እየሳለ ፡ ምስል ፡ እየመሰለ ፡ ለአርጤምስ ፡ ጣዖት ፡ ይሠራ ፡ ነበር ፡ ሐተታ ፡ ሥዕል ፡ የቀለሙ ፡ አምሳል ፡ የወርቁ ፡ የብሩ ። አንድም ፡ ሥዕል ፡ ንድፉ ፡ አምሳል፡ ቅቡ። አንድም፡ ሥዕል ፡ ቅርጹ ፡ አምሳል ፡ ተመቶ ፡ የሚሠራው ፡

ወያስተጌብሮሙ ፡ ለኪነት ፡

አንጥረኞችን፡ እያዘዘ፡ ያሠራቸው፡ ነበር ፡

ወይሁቦሙ ፡ ብዙኀ ፡ ንዋየ ፡

ብዙ ፡ ገንዘብን ፡ ይሰጣቸው ፡ ነበር ፡

ወያረብሖሙ ፡ ብዙኀ ፡

እየነገረ ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ይጠቅማቸው ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ፲፮ ።

፳፭ ፤ ወአስተጋብኦሙ ፡ ለኵሉ ፡ ኪነት ፡

ኪነት ፡ ኪናት ፡ ኪነውት ፡ ይላል ፡ አንጥረኞችን ፡

ወለእለ ፡ ይገብሩ ፡ ምስሌሆሙ ፡

ከነሱ ፡ ጋራ ፡ የሚሠሩትን ፡ ምስሎሙ ፡ ምስል ፡ የሚሠሩትን ፡ ተሰብሰቡ ፡ አለ ፡

ወአንገለጉ ፡

ተሰበሰቡ ፡

ወይቤሎሙ ፡ አንትሙ ፡ አኅዊነ ፡ ለሊክሙ ፡ ተአምሩ ፡ ከመ ፡ በዝ ፡ ተግባርነ ፡ ምርካብነ ፡

ወንድሞቻችን ፡ መኖሪያችን፡ ማግኛችን ፡ በዚህ ፡ በሥራችን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታውቃላችሁ ።

፳፮ ፤ ወናሁ ፡ ዘከመ ፡ ትሬእዩ ፡ ወዘከመ ፡ ትሰምዑ

አሁንም ፡ እንደምታዩት ፡ እንደምትሰሙት ፤

አኮ ፡ ባሕቲቶ ፡ ኤፌሶን ፡

ኤፌሶንን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡

አላ ፡ ኵሎ ፡ እስያ ፡ አስሐተ ፡

እስያንም ፡ ሁሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ዝ ፡ ጳውሎስ ፡ ብዙኃነ ፡ አሕዛበ ፡

ይህ ፡ ጳውሎስ ፡ ብዙ ፡ ምእመናንን ፡ አሳተ ፡ አላቸው፡ ዝ ፡ የነቀፋ፡ ቃል ፡ ነው ፡

ወይቤሎሙ ፡ ኢኮኑ፡ አማልክተ ፡ እለ ፡ በእደ፡ ሰብእ፡ ይትጌበሩ ፡

በሰው ፡ እጅ ፡ የሚሠሩ ፡ ጣዖታት ፡ አማልክት ፡ አይደሉም ። አንድም ፡ እሊህ ፡ ጣዖታት፡ አማልክት፡ አይደሉም፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ እያለ ።

፳፯ ፤ ወዓዲ ፡ አኮ ፡ በዝ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘንትመነሶ ፡

ዳግመኛም ፡ የምንጎዳ ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡

ዓዲ ፡ ለምኵራበ ፡ አርጤምስኒ ፡ ሀለዋ ፡ ይሠዐር ፡ ክብራ ፡ ወይትነሠት ፡ ዕበያ ፡ እንተ ፡ እስያኒ ፡ ወእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ያመልካ ።

እስያ ፡ ዓለሙም ፡ ሁሉ ፡ የሚያመልካት ፡ የአርጤምስ ፡ ጌትነቷ ፡ ይዋረዳል ፡ክብሯ፡ ይቀራል ፡ እንጂ ፡ አላቸው ።

፳፰ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ ተምዑ ፡

ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ተበሳጩ ፡

ወከልሑ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ፡

አሰምተው ፡ ጮሁ ፡

ወይቤሉ፡ ብዙኀ፡ ዕበያ፡ ለአርጤምስ፡ እንተ፡ኤፌሶን፡

የኤፌሶን ፡ እመቤት ፡ የአርጤምስ ፡ ክብሯ ፡ ፍጹም ፡ ነው ፡ እያሉ ።

፳፱ ፤ ወተሀውከ ፡ ኵሉ ፡ ሀገር ፡

ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ ተሸበሩ ፡

ወሮጹ ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ ተውኔት ፡ ኅቡረ ፡

ባንድነት ፡ ወደ ፡ መካነ ፡ ተውኔት ፡ ሂደው ፡ አለ ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ሂደው ።

ወሰሐብዎሙ ፡ ለጋይዮስ ፡ ወለአርስጥሮኮስ፡ ዕደው ፡ መቄዶናውያን ፡ አዕርክቲሁ ፡ ለጳውሎስ ።

የጳውሎስ ፡ ወዳጆች ፡ የሚሆኑ ፡ የመቄዶንያ ፡ ሰዎች ፡ አርስጥሮኮስንና ፡ ጋይዮስን፡ እየጐተቱ፡ ወሰዷቸው፡፪፡ ቆሮ፡፩፡፲፬።

፴ ፤ ወፈቀደ ፡ ጳውሎስ ፡ ይባእ፡ ማዕከለ ፡ አሕዛብ ፡ ወከልእዎ ፡ አርድእት ፡

ጳውሎስም ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ መካከል ፡ ሊገባ ፡ ወዶ ፡ ሳለ፡ ምእመናን፡ ከለከሉት።

፴፩ ፤ ወእለሂ ፡ እምእስያ ፡ አዕርክቲሁ ፡ ለአኩ ፡ ኀቤሁ፡ ኢይባእ፡ ማዕከለ፡ አሕዛብ፡ወአስተብቍዕዎ፡

በእስያ ፡ ያሉ ፡ ወዳጆቹም ፡ ወደ ፡ አሕዛብ



www.ethiopianorthodox.org

እንዳይገባ ፡ አትግባ ፡ ብለው ፡ ማልደው ፡ ላኩበት ፡

ወጐንደዩ ፡ እንዘ ፡ ይኬልሑ ፡ ሕዝብ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ህየ ፡ መካነ ፡ ተውኔት ።

ባደባባይ ፡ ያሉ ፡ ሕዝቡም ፡ ብዙ፡ጊዜ ፡ መላልሰው ፡ ጮሁ ።

፴፪ ወቦ ፡ እለ ፡ ይኬልሑ ፡ በካልእ ፡ ነገር ፡

ሳያውቋት ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ የጮኹም ፡ አሉ ፡ ሐተታ ፡ እንደ፡ ቅማንት ፡ ቅማንት፡ እንዷቱ ፡ ዳረ ፡ ገንዳ ፡ ሁና ፡ የጮኸች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ፊት ፡ አቦ ፡ ድረስ ፡ ተያይዞ ፡ እንዲጮኽ ፡

ወእለሰ ፡ ይበዝኁ ፡ እምኔሆሙ ፡ ኢያእመሩ ፡ በእንተ ፡ ምንት ፡ አንገለጉ ፡ አሕዛብ ።

ከነሱ ፡ የሚበዙት ፡ ሕዝቡ ፡ ግን ፡ አሕዛብ፡ ስለምን፡ እንደ፡ተሰበሰቡ፡አላወቁም።

፴፫ ወሕዝበ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ህየ ፡ አንሥኡ ፡ እምኔሆሙ ፡ ብእሴ ፡ አይሁዳዌ ፡ ዘስሙ ፡ እለ ፡ እስክንድሮስ ።

ከዚያ ፡ ያሉ ፡ የአይሁድ ፡ ወገኖችም፡ እለ እስክንድሮስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ አይሁዳዊ ፡ ሰው ፡ ከነሱ ፡ ወገን ፡ አሥነሱ ፡

ወተንሢኦ ፡ ቀጸበ ፡ በእዴሁ ፡ ወፈቀደ ፡ ይውቅሥ ፡ ለፀውድ ፡

ቆኖሥቶ ፡ እጅ ፡ ለነገር ፡ ያግዛልና ፡ ለሕዝቡ ፡ ሊናገር ፡ ወዶ ፡ በጁ ፡ አመለከተ ።

፴፬ ወአእሚሮሙ ፡ ከመ ፡ አይሁዳዊ ፡ ውእቱ ፡

አይሁዳዊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡

ከልሑ፡ ኵሎሙ፡በአሐዱ፡ቃል፡መጠነ፡ክልኤ፡ሰዓት ፡

ሁሉም ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ጮኹ ፡

እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ስንበት ፡ ዕበያ ፡ ለአርጤምስ ፡ እንተ ፡ ኤፌሶን ፡

የኤፌሶን ፡ እመቤት ፡ የአርጤምስ ፡ ጌትነቷ ፡ ፍጹም ፡ ነው ። አንድም ፡ ሰንበተ ፡ ይላል ፡ ኀለፈ ፡ ተጸርዐ ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ።

፴፭ ወእምዝ ፡ ተንሥአ ፡ ጸሐፌ ፡ ሀገር ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ አገር ፡ አሳዳሪ ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተነሥቶ ፡

ወአስተጋብኦሙ ፡ ለአሕዛብ ፡

ሕዝቡን ፡ ሰበሰባቸው ፡

ወይቤሎሙ ፡ ስምዑ ፡ ሰብአ ፡ ኤፌሶን ፡

እናንት ፡ የኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡ ስሙ ፡

መኑ ፡ ሰብእ ፡ ዘኢየአምራ ፡ ለሀገረ ፡ ኤፌሶን ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ እንተ ፡ አርጤምስ ፡ ዐባይ ፡ ጣዖታ ፡ ዘወረደ ፡ እምሰማይ ፡

አምላክነቷን ፡ የሚመሰክር ፡ ከወደ ፡ ላይ፡ የወረደላት ፡ የአርጤምስ ፡ ጉልት፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ ኤፌሶንን ፡ የማያውቅ ፡ ማነው ።

፴፮ ወበእንተ፡ዝ፡ ይመስለኒ ፡ አልቦ ፡ ዘይክል ፡ ተቃውሞታ ፡ ለዛቲ ፡

ስለዚህ ፡ ሊቃወማት ፡ የሚችል ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ፡ ሊቃወማት ፡ የሚችል ፡ የሌለ ፡ ይመስለኛል ። ታሪክ ፡ ኖኅ ፡ ከመርከብ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ የሦስቱን ፡ ልጆቹን ፡ ስም ፡ በቅፋፍ ፡ ጽፎ ፡ መልአኩን ፡ እንደ ፡ ዳኛ ፡ አድርጎ ፡ ከምሥራቅ ፡እስከ፡ ምዕራብ ፡ መካከሉን ፡ ለሴም ፡ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ግራ ፡ ግራውን ፡ ለካም ፡ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ቀኝ ፡ ቀኙን ፡ ለያፌት ፡ አካፍሏቸዋል ፤ ያፌት ፡ ይህያንን ፡ ይህያን ፡ ዮትራስን ፡ ዮትራስስ ፡ እስያን ፡ እስያ ፡ ሰባቱን ፡ ዮናናውያን ፡ ይወልዳል ፡ እስያንስ ፡ ዘውእቱ ፡ ዮትራስስ ፡ ይለዋል ፡ ብሎ ፡ ዮትራስስ ፡ ሰባቱ ፡ ዮናናውያንን ፡ ይወልዳል ፡ በቋንቋቸው ፡ በዮናኒ ፡ ዮናናውያን ፡ ተብለዋል ፡ ይህስ ፡ ቋንቋ ፡ በሰው ፡ ይጠራል ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ በቋንቋ ፡ አይጠራም ፡ ብሎ ፡ ባባታቸው ፡ በይህያን ፡ ዮናናውያን ፡ ተብለዋል ፡ በይሁዳ ፡ አይሁድ ፡ በኤቦር ፡ ዕብራውያን ፡ በፋሬስ ፡ ፈሪሳውያን ፡ በሳዶቅ ፡ ሰዱቃውያን ፡ እንደ ፡ ተባሉ። አንድም፡ በፀሓይ ፡ያመልኩ ፡ በፀሓይ ፡ ይቈጥሩ ፡ ነበርና ፡ በግብራቸው ፡ ጥንተ ፡ አን ፡ ጥንተ ፡ ዮን ፡ እንዲል ፡ ንድቀተ ፡ ዮንም ፡ ይላል ፡ የሰባቱ ፡ ዮናናውያን ፡ በኵሩ ፡ ኤፌሶን ፡ ነው ፡ ከኤፌሶን ፡ መልክ ፡ ከደም ፡ አስተባብራ ፡ የያዘች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ተወለደች ፡ ስሟን ፡ አርጤምስ ፡ አላት ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባደረሰች ፡ ጊዜ ፡ ሰይጣን ፡ ትዕቢት ፡ አሳደረባት ፡ ባለጸጋ ፡ መጥቶ ፡ ላግባሽ ፡ ሲላት ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖርህ ፡ መልከ ፡ ክፉ ፡ ነህ ፡ ጥበብ ፡ የለህ ፡ ትለዋለች ። ጥበብ ፡ ያለው፡ መጥቶ ፡ ላግባሽ ፡ ሲላት ፡ ጥበብ ፡ ቢኖርህ ፡ መልከ ፡ ክፉ ፡ ነህ ፡ ድኃ ፡ ነህ ፡ ትለዋለች ። መልከ ፡ መልካም ፡ መጥቶ ፡ ላግባሽ ፡ ሲላት ፡ መልክ ፡ ቢኖርህ ፡ ድኃ ፡ ነህ ፡ ጥበብ ፡ የለህ ፡ ትለዋለች ። እንዲህ ፡ እያለች ፡ ስትኖር ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ መሠርይ ፡ መጥቶ ፡ ላግባሽ ፡ አላት ፡ ለብዙ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ለብዙ ፡ ባለገንዘብ ፡ ለብዙ ፡ ባለጥበብ ፡ ያልሆንለት ፡ ላንት ፡ እንደምን ፡ ይሆንልሃል ፡ አለችው ፡ መቸስ ፡ አንች ፡ የምትሽው ፡ መከበሩን ፡ አይደለምን ፡ እንድትከበሪ ፡ ሳድርግልሽ ፡ እንጅ ፡ ምን ፡ ዕዳሽ ፡ አላት ፡ በል ፡ እስቲ ፡ አድርገውና ፡ ልይህ ፡ አለችው ፡ ዘኢሰገደ ፡ ለአርጤምስ ፡ ይትበርበር ፡ ቤቱ ፡ ወይትሐየድ ፡ ንዋዩ ፡ ብሎ ፡ በቅፋፍ ፡ ጽፎ ፡ አጋንንትን ፡ በምስሐብ ፡ ጠርቶ ፡ ሰውን ፡ ሰብስቤ ፡ በማስተምርበት ፡ ጊዜ ፡ ከወደ ፡ ላይ ፡ ድምፅ ፡ እያሰማችሁ ፡ መጥታችሁ ፡ ጣሉልኝ ፡ ብሎ ፡ ሰጣቸው ፡ ሰውን ፡ ሰብስቦ ፡ በሚያስተምርበት ፡ ጊዜ ፡ ከወደ ፡ ላይ ፡ ድምፅ ፡ እያሰሙ ፡ መጡ ፡ እስቲ ፡ እሻ ፡ ከወደ ፡ ላይ ፡ የምሰማው ፡ ድምፅ ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ ተንሣ ፡ ጣሉለት ፡ ያነን ፡ አንሥቶ ፡ እንቦ ፡ አምላክነቷን ፡ የሚመሰክር ፡ ከወደ ፡ ላይ፡ ከወረደላት ፡ ለመቤቴ ፡ ለአርጤምስ ፡ ሰገድሁ ፡ ብሎ ፡ ሰግዷል ፡ እሱን ፡ አብነት ፡ አድርገው ፡ ሁሉም ፡ ሰግደዋል ። አንድም ፡ ዕብነ ፡ መንግኒጦስ ፡ የሚባል ፡ አለ ፡ እንደ ፡ ቁርበት ፡ ሐሊም ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ቁርበት ፡ ሐሊም ፡ ስጦቆ ፡ ማር ፡ ሲያሳዩት ፡ ይዞ ፡ እንዲነሣ ፡ ያሳዩትን ፡ ሁሉ ፡ ሽቅብ ፡ የሚያወጣ ፡ ነው ፡ ሲወጣ ፡ አይታይም ፡ ሲወርድ ፡ ይታያል ፡ በዚያ ፡ አንሥቶ ፡ ጥሎለታል ፡ አንሥቶ ፡ አንቦ፡ አምላክነቷን፡ የሚመሰክር ፡ ከወደ፡ ላይ ፡ ከወረደላት ፡ ለመቤቴ ፡ ለአርጤምስ ፡ ሰገድሁ ፡ ብሎ ፡ ሰግዷል ፡ ሁሉም፡ እሱን ፡ አብነት ፡ አድርገው ፡ ሰግደዋል ፡ እሷን ፡ አግብቶ ፡ ዜውስን ፡ ወልዷል ፡ ዜውስንም ፡ የአምላክ ፡ ልጅ ፡ አምላክ ፡ ብለው ፡ ሰግደውለታል ፡ ያዛቆነ ፡ ሰይጣን ፡ ሳያቀስ ፡ አይቀርም ፡ እንዲሉ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላም ፡ እንደ ፡ ተነሡ ፡ እንደ ፡ ዐረጉ ፡ አድርጎ ፡ ያሳያቸዋል ፡ ሥዕላቸውን ፡ ሥለው ፡ ምስላቸውን ፡ መስለው ፡ የሚኖሩ ፡ ሁነዋልና ፡ ዐባይ ፡ ጣዖታ ፡ ዘወረደ ፡ እምሰማይ ፡ አለ ፡

ወይእዜኒ ፡ ርቱዕ ፡ በድቡት ፡ ንግበሮ ፡ ለዝ ፡

አሁንም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በዝግታ ፡ በጸጥታ ፡ ልናደርገው ፡ ይገባል ፡

ወአኮ ፡ በሀከክ ፡ ወበትዝልፍት ፡

በጠብ ፡ በክርክር ፡ በድፍረት ፡ ልናደርገው ፡ አይገባም ።



www.ethiopianorthodox.org

፴፯ ፤ ናሁ ፡ ተባጽሕክምዎሙ ፡ ለእሉ ፡ ሰብእ ፡ ዘኢሰረቁ ፡ ቤተ ፡ አማልክት ፡

የአማልክትን ፡ ገንዘብ ፡ ያልሰረቁ ፡

ወኢፀረፉ ፡ ዲበ ፡ አማልክቲነ ፡

አማልክቶቻችነንም ፡ ያልሰደቡ ፡ እሌህን ፡ ሰዎች ፡ አዳርሱን ፡ ብላችሁ ፡አመጣችኋቸው ።

፴፰ ፤ ወእመሰ ፡ ቦ ፡ ተስናነ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ምስለ ፡ ኬነት ፡ ለይትዋቀሑ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ናሁ ፡ መኰንን ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡

ድሜጥሮስ ፡ ካንጠረኞች ፡ ጋራ ፡ ባመጣው ፡ ጠብ ፡ ክርክር፡ እንደ ፡ ሆነ፡ እነሆ፡ በሀገር፡ዳኛ፡አለ፡እርስ፡በርሳቸው፡ይባባሉ።

፴፱ ፤ ወእመሰ ፡ ባዕድ ፡ ማኅሠሥ ፡ ብክሙ ፡ ዘበእንተ ፡ ሕግክሙ ፡

ስለ ፡ ሕጋችሁ ፡ አሪት ፡ ትበልጣለች ፡ ወንጌል ፡ ትበልጣለች ፡ በማለት ፡ ሌላ ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ እንዳላችሁ ፡ ግን ፡

ንነሥት ፡ ዐውደ ፡

ጉባኤውን ፡ እንፈታለን ፡ (ንንሥት ፡ ዐውደ) ፡ ጉባኤውን ፡ እንፍታ ።

፵ ፤ እስመ ፡ ንትመነሶ ፡ ዮም ፡ በዘአምጻእክሙ ፡ ለነ ፡ ሀከክ ፡ ዘአልቦ ፡ ጌጋይ ፡

ዕዳ ፡ በደል ፡ ሳይኖር ፡ እናንት ፡ ባመጣችሁት ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ እንገዳለንና ፡

ወአልብነ ፡ ዘንትዋቀስ፡ በእንተ፡ዝ ፡ ሀከክ ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ነሠተ ፡ ዐውደ ፡

ስለዚህ ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ የምንመልሰው ፡ ምላሽ ፡ የምንፈርደው ፡ ፍርድ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ጉባኤውን ፡ ፈታ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳ ፡ ክፍል ፡ ፴፱ ፡

፩ ፤ ወእምድኅረ ፡ ኀልቀ ፡ ሀከክ፡ ፀውዐ ፡ ጳውሎስ፡ አርዳኢሁ ፡ ወመሀሮሙ ፡

ጠቡ ፡ ክርክሩ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ማለት ፡ ጉባኤው ፡ ከተፈታ ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ አስተማራቸው ፡

ወሰዐሞሙ ፡ ወወፅአ ፡ ወሖረ ፡ መቄዶንያ ፡

ተሰነባብቷቸው ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ ሄደ ፡ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፫ ።

፪ ፤ ወኀለፈ ፡ እንተ ፡ ውእቱ ፡ በሐውርት ፡

በመቄዶንያ ፡ አውራጃም ፡ መንገድ ፡ ለመንገድ ፡ እያስተማረ ፡ ሄደ ፡

ወብዙኀ ፡ መሀሮሙ ፡ በቃሉ ፡

በቃሉ፡ ብዙ፡ ትምህርት፡ አስተማራቸው ፡

ወእምዝ፡ ሖረ ፡ ኤልዳ ፡

ከዚያም ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ኤልዳ ፡ ሄደ ።

፫ ፤ ወነበረ ፡ በህየ ፡ ሠለስተ ፡ አውራኀ ፡

በኤልዳም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ኖረ ፡

ወተማከሩ ፡ አይሁድ ፡ ዲቤሁ ፡

አይሁድም ፡ ሊገሉት ፡ መከሩበት ፡

ወፈቀደ ፡ ብሔረ ፡ ሶርያ ፡ ወመከረ ፡ ይሰወጥ ፡ መቄዶንያ ፡

እንደ ፡ መከሩበትም ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ ሊሄድ ፡ ወዶ ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ ሊመለስ ፡ ወደደ ።

፬ ፤ ወሖሩ ፡ ምስሌሁ ፡ ሱሲ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘሀገረ ፡ ቤርያ ፡

ወሐረም ፡ ይላል ፡ የቢርያው ፡ ሰው ፡ ሱሲ ፡ ጴጥሮስ ፡ (ፀሓይ ፡ ማለት ፡ ነው) ፡

ወእምተሰሎንቄ ፡ አርስጥሮኮስ ፡

የተሰሎንቄ ፡ ሰው ፡ አርስጥሮኮስ ፡

ወሲነዱስ ፡

ሲነዱስ ፡

ወጋይዮስ ፡ ደርቤያዊ ፡

የደርቤን ፡ ሰው ፡ ጋይዮስ ፡

ወጢሞቴዎስ ፡ ዘእምልስጥራን ፡

የልስጥራን ፡ ሰው ፡ ጢሞቴዎስ ፡

ወእምእስያ ፡ ጢኪቆስ ፡

ከእስያ ፡ ጢኪቆስ ፡

ወፕሮፌሞስ ፡

ፕሮፌሞስ ፡ ተከትለውት ፡ ሄዱ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፲ ። ም ፡ ፲፱ ፡ ፳፱ ።

፭ ፤ ወእሙንቱ ፡ ሖሩ ፡ ቅድሜነ ፡ ወጸንሑነ ፡ ውስተ ፡ ጢሮአዳ ፡

እነሱም ፡ ቀድመውን፡ሂደው፡ በጢሮአዳ ፡ አርፈው ፡ ቆዩን ፡

፮ ፤ ወንሕነሰ ፡ ነገድነ ፡ እምድኅረ ፡ ፋሲካ ፡ እምፊልጲስ ፡

እኛ ፡ ግን ፡ ከበዓለ ፡ ፋሲካ ፡ በኋላ ፡ የመቄዶንያ ፡ መዲና ፡ ከምትሆን ፡ ከፊልጵስዩስ ፡ ወጥተን ፡

ወበጻሕነ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ውስተ ፡ ጢሮአዳ ፡ በባሕር ፡ በኀምስት ፡ ዕለት ፡

በመርከብ ፡ ተጭነን ፡ ባምስት ፡ ቀን ፡ እነሱ፡ካሉበት፡ ዘንድ፡ ጢሮአዳ፡ ደረስነ ፡

ወነበርነ ፡ ህየ ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ፡

ከዚያም ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ሰነበትነ ።

፯ ፤ ክፍል ፡ ፴ ። ወበዕለተ ፡ እሑድ ፡ እንዘ ፡ ጉቡአን ፡ ንሕነ ፡ከመ ፡ ንባርክ ፡ ማዕደ ፡

እሑድ ፡ ቀን ፡ ጸሎተ ፡ ማዕድ ፡ ለመጸለይ፡ ተሰብስበን ፡ ሳለ ፡

ወይነግሮሙ ፡ ጳውሎስ ፡

ጳውሎስ ፡ ለተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ፡

እስመ ፡ በሳኒታ ፡ ይገይሥ ፡

በነጋው ፡ የሚሄድ ፡ ነውና ፡

ወአንኀ ፡ ነገረ ፡ እስከ ፡ ንፍቀ ፡ ሌሊት ፡

እስከ፡መንፈቀ፡ ሌሊት፡ ድረስ፡ አስተማረ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፪ ። ም ፡ ፪ ፡ ፵፪ ፡ ፵፮ ።

፰ ፤ ወብዙኅ ፡ መኃትው ፡ ውስተ፡ ውእቱ ፡ ጽርሕ፡ ኀበ ፡ ሀሎነ ፡ ጉቡአን ፡

ተሰብስበን ፡ ባለንበትም ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ መብራት ፡ ይበራ ፡ ነበር ።

፱ ፤ ወእንዘ ፡ ይነብር ፡ አሐዱ ፡ ወልድ ፡ ወሬዛ ፡ ውስተ ፡ መስኮት ፡ ዘስሙ ፡ አውጤክስ ፡ ደቀሰ፡ ወኖመ ፡ ዐቢየ ፡ ንዋመ ፡

አሐዱ ፡ ወልድ ፡ ወሬዛ ፡ ዘስሙ ፡ አውጤክስ ፡ አውጤክስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ብላቴና ፡ ከመስኮት ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ጽኑ ፡ እንቅልፍ ፡ አንቀላፋ ፡

ወእንዘ ፡ ይነግር ፡ ጳውሎስ ፡ ብዙኀ ፡ ጐንደየ ፡

ጳውሎስ ፡ ሲያስተምር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆይቶ ፡ ነበርና ፡

ወእምኀበ ፡ ይነውም ፡ ውእቱ ፡ ወልድ ፡ ጸድፈ፡ እምተሥላስ ፡ ታሕተ ፡

ከተኛበት ፡ ሰገነት ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ፡ ታች፡ ወደቀ ፡ ሐተታ ፡ ዐምዱ ፡ ሁለት፡መስኮቱ፡ ሦስት ፡ ነውና ። እምዲበ ፡ ተሥላስ ፡ ይላል ፡ ከሦስቱ ፡ መስኮት ፡ በላይ ፡ አንድ፡ መስኮት ፡ አለ ፡ ከዚያ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወደቀ ፡

ወአንሥእዎ ፡ በድኖ ፡

ሬሳውን ፡ አነሡት ።

፲ ፤ ወወረደ ፡ ጳውሎስ ፡

ጳውሎስም ፡ ከተቀመጠበት ፡ ሰገነት ፡ ወርዶ ።

ወነሥአ ፡ ኀቢሁ ፡

ከነሱ ፡ ተቀብሎ ፡ አቅፎ ፡ ያዘው ፡



www.ethiopianorthodox.org

ወይቤሎሙ ፡ ኢትደንግፁ ፡ ሀለወት ፡ ነፍሱ ፡ ላዕሌሁ ፡

ነፍሱ ፡ አልተለየችውምና ፡ አይዟችሁ ፡ አላቸው ፡ ፩ ፡ ነገሥ ፡ ፲፯ ፡ ፳፩ ።

፲፩ ፤ ወእምዝ ፡ ዐርገ ፡ ወአዕረገ ፡ ምስሌሁ ፡ ወነበረ ፡ ወወሀቦ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይዞት ፡ ከሰገነት ፡ ወጥቶ ፡ ተቀመጠ ፡

ወባረከ ፡ ማዕደ ፡

ጸሎተ ፡ ማዕድ ፡ ባርኮ ፡ ጸልዮ ፡

ወወሀቦ ፡ ለወሬዛ ፡ እምነ ፡ ማዕድ ፡

ከማዕዱ ፡ ቆርሶ ፡ ለብላቴናው ፡ ሰጠው ፡

ወብዙኀ ፡ ነገሮሙ ፡ ወጐንደየ ፡ እስከ ፡ ጎሕ ፡

እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ትምህርት ፡ አስተማራቸው ።

፲፪ ፤ ወእምዝ ፡ ወፅአ ፡ ጌሠመ ፡ ወአወፈዮሙ ፡ ውእተ ፡ ወልደ ፡ ሕያዎ ፡

በነጋው ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ሕያው ፡ አድርጎ ፡ ሰጣቸው ፡ ይርዳችሁ ፡ ያጥባችሁ ፡ ብሎ ፡

ወተፈሥሑ ፡ ፈድፋደ ፡

እጅግ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

፲፫ ፤ ወንሕነሰ ፡ ዐረግነ ፡ ሐመረ ፡ ወሖርነ ፡ አሶን ፡

እኛ ፡ ግን ፡ በመርከብ ፡ ተጭነን ፡ ወደ ፡ አሶን ፡ ሄድነ ፡

እስመ ፡ እምህየ ፡ ፈቀድነ ፡ ንትቀበሎ ፡ ለጳውሎስ ፡

ከአሶን ፡ ተመልሰን ፡ ጳውሎስን ፡ ከዚያ ፡ ልንቀበለው ፡ ወደን ፡ ነበረና ፡

እስመ ፡ ከመዝ ፡ ተናገረነ ፡ ከመ ፡ ይመጽእ ፡ በእግር ፡ ወተቀበልናሁ ፡

በየብስ ፡ በእግር ፡ እንዲመጣ ፡ ስለ ፡ ነገረን፡

፲፬ ፤ ወበጻሕነ ፡ አሶን ፡

አሶን ፡ ደርሰን ፡ ተቀብለን ።

ወነሣእናሁ ፡ ዲበ ፡ ሐመር፡ወሖርነ ፡ ሚልጢኒን ፡

ከዚያም ፡ በመርከብ ፡ ይዘነው ፡ ወደሚልጢኒን ፡ ሄድነ ።

፲፭ ፤ ወእምህየ ፡ ነገድነ ፡ በሳኒታ ፡ ወበጻሕነ ፡ አንጢቅክስዩ ፡

በነጋውም ፡ ከዚያ ፡ ወጥተን ፡ ሄድን ፡ አንጢቅክስዩ ፡ ደረስን ።

ወበሳኒታ ፡ ኀለፍነ ፡ እንተ ፡ አሞን ፡

በነጋው ፡ ከዚያ ፡ ወጥተን ፡ ወደ ፡ አሞን ፡ ሄድነ ።

፲፮ ፤ ወእምድኅረ ፡ ውእቱ ፡ ዕለት ፡ በጻሕነ ፡ መሊጡ ፡

ካንድ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ፈጥነን ፡ መሊጡ ፡ ደረስን ፡

እስመ ፡ አጥብዐ ፡ ጳውሎስ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ኤፌሶን ፡ ከመ ፡ ኢይጐንዲ ፡ ውስተ ፡ እስያ ፡ ወጐጕአ ።

በእስያ ፡ ኑሮ ፡ ኤፌሶን ፡ ሳይደርስ ፡ እንዳይቀር ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ሊሄድ ፡ ወዶ ፡ ነበረና ፡

ለእመ ፡ ይትከሀሎ ፡ ይብጻሕ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለጰንጠቆስቴ ፡

ቢቻለውም ፡ ለበዓለ ፡ ሃምሳ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሊደርስ ፡ ቸኩሎ ፡ ነበርና ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ። ፳፩ ፡ ፬ ፡ ፲፱ ።

፲፯ ፤ ወእምነ ፡ መሊጡ ፡ ለአከ ፡ ኤፌሶን ፡ ይጸውዕዎሙ ፡ ለቀሲሳን ፡ እለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

በመሊጡ ፡ ሁኖ ፡ በምእመናን ፡ ላይ ፡ የተሾሙ ፡ ቀሳውስትን ፡ ጥሩ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ላከ ።

፲፰ ፤ ወበጺሖሙ ፡ ኀቤሁ ፡

ቀሳውስትም ፡ እሱ ፡ ካለበት ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ፡



ይቤሎሙ ፡ ለሊከሙ ፡ ተአምሩ ፡ እምአመ ፡ መጻእኩ ፡ እስያ ፡ ዘከመ ፡ ነበርኩ ፡ ኀቤክሙ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕል ፡

ወደ ፡ እስያ ፡ ከመጣሁ ፡ ጀምሮ ፡ በዘመኑ፡ ሁሉ ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ነበርሁ ፡ ታውቃላችሁ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ። ፲፱ ፡ ፲ ።

፲፱ ፤ እንዘ ፡ እትቀነይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔርን ፡ ሳገለግል፡ እንደ፡ ኖርሁ ፡

ወእሰርሕ ፡ በኵሉ ፡ ሕማም ፡

በመከራው ፡ ሁሉ ፡ ስደክም ፡ እንደ ፡ ኖርሁ ፡ ታውቃላችሁ ፡ ሐተታ ፡ ሌሊት ፡ በስፌት ፡ ቀን ፡ በትምህርት ፡

ወአንብዕ ፡

በኀዘን ፡ በልቅሶ ፡

ወመንሱትኒ ፡ ዘረከበኒ ፡ እምአይሁድ ፡

ከአይሁድም ፡ ባገኘኝ ፡ መከራ ፡ ቍ ፡ ፫ ።

፳ ፤ ወአልቦ ፡ ዘሰወርኩክሙ ፡ እምኵሉ ፡ ዘይደልወክሙ ፡ ዘኢነገርኩክሙ ፡ ወዘኢመሀርኩክሙ ።

ከሚገባችሁ ፡ ሁሉ ፡ ያልነገርኋችሁ ፡ ያላስተማርኋችሁ ፡ ሰውሬ ፡ ያስቀረሁባችሁ ፡ የለም ።

፳፩ ፤ እንዘ ፡ አሰምዖሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ከሠተ ፡ ወለአረሚኒ ፡

ለአይሁድም ፡ ለአረማውያንም ፡ ገልጬ ፡ ሳስተምር ።

በአፍአኒ ፡ ወበውሥጥኒ ፡ ከመ ፡ ይትጋነዩ ፡ ወይነስሑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወይእመኑ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

በውስጥም ፡ በአፍኣም ፡ ሳስተምር ። አንድም ፡ በውስጥ ፡ በአፍኣም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ፡ ሳስተምር ።

፳፪ ፤ ወይእዜኒ ፡ ናሁ ፡ ተአሥርኩ ፡ በመንፈስየ ፡ እሖር ፡ ኢየሩሳሌም ፡

አሁንም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለመሄድ ፡ በልቡናዬ ፡ ተቀጥሬያለሁ ፡

ወኢየአምር ፡ ዘይረክበኒ ፡ በውስቴታ ፡

በኢየሩሳሌም ፡ የሚያገኘኝን ፡ ግን፡ አላውቅም ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ ። ፲፱ ፡ ፳፩ ።

፳፫ ፤ ወባሕቱ ፡ አስምዐ ፡ ሊተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በበአህጉር ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሕማም ፡ ወመዋቅሕት፡ ይጸንሐከ ፡

በየሀገሩ ፡ መከራ ፡ እስራት ፡ ይቆይሃል ፡ ብሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አዳኝቶብኛል ፡ እንጅ ፡ ኢየአምር ፡ ላለው ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፲፮ ። ፳፩ ፡ ፬ ፡ ፲፩ ።

፳፬ ፤ ወባሕቱ፡ ኢአሐስባ፡ ለነፍስየ፡ ወኢምንተኒ፡

ነገር፡ ግን፡ ኢየሐስባ ፡ ምንም፡ምን፡ ለሰውነቴ ፡ አላስብላትም ። ኢአሐስባ ፡ ይህ ፡ ይህ ፡ አለብሽ ፡ ብዬ ፡ ቈጥሬ ፡ አልነግራትም ፡

ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ እፈጽም ፡ መልእክትየ ፡ ወእሠልጥ ፡ ግብርየ ፡ ዘነሣእኩ ፡ እምኀበ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ከመ ፡ እምሀር ፡ ወእስብክ ፡ ወንጌለ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔር ፡ በለጋስነት ፡ የሠራት ፡ ወንጌልን ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ፡ ከጌታችን፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስም፡ ዘንድ ፡ የተሾምሁትን ፡ ሐዋርያነት ፡ እፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ኢየሐስባ ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፲፫ ።

፳፭ ፤ ወይእዜኒ ፡ ናሁ ፡ አነ ፡ አእመርኩ ፡ ከመ ፡ ኢትሬእዩኒ ፡ ገጽየ ፡ እንከ ፡ አንትሙ ፡ ኵልክሙ ፡ እለ ፡ ሰበኩ ፡ ለክሙ ፡ በእንተ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ወንጌልን ፡ ያስተማርኋችሁ ፡ እናንተ ፡ ሁላችሁም ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ መልኬን ፡ እንደ ፡ አታዩኝ ፡ አወቅሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፮ ፤ ወናሁ ፡ አሰምዕ ፡ ለክሙ ፡ ዮም ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ከመ ፡ ንጹሕ ፡ አነ ፡ እምደመ ፡ ኵልክሙ ።

እኔ ፡ በናንት ፡ ከሚመጣው ፡ ፍዳ ፡ ንጹሕ፡ እንደሆንሁ ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ አዳኝባችኋለሁ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፮ ።

፳፯ ፤ ወአልቦ ፡ ዘኅባእኩክሙ ፡ ወዘኢነገርኩክሙ፡ ኵሎ ፡ ምክሮ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ ወዶ ፡ መክሮ ፡ ያደረገ ውን ፡ ሥጋዌውን ፡ ያልነገርኋችሁ ፡ የሰ ወርኋችሁ፡ የለም፡ አንድም፡ ወዶ፡ መክሮ፡ ካደረገው ፡ የሥጋዌው ፡ ምስጢር ፡ ያስ ቀረሁባችሁ ፡ የለም ።

፳፰ ፤ ወይእዜኒ ፡ ዕቀቡ ፡ ርእሰክሙ ፡

አሁንም ፡ ራሳችሁን ፡ ጠብቁ ፡

ወኵሎ ፡ መራዕየ ፡

ምእመናንን ፡ ሁሉ ፡ ጠብቁ ።

ዘሎቱ ፡ ሤመክሙ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጳጳሳተ ፡

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጳጳሳት ፡ አድርጎ ፡ የሾ ማችሁ ፡ እናንት ፡ ዕቀቡ ፡ ጠብቁ ።

ከመ፡ትርአዩ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለክርስቶስ፡ እንተ፡ አጥረያ ፡ በደሙ ፡

በወርቀ ፡ ደሙ ፡ የዋጃት ፡ ምእመንን ፡ ትጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ የሾማችሁ ፡ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፮ ። ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፪ ።

፳፱ ፤ ወአነ ፡ አአምር ፡ ከመ ፡ ይመጽኡ ፡ እምድኅሬየ ፡ ተኵላት ፡ መሰጥ ፡ እለ ፡ ኢይምሕክዋ ፡ ለመርዔት ፡

ከኔ ፡ በኋላ ፡ ለምእመናን ፡ የማያዝኑ ፡ ሰውን ፡ እየነጣጠቁ ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ የሚ ያወርዱ ፡ አሰተኞች ፡ መምሕራን፡ እንዲነ ሡ ፡ አውቃለሁ ፡ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፭ ።

፴ ፤ ወእምውስቴትክሙ ፡ ይትነሥኡ ፡ ዕደው ፡ እለ ፡ ይሜህሩ ፡ ጠዋየ ፡ ነገረ ።

ከናንተም ፡ ወገን፡ የማይገባ፡ ትምህርትን፡ የሚያስተምሩ ፡ ሰዎች ፡ እንዲነሡ ፡ አው ቃለሁ ፡

ከመ ፡ ያግብእዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ኀቤሆሙ ፡

አሕዛብን፡ ወደነሱ፡ይመልሷቸው፡ዘንድ ።

፴፩ ፤ ወይእዜኒ ፡ ትግሁ ፡

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ተግታችሁ ፡ ራሳች ሁን ፡ ጠብቁ ፡ ሌላውንም ፡ ጠብቁ ፡

ወተዘከሩ ፡ ከመ ፡ ሠለስተ ፡ ዓመተ ፡ ኢነተገ ፡ አን ብዕየ ፡ ሌሊተ ፡ ወመዓልተ ፡ እንዘ ፡ እሜህረክሙ ፡ ለኵልክሙ ፡

ለሁላችሁም ፡ ሳስተምር ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ እንባዬ ፡ እንዳላቋረጠ ፡ አስቡ ።

፴፪ ፤ ወይእዜኒ ፡ አማኅፀንኩክሙ ፡ ኀበ ፡ እግዚአ ብሔር ።

አሁንም ፡ ያመናችሁበት ፡ እግዚአብሔ ርን ፡ አትካዱ ፡ ብዬ ፡ አደራ፡ እላችኋለሁ። አንድም ፡ ያመናችሁበት ፡ እግዚአብሔር፡ አይለያችሁ ፡ ብዬ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አደራ ፡ እላለሁ ፡

ወለቃለ ፡ ጸጋሁ ፡

በለጋስነት ፡ የሠራት ፡ ወንጌልንም ፡ አት ካዱ ፡ ብዬ ፡

ዘይክል ፡ ሐኒጸተክሙ ፡

እናንተን ፡ ማጽናት ፡ የሚቻለው ፡

ወየሀብክሙ ፡ ርስተ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ።

ከቅዱሳን ፡ ከሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ቅዱሳን ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ያወርሳችሁ ፡ ዘንድ ።

፴፫ ፤ ተአምሩ ፡ ከመ ፡ ኢተሰቆቁ ፡ ንዋየክሙ ፡

ለከብታችሁ ፡ እንዳልሳሳሁ ፡

ኢወርቀ ፡ ወኢብሩረ ፡

ወርቅም ፡ ብርም ፡ ሆኖ ፡

ወኢአልባሰ ፡ ኢነሣእኩ ፡

ልብስም ፡ ሁኖ ።

ወኢኀበ ፡ አሐዱሂ ፡ እምኔክሙ ፡

ከናንት ፡ ካንዱስ ፡ ስንኳ ፡ እንዳልተቀበ ልሁ ፡ ታውቃላችሁ ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፰ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲፪። ፩ ፡ ሳሙኤ ፡ ፲፪ ፡ ፫ ።

፴፬ ፤ ለሊክሙ ፡ ተአምሩ ፡ ኢለትካዝየ ፡

የኔን ፡ ግዳጅ ፡ ለመፈጸም ፡

ወኢለእለ ፡ ምስሌየ ፡

ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያሉትንም ፡ ሰዎች ፡ ግዳጅ ፡ ለመፈጸም ፡ እንዳልተቀበልሁ ፡ እናንት ፡ ቅሉ ፡ ታውቃላችሁ ፡

አላ ፡ ተቀንያ ፡ እላንቱ፡ እደውየ ፡

በእጆቼ፡ ተግባረ፡ እድ ፡ ይገኔ ፡ ኖርሁ ፡ እንጅ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፫ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ።

፴፭ ፤ እስመ ፡ ከማሁ ፡ ይደልወነ ፡

ይህ ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ መያዙ ፡ ይገባናልና፤

ከመ ፡ በጻማነ ፡ ወበተግባርነ ፡ ንትወከፎሙ፡ ለድኩማን ፡

ጽረን ፡ ግረን ፡ ባመጣነው ፡ ገንዘብ ፡ ነዳ ያንን ፡ እንረዳቸው ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ጽረን ፡ ግረን ፡ ባመጣነው ፡ ገንዘብ ፡ ነዳ ያንን ፡ እንረዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ መር ዳቱ ፡ ይገባናልና ፡

ወዘንተ ፡ መሀርኩክሙ ፡

ይህነንም ፡ ነገርኋችሁ ፡

ተዘከሩ ፡ ቃሎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘይቤ ፡ ብፁዕ ፡ ዘይሁብ ፡ እምዘ ፡ ይነሥእ ፡

በዚያውም ፡ ላይ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሚቀበል ፡ የሚሰጥ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የተናገረ ውን ፡ አስቡ ፡ ብፁዓን ፡ መሐርያን ፡ ያለ ውን ፡ ይሻል ። አንድም ፡ ከሚነሣ ፡ የሚ ሰጥ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ አስቡ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ባዕል ፡ ቦቱ ፡ መጋቢ ፡ ወአስተ ዋደይዎ ፡ ያለውን ፡ ይሻል ። አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጠው ፡ አርሶ ፡ ቆፍሮ ፡ ጽፎ ፡ ደጉሶ ፡ ካገኘው፡ ገንዘብ፡ የሚሰጥ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። መኑ ፡ እንጋ ገብር ፡ ጠቢብ ፡ ወምእመን ፡ ዘይሠይሞ ፡ እግዚኡ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ፡ ያለውን፡ ይሻል። አንድም፡ ካሥር፡ አንድ፡ ከተቀበለው ፡ ገን ዘብ ፡ የሚሰጥ ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ አሥርዓቶ፡ ለአሥርዓት፡አለና። አን ድም፡ ለምኖ፡ ካገኘው ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰጥ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ የጥኋት ፡ ለማኝ ፡ ለማታ ፡ ለማኝ ፡ እንዲሉ ።

፴፮ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ሰገደ ፡ ወጸለየ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ምስሌሁ ፡

ይህን ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ አብረውት ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተንበርክኮ ፡ የሙ ሰነባበቻ ፡ ጸሎት ፡ ጸለየ ።

፴፯ ፤ ወብዙኀ ፡ በከዩ ፡ ኵሎሙ ፡ ወሐቀፍዎ ፡ ክ ሳዶ ፡ ለጳውሎስ ፡ ወሰዐምዎ ፡

ሁሉም ፡ አንገቱን ፡ አቅፈው ፡ እያለቀሱ፡ ተሰነባበቱት ።

፴፰ ፤ ወፈድፋደሰ ፡ እስመ ፡ ይቤሎሙ ፡ ኢትሬ እዩኒ ፡ እንከ ፡ ገጽየ ፡

ይልቁንም ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ መልኬን፡ አታዩኝም ፡ ስላላቸው ፡ እያለቀሱ ፡ ተሰነ ባበቱት ።

ወፈነውዎ ፡ ወዐርገ ፡ ሐመረ ፡

ሸኙት ፡ በመርከብ ፡ ተጫነ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፡ ፳፩ ፡ ክፍል ፡ ፶፩ ።

፩ ፤ ወሐርነ ፡ ንሕነሂ ፡
እኛም ፡ ሄድን ፡
ወእሙንቱሂ ፡ አተዉ ፡
እነሱም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ተመለሱ ፡
ወረዊጸነ ፡ በጸሕነ ፡ ብሔረ ፡ ቆስያ ፡
ፈጥነን ፡ ቆስያ ፡ ደረስነ ፡
፪ ፤ ወበሳኒታ ፡ ወረድነ ፡ ሩድ ፡
በነጋው ፡ ሩድ ፡ ደረስነ ።
ወእምህየ ፡ ሖርነ ፡ ለጳጥራ ፡
ከዚያም ፡ ወጥተን ፡ ወደ ፡ ለጳጥራ ፡ ሄድን፤
ወረከብነ ፡ ሐመረ ፡ ዘየሐውር ፡ ፊንቂ ፡
ወደ ፡ ፊንቂ ፡ የሚሄድ ፡ መርከብ ፡ አግኝ
ተን ፡
ወዐረግነ ፡ ውስቴታ ፡
በሷ ፡ ተጭነን ።
፫ ፤ ወነገድነ ፡ ወርኢናሃ ፡ ለቆጵሮስ ፡ ወኅደግናሃ ፡ በፀጋምነ ፡ ወሖርነ ፡
ቆጵሮስን ፡ እያየን ፡ ግራ ፡ ግራውን ፡ ትተ
ናት ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ ሄድነ ፡ ሐተታ ፡ በር
ናባስ ፡ ከዚያ ፡ አለና ።
ወወረድነ ፡ ጢሮስ ፡
ከዚያም ፡ ወርደን ፡ ወደ ፡ ጢሮስ ፡ ሄድነ ።
እስመ ፡ ህየ ፡ አውረዱ ፡ ኵሎ ፡ ዘውስተ ፡ ሐመር ፡
በመርከብ ፡ ያለውን ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ ከዚያ ፡
አሳርፈው ፡ ነበርና ።
፬ ፤ ወበህየ ፡ ረከብናሆሙ ፡ ለአርድእት ፡
በህየ ፡ በጢሮስ ፡ ምእመናንን ፡ አገኘና
ቸው ፡
ወነበርነ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ፡
ሰባት ፡ ቀን ፡ ከዚያ ፡ ሰነበትነ ፡

ወይቤልዎ ፡ እሙንቱ ፡ ለጳውሎስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኢይዕርግ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
እነሱም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገልጦላ
ቸው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዳይወጣ ፡
ጳውሎስን ፡ አትውጣ ፡ አሉት ፡ ቍ ፡ ፲፩ ፡
፲፪ ። ም ፡ ፳ ፡ ፳፫ ።
፭ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ወፃእነ ፡ ለፍኖት ፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ወጥተን ፡ መንገድ፡
በጀመርነ ፡ ጊዜ ፡
ወአስተፋነዉነ ፡ ኵሉ ፡ ወአንስትኒ ፡ ወደቂቅኒ፡ ለአፍአ ፡ ሀገር ፡
ሴቶቹም ፡ ልጆቹም ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ከተ
ማው ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ተከትለው ፡ ሸኙን ።
ወሰገዱ፡ በብረኪሆሙ፡ ኀበ፡ ጽንፈ፡ ባሕር፡ወጸለይነ፡
ከባሕሩ፡ ወደብ፡ በደረስነ ፡ ጊዜ ፡ ተምበር
ክከው ፡ የመሰነባበቻ ፡ ጸሎት ፡ ጸለይነ ፡
ም ፡ ፳ ፡ ፳፮ ።
፮ ፤ ወተአማኅነ ፡ በበይናቲነ ፡ ወተፋነውነ ፡
እርስ ፡ በርሳችን ፡ ተሰነባብተን ፡ ተለያ
የን ፡
ወእምዝ ፡ ዐረግነ ፡ ሐመረ ፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በመርከብ ፡ ተጭነን ፡
ሄድነ ።
ወእሙንቱሂ ፡ አተዉ ፡ አብያቲሆሙ ፡
እነሱም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ተመለሱ ።
፯ ፤ ወንሕነሰ ፡ ነገድነ ፡ እምጢሮስ ፡ ዘይእቲ ፡ ሱር ፡
እኛ ፡ ግን ፡ ያችውም ፡ ሶርያ ፡ ናት ፡ ከጢ
ሮስ ፡ ወጥተን ፡ ሄድነ ፡
ወበጻሕነ ፡ ሀገረ ፡ አካ፡ ወተአማኅናሆሙ ፡ ለአኅዊነ ።
ወደ ፡ አካ ፡ ደርሰን ፡ ወንድሞቻችነንም ፡
ተገናኘናቸው ፡



ወነበርነ ፡ ኀቤሆሙ ፡ አሐተ ፡ ዕለተ ፡
ከነሱ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አደርነ ።
፰ ፤ ወበሳኒታ ፡ ወጻእነ ፡ ወሖርነ ፡ ቂሣርያ ፡
በነጋውም ፡ ከዚያ ፡ ወጥተን ፡ ወደ ፡ ቂሣ
ርያ ፡ ሄድነ ።
ወቦእነ ፡ ቤተ ፡ ፊልጶስ ፡ ዜናዊ ፡ አሐዱ ፡ እምሰብዐቱ ፡ አኀው ፡ ዲያቆናት ፡
ከሰባቱ ፡ ዲያቆናት ፡ አንዱ ፡ ወንጌልን ፡
ከሚያስተምር ፡ ከፊልጶስ ፡ ቤት ፡ ገባን፡
ም ፡ ፰ ፡ ፶ ።
፱ ፤ ወሀለዋ ፡ ኀቤሁ ፡ አርባዕ ፡ ደናግል ፡ አዋልዲሁ ፡
አራት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፡
ወይትኔበዩ ፡
ወንጌልን ፡ ያስተምሩ ፡ ቋንቋ ፡ ይተረ
ጕሙ ፡ መጻእያትን ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፡
ም ፡ ፪ ፡ ፲፯ ።
፲ ፤ ወነበርነ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ ኀቤሁ ፡
ከሱ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ሰነበትነ ፡
ወወረደ፡ አሐዱ፡ነቢይ፡ እምይሁዳ፡ ዘስሙ፡ አጋቦስ ።
መጻእያትን ፡ የሚናገር ፡ አጋቦስ ፡ የሚ
ባል ፡ ሰው ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፳፰ ፡
፲፩ ፤ ወመጽአ ፡ ኀቤነ ፡
ከይሁዳ ፡ እኛ ፡ ወዳለንበት ፡ መጥቶ ፡
ወነሥአ ፡ ቅናቶ ፡ ለጳውሎስ ፡
የጳውሎስን ፡ ዝናር ፡ አንሥቶ ፡
ወተአሥረ ፡ ለሊሁ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡
እጁን ፡ እግሩን ፡ አሥሮ ፡
ወይቤ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለእግዚእ ፡ ዝ ፡ ቅናት ፡ ከመዝ ፡ የአሥርዎ ፡ አይሁድ ፡ በኢየሩ
ሳሌም ፡
የዚህን ፡ ዝናር ፡ ባለቤት ፡ አይሁድ ፡ በኢ
የሩሳሌም ፡ እንዲህ ፡ ያሥሩታል ፡

ወያገብእዎ ፡ ለአሕዛብ ፡
ለአሕዛብም ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡታል ፡
አለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሎ ፡ ትንቢት ፡
ተናገረ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፳፫ ።
፲፪ ፤ ወዘንተ ፡ ሰሚዐነ ፡ አስተብቍዕናሁ ፡ ለጳውሎስ ፡ ምስለ ፡ ሰብአ ፡ ውእቱ ፡ ብሔር ፡ ከመ ፡ ኢይ
ዕርግ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ይህነን ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ አገር ፡
ያሉ ፡ ሰዎችን ፡ ይዘን ፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡
እንዳይወጣ ፡ ማለድነው ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፳፱ ።
፲፫ ፤ ወተሠጥወ ፡ ጳውሎስ ፡ ወይቤ ፡ ለምንት ፡
ከመዝ ፡ ትገብሩ ፡
ጳውሎስም ፡ ለምን ፡ እንዲህ ፡ ታደርጋላ
ችሁ ፡
ወትበክዩ ፡
ለምን ፡ ታለቅሳላችሁ ፡
ወትሰብሩኒ ፡ ልብየ ፡
ልቡናዬንስ ፡ ለምን ፡ ታደክሙኛላችሁ ፡
አንሰኬ ፡ አኮ ፡ ባሕቲቶ ፡ ማሕሜ ፡ ወመዋቅሕተ ፡
ዘእሴፎ ።
እኔስ ፡ ተስፋ፡ የማደርግ፡ እሥራትን፡ብቻ ፡
አይደለም ፡
ዓዲ ፡ ለመዊትኒ ፡ ጥቡዕ ፡ አነ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በእ
ንተ ፡ ስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ።
የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ስም ፡
ለማስተማር ፡ በኢየሩሳሌም፡ ለመሞትም፡
ቆርጫለሁ ፡ እንጅ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፳፬ ።
፲፬ ፤ ወሶበ ፡ አበየ ፡ አርመምነ ፡
አይሆንም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡
ወኅደግናሁ ፡ ወንቤ ፡ ዘፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለይ
ኩን ፡
እግዚአብሔር ፡ የፈቀደው ፡ ይሁን ፡ ብለ
ን ፡ ተውነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፭ ፤ ክፍል ፡ ፹፪ ። ወእምድኅረ ፡ እማንቱ ፡ መዋዕል ፡ አስተዳሎነ ፡ ወዐረግነ ፡ ኢየሩሳሌም ፡

ወነበርነ ፡ ኀቤሁ ፡ ብዙኀ፡ መዋዕለ ፡ ብሎ፡ ነበርና ፡ ከብዙ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ስንቃች ነን፡አዘጋጅተን፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ወጣን ።

፲፮ ፤ ወቦ ፡ እምነ ፡ አርዳእ ፡ እለ ፡ መጽኡ ፡ ምስሌነ ፡ እምቂሣርያ ፡

በቂሣርያም ፡ ካሉ ፡ ምእመናን ፡ ወገን ፡ እኛን ፡ ተከትለው ፡ የመጡ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ።

ወሐርነ ፡ ወኀደርነ ፡ ኀበ ፡ ምናሶን ፡ ዘሀገረ ፡ ቆጵሮስ፡ ዘእምአርድእት ፡ ቀዳማውያን ፡

ሂደን ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ካመኑ ፡ ከሰብዓ ፡ አርድእት ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡ ከቆጵሮስ ፡ ሰው ፡ ከምናሶን ፡ ቤት ፡ አደርን ።

፲፯ ፤ ወበጺሐነ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተቀበሉነ ፡ አኀዊነ ፡ በፍሥሓ ፡

ኢየሩሳሌም ፡ በደረስን ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አሰኝተው ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ወንድሞቻችን ፡ ተቀበሉን ።

፲፰ ፤ ወበሳኒታ ፡ ቦእነ ፡ ምስለ ፡ ጳውሎስ ፡ ኀበ ፡ ያዕቆብ ፡ ወኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ ቀሲሳን ፡

በነጋው ፡ ጳውሎስን ፡ ተከትለን ፡ ከያዕቆብና ፡ ከቀሳውስት ፡ ዘንድ ፡ ገባን ፡ ሐተታ ፡ ምነው ፡ በጺሐነ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ብሎ ፡ አልነበረምን ፡ ቢሉ ፡ እንደ ፡ቀኑስ ቋም ፡ ገብተው ፡ አድረዋል ፡

ወሰላመ ፡ ንቤሎሙ ፡

ገብተን ፡ እንዴት ፡ ናችሁ ፡ አልናቸው ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፫ ። ገላት ፡ ፩ ፡ ፲፱ ።

፲፱ ፤ ወተአምኆሙ ፡ ጳውሎስ ፡

ጳውሎስም ፡ ተገናኛቸው ፡

ወዜነዎሙ ፡ ኵሎ ፡ ዘገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በውስተ ፡ አሕዛብ ፡ በመልእክተ ፡ ዚአሁ ።

ብሱ ፡ ሐዋርያነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአሕዛብ ፡ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፡ ነገራቸው ። አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ለሱ ፡ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፡ ነገራቸው ።

፳ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ አእኰቱ ፡ እግዚአብሔርሃ ፡

ይህንንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ፡

ወይቤልዎ ፡ ትሬኢኑ ፡ አ ፡ እኁነ ፡ ሚ ፡ መጠን ፡ አእላፍ ፡ በውስተ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡

ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ ያመኑት ፡ ምን፡ ያህል፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ አለ ፡ ብዙ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ታያለህን ፡ አሉት ፡

ወኵሎሙ ፡ ምሁራነ ፡ ኦሪት ፡

ኦሪትን ፡ ከተማሩ ፡ ወገን ፡ ያመኑ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ፩ ።

፳፩ ፤ ወዳዕሙ ፡ ይቤልዎሙ ፡ በእንቲአከ ፡ ከመ ፡ ዘኢይከውን ፡ ትሜህር ፡

የማይገባ ፡ ትምህርት ፡ እንድታስተምር ፡ ያንተን ፡ ነገር ፡ ነግረዋቸው ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ አዝነዋል ፡ እንጅ ፡

ወታኀድጎሙ ፡ ሕገ ፡ ሙሴ ፡

የሙሴን ፡ ሥርዐት ፡ እንድታስተምር ፡

ወትከልአሙ ፡ ለአሕዛብ ፡

አሕዛብን ፡ እንድትከለክላቸው ፡

ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ አምኑ ፡ እምውስተ ፡ አይሁድ ፡ ኢይግዝሩ ፡ ደቂቆሙ ፡

ከአይሁድም ፡ ወገን ፡ ያመኑት ፡ ልጆቻቸውን ፡ እንዳይገዝሩ ፡

ወኢይግበሩ ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡

ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ እንዳይፈጽሙ ፡ እንድትከለክላቸው ፡ ነግረዋቸው ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ አዝነዋል ፡ እንጅ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ፫ ። ሮሜ ፡ ፲ ፡ ፬ ።



፳፪ ፤ ወይእዜኒ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይስምዑ ፡ ከመ ፡ መጻእከ ፡ ዝየ ፡

አሁንም ፡ ከዚህ ፡ መምጣትህን ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ አላቸው ።

፳፫ ፤ ወከመዝ ፡ ግበር ፡ ዘከመ ፡ ንብለከ ፡

እንደምንነግርህ ፡ አድርግ ፡

ሀለዉ ፡ ኀቤነ ፡ አርባዕቱ ፡ ዕደው ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ ብፅዓት ፡ ያንጽሑ ፡ ርእሶሙ ፡

ከኛ ፡ ዘንድ ፡ በዓለ ፡ አንጽሖ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ብፅዓት ፡ ያለባቸው ፡ አራት ፡ ሰዎች ፡ አሉ ።

፳፬ ፤ ንሥኦሙ ፡ ወሰዶሙ ፡

ይዘሃቸው ፡ ተለይ ፡

ወአንጽሕ ፡ ርእሰከ ፡ ምስሌሆሙ ፡

አንተም ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ እንደነሱ ፡ በዓለ፡ አንጽሖ ፡ አድርግ ፡

ወአስተዋፅእ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ከመ ፡ ይትላፀዩ፡ ርእሶሙ ፡

ራሳቸውን ፡ ይላጩ ፡ ዘንድ ፡ ስለነሱ ፡ የምላጩን ፡ ዋጋ ፡ አወጣጣ ። አንድም ፡ ከሰው ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ፡ የሚለዩበትን ፡ ቀን ፡ ቆጥረህ ፡ ንገራቸው ፡

ወያእምሩ ፡ ኵሎሙ ፡ ከመ ፡ ሐሰት ፡ ውእቱ ፡ ዘየሐምዩከ ።

ሁሉም ፡ አንተን ፡ የሚነቅፉበት ፡ ነገር ፡ ሐሰት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ ተዐቅብ ፡ አንተሂ ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡

አንተም ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ እንድትጠብቅ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ንገራቸው ፡ ም ፡ ፲፰፡ ፲፰።

፳፭ ፤ ወበእንተሰ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ የአምኑ ፡ ንሕነ ፡ አዘዝነ ፡ ከመ ፡ ይትዐቀቡ ፡ ዘይትሔረሙ ፡ እምዘ ፡ ይዘብሑ ፡ ለአማልክት ።

ስላመኑ ፡ አሕዛብ ፡ ግን ፡ ለጣዖት ፡ ከሚሠዉት ፡ መሥዋዕት ፡ ይከለከሉ ፡ ዘንድ ፡ የሚከለከሉበትን ፡ ሥራት ፡ ሠርተናል ፡ አሉት ፡

ወእምዝሙት ፡

ከዝሙት ፡ ይከለከሉ ፡ ዘንድ ፡

ወእማውታ ፡

ሙቶ ፡ የተገኘውን ፡ ከመብላት ፡

ወደም ፡

ደም ፡ ከመብላት ፡ ይከለከሉ ፡ ዘንድ ፡ ሐተታ ፡ ደሙ ፡ ሲረጋ ፡ አንፍረው ፡ ቆልተው ፡ ይበሉታልና ፡ ም ፡ ፲፭ ፡ ፳ ፡ ፳፱ ።

፳፮ ፤ ወነሥአሙ ፡ ጳውሎስ ፡ ለእሙንቱ ፡ ዕደው፡ ወተቀደሰ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወቦአ ፡ ምኵራበ ፡

ጳውሎስም ፡ እሊያን ፡ አራቱን ፡ ሰዎች ፡ ይዞ ፡ ተለየ ፡

ወነገሮሙ ፡ መዋዕለ ፡ ዕድሜ ፡ ንጽሖሙ ፡

ከምኵራቡ ፡ ገብቶ ፡ ከሰው ፡ የሚለዩበትን ፡ ቀን ፡ ቆጥሮ ፡ ነገራቸው ፡

እስከ ፡ ያበውኡ ፡ መሥዋዕተ ፡ ለለአሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡

ከነሱ ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ መሥዋዕት ፡ እስኪሠዉ ፡ ድረስ ፡ ነገራቸው ፡ ሐተታ ፡ ብፅዓት ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ ይሰነብታል ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ መሥዋዕት ፡ አሠውቶ ፡ ማየ ፡ ምንዛኅ ፡ ተረጭቶ ፡ ልብሱን ፡ አንጽቶ ፡ ገላውን ፡ ታጥቦ ፡ ከሰው ፡ ይገናኛልና ፡ ዘኁል ፡ ፮ ፡ ፲፫ ።

፳፯ ፤ ክፍል ፡ ፹፫ ። ወአመ ፡ ሰቡዕ ፡ መዋዕል ፡ ርእይዎ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ መጽኡ ፡ እምእስያ ፡ ለጳውሎስ፡ በምኵራብ ፡

በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ከእስያ ፡ የመጡ ፡ አይሁድ ፡ ጳውሎስን ፡ ከምኵራቡ፡ ባዩት፡ ጊዜ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወአስተጋብኡ ፡ ላዕሌሁ ፡ ኵሎ ፡ ሕዝበ ፡ ወአኀዝዎ ።

ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስበው ፡ ያዙት ።

፳፰ ፤ ወዐውየዉ ፡ ወይቤሉ ፡ አንትሙ ፡ ሰብአ ፡ እስራኤል ፡ ርድኡነ ፡

እናንት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እርዱን ፡ እያሉ ፡ ጮሁ ፡

ነዋ ፡ ዝ ፡ ብእሲ ፡ ዘይገብር ፡ ማዕሌተ ፡

በቍጣር ፡ ላይ ፡ አመፅን ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ነው ፡

ወየሀውክ ፡ ሕዝበ ፡ በኵለሄ ፡

ባራቱ ፡ መዓዝን ፡ እየዞረ ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ያሸብራል ፡ የሚያሸብር ፡ ይህ ፡ ነው ፡

ወየዐሉ ፡ ኦሪተ ፡ ወምኵራበ ፡ ወይሜህር ፡ ለኵሉ ፡

ኦሪትን ፡ ያሳልፋል ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ያሳድፋል ፡ አለ ፡ ኦሪት ፡ ትጠፋለች ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ትፈርሳለች ፡ እያለ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ያስተምራል ፡ የሚያስተ ምር ፡ ይህ ፡ ነው ፡

ወዓዲ ፡ አረሚነ ፡ አብአ ፡ ምኵራበ ፡ ወአርኰሰ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡

በዚያውም ፡ ላይ ፡ አረማውያንን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እያገባ ፡ ቤተ ፡ መቅደ ስን ፡ ያሳድፋል ፡ የሚያሳድፍ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ጮሁ ፡ ም ፡ ፮ ፡ ፲፬ ። ሕዝ ፡ ፵፬ ፡ ፯ ።

፳፱ ፤ እስመ ፡ ርእይዎ ፡ ለጥሮፊሞስ ፡ ዘሀገረ ፡ ኤፌሶን ፡ ምስሌሁ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡

የኤፌሶን ፡ ሰው ፡ የሚሆን ፡ ጥሮፊሞስን ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ በከተማ ፡ አይተውት ፡ ነበ ርና ፡

ወመሰሎሙ ፡ ዘአብአ ፡ ጳውሎስ ፡ ምኵራበ ፡

ከምኵራቡ ፡ ያገባው ፡ መስሏቸው ፡ ሳያ ገባው ፡ አይቀርም ፡ ብለው ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፬። ፪ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፳ ።

፴ ፤ ወተሀውከ ፡ ኵሉ ፡ ሀገር ፡

አገሪቱ ፡ ተሸበረች ፡

ወሮጹ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡

ሕዝቡም ፡ ፈጥነው ፡ ሄደው ፡

ወሰሐብዎ ፡ ለጳውሎስ ፡

ጳውሎስን ፡ እየጐተቱ ፡

ወአውፅእዎ ፡ እምኵራብ ፡

ከምኵራቡ ፡ አወጡት ፡

ወዐጸዉ ፡ ኆኅተ ፡ ወፈቀዱ ፡ ይቅትልዎ ፡

ሊገሉት ፡ ወደው ፡ ደጁን ፡ ዘጉበት ፡

ወዘበጥዎ ፡ ብዙኀ ፡

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መላልሰው ፡ ደበደቡት ።

፴፩ ፤ ወበጽሐ ፡ መልእክት ፡ ኀበ ፡ መልአከ ፡ ሴ ጺራ ፡ ከመ ፡ ተሀውከት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኵላ ።

ኢየሩሳሌም ፡ በመላዋ ፡ እንደ ፡ ተሸበ ረች ፡ የሚነግር ፡ ወደ ፡ ጭፍራው ፡ አለቃ፡ መልእክት ፡ ደረሰ ።

፴፪ ፤ ወተንሥአ ፡ መልአከ ፡ ሰቢሃ ፡ ወሮጸ፲፻ኀቤ ሆሙ ፡ ምስለ ፡ ወዓሊሁ ፡

ሹሙም ፡ ተነሥቶ ፡ ብላቴናውን ፡ አስከ ትሎ ፡ ሄደ ፡

ወሶበ ፡ ርእይዎ ፡ ለመልአክ ፡ ወለመስፍን ፡ ምስለ ፡ ወዓሊሁ ፡

ሹሙም ፡ ብላቴናውን ፡ አስከትሎ ፡ ሲ መጣ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡

ኀደጉ ፡ ዘቢጦቶ ፡ ለጳውሎስ ፡

ጳውሎስን ፡ መምታቱን ፡ ተዉ ።

፴፫ ፤ ወእምዝ ፡ ቀርበ ፡ መልአክ ፡ ወአኀዞ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሹሙ ፡ ቀርቦ ፡ ያዘው ፡

ወአዘዘ ፡ ይሞቅሕዎ ፡ (ይእሥርዎ) ፡

እሠሩት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፡



ወሐተተ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡

በደሉ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መረመረ ፡ በደሉ ፡ ምንድነው ፡ ብሎ ፡

ወምንተ ፡ ገብረ ፡

ምን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፡ ብሎ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፳፫ ።

፴፬ ፤ ወይኬልሑ ፡ ሕዝብ ፡

ሕዝቡም ፡ ይጮሁ ፡ ነበር ፡

ወስእነ ፡ መልአክ ፡ አእምሮ ፡ ጥዩቀ ፡ በእንተ ፡ ዘይት ሀወክ ፡ ሰብእ ፡

ሹሙም ፡ ከጩኸቱ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ የነገሩን ፡ ድርስ ፡ ማወቅ ፡ ተሳነው ፡

ወአዘዘ ፡ ያዕርግዎ ፡ ውስተ ፡ ዐውድ ፡

ወደ ፡ ፍርድ ፡ አደባባይ ፡ አውጡት ፡ ብሎ አዘዘ ።

፴፭ ፤ ወሶበ ፡ ዐርገ ፡ መዓርገ ፡

አንዱን ፡ እርከን ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡

አዕረግዎ ፡ እንዘ ፡ ይጸውርዎ ፡ ወዐልት ፡

ጭፍሮች ፡ እየተቀባበሉ ፡ አወጡት ፡ ሐተታ ፡ በገድል ፡ ተቀጥቅጦ ፡ ኗሪ ፡ ነው ፡ ያሞሌን ፡ ያህል ፡ ይከብድን ፡

እስመ ፡ ይጸዐቅ ፡ ሰብእ ፡

ሰው ፡ በዝቶ ፡ ነበርና ፡ አዕረግዎ ፡ ላለው ።

፴፮ ፤ ወይተልውዎ ፡ ብዙኃን ፡ ወይኬልሑ ፡ ሕዝብ ፡

ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ እየተከተሉ ፡ ይጮሁ ፡ ነበር ፡

ወይብሉ ፡ አእትትዎ ።

በሞት ፡ አርቁት ፡ እያሉ ።

፴፯ ፤ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ዐውድ ፡

ወደ ፡ ፍርድ ፡ አደባባይ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡

ይቤሎ ፡ ጳውሎስ ፡ ለመልአክ ፡ ታበውሐኒኑ ፡ እንግ ርከ ፡

ጳውሎስ ፡ ሹሙን ፡ ነገሬን ፡ እነግርህ ፡ ዘንድ ፡ ታሰናብተኛለህን ፡ አለው ።

፴፰ ፤ ወይቤሎ ፡ መልአክ ፡ ተአምርኑ ፡ ጽርዐ ።

የፅርዕ ፡ ሰው ፡ ነህን ። አንድም ፡ የፅርዕ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ታውቃለህን ። አን ድም ፡ የፅርዕን ፡ ቋንቋ ፡ ታውቃለህን ።

አንተሁ ፡ እንጋ ፡ ዝኩ ፡ ግብጻዊ ፡ ዘቀዲሙ ፡ ገበርከ፡ ማዕሌተ ።

ወይስ ፡ በቍጣር ፡ ላይ ፡ ዐመፅን ፡ ያደር ጋል ፡ ይሉህ ፡ የነበረ ፡ ግብጻዊ ፡ አንተ ፡ ነህን ፡

ወአውፃእከ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ አርብዓ ፡ ምእተ ፡ ብ እሴ ፡ ዘሕዝበ ፡ ቢቃርዮን ።

ከቢቃርዮን ፡ ወገን ፡ አራት ፡ ሽሕ ፡ ሰዎ ች ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ይዞ ፡ ወጣ ፡ ይሉህ ፡ የነበረ ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ አለው ።

፴፱ ፤ ወይቤሎ ፡ ጳውሎስ ፡ አንሰ ፡ ብእሲ ፡ አይሁ ዳዊ ፡ ዘሀገረ ፡ ጠርሴስ ፡ ዘቂልቅያ ፡

ጳውሎስም ፡ እኔ ፡ የቂልቅያ ፡ አውራጃ ፡ የምትሆን ፡ የጠርሴስ ፡ ሰው ፡ የምሆን ፡ አይሁዳዊ ፡ ነኝ ፡

ሀገር ፡ እምርት ፡ እንተ ፡ ተወለድኩ ፡ ባቲ ፡

የተወለድሁባትም፡አገር፡የታወቀች፡ናት ።

አስተበቍዕ ፡ ኀቤከ ፡ ከመ ፡ ታብሐኒ ፡ እንግሮሙ ፡ ለሕዝብ ።

ነገሬን ፡ ለሕዝቡ ፡ እነግራቸው ፡ ዘንድ ፡ እንድታሰናብተኝ ፡ እማልድሃለሁ፡ አለው፡ ም ፡ ፱ ፡ ፲፭ ።

፵ ፤ ወሶበ ፡ አብሖ ፡

ተናገር ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡

ወቆመ ፡ ውስተ ፡ መዓርግ ፡ ጳውሎስ ፡

ከፍ ፡ ካለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ቁሞ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወአንሥአ ፡ እዴሁ ፡ ኀበ ፡ ሕዝብ ፡

እጁን ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ አመለከተ ፡ እጅ ፡ ለነገር ፡ ያግዛልና ፡

ወይቤሎሙ ፡ አርምሙ ፡

ዝም ፡ በሉ ፡ አላቸው ፡

ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ አርመሙ ፡ ከልሐ ፡ ጳውሎስ ፡ በነገረ ፡ ዕብራይስጥ ።

ዝም ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ተናገረ ፡ ም ፡ ፲፪ ፡ ፲፯ ። ፲፫ ፡ ፲፮ ። ፲፱ ፡ ፴፫ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፪ ።

፩ ፤ ወይቤ ፡ ስምዑ ፡ አኀዊነ ፡ ወአበዊነ ፡ ዘእወቅሥ ፡ ለክሙ ፡ ይእዜ ።

አባቶቻችን ፡ ወንድሞቻችን ፡ ዛሬ ፡ እኔ ፡ የምነግራችሁን ፡ ነገር ፡ ስሙ ፡ ም ፡ ፯ ፡ ፪ ። ፲፫ ፡ ፳፮ ።

፪ ፤ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ከመ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ይነግሮሙ ፡ ፈድፋደ ፡ አፅምዕዎ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ጳውሎስ ።

በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ሲናገር ፡ በሰሙት ፡ ጊዜ ፡ ጸጥ ፡ ብለው ፡ አደመጡት ። እሱም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፵ ።

፫ ፤ አንሰ ፡ ብእሲ ፡ አይሁዳዊ ፡

እኔ ፡ አይሁዳዊ ፡ ነኝ ፡

ወተወለድኩ ፡ በሀገረ ፡ ጠርሴስ ፡ ዘቂልቅያ ፡

የቂልቅያ ፡ አውራጃ ፡ በምትሆን ፡ በጠርሴስ ፡ አገር ፡ ተወልጃለሁ ፡

ወልህቁ ፡ በዛቲ ፡ ሀገር ፡ በታሕተ ፡ እገሪሁ ፡ ለገማልያል ፡

ከገማልያል ፡ ቤት ፡ ስማር ፡ አድጌያለሁ ።

ወተምህርኩ ፡ በሕገ ፡ አበውየ ፡

የአባቶቼን ፡ ሕግ ፡ አሪትን ፡ ስማር ፡ አድጌያለሁ ፡

ወኮንኩ ፡ ቀናኤ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

ለእግዚአብሔር ፡ እቀናለሁ ፡ እል ፡ ነበርና ፡

ከመ ፡ ኵልክሙ ፡ አንትሙ ፡ ዮም ።

እናንት ፡ ዛሬ ፡ እንቀናለን ፡ እንድትሉ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ፴፬ ። ም ፡ ፱ ፡ ፩—፳፪ ። ፳፮ ፡ ፱—፲፳ ።

፬ ፤ ወሰደድክዎሙ ፡

ምእመናንን ፡ ከዋሉበት ፡ አላሳድር ፡ ካደሩበት ፡ አላውል ፡ እል ፡ ነበር ፡

ወቀተልክዎሙ ፡ እንዘ ፡ እሞቅሖሙ ፡ ለእደዊሆሙ ፡ ወለአንስትያሆሙ ፡

ሴቶቹንም ፡ ወንዶቹንም ፡ እያሠርሁ ፡ መከራ ፡ አጸናባቸው ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፰ ፡ ፫ ።

፭ ፤ ወየአምሩ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወረበናት ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ነሣእኩ ፡ እምኀቤሆሙ ፡ መጽሐፈ ፡ መባሕት ፡

ቃድነት ፡ ሹመት ፡ የተካሰስሁባቸው ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ረበናትም ፡ ሁሉ ፡ ያውቃሉ ።

ከመ ፡ እሑር ፡ ኀበ ፡ አኀው ፡ እለ ፡ በደማስቆ ፡

በደማስቆ ፡ ወዳሉ ፡ ወደ ፡ አኀው ፡ ሂጄ ።

ከመ ፡ አምጽእሙ ፡ ለእለ ፡ ሀለዉ ፡ ህየ ፡ ወአእትዎሙ ፡ ሙቁሓኒሆሙ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይትኰነኑ ።

ከዚያ ፡ ያሉትን ፡ እያሠርሁ ፡ እንዲቀጡ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እወስዳቸው ፡ ዘንድ ።

፮ ፤ ክፍል ፡ ፴፬ ። ወእምዝ ፡ እንዘ ፡ አሐውር ፡ ደማስቆ ፡ አልጺቅየ ፡ ኀበ ፡ ሀገር ፡

ቃስድነት ፡ ሹመት ፡ ተካስሼ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ስሄድ ፡ ከከተማው ፡ በደረስሁ ፡ ጊዜ ።

ሠሶበ ፡ ይከውን ፡ ቀትረ ፡ ግብተ ፡ በረቀ ፡ መብረቅ ፡ ዐቢይ ፡ እምሰማይ ፡ ላዕሌየ ።

ቀትር ፡ ሲሆን ፡ በላዬ ፡ ላይ ፡ ከወደ ፡



ሰማይ ፡ ብርሃን ፡ በራ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፫—፲፯ ። ፮ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፳ ።

፯ ፤ ወነጽሐኒ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡

ወደ ፡ ምድር ፡ ጣለኝ ።

ወሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ ዘይብለኒ ፡ ሳውል ፡ ሳውል ፡ ለምንት ፡ ትሰድደኒ ።

ሳውል ፡ ከዋልሁበት ፡ አላሳድር ፡ ካደርሁበት ፡ አላውል ፡ ለምን ፡ ትለኛለህ ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ ፡ ም ፡ ፳፮ ፡ ፲፬ ፡ ፲፫ ።

፰ ፤ ወተሠጠውክዎ ፡ ወእቤሎ ፡ መኑ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ማነህ ፡ አልሁት ።

ወይቤለኒ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ናዝራዊ ፡ ዘአንተ ፡ ትሰድደኒ ፡

አንተ ፡ ከዋልሁበት ፡ አላሳድር ፡ ካደርሁበት ፡ አላውል ፡ የምትለኝ ፡ የናዝሬቱ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ኢየሱስ ፡ ነኝ ፡ አለኝ ።

፱ ፤ ወእለ ፡ ሀለዉ ፡ ምስሌየ ፡ ርእዩ ፡ መብረቆ ፡ ወደንገፁ ።

ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያሉትም ፡ ብርሃኑን ፡ አይተው ፡ ደነገጡ ፡ (ዕርቅ) ፡ ከዚህ ፡ ርእዩ ፡ አለ ፡ ከዚያ ፡ ኢርእዩ ፡ ይላል ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ መልኩን ፡ አላዩምና ፡ ከዚያ ፡ ኢርእዩ ፡ አለ ፡ ብርሃን ፡ አይተዋልና ፡ ከዚህ ፡ ርእዩ ፡ አለ ።

ወቃለሰ ፡ ዘይትናገረኒ ፡ ኢሰምዑ ፡

የሚነግረኝን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልሰሙም ፡ (ዕርቅ) ፡ ከዚያ ፡ ሰምዑ ፡ አለ ፡ ከዚህ ፡ ኢሰምዑ ፡ አለ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ድምፁን ፡ ሰምተዋልና ፡ ከዚያ ፡ ሰምዑ ፡ አለ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ አልሰሙምና ፡ ከዚህ ፡ ኢሰምዑ ፡ አለ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፯ ።

፲ ፤ ወእቤ ፡ ምንተ ፡ እግበር ፡ እግዚእየ ፡

ጌታዬ ፡ ምን ፡ ልሥራ ፡ አልሁ ።

ወይቤለኒ ፡ ተንሥእ ፡ ወሑር ፡ ደማስቆ ፡ ወበህየ ፡ ይነግሩከ ፡ ዘሀለወከ ፡ ትግበር ።

ትሠራው ፡ ዘንድ ፡ ያለህን ፡ በደማስቆ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ይነግሩሃል ፡ ተነሥተህ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ሂድ ፡ አለኝ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፯ ።

፲፩ ፤ ወእምዝ ፡ ተጸለልኩ ፡ አዕይንትየ ፡ እምግርማ ፡ መብረቅ ፡

ከብርሃኑ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ዐይኔ ፡ ታወረ ፡

ወአልቦ ፡ ዘእሬኢ ፡

የማየው ፡ አልነበረም ።

ወእንዘ ፡ ይመርሑኒ ፡ እለ ፡ ምስሌየ ፡ በጻሕኩ ፡ ደማስቆ ፡

ከኔ ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ እየመሩኝ ፡ ደማስቆ ፡ ደረስሁ ።

፲፪ ፤ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ ሐናንያ ፡ ኄር ፡ ወፈራሂ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሕግ ።

በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ (በሕግ) ፡ ጸንቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ቸርነት ፡ ያለው ፡ ሐናንያ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ።

ወይንእድዎ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ደማስቆ ፡ አይሁድ ፡

በደማስቆ ፡ የሚኖሩ ፡ አይሁድ ፡ ሁሉ ፡ ያከብሩት ፡ ነበር ።

፲፫ ፤ ወመጽአ ፡ ኀቤየ ፡ ወቆመ ፡ ቅድሜየ ።

ወደኔ ፡ መጥቶ ፡ በፊቴ ፡ ቆመ ።

ወይቤለኒ ፡ ሳውል ፡ እኁየ ፡ ርኢ ፡

ሳውል ፡ ወንድሜ ፡ እይ ፡ አለኝ ።

ወርኢኩ ፡ ሶቤሃ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ ብርሃን ፡ አየሁ ።

፲፬ ፤ ወይቤለኒ ፡ አምላከ ፡ አበዊነ ፡ ሤመከ ፡

ያባቶቻችን ፡ ፈጣሪ ፡ መርጦሃል ፡ (ሹሞሃል) ።

ከመ ፡ ታእምር ፡ ፈቃዶ ፡

ፈቃዱ ፡ ወንጌልን ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወትርአዮ ፡ ለጻድቅ ፡

የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታው
ቀው ፡ ዘንድ ።

ወትስማዕ ፡ ቃሎ ፡ እምአፉሁ ፡

ያዘዘህን ፡ ትእዛዝ ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ ም ፡
፱ ፡ ፲፫ ።

፲፭ ፤ ወትኩኖ ፡ ሰማዕቶ ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡
በዘርኢከ ፡ ወበዘሰማዕከ ፡

ባየህ ፡ በሰማህ ፡ ገንዘብ ፡ ያየኸውን ፡ የሰ
ማኸውን ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ትመሰክር ፡
ዘንድ ።

፲፮ ፤ ወይእዜኒ ፡ ዘከመ ፡ ትገብር ፡ እነግረከ ፡

አሁንም ፡ የምታደርገውን ፡ እነግርሃለሁ ።

ተንሥእ ፡ ወተጠመቅ ፡

ተነሥተህ ፡ ተጠመቅ ።

ወተኀፀብ ፡ እምኀጣውኢከ ፡

ከኃጢአትህ ፡ ተለይ ።

ወጸውዕ ፡ ስሞ ፡

በስሙ ፡ እመን ፡ ስሙን ፡ አስተምር ፡
አለኝ ።

፲፯ ፤ ወእምዝ ፡ ገቢእየ ፡ ኢየሩሳሌም ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በተመ
ለስሁ ፡ ጊዜ ።

እንዘ ፡ እጼሊ ፡ በሌሊት ፡ በቤተ፡ መቅደስ፡ ደንገፅኩ ፡

ሌሊት ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ስጸልይ ፡ ተ
ደሞ ፡ መጣብኝ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፳፯ ።

፲፰ ፤ ወርኢክዎ ፡ እንዘ ፡ ይብለኒ ፡ ፃእ ፡ ፍጡነ ፡
እምኢየሩሳሌም ፡

ከኢየሩሳሌም ፡ ፈጥነህ ፡ ውጣ ፡ ሲለኝ ፡
ሰማሁ ፡

እስመ ፡ ኢይትዌከፉ ፡ ስምዐ ፡ ዚአከ ፡ በእንቲአየ ፡

ስለኔ ፡ የምትመሰክረውን ፡ ምስክርነት ፡
አይቀበሉህምና ።

፲፱ ፤ ወእቤ ፡ አነ ፡ እወ ፡ እግዚኦ ፡ ለሊሆሙ ፡ የኢ
ምሩ ፡ ከመ ፡ አነ ፡ ዘእሞቅሖሙ ፡ ወእቀሥፎሙ ፡
ለእለ ፡ የአምኑ ፡ ብከ ፡ በምኵራባቲሆሙ ።

ያመኑብህን ፡ ሁሉ ፡ ከምኵራባቸው ፡ እያ
ገባሁ ፡ እያሠርሁ ፡ የምገርፋቸው ፡ እኔ ፡
እንደ ፡ ነበርሁ ፡ ያውቃሉና ፡ አቤቱ ፡
አዎን ፡ አይቀበሉኝም ፡ ቊ ፡ ፬ ።

፳ ፤ ወአመሂ ፡ ቀተልዎ ፡ ለእስጢፋኖስ ፡ ሰማዕ
ትከ ፡ ሀሎኩ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ህየ ፡ ኀቡረ ፡

ያንተን ፡ ነገር ፡ የሚመሰክር ፡ የሚያስተ
ምር ፡ እስጢፋኖስንም ፡ በገደሉት ፡ ጊዜ ፡
በነገሩ ፡ ነበርሁበት ፡

ወአዐቀብ ፡ አልባሲሆሙ ፡ ለእለ ፡ ቀተልዎ ፡

የገደሉትን ፡ ሰዎች ፡ ልብስ ፡ እጠብቅ ፡
ነበር ፡ ም ፡ ፯ ፡ ፶፯ ። ፰ ፡ ፩ ።

፳፩ ፤ ወይቤለኒ ፡ ሑር ፡ እስመ ፡ እፌንወከ ፡ ኀበ ፡
አሕዛብ ፡ እለ ፡ ርሑቃን ፡ ትስብክ ፡

ከተስፋው ፡ ርቀው ፡ የነበሩ ፡ አሕዛብን ፡
ታስተምር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ እሰ
ድሃለሁና ፡ ሂድ ፡ አለኝ ፡

ወሰማዕክዎ ፡ ከመዝ ፡ ይቤለኒ ፡

እንዲህ ፡ ሲለኝ ፡ ሰማሁት ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፲፭ ።
፲፫ ፡ ፪ ።

፳፪ ፤ ወሰበ ፡ ሰምዑ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ እምጳውሎስ ፡
ከልሑ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ፡

ይህን ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡
ቃል ፡ ጮሁ ።

ወይቤሉ ፡ አእትትዎ ፡ ለዘከመዝ ፡ እምብሔርነ ፡

ከሀገራችን ፡ አስወጡት ፡

እስመ ፡ ኢይደልዎ ፡ ይሕየው ፡

በሀገራችን ፡ መኖር ፡ አይገባውምና ። አን
ድም ፡ በሞት ፡ አርቁት ፡ በሕይወት ፡
መኖር ፡ አይገባውምና ፡ እያሉ ፡ ጮሁ ፡
ም ፡ ፳፩ ፡ ፴፯ ።



፳፫ ፤ ወእንዘ፡ ይጠርኡ፡ ወይዌርዉ፡አልባሲሆሙ ፡

ልብሳቸውን ፡ እየወረወሩ ፡

ወይዘርዉ ፡ ጸበለ ፡ ውስተ ፡ ነፋስ ፡

ትቢያ ፡ በነፋስ ፡ እየበተኑ ፡ ሲጮሁ ።

፳፬ ፤ አዘዘ ፡ መልአክ ፡ ያብእዎ ፡ ውስተ ፡ ምኵ
ናን ፡ ወይቅሥፍዎ ፡ ወይሕትትዎ ፡ ጌጋዮ ፡

ሹሙም ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አግብታ
ችሁ ፡ ገርፋችሁ ፡ በደሉን ፡ አናግሩት ፡
ብሎ ፡ አዘዘ ።

ከመ፡ ያእምር፡ በእንተ፡ ምንት፡ የዐወይዉ፡ ላዕሌሁ ፡

የሚጮሁ ፡ ስለምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያውቅ፡
ዘንድ ።

፳፭ ፤ ወሶበ ፡ ሰሐብዎ ፡ በእገሪሁ ፡ ማእከለ ፡ እለ ፡
ይቀሥፍዎ ።

በሚገርፉት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ እግሩን ፡
ይዘው ፡ በጎተቱት ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱ ፡ በግራ
ና ፡ በቀኝ ፡ ሁነው ፡ ይገርፉታል ፡ የቀሩት፡
እግሩን ፡ ይዘው ፡ ይጐትቱታልና ። አን
ድም ፡ የሚገርፉት ፡ ሰዎች ፡ ባደባባይ ፡
መካከል ፡ እግሩን ፡ ይዘው ፡ በጐተቱት ፡
ጊዜ ፡

ይቤሎ ፡ ጳውሎስ ፡ ለሐቢ ፡ ዘይቀውም ፡ ኀቤሁ ፡
ይከውነክሙሁ ፡ ትቅሥፉ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ ዘእንበለ ፡
አበሳ ፡

ጳውሎስ ፡ ባጠገቡ ፡ ቁሞ ፡ ያለውን ፡ ሹ
ሙን ፡ በደል ፡ ሳይኖርበት ፡ የሮምን ፡ ሰ
ው ፡ ልትገርፉ ፡ ይገባችኋልን ፡ አለው ፡
ም ፡ ፲፮ ፡ ፴፯ ። ፳፫ ፡ ፳፯ ።

፳፮ ፤ ወሰሚዖ ፡ ሐቢ ፡

ሹሙም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡

ሖረ ፡ ኀበ ፡ መልአክ ፡ ወነገሮ ፡ ወይቤሎ ፡ አእምር ፡
ዘትገብር ፡ ዝኩ ፡ ብእሲ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ ውእቱ ፡

ሂዶ ፡ ላለቃው ፡ የሮም ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ አለ ፡
የምታደርገውን ፡ ዕወቅ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

፳፯ ፤ ወቀርበ ፡ ኀቤሁ ፡ መልአክ ፡ ወይቤሎ ፡ ንግ
ረኒ ፡ እስኩ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜኑ ፡ አንተ ።

ሹሙም ፡ ቀርቦ ፡ የሮም ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡
ትላለህን ፡ እስቲ ፡ ንገረኝ ፡ አለው ፡

ወይቤ ፡ እወ ፡

እሱም ፡ አዎን ፡ አለ ።

፳፰ ፤ ወተሠጥዎ ፡ መልአክ ፡ ወይቤሎ ፡ አንሰኬ ፡
ብዙኀ ፡ ንዋየ ፡ ውሂብየ ፡ ረከብክዋ ፡ ለዛቲ ፡ ሢመት፡

ይቺን ፡ ሹመት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥቼ ፡
ተሹሜያታለሁ ፡ የሮም ፡ ሰው ፡ መሆን
ህን ፡ ለምን ፡ ያልነገርኸኝ ፡ አንተን ፡ ለማ
ዳን ፡ ሳትሆነኝ ፡ ትቀርን ፡ ነበር ፡ አለው ፡
የርኅራኄ ፡ አነጋገር ። አንድም ፡ ይቺን ፡
ሹመት ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥቼ ፡ ተሹሜ
ያታለሁ ፡ የሮም ፡ ሰው ፡ ብትሆን ፡ ምን ፡
ላድርግህ ፡ ያለጊዜዬ ፡ እሽርልሃለሁን ፡
አለው ፡ የተግሣፅ ፡ አነጋገር ። አንድም ፡
የሮም ፡ ሰው ፡ መሆንህን ፡ አልነግረኝ ፡
ብለህ ፡ ልታሽረኝ ፡ ኑረህ ፡ ሳትነግረኝ ፡
ቀርተህ ፡ አሽረዋለሁ ፡ ብለህ ፡ አለው ፡

ወይቤሎ ፡ ጳውሎስ ፡ አንሰኬ ፡ በህየ ፡ ተወለድኩ ፡

ጳውሎስም ፡ እኔስ ፡ በዚያች ፡ አገር ፡ ተወ
ልጃለሁ ፡ አለው ።

፳፱ ፤ ወእምዝ ፡ ኀደግዎ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ይቅሥ
ፍዎ ፡

ከዚህ፡በኋላ፡የሚገርፉት ፡ ሰዎች ፡ ተዉት፤

ወመልአክኒ ፡ ፈርሀ ፡ አእሚሮ ፡ ከመ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡
ውእቱ ፡

ሹሙም ፡ የሮም ፡ ሰው ፡ መሆኑን ፡ አው
ቆ ፡ ስላሠረው ፡ ፈራ ።

፴ ፤ ወበሳኒታ ፡ ፈቀደ ፡ መልአክ ፡ ያእምር ፡ ጥዩቀ፡
በእንተ ፡ ምንት ፡ ያስተዋድይዎ ፡ አይሁድ ።

በነጋውም ፡ ሹሙ ፡ አይሁድ ፡ ስለምን ፡
እንደ ፡ ከሰሱት ፡ ሊያውቅ ፡ ወዶ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወፈትሐ ፡ ማእሠሮ ፡

ከእሥራቱ ፡ ፈታው ።

ወአዘዘ ፡ ይምጽኡ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወኵሉ ፡ ዐውድ

ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ሕዝቡ ፡ መጥተው ፡ ይጋጠሙ ፡ ዘንድ ፡ ይጋጠሙ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

ወአምጽኦ ፡ ለጳውሎስ ፡ ወአቀሞ ፡ ማእከሎሙ ፡

ጳውሎስንም ፡ አስመጥቶ ፡ ከእነሱ ፡ ጋራ ፡ ገጠመው ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፫ ፡

፩፤ ወነጸሮ ፡ ጳውሎስ ፡ ዐውደ ።

ጳውሎስም ፡ ሕዝቡን ፡ ተሰብስበው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡

ይቤሎሙ ፡ አንስኬ ፡ አ፡ አኀውየ፡ በኵሉ፡ ትምህርት፡ ሠናይ፡ ተፀመድክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስከ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡

እኔስ ፡ ወንድሞቼ ፡ በፍጹም፡ ትምህርት ፡ ሁኜ ፡ እስከዚች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገለገልሁት ፡ ም ፡ ፳፬ ፡ ፲፯ ።

፪፤ ወአዘዘ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሐናንያ ፡ ይጽፍዕዎ ፡ አፉሁ ፡ ለጳውሎስ ።

ይህን ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ሐናንያ ፡ አፉን ፡ በሉት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፫፤ ወይቤሎ ፡ ጳውሎስ ፡ ሀሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጸፍዐከ ፡ በመቅሠፍት፡ መዓቱ፡ አ፡ ነኪር ፡ ዘትመስል ፡ አረፍት ፡ ግብስስት ፡

የተለሰነ፡ የተለቀለቀ ፡ ግድግዳ፡ የምትመስል ፡ ጉድ ፡ ያለህ ፡ ውዴላ ፡ እግዚአብሔር ፡ መዓቱ ፡ በሚፈጸምበት ፡ መቅሠፍት ፡ ይጸፋህ ፡ ዘንድ ፡ አለው ፡ አለው ፡

አንተስ ፡ ነበርከ ፡ ትኰንነኒ ፡ በሕጉ ፡

ከዳኛ ፡ ፊት ፡ ሳልቆም ፡ ልታስመታኝ ፡ ይገባህ ፡ ነበር ፡

ወዘእንበለ ፡ ሕጉ ፡ ትኤዝዝ ፡ ይዝብጡኒ ፡

ከዳኛ ፡ ፊት ፡ ቁሜ ፡ ግን ፡ ለምን ፡ ታስመታኛለህ ፡ አለ ፡ ሥራት ፡ ለማስተማር ። አንድም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሳለህ ፡ ልታስመታኝ ፡ ይገባህ ፡ ነበር። ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሳትሆን ፡ ለምን ፡ ታስመታኛለህ ፡ አለ ፡ ጌታ ፡ ገብቶበት ፡ እንደ ፡ ተሻረ ፡ ለማጠየቅ ። አንድም ፡ በአሪት ፡ ሳለሁ ፡ ልታስመታኝ ፡ ይገባህ ፡ ነበር ፡ አሪትን ፡ ከተውሁ ፡ በኋላ ፡ ለምን ፡ ታስመታኛለህ ። አንድም ፡ ከቤተ ፡ ገማልያል ፡ ስማር ፡ ሳለሁ ፡ ልታስመታኝ ፡ ይገባህ፡ ነበር ፡ የባልንጀራ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ደቀ፡ መዝሙር፡ ነውና ፡ ያን ፡ ከተውሁት ፡ በኋላ ፡ ለምን፡ ታስመታኛለህ ፡ አለው ።

፬፤ ወይቤልዎ ፡ ለጳውሎስ ፡ እለ ፡ ይቀውሙ ፡ በቅድሜሁ ፡ ትጼእል ፡ ሊቀ ፡ ካህናቲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

ከዚያ ፡ የተቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱን ፡ ለምን ፡ ትሳደባለህ ፡ አሉት ።

፭፤ ወይቤሎሙ ፡ ጳውሎስ ፡ ኢያእመርኩ ፡ አኀውየ ፡ ለእመ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ውእቱ ፡

ጳውሎስም ፡ እኔስ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ መሆኑን ፡ አላወቅሁም ፡

ወይብል ፡ መጽሐፍ ፡ ኢታሕሥም ፡ ዲበ ፡ መኰንነ፡ ሕዝብከ ፡

መሆኑንማ ፡ ባውቅ ፡ አሪት ፡ ኢትበሎ ፡ እኪተ ፡ ለመኰንነ ፡ ሕዝብከ ፡ ትላለች ፡ ለምን ፡ እሰድበው ፡ ነበር ፡ አላቸው ፡ ዘፀአ ፡ ፳፪ ፡ ፳፰ ። ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲ ።

፮፤ ወርእዮ ፡ ጳውሎስ ፡ ከመ ፡ አሐዱ ፡ ገጽ ፡ ሰዱቃውያን ፡

አንዱ ፡ ወገን ፡ ሰዱቃውያን ፡



ወመንፈቆሙ ፡ ፈሪሳውያን ፡

አንዱ ፡ ወገን ፡ ፈሪሳውያን ። አንድም ፡ እኩሌቶቹ ፡ ሰዱቃውያን ፡ እኩሌቶቹ ፡ ፈሪሳውያን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡

ከልሐ ፡ በውስተ ፡ ዐውድ ፡

ባደባባይ ፡ አሰምቶ ፡ ተናገረ ፡

ወይቤ ፡ አንሰ ፡ ፈሪሳዊ ፡ ወልደ ፡ ፈሪሳዊ ፡ አነ ፡

እኔ ፡ የፈሪሳዊ ፡ ልጅ ፡ ፈሪሳዊ ፡ ነኝ ።

በእንተ ፡ ተስፋ ፡ ሕይወተ ፡ ሙታን ፡ እትኴነን ።

ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ አለ ፡ ብዬ ፡ ስላስተማርሁ ፡ ይሞት ፡ በቃ ፡ ይፈረድብኛል ፡ ም ፡ ፳፮ ፡ ፭ ።

፯፤ ወሶበ ፡ ከመዝ ፡ ይብል ፡ ተበአሱ ፡ ፈሪሳውያን፡ ወሰዱቃውያን ፡

እንዲህም ፡ ብሎ ፡ ባስተማረ ፡ ጊዜ ፡ ፈሪሳውያንና ፡ ሰዱቃውያን ፡ ተጣሉ ፡

ወተናፈቁ ፡ ሕዝብ ።

ሕዝቡም ፡ ተለያዩ ።

፰፤ እስመ ፡ ሰዱቃውያን ፡ ይብሉ ፡ ኢየሐይዉ ፡ ሙታን ።

ሰዱቃውያን ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ የለም ፡ ባዮች ፡ ናቸውና ፡

ወአልቦ ፡ መልአክ ፡

መልአክ ፡ የለም ፡

ወኢመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የለም፡ ባዮች፡ ናቸውና ፡

ወፈሪሳውያንሰ ፡ የአምኑ ፡ ከመ ፡ ቦ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡

ፈሪሳውያን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ እንዳለ ፡ ያምናሉና ፡ ተጣሉ ፡ ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፳፫ ።

፱፤ ወኮነ ፡ ዐቢይ ፡ ዐውያት ፡

ታላቅ ፡ [illegible] ፡ ሆነ ።

ወተንሥኡ ፡ ጸሐፍት ፡ ወፈሪሳውያን ፡ ወአኀዙ ፡ ይትበአሱ ፡ ወይትላኰዩ ፡

ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ተነሥተው ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ ጀመሩ ።

ወይቤሉ ፡ አልቦ ፡ ዘረከብነ፡ እኩይ፡ ላዕለ፡ ዝ፡ ብእሲ፡

በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ያገኘነው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የለም ፡

እንዳዒ ፡ ለእመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተናገሮ ።

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አናግሮት ፡ እንደ ፡ ሆነ፤

አው ፡ መልአክ ፡

ወይም ፡ መላክ ፡ አናግሮት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አናውቅም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አንጣላ ፡ አሉ ፡ ም ፡ ፳፭ ፡ ፳፭ ። ም ፡ ፭ ፡ ፴፱ ።

፲፤ ክፍል ፡ ፵፭ ። ወሶበ ፡ ተሀውኩ ፡ ፈድፋደ ።

እጅግ ፡ በታወኩ ፡ ጊዜ ፡

ፈርሀ ፡ መልአክ ፡ ኢይምስጥዎ ፡ ለጳውሎስ ፡

ጳውሎስን ፡ ነጥቀው ፡ እንዳይወስዱት ፡ ፈርቶ ።

ወአዘዘ ፡ ሠገራተ ፡ ይምጽኡ ፡ ወይንሥእዎ ፡ እማዕከሎሙ ፡ ወይሰድዎ ፡ ኀበ ፡ ምኵናን ።

መጥተው ፡ ከመካከላቸው ፡ ነጥቀው ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ ቤት ፡ ይወስዱት ፡ ዘንድ ፡ ውሰዱት ፡ ብሎ ፡ ጭፍሮቹን ፡ አዘዘ ።

፲፩፤ ወበካልእት ፡ ሌሊት ፡ አስተርአዮ ፡ እግዚእነ፡ ለጳውሎስ ፡ ወይቤሎ ፡ ተአመን ።

በሁለተኛው ፡ ሌሊት ፡ ጌታችን ፡ በራእይ ፡ ታይቶ ፡ አይዞህ ፡ ጽና ፡

በከመ ፡ ኮንከኒ ፡ ሰማዕትየ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከማሁ ፡ ሀለወከ ፡ ትኩነኒ ፡ ሰማዕትየ ፡ በሮሜ ።

በኢየሩሳሌም ፡ እንደመሰከርህልኝ ፡ እንደዚህም ፡ በሮም ፡ ትመሰክርልኛለህ ፡ አለው ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፱ ። ም ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪ ፤ ወጸቢሐ ፡ ተጋብኡ ፡ አይሁድ ፡ ወተማሐሉ ፡ ወተሰካተዩ ፡

በነጋም ፡ ጊዜ ፡ አይሁድ ፡ ተሰብስበው ፡ ተማማሉ ፡ ሤራ ፡ ቆረጡ ፡

ወነገሩ ፡ ኅብስተ ፡ ወማየ ፡ ወይቤሉ ፡ ኢንበልዕ ፡ ወኢንስተይ ፡ እስከ ፡ ንቀትሎ ፡ ለጳውሎስ ።

ጳውሎስን ፡ እስክንገለው ፡ ድረስ ፡ እህል ፡ ውኃ ፡ አንቀምስም ፡ ኢንብላዕ ፡ ወኢን ስተይ ፡ እህል ፡ ውኃ ፡ አንቅመስ ፡ ብለው፡ ከእህል ፡ ከውኃ ፡ ተከለከሉ ።

፲፫ ፤ ወእለሰ ፡ ከመዝ ፡ ተማሐሉ ፡ ይበዝኁ ፡ እም አርብዓ ፡ ብእሲ ።

እንዲህ ፡ ብለው ፡ የተማማሉትም፡ ሰዎች፡ ካርባ ፡ ይበዛሉ ።

፲፬ ፤ እሙንቱሰ ፡ ሐሩ ፡ ኀበ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወረበናት ፡

እነሱም ፡ ከሊቃነ ፡ ካህናትና ፡ ከረበ ናት ፡ ዘንድ ፡ ሂደው ፡

ወይቤልዎሙ ፡ ናሁኬ ፡ ተማሐልነ ፡ ወተሰካተይነ ፡ ከመ ፡ ኢንብላዕ ፡ ወኢንስተይ ፡ እስከ ፡ ንቀትሎ ፡ ለጳውሎስ ።

ጳውሎስን ፡ እስክንገለው ፡ ድረስ ፡ እህል፡ ውኃ ፡ እንዳንቀምስ ፡ እነሆ ፡ ተማምለ ናል ፡ ሤራ ፡ ቆርጠናል ።

፲፭ ፤ ወይእዜኒ ፡ ሑሩ ፡ ኀበ ፡ መልአክ ፡

አሁንም ፡ ከሹሙ ፡ ዘንድ ፡ ሂዳችሁ ፡

ወበልዎ ፡ ከመ ፡ ያምጽኦ ፡ ለጳውሎስ ፡ ኀቤክሙ ፡ ከመ ፡ ዘተሐትትዎ ፡ ወትጠይቅዎ ።

የምትመረምሩት ፡ የምትጠይቁት ፡ አስመ ስላችሁ ፡ እንደምትመረምሩት ፡ እንደ ፡ ምትጠይቁት ፡ አድርጋችሁ ፡ ጳውሎስን ፡ ወዳንት ፡ አስመጣልን ፡ በሉት ፡

ወንሕነሰ ፡ ጥቡዓን ፡ ንሕነ ፡ ንቅትሎ ፡ ዘእንበለ ፡ ይብጻሕ ፡ ኀቤክሙ ፡

እኛ፡ግን፡ ከናንት፡ ሳይደርስ፡ በመንገድ፡ ሸ ምቀን ፡ ልንገለው ፡ ቆርጠናል፡ አሏቸው ።

፲፮ ፤ ወሰሚዖ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ፡ ወልደ ፡ እኅቱ ፡ ለጳ ውሎስ ፡ ምክሮሙ ፡

የጳውሎስ ፡ የእኅቱ ፡ ልጅ ፡ ምክራቸውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሐተታ ፡ የእኅት ፡ ልጅ ፡ ባይወልዱትም ፡ ልጅ ፡ እንዲሉ ፡

ሖረ ፡ ወቦአ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ወነገሮ ፡ ለጳውሎስ ፡

ሂዶ ፡ ከሥር ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ሊገሉህ ፡ መክረውብሃል፡ብሎ፡ለጳውሎስ፡ ነገረው ።

፲፯ ፤ ወጸውዖ ፡ ጳውሎስ ፡ ለሐቢ ፡

ጳውሎስም ፡ የሥር ፡ ቤት ፡ ጠባቂውን ፡ ጠርቶ ፡

ወይቤሎ ፡ አብጽሖ ፡ ሊተ ፡ ኀበ ፡ መልአክ ፡ ለዝ ፡ ወልድ ፡

ይህን ፡ ብላቴና ፡ ወስደህ ፡ ከሹሙ ፡ አገ ናኝልኝ ፡ አለው ፡

እስመ ፡ ቦ ፡ ነገር ፡ ዘይነግሮ ፡

የሚነግረው ፡ ነገር ፡ አለና ፡ ብሎ ።

፲፰ ፤ ወነሥኦ ፡ ሐቢ ፡ ለወልድ ፡ ወወሰዶ ፡ ኀበ ፡ መልአክ ፡

የሥር ፡ ቤት ፡ ጠባቂውም ፡ ወስዶ ፡ ከሹ ሙ ፡ አገናኘው ፡

ወይቤሎ ፡ ጳውሎስ ፡ ሙቁሕ ፡ አስተብቍዐኒ ፡ አብ ጽሖ ፡ ኀቤከ ፡ ለዝ ፡ ወልድ ።

ይህን ፡ ብላቴና ፡ ካንት ፡ አደርሰው ፡ ዘ ንድ ፡ እሥሩ ፡ ጳውሎስ ፡ ማልዶኛል ፡

እስመ ፡ ቦ ፡ ዘይነግረከ ።

የሚነግርህ ፡ ነገር ፡ አለና ፡ አለና ፡ ብሎ ፡ አለው ።

፲፱ ፤ ወአኀዞ ፡ መልአክ ፡ ለወልድ ፡ በእዴሁ ፡ ወአ ግሐሦ ፡ በባሕቲቱ ፡

ሹሙም ፡ ብላቴናውን ፡ በጁ ፡ ይዞ ፡ የብ ቻው ፡ ፈቅ ፡ አድርጎ ፡

ወይቤሎ ፡ ምንትኑ ፡ ነገሩ ፡ ዘታየድዐኒ ፡

የምትነግረኝ፡ነገሩ፡ ምንድን፡ነው፡ አለው።



፳ ፤ ወይቤሎ ፡ ከመዝ ፡ ተማከሩ ፡ አይሁድ ፡ ያስተ ብቍዑከ ፡ ታምጽኦ ፡ ጌሠመ ፡ ለጳውሎስ ፡ ውስተ ፡ ዐውድ ፡ ከመ ፡ ትሕትቶ ፡ ወትጠይቆ ።

የምትጠይቀው ፡ የምትመረምረው ፡ አስ መስለህ ፡ ነገ ፡ ጳውሎስን ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ አደባባይ ፡ እንድታስመጣላቸው ፡ ይማ ልዱህ ፡ ዘንድ ፡ አይሁድ ፡ መክረዋል ።

፳፩ ፤ አንተኬ ፡ አሆ ፡ ኢትበሎሙ ፡

አንተ ፡ ግን ፡ በጅ ፡ አትበላቸው ፡

እስመ ፡ ይጸንሑ ፡ ይቅትልዎ ።

ይገሉት ፡ ዘንድ ፡ ሸምቀዋልና ፡

ወይበዝኁ ፡ እምአርብዓ ፡ ዕደው ፡ እለ ፡ ከመዝ ፡ ተማ ሐሉ ፡ ኢይብልዑ ፡ ወኢይስተዩ ፡ እስከ ፡ ይቀትልዎ ፡

ጳውሎስን ፡ እስኪገሉት ፡ ድረስ ፡ እህል ፡ ውኃ ፡ እንዳይቀምሱ ፡ የተማማሉት ፡ ሰዎች ፡ ካርባ ፡ ይበዛሉ ፤

ወይእዜኒ ፡ ጥቡዓን ፡ እሙንቱ ፡ ዳዕሙ ፡ እስከ ፡ ትል እከ ፡ ሎሙ ፡ ይጸንሕዎ ።

አሁንም ፡ እስክትልክላቸው ፡ ድረስ ፡ ይጠብቃሉ ፡ እንጅ ፡ ሊገሉት ፡ ቆርጠ ዋል ፡ አለው ።

፳፪ ፤ ወእምዝ ፡ ፈነዎ ፡ መልአክ ፡ ለውእቱ ፡ ወል ድ ፡ ወይቤሎ ፡ ከመ ፡ ኢይንግር ፡ ወኢለመኑሂ ፡ እ ምዘነገሮ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሹሙ ፡ ብላቴናውን ፡ ከዚ ህ ፡ ከነገረው ፡ ነገር ፡ ለማንም፡ ለማን ፡ እንዳይነግር ፡ አትንገር ፡ ብሎ ፡ መክሮ ፡ አሰናበተው ።

፳፫ ፤ ወጸውዐ ፡ ክልኤተ ፡ እምወዓልያኒሁ ፡

ከብላቴኖቹ ፡ ሁለቱን ፡ ጠርቶ ፡

ወይቤሎሙ ፡ ንሥኡ ፡ ክልኤ ፡ ምእተ ፡ ብእሴ ፡ እም ውስተ ፡ ሐራ ፡

ከጭፍሮቹ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡

ወሰብዓ ፡ ሰብአ ፡ አፍራስ ፡ ወሰማንያ ፡ ሰብአ፡ ቀስት፡

ሰባ ፡ ፈረሰኛ ፡ ሰማንያ ፡ ቀስተኛ ፡ ከሁ ሉቱ ፡ መቶ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። አንድም ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ይዛችሁ ፡

ወይሖሩ ፡ ቂሣርያ፡ ጊዜ ፡ ሠለስቱ ፡ ሰዓተ ፡ ሌሊት ።

ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ሂዱ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፡ ሐተታ ፡ እስከ ፡ ሦስ ት ፡ ሰዓት ፡ ሰው ፡ አይተኛም ፡ እየበላ ፡ እየጠጣ ፡ ሲጫወት ፡ ያመሻል ፡ ሰው ፡ እንዳያያቸው ፡ ይሑሩ ፡ ቂሣርያ ፡ ጊዜ ፡ ሠለስቱ ፡ ሰዓት ፡ አለ ።

፳፬ ፤ ወአዘዞሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ከመ ፡ ይንሥኡ ፡ አድገኒ ፡ ወያጽዕንዎ ፡ ለጳውሎስ ፡

ጳውሎስንም ፡ በቅሎ ፡ ወስደው፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ አስቀምጠው ፡

ወያብጽሕዎ ፡ ኀበ ፡ ፊልክስ ፡ መልአከ ፡ ቂሣርያ ፡

ከቂሣርያው ፡ ሹም ፡ ከፊልክስ ፡ ዘንድ ፡ እንዲያደርሱት ፡ አዘዛቸው ፡

ወገብሩ ፡

እንዳዘዛቸው ፡ አደረጉ ።

፳፭ ፤ ወጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡ መጽሐፈ ፡ እንተ ፡ ትብል ፡

እንዲህ ፡ የምትል ፡ ክታብ ፡ ጻፈ ።

፳፮ ፤ እምቀላውዴዎስ ፡ሉስዮስ ፡

እምሉስዮስ ፡ ገብረ ፡ ቀላውዴዎስ ፡ የቀ ላውዴዎስ ፡ ተገዢ ፡ ከምሆን ፡ ከኔ ፡ ከሉ ስዮስ ፡ የመጣች ፡ ክታብ ፡

ለጽኑዕ ፡ መኰንን ፡ ፊልክስ ፡

ለክቡር ፡ ፊልክስ ፡ ትድረስ ፡

ሰላም ፡ ለከ ፡

ቸር ፡ አለህን ።

፳፯ ፤ ለዝአ ፡ ብእሲአ ፡ አኀዝዎአ ፡ አይሁድአ ፡ ወፈቀዱአ ፡ ይቅትልዎአ ።

ይህን ፡ ሰው ፡ አይሁድ፡ ሊገሉት ፡ ወደው፡ ይዘውት ፡ ነበር ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወቆምኩአ ፡ ሎቱአ ፡ ምስለአ ፡ ወዓልየአ ፡ ወአድኀንክዎአ ፡ አእሚርየአ ፡ ከመ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜአ ፡ ውእቱአ ፡

እኔ ፡ ከብላቴናዬ ፡ ጋራ ፡ ደርሼ ፡ የሮም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቄ ፡ ከጃቸው ፡ አዳንሁት ፡ እሱ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ እንጅ ፡ ጳውሎስስ ፡ እግዚአብሔር ፡ አድኀነኒ ፡ ይላል ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፴፫ ። ም ፡ ፳፪ ፡ ፳፰ ።

፳፰ ፤ ወሐተትክዎ ፡ አእምር ፡ ጌጋዮ ፡ አቅራብየ ፡ ውስተ ፡ ዐውድ ፡ ሐተትኩ ፡

በደሉን ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡ ባደባባይ ፡ አስመጥቼ ፡ መረመርሁት ፡

በእንተ ፡ ምንት ፡ ያስተዋድይዎ ፡

አይሁድ ፡ ስለምን ፡ እንደ ፡ ከሰሱት ፡ መረመርሁ ፡

ወኢረከብኩ ፡ ሎቱ ፡ ጌጋየ ፡

ዕዳ፡ በደል፡ አላገኘሁበትም፡ ም፡ ፳፱፡ ፴ ።

፳፱ ፤ ወአእሚርየ ፡ ከመ ፡ በከ ፡ ያስተዋድይዎ ፡ በእንተ ፡ ሕገጊሆሙ ፡

አይሁድ ፡ በደል ፡ ሳይኖርበት ፡ ኦሪት ፡ ትበልጣለች ፡ ወንጌል ፡ ትበልጣለች ፡ በማለት ፡ እንደ ፡ ከሰሱት ፡ እንዳጣሉት ፡ ባወቅሁ ፡ ጊዜ ፡

ወአልቦ ፡ ባዕድ ፡ ጌጋይ ፡ በዘይመውት ፡ ወበዘይት ሞቃሕ ፡

በሚሞት ፡ ገንዘብ ፡ ስንኳን ፡ መሞት ፡ በሚታሠር ፡ ገንዘብ ፡ የሚታሠርበት ፡ ዕዳ ፡ በደል ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ ባወቅሁ ፡ ጊዜ ፡ ም ፡ ፲፰ ፡ ፲፬ ።

፴ ፤ ወሶበ ፡ ሐለይኩ ፡ ዘገብሩ ፡ አይሁድ ፡ ዲበ ፡ ዝ ፡ ብእሲ ፡ በጸኒሕ ።

አይሁድ ፡ ሸምቀው ፡ ሊገሉት ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የመከሩበትን ፡ ምክር ፡ ባወቅሁ ፡ ጊዜ ፡

ፈነውክዎ ፡ ኀቤከ ፡

ወደ ፡ አንት ፡ ሰደድሁት ፡

ወአዘዝክዎሙ ፡ ለመስተዋድያንሂ ፡ ይምጽኡ ፡ ኀቤከ ፡ ወይትኋነንዎ ፡ በቅድሜከ ፡

ከሳሾቹንም ፡ ወደ ፡ አንት ፡ መጥተው ፡ ባንት ፡ ዳኝነት ፡ ይባባሉ ፡ ዘንድ ፡ አዘዝኋቸው ፡

ዳኅነ ፡ ሀሉ ፡

ደኅና ፡ ነህን ። ዳኅነ ፡ ሀሎ ፡ እስካሁን ፡ ደኅና ፡ ነው ። ደኅና ፡ ሁንም ፡ ይላል ፡ የምትል ፡ ክታብ ፡ ጻፈ ፡ ም ፡ ፳፬ ፡ ፳፫ ።

፴፩ ፤ ወገብሩ ፡ ሐራ ፡ በከመ ፡ አዘዞሙ ፡

ጭፍሮቹም ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አደረጉ ፡

ወነሥእዎ ፡ ለጳውሎስ ፡ በሌሊት ፡ ወወሰድዎ ፡ ውስተ ፡ አህጉረ ፡ አድያም ።

ሌሊት ፡ ጳውሎስን ፡ በበቅሎ ፡ ላይ ፡ አስቀምጠው ፡ በከተማው ፡ ዳር ፡ ለዳር ፡ ይዘውት ፡ ሄዱ ።

፴፪ ፤ ወአውሀሉ ፡ አፍራሲሆሙ ፡

ፈረሶቻቸውንም፡ከቤት፡ አሥረው፡አዋሉ፡ ሐተታ፡ ወዴት፡ ሂደዋል ፡ በተባለ፡ ጊዜ ፡ እነገሌማ ፡ እንጅ ፡ ከቤት ፡ ዋዮች ፡ ሁነዋል ፡ እንዲባሉ ። አንድም ፡ ሲሄዱ ፡ አድረው ፡ ቀን ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ከፈረፈር ፡ አሥረው ፡ አዋሉ ፡ ሰው፡ እንዳያያቸው ።

፴፫ ፤ ወእምዝ ፡ በሳኒታ ፡ ቦኡ ፡ ቂሣርያ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በነጋው ፡ ቂሣርያ ፡ ገቡ ፡

ወበጽሑ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡ ወመጠውዎ ፡ መጽሐፈ ፡ መልእክት ፡ ለመኰንን ፡

ከሹሙ ፡ ዘንድ ፡ ገብተው ፡ ደብዳቤውን ፡ ሰጡት ፡

ወአቅረብዎ ፡ ለጳውሎስ ፡ ኀቤሁ ፡

ጳውሎስንም ፡ አገናኙት ፡



፴፬ ፤ ወአንበቦ ፡

ደብዳቤውን ፡ ተመልክቶ ፡

ሐተቶ ፡ ዘምኑናኒ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡

ከማን ፡ ግዛት ፡ ነህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡

ወአእሚሮ ፡ ከመ ፡ ዘሀገረ ፡ ቂልቅያ ፡ ውእቱ ፡

የቂልቅያ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ፫ ።

፴፭ ፤ ይቤ ፡ እንከሰ ፡ በጺሖሙ ፡ መስተዋድያን ፡ ንሰምዐከሙ ፡

እንኪያስ ፡ ከሳሾች ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እንሰማችኋለን ፡ ብሎ ፡

ወአዘዘ ፡ ይዕቀብዎ ፡ ኀበ ፡ ምኵናነ ፡ ሄሮድስ ፡

ከሄሮድስ ፡ ግዞት ፡ ቤት ፡ ይጠብቁት ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፬ ፡ ክፍል ፡ ፴፮ ።

፩ ፤ ወእመ ፡ ኀሙስ ፡ ዕለት ፡ ወረደ ፡ ሐናንያ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ምስለ ፡ ረበናት ።

እንከሰ ፡ በጺሖሙ ፡ መስተዋድያን ፡ ንሰምዐክሙ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ቂሣርያ ፡ በገቡ ፡ ባምስተኛው ፡ ቀን ፡ የካህናቱ ፡ አለቃ ፡ ሐናንያ ፡ ከረበናት ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ሄደ ፡

ወአሐዱ ፡ ዐቃቤ ፡ ነቢብ ፡ ዘስሙ ፡ ጠርጠሉስ ።

ጠርጠሉስ ፡ የሚባል ፡ ጭብጥ ፡ ያዥ ፡ ውርድ ፡ ነዥ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡

ወአስተዋደይዎ ፡ ለጳውሎስ ፡ ኀበ ፡ መልአክ ።

ጳውሎስን ፡ ከሹሙ ፡ ዘንድ ፡ አሳጡት ፡ አጣሉት ።

፪ ፤ ወአቅረበ ፡ ሎሙ ፡

አስመጥቶ ፡ ገጠማቸው ።

ወአኀዘ ፡ ይንግር ፡ ጠርጠሉስ ፡

ጠባሽ ፡ ከሳሽ ፡ የመረጠውን ፡ ያሽ ፡ እንዲሉ ፡ ጠርጠሉስ ፡ ነገር ፡ ጀመረ ።

፫ ፤ ወይቤ፡ ብዙኀ፡ ሰላመ፡ አድማዕነ፡በመዋዕሊከ ፡

በዘመንህ ፡ ሁሉ ፡ ፍጹም ፡ ዕረፍት ፡ አግኝተናል ፡

ወሠናየ ፡ ኮነ ፡ ንብረቶሙ ፡ ለሕዝብ ፡ በጥበብከ ፡ በኵሉ ፡ ወበኵለሄ ።

ባንት ፡ ፍርድ ፡ መጠንቀቅ ፡ ነገር ፡ ማወቅ ፡ ድኃ ፡ መጠበቅ ፡ የሕዝቡ ፡ አኗኗራቸው ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ሆነ ፡

ወረከብነ ፡ ሥርዐተከ ፡ እንዘ ፡ ትትአኰት ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ አ ፡ ፊልክስ ፡ ክቡር ፡

ክቡር ፡ ፊልክስ ፡ ዳኝነትህ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ስትመሰገን ፡ አግኝተናታል ።

፬ ፤ ወባሕቱ ፡ ከመ ፡ ኢያጽሕብከ ፡ ፈድፋደ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ እንዳልዘበዝብህ ፡

አዕምዐኒ ፡ ብቍዐኒ ፡ ኅጹረ ፡ ነገረ ፡ እንግርከ ፡

ጥቂት ፡ ነገር ፡ እነግርህ ፡ ዘንድ ፡ በጅ ፡ በለኝ ፡ ስማኝ ።

፭ ፤ ረከብናሁ ፡ ለዝ ፡ ብእሲ ፡ ይነብብ ፡ ዕርፈተ ፡

ይህነን ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲሰድብ ፡ ሙሴን ፡ ሲያዋርድ ፡

ወይገብር ፡ ማዕሌተ ፡

በቄሣር ፡ ዐመፅን ፡ ሲያደርግ ፡

ወየሀውክ ፡ ኵሎ ፡ አይሁደ ፡ በኵሉ ፡ በሐውርት ፡

ባሉት ፡ መዓዝን ፡ ያሉ ፡ አይሁድን ፡ ሲያሸብር ፡

ወይሜህር ፡ ካሕደ ፡ ዘሕዝበ ፡ ናዝራውያን ፡

የናዝራውያንን ፡ ክህደት ፡ ሲያስተምር ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ፮ ።

www.ethiopianorthodox.org

፮ ፤ ወአርኰሰ ፡ ቤተ ፡ መቅደሰ ፡ ወአኀዝናሁ ፡
ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ሲያሳድፍ ፡ አግኝተን ፡ ይዘነዋል ።

ወፈቀድነ ፡ ኰንኖቶ ፡ በከመ ፡ ሕግነ ፡
እንደ ፡ ሕጋችን ፡ ልንገለው ፡ ወደን ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፳፰ ።

፯ ፤ ወመጽአ ፡ ሉስዮስ ፡ መልአክ ፡ ወአድኀኖ ፡ እምእደዊነ ፡ በብዙኀ ፡ ግብር ፡
ነገር ፡ ግን ፡ ሹሙ ፡ ሉስዮስ ፡ መጥቶ ፡ በብዙ ፡ ጻዕር ፡ ከእጃችን ፡ አዳነው ፡ እሱ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ እንጅ ፡ ጳውሎስስ ፡ እግዚአብሔር ፡ አድኀነኒ ፡ ይላል ፡

ወፈነዎ ፡ ኀቤከ ፡
ወዳንት ፡ ሰዶታል ።

፰ ፤ ወአዘዞሙ፡ ለመስተዋድያን፡ ይምጽኡ፡ ኀቤከ፡
ከሳሾቹንም ፡ ካንት ፡ ዘንድ ፡ መጥተው ፡ ባንት ፡ ዳኝነት ፡ ይባባሉ ፡ ዘንድ ፡ አዟቸዋል ፡

ወዘኒ ፡ አስተዋደይናሁ ፡ ኵሉ ፡ ሀለወከ ፡ ታእምር ፡ እምኀቤሁ ፡ ሐቲተከ ፡ ከመ ፡ አማን ፡ ውእቱ ፡
የከሰስንበትንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ዕውነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መርምረህ ፡ ከቃሉ ፡ ታገኘዋለህ ፡ አለ ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ፴ ።

፱ ፤ ወተሠጥዉ ፡ አይሁድ ፡ ወይቤሉ ፡ አማን ፡ ከመዝ ፡ ውእቱ ፡
አይሁድም ፡ ዕውነት ፡ ነው ፡ ቃሉ ፡ ቃላችን ፡ ነው ፡ አሉ ።

፲ ፤ ወቀጸቦ ፡ መልአክ ፡ ለጳውሎስ ፡ ከመ ፡ ይትናገር ፡
ሹሙም ፡ ጳውሎስን ፡ ጠቅሶ ፡ ተናገር ፡ አለው ፡

ወይቤሎ ፡ ጳውሎስ ፡ አነ ፡ አአምር ፡ ከመ ፡ እምብዙኀ ፡ ዓመታት ፡ መኰንኖሙ ፡ አንተ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ።
ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ለሊህ ፡ ሰዎች ፡ ዳኛቸው ፡ ገዣቸው ፡ እንደሆንህ ፡ አውቃለሁ ።

ወተአምር ፡ ግዕዞሙ ፡
ግብራቸውንም ፡ ታውቃለህ ፡

፲፩ ፤ ወይእዜኒ ፡ እነግረከ ፡ ተፈሢሕየ ፡ ቅሥትየ ፡ ዘሀለወከ ፡ ታእምር ፡
አሁንም ፡ ውኃ ፡ ሲጸር ፡ ተሻገር ፡ ዳኛ ፡ ሳለ ፡ ተናገር ፡ እንዲሉ ፡ ታውቀው ፡ ዘንድ ፡ ያለህን ፡ ነገሬን ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ እነግርሃለሁ ፡

ወኢየዐከል ፡ ዐሡረ ፡ ወሰኑየ ፡ ዕለተ ፡ እምዘዐረጉ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እስግድ ።
ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እጅ ፡ ልነሣ ፡ ከወጣሁ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ አይሆነኝም ፡ ም ፡ ፳፩ ፡ ፯ ።

፲፪ ፤ ወኢረከቡኒ ፡ እንዘ ፡ እትዋቀሥ ፡ ኢበምኵራብ ፡
በምኵራቡም ፡ ሆኖ ፡

ወኢምስለ ፡ መኑሂ ፡
በአፍአም ፡ ሆኖ ፡

ወኢእንዘ ፡ አሀውክ ፡ ሕዝበ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡
በቤተ ፡ መቅደስም ፡ ሆኖ ።

ወኢበሀገር ፡
በከተማም ፡ ሆኖ ፡ ሕዝቡን ፡ ሳስቸግር ፡ አላገኙኝም ።

፲፫ ፤ ወኢይክሉ ፡ አብጽሖተ ፡ በኵሉ ፡ ዘያስተዋድዩኒ ፡ በቅድሜከ ።
ባንት ፡ ዳኝነት ፡ እኔን ፡ በከሰሱበት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መርታት ፡ አይቻላቸውም ።

፲፬ ፤ ወባሕቱ ፡ ዘይብሉኒ፡ ይሜህር፡ ካሕደ፡ (ጋእዘ)፡
ነገር ፡ ግን ፡ ክህደትን ፡ ያስተምራል ፡ የሚሉኝ ፡
አንሰ ፡ አመልኮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡ እትአመን ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ኦሪት ፡ ወነቢያት ፡
በኦሪት ፡ በነቢያት ፡ በተጻፈው ፡ ግብር ፡ ጸንቼ ፡ እግዚአብሔርን፡ አመልከዋለሁና፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ቍ ፡ ፩ ።

፲፭ ፤ ወእሴፌዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ይትአመኑ ፡ ከመ ፡ ሀለዎሙ ፡ ይትነሥኡ ፡ ምውታን ፡ ጻድቃን ፡ ወኃጥአን ።
ምውታን፡ ያላቸውን፡ ጻድቃን፡ ወኃጥአን ፡ አለ፡ ስለ፡ ጻድቃን፡ ስለ፡ ኃጥአን፡ ይነሡ፡ ዘንድ፡እንዳላቸው፡እነሱም፡ እንዲያምኑ፡እግዚአብሔርን፡ተስፋ፡ አደርገዋለሁና፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ዳን ፡ ፲፪ ፡ ፪ ። ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፳፰ ።

፲፮ ፤ ከማሁ ፡ አነሂ ፡ እትአመኖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በጥቡዕ ፡ ልብ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበቅድመ ፡ ሰብእ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡
እነሱ፡እንዲያምኑ፡እኔም፡በቁርጥ፡ልቡናዬ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሰውም ፡ እግዚአብሔርም ፡ በሚያውቀው ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምነዋለሁና ፡ ስለዚህ ፡ ነው፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ፩ ።

፲፯ ፤ ወእምድኅረ ፡ ብዙኅ ፡ መዋዕል፡ ወዓመታት ፡ መጻእኩ ፡ ለኀበ ፡ ሕዝብየ ፡ ከመ ፡ እግበር ፡ ምጽዋተ ፡
ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ አስተዋፅኦውን ፡ እሠጥ ፡ ዘንድ ።

ወከመ ፡ አዕርግ ፡ መዋሥዕተ ፡
መሥዋዕትም ፡ አሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ወገኖቼ ፡ መጥቼ ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፳፱ ። ገላት ፡ ፪ ፡ ፲ ።

፲፰ ፤ ወረከቡኒ ፡ እሙንቱ ፡ በምኵራብ ፡ እንዘ ፡ አነጽሕ ፡ ርእስየ ፡
በምኵራቡ ፡ በዓለ ፡ አንጽሖ ፡ አድርጌ ፡ አገኙኝ ፡ እንጅ ።

ወኢረከቡኒ ፡ እንዘ ፡ እትገአዝ ፡ ወእትላኰይ ፡
ስጣላ ፡ ስከራከር ፡ አላገኙኝም ፡

ወአልቦ ፡ ዘሆኩ ፡ ሕዝበ ፡
ሕዝቡንም ፡ ያስቸገርሁት ፡ ማስቸገር፡ የለም፡ ሕዝቡን፡አላስቸገርሁም፡ም፡፳፩፡፳፯ ።

፲፱ ፤ ወሀ[illegible] አይሁድ ፡ እለ ፡ መጽኡ ፡ እምእስያ ፡
ከእስያ ፡ የመጡ ፡ አይሁድም ፡ ነበሩ ፡

ወይእዜኒ ፡ ግበር ፡ ኀቤከ ፡ ይምጽኡ ፡ ከመ ፡ ያስተዋድዩኒ ፡
አሁንም ፡ መጥተው ፡ እንዲመሰክሩብኝ ፡ አድርግ ።

፳ ፤ ወእመ ፡ አኮ ፡ ነዮሙ ፡ እሉሂ ፡ ይንግሩ ፡ ጽድቀ ።
እሊያም ፡ ባይመሰክሩ ፡ እሊህ ፡ ከሳሾቹ ፡ ዕውነቱን ፡ ይናገሩ ፡

እመ ፡ ቦ ፡ ዘሰምዑ ፡ ዘአበስኩ ፡ አነ ፡
የበደልሁትን ፡ በደል ፡ ሰምተው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሰሙት ፡ መስማት ፡ እንዳለ ፡

ወእመኒ ፡ ቦ ፡ ዘርእዩ ፡ ዘገፋዕኩ ፡
የቀማሁትን ፡ መቀማት ፡ አይተው ፡ እንደ ሆነ ፡ ያዩት ፡ ማየት ፡ እንዳለ ፡

በዘአምጽኡኒ ፡ ኀበ ፡ ምኵናን ፡ ዘኀቤከ ፡
አንተ ፡ ከምትፈርድበት ፡ አደባባይ ፡ ባመጡኝ ፡ ገንዘብ ፡

በዘአልቦ ፡ እኩይ ፡
የሠራሁት ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሌለ ።

፳፩ ፤ ወኢአሐቲኒ ፡ ትምህርት ፡ ዘመሀርኩ ፡
ያስተማርሁትም ፡ ትምህርት ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ ይመስክሩብኝ ፡

ዳዕሙ ፡ በብሂለ ፡ የሐይዉ ፡ ምውታን ፡ ዘረከበኒ ፡ ተኰንኖ ፡ በኀቤከ ፡ ዮም ፡
ዛሬ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ያገኘኝ ፡ ወቀሳ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ከሡሳ ፡ ሙታን ፡ ይነሣሉ ፡ ብዬ ፡ ስላስተ
ማርሁ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ፮ ።

፳፪ ፤ ወፊልክስሰ ፡ የአምር ፡ ከመ ፡ እምትካት ፡ ይትቃረኑ ፡ አይሁድ ፡ ምስለ ፡ ሕግ ፡ ወትምህርት ፡ ዘሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡

ፊልክስ ፡ ግን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ አይሁድ ፡ ከክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ አሪት ፡ ትበልጣለች ፡ ወንጌል ፡ ትበልጣለች ፡ በማለት ፡ እንዲከራከሩ ፡ ያውቅ ፡ ነበር ፡

ወከመ ፡ አይሁድ ፡ መፃርርቲሃ ፡ ለሃይማኖት ፡

አይሁድ ፡ ለሃይማኖት ፡ ደመኛዋ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ያውቅ ፡ ነበር ፡

ወእምድኅረ፡ዝ ፡ የውሆሙ ፡ ወይቤሎሙ፡ እንከሰኬ ፡ ወሪዶ ፡ ሉስዮስ ፡ መኰንን ፡ ነሐትት ፡ ከመ ፡ ናእምር ፡ ወንጠይቅ ፡ ነገረክሙ

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነገራችሁን ፡ እናውቅ ፡ እንረዳ ፡ ዘንድ ፡ ሉስዮስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እንመረምራለን ፡ ብሎ ፡ አለዘባቸው ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ፳፮ ።

፳፫ ፤ ወአዘዞ ፡ ለሐቤ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ከመ ፡ ኢያጽንዖ ፡ ለጳውሎስ ።

የሥር ፡ ቤት ፡ ጠባቂውንም ፡ በጳውሎስ ፡ እሥራት ፡ እንዳያጸናበት ፡ አታጽናበት ፡

ወያንብሮ ፡ ውስተ ፡ መርህብ ፡

ቦታ ፡ እንዳይወሰንበት ፡ አትወስንበት ፡

ወኢያጽብብ ፡ ላዕሌሁ ፡

ሰንሰለት ፡ እንዳያጠብቅበት ፡ አታጥብቅበት ፡

ወኢይክልአ ፡ ለአሐዱሂ ፡ እምእለ ፡ የአምርዎ፡ ሶበ፡ ይመጽኡ ፡ ይትለአክዎ፡

ከሚያውቁት ፡ ሰዎች ፡ ሊጠይቁት ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰውስ ፡ እንኳ ፡ ጠያቂ ፡ እንዳይከለክልበት ፡ አትከልክልብት ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ፡ ም ፡ ፳፯ ፡ ፫ ።

፳፬ ፤ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ነበረ ፡ ፊልክስ ፡ ምስለ ፡ ዱርሳሌም ፡ ብእሲቱ ፡ አይሁዳዊት ፡

ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ፊልክስ ፡ ከሚሽቱ ፡ ከዱርሳሌም ፡ ጋራ ፡ በቆይታ ፡ ተገኘ ፡

ወለአከ ፡ ወጸውዖ ፡ ለጳውሎስ ፡

ሰው ፡ ልኮ ፡ ጳውሎስን ፡ አስጠራው ፡

ወሰምዕዎ ፡ ቃላተ ፡ ወትምህርታተ ፡ በእንተ ፡ አሚን፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለማመን ፡ የሚያስተምረውን ፡ ትምህርት ፡ እሱም ፡ ምሽቱም ፡ ሰሙት ።

፳፭ ፤ ወሶበ ፡ ነገሮሙ ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ፡

የወንጌልን ፡ ነገር ፡ በነገራቸው ፡ ጊዜ ፡

ወሕይወት ፡

የትንሣኤ ፡ ሙታንን ፡ ነገር ፡

ወበእንተ ፡ ኵነኔ ፡ ዘለዓለም ፡

ተነሥቶ ፡ የሚፈረደውን ፡ ፍርድ ።

ወደይን ፡

በኃጥኡ ፡ ፈርዶ ፡ የሚያመጣውን ፡ ፍዳ ፡

ወፍትሕ ፡

ለጻድቁ ፡ ፈርዶ ፡ የሚሰጠውን ፡ ዋጋ ፡

ወርትዕ ፡

ርትዕ ፡ የወል ፡ ነው ፡

ዘይከውን ፡ በዕለተ ፡ ኵነኔ ፡

በቁርጥ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ የሚሆነውን ፡ በነገራቸው ፡ ጊዜ ፡

ፈርሀ ፡ ፊልክስ ፡ እምዝንቱ ፡

ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ፊልክስ ፡ ፈራ ፡ ከሞቱም ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አለን፡ብሎ ፡



ወይቤሎ ፡ ለጳውሎስ ፡ ይእዜሰኬ ፡ ሑር ፡ ወሶበ ፡ ብሕትትኩ ፡ እልእከ ፡ ዘይጼውዐከ ።

ዛሬስ ፡ ሂድ ፡ ለብቻዬ ፡ በሆንሁ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ልኬ ፡ አስጠራሃለሁ ፡ አለው ።

፳፮ ፤ ወመሰሎ ፡ ለፊልክስ ፡ ከመ ፡ ይሁቦ ፡ ጳውሎስ ፡ ወይኄልዮ ፡ ንዋየ ፡ ይኅድጎ ፡ ወተሰፈወ ፡

ፊልክስም ፡ ይፈታው ፡ ዘንድ ፡ ማማለጃ ፡ የሚሰጠኝ ፡ መስሎት ፡ ነበርና ፡

ወበእንተ ፡ ዝ ፡ ወትረ ፡ ይጼውዖ ፡ ወይትናገሮ ።

ስለዚህ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እየጠራ ፡ ይጠይቀው ፡ ነበር ።

፳፯ ፤ ክፍል ፡ ፵፮። ወሶበ ፡ ኀለፈ ፡ ክልኤቱ ፡ ዓመት ፡ ለዝንቱ ፡ነገር ፡ ተስዕረ ፡ ፊልክስ ፡ ወመጽአ ፡ መካነ ፡ ሢመቱ ፡ ካልእ ፡ መኰንን ፡ ዘስሙ ፡ ፊስጦስ ፡

ይህ ፡ ነገር ፡ በሆነ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ፊልክስ ፡ ተሽሮ ፡ ፊስጦስ ፡ የሚባል ፡ ሌላ ፡ ሹም፡ በሱ፡ ሥፍራ ፡ ተሹሞ ፡ መጣ፤

ወፈቀደ ፡ ፊልክስ ፡ ያድሉ ፡ ለአይሁድ ፡ ገሃደ ፡ ወበእንተ ፡ ዝ ፡

ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ፊልክስ ፡ አይሁድን ፡ ገልጦ ፡ ደስ ፡ ሊያሰኝ ፡ ወዶ ፡

ኀደጎ ፡ ለጳውሎስ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ።

ጳውሎስን ፡ ከእሥር ፡ ቤት ፡ ትቶት ፡ ሄደ ፡ ም ፡ ፳፭ ፡ ፲፬ ። ም ፡ ፳፭ ፡ ፱ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፭ ።

፩ ፤ ወበጺሖ ፡ ፊስጦስ ፡ ቂሣርያ ፡ ጐንደየ ፡ ሠሉሰ፡ መዋዕለ ፡

ፊስጦስም ፡ ቂሣርያ ፡ ገብቶ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሰነበተ ፡

ወእምዝ ፡ ዐርገ ፡ ኢየሩሳሌም ፡

ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም፡ ወጣ ።

፪ ፤ ወያድዎ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወዐበይተ ፡ አይሁድ ፡

በኢየሩሳሌም ፡ ያሉ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ የአይሁድም ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ሹመት፡ ያዳብር ፡ አሉት ፡

ወነገርዎ ፡ በእንተ ፡ ጳውሎስ ፡

የጳውሎስንም፡ ነገር፡ ነገሩት፡ ም፡ ፳፬፡ ፩ ።

፫ ፤ ወሰአልዎ ፡ ከመ ፡ ይጸግዎሙ ፡ ከመ ፡ ይልአክ፡ ያምጽእዎ ፡ ለዐውድ ፡ ዘኢየሩሳሌም ።

ከቂሣርያ ፡ ልኮ ፡ አስመጥቶ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ባለ ፡ አደባባይ ፡ ይገጥማቸው ፡ ዘንድ ፡ ለመኑት ፡

ወእሙንቱሰ ፡ ፈቀዱ ፡ ከመ ፡ ይሑሩ ፡ ህየ ፡ ወበፍኖት ፡ ይቅትልዎ ።

እነሱ ፡ ግን ፡ በመንገድ ፡ ሸምቀው ፡ ቆይተው ፡ ሊገሉት ፡ ወደው ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ፲፭ ።

፬ ፤ ወአውሥአሙ ፡ ከመ ፡ የዐቅብዎ ፡ ለጳውሎስ ፡ በቂሣርያ ፡ ወከመ ፡ የሐውር ፡ ለሊሁ ፡ ፍጡነ ፡ ህየ ።

እነሱም ፡ ጳውሎስን ፡ በቂሣርያ ፡ እንዲጠብቁት ፡ እሱም ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ እንዲሄድ ፡ ነገራቸው ።

፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ለአይሁድ ፡ እለ ፡ ትክሉ ፡ እምውስቴትክሙ ፡ ትትዋቀሡ ፡ ምስለ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘአስተዋደይክምዎ ።

አይሁድን ፡ ከናንተ ፡ ወገን ፡ ጉልበት ፡ ያላችሁ ። አንድም ፡ ነገር ፡ የምታውቁ ፡ ወርዳችሁ ፡ ከከሰሳችሁት ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ተባባሉ ፡ አላቸው ።

፮ ፤ ወነቢሮ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ሰሙነ ፡ መዋዕለ ፡ አው ፡ ዐሡረ ፡ ወረደ ፡ ቂሣርያ ፡

ከነሱም ፡ ዘንድ ፡ ስምንት፡ ቀን፡ ወይም ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዐሥር ፡ ቀን ፡ ከሰነበተ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ሄደ ፡ ሐተታ ፡ ምነው ፡ አጠራጥሮ ፡ ተናገረ ፡ ቢሉ ፡ አንዱ ፡ የሄደበት ፡ አንዱ ፡ የተመለሰበት ፡

ወበሳኒታ ፡ ነበረ ፡ ዐውደ ፡

በነጋው ፡ በነገር ፡ ተገኘ ፡

ወአዘዘ ፡ ያምጽእዎ ፡ ለጳውሎስ ።

ጳውሎስን ፡ አምጡት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፡ ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፲፫ ።

፯ ፤ ወቀሪቦ ፡ ጳውሎስ ፡ አስተዋደይዎ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ ወረዱ ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ ብዙኀ ፡ ጌጋየ ፡ ወከቡደ ፡ በዘኢይክሉ ፡ አብጽሖተ ።

ጳውሎስም ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የሄዱ ፡ አይሁድ ፡ መርታት ፡ በማይቻላቸው ፡ ጽኑ ፡ ነውር ፡ ከሰሱት ፡

፰ ፤ ወእንዘ ፡ ይወቅሥ ፡ ሎሙ ፡ ጳውሎስ ።

ጳውሎስም ፡ ሲከራከር ።

ወይብል ፡ አልቦ ፡ ዘአበስኩ ፡ ላዕለሂ ፡ ኦሪቶሙ ፡ ለአይሁድ ።

ኦሪታቸውን ፡ አላፈረስሁም ፡

ወኢዲበ ፡ ምኵራቦሙ ፡

ምኵራባቸውንም ፡ አላሳደፍሁም ፡

ወኢለንጉሢ ፡

በቄሣርም ፡ ላይ ፡ ዐመፅን ፡ አላደረግሁም፡ እያለ ፡ ሲመልስ ፡ ም ፡ ፳፬ ፡ ፲፪ ።

፱ ፤ ፈቀደ ፡ ፊስጦስ ፡ ያእኵትዎ ፡ አይሁድ ፡

ፊስጦስ ፡ ግን ፡ አይሁድ ፡ ሊያመሰግኑት ፡ ወዶ ፡

ወይቤሎ ፡ ለጳውሎስ ፡ ትፈቅድኑ ፡ ትዕርግ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወበህየ ፡ ትትዋቀሥ ፡

ጳውሎስን ፡ ከዚያ ፡ ትባባል ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ልትወጣ ፡ ትወዳለህን ፡

አው ፡ በኀቤየ ፡

ወይስ ፡ ከዚህ ፡ ከኔ ፡ ዘንድ ፡ ልትባባል ፡ ትወዳለህ ፡ አለው ፡ ም ፡ ፳፬ ፡ ፳፮ ።

፲ ፤ ወአውሥአ ፡ ጳውሎስ ፡ ወይቤሎ ፡ አንሰ ፡ እቀውም ፡ ቅድመ ፡ መንበረ ፡ ቄሣር ፡

ጳውሎስም ፡ እኔስ ፡ ከቄሣር ፡ እደርሳለሁ ፡ ከቄሣር ፡ ይግባኝ ፡

ወበህየ ፡ ይደሉ ፡ ሊተ ፡ ፍትሕ ፡

ከዚያ ፡ ሊፈረድብኝ ፡ ይገባኛል ፡ አለው ፡

ወለሊከ ፡ ተአምር ፡ እምነ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ አልብየ ፡ ዘአበስኩ ፡ ላዕለ ፡ አይሁድ ።

አይሁድን ፡ የበደልሁት ፡ በደል ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ አንት ፡ ቅሉ ፡ ታውቃለህ ፡

፲፩ ፤ ወእመሰ ፡ ቦ ፡ ዘዐመፅኩ ፡

የበደልሁት ፡ በደል ፡ እንዳለ ፡

ወቦ ፡ እኩይ ፡ ዘገበርኩ ፡ በዘእመውት ፡ ኢይትሀከይ፡ መዊተ ፡

በምሞት ፡ ገንዘብ ፡ የሠራሁት ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እንዳለ ፡ ሞት ፡ አይገባኝም ፡ አልልም ፡

ወእመሰ ፡ በከ ፡ ያስተዋድዩኒ ፡ እሉ ፡ ዘአልብየ ፡ ጌጋይ ፡

በደል ፡ ሳይኖርብኝ ፡ እንዲያው ፡ በከንቱ፡ ቢከሱኝ ፡ ቢያጣሉኝ ፡ ግን ፡

ለመኑ ፡ ብእሲ ፡ ይደልዎ ፡ የሀበኒ ፡ ሎሙ ፡ አነ ፡በቄሣር ፡ ንጉሥ ፡ እጠርእ ፡

ከቄሣር ፡ ይግባኝ ፡ ከቄሣር ፡ እደርሳለሁ ፡ ስል ፡ ለሳቸው ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠኝ ፡ ለማን ፡ ይቻለዋል ፡ አለው ።

፲፪ ፤ ወእምዝ ፡ ተናጊሮ ፡ ፊስጦስ ፡ ምስለ ፡ መማክርቲሁ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፊስጦስ ፡ ከባለሟሎቹ ፡ ጋራ ፡ መክሮ ፡

ይቤ ፡ ጠርአ ፡ በቄሣር ፡ ንጉሢ ፡

ከቄሣር ፡ ይግባኝ ፡ ከቄሣር ፡ እደርሳለሁ ፡ ብሏልና ፡

ወኀበ ፡ ቄሣር ፡ የሐውር ፡

ወደ ፡ ቄሣር ፡ ይሄዳል ፡ ይሂድ ፡ አለ ።

፲፫ ፤ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ወረደ ፡ አግሪጳ ፡ ንጉሥ ፡ ወበርንቄ ፡ ወተአምኅዎ ፡ ለፊስጦስ ።

ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ አግሪጳና ፡ በርንቄ ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ሂደው ፡ ፊስጦስን ፡ ሹመት ፡ ያዳብር ፡ አሉት ።

፲፬ ፤ ወነቢሮሙ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ ኀቤሁ ፡

ከሱ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከሰነበቱ ፡ በኋላ ፡

ነገሮሙ ፡ በእንተ ፡ ጳውሎስ ።

የጳውሎስን ፡ ነገር ፡ ነገራቸው ፡

ወይቤሎሙ ፡ ሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ሙቁሕ ፡ ዘኀደጎ ፡ ፊልክስ ፡

ፊልክስ ፡ ከእሥር ፡ ቤት ፡ የተወው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አለ ።

፲፭ ፤ ወእንዘ ፡ ሀሎኩ ፡ ኢየሩሳሌም ፡

ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጥቼ ፡ ሳለሁ ፡

መጽኡ ፡ ኀቤየ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወረበናተ ፡ አይሁድ ።

የካህናት ፡ አለቆች ፡ ረበናተ ፡ አይሁድ ፡ ወደኔ ፡ መጥተው ፡

ወአስተብቍዑኒ ፡ ከመ ፡ እኰንኖ ፡ ሎሙ ፡

ግደልልን ፡ ብለው ፡ ማለዱኝ ።

፲፮ ፤ ወእቤሎሙ ፡ ኢይከውን ፡

አይገባም ፡

ወሕግ ፡ አልቦ ፡ በዘይኴንንዎ ፡ ዘኢዘለፍዎ ፡ ማኅተት ፡ ወዘኢረከቡ ፡ ሎቱ ፡ ጌጋየ ፡

ዕዳ ፡ በደል ፡ ያልተገኘበትን ፡ ምስክር ፡ ያልመሰከረበትን ፡ ሰው ፡ መግደል ፡ ሥርዐት ፡ አይደለም ፡

ሕጉመ ፡ ኢይኴንኑ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ በከመ ፡ ረከቡ ፡

የሮም ፡ ሰዎች ፡ በማይገባ ፡ እንዳገኙ ፡ ሰው ፡ አይገሉም ። አንድም ፡ ሕሩም ፡ አይገባም ። የሮም ፡ ሰዎች ፡ እንዳገኙ ፡ ሰው ፡ አይገሉም ፡ አልኋቸው ፡ ዘዳግ ፡ ፲፯ ፡ ፬ ።

፲፯ ፤ ወእምዝ ፡ መጺእየ ፡ ዝየ ፡ ተጋብኡ ፡ ካዕበ ፡

ከዚህ ፡ በመጣሁም ፡ ጊዜ ፡ ዳግመኛ ፡ ተሰበሰቡ ፡

ወበነግህ ፡ ነበርኩ ፡ ሎሙ ፡ ዐውደ ፡

በነጋው ፡ በነገር ፡ ተገኘሁላቸው ፡

ወአዘዝኩ ፡ ያምጽእዎ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡

ያንን ፡ ሰው ፡ አምጡት ፡ ብዬ ፡ አዘዝኹ ።

፲፰ ፤ ወአቀምኩ ፡ ምስሌሁ ፡ እለ ፡ ያስተዋድይዎ ፡

አስመጥቼ ፡ ከከሳሾቹ ፡ ጋራ ፡ ገጠምኋቸው ።

ወአልቦ ፡ ምንትሂ ፡ እኩይ ፡ ዘገብረ ፡ በዘአብጽሕዎ ፡ ሎቱ ፡ በከመ ፡ ሐለይኩ ፡

እንዳሰብሁ ፡ እንደ ፡ መረመርሁ ፡ ወደኔ ፡ ባመጡት ፡ ገንዘብ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሠራው ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ የለም ።

፲፱ ፤ ዘእንበለ ፡ በእንተ ፡ ሕገጊሆሙ ፡ ዘይትካሐዱ፡

የሚከራከሩት ፡ ኦሪት ፡ ትበልጣለች ፡ ወንጌል ፡ ትበልጣለች ፡ በማለት ፡ ነው ፡ እንጅ ።

ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ ኢየሱስ ፡

ኢየሱስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡

ዘሞተ ፡

አይሁድ ፡ ሞተ ፡ የሚሉት ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወጳውሎስ ፡ ይብል ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡

ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ተነሥቷል፡ ይላል ፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፳፫ ፡፡

፱ ፤ ወኀጢእየ ፡ እንከ ፡ ዘእገብር ፡ ሎሙ ፡ ፍትሐ ፡ በእንተ ፡ ማኅሠሣሙ ፡

እኔም ፡ ስለሚከራከሩት ፡ ክርክር ፡ የምፈ ርደው ፡ ቢቸግረኝ ፡

እቤሎ ፡ ለጳውሎስ ፡ ትፈቅድኑ ፡ ትሑር ፡ ኢየሩ ሳሌም ፡ ወበህየ ፡ ትትዋቀሥ ፡

ጳውሎስን ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሂደህ ፡ ከዚያ ፡ ልትባባል ፡ ትወዳለህን ፡ አልሁት ፡

ወአበየ ፡ ውእቱሰ ፡

እሱ ፡ ግን ፡ አይሆንም ፡ አለ ፡

ወተዘመረ ፡ መድኀኒቶ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡

ከሞት ፡ ፍርድ ፡ ለመዳን ፡ በቄሣር ፡ ተማ ጠነ ፡ አለ ፡ ከቄሣር ፡ እደርሳለሁ ፡ ከቄ ሣር ፡ ይግባኝ ፡ አለ ።

፲ ፤ ወእምዝ ፡ አዘዝኩ ፡ ይዕቀብዎ ፡ እስከ ፡ እፌ ንዎ ፡ ኀበ ፡ ቄሣር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ቄሣር ፡ እስክሰደው ፡ ድረስ ፡ ጠብቁት ፡ ብዬ ፡ አዘዝኹ ።

፳፪ ፤ ወይቤሎ ፡ አግሪጳ ፡ ለፊስጦስ ፡ አነሂ ፡ እፈ ቱ ፡ እስምዖ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡

አግሪጳም ፡ የዚያን ፡ ሰው ፡ ነገር ፡ እኔም ፡ ከቃሉ ፡ ልሰማ ፡ እወዳለሁ ፡ አለው ፡

ወይቤሎ ፡ ፊስጦስ ፡ እንከሰኬ ፡ ጌሠመ ፡ ትሰምዖ ፡

ፊስጦስም ፡ እንኪያስ ፡ ነገ ፡ ትሰማዋለህ ፡ አለው ።

፳፫ ፤ ወበሳኒታ ፡ መጽኡ ፡ አግሪጳ ፡ ወበርንቄ ፡ ተረሲዮሙ ፡ ምስለ ፡ ብዙኅ ፡ ግርማ ፡

በነጋው ፡ አግሪጳና፡በርንቄ ፡ ልብሰ፡ መን ግሥት ፡ ለብሰው ፡ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ አስ ከትለው ፡ መጥተው ፡

ወቦኡ ፡ ወነበሩ ፡ ዐውደ ፡ ምስለ ፡ መሳፍንት ፡ ወዐበይተ ፡ ሀገር ፡

ከመሳፍንቱ ፡ ከወይዛዝሩ ፡ ጋራ ፡ ባደ ባባይ ፡ ተቀመጡ ፡ አለ ፡ በነገር ፡ ተገኙ ፡

ወአዘዘ ፡ ፊስጦስ ፡ ያምጽእዎ ፡ ለጳውሎስ ፡

ፊስጦስም ፡ ጳውሎስን ፡ አምጡት ፡ ብሎ፡ አዘዘ ።

፳፬ ፤ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ጳውሎስ ፡ ይቤ ፡ ፊስጦስ ፡ ስምዑ ፡ ኵልክሙ ፡ እለ ፡ ሀለውክሙ ፡ ምስሌነ ፡

ጳውሎስም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ፊስጦስ ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ያላችሁ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ሁላችሁም ፡ ስሙ ፡

ወነዋኬ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘአስተዋደይዎ ፡ አይሁድ በኢየሩሳሌም ፡

በኢየሩሳሌም ፡ ሳለሁ ፡ አይሁድ ፡ የከሰ ሱት ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ነው ፡

ወበዝየኒ ፡ የዐወይዉ ፡

ከዚህም ፡ ተከትለው ፡ መጥተው ፡ ይጮ ኻሉ ፡

ወይስእሉ ፡ ከመ ፡ ግሙራ ፡ ኢያሕይውዎ ፡

ግደልልን ፡ ብለው ፡ ይካሰሳሉ ፡ አለ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ፳፪ ።

፳፭ ፤ አንሰኬ ፡ ሐቲትየ ፡ ጥዩቀ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ጌጋይ ፡

እኔ ፡ ግን ፡ በደል ፡ እንደሌለበት ፡

ወአልቦ ፡ እኩይ ፡ ዘገብረ ፡ በዘይመውት ፡

በሚሞትበት ፡ ገንዘብ ፡ የሠራው ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እንደሌለ ፡ መርምሬ ፡

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ፈተወ ፡ በጺሐ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡

ኳቄሣር ፡ እደርሳለሁ ፡ ብሏልና ፡

ፈቀድኩ ፡ እንከ ፡ እፈንዎ ፡

ከእንግዲህ፡ወደቄሣር፡ልሰደው፡ወደድሁ።



፳፮ ፤ ወባሕቱሰ ፡ ኀጣእኩ ፡ ዘእብል ፡ አበሳሁ ፡ እንዘ ፡ እጽሕፍ ፡ ለእግዚእየ ፡ ንጉሥ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ጌታዬ፡ ስጽፍ ፡ ዕዳው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ የምጽፈው ፡ በደል ፡ ቸገረኝ ።

ወይእዜኒ ፡ ፈቀድኩ ፡ ከመ ፡ አምጽኦ ፡ ኀቤክሙ ፡

አሁንም፡ ወደናንተ፡ ላመጣው፡ ወደድሁ ፡

ወፈድፋደሰ ፡ እመ፡ቦ፡ ዘተአምር ፡ አንተ ፡ አግሪጳ ፡ ንጉሥ ፡ ሶበ ፡ ትሴአሎ ፡ ወትሰምዕ ፡ ነገሮ ፡ ወተአ ምር ፡ ምንተ ፡ ዘእጽሕፍ፡ ወዘእብል ፡ በእንቲአሁ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ።

ይልቁንም ፡ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ በጠየቅ ኸው ፡ ነገሩን ፡ በሰማኸው ፡ ጊዜ ፡ ስለሱ ፡ ወደ ፡ ጌታዬ ፡ የምጽፈው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አንተ ፡ የምታገኘው ፡ በደል፡ ዕንዳለ ፡ ብዬ ።

፳፯ ፤ እስመ ፡ ኢይደሉ ፡ ንፈንዎ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ሙቁሐ ፡ ዘእልብነ ፡ ጽሕፈተ ፡ አበሳሁ ።

ዕዳው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ሳንል ፡ አሥረን፡ወደ፡ ንጉሥ ፡ ልንሰደው ፡ አይገባምና ፡

ወይእዜኒ ፡ ናሁ ፡ አምጻእክዎ ፡ ኀቤክሙ ፡

አሁንም ፡ ወደናንት ፡ አስመጥቸዋለሁና ፡

ሕትቱ ፡ እስኩ ፡ ለእመ፡ቦ፡ ዘትረክቡ ፡ ጌጋየ ፡ ዘን ጽሕፍ ፡

የምንጽፈው ፡ በደል፡ ታገኙ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እስቲ ፡ መርምሩት ፡

እስመ ፡ ሊተሰ ፡ ዐፀበኒ ፡ ነገሩ ፡

ለኔስ ፡ እኮን ፡ ነገሩ ፡ ቸገረኝ ፡

ወፈንዎቶሂ ፡ ሙቁሐ ፡

ዕዳው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ሳልል ፡ አሥሮ ፡ መስደዱ ፡ ቸገረኝ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፮ ።

፩ ፤ ወይቤሎ ፡ አግሪጳ ፡ ለጳውሎስ ፡ አባሕናከ ፡ ንግር ፡ በእንተ ፡ ርእስከ ፡

አግሪጳም ፡ ጳውሎስን ፡ እስቲ ፡ የራስህን ፡ ነገር ፡ ተናገር ፡ አለው ፡

ወእምዝ ፡ አንሥአ ፡ እዴሁ ፡ ጳውሎስ ፡ ወአኀዘ ፡ ይንግሮሙ ፡

ጳውሎስም ፡ እጅ ፡ ለነገር ፡ ያግዛልና ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ይነግራቸው ፡ ጀመር ።

፪ ፤ ወይቤ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘይትኃሠሡኒ ፡ አይ ሁድ ፡ አአግሪጳ ፡ ንጉሥ ፡ ብፁዕ ፡ አነ ፡ ዮም ፡ ዘበቅድ ቤከ ፡ እትዋቀሥ ፡

አይሁድ ፡ እኔን ፡ ስለ ፡ ከሰሱበት ፡ ነውር፡ ሁሉ ፡ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ዛሬ ፡ ባንተ ፡ ፊት ፡ የምናገር ፡ እኔ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነኝ ፡ ባዋቂ ፡ ፊት ፡ መናገር ፡ መታገም ፡ እንዲሉ ።

፫ ፤ እስመ ፡ ተአምር ፡ ግዕዞሙ ፡

ግብራቸውን ፡ ታውቃለህና ፡

ወተኀሥሦቶሙ ፡ ለአይሁድ ፡

ጠብ ፡ ክርክራቸውንም ፡ ታውቃለህና ፡

ብቍዐኒ ፡

በጅ ፡ በለኝ ፡

ተዐጊሠከ ፡ አፅምዐኒ ፡

ጸጥ ፡ ብለህ ፡ ስማኝ ።

፬ ፤ ንብረትየ ፡ ዘበንእስየ ፡ በውስተ ፡ ሕዝብየ ፡ ልህቁ ፡ በኢየሩሳሌም ፡

ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሮ ፡ አነዋወሬ ፡ በወገ ኖቼ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ (ልህቁ) ፡ በኢየሩሳ ሌም ፡ አድጌያለሁ ።

ወየአምሩኒ ፡ ኵሎሙ ፡ አይሁድ ፡ እምትካት ፡

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ አይሁድ ፡ ሁሉ ፡ ያው ቁኛል ።

www.ethiopianorthodox.org

፭ ፤ ወየአምሩ ፡ ከመ ፡ በሕገ ፡ አበውየ ፡ እገብር ፡ እንዘ ፡ ፈሪሳዊ ፡ አነ ፡

ፈሪሳዊ ፡ ስሆን ፡ ባባቶቼ ፡ ሕግ ፡ በአሪት ፡ ጸንቼ ፡ ሥራ ፡ እሠራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያው ቃሉ ፡ ፈሪሳዊ ፡ ማለት ፡ ዕሉል ፡ ባሕታዊ፡ማለት፡ነው፡ም፡፳፫፡፮። ፊል፡ ፫ ፡ ፭ ።

፮ ፤ ወይእዜኒ ፡ በጺሐ ፡ ዘአሰፈዎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአበዊነ ፡

አሁንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአባቶቻችን ፡ ያናገረው ፡ ተስፋ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ም ፡ ፳፰ ፡ ፳ ።

፯ ፤ መሀርኩ ፡ ለዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ እንዘ ፡ እፀመድ ፡ መዐልተ ፡ ወሌሊተ ፡

በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ፅሙድ ፡ ሁኜ ፡ ላሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ እስራኤል ፡ አስተማርሁ ። አንድም ፡ ላሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ አስተማርሁ ፡

በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ተስፋ ፡ ዘይትኄሠሡኒ ፡ አይሁድ ፡

አይሁድ ፡ የሚከራከሩኝ ፡ የተስፋ ፡ ትንሣኤን ፡ ነገር ፡ አስተማርኋቸው ።

አ ፡ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ምንተ ፡ ትፈትሕ ፡

ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ምን ፡ ትፈርዳለህ ፡ ም ፡ ፳፬ ፡ ፲፭ ።

፰ ፤ አኮኑ ፡ ይደሉ ፡ ንእመን ፡ ከመ፡ እግዚአብሔር፡ ያሕይዎሙ ፡ ለምዉታን ፡

እግዚአብሔር ፡ ሙታን ፡ ሥጋን ፡ እንዲ አስነሣቸው ፡ በሚያስነሣቸው ፡ በእግዚአ ብሔር ፡ ልናምን ፡ አይገባምን ።

፱ ፤ ወአነኒ ፡ አጥባዕኩ ፡ እግበር ፡ እኩየ ፡ ዲበ ፡ ስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ናዝራዊ ፡ ብዙኀ ፡

እኔም፡የናዝሬት፡ሰው፡በሚሆን፡በጌታችን፡ በኢየሱስ ፡ ስም፡ባመኑ፡ ምእመናን፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ላጸናባቸው ፡ ወድጄ ፡ ነበር ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፩-፳፪ ። ም ፡ ፳፪ ፡ ፫-፳፩ ።

፲ ፤ ወገበርኩኒ ፡ በኢየሩሳሌም ፡

ወድጄም ፡ አልቀረሁ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ባሉ ፡ ምእመናን ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ አጸናሁ ባቸው ፡

ወሞቃሕክዎሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ጻድቃን ፡ አስተበዊሕየ ፡ በኀበ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ከመ ፡ እቅትሎሙ ፡

በብዙ ፡ ደጋግ ፡ ሰዎች ፡ መከራ ፡ አጸናባቸው ፡ ዘንድ ፡ ከሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ቃስድ ነት ፡ ሹመት ፡ ተካስሼ ፡ ሂጄ ፡ ዕዳ ፡ በደል ፡ የሌለባቸውን ፡ ሰዎች ፡ እየሠርሁ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እሰዳቸው ፡ ነበር ።

፲፩ ፤ ወአምጻእኩ ፡ መጽሐፈ ፡ መባሕት ፡ ለኵሉ ፡ መኳርብት ፡ ወዘልፈ ፡ አሐምሞሙ ፡ ከመ ፡ በግብር ፡ ይፅርፉ ፡

ለምኵራብ ፡ ሁሉ ፡ ሹመቴን ፡ የሚመሰክር ፡ ደብዳቤ ፡ አምጥቼ ፡ በግድ ፡ ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ፡ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ ይሉ ፡ ዘንድ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መከራ ፡ አጸናባቸው ፡ ነበር ።

ወፈድፋደሰ ፡ አበድኩ ፡ ላዕሌሆሙ ።

ይልቁንም ፡ በምእመናን ፡ ተነሳሣሁባቸው ።

እንዘ ፡ እዴግኖሙ ፡ ውስተ ፡ አህጉር ።

ከዋሉበት ፡ አላሳድር ፡ ካደሩበት ፡ አላ ውል ፡ እያልሁ ።

፲፪ ፤ ወእንዘ ፡ አሐውር ፡ ሀገረ ፡ ደማስቆ ፡ አስተበዊሕየ ፡ በኀበ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ሶበ ፡ ይከውን ፡ ጊዜ ፡ ቀትር ።

ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ቃስድነት ፡ ሹመት ፡ ከሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ዘንድ ፡ ተካስሼ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ስሄድ ፡

፲፫ ፤ ሶበ ፡ ይከውን ፡ ጊዜ ፡ ቀትር ፡ እንዘ ፡ ሀሎኩ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ አ ፡ ንጉሥ ፡

ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ሆይ ፡ በጐዳና ፡ ሳለሁ ፡ ቀትር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡



ርኢኩ ፡ እምሰማይ ፡ በረቀ ፡ መብረቅ ፡ ዘይበርህ ፡ እምፀሓይ ።

ከፀሓይ ፡ ይልቅ ፡ የሚያበራ ፡ ብርሃን ፡ ከወደ ፡ ሰማይ ፡ በላዬ ፡ ላይ ፡ ሲበራ ፡ አየሁ ።

ወኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ዘየሐውሩ ፡ ምስሌየ ፡ ወለልየ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወደቅነ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ኵልነ ።

ከኔ ፡ ጋራ ፡ የሚሄዱትም ፡ ሰዎች ፡ እኔም ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወደቅነ ።

፲፬ ፤ ወሰማዕኩ ፡ ቃለ ፡ ዘይብለኒ ፡ በነገረ ፡ ዕብራይስጥ ፡ ሳውል ፡ ሳውል ፡ ለምንት ፡ ትሰድደኒ ።

በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ሳውል ፡ ከዋልሁ በት ፡ አላሳድር ፡ካደርሁበት ፡ አላውል ፡ ለምን ፡ ትለኛለህ ።

ይብእሰከ ፡ ረጊፅ ፡ ውስተ ፡ ቀኖት ፡ በሊሕ ፡

ሰይፍ ፡ የረገጠ ፡ እሱ ፡ ይጐዳል ፡ እንጂ ፡ ሰይፉ ፡ ይጐዳልን ፡ ሲለኝ ፡ ሰማሁ ።

፲፭ ፤ ወእቤ ፡ አነ ፡ መኑ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ።

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ማነህ ፡ አልሁት ።

ወይቤለኒ ፡ እግዚእነ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘአንተ ፡ ትሰድደኒ ።

አንተ ፡ ከዋልሁበት ፡ አላሳድር ፡ ካደርሁ በት ፡ አላውል ፡ የምትለኝ ፡ እኔ ፡ ኢየሱስ፡ ነኝ ፡ አለኝ ።

፲፮ ፤ ወባሕቱ ፡ ተንሥእ ፡ ወቁም ፡ በእገሪከ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ ተነሥተህ ፡ በግርህ ፡ ቁም ።

እስመ ፡ በእንተ ፡ ዝ ፡ አስተርአይኩከ፡ እሢምከ ፡ ላእከ ፡

ሐዋርያነትን ፡ እሾምህ ፡ ዘንድ ።

ወሰማዕተ ፡ በዘርኢከኒ ።

ባየኸኝ ፡ በሰማኸኝ ፡ ገንዘብ ።

ወበዘሀለወከ ፡ ትርአየኒ ፡

እንግዴህም ፡ በምታየኝ ፡ ገንዘብ ፡ ትመሰክርልኝ ፡ ዘንድ ፡ ስለዚህ ፡ ታዩሁ ።

፲፯ ፤ ወአድኀንከ ፡ እምሕዝብ ፡ ወአሕዛብ ፡ እለ ፡ እፌንወከ ፡ አነ ፡ ኀቤሆሙ ፡

እኔ ፡ አንተን ፡ ከምሰድላቸው ፡ ከሕዝብ ፡ ከአሕዛብ ፡ እጅ ፡ አድንሃለሁ ።

፲፰ ፤ ከመ ፡ ትክሥት ፡ አዕይንቲሆሙ ፡

ዐይነ ፡ ልቡናቸውን ፡ ታበራላቸው ፡ ዘንድ ።

ወትሚጠሙ ፡ እምጽልመት ፡ ውስተ ፡ ብርሃን ።

ከድንቁርና ፡ ወደ ፡ ዕውቀት ፡ ትመልሳ ቸው ፡ ዘንድ ።

ወእምጣዖተ ፡ ሰይጣን ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትመልሳቸው ፡ ዘንድ ፡

ከመ ፡ ይትኀደግ ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ ፡

ኃጢአታቸው ፡ ይሠረይላቸው ፡ ዘንድ ።

ወይርከቡ ፡ መክፈልተ ፡ ምስለ ፡ ቅዱሳን ፡ በአሚን ፡ በስምየ ፡

በስሜ ፡ በማመን ፡ ከቅዱሳን ፡ ከሐዋር ያት ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ቅዱሳን ፡ እንደ ፡ ሐዋ ርያት ፡ ዕድል ፡ ፈንታን ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡ ኢሳ ፡ ፴፫ ፡ ፳ ። ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ። ም ፡ ፳፡ ፴፪ ። ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ።

፲፱ ፤ ወይእዜኒ ፡ አ፡ንጉሥ ፡ አግሪጳ፡ ኢክሕድኩ ፡ ዘአስተርአየኒ ፡ ሊተ ፡ እምሰማይ ፡

አሁንም ፡ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ከወደ፡ ሰማይ፡ ተገልጦ ፡ የነገረኝን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አሉ ፡ አላልሁም ፡ ገላ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ።

፳ ፤ ወቀደምኩ ፡ ወነገርክዎሙ ፡ ለእለ፡ በደማስቆ ፡

በደማስቆ ፡ ላሉ ።

ወለእለ ፡ በኢየሩሳሌም ፡

በኢየሩሳሌምም ፡ ላሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወለኵሉ ፡ በሐውርተ ፡ ይሁዳ ፡ ወለአሕዛብኒ ።

በይሁዳ ፡ አገሮች ፡ ላሉ ፡ ሁሉ፡ ለአሕዛብም ፡ አስቀድሜ ፡ አስተማርኋቸው ።

ወመሀርክዎሙ ፡ ይነስሑ ፡ ወይትመየጡ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡

በንስሓ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ።

ወይግበሩ ፡ ዘይደሉ ፡ ለንስሓሆሙ ፡

ለንስሓም ፡ የሚገባውን ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ አስተማርኋቸው ፡ ም ፡ ፱ ፡ ፳ ።

፳፩ ፤ በእንተዝኬ ፡ አኀዙኒ ፡ አይሁድ ፡ በምኵራብ፡ ወፈቀዱ ፡ ይቅትሉኒ ፡

ስለዚህ ፡ ሊገሉኝ ፡ ወደው ፡ አይሁድ ፡ በምኵራብ ፡ ይዘውኝ ፡ ነበር ።

፳፪ ፤ ወአድኀነኒ ፡ እግዚአብሔር ፡

እግዚአብሔር ፡ ከእጃቸው ፡ አዳነኝ ።

ወበጻሕኩ ፡ እስከ ፡ ዮም ፡ ወቆምኩ ፡ እንዘ ፡ እነግር ፡ ለንኡስ ፡ ወለዓቢይ ፡

ለታናሹም ፡ ለታላቁም ፡ እያስተማርሁ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አለሁ ።

ወአልቦ ፡ ባዕድ ፡ ዘመሀርኩ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ዘይብሉ ፡ ነቢያት ፡ ዘሀለዎ ፡ ይኩን ፡ ወሙሴሂ ፡ ዘይቤ ።

ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ ነቢያት ፡ ከተናገሩት ፡ ነገር ፡ በቀር ። ሙሴም ፡ ከተናገረው ፡ ነገር ፡ በቀር ፡ ሉቃ ፡ ፳፬ ፡ ፵፬ ።

፳፫ ፤ ከመ ፡ ይቅትል ፡ ክርስቶስ ፡

ክርስቶስ ፡ እንዲሞት ።

ወያቀድም ፡ ተንሥአ ፡ እምዉታን ፡

አስቀድሞ ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ እንዲነሣ ።

ወያበርህ ፡ ለሕዝብ ፡ ወለኵሉ ፡ አሕዛብ ፡ ወበሐውርት ፡

ለሕዝቡም፡ለአሕዛቡም፡ሁሉ፡ ትንሣኤን፡ ልጅነትን ፡ እንዲገልጥ ፡ ከተናገረው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ያስተማርሁት ፡ የለም ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፳ ።

፳፬ ፤ ክፍል ፡ ፵፰ ። ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ተሠጥወ ፡ መኰንን ፡ ፊስጦስ ፡ ወጸርሐ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ።

ጳውሎስ፡ይህን፡ በተናገረ፡ ጊዜ፡ አገረ፡ገዡ፡ፊስጦስ ፡ መለሰ፡ለሁሉም፡ በሚሰማ ፡ ቃል ፡ ተናገረ ።

ወይቤሎ ፡ ተአብድኑ ፡ ጳውሎስ ።

ጳውሎስ ፡ አእምሮህን ፡ አጥተሃልን ።

አብዝኆ ፡ መጻሕፍትኬ ፡ ያዘነግዐ ፡ ልበ ፡

ነገር ፡ ማብዛት ፡ እንጅ ፡ አእምሮ ፡ ያሳጣል ፡ አለው ።

፳፭ ፤ ወይቤሎ ፡ ጳውሎስ ፡ እበድስ ፡ አልብየ፡ኦ፡ ፊስጦስ ፡ መኰንን ።

ጳውሎስም ፡ መኰንን ፡ ፊስጦስ ፡ ሆይ ፡ አእምሮ ፡ ማጣትስ ፡ የለብኝም ።

ዳዕሙ ፡ እነግር ፡ ጽድቀ ፡ ወንጽሐ ፡

ሐሰት ፡ የሌለበት ፡ ሰውነት፡ ነገርን ፡ እናገራለሁ ፡ እንጅ ።

፳፮ ፤ ወየአምር ፡ ሊተ ፡ ለሊሁ ፡ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ዘበኀቤሁ ፡ ክሡተ ፡ እነግር ።

ነገሬን ፡ በፊቱ ፡ ገልጬ ፡ የምነግረው ፡ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ እሱ ፡ ቅሉ ፡ ያውቃል ።

ወይመስለኒሂ ፡ አልቦ ፡ ዘይስሕት ፡ እምዝንቱ ፡

ከዚህ ፡ ከተናገርሁት ፡ እሱ ፡ የማያውቀው ፡ የሌለ ፡ ይመስለኛል ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ።

እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ኅቡአ ፡

ነገሩ ፡ የተሠወረ፡ አይደለምና ፡ ዮሐ፡ ፲፰ ፡ ፡ ፳ ።



፳፯ ፤ ናሁ ፡ ትትአመን ፡ በቃለ ፡ ነቢያት፡ኦ፡ንጉሥ፡ አግሪጳ ፡

ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ እነሆ ፡ በነቢያት ፡ ቃል፡ ታምናለህ ።

ወአአምር ፡ ከመሰ ፡ ተአምን ፡

እንድታምንስ ፡ አውቃለሁ ።

፳፰ ፤ ወይቤሎ ፡ አግሪጳ ፡ ለጳውሎስ ፡ ተኀይጠኒኑ ፡ ታብአኒ ፡ ውስተ ፡ ዐቢይ ፡ ክርስቲያን ።

ጳውሎስ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያንነት ፡ ትመልሰኝ ፡ ዘንድ ፡ ታታልለኛለህን ።

ሕቀ ፡ ክመ ፡ ዘእምአባእከኒ ፡ ውስተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይእዜ ።

ዛሬ፡ ወደ፡ ክርስቲያንነት፡ ልትመልሰኝ ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ቀርቶሃል ፡ አለው ።

፳፱ ፤ ወይቤሎ ፡ ጳውሎስ ፡ አንሰ ፡ እጼሊ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

እኔስ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጸልያለሁ ።

እመሂ ፡ በኅዳጥ ፡ ወእመሂ ፡ በብዙኅ ።

በጥቂትም ፡ ቢሆን ፡ በብዙም ፡ ቢሆን ።

አኮ ፡ ባሕቲትከ ፡

የምጸልይም ፡ ላንተ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

አላ ፡ ዓዲ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይሰምዑኒ ፡ ዮም ፡ ይኩኑ ፡ ከማየ ፡

ዛሬ ፡ የሚሰሙኝም ፡ ሁሉ ፡ ሰዎች ፡ እንደኔ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጅ ።

ዘእንበለ ፡ ዝ ፡ መዋቅሕት ።

ከዚህ ፡ እሥራት ፡ በቀር ፡ አሁንስ ፡ እሥራት ፡ ይካሰስብናል ፡ ሆነ ፡ እንዳይሉት ፡ ዘእንበለ ፡ ዝ ፡ መዋቅሕት ፡ አለ ።

፴ ፤ ወእምዝ ፡ ተንሥአ ፡ ንጉሥ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ መወከንን ።

አገረ ፡ ገዡ ፡ ፊስጦስ ።

ወበርንቄ ፡

በርንቄም ።

ወዐበይቶሙ ፡ ወተግሒሦሙ ፡ በባሕቲቶሙ ፡

ታላላቆቹም ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው ፡ ለብቻቸው ፡ ሁነው ።

ተናገሩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡

እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተነጋገሩ ።

፴፩ ፤ ወይቤሉ ፡ አልቦ ፡ ዘአበሰ ፡ ዝ ፡ ብእሲ ፡ በዘ ይመውት ።

ይህ ፡ ሰው ፡ በሚሞት ፡ ገንዘብ ።

ወኢበዘይትሞቃሕ ፡

ስንኳን ፡ መሞት ፡ በሚታሠር ፡ ገንዘብ ፡ የበደለው ፡ በደል ፡ የለም ፡ ብለው ።

፴፪ ፤ ወይቤሎ ፡ አግሪጳ ፡ ለፊስጦስ ፡ መፍትው ፡ እመ ፡ ፈታሕክሙ ፡ ዘንተ ፡ ብእሴ ፡ ወኀደግምዎ ፡ ይሕየው ፡

አግሪጳም ፡ ፊስጦስን ፡ ከቅጣት ፡ ያድነው ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ፈትታችሁ ፡ ልትሰዱት ፡ ይገባ ፡ ነበር ።

ወእመአኮሰ ፡ ተማኅፀነ ፡ በቄሣር ።

ያውም ፡ ባይሆን ፡ ከቄሣር ፡ እደርሳለሁ ፡ ብሏልና ።

ወኀበ ፡ ቄሣር ፡ የሐውር ፡

ወደ ፡ ቄሣር ፡ ይሄዳል ።

ወኀበ ፡ ቄሣር ፡ ፈንዎ ፡

ወደ ፡ ቄሣር ፡ ስደደው ፡ አለው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፡ ፳፯ ፡ ክፍል ፡ ፵፱ ።

፩ ፤ ወእምዝ ፡ አዘዘ ፡ ፊስጦስ ፡ ይስድዎ ፡ ኀበ ፡ ቄሣር ፡ አንጣክያ ።

ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ተማኅፀነ ፡ በቄሣር ፡ ወኀበ ፡ ቄሣር ፡ የሐውር ፡ ወኀበ ፡ ቄሣር ፡ ፈንዎ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቄሣር ፡ ካለበት ፡ አንጣክያ ፡ ውሰዱት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፡ ሐተታ ፡ ምነው ፡ ቄሣር ፡ ያለ ፡ በሮም ፡ አይደለም ፡ ቢሉ ፡ ደርቦ ፡ ገዝቶ ፡ ነበር ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ አንጾኪያ ፡ ወርዶ ፡ ነበርና ። አንድም ፡ መንገድ ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ ቀንቶ ፡ ነበር ፡ አንጾኪያ ፡ ደርሶ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ይወጣልና ፡ ይሰድዎ ፡ ኀበ ፡ ቄሣር ፡ አንጣክያ ፡ አለ ።

ወተውህበ ፡ ጳውሎስ ፡ ወካልአንኒ ፡ ሙቁሐን ፡ ምስሌሁ ፡ ለብእሲ ፡ እምነ ፡ ሐራ ፡ ሰብስጥያ ፡ ዘስሙ ፡ ዩልዮስ ፡ ሐቢ ፡

ሰብስጥያ ፡ ከሚባል ፡ ጭፍራ ፡ ዩልዮስ ፡ ለሚባል ፡ ሹም ፡ ጳውሎስ ፡ አለፈ ። ተውህቡ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ሌሎችም ፡ እሥሮች ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ አለፉ ፡ አገብአ ፡ ለኤልዛቤል ፡ ወለእለኒ ፡ ዘመዉ ፡ ምስሌሃ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ አገብአሙ ፡ እንዳለበት ። ትኤምኃክሙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኅሬት፡ እንተ ፡ ውስተ ፡ ባቢሎን ፡ ዘግብፅ ፡ ወማርቆስ ፡ ወልድየ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ይኤምኃክሙ ፡ እንዳለበት ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ፲፪ ።

፪ ፤ ወሶበ ፡ ወፃእነ ፡ ከመ ፡ ንንግድ ።

መንገድ ፡ በጀመርን ፡ ጊዜ ።

ረከብነ ፡ ሐመረ ፡ እምአሕማረ ፡ አድራማጡስ፡እንተ፡ ትፈቅድ ፡ ሐዊረ ፡ ብሔረ ፡ እስያ ።

ከአድራማጡስ ፡ ከመጡ ፡ መርከቦች ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ የምትሄድ ፡ መርከብ ፡ አግኝተን ፡ በዚያች ፡ ተጭነን ፡ ሄድን ።

ወነገደ ፡ ምስሌነ ፡ አርስጠኬፉ ፡ መቄዶናዊ ፡ ዘሀገረ ፡ ተሰሎንቄ ።

የተሰሎንቄ ፡ አውራጃ ፡ የምትሆን ፡ የመቄዶንያ ፡ ሰው ፡ አርስጠኬፉም ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ሄደ ፡ ም ፡ ፲፱ ፡ ፳፱ ።

፫ ፤ ወበሳኒታ ፡ በጻሕነ ፡ ሳይዳ ፡

በነጋው ፡ ሳይዳ ፡ ደረስን ።

ወመሐሮ ፡ መልአክ ፡ ለጳውሎስ ፡

ሹሙም ፡ ለጳውሎስ ፡ አዘነለት ።

ወአብሖ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡ ዐርካኒሁ ፡ ከመ ፡ ያዕርፍ ፡ ኀቤሆሙ ፡

ከወዳጆቹ ፡ አርፎ ፡ ይሰነብት ፡ ዘንድ ፡ አርፈህ ፡ ሰንብት ፡ አለው ፡ ም ፡ ፳፬ ፡ ፳፫ ። ፳፰ ፡ ፲፮ ።

፬ ፤ ወእምዝ ፡ ሖርነ ፡ እምህየ ፡ ወበጻሕነ ፡ አድያመ ፡ ቆጵሮስ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ወጥተን ፡ ወደ ፡ ቆጵሮስ ፡ አውራጃ ፡ ደረስን ።

እስመ ፡ ነፋስ ፡ እምገጽነ ።

ነፋስ ፡ ከወደ ፡ ፊታችን ፡ ተነሥቶ ፡ ነበርና ።

፭ ፤ ወቦእነ ፡ ባሕረ ፡ ቂልቅያ ፡

ወደ ፡ ቂልቅያ ፡ ባሕር ፡ ገባን ።

ወሖርነ ፡ ለሙራ ፡ ዘብሔረ ፡ ሉቅያ ፡ ይእቲ ፡

ከዚያም ፡ ወጥተን ፡ የሉቅያ ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ ሙራ ፡ ሄድን ።

፮ ፤ ወበህየ ፡ ረከበ ፡ መልአክ ፡ ሐመረ ፡ እስክንድርያ ፡ እንተ ፡ ተሐውር ፡ አንጾኪያ ።

ከዚያም ፡ ሹሙ ፡ ከእስክንድርያ ፡ የመጣች ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ የምትወስድ ፡ መርከብ ፡ አገኘ ።



ወነበርነ ፡ ውስቴታ ፡

በሷ ፡ ተጭነን ፡ ሄድን ።

ወይእቲሰ ፡ ሐመር ፡ ክብድ ፡ ሖረት ።

ይህችም ፡ መርከብ ፡ ዝግ ፡ ብላ ፡ ሄደች ፡ ክብድ ፡ ሖረታ ፡ ክብደ ፡ ሖረት ፡ ይላል ፡ አካሄዱ ፡ ዝግ ፡ ያለ ፡ ነበር ።

፯ ፤ ወእምድኅረ ፡ ዝ ፡ በብዙኅ ፡ መዋዕል፡ በጻሕነ፡ ለገጸ ፡ ደሴተ ፡ ቀኒዶስ ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በብዙ ፡ ቀን ፡ ቀኒዶስ ፡ በሚባል ፡ ደሴት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ደረስን ።

ወበእንተ ፡ ጽንዓ ፡ ነፋስ ፡ ኢክህልነ ፡ ሐዊረ ፡ ርቱዐ ፡

ከነፋሱ ፡ ብርታት ፡ የተነሣ ፡ ፊት ፡ ፊት ፡ ቀንቶ ፡ መሄድ ፡ አልተቻለንም ።

ወነገድነ ፡ አድያመ ፡ አቅሬጥስ ፡ ለገጸ ፡ ሀገረ ፡ ስልማና ፡

ስልማና ፡ ለምትባል ፡ አገር ፡ አንጻር ፡ ወደምትሆን ፡ ወደ ፡ አቅሬጥስ ፡ ሄድን ።

፰ ፤ ወእምዕፁብ ፡ እንዘ ፡ ነሐውር፡ ንሕነ ፡ ጥቃሃ ፡ በጻሕነ ፡ ለመካን ፡ ዘስማ፡ መርስ፡ ሠናይት ፡ ቅሩብ ፡ ለሀገር ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ለአስ ፡

ባጠገብ ፡ ባጠገብ ፡ ስንሄድ ፡ በጭንቅ ፡ ለአስ ፡ ለምትባል ፡ አገር ፡ አቅራቢያ ፡ ወደምትሆን ፡ መርስ ፡ ሠናይት ፡ ወደ ፡ ምትባል ፡ ወደብ ፡ ደረስን ።

፱ ፤ ወጐንደይነ ፡ ህየ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ እስከ ፡ ቦአ ፡ ዕለተ ፡ ጾመ ፡ አይሁድ ።

የአይሁድ ፡ ጾም ፡ እስቲገባ ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ሰነበትን ።

ወበጽሐ ፡ መዋዕል ፡ ዘኢይክሉ ፡ ሰብእ ፡ ነጊደ ፡ በባሕር ፡ ውእተ ፡ ጊዜ ፡

ያን፡ ጊዜ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ በባሕር፡ ሊሄዱ ፡ የማይችሉበት ፡ ወራት ፡ ደረሰ፡ ክረምት፡ ስለ ፡ ገባ ።

ወእምዝ ፡ አምከሮሙ ፡ ጳውሎስ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ መከራቸው ፡ ፪ ፡ ቆሮ፡ ፲፩፡ ፳፫፡ ፳፯። ዘሌዋ፡ ፲፯፡ ፳፱ ።

፲ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ስምዑኒ ፡ አ ፡ ወራዙት ።

ወራዙት ፡ ስሙኝ ።

እስመ ፡ እሬኢ ፡ ንግደተነ ፡ በብዙኅ ፡ ምንዳቤ ፡ ወሐጕል ፡ ዐቢይ ፡

አካሄዳችን ፡ በብዙ ፡ ጭንቅ ፡ በብዙ ፡ ጉዳት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አውቃለሁና ፡ ስሙኝ ።

ወዘንተ ፡ ዘእብል ፡

ይህነንም ፡ የምል ።

አኮ ፡ በእንተ ፡ ጾረ ፡ ሐመር ፡ ባሕቲቱ ።

በመርከብ ፡ ስላለው ፡ ዕቃ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

ዓዲ ፡ ነፍስነሂ ፡ ታሐጕሉነ ፡

ሰውነታችነንም ፡ ታጡናላችሁ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተሐጕሉ፡ ታጠፉናላችሁ ፡ ብየ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ኅድጉ ፡ እስመ ፡ እፈርህ ፡

እፈራለሁና ፡ ተዉ ፡ አላቸው ።

፲፩ ፤ ወመልአክሰ፡ ለሰብአ፡ ሐመር፡ ይትኤዘዞሙ ፡

ሹሙም ፡ በመርከብ ፡ ላሉት ፡ ሰዎች ፡ ለቀዛፎች ፡ ይታዘዛቸው ፡ ነበር ።

ወይትዌከፍ ፡ ቃሎሙ ፡

ቃላቸውንም ፡ ይቀበላቸው ፡ ነበር ።

ወለጳውሎስሰ ፡ ይሰምዖ ፡ ወኢይትዌከፍ ፡ ቃሎ ።

ጳውሎስን ፡ ግን ፡ ሰምቶ ፡ ቃሉን ፡ አይቀበለውም ፡ ነበር ።

፲፪ ፤ ወውእቱሰ ፡ መርሶ ፡ ኢይደሉ ፡ ይክርሙ ፡ ውስቴቱ ፡ ክረምተ ፡

ያም ፡ ወደብ ፡ በክረምት ፡ ሊከርሙበት ፡

www.ethiopianorthodox.org

የማይመች ፡ ነበር ፡ እንደ ፡ ፎገራ ፡ ያለ ፡ ነው ።

ወበእንተ፡ ዝ፡ አፍቀሩ፡ ብዙኃን፡ ከመ፡ይፃኡ፡እምህየ፡

ስለዚህ ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ ከዚያ ፡ ወጥ ተው ፡ ሊሄዱ ፡ ወደዱ ።

ለእመ ፡ ተክህሎሙ ፡ ከመ ፡ ይብጽሑ ፡ ለካልእ ፡ መርሶ ፡

ቢቻላቸው ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ወደብ ፡ ይደ ርሱ ፡ ዘንድ ።

ዘፊንቂ ፡

ይኸውም ፡ ፊንቂ ፡ ነው ።

ዘመንገለ ፡ አቅራጥስ ፡

በአቅራጥስ ፡ አጠገብ ፡ ያለች ።

ዘስማ ፡ ኤውንቄ ፡

ኤውንቄ ፡ የምትባል ።

ዘመንገለ ፡ የማን ፡

በቀኝ ፡ በኩል ፡ ያለች ።

፲፫ ፤ ወነፍኀ ፡ ነፋስ ፡ ዐዜብ ፡

ከወደ ፡ ግራ ፡ ነፋስ ፡ ነፈሰ ።

ወመሰሎሙ ፡ ዘይበጽሑ ፡ በከመ ፡ ፈቀዱ ፡ ወአል ዐሉ ፡ ሥራዓ ፡

እንደ ፡ ወደዱ ፡ ወደ ፡ ወደዱት ፡ ወደብ ፡ የደረሱ ፡ መስሏቸው ፡ ዐላማውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ።

ወሖሩ ፡ ደወለ ፡ አቅራጥስ ፡

ወደ ፡ አቅራጥስ ፡ አውራጃ ፡ ሄዱ ።

፲፬ ፤ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ መጽአ ፡ ላዕ ሌሆሙ ፡ ነፋስ ፡ ጽኑዕ ፡

ከጥቂት ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ጽኑ ፡ ነፋስ ፡ ነፈሰ ።

ጥፉንቂስ ፡

ጥፉንቂስ ፡ የሚባል ።

ዘይብልዎ ፡ አውራቂስ ፡

ባንድ ፡ ልሳን ፡ አውራቂስ ፡ የሚሉት ፡ ሐተታ ፡ ቂልጊ ፡ ጉደሪ ፡ ጽባሒ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ወይእቲ ፡ ነፋስ ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ሰልቢባ ፡

ይህችም ፡ ነፋስ ፡ ሰልቢባ ፡ ትባላለች ፡ አለ ፡ ልክስክስ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፲፭ ፤ ወተለዐለት ፡ ሐመርነ ፡ ወተዘብጠት ፡

መርከባችን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ተነሥታ ፡ ወደ ቀች ።

ወኢክህሉ ፡ ኖትያት ፡ ቀዊመ ፡ ቅድመ ፡ ገጸ ፡ ነፋስ ፡

ቀዛፎቹም ፡ በነፋሱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ቁሞ፡ መቅዘፍ ፡ አልተቻላቸውም ።

ወኀደግዋ ፡

ትሂድ ፡ ብለው ፡ ተዋት ።

ወሖረት ፡

ሄደች ።

፲፮ ፤ ወእምዝ ፡ ነፍሐ ፡ ነፋስ ፡ እስከ ፡ ቦእነ፡ ደሴተ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ቁዳ ፡

ከዚያ ፡ ጀምሮ ፡ ቁዳ፡ ከምትባል ፡ ደሴት ፡ እስትንገባ ፡ ድረስ ፡ ነፋስ ፡ ነፈሰ ።

ወእምዕፁብ ፡ ክህልነ ፡ ከመ ፡ ናርግዝ ፡ ሐመረነ ፡

በጭንቅ ፡ መርከባችነን ፡ ከወደቡ ፡ ማሳ ረፍ ፡ ተቻለን ፡ አርግዙ ፡ እንዲል ፡ ትግሬ፤

፲፯ ፤ ወእምዝ ፡ ተሐጊዘነ ፡ አጽናዕናሃ ፡ በአሕባል ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐላማ ፡ ትከል ፡ መልሕቅ ፡ ጣል ፡ ብለን ፡ አጸናናት ።

ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ፈርሁ ፡ ከመ ፡ ኢይደቁ ፡ ውስተ ፡ ልጐተ ፡ ባሕር ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከጥልቅ ፡ ባሕር ፡ እንዳይ ወድቁ ፡ በፈሩ ፡ ጊዜ ፡ ቀዛፎች ፡ ናቸው ።

አውረዱ ፡ ሥራዓ ፡

ዐላማውን ፡ ዝቅ ፡ አደረጉ ።



ወረሰይነ ፡ ንሑር ፡ ከማሁ ፡

እንደ ፡ ነፋሱ ፡ አነፋፈስ ፡ አለስልሰን ፡ ሄድነ ።

፲፰ ፤ ወበሳኒታ ፡ ጸንዐ ፡ ላዕሌነ ፡ መዋግድ ፡

በነጋው ፡ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ በረታብን ።

ወገደፍነ ፡ አልባሲነ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡

ልብሳችነን ፡ እያነሣን ፡ ከባሕር ፡ ጣልነ ።

፲፱ ፤ ወበሣልስታሂ ፡ ገደፍነ ፡ ኵሎ ፡ ዘውስተ ፡ ሐመር ፡ ዲበ ፡ ባሕር ፡ በእደዊነ ፡

በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ በመርከቡ ፡ ያለውን፡ ሁሉ ፡ ዕቃ ፡ በጃችን ፡ እያነሣን ፡ ከባሕር ፡ ጣልነ ።

፳ ፤ ወነበረ ፡ ይዘንም ፡ ላዕሌነ ፡ ጕንዱየ ፡ ዕለተ ፡ እንዘ ፡ ኢንሬኢ ፡ ፀሐየ ፡ ወወርኀ ፡ ወኢከዋክብተ ።

በመዓልት ፡ ፀሐይን፡ በሌሊት፡ ጨረቃን ፡ ከዋክብትን ፡ ሳናይ ፡ ሲዘንም ፡ ውሎ ፡ ሲዘንም ፡ አደረ ።

ወቀበጽነ ፡ ሐይወ ፡

እንድናለን ፡ የማለትን ፡ ተስፋ ፡ ቆረጥነ ።

፳፩ ፤ ወአልቦ ፡ ዘበልዐ ፡ መብልዐ ፡ እምኔነ ፡

ከኛም ፡ ወገን ፡ እህል ፡ የቀመሰ ፡ የለም ።

ወተንሥአ ፡ ጳውሎስ ፡ ወቆመ ፡ ማእከለ ፡

ጳውሎስም ፡ ተነሥቶ ፡ በመካከል ፡ ቁሞ።

ወይቤሎሙ ፡ ሶበ ፡ ሰማዕክሙኒ ፡ ቀዲሙ ፡ አኀውየ ፡

ወንድሞቼ ፡ ቀድሞ ፡ የነገርኋችሁን ፡ ብት ሰሙ ፡

ወኢወፃእክሙ ፡ እምአቅራጥስ ፡

ከአቅራጥስ ፡ ባትወጡ ።

እምድኅንክሙ ፡ እምዝ ፡ ሐጕል ፡ ወሕማም ፡

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጉዳት ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ባላገኛችሁም ፡ ነበር ።

፳፪ ፤ ወይእዜኒ ፡ እብለክሙ ፡ ኢትፍርሁ ፡

አሁንም ፡ አይዟችሁ ፡ እላችኋለሁ ።

እስመ፡ አልቦ፡ ዘይትሐጐል፡ አሐዱ፡ ነፍስ፡ እምኔነ ፡

ከኛ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ስንኳ ፡ የሚጠፋ ፡ የለምና ።

ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ሐመርነ ፡

መርከባችን ፡ ይሰበራል ፡ እንጂ ።

፳፫ ፤ እስመ ፡ ቆመ ፡ ኀቤየ ፡ በዛቲ ፡ ሌሊት ፡ መል አከ ፡ እግዚአብሔር ።

ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ ካጠገቤ ፡ ቁሞ ።

ዘአነ ፡ ሎቱ ፡

እኔ ፡ ባልደረባው ፡ የምሆን ።

ወኪያሁ ፡ አመልክ ፡

ነገሩን ፡ የማምነው ። አንድም ፡ እኔ ፡ ፍጥ ረቱ ፡ የምሆን ፡ የማመልከው ፡ ብሎ ፡ ለእ ግዚአብሔር ፡ ይቀጥላል ።

፳፬ ፤ ወይቤለኒ ፡ ኢትፍራህ ፡ ጳውሎስ ፡ ሀለወከ ፡ ትቁም ፡ ቅድመ ፡ ቄሣር ፡

ጳውሎስ ፡ ከቄሣር ፡ ፊት ፡ ትደርስ ፡ ዘንድ አለህና ።

ወናሁ ፡ ጸገወከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ነገዱ ፡ ምስሌከ ፡

ካንት ፡ ጋራ ፡ የሚሄዱትን ፡ ሁሉ ፡ እግዚ አብሔር ፡ በሃይማኖት ፡ ገንዘብ ፡ አድርጐ ልሃል ፡ አይዞህ ፡ ብሎኛልና ፡ አትፍሩ ፡ አላቸው ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ፲፩ ።

፳፭ ፤ ወይእዜኒ ፡ ተፈሥሑ ፡ አኀውየ ፡ እስመ ፡ እትአመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይከውን ፡ በ ከመ ፡ ይቤለኒ ፡

አሁንም ፡ ወንድሞቼ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መላክ ፡ የነገረኝ፡ እንደ፡ ነገረኝ፡ እንዲደረግ፡ አምናለሁና፡ ደስ፡ ይበላችሁ ።

፳፮ ፤ ወንበጽሕ ፡ አሐተ ፡ ደሴተ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ ካንዲት ፡ ደሴት ፡ እንደርሳ ለን ፡ ም ፡ ፳፰ ፡ ፩ ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፯ ፤ ወአመ ፡ ዐሡር ፡ ወረቡዕ ፡ ጊዜ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡

ባሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ሲሆን ።

መሰሎሙ ፡ ኖትያት ፡ ከመ ፡ ይበጽሑ ፡ ምድረ ።

ከወደቡ ፡ የደረሱ ፡ መሰሏቸው ።

፳፰ ፤ ወአውረዱ ፡ ሐብለ ፡

መልሕቁን ፡ ጣሉ ።

ወረከቡ ፡ ዕሥራ ፡ በቆመ ፡ ብእሲ ፡

ኻያ ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ አገኙ ።

ወተአተቱ ፡ እምህየ ፡ ወአውረዱ ፡ ካዕበ ፡

ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ብለው ፡ ዳግመኛ ፡ መልሕቅ ፡ ጣሉ ።

ወረከቡ ፡ ዐሠርተ ፡ ወኀምስተ ፡ በቆም ፡

ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ቆመ ፡ ብእሲ ፡ አገኙ ።

፳፱ ፤ ወፈርሁ ፡ ከመ ፡ ኢይደቁ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ዘቦቱ ፡ ኰኵሕ ፡

ደንጊያ ፡ ካለበት ፡ ቦታ ፡ እንዳይወድቁ ፡ በፈሩ ፡ ጊዜ ።

ወከመ ፡ ኢይትጐዳእ ፡ ሐመሮሙ ፡

መርከባቸውም ፡ እንዳይሰበር ፡ ፈርተው።

ወአውረዱ ፡ አርባዕተ ፡ መልሕቀ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ እንተ ፡ ድኅረ ፡ ሐመር ፡

በስተከበሮ ፡ ቤት ፡ ያለውን ፡ አራት ፡ መልሕቅ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ጣሉ ።

ወጸለይነ ፡ ከመ ፡ ፍጡነ ፡ ይጽባሕ ፡

ፈጥኖ ፡ ይነጋ ፡ ዘንድ ፡ ጸለይነ ።

፴ ፤ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ፈቀዱ ፡ ይትኃጥኡ ፡ ኖትያት ፡ እምሐመር ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቀዛፎች ፡ ከመርከቡ ፡ ሊኰበልሉ ፡ በወደዱ ፡ ጊዜ ።

አውረዱ ፡ እምኒሃ ፡ ራግናተ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡

ሻንቡቅ ፡ የምትባለውን ፡ ቀላል ፡ ፈጣን ፡ መርከብ ፡ አንሥተው ፡ ከባሕር ፡ ጣሉ ።

ከመ ፡ ይደሀሉ ፡ ቦቱ ፡

ይኰበልሉባት ፡ ዘንድ ፡

ወያጽንዑ ፡ ሐመሮሙ ፡ በምድር ፡

መርከባቸውንም ፡ ከወደቡ ፡ ያስጠጉ ፡ ዘንድ ።

፴፩ ፤ ወርእዮ ፡ ጳውሎስ ፡

ጳውሎስም ፡ ይህን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ።

ይቤሎሙ ፡ ለሐቢ ፡ ወለሠገራት ፡ እምከመ ፡ ኢነበሩ ፡ እሉ ፡ ኖትያት ፡ ውስተ ፡ ሐመር፡ ኢንክል ፡ ሐይወ ፡

ለሹሙና ፡ ለጭፍሮቹ ፡ እሊህ ፡ ቀዛፎች ፡ ከመርከብ ፡ ከሌሉ ፡ ድኅነት ፡ አናገኝም ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ።

፴፪ ፤ ወተንሥኡ ፡ ሠገራት ፡

ጭፍሮቹም ፡ ተነሥተው ።

ወመተሩ ፡ ሶቤሃ ፡ አሕባለ ፡ ራግናት ፡ ወኀደግዋ ፡ ትደቅ ፡

ያን ፡ ጊዜ ፡ መልሕቁን ፡ ቆርጠው ፡ ትሂድ ፡ ብለው ፡ተዋት ፡ ሄደች ።

፴፫ ፤ ወጸቢሖ ፡ ብሔር ፡ አስተብቍዖሙ ፡ ጳውሎስ ፡ ለኵሎሙ ፡ ይብልዑ ፡ እክለ ፡

በነጋ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ፡ ሁሉንም፡ እህል ፡ ቅመሱ ፡ ብሎ ፡ ማለዳቸው ።

ወይቤሎሙ ፡ ዐሡር ፡ ወረቡዕ ፡ ዮም ፡ እምዘአበላዕክክሙ ፡ እክለ ፡

እህል ፡ ካልቀመሳችሁ ፡ ዛሬ ፡ ዐሥራ ፡ አራተኛ ፡ ቀናችሁ ፡ ነው ። (እምዘበላዕክሙ) ፡ እህል ፡ ከቀመሳችሁ ፡ ዛሬ ፡ ዐሥራ ፡ አራተኛ ፡ ቀናችሁ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቍ ፡ ፳፯ ።



፴፬ ፤ ወዮምኒ ፡ ብቍዑኒ ፡

አሁንም ፡ በጅ ፡ በሉኝ ።

ምስሑ ፡

እህል ፡ ቅመሱ ።

ወብልዑ ፡ ወርድኡ ፡ ነፍሰክሙ ፡

በልታችሁ ፡ ሰውነታችሁን ፡ አጽኑ ።

እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘይትሐጐል ፡ እምእኔክሙ ፡

ከናንት ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ የሚጠፋ ፡ የለምና ።

ወኢሥእርተ ፡ ርእስክሙ ፡

የራስ ፡ ጠጉራችሁ ፡ ስንኳ ፡ አይጠፋምና ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፴ ።

፴፭ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡

ይህን ፡ ተናግሮ ።

ነሥአ ፡ ኅብስተ ፡ ወአእኰተ ፡ እግዚአብሔርሃ ፡

ዳቦውን ፡ አንሥቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገነ ፡ ጸሎተ ፡ ማዕድ ፡ ጸለየ ።

ወከፈለ ፡ ቅድመ ፡ ኵሎሙ ፡

ከፍሎ ፡ ለሁሉም ፡ አደላቸው ።

ወአኀዙ ፡ ይብልዑ ፡

ይበሉ ፡ ጀመሩ ፡ ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፲፩ ። ፩ ፡ ጢሞ ፬ ፡ ፬ ።

፴፮ ፤ ወተናዘዙ ፡ ኵሎሙ ፡ ወጥዕሙ ፡

ሁሉም ፡ በልተው ፡ ጸኑ ።

፴፯ ፤ ወኮነ ፡ ፍቅዶሙ ፡ ለእለ ፡ ሀለዉ ፡ ውስተ ፡ ሐመር ፡ ክልኤ ፡ ምእት ፡ ወሰብዓ ፡ ወስድስቱ ፡ ነፍስ፣

በመርከብ ፡ ያሉትም ፡ ሰዎች ፡ ቍጥራቸው ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ስድስት ፡ ነበር ።

፴፰ ፤ ወተሴሰዮሙ ፡ አቅለሉ ፡ ሐመረ ፡

በልተው ፡ ለመርከቡ ፡ ቀለሉት ፡ ሐተታ ፡ ያልበላ ፡ ሬሳ ፡ እንዲሉ ፡ ያልበላ ፡ ይከብዳልና ። አንድም ፡ መርከባቸውን ፡ አቃለው ፡ ቀዘፉ ።

ወነሥኡ ፡ ሥርናየ ፡ ዘውስተ ፡ ሐመር ፡ ወወገሩ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡

በመርከቡ ፡ ያለውን ፡ ሥንቃቸውን ፡ እያነሡ ፡ ከባሕር ፡ ጣሉ ።

፴፱ ፤ ወጸቢሖ ፡ መዓልተ ፡ ኢያአመሩ ፡ ኖትያት ፡ ውእተ ፡ ምድረ ፡ ወኢያእመሩ ፡ ዘየሐውሩ ፡

በነጋ ፡ ጊዜ ፡ ቀዛፎች ፡ ወደቡን ፡ አላወቁም፡ የሚሄዱበትንም፡ አላወቁም፡ ነበር ።

ወባሕቱ ፡ ርእዩ ፡ አድባረ ፡ ደሴት ፡ ዘቅሩብ ፡ ለሐይቀ ፡ ባሕር ፡

ለባሕሩ ፡ ወደብ ፡ ቅርብ ፡ የምትሆን ፡ የደሴቷን ፡ ተራራ ፡ አዩ ፡ እንጅ ።

ወፈቀዱ ፡ ያብጽሑ ፡ ሐመሮሙ ፡ ህየ ፡

መርከባቸውን ፡ ከዚያ ፡ ሊያስጠጉ ፡ ወደዱ ።

፵ ፤ ወመተሩ፡ መልሕቀ ፡ ወኀደጉ ፡ ውስተ፡ ባሕር ፡

መልሕቁን ፡ ቆርጠው ፡ ከባሕር ፡ ጣሉ ።

ወአሠነዩ ፡ ምቅዋመ ፡

የሚቆሙበትን ፡ አመቻቹ ።

ወሰቀሉ ፡ ሥራዓ ፡ ዘይንእስ ፡ በከመ ፡ ንፍሐተ ፡ ነፍስ ፡

ነፋሱ ፡ በሚነፍስበት ፡ በኩል ፡ ታናሹን ፡ ዐላማ ፡ ሰቀሉ ።

ወሖርነ ፡ መንገለ ፡ ሐይቀ ፡ ባሕር ፡

ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ወደብ ፡ ሄድነ ።

፵፩ ፤ ወተለክአት ፡ ሐመር ፡ ማእከለ ፡ ክልኤቱ ፡ አእባን ፡ ልዑላት ።

መርከቢቱ ፡ ሂዳ ፡ ከሁለት፡ ታላላቅ ፡ ደንጊያዎች ፡ መካከል ፡ ተቀረቀረች ።

ወባሕሩ ፡ ዕሙቅ ፡

ባሕሩም ፡ ጥልቅ ፡ ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

ወተእኅዘት ፡

ከመሄድ ፡ ተገታች ።

ወተሰብረት ፡ ወተመትረት ፡ ገቦሃ ፡ ዘድኅር ፡ እም ገድ ፡

ከማዕበሉ ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ በስተከበሮ ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ ተሰበረች ። ዘድኅፀ ፡ እሞገድ ፡ ይላል ፡ ማዕበሉ ፡ በከረከረበት ፡ በኩል ፡ ተሰበረች ።

ወእምቅድሜሃሰ ፡ ኢክህሉ ፡

ከወደ፡ ፊቷ፡ግን፡ቀዛፎች፡ ሊገቷት፡ አልተቻላቸውም ። አንድም ፡ ድንጊያዎች ፡ ሊገቷት ፡ አልተቻላቸውም ፡ ሐተታ ፡ መርከብ ፡ ከወደ ፡ ፊት ፡ ያሞጠሞጠ ፡ ነው ፡ ከወደ ፡ ኋላ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ነውና ፡ ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭ ።

፵፪ ፤ ወተማከሩ ፡ ሠገራት ፡ ከመ ፡ ይቅትሉ ፡ ሙቁሓነ ፡ ከመ ፡ ኢይጽብቱ ፡ ወኢያምሥጡ ፡

ዋኝተው ፡ እንዳያመልጡ ፡ እሥረኞችን ፡ ይገሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ጭፍሮች ፡ መከሩ ።

፵፫ ፤ ወከልአሙ ፡ ሐቢ ፡

ሹሙ ፡ ግን ፡ ከለከላቸው ።

እስመ ፡ ፈቀደ ፡ ያድኅኖ ፡ ለጳውሎስ ፡

ጳውሎስን ፡ ሊያድነው ፡ ወዷልና ።

ወለእሊ ፡ የአምሩ ፡ ጸቢተ ፡ አዘዞሙ ፡ ይጽብቱ ፡ ወይፃኡ ፡ ለሐይቅ ፡

ዋና ፡ የሚያውቁትንም ፡ ዋኝተው ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ።

፵፬ ፤ ወእለ ፡ ተርፉ ፡ ዐደዉ ፡ ላዕለ ፡ ዕፀ ፡ ሐመር ፡ ወሰላድዉ ፡

የቀሩትም ፡ በመርከቡ ፡ ስባሪ ፡ በሰሌዳው ፡ እየሆኑ ።

ወካልአን ፡ ዐደዉ ፡ በአሕባለ ፡ ሐመር ፡

እኩሌቶቹም ፡ የመርከቡን ፡ ገመድ ፡ እየያዙ ፡ ተሻገሩ ።

ወወፅኡ፡ኵሎሙ፡ወበጽሑ፡ምድረ፡በዘከመ፡ዝ፡ግብር፡

እንዲህ ፡ ባለ ፡ ነገር ፡ ወጥተው ፡ ከወደቡ ፡ ደረሱ ፡ ቍ ፡ ፳፪-፳፭ ።

## ምዕራፍ ፡ ፳፰ ።

፩ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ አእመርነ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ደሴት ፡ ትሰመይ ፡ መላጥያ ፡

ኢፈለጡ ፡ ኖትያት ፡ ብሔሮ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያች ፡ ደሴት ፡ መላጥያ ፡ እንድትባል ፡ አወቅነ ።

፪ ፤ ወመሐሩነ ፡ አረሚ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ህየ ፡

በዚያ ፡ የሚኖሩ ፡ አረማውያንም ፡ አዘኑልን ።

ወአሠነዩ ፡ ላዕሌነ ፡

በጎ ፡ ሥራ ፡ ሠሩልን ።

ወአንደዱ ፡ እሳተ ፡

ሥራውን ፡ አመጣው ፡ እሳት ፡ አንድደው፤

ወአስተጋብኡነ ፡ ለኵልነ ፡

ሁላችነንም ፡ ሰብስበው ።

ከመ ፡ ንስሐን ፡ እምጽንዓተ ፡ ቍር ፡ ወእምብዝኀተ ፡ ዝናም ፡

ከዝናሙ ፡ ብዛት ፡ ከብርዱ ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ ሙቁ ፡ አሉን ፡ ፪ ፡ ቆሮ፡ ፲፩ ፡ ፳፯ ።

፫ ፤ ወአስተጋብአ ፡ ጳውሎስ ፡ ብዙኀ ፡ ሐሠረ ፡ ወወገረ ፡ ላዕለ ፡ እሳት ፡

ጳውሎስም፡ ለትሩፋት፡ አያርፍምና፡ ብዙ፡ ግፋፎ ፡ አጋፎ ፡ ከእሳቱ ፡ ላይ ፡ ጨመረ ።

ወወፅአት ፡ አፍዖት ፡ እምላህበ ፡ እሳት ፡

ከእሳቱ ፡ ላንቃ ፡ እፍኝት ፡ ወጥታ ።



ወነሰከቶ ፡ እዴሁ ፡ ለጳውሎስ ፡

የጳውሎስን ፡ እጁን ፡ ነደፈችው ።

፬ ፤ ወሶበ ፡ ርእዩ ፡ አረሚ ፡ አፍዖተ ፡ ስቅልተ ፡ ላዕለ ፡ እደ ፡ ጳውሎስ ፡

አረማውያንም ፡ እፍኝት ፡ በጳውሎስ ፡ እጅ ፡ ተጠምጥማ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ።

ተበሀሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡

እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንዲህ ፡ ተባባሉ ።

ዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ ይመስል ፡ ቀታሌ ፡ ነፍስ ፡

ይህ ፡ ሰው ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ይመስላል ።

ድኂኖ ፡ እምባሕር ፡ ኢኀደጎ ፡ ፍርደ ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ ፡ ይሕየው ፡

ከባሕርም ፡ ድኖ ፡ ቢወጣ ፡ ይድን ፡ ዘንድ፡ ፍርደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አለቀቀውም ፡ ተባባሉ ።

፭ ፤ ወነገፈ ፡ ጳውሎስ ፡ እዴሁ ፡

ጳውሎስም ፡ እጁን ፡ አራገፈ ።

ወነጽሓ ፡ ለአፍዖት ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡

እፍኝትን ፡ በእሳት ፡ ላይ ፡ ጣላት ።

ወኢረከቦ ፡ ሕሠም ፡

ጉዳት ፡ አላገኘውም ፡ ሕሡም ፡ ይላል ፡ ክፉ ፡ ነገር፡ አላገኘውም ፡ ማር ፡ ፲፮፡ ፲፰።

፮ ፤ ወእሙንቱሰ ፡ መሰሎሙ ፡ ከመ ፡ በጊዜሃ ፡ ይመውት ፡

እነሱ ፡ ግን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የሚሞት ፡ መስሏቸው ፡ ነበርና ።

ወቆሙ ፡ ጕንዱየ ፡ እንዘ ፡ ይኤጽርዎ ፡

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቁመው ፡ እሱን ፡ እሱን ፡ ተመለከቱ ።

ወሶበ ፡ ርእዩ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘብእሶ ፡

የጐዳው ፡ መጉዳት ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ።

መለሱ ፡ ካዕበ ፡ ቃሎሙ ፡

ዳግመኛ ፡ ቃላቸውን ፡ ለወጡ ።

ወይቤሉ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡

አምላክ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ፲፩ ።

፯ ፤ ወሀለወት ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ መካን ፡ ዐጸዱ ፡ ለብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ ፑፕልዩስ ፡

በዚያችም ፡ ደሴት ፡ ፑፕልዩስ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ የተክል ፡ ቦታ ፡ ነበረች ።

ወሥዩም ፡ ውእቱ ፡ በይእቲ ፡ ደሴት ፡

እሱም ፡ በዚያች ፡ ደሴት ፡ ሹም ፡ ነበር ።

ወተወክፈነ ፡ ኀቤሁ ፡ ውስተ ፡ ማኅደሩ ፡ ሠሉሰ ፡ መዋዕለ ፡ በትፍሥሕት ፡

ደስ ፡ ብሎት ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ ፡ ተቀብሎ ፡ በቤቱ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ አሰነበተን ።

፰ ፤ ወሀሎ ፡ አሐዱ ፡ ሕሙም ፡ አቡሁ ፡ ለፑፕልዩስ ፡ ዘቦቱ ፡ ሕማመ ፡ አማዑት ፡

ሆድ ፡ ቁርጠት ፡ የታመመ ፡ የፑፕልዩስ ፡ አባት ፡ የሚሆን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ።

ወቦአ ፡ ኀቤሁ ፡ ጳውሎስ ፡

ጳውሎስም ፡ ወደሱ ፡ ገብቶ ።

ወጸለየ ፡ ወአንበረ ፡ እዴሁ ፡ ላዕሌሁ ፡

እጁን ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ጭኖ ፡ ጸለየለት ።

ወአሕየዎ ፡

ከደዌውም ፡ አዳነው ።

፱ ፤ ወሶበ ፡ ርእዩ ፡ ዘገብረ ፡ ዘንተ ፡

ይህን ፡ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ።

አምጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ኵሎ ፡ ድውያነ ፡ ዘውስተ ፡ ውእቱ ፡ ደሴት ፡

በዚያች ፡ ደሴት ፡ ያሉ ፡ ድውያንን ፡ ሁሉ፡ አመጡለት ።

ወአሕየዎሙ ፡

ሁሉንም ፡ አዳናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

፲ ፤ ወአክበሩነ ፡ ፈድፋደ ፡ ዐቢየ ፡ ክብረ ፡

እጅግ ፡ በፍጹም ፡ ክብር ፡ አከበሩን ።

ወሶበ ፡ ወፃእነ ፡ አሥነቁነ ፡ በሑረትነ ፡ እምኀቤሆሙ እምድኅረ ፡ ሠለስቱ ፡ አውራኅ ፡

ከሦስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ከነሱ ፡ ዘንድ ፡ ወጥተን ፡ በምንሄድበት ፡ ጊዜ ፡ ሥንቃ ችነን ፡ አዘጋጅተው ፡ ሰጡን ።

፲፩ ፤ ወእምዝ ፡ ዐረግነ ፡ ዲበ ፡ ሐመረ ፡ ሰብአ ፡ እስክንድርያ ፡ ዘከረመት ፡ በይእቲ ፡ ደሴት ፡

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከእስክንድርያ ፡ መጥታ ፡ በዚያች ፡ ደሴት ፡ በከረመች ፡ መርከብ ፡ ተጭነን ፡ ሄድነ ።

ወባቲ ፡ ላዕሌሃ ፡ ለይእቲ ፡ ሐመር ፡ ትእምርተ ፡ ዲ ዮስቆሮስ ፡

በዚያችም ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ነበረባት ።

ዘውእቱ ፡ አምላከ ፡ ኖትያት ፡

ይኸውም ፡ ኖትያት ፡ የሚሰግዱበት ፡ ነው ። አንድም ፡ ዲዮስቆሪዶስ ፡ ይላል ፡ ዲዮስቆሪዶስ ፡ የሚባል ፡ የጣዖት ፡ ስም ፡ ተጽፎባት ፡ ነበር ፡ ይኸውም ፡ ኖትያት ፡ የሚያመልኩት ፡ ነው ። አንድም ፡ ዲዮስ ቆሪዲስ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ተጽፎ ባት ፡ ነበር ፡ ይኸውም ፡ የኖትያት ፡ አለ ቃ ፡ ነው ።

፲፪ ፤ ወነገድነ ፡ ወበጻሕነ ፡ ሰራቶስ ፡

ሂደን ፡ ሰራቶስ ፡ ደረስነ ።

ወነበርነ ፡ ህየ ፡ ሠሉስ ፡ መዋዕለ ፡

ከዚያ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሰነበትነ ።

፲፫ ፤ ወነገድነ ፡ እምህየ ፡

ከዚያም ፡ ወጥተን ፡ ሄድነ ።

ወበጻሕነ ፡ ለሀገረ ፡ ራቅዩን ፡

ራቅዩን ፡ ከምትባል ፡ አገር ፡ ደረስነ ።

ወበሳኒታ ፡ ወፃእነ ፡

በነጋው ፡ ከዚያ ፡ ወጥተን ፡ ሄድነ ።

ወእምድኅረ ፡ አሐቲ ፡ ዕለት ፡ ነፍሐ ፡ ነፋስ ፡ እም ገቦሃ ፡

ካንድ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ከወደኋላችን ፡ ነፋስ፡ ነፈሰ ።

ወወሰደነ ፡ ክልኤተ ፡ ዕለተ ፡ እስከ ፡ አብጽሐነ ፡ ቀር ጠበሉስ ፡ እንተ ፡ ሀገረ ፡ አንጾኪያ ።

የአንጾኪያ ፡ አውራጃ ፡ የምትሆን ፡ ቀርጠ በሉስ ፡ እስቲያደርሰን ፡ ድረስ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ወሰደን ።

፲፬ ፤ ወረከብነ ፡ በህየ ፡ አኀዊነ ።

በአንጾኪያ ፡ ወንድሞቻችነን ፡ አገኘን ።

ወአእተዉነ ፡

ተቀብለው ፡ ይዘውን ፡ ገቡ ።

ወነበርነ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ፡

ከነሱ ፡ ዘንድ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ሰነበትነ ።

ወእምዝ ፡ ሖርነ ፡ ወበጻሕነ ፡ ሮሜ ፡

ከሰባት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ወጥተን ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሄድነ ።

፲፭ ፤ ወሶበ ፡ ሰምዑ ፡ አኀዊነ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ህየ ።

በሮም ፡ ያሉት ፡ ወንድሞቻችንም ፡ መም ጣታችነን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ።

ወፅኡ ፡ ወተቀበሉነ ፡ እስከ ፡ ምሥያጥ ፡ ዘስሙ ፡ አፍ ዩስ ፡ ፋሩስ ፡

አፍዩስ ፡ ፋሩስ ፡ እስከሚባል ፡ አደባባይ ፡

ድረስ ፡ ወጥተው ፡ ተቀበሉን ።

ወእስከ ፡ ሠለስቱ ፡ ከዋኒት ፡

እስከ ፡ ሦስት ፡ ምዕራፍ ። አንድም ፡ ሦስ ት ፡ ትክል ፡ ደንጊያ ፡ እስካለበት ፡ ድረስ። አንድም ፡ አፍዩስ ፡ ፋሩስ ፡ እስከሚባል ፡ ገበያ ፡ ድረስ ፡ ሦስት ፡ ነገር ፡ እስከሚሸ ጥበት ፡ ዳቦ ፡ ጠጅ ፡ ሥጋ ።



ወሶበ፡ ርእዮሙ፡ ጳውሎስ፡ አእኰተ፡እግዚአብሔርሃ።

ጳውሎስም ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብ ሔርን ፡ አመሰገነ ።

፲፮ ፤ ወተጸናዕነ ፡ ወቦእነ ፡ ሮሜ ፡

ተጸናንተን ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ገባን ።

ወአብሖ ፡ ሐቢ ፡ ለጳውሎስ ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ኀበ ፡ ፈቀደ ፡

ሹሙም ፡ ጳውሎስን ፡ ከወደደው ፡ አርፎ ፡ ይሰነብት ፡ ዘንድ ፡ አርፈህ ፡ ሰንብት ፡ ብሎ ፡ አሰነበተው ።

ወባሕቱ ፡ ዐቃቢሁስ ፡ ምስሌሁ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ ቂራኛው ፡ አልተለየውም ፡ ነበር ። አንድም ፡ ፍንጁ ፡ አልወለቀለ ትም ፡ ነበር ።

፲፯ ፤ ወእምድኅረ ፡ ሠለስቱ ፡ ዕለት ፡ ለአከ ፡ ጳው ሎስ ፡ ይጸውዖሙ ፡ ለሊቃውንተ ፡ አይሁድ ።

ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ የአይሁ ድን ፡ ሊቃውንት ፡ ልኮ ፡ አስጠራቸው ።

ወመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ብዙኃን ፡ ሰብእ ፡

ብዙዎች ፡ ሰዎችም ፡ ወደሱ ፡ መጡ ።

ወሶበ ፡ ተጋብኡ ፡

በተሰበሰቡም ፡ ጊዜ ።

ይቤሎሙ ፡ አልቦ ፡ እኩይ ፡ ዘገበርኩ ፡ አኀዊነ ፡ ዲበ ፡ ሕዝብ ፡

ወንድሞቻችን ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ የሠራ ሁት ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ የለም ።

ወኢዲበ ፡ አሪት ፡

ኦሪትንም ፡ አላፈረስሁም ።

ወበከመ ፡ ሞቅሑኒ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ወመጠዉኒ ፡ ለሰብአ ፡ ሮሜ ፡

በኢየሩሳሌም ፡ ሳለሁ ፡ አይሁድ ፡ አሥ ረው ፡ ለሮም ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ሰጡኝ ፡ ሰምታችኋል ፡ ም ፡ ፳፫ ፡ ፩ ።

፲፰ ፤ ወሐቲቶሙ ፡ ፈቀዱ ፡ ያሕይዉኒ ፡ እሙንቱ ፡ ሶበ ፡ ኢረከቡ ፡ ላዕሌየ ፡ ጌጋየ ፡ በዘይሞቅሑኒ ፡ ወበ ዘይኴንኑኒ ፡

እነዚያም ፡ መርምረው ፡ በሚያሥሩኝ ፡ በሚገሉኝ፡ ገንዘብ፡ ዕዳ፡ በደል ፡ ባያገኙ ፡ ሊያድኑኝ ፡ ወደው ፡ ነበር ።

፲፱ ፤ ወሶበ ፡ ተንሥኡ ፡ አይሁድ ፡ ይትቃወሙኒ ፡

አይሁድ ፡ ግን ፡ ተነሥተው ፡ በተከራ ከሩኝ ፡ ጊዜ ።

ተማኅፀንኩ ፡ ሎሙ ፡ በቄሣር ፡ ንጉሥ ፡

በቄሣር ፡ ተማፅኛለሁ ፡ ከቄሣር ፡ እደርሳ ለሁ ፡ አልሁ ።

ወአኮሰ ፡ ከመ ፡ አስተዋድዮሙ ፡ ለሕዝብየ ።

እንዲህም ፡ ማለቴ ፡ ወገኖቼን ፡ ልከሣቸ ው ፡ ላጣላቸው ፡ አይደለም፡ ም፡ ፳፭፡፲፪ ።

፳ ፤ ወበእንተዝኬ ፡ አስተብቋዕኩክሙ ፡ ከመ ፡ ትምጽኡ ፡ ኀቤየ ፡ ከመ ፡ አስምዕክሙ ፡ ወእንግር ርክሙ ፡

ነገሬን ፡ እነግራችሁ ፡ ዘንድ ፡ ወደኔ ፡ እን ድትመጡ ፡ ስለዚህ ፡ ማለድኋችሁ ።

እስመ ፡ በእንተ ፡ ተስፋሆሙ ፡ ለእስራኤል ፡ ተሞቃ ሕኩ ፡ በዝንቱ ፡ ሰናስል ፡

የእስራኤልን ፡ ተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ ስላስተ ማርሁ ፡ በዚህ፡ ሰንሰለት፡ ታሥሬያለሁና ፡ ም ፡ ፳፮ ፡ ፮ ፡ ፯ ።

፳፩ ፤ ወይቤልዎ ፡ ረበናት ፡ አይሁድ ፡ ለነሰ ፡ ኢበ ጽሐነ ፡ መጽሐፈ ፡ መልእክት ፡ እምድረ ፡ ይሁዳ ፡ በእንቲአከ ፡

የአይሁድ ፡ ረበናትም ፡ ለኛስ ፡ ያንተን ፡ ነገር ፡ የሚነግር ፡ ደብዳቤ ፡ ከምድረ ፡ ይሁዳ ፡ አልመጣልንም ።

ወኢአሐዱ ፡ እምአኀው ፡ እለ ፡ መጽኡ ፡ እምኢየሩ ሳሌም ፡ ኢተናገረ ፡ ቅድመ ፡ ወኢዜነወነ ፡ በእንቲ አከ ፡ በነገር ፡ እኩይ ፡

ከኢየሩሳሌም ፡ ከመጡ ፡ ከአኀው ፡ አንዱ

www.ethiopianorthodox.org

ስንኳ ፡ ያንተን ፡ ነገር ፡ ከዚህ ፡ አ ስቀድሞ
በክፉ ፡ አንሥቶ ፡ አልነገረንም ።

፳፪ ፤ አላ፡ንሕነ፡ንፈቱ፡ንስማዕ፡እምኔከ፡አሚኖተከ፡

እኛ ፡ ግን ፡ ሃይማኖትህን ።

ወበእንተ ፡ ትምህርተ ፡ ሕግ ፡ ዘትብል ፡

የምታስተምረውንም ፡ ትምህርት ፡ ከቃ
ልህ ፡ ልንሰማው ፡ እንወዳለን ፡ እንጅ ።

እስመ ፡ ሰማዕነ ፡ ከመ ፡ በኵለሄ ፡ ትትካሐዱ ፡

አሪት ፡ ትበልጣለች ፡ ወንጌል ፡ ትበልጣ
ለች ፡ በማለት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንድትከራ
ከሩ ፡ ሰምተናልና ፡ ም ፡ ፳፬ ፡ ፲፬ ። ሉቃ ፡
፪ ፡ ፴፬ ።

፳፫ ፤ ወእምዝ ፡ ወደሞሙ ፡ ዕለተ ፡ በዘይመጽኡ ፡
ኀቤሁ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደሱ ፡ የሚመጡበትን ፡
ቀን ፡ ቀጥሮ ፡ ሰደዳቸው ።

ወመጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ብዙኃን ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ የኀድር ፡

በተቀጠሩበት ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ
ሚያድርበት ፡ ቤት ፡ መጡ ።

ወነገሮሙ ፡ በእንተ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ።

የወንጌልን ፡ ነገር ፡ ነገራቸው ።

እንዘ ፡ ያሰምዖሙ ፡ ወያአምኖሙ ፡ በእንተ ፡ እግዚ
እነ ፡ ኢየሱስ ፡ እምኦሪተ ፡ ሙሴ ፡ ወእምነቢያት ፡
እምነግህ ፡ እስከ ፡ ሠርክ ።

ከጧት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ የጌታችን፡
የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ከኦሪት ፡
ከነቢያት ፡ እየጠቀሰ ፡ እያስረዳ ፡ አስተማ
ራቸው ።

፳፬ ፤ ወቦ ፡ እለሂ ፡ አምንዎ ።

ያመኑበትም ፡ አሉ ።

ወመንፈቆሙሰ፤ አበይዎ ።

እኩሎቹ ፡ ግን ፡ አናምን ፡ አሉ ።

፳፭ ፤ ወእንዘ ፡ ኢየኀብሩ ፡ ተመይጡ ፡ እምኀቤሁ ፡

እንዲህ ፡ ሳይተባበሩ ፡ አለ ፡ እኩሌቶቹ ፡
አምነው ፡ እኩሎቹ ፡ ሳያምኑ ፡ ወደ ፡ ቤታ
ቸው ፡ ተመለሱ ።

ወይቤሎሙ ፡ ጳውሎስ ፡ ሠናየ ፡ ይቤ ፡ መንፈስ ፡ ቅ
ዱስ ፡ በቃለ ፡ ኢሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ ለአበዊክሙ ፡

ጳውሎስም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በኢሳይ
ያስ ፡ አድሮ ፡ ላባቶቻችሁ ፡ እውነት ፡
ነገርን ፡ ተናግሯል ፡ አላቸው ።

፳፮ ፤ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሑር ፡ በሎ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ፡

ወደ ፡ እስራኤል ፡ ሂደህ ።

ሰሚዐ ፡ ትሰምዑ ፡

እንሰማለን ፡ ትላላችሁ ፡ አትሰሙም ።

ወኢትሌብዉ ፡ ወሪእየ ፡ ትሬእዩ ፡ ወኢተአምሩ ።

እናውቃለን ፡ ትላላችሁ ፡ አታውቁም ።
እናያለን ፡ ትላላችሁ ፡ አታስተውሉም ፡
ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፱ ፡ ፲ ።

፳፯ ፤ እስመ ፡ ገዝፈ ፡ ልቡ ፡ ለዝ ፡ ሕዝብ ፡

ልቡናቸው ፡ ደንቁሯልና ፡ ኢትሌብዉ ፡
ላለው ።

ወደንቅወ ፡ እዘኒሆሙ ፡ እምሰ ሚዕ ፡

ጆሮቻቸውም ፡ ከመስማት ፡ ፈዛዛ ፡ ሁኗልና
ኢትሰምዑ ፡ ላለው ።

ወከደኑ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡

ዓይናቸውንም፡ ከማየት ፡ ከልክለዋልና ፡
አታስተሉምው ፡ ላለው ።

ከመ ፡ ኢይርአዩ ፡ በአዕይንቲሆሙ ፡

ባይናቸው ፡ እንዳያዩ ፡ ከደኑ ።

ወኢይስምዑ ፡ በእዘኒሆሙ ፡

በጆሮቻቸው ፡ እንዳይሰሙ ፡ ደንቀወ ።

ወኢይለብዉ፡ በልቦሙ ፡

በልቡናቸው ፡ እንዳያውቁ ፡ ገዝፈ ።



ወኢይትመየጡ ፡ ኀቤየ ፡ ወኢይሠሃሎሙ ፡

ወደኔ ፡ እንዳይመለሱ ፡ ይቅር ፡ እንዳልላ
ቸው ፡ ከደኑ ፡ ደንቀወ ፡ ገዝፈ ፡ ብሎ ፡
በኢሳይያስ ፡ አድሮ ፡ ላባቶቻችሁ ፡ እው
ነተኛ ፡ ነገርን ፡ ተናግሯል ፡ አላቸው ።
ታሪክ ፡ በዖዝያን ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ኃጢ
አት ፡ ሠሩ ፡ ጣዖት ፡ አመለኩ ። ኢሳይ
ያስ ፡ ፈርቶ ፡ ባይገሥፃቸው ፡ ለምፅ ፡ ወጣ
በት ፡ ሀብተ ፡ ትንቢት ፡ ተነሣው ። በዓ
መተ ፡ ሞተ ፡ ዖዝያን ፡ ንጉሥ ፡ ርኢክዎ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ እንዘ ፡ ይነብር፡
ዲበ ፡ መንበሩ ፡ ነዋህ ፡ ወብሩህ ፡ ወም
ሉእ ፡ ቤተ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወሱራፌል ፡
ይቀውሙ ፡ ዓውዶ ፡ ለለአሐዱ ፡ በበስድ
ስቱ ፡ ክነፊሆሙ ፡ በክልኤቱ ፡ ክነፊሆሙ
ይከድኑ ፡ እግሮሙ ፡ ወበክልኤቱ ፡ ክነፊ
ሆሙ ፡ ይከድኑ ፡ ገጾሙ ፡ ወበክልኤቱ ፡
ክነፊሆሙ ፡ ይሠሩ ፡ አንፃረ ፡ ኀቡረ ፡
እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡
እግዚአብሔር ፡ ጸባዖት ፡ ፍጹም፡ ምሉእ ፡
ሰማያተ፡ ወምድረ ፡ ቅድሳተ፡ ስብሐቲከ ፡
እንዲል፡ ዖዝያን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ጌታ፡ በ
መንበረ ፡ መንግሥት፡ ሁኖ ፡ በግርማ ፡ ታ
ይቶ፡ ያ፡ ያፈርኸው፡ የፈራኸው ፡ ንጉሥ ፡
ሞተ ፡ ያላፈርኸኝ፡ ያልፈራኸኝ ፡ እኔ ፡
አለሁ ፡ አሁንስ ፡ መኑ ፡ እፌኑ ፡ ኀበ ፡ ሕዝ
ብየ ፡ ሕዝቤን ፡ ማን ፡ ያስተምርልኛል ፡
አንተም፡ ፈራሁ፡ አልህ፡ አለው።እስመ፡ ር
ኩሰ፡ ከናፍር፡ አነ፡ ለምጽ፡ ወጥቶብኛልና፡
ይጸየፉኛል ፡ እንጅ ፡ እኔ ፡ ባስተማርሁ ፡
ነበር ፡ አለው ፡ ይህማ ፡ ወማዕከለ ፡ ሕዝ
ብ ፡ ዘርኩስ ፡ ከናፍሪሁ ፡ ይላል ፡ ሕዝ
ቡን ፡ ሁሉ ፡ ለምጻም ፡ ማለት ፡ ነውን ፡
ብሎ ፡ ሀብተ ፡ ትንቢት ፡ ተነሥቶኛል ፡
ማለቱ ፡ ነው ፡ ሱራፌን ፡ ከምሥዋዕ ፡
ሰማያዊ፡ በጉጠት ፡ ፍሕም ፡ አምጥተህ ፡
ከንፈሩን ፡ አስነካው ፡ አለው ፡ ወአልከፎ፡
ከናፍሪሁ፡ ይላል ፡ ፍሕሙን ፡ በጉጠት ፡ አ
ምጥቶ፡ ከንፈሩን፡ አስነካው፡ ለምጹ፡ ድኖ
ለታል ፡ ሀብተ ፡ ትንቢቱም ፡ ተመልሶ
ለት ፡ ሂዶ ፡ ሰሚዐ ፡ ትሰምዑ ፡ ወኢትሌ
ብው ፡ ወሪእየ ፡ ትሬእዩ ፡ ወኢታአምሩ ፡
ብሎ ፡ ይህንን ፡ ነግሯቸዋል ። ሱራፌ ፡
የቀሳውስት ፡ ኢሳይያስ ፡ የምእመናን ፡
ጉጠት ፡ የሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ፍሕም ፡
የሥጋው ፡ የደሙ ፡ ለምጽ ፡ የፍዳ ፡ የመ
ርገም ፡ ምሳሌ ፡ በዚህም ፡ ሊቁ ፡ጢሞቴ
ዎስ ፡ ዘአልቦ፡ ጥሪት፡ መቅዶንዮስን፡ ረቶ
በታል ፡ ለአብ ፡ መንበር ፡ አለው ፡ መን
በር ፡ ሰጥቶ ፡ የተናገረበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡
ድልው ፡ መንበርከ ፡ እግዚኦ ፡ ይላል ።
ለወልድም ፡ መንበር ፡ አለው ፡ መንበር ፡
ሰጥቶ ፡ የተናገረበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ መንበ
ርከ ፡ እግዚኦ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ይላል ፡
ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ግን ፡ መንበር ፡ የለ
ውም፡መንበር፡ ሰጥቶ፡ የተናገረበት፡ ጊዜ ፡
የለም ፡ ብሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሕጹጽ ፡
ፍጡር ፡ ብሏል ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ይህን፡
በዓለ ፡ መንበር ፡ በቃለ ፡ ኢሳይያስ ፡ ለመ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰጥቶ ፡ ከተናገረ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደምን ፡ የባሕርይ ፡ ምላ
እክ ፡ አይደለ ፡ ብሎ ፡ ረቶበታል። አ.ይቤ፡
ሠናየ ፡ ይቤ ፡ አብ ፡ ኢ.ይቤ ፡ ሠናየ ፡ ይቤ ፡
ወልድ ፡ አላ ፡ ይቤ ፡ ሠናየ ፡ ይቤ ፡ መን
ንፈ ፡ ቅዱስ ፡ ብሎ ፡ ረቶበታል ።

፳፰ ፤ አእምሩ ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ ለአሕዛብ ፡ ትከውን ፡
ዛቲ ፡ ሕይወት ፡ እንተ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተ
ገኘች ፡ ድኅነት ፡ ልጅነት ፡ ለአሕዛብ ፡
እንድትሰጥ ፡ ዕወቁ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወእሙንቱ ፡ እለ ፡ ይሰምዕዎ ፡ ወይሴብዉ ፡ ወይትኤ
ዘዙ ፡ ሎቱ ፡

ሰምተው ፡ የሚገዙለት ፡ የሚታዘዙት ፡
እነሱ ፡ ናቸውና ።

፴ ፤ ወነበረ ፡ ጳውሎስ ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ዘተዐሰበ ፡
በንዋዩ ፡ ክልኤተ ፡ ዓመተ ፡

ጳውሎስ ፡ በገንዘቡ ፡ በገዛው ፡ ቦታ ፡
ሁለት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ።

ወይትቄበል ፡ ኵሎ ፡ ዘአተወ ፡

የወጣ ፡ የገባውን ፡ እንግድነት ፡ እየተቀ
በለ ፡ ኖረ ።

፴፩ ፤ ወይጼውዖሙ ፡ ለመንግሥተ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡

ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እየጠራ ፡
አለ ፡ አሕዛብን፡ ወደ፡ ወንጌል፡ እየመለሰ ፡

ወይሰብክ ፡ ወይሜህር ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ፡
ክርስቶስ ፡

የጌታችን ፡ የኢየሱስ፡ክርስቶስንም፡ ነገር ፡
እያስተማረ ፡ ኖረ ።

እንዘ ፡ ክሡተ ፡ ይነግር ፡ ወአልቦ ፡ ዘይከልኦ ፡

ገልጦ ፡ ሲያስተምር ፡ የሚከለክለው ፡ አል
ነበረም ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ቦአ ፡ ኀበ ፡ ኔሮን ፡ በቀዳማይ ፡ ጊዜ ፡

በመጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ኔሮን ፡ ቄሣር ፡ ገብቶ

ወሞአ ፡

ተከራክሮ ፡ ረቶ ።

ወሖረ ፡ በሰላም ፡ ወነበረ ፡ እምድኅረዝ፡ኑኀ ፡ ክል
ኤቱ ፡ ዓመተ ፡

ሖረና ፡ ነበረ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ በፍቅር ፡
ሁለት ፡ ዓመት ፡ በሮም ፡ ኖረ ።

ወወፅአ ፡

ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከሮም ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡
እንድልስ ፡ ሄደ ።

ወእምዝ ፡ ተመይጠ ፡ ወአጥመቀ ፡ አዝማዲሁ ፡ ለኔ
ሮን ፡

ከእንድልስ ፡ ተመልሶ ፡ የኔሮን ፡ ቄሣርን ፡
ዘመዶች ፡ አጠመቀ ።

ወስምዓ ፡ ኮነ ፡ በእዴሁ ፡ በሰይፍ ፡ ዕጉሠ ፡

ኔሮን ፡ ቄሣር ፡ ማን ፡ አሰናብቶህ ፡ ነው ፡
ብሎ ፡ በሰይፍ ፡ አስመታው ፡ ሰማዕት ፡
ሆነ ። አንድም ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡
ወደ ፡ ኔሮን ፡ ቄሣር ፡ ገብቶ ፡ ተከራክሮ ፡
በፍቅር ፡ ከሮም ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ እንድ
ልስ ፡ ሂዶ ፡ በእንድልስ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡
ኖረ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ከእንድ
ልስ ፡ ተመልሶ ፡ የኔሮን ፡ ቄሣርን ፡ ዘመ
ዶች ፡ አጠመቀ ፡ ማን ፡ አሰናብቶህ ፡
ነው ፡ ብሎ ፡ በሰይፍ ፡ አስመታው ፡ ሰማ
ዕት ፡ ሆነ ።

እስከ ፡ ዝ ፡ ነገር ፡ አብጽሐ ፡ ሉቃስ ፡ በዜናሁ ፡

እስከዚህ ፡ ድረስ፡ ሉቃስ፡ በታሪኩ፡ ጻፈ ።

ወዘተሠወረ ፡ እምኔሁ ፡ እስመ ፡ እንተ ፡ ትረክብ ፡
በቀዳማይ ፡ ፍካሬ ፡ መልእክቱ ፡ ለጳውሎስ ፡ ዜና ፡
ግብሩ ፡ ለጳውሎስ ፡

ከዚህ ፡ የቀረውን ፡ ግን ፡ ጳውሎስ ፡ ያስተ
ማረውን ፡ ትምህርት ፡ የሠራውን ፡ ትሩ
ፋት ፡ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፡ በሚና
ገሩ ፡ ባሥራ ፡ ሦስቱ ፡ ክታብ ፡ በመጀመ
ሪያው ፡ ታገኘዋለህና ፡ ተመልከት ። (በም
ክንያቱ ፡ ማለት ፡ ነው) ።

ተፈጸመ ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ልኡካን ።

ሐዋርያት ፡ ያስተማሩትን ፡ ትምህርት ፡
የሠሩትን ፡ ትሩፋት ፡ ያደረጉትን ፡ ተአ
ምራት ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ደረሰ ፡
ተፈጸመ ።

ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።

አስጀምሮ ፡ ላስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡
ምስጋና ፡ ይግባው ።

# ፲፬ቱ ፡ መልእክታተ ፡ ሐዋርያ ።

www.ethiopianorthodox.org